አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ፣ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

በፎክሎር መርሐ ግብር የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት

# የዋግ ኽምራ የወሊድ፣ የጋብቻ እና የሞት ሥነ-ሥርዓት ፋይዳ ትንተና

በ

አፀደ ተፈራ መኮነን

አማካሪ

አቶ ዘሪሁን አስፋው(ተባባሪ ፕሮፌሰር)

2007 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የዋግ ኽምራ የወሊድ፣ የጋብቻ እና የሞት ሥነ-ሥርዓት ፋይዳ ትንተና

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ፣ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

በፎክሎር መርሐ ግብር የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት


በ

አፀደ ተፈራ መኮነን

አማካሪ

አቶ ዘሪሁን አስፋው(ተባባሪ ፕሮፌሰር)


2007 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምርቃ መርሐ ግብር

# የዋግ ኽምራ የወሊድ፣ የጋብቻ እና የሞት ሥነ-ሥርዓት ፋይዳ ትንተና

በ

አፀደ ተፈራ

የፈተና ቦርድ አባላት

| | |
|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ |
| ዘሪሁን አስፋው | |
| የውስጥ ፈታኝ | |
| ፋቃዱ ፡ ካሳዘ | |
| የውጭ ፈታኝ | |
| ደሳለው ፡ እንዳዉቀ (ዶ/ር) | |

## ማውጫ


ርእስ ገጽ

ምስጋና------------------------------------------------------------ i

ምህጻረ ቃላት------------------------------------------------------ iv

በጽሁፉ ውስጥ የሚገኙ ፎቶዎች------------------------------------------ v

አጠቃሎ------------------------------------------------------------ vii

ምዕራፍ አንድ መግቢያ ------------------------------------------------ 1

1.1.የጥናቱ ዳራ ------------------------------------------------------ 1

1.2. የጥናት አካባቢው፣ የማህበረሰቡ የዘር ሀረግ፣ ታሪካዊ ዳራ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ-------------------------------------------------------- 1

1.2.1 የጥናቱ አካባቢ------------------------------------------------ 2

1.2.2. የህብረተሰቡ የዘር ሀረግ ፣ ታሪካዊ ዳራ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ----------6

1.2.2.1 የህብረተሰቡ የዘር ሀረግ------------------------------------------ 6

1.2.2.2. ታሪካዊ ዳራ---------------------------------------------------- 10

1.2.2.2.1 የአገዎች ታሪካዊ ዳራ-------------------------------------------- 10

1.2.2.2.2 የዋግ ኽምራዎች ታሪካዊ ዳራ-------------------------------------- 13

1.2.2.3 የማህበረሰቡ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ------------------------------------- 15

1.2.2.4 የማህበረሰቡ ማህበራዊ ሁኔታ-------------------------------------- 15

1.2.2.5 የዞኑ ማህበረሰብ የቤት አሰራር፣ አለባበስ፣ አጊያጊያጥና አመጋገብ------ 18

1.3 የጥናቱ ቦታ የተመረጠበት ምክንያትና የጥናቱ ወሰን------------------------- 29

1.4 ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች-------------------------------------- 33

1.5 የጥናቱ ዓላማ--------------------------------------------------- 33

1.5.1 አቢይ ዓላማ---------------------------------------------------- 33

1.5.2.ዝርዝር ዓላማ-------------------------------------------------- 34

1.6.የጥናቱ ጠቀሜታ------------------------------------------------ 34

ምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳን------------------------------------------- 36

2.1 ሥነ-ሥርዓት------------------------------------------------------ 36

2.1.1 የሥነ-ሥርዓት ጠባይ------------------------------------- 37

2.1.2 የሥነ-ሥርዓት አይነቶች------------------------------------------ 38
2.1.3 የሥነ-ሥርዓት ፋይዳ-------------------------------------------- 40
2.1.4 የሽግግር ሥነ-ሥርዓት---------------------------------------------- 41
2.1.4.1 የሽግግር ሥነ-ሥርዓት አይነቶች---------------------------------- 42
2.1.4.1.1 የወሊድ ሥነ-ሥርዓት---------------------------------------- 43
2.1.4.1.2.የጋብቻ ሥነ-ሥርዓት------------------------------------- 44
2.1.4.1.3. የሞት ሥነ-ሥርዓት-------------------------------------- 49
2.1.4.2 የሽግግር ሥነ-ሥርዓት ደረጃዎች------------------------------- 50

2.2 የመረጃ እይታና የመረጃ መተንተኛ ማእቀፍ ጽንሰ-ሀሳብ---------------------- 52

2.2.1 የመረጃ እይታ----------------------------------------------------- 52

2.2.2 የመረጃ መተንተኛ ማእቀፍ ጽንሰ ሀሳብ--------------------------------- 52

2.2.2.1 ክዋኔ ተኮር ጥናት (Performance study) ------------------------ 56

2.2.2.2 አውዳዊ እይታ (contextual approach) ------------------------------ 57

2.2.2.3 ተምሳሌታዊ እይታ (symbolic approach)--------------------------- 58

2.2.2.4 መዋቅራዊ-ፋይዳዊነት (structural-functional paradigm) ------------- 58

ምዕራፍ ሶስት የጥናቱ ዘዴ---------------------------------------------------- 63

3.1 የጥናት ንድፍ------------------------------------------------------- 63

3.2.የጥናቱ አቀራረብ---------------------------------------------------- 63

3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች--------------------------------------- 64

3.3.1 ምልከታ------------------------------------------------------- 65

3.3.2 ቃለመጠይቅ------------------------------------------------------ 67

3.3.3 ቡድን ተኮር ውይይት------------------------------------------- 68
3.3.4 የውይይት መድረክ------------------------------------------ 68

3.4 የመረጃ አቀባዮች ወይም ምንጮች------------------------------------- 69

3.5 ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች የተሰበሰቡበት አውድ--------------------- 70

3.6 የመቅረጫ መሳሪያዎች አጠቃቀም-------------------------------------- 71

3.7 የመስክ ጉዞ--------------------------------------------------------- 73

3.8 የመስክ ገጠመኝ----------------------------------------------------- 74

3.9 የጥናቱ አከዋወን ሂደት---------------------------------------------- 78

3.10 የጥናትና ምርምር ስነ-ምግባር----------------------------------------- 79

ምዕራፍ አራት የዋግ ኽምራ ዞን ህብረተሰብ የወሊድ ሥነ-ሥርዓት------------- 82

4.1 ቅድመ-ወሊድ--------------------------------------------------------- 82

4.1.1 ለነፍሰ-ጡር ሴት የሚደረግ እንክብካቤ እና ጥንቃቄ------------------ 82

4.1.2 የምግብና የመጠጥ ዝግጅት ------------------------------------------ 84

4.2 ጊዜ ወሊድ ------------------------------------------------------------ 85

4.3 ድህረ ወሊድ-------------------------------------------------------- 93

4.3.1 የአራስ ቤት ቆይታ እና አራስን መጠየቅ----------------------------- 93

4.3.2.የአራስ ሴት ልብስ አጠባ ----------------------------------------------- 96

4.3.3 የክርስትና አነሳስ (የመጠመቅ) ስርዓት-------------------------------- 99

4.4 በወሊድ ሥነ-ሥርዓት የባል ተሳትፎ------------------------------------ 108

ምዕራፍ አምስት የዋግ ኽምራ ዞን ህብረተሰብ የጋብቻ ሥነ-ሥርዓት -------------- 110

5.1 የጋብቻ አይነቶች------------------------------------------------------ 110

5.2 ቅድመ-ሰርግ ------------------------------------------------------------ 114

5.2.1 የዝምድና ርቀትን ማጣራት----------------------------------------------- 114
5.2.2 የማጨት ስርዓት------------------------------------------------------------ 116
5.2.2.1 የማጨት ስርዓት ሂደት------------------------------------------------ 116
5.2.2.2 በእጮኝነት ሂደት ወቅት የሴቶች (የእናቶች) ተሳትፎ------------ 126
5.2.3 የሰርግ ቀን መወስን (ቆረጣ)------------------------------------------- 127
5.2.4 የሚዜ ምልመላ----------------------------------------------------------- 130
5.2.5.ምኩትና ማሰሮ ቅቤ መውሰድ------------------------------------------- 134
5.3 ሰርግ--------------------------------------------------------------------- 137
5.3.1 የሰርግ ድግስ ዝግጅት---------------------------------------------------- 137
5.3.2 የወንድ ወገን ወደ የሙሽራዋ ቤት ዘመቻ እና የዳስ ውስጥ ስርዓት------- 154
5.4.ድህረ ሰርግ ተግባራት------------------------------------------------------ 183
5.4.1 የሙሽራዎች የጫጉላ ቤት ቆይታ------------------------------------------ 183
5.4.2 የሚዜዎችና የሙሽራዎች ቃል መግባት------------------------------------ 183
5.4.3 መልስ (ምላሽ)፣ (በኽምጣኛ ዋጥር)-------------------------------------- 184
5.4.4 የሙሽራ ስም አወጣጥ------------------------------------------------------ 185
5.4.5 የጎጆ አወጣጥ------------------------------------------------------------ 186

ምዕራፍ ስድስት የዋግ ኽምራ ዞን ህብረተሰብ የሞት ሥነ-ሥርዓት------------- 189

6.1 ህብረተሰቡ ስለ ሞት ያለው አመለካከት---------------------------------------- 189

6.2. ቅድመ-ቀብር------------------------------------------------------------ 191

6.3 የቀብር ሥነ-ሥርዓት---------------------------------------------------- 203

6.4 ድህረ-ቀብር ክዋኔዎች -------------------------------------------------- 205

6.4.1 ስንብት--------------------------------------------------------- 205

6.4 2 ማስተዛዘን (መደበስ )--------------------------------------------- 208

6.4.3 አነበር (በኽምጣኝ አግበር )------------------------------------- 209

6.4.4 የሟች መታሰቢያዎች (መዘከሪያዎች)-------------------------------- 217

**ምዕራፍ ሰባት የሶስቱ ሥነ-ሥርዓቶች ትንተና፣ ማጠቃለያና ይሁንታ**-------------- 220

7.1 የወሊድ ሥነ-ሥርዓት ትንተና-------------------------------------------- 221

7.1.1 ከተምሳሌታዊነት አንጻር-------------------------------------------- 221

7.1.2 ከመዋቅራዊ-ፋይዳዊነት አንጻር------------------------------------- 223

7.1.2.1 ከመዋቅራዊነት አንጻር------------------------------------------ 223

7.1.2.2 ከፋይዳዊነት አንጻር-------------------------------------------- 225

7.2 የጋብቻ ሥነ-ሥርዓት ትንተና-------------------------------------------- 230

7.2.1 ከተምሳሌታዊነት አንጻር-------------------------------------------- 230

7.2.2 ከመዋቅራዊ-ፋይዳዊነት አንጻር------------------------------------- 233

7.2.2.1 ከመዋቅራዊነት አንጻር------------------------------------------ 234

7.2.2.2 ከፋይዳዊነት አንጻር--------------------------------------------- 235

7.3 የሞት ሥነ-ሥርዓት ትንተና ----------------------------------------------- 243

7.3.1 ከተምሳሌታዊነት አንጻር-------------------------------------------- 243

7.3.2 ከመዋቅራዊ-ፋይዳዊነት አንጻር------------------------------------- 244

7.3.2.1 ከመዋቅራዊነት አንጻር------------------------------------------ 244

7.3.2.2 ከፋይዳዊነት አንጻር-------------------------------------------- 245

7.4 ለውጥና ቀጣይነት በሶስቱ ሥነ-ሥርዓቶች -------------------------------- 250

7.4.1 ለውጥና ቀጣይነት በወሊድ ሥነ-ሥርዓት------------------------------ 250

7.4.2 ለውጥና ቀጣይነት በጋብቻ ሥነ-ሥርዓት----------------------------- 256

7.4.3 ለውጥና ቀጣይነት በሞት ሥነ-ሥርዓት------------------------------- 263

7.5 ማጠቃለያ------------------------------------------------------------- 264

7.6 ይሁንታ---------------------------------------------------------------- 266

የዋቢ መጻህፍት ዝርዝር------------------------------------------------ 267

ሀ/የታተሙ------------------------------------------------------------ 267

ለ/ያልታተሙ------------------------------------------------------------ 277

<u>አባሪዎች</u>

<u>አባሪ አንድ</u> የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር

<u>አባሪ ሁለት</u> ምልከታ የተከናወነባቸው ሥነ-ሥርዓቶች

<u>አባሪ ሶስት</u> መሰረታዊ የቃለመጠይቅ ጥያቄዎች

<u>አባሪ አራት</u> የአካባቢያዊ ቃላት ፍች

<u>አባሪ አምስት</u> የኸምጣኛ ቃላት፣ ሀረጋትና ዓርፍተ ነገሮች የአማርኛ ትርጉም

<u>አባሪ ስድስት</u> የአማራ ክልል እና የዋግ ኽምራ ዞን ካርታ

## ምስጋና

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ እዚህ ደረጃ ላይ እንዲደርስ በርካታ አካላት አስተዋጽኦ አድርገዋልና እነዚህን አካላት ማመስገን ተገቢ ነው፡፡ በመጀመሪያ ውድ ጊዜያቸውን መስዋእት በማድረግ ትልመ-ጥናቱንና የጥናቱን ረቂቅ በማንበብና በማረም ገንቢ አስተያየታቸውን ለለገሱኝ ለአማካሪየ ለተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን አስፋው ምስጋናየን አቀርባለሁ፡፡

በመቀጠል አቅመ ደካማነቷና የአቅም ውስንነቷ ሳይገድባት ዛሬም የሞራልና የማቴሪያል ድጋፏ ያልተለየኝ እናቴ እማሆይ አዛሉ ወ/ሰንበት አይዞሽታዋን ምንጊዜም አልረሳውምና ውለታዋን ለመመለስ ያብቃኝ እላለሁ፡፡ ወንድሞቼ አብርሃ ተፈራንና መልሰው ተፈራንም ለድጋፋቸው ሳላመሰግናቸው አላልፍም፡፡ በተለይ እህቴ ወ/ሮ ብርሃን ተፈራ ወደ ጥናት ቦታየ በተመላለስኩበት ወቅት ላደረገችልኝ ድጋፍና ዞኑን በሚመለከት ለጥናቴ የሚያስፈልጉኝን መረጃዎች በተለያዩ ጊዜያት ስጠይቃት ያለመሰልቸት እያፈላለገች ወደ አዲስ አበባ በመላክ ላደረገችልኝ እርዳታ በጣም አመሰግናታለሁ፡፡ ባንድ የክረምት ቆይታ ትውውቅ እህታዊ ጓደኝነቷን አጠናክራ በመቀጠል በትምህርት ቆይታየ ወቅት ሳትሰለች የማቴሪያልና የሞራል ድጋፍ ላደረገችልኝ ለወ/ሮ ሰብለ አለባቸውና ለባለቤቷ ለአቶ ከበደ አበበ ውለታችሁን እግዚአብሄር ይመልስላችሁ እላለሁ፡፡

የትምህርት እድል የሰጠኝንና ለጥናቱ የገንዘብ ድጋፍ ያደረገልኝን ወሎ ዩኒቨርሲቲንም ሳላመሰግን አላልፍም፡፡ ምንም እንኳ ከመስክ በሚሰበሰብ መረጃ ላይ ለተመሰረተ ጥናት በቂ ነው ባይባልም፤ ለጥናቱ ላደረገው የገንዘብ ድጋፍ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲንም አመሰግናለሁ፡፡

አስቸጋሪ የሆነውን የእግር መንገድ ተቋቁመው ወደ ገጠር ቀበሌዎች በመጓዝ በቪዲዮና በፎቶ ካሜራ መረጃ እንድሰበስብ ለረዱኝ ለዞኑ የተለያዩ መስሪያ ቤቶች የካሜራ ባለሙያዎች፣ በተለይም አቶ መብራት መኮነን፣ አቶ አበበ ደምሴንና አቶ ብዙአየሁ ማሞን ሳላመሰግናቸው አላልፍም፡፡ የልጅነት አቅሙ የመንገዱ ውጣ ውረድና አስቸጋሪነት፣ የቀኑ ሙቀት፣ የምሽቱ ቅዝቃዜ ሳይገድበው፣ ሥነ-ሥርዓቶቹን ስመልከት ወደ ቀበሌዎች ከእኔ ጋር በመጓዝ የአቅሙን ያህል የረዳኝ ተማሪ ናትናኤል መስፍንም ባለውለታየ ነው፡፡

በዋግ ኽምራ ዞን በስድስቱም ወረዳዎች የቃል መረጃ የሰጡኝን የመረጃ አቀባዮች በሙሉ አመሰግናቸዋለሁ፡፡ በተለይ ደግሞ በሰቆጣ ከተማ በጥናቱ ላይ በተካሄደው የውይይት መድረክ ተሳታፊ በመሆን ገንቢ ሃሳባቸውን የሰጡኝን በጣም አመሰግናቸዋለሁ፡፡ የሥነ-ሥርዓቶቹን ክዋኔ ምልከታ ለማድረግ ወደ ተለያዩ ቀበሌዎች በሄድኩበት ወቅት ማረፊያ በመስጠት የተባበሩኝን ሁሉ አመሰግናቸዋለሁ፡፡ በእግር በምጓዝበት ወቅት መንገድ በመምራት፣ አብሮ በመጓዝ፣ የጥናቴን አላማ ለመረጃ አቀባዮች በማስረዳት መረጃ እንድሰበስብ ለረዱኝም ምስጋናየ ይድረሳቸው፤ በተለይ ለአቶ ሞገስ አወጣ እና ለአቶ አካሉ ግርማይ ምስጋናየ ላቅ ያለ ነው፡፡

ከዞን ወደ ወረዳ ዋና ከተማ እና ከወረዳ ዋና ከተማ ወደ ገጠር ቀበሌዎች ለመጓዝ የመስክ መኪና ትብብር ያደረጉልኝን የዋግ ኽምራ ዞን ሴክተር መስሪያ ቤት ኃላፊዎች አመሰግናቸዋለሁ፡፡ በተለይም ከወረዳ ዋና ከተማ ወደ ቀበሌዎች የሥነ-ሥርዓቶች ምልከታ ለማድረግ እንድችል ያለመሰልቸት በተደጋጋሚ የመስክ መኪና በመስጠት ለተባበሩኝ የሰቆጣ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ ለነበሩት አቶ መብራት አለማየሁ ምስጋናየ ላቅ ያለ ነው፡፡ የስሃላ ዋና አስተዳዳሪ አቶ በሪሁን ኪዴ፣ የድሃና ምክትል አስተዳዳሪ አቶ ዘውዱ የኋላውም ለተመሳሳይ እገዛቸው ምስጋናየ ይድረሳቸው፡፡

ከወረዳ ዋና ከተማ ምልከታ ወደማደርግባቸው ቀበሌዎች ለማጓጓዝ የመንገዱ አስቼጋሪነት ሳይበግራቸው የተባበሩኝን ሹፌሮች በሙሉ በተለይም አቶ አያሌው አበራ፣ አቶ አዱኛ አሰፋ፣ አቶ ቢኒያም ጌታቸው፣ አቶ ዮሀንስ ኤልያስ፣ አቶ አበባው መንግስቱ፣ አቶ ምስጋን አበበ እና አቶ ተመስጌን ዳምጤን ሳላመሰግናቸው አላልፍም፡፡

የጥናቱን ውጤት ጠቀሜታ በመገንዘብ የገንዘብ ድጋፍ ላደረጉልኝና በዞን ደረጃ ለተካሄደው የውይይት መድረክ ወጭ የሆነ ገንዘብም እንዲመደብ በማድረግ ለተባበሩኝ የዋግ ኽምራ ብሄረሰብ ዞን ዋና አስተዳዳሪን አቶ ይልማ ወርቁን ሳላመሰግናቸው አላልፍም፡፡

የውይይት መድረኩን በማዘጋጀት፣ በማስተባበርና በማስፈጸም ለረዱኝ ለዋግ ኽምራ ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ሠራተኞች በተለይም ለአቶ ጣምተው ገላስና ለአቶ አሸናፊ ጌታሁን ምስጋናየ ይድረሳቸው፡፡

በየወረዳው ለመረጃ አቀባይነት የተጠቀምኩባቸውን ሰዎች እያፈላለጉ፣ የጥናቴን አላማ እያስረዱ፣ ከእኔ ጋርም በየቤታቸው በመሄድ የመረጃ መሰብሰብ ሂደቱ ስኬታማ እንዲሆን የተባበሩኝን የስድስቱም ወረዳዎች የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ባለሙያዎችን ሳላመሰግናቸው አላልፍም፡፡

በትምህርት ቆይታየ ወቅት የሞራል ድጋፏ ያልተለየኝ፣ ከትልመ-ጥናቱ ዝግጅት ጀምሮ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ ጽሁፋዊ መረጃዎችን የጠቆመችኝንና የጥናቱን ረቂቅ በማንበብ ገንቢ አስተያየቷን የለገሰችኝን የክፍል ጓደኛየን ወ/ሮ ደስታ አማረን በጣም አመሰግናታለሁ፡፡ ከትልመ-ጥናቱ ዝግጅት ጀምሮ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ ጽሁፋዊ መረጃዎችን ለጠቆሙኝና ለለገሱኝ ለዶ/ር አጋረደች ጀማነህ፣ ለዶ/ር ጉዳይ እምሬ እና ለዶ/ር ውዱ ጣፈጠም ምስጋናየ ይድረሳቸው፡፡

በኽምጣኛ ቋንቋ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ወደ አማርኛ የተረጎሙልኝን ወ/ሮ ውቢት ኪዴንና አቶ ከበደ ተገኘንም ሳላመሰግናቸው አላልፍም፡፡ የጽሁፉን ረቂቅ በማንበብ ገንቢ አስተያየታቸውን የሰጡኝን የወሎ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋ መምህራን የሆኑትን አቶ በአካል ንጉሴንና አቶ ብርሃኑ ቦጋለንም ምስጋናየ ይድረሳችሁ እላለሁ፡፡

## ምህጻረ ቃላት

| | |
|---|---|
| አ.ቀ | አቀንቃኝ |
| ተ.ቀ | ተቀባይ |
| የቤ.እ | የቤት እመቤት |
| የመ.ሰ | የመንግሥት ሰራተኛ |
| ሰ.ወ | ሰቆጣ ወረዳ |
| ባ.ቱ | ባህልና ቱሪዝም |
| ወ/ሮ | ወይዘሮ |
| ወ/ሪት | ወይዘሪት |
| ቡ.ተ.ው | ቡድን ተኮር ውይይት |
| ቡ.ቃ | የቡድን ቃለ መጠይቅ |
| ቃ.መ | ቃለ መጠይቅ |
| ቁ.የ.መ.አ. | ቁልፍ የሆነ የመረጃ አቀባይ |
| ቁ.ያ.መ.አ. | ቁልፍ ያልሆነ የመረጃ አቀባይ |
| ው.መ | የውይይት መድረክ |
| ኢ.ኦ.ተ.ቤ | የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን |
| ጤ.ጥ.ሚ. | የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር |
| ኢ.ም.ጥ.ድ | የኢትዮጵያ ምግብ ጥናት ድርጅት |

## በጽሁፉ ውስጥ የሚገኙ ፎቶዎች


| | |
|---|---|
| ፎቶ 1 የህድሞ ቤት | ገጽ 18 |
| ፎቶ 2 የሀሙሲት ቀበሌ ከፊል ገጽታ | ገጽ 19 |
| ፎቶ 3 ጸጉራቸውን ቁንጮ የተላጩና ኪታ የለበሱ ልጆች ቁርንጮ ላይ ተቀምጠው | ገጽ 21 |
| ፎቶ 4 ኳርቶ የለበሰ ወጣት | ገጽ 21 |
| ፎቶ 5 ቁንጮና ጋሜ የተሰራችና ቃቂዳ ያሰረች ወጣት | ገጽ 22 |
| ፎቶ 6 ቃንጃ አመትር መቀነት የታጠቀች ወጣት | ገጽ 25 |
| ፎቶ 7 በአብዛኛዎቹ የልጃገረድ ጌጣጌጦች ያጌጠች ወጣት | ገጽ 25 |
| ፎቶ 8 ጸጉራቸውን ድፍን የተሰሩና በተለያዩ ጌጣጌጦች ያጌጡ እናቶች | ገጽ 26 |
| ፎቶ 9 ክርስትና የተነሳችን ሕፃን የክርስትና እናቷ አዝላት ቋት ላይ ተቀምጣ | ገጽ 105 |
| ፎቶ 10 ማርዳ ያሰረች ልጅ | ገጽ 124 |
| ፎቶ 11 የአውራጅ ምግብ አቀራረብ | ገጽ 142 |
| ፎቶ 12 አዋጅ ነጋሪ ገንዘብ ሲሰበስብ | ገጽ 144 |
| ፎቶ 13 ወጥ ከተሰራባቸው የሸክላ ድስቶች ውስጥ (በከፊል) | ገጽ 147 |
| ፎቶ 14 ወንድ በጎላ ወጥ ሲሰራ | ገጽ 148 |
| ፎቶ 15 ዳስ ውስጥ የወንዶች አቀማመጥ | ገጽ 150 |
| ፎቶ 16 ሠርግ ላይ ሴቶች ሲመገቡ (በከፊል) | ገጽ 151 |
| ፎቶ 17 ሠርግ ላይ ወንዶች ሲመገቡ (በከፊል) | ገጽ 152 |
| ፎቶ 18 ለሽማግሌዎች የቀረበ ዝልዝል ፍሪምባ | ገጽ 153 |
| ፎቶ 19 ሠርግ ላይ ልጆች ሲመገቡ | ገጽ 154 |
| ፎቶ 20 የወንድ ሙሽራ | ገጽ 157 |
| ፎቶ 21 የሴት ወገን ሴቶች ሙሽራውን በዘፈን ሲቀበሉት | ገጽ 158 |
| ፎቶ 22 ሙሽራው ተጋርዶና በሚዜዎቹ ታጅቦ | ገጽ 161 |

ፎቶ 23 ትልቅና ትንሽ ሚዜዎች የሸኙን ሸኙን ጥያቄ ሲያቀርቡ ገጽ 165

ፎቶ 24 ዳስ ውስጥ የሚዜዎች ጭፈራ ገጽ 166

ፎቶ 25 ሴት ሙሽራ ገጽ 174

ፎቶ 26 የእናቷ ወንድም ሙሽራዋን አዝሎ ወደ ዳስ ሲያስገባት ገጽ 175

ፎቶ 27 የሙሽራዋ ዘመድ አስራ ሁለቱን እቃዎች እያሳየች ገጽ 178

ፎቶ 28 ሚዜዎች ወንዝ ላይ የምትታረደውን ጫጩትና የሴት እቃዎች ይዘው ገጽ 182

ፎቶ 29 በማርገጃ ቦታ በአስተባባሪዎች አማካይነት ለቅሶ ሲካሄድ ገጽ 199

ፎቶ 30 ስንብት (በከፊል) ገጽ 207

ፎቶ 31 ለአጎበር በአገልግል የመጣው እንጀራ ከርክክብ በፊት በከፊል ገጽ 212

ፎቶ 32 የአጎበር እንጀራ ርክክብ ገጽ 213

ፎቶ 33 በአጎበር ወንዶች ሲመገቡ (በከፊል) ገጽ 214

ፎቶ 34 በአጎበር ሴቶች ሲመገቡ (በከፊል) ገጽ 215

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት የዋግ ኽምራ ዞን ህብረተሰብ የወሊድ፣ የጋብቻና የወሊድ ሥነ-ሥርዓት ፋይዳ ትንተና በሚል ርእስ የተጠና ነው፡፡ ይህ ርእስ ትኩረት ያደረገውም በዞኑ ከሚገኙት ሰባት ወረዳዎች መካከል በስድስቱ የገጠር ወረዳዎች ላይ ነው፡፡ የጥናት ቦታው የተመረጠበት ምክንያትም በአካባቢው በዚህ መስክ በዚህ ደረጃ የተጠና ጥናት ባለመኖሩ ነው፡፡ ጥናቱ የተካሄደበት አቢይ አላማም የማህበረሰቡ የወሊድ፣ የጋብቻና፣ የሞት ሥነ-ሥርዓቶች ክዋኔያቸው በዘመናዊነትና በሉላዊነት ሰበብ ሙሉ በሙሉ ሳይለወጥና ሳይጠፋ ዛሬ ባሉበት መልክ አውዳቸውን መሰረት በማድረግ መረጃ በመሰብሰብ እንዲሰነድ እና እንዲቀረስ ለማድረግ ነው፡፡

የጥናቱ መረጃ የተሰበሰበው በቀዳማይ እና በካልኣይ የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ነው፡፡ የመረጃ አቀባዮቹም ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍል የሚወክሉ ማለትም ወንዶች፣ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ አባቶች፣ እናቶችና የሃይማኖት መሪዎች የመንግስት ሰራተኞች፤ ተማሪዎች የሆኑ የመረጃ አቀባዮች ናቸው፤ ከመስክ የተሰበሰበን መረጃ በመጠቀምም የሶስቱን ሥነ-ሥርዓቶች ክዋኔና አውድ በመግለጽ አስፍሬያለሁ፡፡ ሶስቱም ሥነ-ሥርዓቶች የሽግግር ሥነ-ሥርዓቶች ናቸውና የተሰበሰበውን መረጃ ለመተንተን በማእቀፍነት የተጠቀምኩት ጽንሰ-ሃሳብ የVan Gennep የሽግግር ሥነ-ሥርዓት ጽንሰ-ሃሳብ (Rites of Passage Theory) ነው፡፡ በዚህ ጽንሰ ሃሳብ መሰረታዊ ጉዳዮቹ የሥነ-ሥርዓቶቹ ክዋኔ፣ የክዋኔያቸው አውድ፣ በክዋኔያቸው ወቅት የሚታዩ ድርጊቶችና ቁሳቁሶች ተምሳሌትና የሥነ-ሥርዓቶቹ መዋቅራዊ-ፋይዳ ናቸው፡፡

በመተንተኛ ማእቀፉ ትንተና ከተደረገ በኋላ እንደተጠቃለለው የሶስቱም ሥነ-ሥርዓቶች ክዋኔ ዘፈቃዳዊ ሳይሆን በቅድመ-ዝግጅት ነው፡፡ በዚህ ክዋኔ ወቅት በደስታው ሃዘን፣ በሀዘኑ ደግሞ ደስታ ታይቷል፡፡ የሶስቱም ሥነ-ሥርዓቶች ተዋናዮች እንደ የሽግግር ደረጃ ተዋናይነታቸው ከቀደምት ማንነታቸው ተነጥለዋል፤ መካከል ላይ ቆይተዋል፤ በመጨረሻም ወደ አዲሱ ማንነታቸው ምድብ ተቀላቅለዋል፡፡ ይኸውም ነፍሰ-ጡር ሴት ነፍሰ-ጡር ካልሆኑት ተነጠላ ከወለዱትና ካልወለዱት መካከል ላይ ቆይታለች፤ ስትወልድም ከወላጆች ጋር ተቀላቅላለች፡፡ በሠርግም የሠርግ ቀን ሲወሰን ሙሽራዎች ከሌሎች ጓደኞቻቸው

ተነጥለዋል፤ በዚህም ምክንያት መጥፎ ነገር እንዳይደርስባቸው በማለት ልዩ ጥበቃ እየተደረገላቸው ካገቡት ጋር ሳይቀላቀሉ መካከል ላይ ቆይተዋል፤ የጋብቻ ሥነ-ሥርዓታቸውን ሲፈጽሙ ከሁለትነት ወደ አንድነት ተቀይረዋል፤ ጎጆ እስከሚወጡ ድረስ ግን አሁንም መካከል ላይ ቆይተዋል፤ ጎጆ ወጥተው ቤታቸውን መምራት ሲጀምሩ ግን ከሌሎች ጎጆ ወጭዎች ጋር ተቀላቅለዋል፡፡ በሞት ሟች ነፍሱ ስትወጣ ከህያዋን ተለይቷል፤ ወደ ቀብር ከመውረዱ በፊትም መካከል ላይ ቆይቷል፤ ሲቀበር ደግሞ ወደ መሬት ከገቡት ጋር ተቀላቅሏል፡፡

በሶስቱም ሥነ-ሥርዓቶች ክዋኔ ወቅት ተምሳሌታዊ የሆኑ ቁሳቁሶችና ድርጊቶች በብዛት ተስተውለዋል፤ ለአብነት ያህል በወሊድ የአራስ ሴት ልብስ አጠባ ወቅት አጣቢዎቹ ከአጠባ መልስ ሕጻኗ ሴት ከሆነች የሴት የቤት እቃዎች፣ ወንድ ከሆነ ደግሞ የእርሻ መሳሪያዎች ማምጣታቸው ሥርዓተ-ጾታን የሚያመለክት ነው፤ በጋብቻ ወቅት ባንድ ባል የጸናች ሴት ሙሽራዎችን እንድታጥብ መደረጉ ሙሽራዎችም በጋብቻቸው ጸንተው የመኖር ተምሳሌት ነው፤ በሞት ወቅት ሴት ሀዘንተኞች ሀዘንተኛነታቸውን ለማመልከት የጥልፍ ቀሚሳቸውን ገልብጠው መልበሳቸው ይጠቀሳሉ፡፡

ሶስቱም ሥነ-ሥርዓቶች እንደ ፎክሎር ዘውግነታቸው ለማህበረሰቡ በርካታ ፋይዳዎችን የሚያበረክቱ ናቸው፡፡ የመረዳዳት ስሜትን አጎልብተዋል፤ በመማሪያ መድረክነት፣ በመዝናኛነት፣ የፈጠራ ችሎታን በማንጸባረቂያነት አገልግለዋል፤ የማህበረሰቡን ሃገረሰባዊ እውቀት ለማሸጋገርም መድረክ ሆነዋል፡፡ የማህበረሰቡን ማንነት ለማሳየትም መስታወት ናቸው፡፡ በጥቅሉ ማህበረሰቡ ሰላማዊ ህይወት እንዲቀጥል በማድረግ በኩል ፋይዳቸው ላቅ ያለ ነው፡፡ ሶስቱም ሥነ-ሥርዓቶች ሲከወኑ ለውጥና ቀጣይነት ታይቶባቸዋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## 1.1.የጥናቱ ዳራ

## መግቢያ

ይህ ጥናት የተካሄደው በእንግሊዝኛው ritual በሚባለው ላይ ነው፡፡ የአማርኛ አቻ ፍቹን ሥነ-ሥርዓት ብየዋለሁ። ምክንያቱም Leslaw(2007:55),cermoney,procedure, properties,rite,ritual ለሚሉት የእንግሊዝኛ ቃላት የሰጡት የአማርኛ ትርጉም ሥነ-ሥርዓት ነው፤ ሥነ-ሥርዓትና የሽግግር ሥነ-ሥርዓት የሚሉት በተከታታይ ritual እና Rites of Passage የሚሉትን የእንግሊዝኛ ቃላት ትርጉም የሚተኩ ናቸው፡፡ ሥነ-ሥርዓት ደግሞ በፎክሎር ስር የሚጠቀሱትን አራቱን በአንዳንዶቹም ሶስቱን ዘውጎች ወይም ዘርፎች አጠቃሎ ይይዛል። ጥናቱ ከሥነ-ሥርዓቶች መካከል መሰረታዊ ወይም አቢይ በሚባሉት የሥነ-ሥርዓት አይነቶች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ እነዚህም የሽግግር ሥነ-ሥርዓት ከሚባሉት መካከል መሰረታዊ የሆኑት የወሊድ፣ የጋብቻና የሞት[1]ሥነ-ሥርዓት ናቸው፡፡

ጥናቱ የተካሄደው በአማራ ክልል ውስጥ ከሚገኙት አስራ አንድ ዞኖች መካከል አንዱ በሆነው፣ በዋግ ኽምራ ብሄረሰብ ዞን ነው፡፡ የጥናቱ አካባቢ፣ የማህበረሰቡ ዝርያና ታሪካዊ ዳራ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ፣ የሥነ-ሥርዓቶቹን ምንነትና ክዋኔ ይወስናል፡፡ ስለዚህ ቀጥለን ለጥናቱ ዳራ ይሆን ዘንድ ስለ አካባቢውና ስለ ማህበረሰቡ አንዳንድ ነጥቦችን እንመለከታለን።

### 1.2. የጥናቱ አካባቢና፣የማህበረሰቡ የዘር ሀረግ፣ታሪካዊ ዳራ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ፣

በአንድ የፎክሎር ዘውግ ላይ የሚከናወን ጥናት የሚጠናበትን ማህበረሰብ የት መጣነት መግለጽ ያስፈልጋል፤ እኔም ስለአገውና ስለዋግሹምነት ታሪክ የገለጽኩት የዋግ ኽምራ ህብረተሰብን ማንነት ለማሳወቅ ነው፡፡ የህብረተሰቡ የቤት አሰራር፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣

[1] የሃዘን ሥነ-ሥርዓትም በዚሁ ውስጥ ተካቶ ይቀርባል፡፡

አለባበስ ወዘተ.መገለጽ ደግሞ ለጥናቱ ርእሰ-ጉዳይ ፋይዳ አለው፤ ምክንያቱም የሶስቱም ሥነ-ሥርዓቶች ክዋኔና አውድ የሚገለጸው በቋንቋ ነው፤ በሥነ-ሥርዓት ሃይማኖት ይንጸባረቃል፤በጋብቻና በሞት ሥነ-ሥርዓት የታዳሚዎች አለባበስ ከዘወትሩ የተለየ ነውና ልዩነቱን ለማሳየት አለባበስን መግለጽ ተገቢ ነው፡፡

በዚህ ንኡስ ክፍል የሚገለጸውም ስለ የጥናቱ አካባቢ፣ የማህበረሰቡ የዘር ሀረግ፣ ታሪካዊ ዳራው በሁለት ተከፍሎ እና የማህበረሰቡ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ ነው፡፡

### 1.2.1 የጥናቱ አካባቢ

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ከሚገኙት ዘጠኝ የአስተዳደር ክልሎች መካከል አንዱ የአማራ ክልል ነው። ይህ ክልል አስራ አንድ የአስተዳደር ዞኖች ይገኙበታል። እነዚህም ሰሜን ጎንደር፣ ደቡብ ጎንደር፣ ምእራብ ጎጃም፣ ምስራቅ ጎጃም፣ የአዊ ብሄረሰብ፣ ሰሜን ወሎ፣ ደቡብ ወሎ፣ የኦሮሚያ ብሄረሰብ፣ ሰሜን ሸዋ፣ የባህር ዳር ከተማ ልዩ ዞን እና የዋግ[2] ኽምራ ብሄረሰብ ዞን ናቸው (አበባው፣2001፣3)።

ቀደም ሲል በወሎ ክፍለ ሃገር ከነበሩት አስራ ሁለት አውራጃዎች መካከል አንዱ የነበረው የዋግ አውራጃ ከሚያዝያ 1986 ዓ.ም ጀምሮ በዞን ደረጃ ተዋቅሮ የዋግ ኽምራ ብሄረሰብ ዞን ተብሎ፣ በክልሉ ከሚገኙ ሶስት[3] የብሄረሰብ ዞኖች አንዱ ሆኗል (አበባው፣2001፣3)። የዚህ ዞን ስያሜ የተወሰደው ዋግ ከሚለው የቀድሞ የአውራጃ ስሙና ኽምራ ከሚለው በዞኑ ኽምጣኛን በአፍ መፍቻ ቋንቋነት ከሚናገረው ማህበረሰብ ስም ጥምረት ነው። ይህንን አሰያየም በሚመለከት *Vaughan(2003:242)* እንደሚከተለው አስፍረዋል፤ በአሁኑ የዞኑ ስያሜ ላይ ታሪካዊ የሆነው ስነ ምህዳራዊና ፖለቲካዊ ስያሜው ዋግ እና የማንነት መግለጫው ኽምራ በጥምረት ተካተውበታል፡፡

የዋግ ኽምራ ዞን የሚገኘው በአማራ ክልል ሰሜናዊ ጫፍ፣ በሰሜን፣ በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ ከትግራይ ክልል፣ በደቡብ ከሰሜን ወሎ፣ በምእራብ ከሰሜንና ከደቡብ ጎንደር፣ በመዋሰን ነው። በማእከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ (2003 ዓ.ም፣24) መረጃ መሰረት፣ የዋግ

---

[2] ዋግ የሚለው ቃል ምንጩ ወይ የሚለው የኽምጣኛ ቃል ሲሆን፣ የአማርኛ ትርጉሙም ዋጋ ማለት ነው፡፡
[3] ሌላዎቹ የኦሮሚያ እና የአዊ ብሄረሰብ ዞን ናቸው፡፡

ኸምራ አስተዳደር ዞን ስፋት 9039.04 ካሬ ኪሎ ሜትር ነው፡፡ ዞኑ እስከ 1998 ዓ.ም ድረስ በሶስት ወረዳዎች ማለትም ድሃና ወረዳ፣ ሰቆጣ ወረዳና ዝቋላ ወረዳ የተከፈለ ነበር። ከዚያን ወዲህ ግን በስድስት ወረዳዎችና በአንድ የከተማ አስተዳደር ተከፍሏል። እነዚህም ሰቆጣ ከተማ አስተዳደር፣ ሰቆጣ ወረዳ፣ ድሃና ወረዳ፣ ስሃላ ሰየምት ወረዳ፣ አብርገሌ ወረዳ፣ ጋዝጊብላ ወረዳ፣ እና ዝቋላ ወረዳ ናቸው። በዞኑ ውስጥ 122 የገጠርና 3 የከተማ በድምሩ 125 ቀበሌዎች ይገኙበታል። እንደ ኤ.አ 2007 የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤት መሰረት የዞኑ የህዝብ ብዛት 426,213 ነው። ከዚህ ውስጥ 213,845(50.1%) ወንድ፣ 212,368 (49.83%) ደግሞ ሴት ነው። ይህ ቁጥር በገጠርና በከተማ ተከፍሎ ሲገለፅ ደግሞ፣ በከተማ 29,951 (7.02%) ሲሆን ይህም ወንድ 14,243 (47.55%)፣ ሴት 15,706 (52.44%) ነው። በገጠር ደግሞ 396,262 (92.98%)[4] ሲሆን ይህም፣ ወንድ 199,602 (50.37%)፣ ሴት ደግሞ 196,660 (49.63%) ነው። በዞኑ ዝቅተኛ ቦታው የተከዜ በረሃ ከባህር ወለል በላይ 1000 ሜትር ሲሆን፣ ከፍተኛው ደግሞ ከባህር ወለል በላይ 3,715 ሜትር ከፍታ ላይ የሚገኘው የቤላ መስቀሎ ሰንሰለታማ ተራራ ነው። በዞኑ ከሚገኙት ወንዞች መካከል ትልቁና ዞኑን ከትግራይ ክልል የሚያዋስነው የጥራሪ ወንዝ ነው። ጥራሪ ወንዝ የሚገኘው በወጣ ገባ እና ተራራማ ቦታ መሃል ነው፤ ከዚህም ሌላ ሞቃታማም ነው፡፡

ጌታቸው (2000፣160) እንዳሰፈሩት፣ ዞኑ ሶስት የአየር ጸባይ ማለትም ደጋ፣ ወይና ደጋ እና ቆላ ሲኖሩት በመቶኛ በተከታታይ 8.3 % ፣ 34.5 % እና 57.2 % ነው። አማካይ ዓመታዊ የዝናብ መጠኑም ከፍተኛው 681 ሚሊ ሜትር ሲሆን ይህም በክረምት ብቻ የሚገኝ ነው። ዞኑ በበጋ ዝናብ አያገኝም። የዞኑ አርሶ አደር የሚያመርተውም በዓመት አንድ ጊዜ በመኸር ብቻ ነው። ከተወሰኑ የመስኖ ምርት አምራች አካባቢዎች በስተቀር በዞኑ የበልግ ምርት የሚባል አይታወቅም፡፡

በአማራ ክልል ድርቅ በተደጋጋሚ ከሚያጠቃቸው አካባቢዎች መካከል አንዱ ይህ ዞን ነው፡፡ በኸምራ ጎኸ (1993፣6) ሰፍሮ እንደሚገኘው በተለይም በቅርቡ በኢትዮጵያ የድርቅና የርሃብ ወቅት ተብለው በሚጠቀሱት እንደ ኢትዮጵያውያን አቆጣጠር የ1966 እና የ1977ቱ ድርቅ የዞኑን ህዝብና እንስሳት እጅግ በጣም የጎዳና ህዝቡን ለእልቂትና ለስደትም የዳረገ ነበር፡፡

[4] ከዚህ መረጃ እንደምንረዳው አብዛኛው የዞኑ ህዝብ የሚኖረው በገጠር ነው ፡፡

በተለይ በ1977 አቅም ያለው ወደ ስደት ሲሄድ ሌላው ደግሞ ኮረም ከተማ ጋንዶ በሚባለው ሜዳ ላይ በነበረው መጠለያ ተሰባስቦ ይረዳ ነበር፡፡

የዋግ ኽምራ ዞን ዋና ከተማ ሰቆጣ ናት። ሰቆጣ ከአዲስ አበባ ሰባት መቶ ሃያ ኪሎ ሜትር፣ ከክልሉ ዋና ከተማ ከባህር ዳር አምስት መቶ ስልሳ ኪሎ ሜትር፣ ከላሊበላ እና ከመቀሌ ደግሞ አንድ መቶ ሰላሳ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች።ይህች ከተማ ጥንታዊ ከሚባሉት ከተማዎች መካከል ትጠቀሳለች። ይህንንም Pankhurst(1982:125) ሲገልጹ፣ ሰቆጣ፣ የዋግ ዋና ከተማ፣ በዘር ሀረግ እየተወራረሱ የሚገዙት የዋግ ሹሞች መቀመጫ ስትሆን፣ በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ-ዘመን በሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢ ታዋቂ ከነበሩት ከተማዎች ውስጥ አንዷ ናት ብለዋል። McCan(1984:24)ም የዋግሹሞች መቀመጫነቷንና ጥንታዊ ከተማነቷን በሚመለከት፣ ሰቆጣ ከ17ኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ በሰሜን ወሎ የታወቀች የከተማ ማእከል የነበረች ከተማ ስትሆን ለረዥም ጊዜም የዋግሹሞች መቀመጫ ነበረች በማለት አስፍረዋል፡፡

የአካባቢው የባህላዊ ዘፈን ተጫዋቾችም ሰቆጣን የሚያሞግሷት (የሚያወድሷት) ከዋግ ሹሞች መቀመጫነቷ ጋር እያይዘው ነው፡፡ እንዲህ የሚል ቃል ግጥምም አላቸው፤

ካልተቀጠቀጠ አይበላም ቋንጣ፣
አየር ባይር ሲሉት ይሸሻል አንበጣ፣
የዋግ ሹሞች አገር ናፈቀኝ ሰቆጣ፡፡

ሰቆጣ የምትታወቀው በጥንታዊነቷና በዋግ ሹሞች መቀመጫነቷ ብቻ አይደለም፤ በድሮ ጊዜ የታወቀች የገበያ ቦታም ነበረች፡፡ይህንንም McCan(1987:24)) ሲገልጹ፣ የሰቆጣ እድገት እና መረጋጋት የተገኘው በአስተዳደራዊ ሚናዋ ብቻ አይደለም። በገበያ ቦታነት አገልግሎቷም እንጂ። ከቅርብ፣ ከመካከልና ከሩቅ ለሚመጡ በጥቅሉ ለኢትዮጵያውያን ሁሉ፣ ከሰሜን ወደ ደቡብ፣ከደቡብ ወደ ሰሜን ለሚደረግ የንግድ እንቅስቃሴ ቁልፍ ቦታ ነበረች ብለዋል፡፡ *Vaughan(2003*:248)Pankhurst,1968:520)ን ጠቅሰው የሰቆጣን የገበያ ቦታነት እንደሚከተለው አስፍረዋል፤ በሰሜን ኢትዮጵያ የነጋድራስነት[5] ማእረግ ያላቸው ሰዎች

[5](ርእሰ-ነጋድያን) የነጋዴ አለቃ፡፡ ከመንግስት የተሾመ(ደስታ፣1962፣837)

ይገኙባቸው ከነበሩት ስድስት ታዋቂ የገበያ ቦታዎች መካከል አንዷ ሰቆጣ ናት፡፡ ስለዚህ ሰቆጣ በቁጥር የተወሰኑ ከነበሩት የገበያ ከተሞች ተርታ የምትሰለፍ እንደነበረች እንረዳለን፡፡

አላምረው(1986፣14) በሰቆጣ ገበያ የሚገበያዩ አካላትንና ከተማዋ የተለያዩ ማህበረሰቦች የባህል ልውውጥ የሚያደርጉባት እንደ ነበረች ጠቅሰው እንደሚከተለው አስፍረዋል።

> የሰቆጣ ገበያ ለትግራይ፣ ለሰሜን፣ ለቤጌምድር፣ ለጎጃም፣ ለአማራና ለወሎ ገበያተኞች አማካይ ሆኖ የተለያዩ ሸቀጦች ይውሉበት ነበር። በዚህም የተነሳ የሰቆጣ ስም በጣም ገናና ነበር። የአገው፣ የአማራ፣ የትግሬና የሌሎችም ማህበረሰቦች ወግና ባህሎች የሚገናኙበት ከተማ ሰቆጣ ከተማ ነበር ብሎ ለመናገር ያስችላል። ከ17ኛው እስከ 20ኛው ምእተ ዓመት አጋማሽ ድረስ ሰቆጣ በዝናዋ የገነነች እንደ ነበረች በዘመኑ የተጻፉ መጻህፍትን በዋቢነት ማቅረብ ይቻላል።

አፀደ(1996፣21) የአካባቢውን አባቶች[6]በመጥቀስ፣ የሰቆጣን ታዋቂ የገበያ ቦታነት በሚመለከት እንደሚከተለው እንዳሰፈረችውም በከተማዋ የተለያዩ ነገሮች ግብይት ይካሄድ እንደነበርና ለመገበያየት የሚመጡት ሰዎች ማረፊያም የተለያየ ሰፈር እንደ ነበር ነው።

> በድሮ ጊዜ ወደ ሰቆጣ የማይመጣ አልነበረም፤ ከኤርትራ፣ ከጎጃም፣ ከቤጌምድ ከወለጋ፣ ጨርቁን በርበሬውን ጨውን ይዞ ይመጣል፤ ከዚህ (ከሰቆጣ) ደግሞ፣ ቅቤውን፣ ማሩን፣ ከብቱን ፍየሉን ቆዳውን ገዝቶ ይሄዳል።ለገበያ ከሚመጡት ውስጥ አማራዎች የሚያርፉት አሁንም "አማራ ተራ" ተብሎ በሚጠራው ሰፈር ነው።ይህ ሰፈር ይህንን ስም ያገኘውም ሲያርፉ ከነበሩት ነጋዴዎች ማንነት ነው ፤…የገበያው ቀንም ማክሰኞና ረቡእ ነበር።ገበያተኛውና የሚገበያዩት ነገርም በርካታ ስለ ነበረ፣ተራውም (የሚገዛበትና የሚሸጥበት) እንደ ዛሬ በአንድ ቦታ ላይ አልነበረም።አህያ፣ ቅቤና ማር፣ በርበሬ፣ ቡና፣ አቡጀዴ፣ ጫማ፣ ጨው ፣ ፍየል በተለያዩ ቦታዎች ነበር የሚገዙትና የሚሸጡት፤ እነዚህም ተራዎች፣ አህያ ተራ፣ እህል ተራ፣ ቅቤና ማር ተራ፣ ጨው ተራና ፍየል ተራ ተብለው ይጠሩ ነበር። ከእነዚህ ውስጥ እስካሁን የሰፈር ስም መጠሪያ ሆነው የቀጠሉት "አማራ ተራ" እና "አህያ ተራ" ብቻ ናቸው፤ ሌሎቹ ተረስተዋል።

ይሁን እንጂ ይህ በማእከላዊነት ያገለግል የነበረው የገበያ ቦታነቷ ባሁኑ ጊዜ ግን አይታይም፡፡

[6] ሻምበል ሲሳይ ዘገየ፣ ቄስ ካሴ አስረስ፣ መቶ አለቃ ወዳጅ አደራ እና አቶ ካሴ ሹምየ ናቸው፡፡

ስለዚህ የዛሬዋ የዋግ ኽምራ አስተዳደር ዞን ዋና ከተማ ሰቆጣ፣ ከቀደምት የኢትዮጵያ ከተሞች ውስጥ አንዷ ስትሆን፣ በዋግ ሹሞች መቀመጫነቷ እና በገበያ ቦታነቷ የምትታወቅ ነበረች።

### 1.2.2. የህብረተሰቡ የዘር ሀረግ፣ ታሪካዊ ዳራ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ

ቀጥሎ ስለ የህብረተሰቡ የዘር ሀረግ፣ ታሪካዊ ዳራ እና የማህበረሰቡ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ ይቀርባል፡፡

#### 1.2.2.1 የህብረተሰቡ የዘር ሀረግ

ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው በአሁኑ ጊዜ የዋግ ኽምራ ዞን የብሄረሰብ አስተዳደር ዞን ነው፡፡ ለዚህ ምክንያቱም የአገዎች መኖሪያ ከሆኑት ዞኖች ውስጥ አንዱ በመሆኑ ነው፡፡ የአገው ህዝብ ደግሞ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ህዝብ መሆኑን የተለያዩ የታሪክ ምሁራን በጽሁፎቻቸው አስፍረው እናገኛለን። ለአብነት ያህል Taddesse(1988:6) በጽሁፋዊ ምንጮች ተገልጸው ከምናገኛቸው የኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል የአካባቢው በጣም ጥንታዊ ነዋሪዎቹ አገዎች ናቸው ሲሉ፣ በሌላ ስራቸው (1972:37) ደግሞ አገዎች ከጃማ ወንዝ በስተሰሜን በሚገኙ ከፍተኛ ቦታዎች ላይ ቀደምት ነዋሪዎች ናቸው ብለዋል። Bahruም (2002:5) ዋና ዋና ከሚባሉት ቀደምት የኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል አገዎች ተጠቃሽ እንደሆኑ ሲገልጹ፣ የኩሽ ቋንቋ ተናጋሪ ከሆኑት ኢትዮጵያውያን ውስጥ በታሪክ ታዋቂዎቹና ዋና ዋናዎቹ አገውና ቤጃ ናቸው ብለዋል፡፡

Bender እና and others (1976:40) ደግሞ የአገውን ህዝብ ጥንታዊነትና በአሁኑ ጊዜ መኖሪያቸው የተለያየ መሆኑን አስመልክተው ሲገልጹ፣ የአገው ህዝቦች በአንድ ወቅት ብዙውን የኢትዮጵያ ከፍተኛ ቦታ ሸፍነው የነበሩ ናቸው፤ በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ ቦታዎች ተበታትነው ለመገኘታቸው ምክንያቱ በሴም ቋንቋ ተናጋሪ ህዝቦች ቦታቸውን እንዲለቁ በመገደዳቸው መሆኑ ይታመናል ይላሉ።

አገዎች ከጥንታዊ የኢትዮጵያ ህዝብነታቸው በተጨማሪ፣ የተለያዩ የጥራጥሬ ተክሎች ማምረትን በኢትዮጵያ ያለማመዱ እንደ ሆኑም (Levine,2000:29;Melakneh,1990:20 እና Gamst,1968:12(Murdock,1959ን በመጥቀስ) ገልጸዋል። ሽቱ አያን እና

ሌሎችም(1988፣6) ይህንኑ ሲገልጹ፣ አገዎች በኢትዮጵያ ከሌሎች ሁሉ ቀደምትነት ያላቸው ናቸው። በግብርና ስራ በዋናነት የሚጠቀሱ አንኳር አንኳር የሆኑ የእህል አይነቶችን አበርክተዋል ብለዋል።

በአንድ ወቅት በአንድ አካባቢ ይኖሩ የነበሩት ጥንታዊዎቹ የአገው ህዝቦች በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ ቦታዎች ተበታትነው ይገኛሉ። ይህንንም Levine(2000:37) ሲገልጹ፣

> አገዎች ከአክሱም መነሳት በፊት በሰሜን ኢትዮጵያ ከፍተኛ ቦታዎች ከሌላው ልቀው ይኖሩ የነበሩ ህዝቦች ሲሆኑ፣ እስከ 17ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ጠንካራ ኀይል ያላቸው ሆነው በአካባቢው ቀጥለው ነበር...በአሁኑ ጊዜ የአገው ቅሪቶች በኤርትራ፣ በቤጌምድር በወሎና በጎጃም ኪስ ቦታዎች ይገኛሉ።

በሌላ በኩል አገዎች በሶስት እንደሚከፈሉና የዋግ አገዎች (ኽምራዎች) ቀደምት ቦታቸውን ሳይለቁ በነበሩበት ቦታ እንደሚገኙ ታዬ(1964፣32) እንደሚከተለው አስፍረዋል፤

> አገዎች ግን በ3 ተከፍለው ቋንቋቸውም ስሩ አንድ ሲሆን በየክፍላቸውና በየአገራቸው ጥቂት ጥቂት ልዩነት ያለው ሆነ፡፡ እነርሳቸውም በ3 አገር ስም ይጠራሉ፡፡የላስታ አገው፣ የዳሞት አገው፣ የሐልሐል በጎስ አገው ይባላሉ።የሁሉም መሰረትና ምንጭ የላስታ አገው ነው፤ ...የላስታ አገዎች **በዋግ የሚኖሩ ዋኖቹ ናቸውና** በቀዳማዊ ምኒልክ ጊዜ የያዙትን አገር አልለቀቁም፤ እስከ ዛሬ አልተነቃነቁም፡፡ (አጽንኦት የራሴ)

እነዚህ የአገው ዘሮች መቼና በምን ምክንያት ከዋግ ተነስተው ወደ ተለያዩ ቦታዎች እንደ ሄዱ ደግሞ በጽሁፋዊ ምንጮችና በአፈ-ታሪክ በተለያየ መንገድ ተገልጿል።ከእነዚህ የአገው ዘሮች መካከል የሁለቱን[7]፣ የቢለንና የአዊን የእንቅስቃሴ ምክንያትና ዘመን እንመልከት።

ቢለኖች ከዋግ ላስታ የተንቀሳቀሱበት ምክንያት ተብሎ በጽሁፋዊ ምንጮች የተገለጸው ሁለት አይነት ነው። አንዱ ችግር ነው የሚል ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ድንበር ጥበቃ ነው የሚል ነው። ለምሳሌ ዮሀንስ(1940፣120) የሐልሐል በጎስ አገዎች ግን በአንድ ዘመን በየሀገሩ ረሃብ ስለሆነ እንዲሁ ከላስታ አገው ተለይተው 7 ወንድማማቾች ከነ ሚስቶቻቸውና ከነልጆቻቸው 5 እህቶቻቸው ባሎቻቸው ተሰደው ሀልሀል በጎስ ገቡ። ከዚያም ዱሩን መንጥረው እባቡን ፈጅተው ቤት ሰርተው አገር አቅንተው ተቀመጡ ይባላል።በማለት ለመንቀሳቀሳቸው ምክንያቱ ረሃብ እንደ ሆነ ሲገልጹ፣ Adhana(1988:747)

[7] ቅማንቶች ከጥንታዊዎቹ አገዎች እንዴት ተለይተው ወደ ጎንደር እንደሄዱ የሚገልጽ የጽሁፍም ሆነ የቃል መረጃ አላገኘሁም፡፡

ደግሞ የነገሱበት ጊዜ የማይታወቀው የዛጉዌ ነገሥታት፣ ቢለኖችን ወደ ሰሜን የላኩዋቸው በቤጃዎች የሚወሰደውን መሬት እንዲከላከሉና የንግድ መስመሩን ከስዋኪን ወደ የተቀደሱ ቦታዎች የሚደረገውን ጉዞ ነፃ እንዲያደርጉ ነው ብለዋል። Kiflmariam(1986:7) ደግሞ ይህንን ስደት የሚያመለክቱ የቦታ ስሞች መኖራቸውን እንዲህ በማለት ገልጸዋል፤ ስደቱ ከላስታ እስከ ከረን በሚገኙ የአገውኛ የቦታ ስሞች ምልክቱን አስቀምጧል፤እነዚህም ዲበራዋ በሰራየ፣ቺንዱዋ፣ቲልኩስትዋ፣ጀገርታው የመሳሰሉት ደግሞ በሃማሴን ይገኛሉ፡፡

ቢለኖች ተንቀሳቀሱበት ተብሎ የሚገለጸው ዘመንም የተለያየ ሆኖ እናገኘዋለን፤ Levine

(2000:71) ...ምን አልባት ወደ ሰሜን መጥተው የሰፈሩት ከ10ኛው ምእተ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ ላይ ይሆናል ይላሉ። Kiflmariam(1986:6) ደግሞ Conti Rossiniን በመጥቀስ ስደቱ በሁለት ዙር የተካሄደ ሲሆን የመጀመሪያው በአስረኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛው ደግሞ ከ1270 በኋላ የተካሄደ መሆኑን አስፍረዋል፡፡ Adhana(1988:747)ም ቢለኖች ወደ እዚህ አካባቢ የመጡት በዛጉዌ ስርወ-መንግሥት በኋላ በ11ኛው ክፍለ ዘመን ነው በማለት የሁለቱን ሀሳብ ተጋርተው አስፍረዋል።

ሌላው የአገው ብሂረሰብ አዊ ነው። አዊዎች ከዋግ ላስታ ተነስተው መሄዳቸውን የተለያዩ ምንጮች ቢያሰፍሩም፣የተንቀሳቀሱበት ምክንያትና ዘመን ግን የተለያየ ሆኖ እናገኘዋለን። በመጀመሪያ የምናገኘው በዮሀንስ(1940፤120) የተገለጸው ነው። እንደ እሳቸው አገላለጽ አዊዎች ከዋግ ላስታ ተነስተው የሄዱት ለአደን ነው። Melakneh(1990:29)ም ለአደን እንደሄዱ አስፍረዋል፡፡

አዊዎች ወደ ጎጃም ሄዱ የሚባለው በአንድ ዙር ሳይሆን በሁለት ዙር ነው። የመጀመሪያዎቹ ሰባት ሆነው መሰደዳቸውን የሄዱበትንም አካባቢ በእነዚህ ሰባት ሰዎች ስም መጥራታቸውን Taddesse(1988:11) ዘርዘር አድርገው እንደሚከተለው አስፍረዋል፡፡

> የአገው ምድር እና የመተከል አገዎች Laneta Awiya ወይም ሰባት ቤት አገውን (Seven House Agaw) ለመመስረት ከላስታ ሰቆጣ እንደመጡት ሰባት ወንድማማች አያቶቻቸው አይነት ባህል አላቸው፤ሰባት ቤት የተሰየመው ከሰባት ወንድማማቾች፣ ባንጃ (Banja)፣ አንካሻ (Ankasha)፣ ክዋክውራ (Kwakwra)፣ ጫራ (Chara)፣ መተከል (Metekkel)፣ ዚገም (Zigem)፣ እና አዘና (Azena) ነው፡፡ሌሎቹ አነስተኛ የቡድን አባላት የሆኑት ቱምሃ (Tumha)፣ ዳንጊዝሀ ወይም ዳንግላ (Dangizh (Dangla)፣

ቢል ወይ ባላያ Bil (Belaya) እና ጓዋጉሳ (Gwagwsa) ወይ ዘግየት ብለው የመጡ፣ ካልሆነም የመጀመሪያዎቹ የሰባቱ ዝርያዎች (descendants) ናቸው።እነዚህ ጥንታዊ አባቶች የሰፈሩባቸው ቦታዎች ስሞች የአውራጃ፣ የወረዳ ወይም የንኡስ ወረዳ መጠሪያ ሆነው ያገለግላሉ።

Melaknehም (1990:32-33) ታዬ ረታን በመጥቀስ የጉዞው ምክንያት አደን መሆኑን፣ ጉዞው ሁለት ዙር እንደ ነበርና የመጀመሪያና የሁለተኛ ዙር ሰፋሪዎች በተከታታይ ሰባትና አምስት መሆናቸውን በእነዚህ ሰዎች ስም የተሰየሙ ቦታዎች የአውራጃ፣ የወረዳና የንኡስ ወረዳ መጠሪያ እንደ ነበሩ፣ የአዊዎች አጠራር (አሰያየም)ም ከአማርኛው የተለየ እንደሆነ በዝርዝር አስፍረዋል።

የአገው ዘሮች በአንድ ወቅት በአንድ ላይ ይኖሩበት ከነበረው አካባቢ በተለያዩ ምክንያቶችና ጊዜያት ወደ ተለያዩ ቦታዎች መንቀሳቀሳቸውን በሚመለከት በጽሁፋዊ ምንጮች የሰፈረውን ተመልክተናል፤ ቀጥለን ደግሞ፣ የብሌንና የአዊ አገዎች ከዋግ ላስታ ተነስተው ወደ ተለያዩ ቦታዎች በምን ምክንያት እንደ ሄዱ የዋግ ኽምራ አባቶች ከገለጹት አፈ-ታሪክ መካከል የተወሰነውን እንመልከት።

ቢለኖችን በሚመለከት በአፈ-ታሪክ የተገለጸውን አፀደ(1989፤3) እንዳሰፈረችው የሂዱት በዘመኑ (በሂዱበት ዘመን) የቀይ ባህርን ወደብ አረብ፣ ጣሊያንና ቱርክ እንዳይሻገሩ ለመከላከል አስፈላጊ ስለ ነበር፣ በአጼ ካሌብ ዘመነ መንግሥት ወታደሮች በሰቆጣ አካባቢ ከሚገኘው ቤላ ተራራ ከሚባለው አካባቢ ተነስተው ለጥበቃ ሄዱ፤ የአካባቢውን ለምለምነትና ተስማሚነትን በማየት ከዚያው ለምደው ቀሩ፤ ቢለን የሚለውም ስያሜ የመነጨው ተነስተው ከሂዱበት ቦታ ቤላ ከሚለው ነው ይላሉ።

ከዚህ የምንረዳው የጉዞው ምክንያት ድንበር ለመጠበቅ ሲሆን፣ የሂዱበት ዘመንም በጽሁፋዊ ምንጮች ከተገለጸው ዘመን ቀደም ብሎ በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደሆነ ነው።

አዊዎችን በሚመለከት ደግሞ ከዋግ ተነስተው የሂዱበትን ቦታና ምክንያት አስመልክቶ በዋግ ኽምራ አባቶች የሚገለጸው የተለያየ ነው፤ አንዳንዶቹ ሰቆጣ አካባቢ ከሚገኘው ብርብር ከተባለው ቦታ ተነስተው የሂዱት በችግር ምክንያት ነው። የሂዱበት ቦታ ጎጃም ለምለም ሆኖ ስላገኙት ቦታውን አቅንተው እዚያው ቀሩ ሲሉ፣ ሌላዎቹ ደግሞ የሂዱት

ከተላጀ፣ ጉድያ እየሱስ ከተባለው ቦታ ነው፤ ሰባት ወንድማማቾች ለአደን ሄዱ፤ የሄዱበት ቦታ ለምና ማር የበዛበት በመሆኑ ወደ ዋግ መጥተው ወገኖቻቸውን ይዘው በመሄድ ሰባት ቤት አገውን አቀኑ። የተንቀሳቀሱበት ዘመን ደግሞ በዋግ ሹም ጅርወሰን ዘመን ነው ይላሉ (አፀደ፣1989፣4)፡፡

ከዚህ የምንረዳው በጽሁፋዊ ምንጮች የሰፈረው ለአዊዎች መንቀሳቀስ ምክንያት ነው የተባለው አደን፣ አባቶች በአፈ-ታሪክ ከገለጹት ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ነው።

ስለዚህ ይህ ጥናት የተመለከተው የዋግ ኽምራ ማህበረሰብ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ነዋሪ ከመሆኑም በላይ፣ በቀደምት ጊዜ የሰፈረበትን ቦታ ያልለቀቀ መሆኑን እንረዳለን፡፡

## 1.2.2.2. ታሪካዊ ዳራ

የጥናቱን ቦታ ታሪካዊ ዳራ በሚመለከት በሁለት ክፍሎ ማየት ተገቢ ነው፤ በጥቅል የአገዎችን በተናጠል ደግሞ የኽምራዎችን፣ በተከታታይም የዛጔ ስርወ-መንግስትንና ዋግ ሹምነትን በሚመለከት እገልጻለሁ፤ ምክንያቱም ሁለቱም ታሪካዊ ዳራዎች በአንድ ወቅት በኢትዮጵያ ከፍተኛ ግምት ተሰጥቷቸው የነበሩና በአሁኑ ጊዜ የሚገኙትን አገዎች ታሪካዊ ሁኔታ የሚመለከቱ ናቸው፡፡

### 1.2.2.2.1 የአገዎች ታሪካዊ ዳራ

አገዎች በአንድ ወቅት በኢትዮጵያ በከፍተኛ ስልጣን ላይ የነበሩ መሆናቸውን በታሪክ ምሁራን ስራዎች ውስጥ ሰፍሮ እናገኛለን። በትረ-ስልጣናቸውም የዛጔ ስርወ-መንግስት ሲሆን ዋና ከተማቸውም ላሊበላ ነበር (Ullendorf,1966:64;Wudu,1995:7; Melakneh,1990:24) )። የስርወ-መንግስቱን ስያሜ በሚመለከት የተለያዩ የታሪክ ጸሀፊዎች ሶስት የተለያየ ሀሳብ አስፍረዋል፤ አንዳንዶቹ ከአገዎች ስያሜ ጋር የተያያዘ መሆኑን ሲገልጹ፣ ሌላዎቹ ደግሞ በትረ ስልጣኑን ጨብጠው ከነበሩት ሰዎችና ወደ ስልጣን ለመውጣት ካከናወኑት ድርጊት ጋር የተያያዘ ስያሜ መሆኑን ይገልጻሉ።ከእነዚህ መካከል የተወሰኑትን እንመለከታለን። ተክለ ጻድቅ(1966፣344) በትረ-ስልጣኑ ሁለት አይነት የስያሜ መነሻ እንዳለው ሲገልጹ፣...ከዚህ በኋላ መራ ተክለ ሃይማኖት በኢትዮጵያ ነገሠና አዲስ ስርወ-መንግሥት አቀመ። ስመ-መንግሥቱም ዛጉዬ ተባለ፤ ዛጉዬ የተባለበት

ምክንያት እንደ ግማሾቹ ዘአገው (የአገው ወገን) ማለት ነው። እንደ ግማሾቹ ደግሞ ድል ነዓድን ስላባረረ፤ ግዕዝኛውን ቃል ዘአጉየየ (ያባረረ) የሚለውን በመከተል ዛጔ ተባለ ይላሉ።

የዛጔ ስርወ-መንግስት የስያሜ መነሻ ብቻ ሳይሆን፣ ወደ ስልጣን የወጣበት ምክንያትም ቢሆን ጥርት ብሎ አለመቀመጡን የታሪክ ምሁራን በስራዎቻቸው አስፍረዋል(Gamst (1968:12 and Bahru,2002;8)። አያሌው(2007፣88) ደግሞ የአክሱም ዘመነ መንግሥት ወደ ዛጔ ዘመነ መንግሥት ሊሸጋገር የቻለበትን ምክንያት በሚመለከት፣ በርካታ ምንጮችን እያጣቀሱ ከገለጹ በኋላ፣ የሚስማሙበትን እንደሚከተለው አስፍረዋል፤

> ...በምክንያትነት የተገለጸው የጋብቻ ጉዳይ (የንጉሱ ልጅ መሶበ ወርቅ) መራ ተክለ ሃይማኖትን አግብታ ከሚለው ይልቅ የአገዎች ሃይል እየበረታ መጥቶ በትረ-ስልጣኑን በሽግግር መልክ ወይም በጦር ሃይል በመውሰድ መዲናቸውን በላስታ ዋግ አድርገው ከ300 ዓመታት የበለጠ ዙፋን ላይ ሊቀመጡ በቅተዋል... የሚለው ተቀባይነት አለው።

ተክለጻድቅም (1966፣331) ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሀሳብ አስፍረዋል፡፡

ሌላው ደግሞ የዛጔ ስርወ-መንግስት ወደ ስልጣን የመጣበትም ዘመን በትክክል በዚህ ዘመን ተብሎ በእርግጠኛነት አለመስፈሩን የታሪክ ምሁራን አስፍረዋል፡፡ ይህንን አስመልክተው፣ Sergew (1972,40) የዛጉዌ ስርወመንግስት የተጀመረው በ1030 እና 1050 መካከል ሊሆን እንደሚችል ማሰላት እንችላለን ብለዋል፡፡

ይህ ብቻ አይደለም ስልጣን ላይ የወጣው በተለያዩ ምክንያቶች ነው የተባለው የአገው ስርወ መንግስት ስልጣን ላይ የቆየባቸው ዓመታትን በሚመለከትም በተለያዩ የታሪክ ምሁራን የተገለጸው የተለያየ ነው። Taddesse(1972:55) የዛጔን ስርወ-መንግስት የግዛት ዘመን በሚመለከት ሁለት የማይጣጣሙ አገላለጾች አሉ። የተለመደው ይኩኖ አምላክ በ1270 ስልጣኑን እስኪይዝ ድረስ ለ333 ዓመታት ቆይቷል የሚለው ሲሆን ፣ ሌላው ደግሞ 133 ዓመት ብቻ ነው የሚል ነው ሲሉ፣ Levine(2000:71) ደግሞ የዛጔ ስርወ-መንግስት በ1135 ላስታ ላይ ተመሰረተና ለ135 ዓመታት ገዛ ይላሉ። Bahru(2002;8) ደግሞ በትረ-ስልጣኑ ለ120 ዓመታት የቆየ መሆኑን አስፍረዋል፡፡ Aymro(1970:5) ደግሞ በትረ ስልጣኑ የቆየባቸው ዓመታት ሁለት መቶ መሆናቸውን አስፍረዋል፡፡ ለዚህ ሳይሆን አይቀርም

Sergew(1972,39) የዛጌ ስርወ-መንግስት ዘመንን አስመልክቶ በጽሁፋዊ ምንጮች የሚታየው የሚጣጣም አይደለም። የግዛት ዘመኑ ከ133-375 ዓመት ድረስ የሚል የተለያየ ነው። የሚታወቀው ያከተመበት በ1268 ወይም በ1270 መሆኑን ነው ያሉት። Bahruም (2002;8) ስርወ-መንግስቱ በ1270 ማክተሙን አስፍረዋል፡፡

Sergew(1972:30) በማያያዝ የገለጹትም ስርወ-መንግስቱ የተጀመረበትንና ስልጣን ላይ የቆየበትን ዘመን ብቻ ሳይሆን፣ በስርወ-መንግስቱ ወቅት የገዙት ንጉሦች መጠንም በትክክል አለ መታወቁን ነው፤...ሶስት አይነት ዝርዝር አለ፤ አጭር፣ ረጂም እና በጣም ረጂም። አጭሩ አምስት ገዥዎችን የያዘ ነው፤ ረጂሙ አስራ አንድ ገዥዎችን ይዟል፤ በጣም ረጂሙ ደግሞ አስራ ስድስት ገዥዎችን የያዘ ነው። በማለት ዝርዝራቸውን አስፍረዋል። Melaknehም (1990) ታዬን በመጥቀስ ከ920-1255 (1253) ለሶስት መቶ ሰላሳ ሶስት ዓመታት አስራ አንድ ነገስታት መግዛታቸውን ስም ዝርዝራቸውን እና እያንዳንዳቸውም ስንት ዓመት ስልጣን ላይ እንደቆዩ በመግለጽ አስፍረዋል።

የዛጌ ስርወ መንግስት ከስልጣን የወረደበት ምክንያትም ቢሆን ይህ ነው ተብሎ ተለይቶ የታወቀ አይደለም፤ ምክንያቱም በተለያዩ ምንጮች ሰፍሮ የምናገኘው ምክንያት የተለያየ ነው። ለአብነት ያህል Taddesse(1972:283) የዛጌ የሰለሞናውያን ስርወ-መንግስት እንደገና ወደ ስልጣን የመውጣት ሁኔታ እንዴት እንደ ተከናወነ የሚያመለክቱ ሁለት አገላለጾች አሉ፡አንዱ በሃይል ነው ሲል፣ ሌላው ደግሞ በቤተክርስቲያን መሪዎች ጣልቃ ገብነት በድርድርና በሰላም የተከናወነ ነው ይላል ብለዋል። Levine(2007:73) ደግሞ ስርወ-መንግስቱ በጦርነት መውደቁን ሲገልጹ፣ አማራ የሆነውና ዘመቻውን የመራው ይኩኖ አምላክ የዛጌ ስርወ-መንግስት እንዲያከትም አደረገ፤ ንጉሡን ገድሎም ተስፋ ኢየሱስ በሚል ስም ዘውድ ደፋ ይላሉ። ሌሎችም (Levine 2007:73; Kiflmariam 1986:9 and Taddesse,1972:68) የዛጌ-ስርወ መንግስት በሃይል ስልጣኑን እንዲለቅ መደረጉን አስፍረዋል፡፡

ስለዚህ በአንድ ወቅት ከፍተኛ ስልጣን ላይ የነበረው የአገዎች የዛጌ ስርወ-መንግስት የስያሜው መነሻ፣ ስልጣን ላይ የወጣበት ምክንያት፣ በትረ ስልጣኑ ላይ የተቀመጡት ሰዎች መጠን፣ ስልጣን ላይ የቆየበትና ከስልጣን የወረደበት ምክንያት እስካሁን በትክክል የማይታወቅ መሆኑን የመስኩ ምሁራን በስራዎቻቸው ማስፈራቸውን መረዳት እንችላለን።

ይሁን እንጂ ስርወ-መንግስቱ በትረ ስልጣኑን ተረክቦ በርካታ ተግባራት ማከናወኑ ግን ይታወቅለታል፤ ለአብነት ያህልም የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናትን መጥቀስ ይቻላል፤(Kiflmariam,1986:9;Lipsky,1962:44;Bahru,2002;8,Aymro,1970:5-6,and Wudu,1995,iii)) እንደ ገለጹት ዝናን ያተረፉት የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት የተገነቡት በዛጔ ዘመነ መንግስት ነው፡፡

1.2.2.2.2 የዋግ ኽምራዎች ታሪካዊ ዳራ

የድሮዋ ዋግ የአሁኗ ዋግ ኽምራ በጥንታዊ ህዝቦች መኖሪያነቷ ብቻ ሳይሆን በገዥዎቿም ትታወቃለች።የዋግ ገዥች ዋግ ሹሞች ይባሉ ነበር።ይህንንም Wudu(1995:14); እና 1998:228) በስራዎቻቸው አስፍረዋል። ዮሀንስ (1940፣223) ደግሞ የተለያዩ አካባቢዎች ገዥዎች፣ የሚገዙበት አካባቢ ገዥነታቸው እየተገለጸ ማእረጉ ይሰጣቸው እንደ ነበር፣ ዘላቂነት ያገኘው ግን የዋግ ሹሞች ብቻ እንደሆነ እንደሚከተለው አስፍረዋል፤ በዚህ ስም የዋጉ፣ የሽሬውና የጉራጌው አገረ ገዥዎች ዋግ ሹም፣ ሽሬ ሹም፣ ጉራጌ ሹም እየተባሉ ይጠሩበት ነበር። ነገር ግን የሌላዎቹ እየቀረ ሲሄድ የላስታው (የዋጉ) ዋግ ሹም እየተባለ ይኸው ከፍ ባለ ማእረግ እስከ ጊዜያችን ደርሷል።

የዋግ ሹምነትን አጀማመር በሚመለከት በጽሁፍና በአፌ-ታሪክ የሚገለጸው በጣም የተለያየ ነው። የዋግ ኽምራ አባቶች ማእረጉ የተጀመረው ከክርስቶስ ልደት በፊት እንደ ነበረ መግለጻቸውን ነው አፀደ (1989፣21) ያሰፈረችው፣ እንደ አፌ ታሪኩ ከሆነ ዋግ ሹምነት የተጀመረው በዚህ ወቅት አካባቢው ይመራ በነበረው በዋግ ሹም ሲራክ ነው።

ጽሁፋዊ ምንጮች ደግሞ የተለያየ ዘመን አስፍረዋል፣ የአንዳንዶቹ በ13ኛው ክፍለ ዘመንም በ16ኛው ክፍለ ዘመን የሚል ሲሆን የሌላዎቹ ደግሞ 16ኛው ክፍለ ዘመን የሚል ነው። በ13ኛውና በ16ኛው ካሉት መካከል፣ Wudu(1995,14 and 1998:221) ይህ ሹመት የተጀመረው በ1270 ዓ.ም የዛጉዌ ስርወ-መንግስት ተገርስሶ በሰለሞናውያን ሲተካ ነው የሚልና ሌላው ደግሞ በ16ኛው ክፍለ ዘመን የሚለው ከዋግሹም ዮናታን ጋር የተያያዘ መሆኑን የሚገልጸው ነው፡፡ ዋግሹሙ በግራኝ ጦርነት ጊዜ ላደረጉት ተጋድሎ የተሰጠ ማእረግ ነው፡፡ ለክብሩ ሲባልም በአካባቢው፤

ለክብረ መንግስቱ ቢዋጋ ዮናታን፤

ግምጃ ሱሪ ታጥቆ ታጠበ በዳታን፡፡

የሚል ቃል ግጥም እንደተገጠመላቸው አስፍረዋል (Wudu,1995:23)፡፡

ብርሃነ መስቀል(1951፣118-119)ም የዋግ ሹምነት ማእረግ የተሰጠው (የተጀመረው) በ16ኛው ክፍለ ዘመን ነው፤ ይኸውም፣ የዋግና የላስታ ህዝቦች የግራኝ መሐመድን ወረራ ለመቋቋም ላደረጉት ግንባር ቀደም ተፋላሚነት ቃል ከተገባላቸው ውስጥ አንዱ በመሆኑ ነው ብለዋል፡፡

ስለተጀመረበት ዘመን የሚገለጸው ቢለያይም እስከ 1966 የዘውድ አገዛዝ መውደቅ ድረስ አካባቢው ይተዳደር የነበረው በዋግ ሹሞች ነበር። ዋግ ሹምነት በወቅቱ ልዩ ክብር የሚሰጠው ማዕረግ ነበር፡፡ ይህንንም አባቶች በአፈ-ታሪክ ያገኙትን ጠቅሰው የገለጹላትን አፀደ(1989፣24) እንደሚከተለው አስፍራለች፡፡

> የማእከላዊ መንግሥት ንግሥና በሚካሄድበት ወቅት ዋግ ሹሞች አንጋሽ ነበሩ፡፡ ለምሳሌ አጼ ኃይለሥላሴን ያነገሱት (ያለበሱት) ዋግ ሹም ከበደ ናቸው፡፡ ዋግሹሞች ስልጣናቸው የሚሻረውም ሆነ የሚጸናው በማእከላዊ መንግሥት ነው፡፡ ንጉሦች ግብር በሚያበሉበት ወቅት ወደ ግብር መብያው አዳራሽ በመጀመሪያ እንዲገቡ የሚጠሩት ዋግሹም ናቸው፡፡ በዋግ ሹሞችና በንጉሦች መካከል ጋብቻ ነበር፡፡ ይህም የዋግሹምነትን ትልቅነት ያሳያል፡፡

Wudu(1995)ም ዋግሹሞች ከራሶች ይበልጥ በንጉሦች ዘንድ ልዩ ከበሬታ የሚሰጣቸው እንደ ነበሩ እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡

> ዋግ ሹሞች እስከ ቤተ-መንግሥቱ በር ድረስ የብር ነጋሪት ይጎስሙ ነበር፡፡ ዋግ ሹም ብሩም ወደ አጼ ሚኒልክ ቤተ-መንግሥት ሲገቡ ለሌሎች የማይፈቀደውን ነጋሪታቸውን እስከ ቤተመንግሥት ቅጥር ግቢ ድረስ እየጎሰሙ ገብተዋል፡፡ ንጉሡ በሚታጠብበት የወርቅ ዳታን ይታጠቡ እንደ ነበርና በዚህም ዋግሹም ተፈሪ አጼ ዮሐንስ በታጠቡበት የወርቅ ዳታን መታጠባቸውን፣ ግብር የማይገብሩ እንደ ነበር፣ በብር ወንበርም ከንጉሡ ጎን እንደሚቀመጡና Beke 1940ን በመጥቀስም ፣
>
> ዋግ ሹም ለወንበር፣
>
> ንጉሥ ለመንበር፡፡

የሚል ቃል ግጥም እንደተገጠመ አስፍረዋል፡፡

### 1.2.2.3 የማህበረሰቡ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ

ከዞኑ ህዝብ አብዛኛው (95%) የሚሆነው የሚተዳደረው በግብርና በተለይም እርሻ በማረስ ሲሆን፣ መሬቱ ወጣ ገባና ለምነቱ የታጠበ በመሆኑ፣ ከፍጆታ ያለፈ ምርት አይመረትበትም፤ በዚህም ምክንያት በአማራ ክልል ድርቅ በተደጋጋሚ ከሚያጠቃቸው አካባቢዎች አንዱ ይህ ዞን ነው። ጌታቸው (2000፣174) እንዳሰፈሩት ከብት ማርባትና በተለይም በቆላማው አካባቢ በብዛት ፍየል ማርባት፣ ንብ ማንባት በአካባቢው ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው። የዞኑ የገጠር ነዋሪዎች፣ቅቤውን፣ ቆዳውንና ማሩን በመሸጥም በገቢ ምንጭነት ይጠቀማሉ። በንግድና በእደ-ጥበብ ስራ የሚተዳደሩም አሉ።

### 1.2.2.4 የማህበረሰቡ ማህበራዊ ሁኔታ፣

#### ቋንቋ

የ2007 የህዝብና ቤት ቆጠራ ሪፖርት እንዳመለከተው፣ ከጠቅላላው የህዝብ ቁጥር(426213) መካከል የአገው ብሄረሰብ አባል የሆኑት 225,564 (52.92%) ሲሆን፣ ይህም በከተማ 16,098 (7.13% )፣ በገጠር ደግሞ 209,466 (92.87%) ነው፡፡ የአገው ብሄረሰብ አባል ከሆኑት ውስጥ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አገውኛ (ኽምጣኛ) የሆነው 178,236 ሲሆን (79.01%) ይህም በከተማ 9,844 (5.52%)፣ በገጠር ደግሞ 168,392 (94.47%) እንደ ሆነ ሪፖርቱ አስፍሯል። አማርኛና ትግርኛን በአፍ መፍቻነት የሚናገሩት ደግሞ በተከታታይ 239,843 (56.27% ) እና 7,125 (1.67% )ናቸው፡፡

ኽምጣኛ ከአራቱ የአገው ቋንቋ አይነቶች (ሌሎቹ፣ አውኚ፣ ቅማንትና ብሌን ናቸው) አንዱ ነው። (Appleyard,1988:245;McCann, 1987:36); Adhana,1984:51;Bender and others, 1976:40);Ullendorf,1966:39;Zelalm,2000:30)። አራቱ የአገው ቋንቋዎች የማእከላዊ የኩሽ ቋንቋ ቤተሰብ መሆናቸውንም እነዚህ ምንጮች አስፍረዋል። ኽምጣኛ እስከ አስራ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ ሰባት መገባደጃ ድረስ ፊደል ሳይቀረጽለት የንግግር ቋንቋ ብቻ ሆኖ ለረጅም ጊዜ ያገለገለ ቋንቋ ነው። እንዲያውም በአንዳንድ ምንጮች በመሞት ላይ የነበረ ቋንቋ ተብሎ ነበር፡፡ ለአብነት ያህል Bender and others (1976:41) ኽምጣኛ በከፍተኛ ሁኔታ

በአማርኛ ተጽእኖ እየተደረገበት እንደሆነና የሚነገርባቸው ቦታዎች እየጠበቡ መምጣታቸውን አስፍረዋል፡፡ ለዚህም ነው Vaughan(2003:243) በአሁኑ ጊዜ ሽምጣኛ ተናጋሪ ያልሆኑት አጎራባቾቹ ላስቴዎችም እንደ ዋጎች ሁሉ የአገው ማንነት ያላቸው ነበሩ ያሉት፡፡

ታደሰና አፀደ(1993፣7) እንዳሰፈሩት ከንግግር ቋንቋነት አልፎ የራሱ ፊደል ተቀርጾለት በጽሁፍ የዋለውና ለማስተማሪያ ቋንቋነት እንዲያገለግል የተደረገው በግንቦት ወር 1987 ዓ.ም የአካባቢው ተወላጆች ባካሄዱት አጠቃላይ ስብሰባና የፊደል ምርጫ ውሳኔ ጀምሮ ነው፡፡ የተመረጠውና እየተጻፈበት የሚገኘው ፊደልም የግእዝ ፊደል ነው፡፡ ከዞኑ ትምህርት መምሪያ የስርዓተ ትምህርት የስራ ሂደት የሽምጣኛ ቋንቋ ጉዳይ ክፍል የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ባሁኑ ጊዜ (2006 ዓ.ም) ሽምጣኛ በአንድ መቶ አስር ትምህርት ቤቶች በመሰጠት ላይ ነው፤ ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍል ሙሉ በሙሉ በሽምጣኛ ቋንቋ ትምህርት የሚሰጥባቸው (በማስተማሪያ ቋንቋነት የሚያገለግልባቸው) ትምህርት ቤቶች አርባ ስድስት ናቸው፡፡ ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ደግሞ በስልሳ አራት ትምህርት ቤቶች ይሰጣል፡፡ ከዚህ ውስጥም በሰባተኛ ክፍል በአስራ አራት፣ በስምንተኛ ክፍል ደግሞ በአስራ አንድ ትምህርት ቤቶች ሙሉ በሙሉ በሽምጣኛ ትምህርት ይሰጣል፡፡ በሰላሳ ዘጠኙ ትምህርት ቤቶች ደግሞ በትምህርት ዓይነትነት ይሰጣል፡፡

Melakneh(1990:31) እንደገለጹት በአሁኑ ጊዜ አብዛኛዎቹ አገዎች ልሳነ ክልኤ ናቸው፤ ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በተጨማሪ አማርኛን ወይም ትግርኛን ይናገራሉ፡፡ ዋግ ሽምራዎችም ሽምጣኛ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ቋንቋዎችንም ይናገራሉ፡፡ Teshome(2007:1) እንደ ገለጹት የዞኑ ህዝብ አብዛኛው ሽምጣኛና አማርኛ ተናጋሪ ሲሆን አልፎ አልፎም ሶስቱን ቋንቋዎች (ሽምጣኛ፣አማርኛና ትግርኛ) የሚናገሩም አሉ፡፡

## ሃይማኖት

የክርስትናን እምነት ቀደም ብለው ከተቀበሉት አካባቢዎች ውስጥ አንዱ የዋግ ሽምራ ዞን ነው።ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ገባ የሚባለው ደግሞ በ4ኛው ክፍለ ዘመን ነው።(Aymro 1970:6;and Gamst,1968:8)። አያሌው(2007፣37)ም የዋግ ማህበረሰብ የክርስትናን እምነት

ቀደም ብሎ የተቀበለ መሆኑን አስፍረዋል፡፡ በዋግና ላስታ አገዎች አካባቢ እምነቱ የተስፋፋው በ6ኛው ክፍለ ዘመን በአጼ ካሌብ ዘመን ነው (Taddesse,1972,25)። በአካባቢው የበርካታ አብያተ ክርስቲያናት መገንባትም ከአጼ ካሌብና ከልጃቸው ከገብረ መስቀል ዘመን ጋር የሚያያዝ መሆኑን (Wudu,1995:7) ገልጸዋል።

እንደ ኤ.አ. በ2007 የተካሄደው የህዝብና ቤት ቆጠራ ሪፖርት እንደሚያመለክተው፣ ከዋግ ኽምራ ነዋሪዎች መካከል 424,584 ወይም (99.6%) የኦርቶዶክስ ክርስትና፣ 1,445 ወይም (0.33%) የእስልምና እምነት ተከታይ ሲሆን፣ ቀሪው ደግሞ የፕሮቴስታንትና የካቶሊክ ሃይማኖት ተከታይ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በዞኑ በርካታ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት በድምቀት ይከበራሉ፡፡ ለአብነት ያህል የድንግል ማርያምን እርገት ምክንያት በማድረግ ከነሐሴ አስራ ስድስት እስከ አስራ ስምንት «ሻደይ»፣ ከመስከረም አንድ እስከ አስራ ስድስት፣ «ዋርዳ ሆዬ እና አሸኮለለ» በተከታታይ በሴቶችና በወንዶች የሚካሄዱ ጨዋታዎች ናቸው፡፡ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ « ሰቆጣን በጥምቀት፣ ላሊበላን በልደት ያላየ ምን አየ ሊባል ነው» የሚባልለት የጥምቀት ክብረ-በዓልም በዞኑ በድምቀት ይከበራል፡፡


በዞኑ ማንኛውም የክርስትና እምነት ተከታይ ማተብ ያስራል፤ በኢትዮጵያ ማተብ ማሰርን አስመልክተው Taddesse(2002:357) እንደሚከተለው አስፍረዋል፡፡ ማተብ ማሰር በኢትዮጵያውያን በተለይም በቀደምት ትውልድ ዘንድ ትልቅ ስፍራ ይሰጠዋል፡፡ ማተብ ለእርሱ የማይናወጥ እምነትና የትክክለኛና ጽኑ አእምሮ ምልክት ነው፡፡ በዞኑ ማተብ ያላሰረ «እስላም ነው»፤ ቢበላም አይጠግብም (አይጠረቃም) ይባላል፡፡ ማተብ የመተማመንና የመቀራረብ ምልክትም ነው፡፡ አንድ ሰው አምርሮ ከተጣላ «ማተቤን በጥሻለሁ» ይላል፡፡ በቃን ካሁን በኋላ መገናኘት አንችልም ማለቱ ነው፡፡ ማተብ ለክህደት ማፍረሻም በምስክርነት ይጠራል፡፡ አንድ ሰው ሌላውን ሰው ቢክደው «ማተብህ ይታዘብ (ቅምጽ ይበል) ይባላል፡፡ ምክንያቱም ድርጊቱ ሲፈጸም ሌላ ሰው ባይኖርም ማተቡ ግን በሰውየው አንገት ላይ አለና ሁሉን ያውቃል፤ይታዘባል ለማለት ነው፡፡ «ማተብ የሌለው » ከተባለም ከሃዲ ነው ማለት ነው፡፡

በዚህም ምክንያት አፀደ (1996፣ 23-24) እንደገለጸችው፣ ማተብ በዞኑ ማህበረሰብ ዘንድ ከአንድ እምነት ተከታይ ምልክነቱ አልፎ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው፡፡

## 1.2.2.5 የዋግ ኽምራ ማህበረሰብ የቤት አሰራር፣ አለባበስ፣ አጊያጊያጥና አመጋገብ

### የቤት አሰራር


በዋግ ኽምራ ዞን የሚገኝ የቤት አሰራር  አይነት አምስት ነው። እነዚህም ክብ ፎቅ ቤት (ህድሞ)፣ ባለ አራት ማእዘን ፎቅ ቤት (ደብር)፣ ባለ አንድ ወለል ቆርቆሮ ክዳን ቤት፣ አዳራሽና ጎጆ ቤት ናቸው፡፡ ህድሞ፣ በምድር ቤቱ ሶስት ክፍሎችን የያዘ ነው፤ እነዚህም ጓዳ፣ (የእቃ ቤት) የእንግዳ መቀበያ (ሳሎን)  እና የምኝታ ክፍል  ናቸው። ደብር ደግሞ አራት ማእዘን ቅርጽ ያለው ሲሆን በምድር ቤቱ ሶስት ወይም ሁለት ክፍሎች ሊኖሩት ይችላል፤ ባለ ሶስቱ ጓዳ፣ (የእቃ ቤት) የእንግዳ መቀበያ (ሳሎን) እና የምኝታ ክፍል ናቸው።ባለ ሁለቱ ደግሞ ሳሎንና አንድ ጓዳ ብቻ ይኖረዋል፡፡ የህድሞም ሆነ የደብር ወደ ሁለተኛ ፎቅ መውጫ ደረጃ (**መንጫጫ**) በቤቱ ውስጥ ወይም በውጭ በኩል ሊሆን ይችላል፡፡



የህድሞ ቤት (ፎቶ በአፀደ ተፈራ)

ሶስተኛው የቤት ዓይነት ደግሞ ባለ አንድ ወለል ቆርቆሮ ክዳን ቤት ነው፡፡ ይህ ቤት ጓዳም ሊኖረው ይችላል፡፡ አዳራሽ  እንደ ህድሞ ሁሉ ክብ ሲሆን፣ በውስጡም በርካታ

ክፍሎች ማለትም ጓዳ፣ የእቃ ቤት የእንግዳ መቀበያ (ሳሎን) ምኝታ ክፍል ያለው ነው። ጎጆ ቤት በአብዛኛው አንድ ክፍል ብቻ ያላት ትንሽ ቤት ስትሆን ክዳኗም ሳር ነው፤ ይህች የቤት ዓይነት በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰዎች ቤት ናት። ሀድሞና ደብር የሀብታሞች፣ ባለ አንድ ወለል የቆርቆሮ ክዳን እና አዳራሽ ደግሞ የመካከለኞች ቤት ነው። ስለዚህ አብዛኛውን ጊዜ፣ ቤቶቹን በመመልከት የባለቤቶቹን የሀብት ደረጃ ለማወቅ ይቻላል። ቀደም ሲል በተለይም በገጠሩ፣ የአብዛኞቹ የቤት አይነቶች ክዳናቸው ሳር የነበረ ቢሆንም፣ አሁን አሁን ግን ለክዳን የሚሆን ሰንበሌጥ በመታጣቱ ምክንያትና የአርሶ አደሩ ቆርቆሮ የመግዛት አቅም ከፍ እያለ በመሄዱ የሳር ክዳን የነበራቸው ቤቶች በቆርቆሮ ክዳን እየተቀየሩ ነው፡፡ በመሆኑም በየገጠር ቀበሌዎች በርካታ የቆርቆሮ ክዳን ያላቸው ቤቶች ይገኛሉ። ለአብነት ከሰቆጣ ወረዳ የቀበሌ መንደሮች መካከል የሀሙሲትን መመልከት ይቻላል፡፡



**የሀሙሲት ቀበሌ ከፊል ገጽታ (ፎቶ በአፀደ ተፈራ)**

ዞኑ ደን የተራቆተበት አካባቢ በመሆኑ በአካባቢው የሚሰሩት ቤቶች ግድግዳቸው እንጨት የሆነ ጥቂት ቢኖሩም፣ በብዛት ግድግዳቸው የሚሰራው ከድንጋይ ግንብ (ናስ) ነው።

የቤቶቹ የግቢ አጥር የሚሰራውም በግንብ፣ አልፎ አልፎም በካብ ሲሆን፣ ከእንጨትና ከቅጠል በተለይም ጥንጁትና ደደሆ ከሚባሉ ተክሎች ቅጠል ጨፈቃ አጥር (ሽምጥጥ)

ያላቸው ቤቶችም አልፎ አልፎ ይገኛሉ፤ የቦታ ጥበት ያለባቸው ሰዎች ቤቶች ደግሞ ያለ አጥር ይገኛሉ።

**አለባበስና አጊያጌጥ**

የዞኑን ማህበረሰብ አለባበስና አጊያጌጥ የወንዶችና የሴቶች በማለት በጾታ ከፍየ እንደሚከተለው ተመልክቸዋለሁ፡፡

**የወንዶች አለባበስና አጊያጌጥ**


የወንዶችን አለባበስ የህፃናት፣ የወጣቶችና የትላልቆች በማለት በሶስት ከፍሎ መመልከት ይቻላል። ህጻናት ወንዶች የሚለብሱት ኪታ ነው። ይህም ከተለያዩ የልብስ አይነቶች የተሰፋ ሆኖ የኪሱ ጫፍ በጥልፍ ወይም በዛጎልና ድባ ይዋባል። ጸጉራቸውንም ከመሃል ቁንጮ አስቀርተው ሌላውን ይላጫሉ፡፡

ወጣት ወንዶች ደግሞ ቁምጣና እጅጌው አጭር ሆኖ በጀርባና በፊት ለፊት በልብስ ቁልፍ (መከተሪያ) እና በዛጎል ያጌጠ፣ ሸሚዝ ኳርቶ[8]ይለብሳሉ፤ በቁምጣቸው ላይ ለውበትና እሾህ ሲወጋቸው ለማውጣት የሚጠቀሙባትን ወረንጦም ያንጠለጥላሉ። በስራ ጊዜ በአካባቢው የእደ ጥበብ ባለሙያዎች ከጎማ የተሰራ ጥልፍልፍ ጫማ በአካባቢው አጠራር እንደርታ ወይም ባራባሶ፣ በሌላ ጊዜ ግን በፋብሪካ የተሰራ ዘመናዊ ጫማ ያደርጋሉ። ጸጉራቸውንም ጎፈሬ ያደርጋሉ። አንዳንዶችም ለጌጥ ጥርሳቸውን ሙሉ በሙሉ ወይም ጉራማይሌ ይነቀሳሉ። ክንዳቸው ላይም የመስቀል ቅርጽ ይነቀሳሉ፣ ክንዳቸውንም የክብ ቅርጽ ያለው አድርገው በእሳት በማቃጠል (በምስር ቂጣ) የጀግንነት ምልክት ተብሎ የሚገመት ጠባሳ ያደርጋሉ።

[8] ሶራ የተሰኘውን ዘፈን የሚያቀነቅነውም ሆነ የሚቀበሉት ወንዶች፣ ይህንን በመልበሳቸው ፣ በአሁኑ ጊዜ ይህ ልብስ ሶራ ተብሎ እየተጠራ ነው፡፡



**ጸጉራቸውን ቁንጮ የተላጩና ኪታ የለበሱ ልጆች ቁርንጮ ላይ ተቀምጠው (ፎቶ በዋግ ኽምራ ዞን ባቱ)**




**ኳርቶ የለበሰ ወጣት (ፎቶ በጋዝጊብላ ወረዳ ባቱ)**

የአባቶች አለባበስ ደግሞ በክትና በዘወትር የሚከፈል ነው። ዘወትር የሚለብሱት በተለይም በእርሻ ስራ ወቅት ቆሸሽ ያለ ቁምጣና እጅጌው አጭር የሆነ ሸሚዝ ነው፤ ዝናብ ሲመጣ

ለመከላከል ያስችላቸው ዘንድ ትከሻቸው ላይ ጣል የሚያደርጉት ደግሞ በአካባቢው የእደ ጥበብ ባለሙያ ከቆዳ የተሰራ ቁርንጮ (በኽምጣኛ በልባል)ነው። የክት ልብሳቸው ነጭ ባት ተሁለት ሱሪ ወይም ሌላ ሱሪና ኮት በቀጭኑ ተፈትሎ የተሰራ ጋቢ ከጭራ ጋር ነው። ጸጉራቸውንም እንደ ወጣቶቹ በጣም አያጎፍሩትም፤ ያሳጥሩታል፤ በእድሜ የገፉት ግን ጸጉራቸውን አያሳድጉም፤ ይላጩታል።

## **የሴቶች አለባበስና አጊያጌጥ**

የሴቶችን አለባበስም የህፃናት፣ የወጣቶችና የትላልቆች በማለት በሶስት ከፍሎ መመልከት ይቻላል። ህጻናት ሴቶች ያልተሸበሸበ ቀሚስ (ጥብቆ) ይለብሳሉ። ይህም በአብዛኛው ከጥጥ የተሰራና በመቀነት የሚታጠቁት ነው። ጸጉራቸውንም ሌላውን ተላጭተው አራት ማእዘን ቅርጽ ያለው ጸጉር መሃል ላይ ብቻ ትተው  በመሰራት በሰለላ ጀምረው፣ ሁለት ዙር ጋሜና ቁንጮ ይሰራሉ።



**ጋሜና ቁንጮ የተሰራችና ቃቂዳ ያሰረች ወጣት (ፎቶ በአፀደ ተፈራ)**

ወጣቶቹ ደግሞ ቀሚስ በመቀነት ታጥቀው ይለብሳሉ፡፡ እስከሚወልዱ ድረስ ሰፋ ያለ ጋሜና ቁንጮ ይሰራሉ፤ ደጋግመው ከወለዱ በኋላም ሳዱላ (ቅርድድ)ይሰራሉ፤ ይህም ከመሀል ጸጉራቸውን በክብ ቅርጽ በመላጨት ሌላውን ሹሩባ የሚሰሩት ነው። ትልቅ ሴት ወይም እናት ሲሆኑ ደግሞ ጸጉራቸውን ሙሉ በሙሉ ሳይላጩ ያሳድጉና ሹርባ ይሰራሉ፤ (ድፍን ያደርጋሉ)። አሁን አሁን ግን ከዘመናዊ ትምህርት ጋር ተያይዞ ህጻናትም ሆኑ ወጣቶች ፀጉራቸውን ድፍን እያደረጉ ነው።

ይህም ቀደም ሲል የእድሜ ልዩነት መግለጫና መለያ የነበረው የጸጉር አስተዳደግና አለጫጨት ሙሉ በሙሉ ባይጠፋም እየቀነሰ መምጣቱን ያመለክታል።

ሴቶች ሹሩባቸውን በተለያየ አይነት ይሰራሉ፤ መደረቢያ የሌለው በወፍራሙ የሚሰራ ሹሩባ (**አሻሞ**)፣ መደረቢያ ያለው በወፍራሙ የሚሰራ ሹሩባ (**አልባሶ**)፣ ገፅታው ተገልብጦ የሚሰራ ሹሩባ (**ግልብጭ**)፣ ገፅታው ሳይገለበጥ የሚሰራ ሹሩባ (**ግጫ**)፣ በጣም ወፍራም ሹሩባ፣ (**ጉንጉን**)፣ ጫፉ ወይም ዱርላው ተሰብስቦ የሚሰራ ሹሩባ (ድርማሞ) እና ወፍራምና ቀጭን ተደባልቆ የሚሰራ ሹሩባና በቅርብ የሚታይ **ኀበዝና ቆንጆ** ይሰራሉ፤ በተለይ ወጣቶቹ በሹርባቸው መሀል ላይ በጌጥነት ወለባቸውን ይሰካሉ። በቆላው አካባቢ ደግሞ **ቃቂዳ** የምትባል ከሳር የምትሰራ የጸጉር ጌጥ ያስራሉ፡፡

እነዚህ የጸጉር አሰራር አይነቶች ወቅትንና ሴቷ የምትገኝበትን ሁኔታ መሰረት ያደርጋሉ። አሻሞና ጉንጉን ለአጣዳፊ ጊዜና በሀዘን ወቅት የሚሰሯቸው ናቸው፤ድርማሞ ደግሞ ሴትየዋ በእድሜ በመግፋቷ በዱርላዋ ላለማጌጥ ስትፈልግና የሀዘን ጊዜዋን ወደ ማጠናቀቅ ደረጃ ላይ ስትደርስ የምትሰራው ነው። አልባሶ በማንኛውም ጊዜ የሚሰሩት ሲሆን፣ ግልብጭና ግጫ ግን ሴቶች ከሌላው ጊዜ በተለየ ሁኔታ ተውበው መታየት በሚገባቸው፣ በክብረ በዓላት፣ በሰርግ፣ በክርስትና ወዘተ.የሚሰሯቸው ናቸው። እነዚህ የጸጉር አሰራር አይነቶች ረዘም ያለ ጊዜ የሚጠይቁ ናቸው፡፡ በተለይ ጸጉራቸው ብዙ የሆነ ሴቶች ቀኑን ሙሉ ሲሰሩ የሚውሉበትም ጊዜ አለ፡፡ ለነዚህ ነው በአካባቢው፣

አንድ ቀን ተሰርቶ አያልቅም እራሷ፣[9]

ላምባዲና ይዤ ልቁም ከትራሷ፡፡

[9] ጸጉሯ ለማለት ነው፡፡

የሚል የፍቅር ቃል ግጥም የሚገጠምላቸው፡፡

አለባበስን በሚመለከት ወጣቶቹም ሆኑ እናቶች ከጥጥ ፈትል የተሰራ ወይም ከዝሃ ብቻ የተሰራ (እሱ በእሱ) ወይም ከፈትልና ከዝሃ ተደባልቆ የሚሰራ (ጀበርባሬ) ይለብሳሉ፤ ቀሚሳቸውንም ሆነ ኩታቸውን የተለያየ ቀለም ባላቸው የክር አይነቶች (እዳይቶች) ያስውቡታል። በአካባቢው ተዘውትረው የሚመረጡት የክር ዓይነቶችም አረንጓዴ (ቅጠልያ) ወይም (ወንዝ አይፌሬ)[10]እና ሰማያዊ (ድባ ዓይነት) ናቸው። ቀሚሳቸውንም በጥልፍ ያሳምሩታል፤ ጥልፉ የቀሚሱ ግማሽ ብቻ የተጠለፈ (ፍቅር ቁምጥ) ወይም ሙሉ ጥልፍ ሊሆን ይችላል። በቀሚሱ ጥልፍ ላይ የሚያያዝ መልጎምም ያደርጋሉ፡፡ መልጎም ከብር ወይም ከኒኬል የሚሰራ ክብ ቅርጽ ያለው ነው፡፡ የሚታጠቁት መቀነትም ተራ ወይም እስከ ስድስት ዓይነት በሚደርሱ የተለያየ ቀለም ባላቸው ክር የተዋበ፣ ሰፊ ጥለት ያለውና ዋጋው እጅግ በጣም ውድ የሆነ (ቃንጃ መትር)[11]ሊሆን ይችላል። ነጠላም ይደርባሉ። በአሁኑ ጊዜ በዞኑ ዘመናዊ አለባበስም እየተስፋፋ ነው፡፡

አጊያጌጣቸውን በሚመለከት እንደ እድሜ ደረጃቸው ከእራሳቸው እስከ እግራቸው ከተለያዩ ነገሮች የተሰሩ ጌጣጌጦችን ይጠቀማሉ። ከእነዚህም መካከል፣ ቀራንዮ መስቀል (ትንሽና ትልቁን) በአንገታቸው ያስራሉ፤ ድሪና ድንብል ቀለበትም የተለያየ ቀለም ባላቸው ክሮችና ለስላሳ በሆነ ጥቁር ክር (ካሉስ) በሚባለው ክር ታስሮ መዋቢያ ነው። ጣታቸው ላይም ቀለበት ያደርጋሉ። ክንዳቸው ላይም ባለ ማፈኛና ማፈኛ የሌለው ሁለት ዓይነት ድኮት ያደርጋሉ። እግራቸው ላይም አልቦ ያስራሉ። በጣታቸውም ከብር፣ ከኒኬል ወይም ከመዳብ የሚሰራ ቀለበት፣ በግንባራቸው ላይ ደግሞ ከስንድድና ከአሸክት (ቅጠሉ ትንንሽና የሚያጣብቅ የሆነ የተክል) ፍሬ በክር ተደርድሮ ወይም ከሳር የሚሰራ የጌጥ አይነት (ቃቂዳ) ያስራሉ፣ በጆሮቻቸው ደግሞ በታችኛው ክፍል ቀለበት (አላድ) ወይም ጉትቻ፣ የላይኛው ጫፍ ደግሞ ሽንቆር ያደርጋሉ፡፡

---

10 አረንጓዴ ለማለት ነው፡፡

11 ከዋጋው ውድነት የተነሳ ከአንድ በሬ ዋጋ ጋር እኩል ነው ለማለት ነው፡፡



**ቃንጃ መትር መቀነት የታጠቀች ወጣት ( ፎቶ በዋግ በኽምራ ዞን ባቱ)**



**በአብዛኞዎቹ የልጃገረድ ጌጣጌጦች ያጌጠች ወጣት (ፎቶ በዋግ ኽምራ ዞን ባቱ)**

ሌላው የሴቶች ማጌጫ ደግሞ ንቅሳት (ውቅራት) ነው። ግንባራቸውን፣ የአይኖቻቸውን ጎንና ጎን፣ አገጫቸውን፣ ጥርሶቻቸውንና በተለይ እናቶች ደግሞ፣ ከአንገታቸው ጀምሮ ወደታች እስከ ጡታቸው ጫፍ ድረስ ይነቀሳሉ (ይወቀራሉ)። የግንባራቸውንና የአገጫቸውን ንቅሳት ቅርጽ በሚመለከት ከፍያለው(1992፣13)፣ ህዝቡ ከሚከተለው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና መስፋፋት ጋር የተያያዘ መሆኑን በመግለጽ በምስል አስደግፈው አቅርበዋል።



ጸጉራቸውን ድፍን የተሰሩና በተለያዩ ጌጣጌጦች ያጌጡ እናቶች (ፎቶ በጋዝጊብላ ወረዳ ባቱ)

## አመጋገብ

በዋግ ኽምራ ዞን ተዘውትሮ የሚበላው እንጀራ ሲሆን ይህም ጣቢታ፣ወይም ድጉሎ ሊሆን ይችላል። ጣቢታ ከጤፍ ብቻ የሚዘጋጅ ሲሆን ድጉሎ ደግሞ ከስንዴ፣ ከማሽላና ከገብስ ቅልቅል የሚዘጋጅ ነው። የድጉሎ አገጋገር ከጣቢታ ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም፣ አቦካኩና አቀጣጠኑ ግን የተለየ ነው። የጣቢታ ሊጥ (ብሆ) የሚቦካው ዱቄቱ ታምሶ ሲሆን፣ የድጉሎ ግን አይታመስም፤ የጣቢታ ሊጥ ቀጠን ያለ ሲሆን የድጉሎ ግን ወፈር ያለና በተደጋጋሚም የሚታሽ፣ የሚደጎል[12]ነው። ሊጡ የሚቀጠነው የጣቢታ፣ በቀዝቃዛ ውሃ ሲሆን የድጉሎ ግን በፈላ ውሃ ነው። ሌላው ተዘውታሪ ምግብ ቂጣ ነው። ቂጣው የስንዴ ወይም የስራና ሊሆን ይችላል፤ የስራና ቂጣ ከስንዴ ዱቄትና ከአተር ወይም ከባቄላ ዱቄት

[12] ስያሜውን ያገኘው ከዚህ ይመስላል፡፡

ቅልቅል የሚዘጋጅ ነው፡፡ ሌላው ቦትዷቴ ነው። ልክ እንደ ቂጣ ሆኖ ነገር ግን ማታ በጥበጥ (ቦትቦት) ተደረጎ፣ ተቦክቶ ያደረ ነው። አነባብሮም ሌላው የምግብ አይነት ነው። ይህም ሁለት ቦትዷቴ አንድ ላይ ተደርቦ የሚጋገር ነው። እሪጦ ደግሞ ባይዘወተርም በበዓል፣ በተለይም ለሀምሌ አምስት (ለግቫና አቦ)፣ በየቤቱ፣ በአርሶ አደሩ ቤት ደግሞ በውቂያ ጊዜ ይጋገራል። አዘገጃጀቱም ሁለት አነባብሮን በተልባ፣ በኑግና በድልህ ቀብቶ (ለምጥጦ) በሀብታሞች ቤትም በቅቤ ይቀባል፤ በመደራረብ ነው።

ሌላው ደግሞ አምባሻ ነው። በሌላው አካባቢ ዳቦ የሚባለው ነውና የተለየ አዘገጃጀት የለውም። ትኩሴ ደግሞ በተወሰኑ በዓላትና (በተለይም በሁሉም ቤት በጸሎተ ሀሙስ) በዝክር፣ እንግዳ ለመቀበልና ወደ የክርስትና ድግስ ቤት ለመሄድም ይጋገራል። በሌላው አካባቢ ድፎ የሚባለው ነው፡፡ አገጋገሩ ግን ከድፎ ዳቦ አገጋገር የተለየ ነው። ማታ ትንሽ የስንዴ ዱቄት በጥበጥ ተደርጎ (ተገብጦ ) ያድራል፤ በማግስቱም ለብ ባለ ውሃና በዛ ባለ ዱቄት ይለወሳል (ይሸበለላል)። ለማጣፈጫም የአብሽ ዱቄት ይጨመርበታል። ሶስት ጊዜ ከተነሳ (ኩፍ ካለ) በኋላ ሰፌድ ላይ ይጠፈጠፍና ቅርጽ ወጥቶለት (ተሸልሞ) ወፍራራም እንጨት በተማገደበት ምጣድ (የብረት ምጣድ) ላይ እንዳሁላ (የተክል አይነት) ወይም የቁልቋል (የበለስ) ትልታይ ይደለደላል (ይረበረባል)፡፡ ከዚያም ከሸክላ ወይም ከጭቃ የተዘጋጀ ክዳን (ወዛንታ) ይከደንና ትኩሴው ጢስ እንዳይገባበትና እንዳይቀላ፣ ዙሪያው በጭቃ ይደፈናል። በአካባቢው የታወቁ ቄሶችን ወይም ዲያቆናትን ስም በመጥራትም ከወዛንታው ላይ በነዲዱ፣የመስቀል ቅርጽ ይደረግበታል። ይህም በደንብ እንዲነፋ ለማድረግ ነው ተብሎ ይታመንበታል። በሌላው አካባቢ ድፎ ሲጋገር ክዳኑ ላይም እሳት፣ በተለይም የኩበት እንዲነድበት ሲደረግ፣ ትኩሴ ሲጋገር ግን ወዛንታው ላይ እሳት አይነድም።

ለተወሰኑ ቀናት የሚዘጋጀው የምግብ አይነት ደግሞ ቃተኛ ነው። አዘገጃጀቱም ትኩስ እንጀራን በአዋዜና በቅቤ፣ ጾም ከሆነም ከኑግ ወይም ከሱፍ የሚሰራ ባህላዊ ዘይት(ቅባኑግ ) በመቀባት ነው። በምግብነት የሚዘጋጀውም ለአራስ፣ ለሙሽራ፣ ለእንግዳ ወይም ሀብታሞች ቤት ለቁርስ ነው። ለአስቸኳይነት የሚዘጋጀው ሌላው የቂጣ ዓይነት ቋቋቴ ነው፡፡ የሚጋገረውም በብረት ምጣድ ወይም በምጣድ ላይ ነው፡፡ ሊጡም በወፍራሙ ሆኖ በጣት ጌጥ እየወጣለት ነው። ምልስ ደግሞ ለስንቅነት የሚዘጋጅ የምግብ አይነት ነው።

አዘገጃጀቱም ትኩስ እንጀራ በአዋዜ ይቀባና ተጨባብጦ ነው። ብርኩታ ደግሞ እሩቅ ተጓገሮች ወይም ከቤታቸው ርቀው የሚሄዱ ከብት ጠባቂዎች የሚያዘጋጁትና የሚመገቡት ነው። አዘገጃጀቱም የስንዴ ወይም የማሽላ ዱቄት በተገኘው ሁሉ በገበታ፣ በጎድጓዳ ድንጋይ ይለወስና የጋሉ ድንጋዮች ላይ ተጠፍጥፎ እሳት ውስጥ በመክተት ይጋገራል። ጋጋሪዎቹም ወንዶች ናቸው። ንፍሮና ቆሎም ባይዘወተሩም ለምግብነት የሚውሉ ናቸው። ንፍሮ በልደታ(በመባቻ)ይቀቀላል፡፡ ቆሎ ለቡና ቁርስነትና ለመክሰስ (ለመቆያ) ለመተከዣነትም ያገለግላል፤ አርሶ አደሩ በስራ የደከመ አእምሮውን በጠላው እያወራረደ ይቆነጣጥረዋል። ዳቦ በማርም[13] ይበላል።

ለማጣፈጫነትም የተለያዩ የወጥ አይነቶች ይዘጋጃሉ። ከእነዚህ ውስጥ ዋናው ስልስ ነው። የሚዘጋጀውም ከእርጎና ከበርበሬ ነው። ሌላው ደግሞ ስቅስቆ ነው። ይህም የሚዘጋጀው በደቃቁ ከተከተፈ ስጋ ሲሆን ማቁላሊያውና ማብሰያው(መሰለሻው) ቅቤ ብቻ ነው፤ ምንም ውሃ አይጨመርበትም። በዚህ ምክንያት የሚሰራው በተወሰኑ ሀብታሞች ቤት ነው፡፡ የምስር፣ የአተርና የባቄላ ክክ ወጥም ተዘውታሪ ሲሆኑ፣ ፍልቅልቅም አልፎ አልፎ ለችኮላ ከተልባና ከአዋዜ ብቻ ይዘጋጃል። ዶሮ ወጥም ለዓመት በዓልና እንግዳ ለመቀበል የሚዘጋጅ ነው። ሀብታሞች ግን አዘውትረውም ይመገቡታል፣ የበግ፣ የፍየልና የከብት ስጋ ወጥም ይሰራል። ለጾም ወቅትና ለድግስ ደግሞ እልበት[14] (በኽምጣኛ አዞ) ይዘጋጃል፡፡

በመጠጥነት በኩል ተዘውታሪው ጠላ(በኽምጣኛ ሽላ) ነው፤ ይህም ከገብስ ብቻ የሚዘጋጅ (ኮረፌ)፣ ከኮረፌ የጠራ ጠላ፣ ከበቆሎ ወይም ከማሽላ የሚዘጋጅ ቀጠንና ጠራ ያለ ጠላ (ዝልል)[15] ነው። ለአራስና ለእንግዳም፣ ወፍራም ኮረፌ(ዱቃ) ይጠመቃል፤ ከተገኘም ማር ጣል ይደረግበታል። ባይዘወተርም ጠጅም አልፎ አልፎ የሚጠጣ ነው። ወተትና የወተት ተዋጽኦዎችም በተለይ በገጠሩ ተዘውትረው የሚጠጡ ናቸው።

---

[13] ምንም እንኳ ባሁኑ ጊዜ መጠኑ ቢቀንስም አካባበቢው በማር ምርት የታወቀ ነው ::

[14] እልበት የሚዘጋጀው ሱፍ ተነክሮ ያድርና ይቀቀላል ፤ በማግስቱ ታጥቦ ይደቆሳል ፤ በሚቀጥለው ቀን ደግሞ ይጠመቃል :: በማወፈሪያነትም የባቄላ ክክ በሱፉ አሰር ውሃ ተበጥብጦ ይጠመቃል፡፡ በአንዳንድ አካባቢ ደግሞ ባቄላ ሲታጣ የማሽላና የስንዴ ንፍሮ ተጠምቆ ወይም የገብስ ቂጣን ፈትፍቶ በመጥመቅ ይጠቀሙበታል :: ለማጣፈጫም ቃሪያ ፣ ነጭ ሽንኩርትና ዝንጅብል ተደቁሶ ይቀላቀልበታል፡፡ ለጥሩ ጣእም ሲባልም በርከት ያለ ነጭ ሽንኩርት ተልጦና በእንጨት ተሰክቶ ከጤና አዳም ቅጠል ጋር ጣል ይደረግበታል፡፡ ከሶስተኛው ቀን ጀምሮም በጣም ቀጭን ከሆነ ውሃው ተጠሎ ፤ ወፍራም ከሆነም ሳይጠለል እየተቀዳ ለመመገቢያነት ይቀርባል፡፡

[15] በደጋው ኮረፌ፣ በቆላው ደግሞ ዝልል የሚዘወተር መጠጥ ነው ::

## 1.3 የጥናቱ ቦታ የተመረጠበት ምክንያትና የጥናቱ ወሰን

የዋግ ኽምራ ህብረተሰብ ለረጅም ዓመታት የተለያዩ ማህበራዊ ተቋማት ያልተሟሉለትና፣ ቋንቋውም (ኽምጣኝ) ከንግግር ቋንቋነት አልፎ በጽሁፍ ያልዋለ ነበር። በዚህም ምክንያት በተለያዩ አጋጣሚዎች ወደ ቦታው ጉዞ ያደረጉ የውጭ ተመራማሪዎች ስለ ቋንቋውና ህዝቡ ጥንታዊነት በጨረፍታ ከመመልከታቸው በስተቀር፣ ባህልና ወጉ አልተጠናም። ህብረተሰቡ ግን ምንም እንኳ በትግርኛና በአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ተዋስኖ፣ በታሪክ አጋጣሚ በሰፊው በቋንቋው (በኽምጣኝ) መገልገሉን እየተወ (እየቀነሰ) የሁለቱ ቋንቋዎች ተናጋሪ እየሆነ ያለ ቢኖርም፣ አሁንም ቢሆን የራሱን ባህልና ማንነት ጠብቆ የሚገኝ ነው። ይህንንም አያሌው (2007፡80) የዋግን መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ በመጥቀስ ሲገልጹ፣...በተከዜና በጥራሪ ወንዞች የተዘጋውን ወይም የተከበበውን፣ ለመድረስ የማይቻለውን የቦታውን የተፈጥሮ ምሽግነት ተገን በማድረግ የላስታ ዋግ አገዎች ነገዳዊና ቋንቋዊ ማንነታቸውን ሳያስበርዙ ሊቆዩ እንደቻሉ ግልጽ ነው ብለዋል፡፡

ይሁን እንጅ ህብረተሰቡ ለረጂም ዓመታት ጠብቆ ያቆየው ወግና ባህል በወጉ በጥናት ተዳስሶ አልተገለጸም፤ አልታወቀም። የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት ባደረግሁበት ወቅት እንዳረጋገጥሁትም፣ በዋግ ኽምራዎች ፎክሎር ላይ ጥናት የተደረገባቸው ስራዎች አራት የባችለር እና ሶስት የኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ስራዎች ብቻ[16] ናቸው። በተለይም የባችለር ዲግሪ ማሟያዎቹ ሶስቱ በስነቃል ይዘት ትንተና ላይ ያተኮሩ ከመሆናቸውም በላይ ፎክሎሩን በዳሰሳ የቃኙ እንጂ በጥልቀት ያዩ አይደሉም፤ የኤም ኤ ዲግሪ ማሟያዎቹም ቢሆኑ ከዞኑ በተወሰኑ አካባቢዎች፣ በተወሰኑ የፎክሎር ዘውጎች (በቃል ግጥም)፣ በክብረ በዓልና በቁሳዊ ባህል፣ በአለባበስና አጊያጌጥ ላይ የተሰሩ ናቸው። የባችለር ዲግሪ ማሟያ ጥናቶችን አጥኚዎች፣ የተጠኑበት ዘመንና ርእሶች፣ የኤም ኤ ዲግሪ ማሟያዎችን ደግሞ ከመጠነኛ ቅኝት ጋር እንደሚከተለው አቅርቤያለሁ፡፡

የባችለር ዲግሪ ማሟያዎችን በሚመለከት፣ መኮንን ዓለማየሁ፤ (1974 ዓ.ም) ‹‹የዋግ አውራጃ የአማርኛ ግጥሞች›› በሚል ርእስ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ክፍል፣ Haile Mariam Kebede. (1983). ‹‹Cultural and

[16] የአንድነት ግዛቸው ጥናት ፎክሎርን በዳሰሳ የተመለከተ ስለሆነ፣በፎክሎር ጥናት ሊጠቀስ አይችልም፡፡

Economical life of the Agew people of Wag Awraja›› በሚል፣ ማሞ ብሂል፤(1988 ዓ.ም)፡፡ ‹‹በሰቆጣ ከተማ የአሸንድዬ ቃል ግጥሞች ጥናት››፣ ታደሰ እሸቱ ፤(1997 ዓ.ም) ‹‹የሰቆጣ ከተማ እና አካባቢዋ የርሃብ ግጥሞች ይዘት ትንተና›› ናቸው፡፡

የኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ስራዎቹ ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1.አፀደ ተፈራ፤1996 ዓ.ም። ‹‹በሰቆጣ ከተማና አካባቢዋ የክብረ በዓላት አከባበርና ባህላዊ ጨዋታዎች›› በሚል ርእስ፣ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የቀረበ፡፡

ይህ ጥናት የሶስት ክብረ በዓላት፣ የፍልሰታ በዓል አከባበርና የሻደይ ጨዋታ፣ የመስቀል በዓል አከባበርና ባህላዊ ጨዋታዎች እና የጥምቀት በዓል አከባበርንና ባህላዊ ጨዋታዎች በተፈጥሯዊ መቼት በመቅረጸ-ምስል፣ ድምጽ እና በፎቶግራፍ በተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ፣ አውዳዊ ክዋኔያቸው የተገለጸበት ጥናት ነው። በክብረ በዓላቱ ወቅት የሚገጠሙ ከአራት መቶ ስልሳ በላይ የሆኑ ቃል-ግጥሞችም ተሰብስበው፣ አንድ መቶ ዘጠናዎቹ ምደባ ተካሂዶባቸዋል፤ ጭብጣዊ ትንታኔም ተደርጎባቸዋል፣ ሁለት መቶ ሰባ ስምንት ቃል-ግጥሞች ደግሞ በአባሪነት ተያይዘዋል። አፀደ የሰቆጣ ነዋሪን ማህበራዊና፣ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ስትገልጽ የወሊድ፣ የጋብቻንና የሞትና ሥነ-ሥርዓቶችንም በጨረፍታ ቃኝታለች፤ በጥልቀት ግን አላየችም፤ ማየትም አይጠበቅባትም፤ ርእሷም አያስገድዳትም። የተመለከቱትም የከተማውንና የአካባቢውን ብቻ ነው። ስለዚህ ከአሁኑ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በጥናት ቦታው ነው።

2. Alebachew Merka. 2007." Socio-economic and Political Issues in Wag Himra Oral Poetry" በሚል ርእስ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለውጭ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል የቀረበ ።

ጥናቱ በወቅቱ በዋግ ኽምራ ዞን በነበሩት ሶስት ወረዳዎች፣ ከሰላሳ ሰዎች፣ ከእያንዳንዱ ወረዳ አስር አስር ሰዎችን በመረጃ አቀባይነት በመጠቀም በቃለ መጠይቅና በምልከታ በተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ የተጠና ጥናት እንደ ሆነ አጥኚው ገልጸዋል። የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝትም አድርገዋል፤ ነገር ግን በወጉ የተካሄደ ቅኝት አይደለም፣ ምክንያቱም በዞኑ የመጀመሪያ የፎክሎር ጥናት ነው ብለው የጠቀሱት በ1996 ዓ.ም

የተጠናውን የአፀደ ጥናት ነው፤ ከአፀደ ጥናት ከሃያ ዓመት በፊት የተጠናው የመኮነን አለማየሁ ጥናት ግን አልተገለጸም። አለባቸው የባችለር ዲግሪ ማሟያ ስራዎችን አልቃኙም እንዳይባል ደግሞ የታደሰ እሸቱን የ1997ን ጠቅሰዋል፤ የአፀደን ጥናት አስመልክተው በጥንካሬ የጠቆሙት በዞኑ ፎክሎር ላይ በመጀመሪያ የተካሄደ ጥናት እንደሆነ ሲሆን (እንዴት እንደተጠና ባያሰፍሩም) በድክመት ያነሱት ደግሞ የቃል ግጥሟ ስብስብ ግን ውስን ነው የሚል ነው።

ይሁን እንጂ አፀደ የሰበሰበችው ቃል-ግጥም ከአራት መቶ በላይ ሲሆን፣ እሳቸው የሰበሰቡት ግን ሃምሳ አራት ነው። ጥናቱን ያከናወኑት የቀደምት ጥናቶችን ክፍተት ለመሙላት ከሆነ (መሆንም አለበትና) የቀዳሚውን ድክመት ቀርፎ ከአራት መቶ በላይ ቃል-ግጥሞችን መሰብሰብና መተንተን ይገባቸው ነበር። የአለባቸው ጥናት ከቦታ መመሳሰል ውጭ ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት የለውም።

3. ያሬድ ተፈራ (2002 ዓ.ም)። ‹‹በሰቆጣ እና በአብርገሌ ገጠራማ ወረዳዎች የሴቶችና የወንዶች የአለባበስና የአጊያጌጥ ማህበራዊ እሴቶች›› በሚል ርእስ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የቀረበ ነው።

አጥኚው መረጃቸውን የሰበሰቡት ወደ ጥናት ቦታው በመሄድና ፎቶ፣ መቅረጸ-ምስልና ድምጽ በመጠቀም ነው። ጥናታቸው ያተኮረውም በቁሳዊ ባህል ማለትም አልባሳትና ማጌጫ ነገሮች ላይ ነው፡፡ የያሬድ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው በጥናት ቦታው ብቻ ሳይሆን ስለ ማህበረሰቡ ሁኔታ ቅኝት ሲያደርጉ፣ በጨረፍታም ቢሆን (በዝርዝር ለማየት ርእሱ አያስገድዳቸውምና) የጋብቻ ሥነ-ሥርዓትን በመመልከታቸውና እኔም ስለ ማህበረሰቡ አልባሳትና አጊያጌጥ በዳራነት በመግለጼ ነው።

ከእነዚህ በተጨማሪ Andenet Gizachew.(2010). ‹‹Development-Induiced Displacment and Impoverishment: The Case of Tekeze Hydropower Project and Its Impacts on the affected villages of Wag Hemra Zone, North East Ethiopia›› በሚል ርእስ በSocial Anthropology. ለኤም ኤ ዲግሪ ባጠኑት ጥናት የዋግ ኽምራን ዞን ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ዳራ በተመለከቱበት ንኡስ ክፍል፣ ቤተሰብ፣ ዝምድናና ጋብቻ በዋግ ኽምራ በሚል ንኡስ ርእስ ስለ የዋግ ኽምራ ዞን ጋብቻ በጨረፍታ ተመልክተዋል፡፡

ሌላው በአሸናፊ ጌታሁን ‹‹የዋግ ብሔረሰብ የሠርግ ሥነ-ሥርዓት አሉታዊና አዎንታዊ ገጽታ›› በሚል ርእስ የተጠናው ጥናትም በጥልቀት ሳይሆን የሠርግ ሥነ-ሥርዓትን በዳሰሳ የተመለከተ ነው፡፡

ስለዚህ ይህ ጥናት ካሁን በፊት በዋግ ኽምራ ዞን በተለያዩ የፎክሎር ዘውጎች ላይ ጥናትና ምርምር ያደረጉ አጥኚዎች ያልተመለከቱት፣ ነገር ግን ሁሉንም የፎክሎር ዘውጎች አካቶ በሚገኘው የሽግግር ሥነ-ሥርዓት ላይ የተካሄደ አዲስ ጥናት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የፎክሎር ዘውጎቹን በመግለጽ የሚያቆም አይደለም፤ የሥነ-ሥርዓቶቹን ክዋኔ፣ አውድ፣ መዋቅርና በሥነ-ሥርዓቶቹ አከዋወን ወቅት አገልግሎት የሚሰጡ ቁሳቁሶችና ድርጊቶች የሚኖራቸውን ተምሳሌታዊ ፍች ይገልጻል፤ የሥነ-ሥርዓቶቹ ክዋኔ ለማህበረሰቡ የሚሰጠውን ጥቅምና ቀጣይነቱንና ለውጡንም ይተነትናል፡፡

ስለዚህ የጥናቱን ቦታ በሁለት ምክንያቶች መርጨዋለሁ። በመጀመሪያ ማህበረሰቡ ከትውልድ ትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ባህል ጠብቆና ማንነቱን በሚያንጸባርቅ መንገድ የሚከውነውን ሥነ-ሥርዓት በዘመናዊነት ሰበብ ሙሉ በሙሉ ተለውጦ ሳይጠፋ አሁን በሚገኝበት ሁኔታ ማጥናት አስፈላጊ በመሆኑ በጽሁፍና በተወሰኑ ምስሎች ለመሰነድ፡፡ ለዚህም ጠብቆ ካቆያቸው ባህላዊ ስርዓቶቹና ክዋኔዎቹ መካከልም ሁሉንም የፎክሎር ዘውጎች አካተው የሚገኙትንና በሰው ልጅ ህይወት ወቅት መሰረታዊ በሆኑት፣ በወሊድ፣ በጋብቻና በሞት ሥነ-ሥርዓቶች ክዋኔ ላይ ትኩረት ተደርጓል፣ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ፣ የጥናት ቦታው የትውልድና የእድገት፣ ለተወሰኑ ዓመታትም የስራ ቦታየ ስለነበር ጥናቱን ለማካሄድ አንጻራዊ በሆነ መንገድ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥርልኝ ስለሆነ ነው። ምክንያቱም Wilson(1989:228) እንዳሰፈሩት አንድ የፎክሎር ተመራማሪ መረጃውን በሚያውቀው ህዝብ አካባቢ ቢሰበስብ ጥናቱ ስኬታማ ሊሆን ይችላል፡፡

አንድ ጥናት በሚከናወንበት ወቅት ጉልበትን፣ አቅምንና ገንዘብን ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል። ይህ ጥናትም በተጠናበት አካባቢና ርእስ የተወሰነ ነው፤ ይኸውም ርእሱን በሚመለከት በሽግግር ሥነ-ሥርዓት ውስጥ የሚካተቱት ሥነ-ሥርዓቶች በርካታ ቢሆኑም፣ ይህ ጥናት የተመለከተው ግን መሰረታዊ የሆኑትን የወሊድ፣ የጋብቻና የሞት ሥነ-ሥርዓቶችን ብቻ ነው።

ለጥናቱ የተሰበሰበው መረጃም በዞኑ ውስጥ ከሚገኙ ሰባት ወረዳዎች መካከል የሰቆጣ ከተማ አስተዳደርን በመተው፣ በስድስቱም የገጠር ወረዳዎች ነው፡፡ በገጠራማ ወረዳዎች ላይ ትኩረት ያደረግሁበት ምክንያትም የገጠራማ ወረዳዎቹ ማህበረሰብ ፎክሎራዊ ዘውጎች በዘመናዊነትና ሉላዊነት[17] ሰበብ በሚታዩ እንቅስቃሴዎች ብዙም ያልተለወጡ በመሆናቸው ከሞላ ጎደል ሀገረሰባዊ የሆነውን የዞኑ የሥነ-ሥርዓት አከዋወን ለማግኘት ይቻላል ብየ ስላሰብኩና ስላገኘሁም ነው።

## 1.4 ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች

- በዋግ ኽምራ የወሊድ፣ የጋብቻና የሞት ሥነ-ሥርዓቶች እንዴት፣ በማን፣ መቼ እና የት ይከወናሉ?
- ሥነ-ሥርዓቶቹ የሚከወኑት በምን አይነት አውድ ነው?
- የወሊድ፣ የጋብቻና የሞት ሥነ-ሥርዓቶች ቅደም ተከተላዊ ክዋኔ ምን ይመስላል?
- የሥነ-ሥርዓቶቹ ንኡስ ክፍሎች የእርስ በርስ ትስስርስ ምን ይመስላል?
- በሥነ-ሥርዓቶች አከባበር ወቅት አገልግሎት ላይ የሚውሉ ቁሳቁሶችና ድርጊቶች ተምሳሌትነታቸው ለምንድን ነው?
- የሥነ-ሥርዓቶች ክዋኔ ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ጥቅም ምንድን ነው?
- የሥነ ሥርዓቶቹ ለውጥና ቀጣይነት ምን ይመስላል? የሚሉት በጥናቱ የሚመለሱ ጥያቄዎች ናቸው፡፡

## 1.5 የጥናቱ ዓላማ

ጥናቱ የሚከተሉት አቢይና ዝርዝር አላማዎች አሉት።

### 1.5.1. አቢይ ዓላማ

የጥናቱ አቢይ ዓላማ የዋግ ኽምራ አስተዳደር ዞን ህብረተሰብ የወሊድ፣ የጋብቻና፣ የሞት ሥነ-ሥርዓቶች ክዋኔያቸው በዘመናዊነትና በሉላዊነት ሰበብ ሙሉ በሙሉ ሳይለወጥና

---

[17] ግሎባላይዜሽን ለማለት ነው፡፡

ሳይጠፉ[18]አውዳቸውን መሰረት በማድረግ በመቅረጸ-ምስል፣ ድምጽና በፎቶ ካሜራ መረጃ በመሰብሰብ አሁን ባለበት ሁኔታ የሚገኘውን እንዲሰነድ ለማድረግ ነው፡፡

### 1.5.2.ዝርዝር ዓላማ

ዝርዝር አላማዎቹ ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፤

1. ሥነ-ሥርዓቶቹ ማለትም የወሊድ፣ የጋብቻና የሞት እንዴት? በማን? መቼ እና የት? እንደሚከወኑ መግለጽና መተንተን፣
2. የወሊድ፣ የጋብቻና የሞት ሥነ-ሥርዓቶች ሲከወኑ ምን አይነት አውድ እንደሚኖራቸው መግለጽ፣
3. የወሊድ፣ የጋብቻና የሞት ሥነ-ሥርዓቶች ቅደም ተከተላዊ ክዋኔ ምን እንደሚመስል መግለጽና፣ መተንተን፣
4. በሥነ-ሥርዓቶች አከዋወን ወቅት አገልግሎት ላይ የሚውሉ ቁሳቁሶችና ድርጊቶች ተምሳሌትነታቸው ምን እንደሆነ መግለጽ፣
5. የሥነ-ሥርዓቶቹን መዋቅር ከሽግግር ሥነ-ሥርዓት ደረጃዎች አንጻር መተንተን ክዋኔዎቹ ለማህበረሰቡ የሚሰጡት ጥቅም ምን እንደሆነ መግለጽ፣
6. በሥነ-ሥርዓቶቹ አከዋወን ላይ የሚታየውን ቀጣይነትና ለውጥ ማሳየት፡፡

### 1.6 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት ለሚከተሉት አካላት ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

በተለያዩ ምክንያቶች ለአብነት ያህል በዘመናዊነት ምክንያት በመለወጥ ላይ ያለው የአካባቢው ማህበረሰብ ባህል፣ በተለይም የወሊድ፣ የጋብቻና፣ የሞት ሥነ-ሥርዓት እንዲቀረስና እንዲሰነድ ያደርጋል፤ ይህም የአገውን(የኽምራን) ማህበረሰብ ማንነት ይበልጥ ለማወቅ ሊረዳ ይችላል፤

[18] ይህ ሲባል ባህል የማይለወጥ ቋሚ ነው ለማለት ሳይሆን (እንዲያውም ለባህል የህያውነቱ አይነተኛ መንገድ ይኸው መለወጡ ነው)፤ ነገር ግን የማሕበረሰቡን ማንንት የሚገልጹትና የራሱ ናቸው ሊባሉ የሚችሉ ባህላዊ ክዋኔዎች ለማግኘት ሲባል ነው፡፡

ወጉና ባህሉ በሚገባ ለማይታወቀው የዋግ ኽምራ ማህበረሰብም፣ ባህሉ በሌሎች እንዲታወቅ ስለሚያደርግ፣ በማንነቱ ይበልጥ እንዲተማመን እና እንዲኮራ ሊያደርግ ይችላል።

ባህላዊ ጋብቻን በመስህብነት እንዲውል ለሚያደርጉ በየትኛውም ደረጃ (በማእከል፣ በክልል፣ በዞንና በወረዳ) ለሚገኙ የባህልና ቱሪዝም መስሪያ ቤቶች አጋዥ ይሆናል።

በዞኑ ባህል በተለይም ፎክሎር ላይ ጥናት ለሚያደርጉ ይህ ጥናት ያልተመለከተውን እንዲመለከቱ በመነሻነት ያገለግላል።

ብዙም ላልተጓዘው የኢትዮጵያ ፎክሎር ጥናትም የአገዎች (በተለይም የኽምራዎች) የወሊድ፣ የጋብቻና የሞት ሥነ-ሥርዓት ምን እንደሚመስል ስለገለጸ በግብዓትነት ያገለግላል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳን

አንድ ጥናትና ምርምር በሚከናወንበት ወቅት ወደፊት ስለሚጠናው ጥናት በመንደርደሪያነት ሊያገለግሉ የሚችሉ ነጥቦችን፣ የመረጃ እይታንና በመረጃ መተንተኛ ማእቀፍነት ያገለገለውን ጽንሰ-ሀሳብ መግለጽ ተገቢ ነው፡፡ እኔም ቀደም ሲል እንደገለጽሁት ጥናቴ የሥነ-ሥርዓት ጥናት ነውና ስለ ሥነ-ሥርዓት ምንነት፣ ጠባይ፣ ዓይነቶችና ፋይዳ፣ የሽግግር ሥነ-ሥርዓት ምንነት፣ አይነቶችና ደረጃዎች፣ የመረጃ እይታን፤ የመረጃ መተንተኛና በመረጃ መተንተኛ ማእቀፍነት ያገለገለውን ጽንሰ-ሀሳብ በሚመለከት አንዳንድ ነጥቦችን እንደሚከተለው አቅርቤያለሁ፡፡

### 2.1 ሥነ-ሥርዓት

ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው Van Gennep (1960) የሽግግር ሥነ-ሥርዓት Rites of passage ብለው ከዘረዘሯቸው መካከል በዋና ዋናዎቹ የወሊድ፣ የጋብቻ እና የሞት ሥነ-ሥርዓቶች ላይ ነው። እነዚህ የሽግግር ሥነ-ሥርዓቶች ደግሞ ከሥነ-ሥርዓት አይነቶች ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፡፡ ስለዚህ የሥነ-ሥርዓትን ምንነት፣ ጠባይ፣ ፋይዳና አይነቶች መመልከቱ በመንደርደሪያነት ከማገልገሉም በላይ፣ ሶስቱ የሽግግር ሥነ-ሥርዓቶች በሥነ-ሥርዓት የሚገለጹትን ሀሳቦች ይጋሯቸዋልና ለትንታኔያቸውም ፋይዳቸው ላቅ ያለ ነው።

ማንኛውም ማህበረሰብ እንደ ደረሰበትና እንደሚኖርበት የእድገት ደረጃ እና እንደሚኖርበት አካባቢ ለሚያከናውናቸው ተናጠላዊም ሆነ ቡድናዊ ለሆኑ አንዳንድ ተግባራት ሃይማኖታዊም (religious) ይሁን ዓለማዊ (secular) ሥነ-ሥርዓት ያከናውናል። የሥነ-ሥርዓትን ምንነት በሚመለከት የተለያዩ ምሁራን እንደሚከተለው አስፍረዋል፤ Sims and Stephens(2005:95) ሥነ-ሥርዓቶች ድግግሞሽ የሚታይባቸው፣ ልማዳዊ ድርጊቶች ቢሆኑም፣ ከልማድ ይልቅ አላማ ተኮር ናቸው። በተደጋጋሚ በከፍተኛ ሁኔታ የተደራጁና ቁጥጥር የሚደረግባቸው ሁል ጊዜም አንድ አካል የቡድኑ አባል መሆኑን የሚያመላክቱ ወይም የሚያሳዩ ናቸው። በማለት የሥነ-ሥርዓት አከዋወንን ድግግሞሽ፣ ለምን አላማ ወይም ተግባር እንደሚከወንና ከዋኞችም የሚያገኙትን ጥቅም አስፍረዋል፡፡

ይኸውም ሥነ-ሥርዓቶች አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በተደጋጋሚ የሚከናወኑ ናቸው፡፡ በልማድ መከናወናቸው ባይቀርም እንኳ ያ ልማድ ግን የራሱ የሆነ አላማ ያለውና በዘፈቀደ ሳይሆን በስርዓት የሚከናወን ነው፡፡ ግለሰቦችም የሥነ-ሥርዓቱ ተሳታፊ በሚሆኑበት ወቅት ቡድናዊ ተሳትፎ በማድረጋቸው የቡድን አባልነታቸውን ያጠናክርላቸዋል። ወደፊት የተመለከትኳቸው ሥነ-ሥርዓቶች የሚከወኑትም ዓላማን መሰረት አድርገው ሲሆን ለማህበረሰቡ የሚሰጡት ጥቅምም አለ ይህም ወደፊት ይገለጻል፡፡

Kassam(1999:489) ደግሞ ሥነ-ሥርዓትን እንደሚከተለው ይበይኑታል። ሥነ-ሥርዓቶች ክብረ-በዓላዊ ድርጊቶች ሲሆኑ፣ የማህበረሰቡ አባላትም ግላዊና ማህበራዊ ስኬቶቻቸውን በደስታ ያከብሩዋቸዋል። የKassam ብያኔ ትኩረት ያደረገው፣ ሥነ-ሥርዓቶች የደስታ ድባብ ያላቸው መሆናቸውን ነው፡፡ በተጨማሪም ለክዋኔያቸው ምክንያት የሚሆነውም ተናጠላዊ ወይም ቡድናዊ ጉዳይ እንደሆነና የተገኘ ድልም በሥነ-ሥርዓቶች አከባበር ወቅት የጋራ ደስታ የሚንጸባረቅበት መሆኑን ነው።

ስለዚህ ሥነ-ሥርዓት አንድ ማህበረሰብ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ ወይም ከአንድ ወቅት ወደ ሌላ ወቅት መሸጋገርን ምክንያት በማድረግ በጋራ የሚያከናውነው፣ አለማዊ ወይም ሃይማኖታዊ ይዘት ያለው ክዋኔ ነው ማለት ነው። ለዚህ ነው በዋግ ኽምራ ህብረተሰብ የወሊድ፣የጋብቻ እና የሞት ሥነ-ሥርዓት ክዋኔም ሃይማኖታዊ ይዘቶች የተንጸባረቁበት፡፡

### 2.1.1 የሥነ-ሥርዓት ጠባይ

በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚከወን ሥነ-ሥርዓት እንደ ማህበረሰቡ ሁኔታ የሚወሰን፣ የራሱ የሆኑ ጠባያት አሉት። ጠባያቱም ከምንነቱ የመነጩ ናቸው። ሥነ-ሥርዓቱን ሥነ-ሥርዓት የሚያደርጉትም የእነዚህ ጠባያት ጥምረት ነው። እነዚህ ጠባያቱም ክዋኔ፣ ለመከወን የመከወኛ ቦታ፣ ጊዜ እና ከዋኝ ናቸው። Sims and Stephens(2005:101-102) የሥነ-ሥርዓትን ጠባይ አስመልክተው ሲገልጹ፣

> ከበርካታዎቹ የሥነ-ሥርዓት ጠባያት መካከል፣ ልዩ የሆነ ድርጊት፣ ቃላዊ ክዋኔ፣ (ዘፈን፣ትወናዊ መነባንብ ወይም በቃል መግጠም) እስክስታ፣ የተለየ የምግብ ዝግጅት ክብረ-በዓላዊ አለባበስ፣ በቡድኑ አባላትና አለቃዎች ክዋኔ ወቅት አገልግሎት የሚሰጡ የእደ ጥበብ ውጤቶች የሚገኙበት ነው። እነዚህ ቁሳዊና ባህላዊ ነገሮች በሥነ-ሥርዓት አከባበር

ወቅት መገኘታቸው፣ ለሥነ-ሥርዓቱ ሂደት ክብደት ከመስጠታቸውም በላይ ስሜት ነኪነቱን ተጨባጭ ያደርጉታል።

ከዚህ የሥነ-ሥርዓት ጠባይ የምንገነዘበው፣ በተለያዩ ምሁራን ፈቃደ (ዶርሰንን ጠቅሰው)፣ 1991፣11-15; Dorson,1972:2-4; Sims and Stephens,2005:12; Wilson,1989:228) የፎክሎር ዓይነቶች ተብለው የተዘረዘሩት ዘውጎች በሙሉ በሥነ- ሥርዓት ውስጥ ተካተው የሚገኙ መሆናቸውን ነው። እነዚህም እንደ ፈቃደና Dorson አራቱን ማለትም፣ ስነ-ቃል፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት፣ ሀገረሰባዊ ልማድ እና ቁሳዊ ባህልን፣ እንደ Sims and Stephens(2005:99) ደግሞ ሶስቱን ማለትም ስነ-ቃል፣ ቁሳዊ ባህል እና ልማድንና ክብረ በዓላትን ወይም ሰዎች በቃላት የሚገልጿቸው ቃላዊ ሎር፣ ሰዎች በእጅ የሚሰሯቸው ቁሳዊ ሎር፣ ሰዎች በድርጊት የሚፈጽሟቸው ልማዳዊ ሎርን ነው፡፡

በዚህ ምክንያት Sims and Stephens (2005:99) ሥነ-ሥርዓቶች አብዛኛዎቹን የፎክሎር ዓይነቶች ቃል-ግጥምን፣ ዘፈንን፣ እስክስታን፣ ምግብን፣ አልባሳትን፣ እና ጌጣ ጌጥን ይይዛሉ በማለት ገልጸዋል።

ስለዚህ ቀደም ሲል ስለ የጥናቱ ቦታ ማህበረሰብ አለባበስ፣ አጊያጌጥና አንዳንድ ቃል ግጥሞች መጠቀሳቸውም (ወደፊትም ይጠቀሳሉ) ከሥነ-ሥርዓት ክዋኔ የማይነጠሉ በመሆናቸው ነው፡፡

### 2.1.2 የሥነ-ሥርዓት አይነቶች

ሥነ-ሥርዓት በተለያዩ አይነቶች ሊከፈል እንደሚችል፣ የተለያዩ ምሁራን በስራዎቻቸው አስፍረዋል፤ በአይነት ለመከፈል የተጠቀሙባቸው መስፈርቶች ግን የተለያዩ ናቸው። አንዳንዶቹ ይዘታቸው ምን እንደ ሆነ በመለኪያነት በመውሰድ፣ ሌሎች ደግሞ ሥነ-ሥርዓቱ በሚከወንበት ወቅት የሚፈጠረውን ድባብ መለኪያ በማድረግ በአይነት በአይነት ይከፋፍሏቸዋል። ሥነ-ሥርዓቶች የሚከናወኑበትን ቦታ፣ ጊዜና የተሳታፊ አባላት መጠንን በመስፈርትነት በመውሰድ በተለያዩ አይነቶች ለመመደብ የተጠቀሙም አሉ። ለአብነት ያህል Sims and Stephens(2005:100-114) አበይት የሆኑት የሥነ-ሥርዓት አይነቶች አራት ናቸው በማለት ገልጸዋል፤ እነዚህም የሽግግር ሥነ-ሥርዓት፣በእድሜ የመድረስ ሥነ-ሥርዓት፣ አዲስ አባል የመቀበል ሥነ-ሥርዓት እና የስም አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት ናቸው።

Bell (1997:94) ደግሞ ስድስት መስፈርቶችን በመጠቀም ሥነ-ሥርዓትን እንደሚከተለው ከፍለውታል፡፡

1. የሽግግር ሥነ-ሥርዓቶች፣
2. ሰሌዳዊ እና መዘክራዊ ሥነ-ሥርዓቶች፣
3. የልውውጥ እና የቁርባን ሥነ-ሥርዓት፣
4. የመከራ ወይም የስቃይ ሥነ-ሥርዓት፣
5. የፍስግ፣ የጾምና የክብረ-በዓል ሥነ-ሥርዓት፣ እና
6. ፖለቲካዊ ሥነ-ሥርዓቶች

ይህ አከፋፈል ሥነ-ሥርዓቶች እንዲከወኑ ምክንያት የሆነውን ነገር መሰረት ያደረገ ነው፡፡ የእኔም ጥናት በሁለቱም አከፋፈል ተጠቅሶ የሚገኘው የሽግግር ሥነ-ሥርዓት ነው፡፡ ምክንያቱም ሶስቱም ሥነ-ሥርዓቶች የሚከወኑት ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጅ መሸጋገርን ምክንያት በማድረግ የሚከወኑ ናቸው፡፡

ሥነ-ሥርዓቱ በሚከወንበት ወቅት የሚኖረውን አውድ እንደ መለኪያ በመውሰድ ደግሞ ዝቅተኛ ወይም ከፍተኛ አውድ ያላቸው ብሎ መክፈል እንደሚቻል ተገልጿል። Sims and Stephens(2005:99) እንዳሰፈሩት ዝቅተኛ አውድ ያላቸው የሚባሉት በመደበኛነት ያልተመረጡና አስቀድሞ እቅድ የማይወጣላቸው ወይም አስቀድሞ ትውውቅ የማይደረግላቸው ሲሆኑ፣ ከፍተኛ አውድ ያላቸው የሚባሉት ደግሞ ለተወሰነ የታወቀ ኣላማ እና ለተወሰነ ጊዜ የሚከወኑና በጣም ቅርጻዊ የሆኑ ናቸው። እነዚህም ህዝባዊ የሆኑና በጣም አስፈላጊ ድርጊቶች ሲሆኑ፣ እንደ የሠርግሥነ-ሥርዓት እና የጥምቀት ክብረ-በዓል አከባበር የመሳሰሉት በዚህ ውስጥ ይካተታሉ። በከፍተኛ አውድ ስርዓት ወቅት ተሳታፊዎች የሚለብሷቸው ወይም የሚያጌጡባቸው ክብረ-በዓላዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች እንደሚኖሩም አስፍረዋል፡፡

ከዚህ በመነሳት አንድ ሥነ-ሥርዓት ታቅዶ በመከወኑና ሳይታቀድ በመከወኑ በተለያየ አይነት ሊመደብ እንደሚችል እንረዳለን። Malefijt(1968:189) ደግሞ የሚከወንበትን ጊዜ በመስፈርትነት በመጠቀም ሥነ-ሥርዓትን በተወሰነ ጊዜ የሚከወን ወይም መደበኛ የሆነና

በተወሰነ ጊዜ የማይከወን ወይም መደበኛ ያልሆነ ብሎ በሁለት መከፈል ይቻላል ይላሉ፡፡ በዚህ አከፋፈል የወሊድ፣ የጋብቻ እና የሞት ሥነ-ሥርዓት በሁለተኛው አይነት የሚካተት ነው፡፡

### 2.1.3 የሥነ-ሥርዓት ፋይዳ

የሥነ-ሥርዓትን ምንነትና ጠባይ እንደ ተመለከትነው በዘፈቀደ የሚከወን ድርጊት አይደለም። ጊዜ ተወስኖለት፣ ቦታ ተይዞለት፣ የስርዓቱ ተሳታፊዎችም (ተዋናዮችም ሆኑ ታዳሚዎች) ድርጊቱ የሚከናወንበትን አላማ ተረድተው፣ በስነ-ስርዓትና ደረጃ በደረጃ የሚከናወን ነው። የሥነ-ሥርዓት ይዘት አለማዊና ሃይማኖታዊ ሊሆን ይችላል፡፡ በሚከወንበት ወቅትም ለሚከወንለት ግለሰብም ሆነ ቡድን ወይም ለሚታደመው ማህበረሰብ የሚያበረክተው አንዳች ፋይዳም አለ። ይህንንም Bell(1997:29) ማህበራዊ ፋይዳውያንን፣ በመጥቀስ የሥነ-ሥርዓትን ፋይዳ እንደሚከተለው ይገልጻሉ፤ እንደ ማህበራዊ ፋይዳውያን ሥነ-ሥርዓት የሚከተሉት ፋይዳዎች አሉት። የማህበረሰቡን ስርዓት ለመቆጣጠርና ለማረጋጋት ያስችላል፤ ውስጣዊ መስተጋብሩንም ያስተካክላል፤ ቡድናዊ እምነቱን ወይም ጸባዩን ያስጠብቃል፤ ከተወሰነ መናጋት በኋላም ውስጣዊ ስምምነት እንዲፈጠር የማድረግ ፋይዳ አለው። ከዚህ የምንረዳው ሥነ-ሥርዓት አንድ ማህበረሰብ ማህበረሰባዊ እሴነቱን እንዲቀጥል የሚጫወተው ሚና ላቅ ያለ መሆኑን ነው፡፡ Marshall(2002:361) ደግሞ እጅግ በጣም ከታወቁት የሥነ-ሥርዓት ፋይዳዎች መካከል ማህበራዊ ትስስርንና የአንድነትን ስሜት መፍጠር ናቸው በማለት ገልጸዋል፡፡ በዚህ ምክንያት አንድ ሰው በአንድ ሥነ-ሥርዓት ላይ ተሳታፊ በሚሆንበት ወቅት አባል ከሆነበት ማህበረሰብ ጋር የሚኖረውን ግንኙነት እንደሚያጠናክርለት Galaty(1983:366) አስፍረዋል፡፡ ይህም የሚያመለክተው የአንድ ማህበረሰብ አባል የሆነ ግለሰብ በማህበረሰቡ በሚከወኑ ስርዓቶች ተሳታፊ በሚሆንበት ወቅት ከዚያ ማህበረሰብ ጋር ጥብቅ የሆነ ትስስር ለመፍጠር የሚያስችለው መሆኑን ነው፡፡

ከላይ እንደ ተገለጸው ሥነ-ሥርዓት ግላዊና ቡድናዊ ፋይዳ ብቻ ሳይሆን፣ ማህበረሰባዊ ፋይዳም አለው። ምክንያቱም በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎች እርስ በእርስ ተከባብረው እንዲቀጥሉ የማድረግ ሃይል ስላለው፣ የማህበረሰቡን ህልውና ከመጠበቅ አኳያ የሚጫወተው ሚና ላቅ ያለ ነው። ስለዚህ የአንድ ማህበረሰብ አባላት አንድን ሥነ-

ሥርዓት በሚከውኑበት ወቅት፣ እንደ ልማድ ብቻ ተቆጥሮ የሚከውኑት ሳይሆን፣ ከክዋኔው የሚያገኙት ጥቅምም አለ።

ስለዚህ ይህ ጥናትም በትንታኔ ምዕራፉ ሶስቱ ሥነ-ሥርዓቶች ለማህበረሰቡ ያላቸውን ፋይዳ ተመልክቷል፡፡

### 2.1.4. የሽግግር ሥነ-ሥርዓት

ቀደም ሲል እንደ ተመለከትነው ከሥነ-ሥርዓት አይነቶች አንዱ፣ በተለያዩ ስያሜዎች የሚጠራው የሽግግር ሥነ-ሥርዓት ነው። ይህም ከሌሎች የሥነ-ሥርዓት ዓይነቶች መካከል በይበልጥ ጎልቶ የሚጠቀስ ነው፡፡ የሽግግር ሥነ-ሥርዓትን ምንነት በሚመለከት የተለያዩ ምሁራን የተለያየ የሚመስል ነገር ግን የጋራ ነጥቦች የተካተቱበት ብያኔ ሰጥተው እናገኛለን። Debika(2010:767) የሽግግር ሥነ-ሥርዓት የአንድን ሰው የማህበራዊ ደረጃ ለውጥ የሚያመለክት አለማቀፋዊ ክስተት ሲሆን፣ የአንድ ባህል ማህበራዊ ደረጃዎች፣ እሴቶችና እምነቶች የሚገለጽበት ነው ብለዋል፡፡ Kearney(2009:74) ደግሞ ከብዙዎቹ የሥነ-ሥርዓት አይነቶች መካከል የሽግግር ሥነ-ሥርዓት መሰረታዊ አይነት ሲሆን፣ ይህም አንድ ሰው ከአንድ ማህበራዊ ደረጃ ወደ ሌላ ማህበራዊ ደረጃ መሸጋገሩን የሚያመለክት ነው ብለዋል፡፡

ከእነዚህ ምሁራን ብያኔዎች የምንገነዘበው የሽግግር ሥነ-ሥርዓት አንድ አካል፣ ግለሰብም ይሁን ማህበረሰብ ቀደም ሲል የነበረበትን ማህበራዊ ደረጃም ሆነ አካላዊ ገጽታ ትቶ፣ ወደ ሌላ ማህበራዊ ወይም አካላዊ ደረጃ መሸጋገሩን ለማመልከት የሚከናወን የሥነ-ሥርዓት አይነት መሆኑን ነው።ይህ ጥናትም የሶስቱን ሥነ-ሥርዓቶች ከመዋቅር አንጻር ሲመለከት ይህንን ማህበራዊ ሽግግር ተመልክቷል፡፡

የሽግግር ሥነ-ሥርዓት በአንድ በተወሰነ የማህበረሰብ ክፍል ወይም የተወሰነ ቦታ ብቻ የሚከወን አይደለም። ክዋኔያቸው ቢለያይም ሥነ-ሥርዓቶቹ በመላው ዓለም የሚከወኑ ናቸው፣ ለዚህ ነው Leach(1950:946) እነዚህ ሥነ-ሥርዓቶች በጥንታዊ ማህበረሰቦች በዘመናዊዎቹ ማህበረሰቦች፣ በአርሶ አደሩ በከተሜው፣ በማንኛውም ቦታና ባህል ውስጥ ይገኛሉ ያሉት፡፡ የአከባበራቸው ወይም የአከዋወናቸው ሁኔታ ግን ከባህል ባህል የተለያየ ነው፤ ይኸውም በአንዳንዶች ዘንድ ድግስ መደገስ፣ ማጊያጌጥና የተለየ የምግብ ዝግጅት

ሲጠይቅ፣ ባንዳንዶች ግን እንደዚህ የጎላ ሳይሆን በተወሰኑ የቡድን አባላት ተራ መስተጋብር ብቻ የሚከናወን ይሆናል።.

ስለዚህ ተመሳሳይ የሆነ የሽግግር ሥነ-ሥርዓት በተለያዩ አካባቢዎችና ማህበረሰቦች ዘንድ በተለያየ የአከባበር ሁኔታ ሊከወን ይችላል፡፡ የዋግ ኽምራ ህብረተሰብ የሽግግር ሥነ-ሥርዓትም የራሱ የሆነ አከዋወን አለውና ያንን የመግለጽና የመተንተን አስፈላጊነት ከዚህ የመነጨ ነው፡፡

### 2.1.4.1 የሽግግር ሥነ-ሥርዓት ዓይነቶች

በሽግግር ሥነ-ሥርዓት ውስጥ የተለያዩ የሥነ-ሥርዓት አይነቶች ይገኛሉ። Cox(1998,X) Van Gennepን እና Turnerን በመጥቀስ የመጀመሪያው የሽግግር ሥነ-ሥርዓትን የወሊድ፣ የጋብቻና የሞት ሥነ-ሥርዓት እና ቀመራዊ ሥነ-ሥርዓት በማለት በሁለት መክፈላቸውን፣ ሁለተኛው ደግሞ የውድቀትን ሥነ-ሥርዓት በመጨመር በሶስት መክፈላቸውን አስፍረዋል። Van Gennep ቀመራዊ ሥነ-ሥርዓት ካሏቸው መካከል የወርን፣ የዓመትን እንዲሁም የወራትን ለውጥ ምክንያት በማድረግ የሚከናወኑ ሥነ-ሥርዓቶች ይገኙበታል፡፡ Turner የውድቀት ስርዓት ያሏቸው ደግሞ የጭንቀት ሥነ-ሥርዓቶች ሲሆኑ፣ እነዚህም ህመምን፣ መካንነትን፣ ድርቅን፣ እና ጦርነትን የሚመለከቱ ናቸው። እነዚህም ወጥነት የሌላቸውና በሁኔታዎች የተወሰኑ፣ አንድን ግለሰብ ወይም የተወሰነ አካል ብቻ የሚመለከቱ ናቸው።

ስለዚህ የወሊድ፣ የጋብቻና የሞት ሥነ-ሥርዓት እንደ Van Gennep ከሁለቱ፣ እንደ Turner ደግሞ ከሶስቱ የሽግግር ሥነ-ሥርዓት ዓይነቶች መካከል አንዱ ነው፡፡

እነዚህ ሶስት ሥነ-ሥርዓቶች በአንድ ግለሰብ ህይወት ወቅት ትላልቅ ድርጊቶች ናቸው። Rasing (1995:35) እና Blumenkrantz, DG. & Goldstein, MB.(2010,41) Van Gennepን ጠቅሰው እንዳሰፈሩት ከሽግግር ሥነ-ሥርዓት ዓይነቶች መካከል በአበይትነት የሚጠቀሱት የወሊድ፣ የጋብቻ እና የሞት ሥነ-ሥርዓቶች ናቸው፡፡ ለዚህ ነው Hilbers(2006:90) ሰዎች ስለ የሽግግር ሥነ-ሥርዓት ማውሳት ከፈለጉ በመሰረታዊነት የሚጠቅሱት ወሊድ፣ ጋብቻና ሞትን ነው ያሉት፡፡

ይህ ጥናት የተመለከተውም እነዚህን ሶስት አበይት ሥነ-ሥርዓቶች ነው፡፡ በመቀጠል ስለ እያንዳንዳቸው ምንነትና ሊገለጹ ስለሚገባቸው ጉዳዮች፣ የተወሰኑ ነጥቦችን እጠቅሳለሁ።

### 2.1.4.1.1 የወሊድ ሥነ-ሥርዓት

የወሊድን ሥነ-ሥርዓት አከባበር ወይም አከዋወን ለመግለጽ፣ ከወሊድ በፊትና በኋላ የነበሩና የሚመጡ ሥነ-ሥርዓቶችን መመልከት ይገባል። Van Gennep(1960) በወሊድ ሥነ-ሥርዓት ወቅት መታየት የሚገባቸው የሚከተሉት መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡ ጽንሱ ከመወለዱ በፊት፣ ከእርግዝና ጋር የተያያዙ የተለያዩ ሥነ-ሥርዓቶች ይኖራሉ። እንደ ማህበረሰቡ ሁኔታ ቢለያይም፣ በምጥ ወቅት ምጡ ረጂም ጊዜ እንዳይወስድ፣ የሚወስድ መስሎ ከታየም የሚያጥርበትን ሁኔታ የሚያመቻቹ ክዋኔዎችና መማጸኖች ይኖራሉ። ህፃኑ/ህፃኗ ከተወለደ/ከተወለደች በኋላም የእሱም/የእሷም ሆነ የእናቲቱ ጤና አጠባበቅ ስርዓት፣ የእሱም/የእሷም ሆነ የእናቲቱ የአመጋገብ ስርዓት፣ የጥምቀት ስርዓት[19]፣ የስም አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት የመሳሰሉት የሚታዩ ናቸው።

እኔም የወሊድ ሥነ-ሥርዓትን ክዋኔና አውድ ስገልጽ ቅድመ-ወሊድ፣ወሊድና ድህረ-ወሊድ በማለት ከፍየ አቅርቤያለሁ፡፡

የወሊድ ሥነ-ሥርዓት ለግለሰብ ወይም ለማህበረሰብ የሚሰጠው ፋይዳም አለ፤ አንድ ሰው አይኑን በአይን ለማየት ያስችላል፤ ትውልድ እንዲተካ ከማድረጉም በላይ፣ እንደ ማህበረሰቡ የእድገት ደረጃ እና የባህሉ ስርዓት በርካታ ጥቅሞችን ይለግሳል። ለአብነት ያህል Van Gennep(1960:48) እንዳሰፈሩት በPhilippines የBontok Igrot ማህበረሰብ ዘንድ አንዲት ሴት ወልዳ ወላድነቷ ካልተረጋገጠ በስተቀር፣ጋብቻ መመስረት አትችልም፡፡ ከዚህ የምንረዳው ወሊድ ለሴት ልጅ ጋብቻ በቅድመ-መስፈርትነት የሚያገለግል መሆኑን ነው፡፡

ከወሊድ ሥነ-ሥርዓት ጋር ተያይዞ የሚታየው ደግሞ ለሕፃን የሚሰጥ ስም ነው፡፡ይህም አለማዊና ሃይማኖታዊ ሊሆን ይችላል፤ ይህን በሚመለከት Gamst (1968:124) ሲገልጹ

---

[19] የሥነ-ሥርዓቱ ከዋኞች በሚከተሉት የእምነት ዓይነት የሚወሰንና የሚለያይ ይሆናል፡፡

ለአንድ ሕጻን የክርስትና ስም መሰጠቱ በተምሳሌት ሙሉ ሰው መሆኑን የሚያመለክት ነው ይላሉ፡፡

ይህ ጥናትም በወሊድ፣ጋብቻና ሞት ሥነ-ሥርዓት ትንተና ላይ ሶስቱ ሥነ-ሥርዓቶች ለግለሰብም ሆነ ለማህበረሰብ የሚሰጠውን ፋይዳ ተመልክቷል፤ በክዋኔና አውድ ገለጻ ላይም ስም አወጣጥ ምን እንደሚመስል አስፍሯል፡፡

## 2.1.4.1.2 የጋብቻ ሥነ-ሥርዓት

በሽግግር ሥነ-ሥርዓት ውስጥ ከሚካተቱት መካከል አንዱ የጋብቻ ሥነ-ሥርዓት ነው፡፡ የጋብቻ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም ከቦታ ቦታ፣ ከማህበረሰብ ማህበረሰብ የተለያየ በመሆኑ፣ አንድ ወጥ የሆነ ብያኔ ለመስጠት ያስቸግራል፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ ብያኔዎችን እናገኛለን፡፡ ለአብነት ያህል Vaughn(2010:162 ) በማህበረሰቦች አካባቢ የጋራ መስፈርት ቢኖረውም እያንዳንዱ ባህል ጋብቻን በተለያየ መንገድ ይበይነዋል፡፡ በቀላሉ ጋብቻ ማለት ግን በማህበረሰቡ ዘንድ እውቅና ያገኘ በወንድና በሴት መካከል የሚፈጸም ጾታዊና ኢኮኖሚያዊ ጥምረት ነው ሲሉ፤ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቤተሰብ ህግ(1997) አንቀጽ አስራ አንድ ደግሞ ጋብቻን እንደሚከተለው ይበይነዋል፤ ጋብቻ ማለት ለአካለ መጠን የደረሱ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ለዘለቄታው አብሮ በመኖር ሃሳብ በራሳቸው ነፃ ምርጫ በሕግ ለመዋሃድ ፈቅደው በይፋ የሚመሠርቱት ግንኙነት ወይም በዚሁ ግንኙነታቸው አማካኝነት የሚዋቀር ሕጋዊ ተቋም ነው፡፡ ዓለማየሁ(1956፣22) ደግሞ የጋብቻ ምንነትን ለሃይማኖታዊ የጋብቻ አይነት ትኩረት በመስጠት እንዲህ አስፍረዋል፤

> ጋብቻ ሁለት በጾታ ተፋቃሪ ሰዎች ሕይወታቸውን ሙሉ በዚህ ዓለም የሚመጣባቸውን መከራ በትዕግሥት አሳልፈው ደስታቸውን በኅብረት ተካፍለው፣ አብረው እየኖሩ ሥጋውን ደሙን በመቀበል የሚገኘውን ጸጋ አምላክ፣ ሀብተ-እግዚአብሔር ተቀብለው መንግሥተ ሰማይን ለመውረስ አንድ አካል የሚሆኑበት የቃል ኪዳን መተሳሰሪያ ሰንሰለት ነው፡፡

ዋጋውም (2001፣41) ጋብቻ ቤተሰብን ለመመስረት ወንድና ሴት ልዩ በሆነ ማህበራዊና ህጋዊ ዝምድና የሚተሳሰሩበት ስርዓት ወይም ተቋም ነው፡፡ ጋብቻ በተጋቢዎቹ ጥንዶች ብቻ ሳይሆን በእነርሱም ወላጆችና የቅርብ ዘመዶች ጋር ፈርጀ ብዙ የሆነ ማህበረሰባዊ ትስስር የሚመሰርቱበት ስርዓት ነው፡፡ በማለት የጋብቻን ምንነትና የሚፈጥረውን ትስስርም ገልጸዋል፡፡

የተሻሻለው የኢትዮጵያ የቤተሰብ ህግ (1991)[20]ደግሞ በአንቀጽ 31፣ የጋብቻን ምንነት ከሚሰጠው ጠቀሜታ ጋር በማያያዝ ሲገልጽ፣ ጋብቻ አንድ ወንድና ሴት በእኩልነትና በፈቃደኝነት ቤተሰብ ለማቋቋም የሚመሰረቱት ጽምረት ነው። ጋብቻ እንደ ማህበረሰቡ ሁኔታ ተጋቢዎቹን፣ ቤተሰቦቻቸውን ብሎም ማህበረሰቡን በማስተሳሰር ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው ተቋም ነው ይላል፡፡

ከዚህ ብያኔ የምንረዳው ጋብቻ እንደ ተቋም የሚዋቀረው በሁለት ሰዎች ፈቃደኝነት ቢሆንም ፋይዳው ግን ከእነሱም አልፎ ለቤተሰቦቻቸው ብሎም ለሚገኙበት ማህበረሰብ ጭምር መሆኑን ነው፡፡ ለጋብቻው የሚከናወነውን ሠርግበመጥቀስ ዋጋው(2001፣30) ፋይዳውን ሲገልጹ ፣...ሠርግ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ማህበራዊ አውድ በመሆኑ ልዩ ልዩ የህብረተሰብ አባላት እርስ በእርስ እንዲተዋወቁ፣ ወዳጅነት እንዲመሰረቱና እንዲቀራረቡ አጋጣሚ ይፈጥራል ብለዋል፡፡ መሓሪ(1995፣32)ም ጋብቻ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ እንደሚከተለው አስፍረዋል፤ ጋብቻ የተጋቢዎች የግል ጉዳይ ነው ማለት አይደለም። እንዲያውም ጋብቻ የህብረተሰብ መሰረት በመሆኑ የመንግሥትና ህብረተሰብ ጥበቃና እንክብካቤ የሚጠይቅ ተቋም ነው ብለዋል። Keesing and Andrew Strathern (1998:217) Goughን ጠቅሰው እንዳሰፈሩት ደግሞ፣ ጋብቻ በሁሉም ቦታና ጊዜ ባህላዊ ውል ሲሆን፣ አዲስ የሚወለድን ሕፃን ተቀባይነት ያለው የማህበረሰቡ አባል እንዲሆን ያገለግላል ብለዋል፡፡

በጥቅሉ የጋብቻ ሥነ-ሥርዓት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች በተለያዩ መንገዶች ወይም የጋብቻ አይነቶች በመጠቀም አንድ ሆነው፣ ቤታቸውን የሚመሩበትና ቀጣይ ትውልድ የሚያፈሩበት ተቋም ነው ማለት ይቻላል።

## የጋብቻ ዓይነቶች

የጋብቻ አይነት በተለያየ መንገድ ሊገለጽ ይችላል፤ ዋናው ምክንያትም በዓይነት ለመክፈል በመስፈርትነት ያገለገለው ምንድን ነው? የሚለው ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የሚጋቡ ሰዎችን መጠን ወይም ጋብቻው የሚከናወንበትን የስርዓት አይነት በመለኪያነት በመውሰድ ጋብቻን በአይነት መክፈል ይቻላል፡፡ Randall(1988) የሚጋቡ ሰዎችን መጠን

[20] ለውይይት የቀረበው ነው፡፡

መለኪያ በማድረግ ጋብቻ በሁለት ሊከፈል እንደሚችል አስፍረዋል፤ እነዚህም Monogamy አንድ ለአንድ ጋብቻ፣ ማለትም አንድ ወንድ ለአንድ ሴት ወይም አንድ ሴት ለአንድ ወንድ ብቻ፤ Polygamy ደግሞ ብዙ የትዳር ጓደኛ መኖር ሲሆን ይህም በሁለት ይከፈላል፤ Polyandry አንድ ሴት ከሁለት ወይም ከሁለት በላይ ከሆኑ ወንዶች ጋር ጋብቻ መፈጸም፤ እና Polygyny አንድ ወንድ ከሁለት ወይም ከሁለት በላይ ከሆኑ ሴቶች ጋር ጋብቻ መፈጸም ናቸው።

ከዚህ አንጻር በዋግ ኽምራ ማህበረሰብ ዘንድ በብዛት የሚፈጸመው የጋብቻ ዓይነት አንድ ወንድ ለአንድ ሴት፣ አንዲት ሴት ለአንድ ወንድ ነው፡፡

በሌላ በኩል ጋብቻው የሚከናወንበትን የሥነ-ሥርዓት አይነት መለኪያ በማድረግ ጋብቻ በተለያየ ዓይነት ሊከፈል ይችላል። ለምሳሌ በኢትዮጵያ የሚታዩ የጋብቻ አይነቶችን በሚመለከት በተለያዩ ጽሁፋዊ ምንጮች የተለያየ አይነት ሰፍሮ እናገኛለን። Kifle (2002:27-28)

> በአማራዎች ዘንድ የተለመዱ ሁለት የጋብቻ አይነቶች አሉ፤ የመጀመሪያው የቤተክርስቲያን ጋብቻ ሌላው ደግሞ ከቤተክርስቲያን ውጭ ነው።...በአብዛኛው የሚመሰረተው የጋብቻ አይነትም በቤተሰብ የሚወሰን ነው፤ በፍቅር ላይ ተመስርቶ የሚፈጽም ጋብቻ በጣም ውሱን ነው፡፡

በማለት ይገልጻሉ። ከዚህ የምንረዳው ጋብቻን በአይነት ለመመደብ የተጠቀሙት መስፈርት ጋብቻው የሚፈጸመው በቤተክርስቲያን ስርዓት መሆንንና አለመሆንንና በተጋቢዎች በጎ ፈቃድ ወይስ በቤተሰብ በኩል መሆኑን ነው። በብያኔያቸውም ወደ ፊት በተለያየ ጋብቻ ዓይነትነት የምንመለከታቸው ከቤተክርስቲያን ውጭ የሚፈጸሙት ሁለት የጋብቻ አይነቶች በአንድ ላይ ተጠቃለው ቀርበዋል። ዋጋው(2001፤47) የጋብቻ አይነቶችን በሁለት በመክፈል እንደሚከተለው አስፍረዋል፤ እነዚህም የጋብቻ ስርዓቶች፣ የሰማንያ ጋብቻ፣ የሃይማኖት ጋብቻ በመባል ይታወቃሉ፡፡ የሰማንያ ጋብቻ በባህላዊ ስርዓት የአገር ሽማግሌዎች በሚገኙበት በሚፈረም የጋብቻ ስምምነት ህጋዊና ማህበረሰባዊ እውቅናና ጥበቃ የሚያገኝ የጋብቻ አፈጻጸም ስርዓት ነው፡፡ በማለት ሰማንያ ጋብቻ የሽማግሌ (የአገር ባህል ጋብቻ) እና የመዘጋጃ ቤት ጋብቻን እንደሚያካትት ገልጸዋል፡፡

በ1952 ዓ.ም በወጣው ፍትሐብሔር ህግ ነጋሪት ጋዜጣ ከአንቀጽ 578-580 የተገለጹት የጋብቻ አይነቶች ደግሞ ሶስት ናቸው፡፡ እነዚህም ብሄራዊ፣ የሃይማኖት እና የልማድ ጋብቻ ናቸው፡፡ The revised Family Code Proclamation No.213/2000 እንዳሰፈረው ደግሞ በዋናነት ሶስት አይነት ጋብቻ ማስፈጸሚያ ስርአቶች አሉ። እነዚህም በክብር መዝገብ ሹም ፊት የሚፈጸም፣ በሃይማኖት ስርአት መሰረት የሚፈጸም[21] እና በባህል ስርአት መሰረት የሚፈጸም ጋብቻ ናቸው።

ይህንን አከፋፈል በ1952 ከተገለጸው ጋር ስናነጻጽረው ሶስት ልዩነቶች እናይበታለን፡፡ በመጀመሪያ የ1952ቱ የጋብቻ ዓይነቶች ሲል፣ በ2000 ዓ.ም የተገለጸው ግን የጋብቻ ማስፈጸሚያ ስርዓቶች ብሏል፡፡ ሌላው ደግሞ የ1952ቱ ብሄራዊ ጋብቻ ያለውን የ2000ው ግን በክብር መዝገብ ሹም ፊት የሚፈጸም ጋብቻ በማለት አሻሽሎታል፡፡ ሶስተኛው ልዩነት ደግሞ የ1952ቱ የልማድ ጋብቻ ያለውን የ2000ው ግን በባህል ስርአት መሰረት የሚፈጸም ጋብቻ በማለት ገልጾታል፡፡ ስለዚህ የጋብቻ ሥነ-ሥርዓት አይነቶችን በሚመለከት ቀደም ካለው ከ1952ቱ ይልቅ በ2000ው በተሻለ አገላለጽ የቀረበ መሆኑ ያስታውቃል፡፡ ይህንንም መሓሪ(1995፣13) እንደሚከተለው ገልጸውታል፡፡

> ልዩነቱና ልዩ ልዩ የሚሆነው በአፈጻጸሙ ላይ እንጂ የተለያዩ የጋብቻ ዓይነቶች ሊኖሩ አይገባም ምክንያቱም የአፈጻጸም ስርዓታቸው ቢለያይም ውጤታቸው አንድ አይነት ነው፡፡ ስለሆነም ‹‹ልዩ ልዩ ዓይነት ጋብቻዎች የሚለው አቀራረጽ (የ1952ቱ) አግባብ ስላልነበር አዲሱ አቀራረጽ ማለትም ‹‹ልዩ ልዩ የጋብቻ አፈጻጸም ሥርዓቶች›› የሚለው ተመራጭ ሆኗል፡፡

የሁለቱ ተመሳሳይነት ደግሞ በሁለቱም በሃይማኖት የሚለው የጋብቻ ዓይነት ነው፡፡ የሃይማኖት ጋብቻ እንደ እምነቱ ዓይነት ተከታይ የተለያየ ቢሆንም፣ የሚፈጸመው ግን በቤተክርስቲያን ስርዓትና ደንብ ነው፡፡ በቤተክርስቲያን የሚከናወን ጋብቻ ደግሞ አንድ ለአንድ ለመወሰንና ላለመለያየት ቃል ተገብቶ በቁርባን[22] ወይም በተክሊል[23]የሚከናወን የጋብቻ ዓይነት ነው፡፡ በመጽሀፈ ክርስትና፣መጽሀፈ ተክሊል.መጽሀፈ ቁደር ወመጽሀፈ ቀንዲል (1992፣73) ደግሞ በቤተክርስቲያን ስርዓት የሚፈጸም ጋብቻ አንድ ለአንድ መሆን

---

[21] ይህንን የጋብቻ አይነት ዋጋው ( 2001፣49) የቤተክርስቲያን (የተክሊል) ጋብቻ ብለውታል፡፡ ነገር ግን የቤተክርስቲያን ጋብቻ በተክሊል ብቻ የሚፈጸም አይደለም ፤ተጋቢዎች ደናግል ካልሆኑ፣ አክሊል ሳይደፉ በቅዱስ ቁርባን ብቻ የቤተክርስቲያን ጋብቻ ሊፈጽሙ ይችላሉ፡፡

[22] ድንግልና የሌላቸው ተጋቢዎች የሚፈጽሙት የጋብቻ ዓይነት ነው፡፡

[23]ድንግልና ያላቸው ተጋቢዎች የሚፈጽሙት የጋብቻ ዓይነት ነው፡፡

እንደሚገባው እንዲህ ሰፍሯል፤ ጋብቻ አንድ በአንድ ይጸናል እንጂ ሁለተኛ ቁጥርን አይነካም ማለት ለአንድ ወንድ አንዲት ሴት ለአንዲት ሴት አንድ ወንድ ነው እንጂ፣ ለአንድ ወንድ ሁለት ሴት ለአንዲት ሴት ሁለት ወንድ አልተፈቀደም፡፡ ባል ከሚስቱ፣ ሚስት ከባሏ መተላለፍ የለባቸውም፡፡ ባል ሚስቱ ብቻ፣ ሚስትም በባሏ ብቻ ተወስነው ይኖራሉ፡፡

ዋጋው (2001፣47) ደግሞ ቀደም ሲል የልማድ ወይም በባህል ስርአት መሰረት የሚፈጸም ጋብቻን የሽማግሌ (የአገር ባህል ጋብቻ) በማለት ሰይመዋል፡፡ የጋብቻ አይነቱም በገጠር አካባቢ የሚኖሩ የአማራ ብሄር አባላት ጋብቻቸውን የሚፈጽሙት በአገር ባህል ስርዓት ወይም በሽማግሌዎች አማካይነት ሲሆን ይህም ባህል ለዘመናት የኖረ አሁንም በሰፊው የሚተገበር እንደሆነ ይታወቃል ብለዋል፡፡

Guday (2005:125) ደግሞ የሴቶች የጋብቻ እድሜን መለኪያ በማድረግ ያለእድሜ ጋብቻ አይነትን አስመልከተው እንደሚከተለው አስፍረዋል፡፡

> ከመስክ የሰብሰብኩት መረጃ እንደሚያመለክተው ሴት ልጆች ያለ እድሜ ጋብቻ የሚመሰርቱባቸው መንገዶች በአራት ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡
>
> 1.የቃል ኪዳን ጋብቻ-(ከመወለድ በፊት መታጨት)፣
>
> 2.የአንቃልባ ጋብቻ-(አንዲት ሕፃን የእናቷን ጡት እየጠባችና ታዝላ እያለች ወይም በአንድና በአራት ዓመት መካከል እያለች ጋብቻ የምትመሰርትበት፣
>
> 3.የማደጎ ጋብቻ-አንዲት ልጅ በአምስትና በዘጠኝ ዓመቷ ጋብቻ የምትመሰርትበት፣ እና
>
> 4.የልጅነት ጋብቻ ሴቶች በአስርና በአስራ አራት ዓመታቸው መካከል ወንዶች ደግሞ በአስራ አምስትና በአስራ ሰባት ዓመታቸው መካከል ጋብቻ የሚመሰርቱበት፣

የተጋቢዎች የማህበረሰብ አባልነትን መስፈርት በማድረግ ደግሞ ጋብቻ በአይነት ሊከፍል ይችላል፡፡ ይህም ተጋቢዎቹ የአንድ ማህበረሰብ አባላት(Endogamy) ወይም የተለያየ ማህበረሰብ አባል(Exogamy) መሆናቸውን የሚመለከት ነው፡፡ ከአንድ ማህበረሰብ አባላት ይልቅ የተለያዩ ማህበረሰቦች አባላት ጋብቻ ጥቅም እንዳለው Vaughn(2010:164) ሲገልጹ ከራስ ማህበረሰብ አባል ውጭ ባል ወይም ሚስት መፈለግ ጠቀሜታ አለው፡፡ ምክንያቱም

ህዝቦችን በስፋት የሚያገናኝ ሰንሰለት ሊሆን ከመቻሉም በላይ፤ የአንዱ ማህበረሰብ አባል ለአንድ ጉዳይ በሚፈለግበት ጊዜ ያገለግላል፤ ወይም መከላከያ ይሆናል፡፡ በማለት አስፍረዋል፡፡ በለውጥና ቀጣይነት እንደተገለጸው የዋግ ኽምራ ህብረተሰብ ጋብቻ በብዛት ከአገው ውጭ ጋርም ነው፡፡

አንድ ጋብቻ ከተጠቀሱት የጋብቻ አይነቶች መካከል በየትኛውም አይነት ቢከናወን፣ በአንድ ጊዜ የሚፈጸም ሳይሆን የራሱ የሆነ ቅደም ተከተላዊ ክዋኔዎች አሉት። ለዚህ ነው Keesing and Andrew J, Strathern (1998:221)

> ጋብቻ ረዥም ጊዜና በርካታ ደረጃዎችን የሚጠይቅ ሂደት ነው። ከተጋቢዎቹ አንዱ ወይም ሁለቱ ከሞቱ በኋላም፣ የጋብቻው ውል ለረጂም ጊዜ ይቀጥላል፤ ለአብነት ያህል በአንዳንድ ማህበረሰቦች ዘንድ በመጀመሪያ በክፍያ ተጀምሮ፣ ድል ያለ ድግስ ተከትሎ፣ የሙሽራ ክፍያ ተከፍሎ፣ የሙሽራዋ እናት ለሙሽራዋ የቤት ቁሳቁስ ስጦታ ታበረክታለች ያሉት፡፡

ከእነዚህ ክፍያዎች መካከል የሚጠቀሰው ደግሞ ማጫ ነው፡፡ እንደ Vaughn(2010:167) ማጫ (dowry) ማለት ከሙሽራዋ ወገኖች በብር ወይም በአይነት መልክ ለአዲስ ተጋቢዎች የሚሰጥ ነው፤ይህም የቤት ቁሳቁሶች፣ የማብሰያ እቃዎችና ቤትም ሊሆን ይችላል፡፡

ስለዚህ የጋብቻ ሥነ-ሥርዓት በሚጠናበት ወቅት ማህበረሰቡ በሥነ-ሥርዓቱ አፈጻጸም ወቅት የሚከተላቸውን ቅደም ተከተላዊ ተግባራት መመልከትና መግለጽ ተገቢ ይሆናል፡፡ እኔም የጋብቻ ሥነ-ሥርዓትን ክዋኔና አውድ የገለጽኩት ቅደም ተከተላዊ ሂደቶችን መሰረት በማድረግ ቅድመ-ሰርግ፣ሰርግና ድህረ-ሠርግ በማለት ተመልክቼዋለሁ፤ የማጫ ሁኔታም ተጠቅሷል፡፡

#### 2.1.4.1.3 የሞት ሥነ-ሥርዓት

ሶስተኛው የሽግግር ሥነ-ሥርዓት አይነት ደግሞ፣ ከሌላዎቹ ይልቅ በየትኛውም ማህበረሰብ አይቀሬ የሆነው፣ የሞት ሥነ-ሥርዓት ነው። የሞት ሥነ-ሥርዓት መሸጋገሪያነቱ ለሟች ብቻ ሳይሆን ለነዋሪውም ነው፤ ምክንያቱም አንድ ሰው በሞት የተለየባቸው ቤተሰቦች ከዘወትራዊ አኗኗራቸው የተለየ አኗኗርና ገጽታ ይታይባቸዋል፡፡ ይህም ማለት በሞት ሥነ-ሥርዓት ወቅት በህይወት የሚገኙት የሀዘኑ ተጠቂዎችም ከቀደምት ህይወታቸው

በተለየ ሁኔታ ሊታዩ ይችላሉ፡፡ Hilbersም(2006:93) የቀብር ሥነ-ሥርዓት ለሞተውም ሆነ በህይወት ላለው ማህበረሰብም የሽግግር ሥነ-ሥርዓት ነው፡፡ የሞተውን ከህያውነት ወደ ህይወት አልባነት ሲያሸጋገረው፣ በህይወት ያለውን ደግሞ የሞተው ባል ቢሆን ሚስት ከባለትዳርነት ወደ ባል የሞተባት ትሸጋገራለች በማለት ገልጸዋል፡፡

እንደ የሠርግሥነ-ሥርዓት ሁሉ የሞት ሥነ-ሥርዓት ታዳሚዎችም የሚከተሏቸው በርካታ ቅደም ተከተላዊ ተግባራት አሉ፡፡ እነዚህንም Van Gennep(1960) እንደሚከተለው አስፍረዋል፡፡ ማህበረሰቡ አስከሬኑን ከአካባቢው የሚያርቅበት፣ የሚያስወግድበት፣ ቦታ የሚያሲዝበትና በሞት የተለየው ሰው በቀሪዎቹ ላይ ያሳደረውን ስሜት የሚገልጽበት ስርዓት ይኖራል። ይህ ስርዓትም የአንድን ሰው መሞት ከማስተጋባት ጀምሮ ሀዘንተኞች ሀዘናቸውን እስከሚተውበት (እስከሚረሱበት) ድረስ የሚከናወን ነው።

የሞት ሥነ-ሥርዓት በጥቅሉ እንደ ሥነ-ሥርዓት፣ በተለይም እንደ የሽግግር ሥነ-ሥርዓት አይነትነቱ በተምሳሌት የበለጸገ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የሞት ሥነ-ሥርዓት ክዋኔ ለታዳሚው የሚሰጠው ጠቀሜታም አለ፤ ለአብነት ያህል ለሟች ተብለው የሚከናወኑ መታሰቢያዎች የማህበረሰቡን ቀጣይነት በማረጋገጥ፣ ግለሰቡ (መታሰቢያ አድራጊው) ወደ የጋራ የሆነው ማህበረሰብ እንዲቀላቀል ያደርገዋል፡፡ ምክንያቱም የሥነ-ሥርዓቱ ከዋኝ በቀብርም ሆነ በተዝካር ስርዓት ወቅት፣ ማህበረሰቡ እንዲከናወን የሚፈልጋቸውን ተግባራት በማከናወኑ ማህበረሰባዊ ግዴታውን እንዲወጣ ያደርገዋል፡፡ ስለዚህ እነዚህ ክዋኔዎች ከዋኙ በማህበረሰቡ ዘንድ ይሁንታ ማግኘቱን የሚያረጋግጡለትም ናቸው።

ስለዚህ እንደ ማህበረሰቡ ሁኔታ በተለያየ አካባቢ የሚከናወን የሞትና የሀዘን ሥነ-ሥርዓት ሲጠና፣ ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ፋይዳ ምን እንደሆነ መግለጽ ተገቢ ነው። በመሆኑም ይህ ጥናትም በመረጃ መተንተኛ ማእቀፍነት ከተጠቀመው አንዱ መዋቅራዊ-ፋይዳዊነት ነው፡፡

### 2.1.4.2 የሽግግር ሥነ-ሥርዓት ደረጃዎች

ቀደም ሲል እንደ ተመለከትነው የሽግግር ሥነ-ሥርዓቶች፣ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ ለመሸጋገር የሚከወኑ ሥነ-ሥርዓቶች ናቸው፤ በእነርሱ ስር የሚካተቱ ንኡስ የሽግግር

ደረጃዎች ወይም ንኡስ-ምድቦችም አሉ። Daniel(2009:160-161) እና Callais(2002:43-44) እንዳሰፈሩት፣ የመለየት ስርዓት፣ የመሸጋገሪያ ስርዓት እና የመቀላቀል ስርዓት ናቸው። የእነዚህን ሶስት ደረጃዎች ምንነት ደግሞ (Hill and Peggy Daniels,2008:XI; Draper ,2003:85-86, and Blumenkrantz,DG.& Goldstein,MB,2010:42) እንደሚከተለው አስፍረዋል፤ የመጀመሪያው ደረጃ ቀዳሚውን ማህበራዊ ቦታ ወደ ኋላ መተው ነው፤ የሁለተኛው ደረጃ የሚያተኩረው ደግሞ በሽግግር ሂደት ላይ መሆንን ነው፤ ሶስተኛውና የመጨረሻው ደግሞ ወደ አዲስ ማህበራዊ ቦታ መግባትን ወይም መቀላቀልን ያመለክታል፡፡ Davies(1994:3) ደግሞ እነዚህን ሶስት ደረጃዎች አንድ ሰው ከአንድ ክፍል ወደ ሌላ ክፍል ከሚኖረው እንቅስቃሴ ጋር በማያያዝ እንደሚከተለው ገልጸዋል፤ ሶስቱ የሽግግር ሥነ-ሥርዓት ደረጃዎች፣ የመጀመሪያው አንድ ሰው ከአንድ ክፍል ሲወጣ፣ ሁለተኛው ወደ ሌላ ክፍል ሳይገባ መቆየትን፣ ሶስተኛው ደግሞ ወደ ሌላ ክፍል መግባቱን የሚገልጹ ጽንሰ ሃሳቦች ናቸው፡፡ ከዚህም ሌላ Davies(1994:3) Van Gennep እነዚህን ሶስት ደረጃዎች በላቲን ቋንቋ ቅድመ-መካከል፣ መካከልና ድህረ መካከል ብለው መሰየማቸውን አስፍረዋል፡፡

የወሊድ፣ የጋብቻና የሞት ሥነ-ሥርዓቶችም እነዚህን ሶስት ደረጃዎች ያካተቱ መሆናቸውን (Hill And Peggy Daniels,2008 and Draper,2003) አስፍረዋል። ይሁን እንጂ እነዚህ ደረጃዎች በሶስቱም የሚገኙበት መጠን አንድ አይነት ሳይሆን የተለያየ ነው፡፡ ምክንያቱም መለየት በሞት፣ መሸጋገሪያ በነፍሰ-ጡርነት፣ መቀላቀል ደግሞ በጋብቻ ጎልተው ይገኛሉ (Draper,2003:71)። እነዚህ ሶስቱ የሽግግር ሥነ-ሥርዓት ደረጃዎች የሽግግር ሥነ-ሥርዓት መዋቅሮችም ናቸው፡፡ ምክንያቱም የመጀመሪያው ደረጃ ለሁለተኛው መነሻ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደረጃ ደግሞ ለሶስተኛው ደረጃ መንደርደሪያ ነው፤ በመሆኑም የአንድ ሥነ-ሥርዓት ተዋናይ ከነበረበት ደረጃ ሳይነጠል ወይም ሳይለይ ወደሚቀጥለው ደረጃ ለመሸጋገር አይዘጋጅም፤ ሳይሸጋገር ደግሞ ከሶስተኛው ደረጃ ጋር አይቀላቀልም፡፡

ይህ ጥናትም እነዚህ ሶስት ደረጃዎች በሶስቱ ሥነ-ሥርዓቶች ውስጥ ምን እንደሚመስሉ ተመልክቷል፡፡

## 2.2 የመረጃ እይታና የመረጃ መተንተኛ ማእቀፍ ጽንሰ-ሀሳብ

### 2.2.1 የመረጃ እይታ

በአንድ አካባቢ የሚሰበሰብ መረጃ በሁለት መንገድ ሊተነተን ይችላል፤ የባህሉ ባለቤት ስለ ባህሉ ምንነት የሚሰጠውን መግለጫ መሰረት በማድረግና የባህሉ ባለቤት ባልሆነው ወይም በተመራማሪው የምንነት መግለጫ፣ እነዚህም በተከታታይ ውስጣዊ እና ውጫዊ እይታ ይባላሉ (Dundes,2007:88)። ውስጣዊ እይታ አንድ የባህል ጥናት በባህሉ ባለቤት አመለካከት የሚሰጠው ትርጉም ሲሆን፣ ይህም የአንድን ባህል ማህበረሰባዊ ፋይዳ ሊገልጽ የሚችለው የባህሉ ባለቤት ነው የሚል ነው፤ ውጫዊ እይታ ደግሞ ስለ አንድ የተወሰነ አካባቢ ባህል፣ የባህሉ ባለቤት ባልሆነው የሚሰጥ ግንዛቤ ወይም ትርጉም ነው። ውስጣዊ እይታን ከውጫዊ እይታ የሚለየው፣ ተመራማሪው ለረጅም ጊዜ በጥናት ቦታው ቆይታ በማድረግ መረጃውን በተሳትፏዊ ምልከታ እና በቃለ መጠይቅ በመሰብሰብ፣ አጥኚው ይህን ባህል ከኢኮኖሚ ወይም ከስነ-ምህዳር ጋር ሳያስተያይና አንድን ጽንሰ-ሀሳብ ለመፈተሽ ሳያውለው የባህሉ ባለቤቶች ስለ ባህላቸው የገለጹትን ብቻ በስራው ሲያሰፍር ነው።

እኔም ጥናቱን ያከናወንኩት በሁለቱም እይታዎች ነው፡፡ ምክንያቱም የመረጃ አቀባዮቼ ስለ ሥነ-ሥርዓቶቹ የገለጹትን አደራጅቼ ገለጻ አድርጌያለሁ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በመስኩ (ፎክሎር) ያለኝን ግንዛቤ መሰረት በማድረግ የሥነ-ሥርዓቶቹን ክዋኔ ከተለያዩ ጽንሰ-ሀሳቦች አንጻር አብራርቻለሁ፤ ለውጥና ቀጣይነታቸውንም አስፍሬያለሁ፤ እንደ ባህሉ ባለቤትነቴ የማውቀውንና የተመለከትኩትን እንዳለ አላቀረብሁም፡፡ ስለዚህ የሥነ-ሥርዓቶቹን ክዋኔና አውድ ከመግለጽ በተጨማሪ Duranti (1997) እንዳሉት ግንዛቤ ተኮር የማብራራት ዘዴን በመጠቀም መረጃውን ከተለያዩ መስፈርቶችና የመረጃ መተንተኛ ማእቀፎች አንጻር ተንትኛለሁና ውጫዊና ውስጣዊ እይታን ተግባራዊ አድርጌያለሁ፡፡

### 2.2.2 የመረጃ መተንተኛ ማእቀፍ ጽንሰ ሀሳብ

አንድ ተመራማሪ መረጃውን ለመተንተን በማእቀፍነት የመረጣቸውን ዘዴዎች (ጽንሰ ሀሳቦች) እስከ ምክንያቱ መግለጽ ይጠበቅበታል፡፡ ምክንያቱም ያለው(1998፡452) እንዳሰፈሩት፣ ተመራማሪው የመረጃ መተንተኛ ዘዴን ሲመርጥ ምን ሊያድርግበት እንደ ሆነና ለምን እንደ መረጠው መግለጽ ይኖርበታል፡፡ በተለያዩ ዘመናት በፎክሎር ላይ

ጥናትና ምርምር ያደረጉ ሰዎች የሰበሰቧቸውን የፎክሎር ዘውጎች መረጃ ለመተንተኛነት በማእቀፍነት የተጠቀሙባቸውን አስራ ሁለት[24]ጽንሰ ሀሳቦች ወይም ዘዴዎች Dorson(1972) ዘርዝረዋል፡፡ በአንድ ማህበረሰብ ክብረ በዓሎች እና ሥነ-ሥርዓት ላይ ጥናት የሚያደርግ ደግሞ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም መረጃውን ሊተነትን ይችላል፡፡ ይህንን በሚመለከት Svoboda (2010) ክብረ በዓላትና እና ሥነ-ሥርዓቶች ሲጠኑ በመተንተኛ ማእቀፍነት ሊያገለግሉ ይችላሉ ብለው ከዘረዘሯቸው መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

1.የክብረ በዓላት አከባበርና የሥነ-ሥርዓት ክዋኔ ከታሪክ ጋር አጣቅሶ የሚመለከቱበት (Evolutionary Approach),

2.የክብረ በዓላት አከባበርና የሥነ-ሥርዓቱ ክዋኔ ለማህበረሰቡ ምን ጠቀሜታ እንዳለው የሚመለከቱበት (Functional Approach),

3.በክብረ በዓላት አከባበርና በሥነ-ሥርዓቶቹ ክዋኔ ወቅት የሚታዩ ውቅሮችንና ትስስራቸውን የሚመለከቱበት (Structural Approach),

4.በክብረ በዓላት አከባበርና በሥነ-ሥርዓቶች ክዋኔ ወቅት የሚገኙ ድርጊቶችንና ቁሳቁሶችን ተምሳሌታዊ ፍች በመተንተን የሚያጠኑበት (Symbolic and Interpretive Approach) በሥነ-ሥርዓት ጥናት ተምሳሌታዊ ነገሮችን በመተንተን በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱት Turner ናቸው፡፡

5.የክብረ በዓላቱን አከባበርና የሥነ-ሥርዓቶቹን ክዋኔ የሚተነትኑበት (Performative Approach),

6.በሥነ-ሥርዓቶቹ ክዋኔ ወቅት ተዋናዮቹ የሚገኙበት ደረጃ የሚጠቅሱበት፣ ቅድመ-መዋቅራዊነት (Proto-structural Approach)፡፡ በዚህ ጽንሰ ሃሳብ የሚጠቀሱት ደግሞ Van Gennep ናቸው፡፡

---

[24] እነዚህም፡- Historic-geographical, historical-reconstractional, ideological, functional, psychoanalytical, structural, oral formalic,cross-cultural, folk-cultural,mass -cultural hemisoheric and contextual ናቸው፡፡

በሥነ-ሥርዓት በተለይም በሽግግር ሥነ-ሥርዓት ጥናት በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱት Van Gennep የሽግግር ሥነ-ሥርዓት መረጃቸውን በስማቸው በሚጠቀሰው የVan Gennep የሽግግር ሥነ-ሥርዓት ጽንሰ ሃሳብ (Van Gennep's theory of the rite of passage) በመጠቀም ትንተና አድርገዋል Van Gennep(1960)፡፡ ይህ ጽንሰ ሀሳብ ሥነ-ሥርዓትን በተለይም የሽግግር ሥነ-ሥርዓትን ለመተንተን የሚያስችል ጽንሰ-ሃሳብ ነው፡፡ ለዚህም Carla(1993) የVan Gennep የሽግግር ሥነ-ሥርዓት ጽንሰ ሃሳብ ለበርካታ ሥነ-ሥርዓቶች መተንተኛነት ሊያገለግል ይችላል ብለዋል፤ ራሳቸውም የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ወደ ኮሌጅ ከመግባታቸው በፊት በሚሰጠው የክረምት የሽግግር መርሃ-ግብር ላይ ጥናት ለማድረግ ተጠቅመውበታል፡፡ ይህ ጽንሰ ሀሳብ ቀደምትነት ያለው ቢሆንም ባለንበት ዘመንም የሽግግር ሥነ-ሥርዓትን ለመግለጽና ለማጥናት የሚያስችል መሆኑን ምሁራን ገልጸዋል፡፡ ለአብነት ያህል Draper(2002:92) ምንም እንኳ የሽግግር ሥነ-ሥርዓት ጽንሰ-ሀሳብ መነሻው ከሃያኛው ክፍለ ዘመን ቀደም ብሎ ቢሆንም፣ በአሁኑ ጊዜ የሚገኝ ማህበረሰብን ማህበራዊ ሽግግር በግለሰብም ሆነ በቡድን ደረጃ ለመግለጽና ለመረዳት ዓይነተኛ ማእቀፍ ነው ብለዋል፡፡

እኔም ለመረጃ መተንተኛ ማእቀፍ የመረጥሁት ይህንን ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡ ምክንያቱም በተለያዩ ማህበረሰቦች ሥነ-ሥርዓት ላይ ጥናትና ምርምር በማድረግ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱት Van Gennep እና Victor Turner መረጃዎቻቸውን ለመተንተን ይህን ጽንሰ ሀሳብ ተጠቅመውበታል፡፡ Van Gennep(1960) የተለያዩ ሀገራትን የሽግግር ሥነ-ሥርዓቶች፣ በዚህ ጽንሰ ሃሳብ መሰረትነት ክዋኔን፣ አውድን፣ መዋቅርንና ፋይዳን ሲጠቅሱ፣ በሥነ-ሥርዓቶቹ ውስጥ የሚገኙ ድርጊቶችንና ቁሳቁሶችን ተምሳሌታዊ ፍችም ገልጸዋል፡፡ Turner(1967) በአፍሪካ በሰሜን ምእራብ ዛምቢያ የሚገኙ የNdembu ህዝቦችን ሥነ-ሥርዓት በመስክ ጥናት በቦታው በመገኘት በሰበሰቡት መረጃ ይህንን ጽንሰ-ሀሳብ በመጠቀም ጥናት አድርገዋል፡፡ የጥናት ጽሁፋቸውም በሁለት አበይት ክፍሎች የተከፈለ ነው፡፡ የመጀመሪያው የሥነ-ሥርዓቱን ክዋኔ፣ ሲከወን የሚታየውን አውድ፣ የድርጊቶችና ቁሳቁሶች ተምሳሌታዊ ፍች፣ የክዋኔውን መዋቅርና ሥነ-ሥርዓቱ ለማህበረሰቡ የሚሰጠውን ፋይዳ ትንታኔ ያካተተ ነው፡፡ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የሥነ-ሥርዓቱ ክዋኔ ተገልጾበታል፡፡ ስለዚህ ሥነ-ሥርዓት ሲነሳ እንደ Van Gennep ሁሉ ስማቸው ጎልቶ የሚጠቀሰው Turner የሽግግር ሥነ-ሥርዓት ጽንሰ ሃሳብን ለመተንተኛነት

ተጠቅመውበታል፡፡ ሌላው Zebec(1995) ናቸው፡፡ ጽንሰ ሃሳቡን የተጠቀሙበትም የCarnivalን ዳንስ ለመተንተን ነው፡፡ በትንተናቸውም የዳንሱን ክዋኔ፤ በክዋኔው ወቅት የሚፈጠረውን አውድ፣ የድርጊቶችንና ቁሳቁሶችን ተምሳሌታዊ ፍች፣ የክዋኔውን አወቃቀር ከVan Gennep የሽግግር ሥነ-ሥርዓት ደረጃዎች አንጻር እና የዳንሱ ክዋኔ ለማህበረሰቡ የሚሰጠውን ፋይዳ አሳይተዋል፡፡ ለዚህ ነው Davies(1994:3) የሽግግር ሥነ-ሥርዓት ሰዎች በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖራቸውን የደረጃ ለውጥ ለመተንተን የሚያስችል ጽንሰ-ሀሳብ ነው ያሉት፡፡

ስለዚህ የሽግግር ሥነ-ሥርዓት ጽንሰ ሀሳብ በአንድ ሥነ-ሥርዓት ክዋኔና አውድ ላይ የተመሰረተ ነው ማለት ነው፡፡ የሥነ-ሥርዓቱን ድርጊቶችና አገልግሎት ላይ የሚውሉ ቁሳቁሶች ተጨማሪ ፍችም ይፈተሸበታል፤ የሥነ-ሥርዓቱን መዋቅርና የሥነ-ሥርዓቱ ከዋኞች ከሥነ-ሥርዓቱ መከወን የሚያገኙት ጥቅምም ይተነተንበታል፡፡

እኔም የሶስቱን ሥነ-ሥርዓቶች መረጃ ለመተንተን የሽግግር ሥነ-ሥርዓት ጽንሰ ሀሳብን በማእቀፍነት ስጠቀም፣ በዚህ ጽንሰ-ሃሳብ ስር ለሚካተቱት የመተንተኛ ዘዴዎች ትኩረት ሰጥቻለሁ፡፡ እነዚህም ክዋኔ ተኮር ጥናት (Performance study)፣ አውዳዊ እይታ (contextual approach) ተምሳሌታዊነት (symbolism)፣ መዋቅራዊ-ፋይዳዊነት (structural-functional paradigm) ናቸው፡፡ ምክንያቱም Laneri(2008:2) Rappaportን በመጥቀስ እንደ ገለጹት፣ ሥነ-ሥርዓት ያካትታቸዋል ካሏቸው አምስት መሰረታዊ የሆኑ ገጽታዎች መካከል ሶስቱ፣ የሥነ-ሥርዓት ከዋኞች በሌሎች የተዘጋጀን ቅደም ተከተል ይጠብቃሉ፤ ሥነ-ሥርዓት በአንድ በተወሰነ አውድ ይከወናል፤ ያለ ክዋኔ ሥነ-ሥርዓት አይኖርም (አጽንኦት የራሴ)። በሥነ-ሥርዓት ላይ ጥናት የሚያደርግ ሰው እነዚህን መሰረታዊ ባህርያት ካልተመለከተ ደግሞ ሥነ-ሥርዓቱን በተገቢው ሁኔታ መግለጽ አይችልም፡፡

ቀደም ሲል የጠቀስኳቸው በሽግግር ሥነ-ሥርዓት ጽንሰ-ሃሳብ ስር የሚካተቱት የመተንተኛ ማእቀፎች ለመረጃ መተንተኛነት ለምን እንደ ተመረጡና የመተንተኛ ተገቢነታቸውን ለማሳየት እንዲቻል በጥቅሉም ቢሆን ምንነታቸውን እንደሚከተለው አንድ ባንድ እገልጻለሁ።

2.2.2.1 ክዋኔ ተኮር ጥናት (Performance study)

ለአንድ የፎክሎር ዘውግ ህልውና መሰረቱ ክዋኔ ነው። ክዋኔ የምንለው ደግሞ ቁሳዊው ቦታ ከሰብዓዊ ንክኪ ጋር ባለ ግንኙነት በአካላዊ እንቅስቃሴ እና ድምጽ አማካይነት የሚበለጽግ ንግግር ነው፡፡ Sims and Stephens(2005:26) Roger Abramsን ጠቅሰው እንደ ገለጹት የክዋኔን ጽንሰ ሀሳብ የአንድ ማህበረሰብ አባላት ማንነታቸውን የሚገልጹበትና የሚያጠናክሩበት ባህላዊ ድንጋጌ ነው፡፡ ስለዚህ ያለ ክዋኔ የፎክሎር ዘውጉ ምንነት በትክክል ሊገለጽ ወይም ሊታወቅ አይችልም። ህያው የሚሆነውም ሲከወን ነው፡፡ Finnegan(1977:28) አንዱ የፎክሎር ዘውግ ስለሆነው ቃል ግጥም ክዋኔ ሲገልጹ ቃል ግጥም ያለ ክዋኔ ህልውናም ሆነ ዘላቂነት አይኖረውም ብለዋል፡፡ Rappaport(1999) ደግሞ በሥነ-ሥርዓት ክዋኔ ወቅት ሊካተቱ የሚችሉ ነገሮችን በመዘርዘርና፣ ክዋኔ ቅደም ተከተላዊ የሆነ ብቻ ሳይሆን፣ መልእክትን ለመረዳት የሚያስችልም መሆኑን እንዲህ አስፍረዋል፡፡

> ክዋኔ ከሌለ ሥነ-ሥርዓት የለም፤ ሲከወንም ከዋኝ፣ አድማጭ ወይም ተመልካች፣ አጀቢ መሳሪያዎች ወዘተ. ይኖራሉ። የእነዚህ ነገሮች ጥምረት ነው ክዋኔውን ክዋኔ የሚያደርጉት። ክዋኔ ሃይማኖታዊ ቅደም ተከተሎች የሚገለጹበት አንዱ መንገድ ብቻ ሳይሆን እነዚህ ቅደም ተከተሎች የያዙት መልእክት የሚገለጽበት መሰረታዊ ክፍልም ነው ብለዋል፡፡

ክዋኔ የሚያካትታቸውን አካላት መቅረጽና መተንተን እንደሚገባም Dundes(2004:389) እንደሚከተለው አስፍረዋል፤ ፎክሎር ህያው የሚሆነው ሲከወን ብቻ መሆኑን ማንም የፎክሎር ባለሙያ ሊክድ አይችልም፡፡ የፎክሎር ክዋኔ የሚያካትተውም ተዋናዮችንና ታዳሚዎችን ነው፡፡ የክዋኔው ብቃትና ገጽታም መቀረጽና መተንተን አለበት ብለዋል፡፡

በዚህም መሰረት አንድ የፎክሎር ተመራማሪ በትክክል የፎክሎር ጥናት አደረገ የሚባለው ያ የፎክሎር ዘውግ እንዴት? መቼ? የት ቦታ? በምን መሳሪያዎች ታጅቦ? በእነማን? ወዘተ. እንደሚከወን ሂደቱንና ቅደም ተከተሉን በዝርዝር ሲገልጽ ወይም ክዋኔ ተኮር ጥናት ሲያደርግ ነው። በሥነ-ሥርዓት ላይ ጥናትና ምርምር የሚያደርግ የፎክሎር የመስክ ተመራማሪም፣ ተቀዳሚ ተግባሩ የሚሆነው፣ ሥነ-ሥርዓቱ እንዴት? በማን? የት? እና መቼ? እንደሚከወን በጥልቀት መመልከትና መረዳት ነው፤ ለዚህ ነው Vansina(1985:39) ክዋኔ የሚፈጸምባቸው ጊዜያት ዘፈቀዳዊ አይደሉም፤ የሚከወኑበት ወቅትም የተወሰነ በመሆኑ ምልከታቸው መስክ ላይ ተገኝቶ መሆን አለበት በማለት ያሰፈሩት። ከዚህ

መረዳት የሚቻለው መስክ ላይ ተገኝቶ ክዋኔውን ካልተመለከቱ በተገቢው መንገድ መከወኑን ለመግለጽ እንደማይቻል ነው፡፡

እኔም ክዋኔ ለሥነ-ሥርዓት ጥናት አይቀሬ መሆኑን በመገንዘብ እያንዳንዱ ሥነ-ሥርዓት እንዴት እንደሚከወን ገልጫለሁ፡፡

### 2.2.2.2 አውዳዊ እይታ (contextual approach)

አንድ የፎክሎር ዘውግ በሚከወንበት ወቅት አንዳች አይነት ድባብ ይፈጠራል። ያም ድባብ በከዋኙ ወይም በታዳሚው ላይ የሚያጭረው ስሜት ይኖራል፤ ሊያስደስት፣ ሊያሳዝን፣ ሊያስቆጭ፣ ሊያናድድ፣ ሊያስጨፍር ወዘተ ይችላል፡፡ Bauman and Briggs(1990:68) Dundesን በመጥቀስ እንዳሰፈሩት፣ የአንድ ፎክሎር ዘውግ አውድ ማለት ያ ዘውግ የሚከወንበት ማህበረሰባዊ ሁኔታ ነው። Ben-Amos(1988:4) ደግሞ አውድ በክዋኔ ላይ የሚጫወተውን ሚና ሲገልጹ፣ አውድ በክዋኔ ላይ የራሱ የሆነ ተጽእኖ ያሳድራል። ክዋኔው እንዲቋረጥ፣ እንዲቀጥል፣ እንዲደምቅ፣ እንዲቀዘቅዝ፣ ወዘተ.ሊያደርግ ይችላል። ምክንያቱም የፎክሎር ህልውና የተመሰረተው በማህበራዊ አውድ ነው ይላሉ፡፡

ስለሆነም አውድ ለክዋኔው ሂደትና ቅደም ተከተል ብቻ ሳይሆን ለዘላቂነቱና ለህልውናውም የጎላ ሚና ይጫወታል ማለት ነው። በዚህም ምክንያት አንድን የፎክሎር ዘውግ ከአውዱ ነጥሎ መመልከት ትክክለኛ መልእክቱን ለመግለጽ አያስችልም፡፡ ለዚህም Bauman and Briggs(1990:72) የአንድን ቃል ግጥም ቅርጽ፣ ፋይዳ እና ፍች ከአውዱ ውጭ መረዳት አይቻልም፤... ክዋኔ ተኮር ላይ ጥናት የሚያደርግ አጥኚ፣ ትኩረቱ በሁኔታዊ አውድ ወቅት የሚኖረውን ክዋኔ መሰረት አድርጎ ነው፡፡ በማለት አውድና ክዋኔ የማይነጣጠሉ መሆናቸውን አስፍረዋል፡፡ Dundesም (1980፡30) አውድን መመልከት ለሁሉም የፎክሎር ዘውጎች አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡ ይህ አስፈላጊነትም አውድ ከክዋኔ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ሊገለጽ የተፈለገውን ይዘትም ለማሳየት የሚረዳ መሳሪያ መሆኑን ያመለክታል፡፡

እኔም ሥነ-ሥርዓቶቹ በምን አይነት አውድ እንደሚከወኑ የገለጽኩት ከክዋኔያቸው ጋር በማጣመር ነው፤ ምክንያቱም ሁለቱም የማይነጣጠሉ ናቸው፡፡

### 2.2.2.3.ተምሳሌታዊ እይታ (symbolic approach)

ተምሳሌት የሚባለው አንድ ነገር ሌላ ነገርን ሲወክል ነው፤ የሚተነተነውም በማህበራዊና በባህላዊ አውድ ውስጥ ነው፡፡ እንደ Rappaport(1999:26) ሥነ-ሥርዓት ተምሳሌታዊ ቅርጽ ነው፡፡ ምንም እንኳ የአንዳንድ ነገሮች ተምሳሌታዊ ፍች አለማቀፋዊነት ያለው ቢሆንም፣ ለምሳሌ እርግብ ሰላም፣ ብርሃን እውቀት፣ መስቀል ክርስትና፣ ኮከብና ጨረቃ እስልምና ወዘተ. እየተባለ ከነገሮቹ ተጨማሪ የሆነ ተምሳሌታዊ ፍች ቢኖራቸውም፣ በአብዛኛው ተምሳሌት የሚተነተነው ግን በሚገለጽበት ማህበረሰብ ባህላዊ አውድ ላይ በመመርኮዝ ነው፡፡ ምክንያቱም በአንዱ ማህበረሰብ ባህል የሚኖረው ፍች በሌላው ማህበረሰብ ባህል ከሚሰጠው ፍች የተለየ እንዲያውም ተቃራኒ ሊሆን ይችላል፡፡

ከዚህ የምንረዳው ተምሳሌት ከሥነ-ሥርዓት ጋር የተቆራኘ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በየማህበረሰቡ የሚከናወኑ ሥነ-ሥርዓቶች በድርጊትና ድርጊቱ በሚከወንባቸው ቁሳቁሶች የተሞሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ቁሳቁሶችና ድርጊቶች ደግሞ በወቅቱ ከሚሰጡት አገልግሎት በተጨማሪ በውክልና የሚገልጹት መልእክት ይኖራል። ይህ መልእክትም ሃይማኖታዊ ወይም አለማዊ ሊሆን ይችላል፤ ተምሳሌታዊ የሚያደርጋቸውም ያንን መልእክት መሸከማቸው ነው። ስለዚህ የአንድ ነገር ተምሳሌታዊ ፍች የሚገኘው ከሚያመለክተው ነገር፣ ንግግር፣ ቁሳቁስና ድርጊት ጋር ተጣምሮ ነው። Turner(1970:52) አንድ ተምሳሌታዊ ነገር በአንድ ጊዜ በርካታ ነገሮችን ሊወክል እንደሚችል አስፍረዋል።

በአንድ ሥነ-ሥርዓት ላይ ጥናትና ምርምር የሚያካሂድ የፎክሎር ተመራማሪም በሥነ-ሥርዓቶቹ ውስጥ የሚኖሩትን ድርጊቶችና ቁሳቁሶች ተምሳሌታዊ ፍች መግለጽ ይገባዋል። እኔም በሶስቱ ሥነ-ሥርዓቶች ክዋኔ ወቅት ለሚታዩ ተምሳሌታዊ ነገሮችና ደርጊቶች ማብራሪያ ሰጥቻለሁ፡፡

### 2.2.2.4. መዋቅራዊ-ፋይዳዊነት (structural-functional paradigm)

መዋቅራዊ ፋይዳዊነት ሁለት ነገሮችን ይገልጻል፤ይህንን አስመልክተው Kurtz(2001:71) ሲገልጹ፤ይህ ጽንሰ-ሃሳብ የBranislaw Malinowski ፋይዳዊነትና የRadcliffc-Brown መዋቅራዊነት ጥምረት ሲሆን፣ የሚመለከተውም የማህበራዊ መዋቅር እና ተዛማጅ የሆኑ ሰብዓዊ ክንዋኔዎች ባንድ ወይም በሌላ በኩል ለማህበረሰባዊ ሥርዓቱ ጥምረት

የሚኖራቸውን ፋይዳ  ነው፡፡ ስለዚህ የአንድ ሥነ-ሥርዓት ትንተና በሚካሄድበት ወቅት ፋይዳው ከመዋቅሩ ተነጥሎ የሚታይ አይደለም፡፡ ስለዚህ መዋቅራዊ ፋይዳዊነት መዋቅራዊነትንና ፋይዳዊነትን አንዱን ከሌላው በመነጠል ሳይሆን በጥምረት የሚመለከት ጽንሰ-ሃሳብ ነው፡፡ በመቀጠል የእያንዳንዳቸውን ምንነት ገልጫለሁ፡፡

**መዋቅራዊነት** (structuracturalist approach)

ሥነ-ሥርዓት እንደ ፎክሎር ዘውግነቱ ድርጊቶቹ በቅደም ተከተል የተዋቀሩ ናቸው፡፡ ቅደም ተከተሉም መሰረታዊ የሆኑትን የስርዓት ባህሪዎች ያካተተ በመሆኑ በመለየት ይጀምራል፤ በመሸጋገሪያ ይቀጥላል፤ በመቀላቀል ይቋጫል፡፡ እነዚህም ቀደም ሲል በVan Gennep የሽግግር ሥነ-ሥርዓት ደረጃዎች የተባሉት ናቸው፡፡ ስለዚህ በጥቅሉ ሥነ-ሥርዓት፣ በተናጠል ደግሞ የሽግግር ሥነ-ሥርዓት መነሻ፣ መሸጋገሪያ እና መድረሻ አላቸው፤ የአንድ ድርጊት ህልውና የሚረጋገጠውም እነዚህ እርስ በእርሳቸው ሲያያዙና እነዚህ ክፍልፋዮች እውን ሲሆኑ ዋናው ሥነ-ሥርዓት ይከናወናል። ስለዚህ ዋናውን ስርዓት በጥቅሉ ከመመልከት አስቀድሞ፣ በውስጡ የሚገኙትን ጥቃቅን ክፍሎችና የእነዚህን ክፍሎች ወይም አካላት ምንነትና ትስስር መመልከት ያስፈልጋል። ምክንያቱም ዋናው አካል የእነዚህ ውቅሮች የእርስ በርስ ትስስር ድምር ውጤት ነው። መዋቅራዊነት ሲባልም እነዚህን ትስስሮች መመልከት ነው፡፡

የሶስቱን ሥነ-ሥርዓቶች መረጃ ትንተና ከመዋቅር አንጻር የተመለከትኩትም Van Gennep ሶስቱ መሰረታዊ የሽግግር ሥነ-ሥርዓት ደረጃዎች ካሏቸው የመለየት ስርዓት፣ የመሸጋገሪያ ስርዓት እና የመቀላቀል ስርዓት አንጻር ነው፡፡

**ፋይዳዊነት** (Functionalist Approach)

በየትኛውም ቦታ እና በማንኛውም ማህበረሰብ አማካይነት የሚከወን የፎክሎር ዘውግ ክዋኔ፣ በከዋኙ ማህበረሰብ እይታ ለዚያ ማህበረሰብ የሚሰጠው ፋይዳ ወይም ጠቀሜታ አለ፡፡ Oring(1976:68) የፎክሎርን ፋይዳ ምንነት አስመልክተው ሲገልጹ ፋይዳ የማህበረሰቡን የህልውና ሂደት ለመጠበቅና ለማህበራዊ አወቃቀሩ ቀጣይነት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተው ፎክሎር ማህበረሰብን የሚያስተሳስር መሳሪያ መሆኑን ነው፡፡ ባህል ለማህበረሰቡ የሚፈይደው ነገር ካልኖረ  ህልውና ሊኖረው አይችልም፤ይህንንም

Vansina(1985:100) ሲገልጹ፤ ማንኛውም ባህላዊ የሆነ መልእክት አላማ እና የሚፈይደው ነገር አለ፤ ካልሆነ ህልውና አይኖረውም፡፡ ያ የባህል ይዘት ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ጠቀሜታም ፋይዳ ይባላል፡፡ Wilsonም (1989:234) ለፎክሎር ህልውና ምክንያቱ የሰዎችን መሰረታዊ ፍላጎት ማሟላቱ ነው በማለት ተመሳሳይ ሀሳብ አስፍረዋል፡፡

ከዚህ አንጻር ለአብነት ያህል ፈቃደ(1991፤17-18) እንዳሰፈሩት ስነ-ቃል አምስት ተግባራት አሉት፤ የማምለጥ፣ የማጠናከር፣ የመትከል፣ የመግለጭ፣ የማስተማር፣ የመግታትና የመቆጣጠር ተግባራት። Bascom(1965:293-294) እንዳሰፈሩት ደግሞ በማህበረሰቡ ውስጥ ህልውና እንዲያገኝ ያስቻሉ የፎክሎር በርካታ ፋይዳዎች ቢኖሩም ዋና ዋናዎቹ የፎክሎር ተግባራት አራት ናቸው፤ እነዚህም የማምለጥ፣ የማጠናከር፣ የማስተማር እና የማህበረሰቡን የጋራ ህይወት በመንከባከብ ባህላቸውን ዘላቂነት እንዲኖረው በማስቻል የማህበረሰቡን የህይወት ሂደት እንዲጠበቅ የማድረግ ተግባራት ናቸው። Finneganም (1984:330) አንድ የስነ ቃል ዘውግ በርካታ ፋይዳዎች ሊኖሩት እንደሚችል ተረትን በመጥቀስ፣ ህጻናትን የማስተማር፣ ማህበራዊ ግንኙነት እንዲጠነክር፣ ህጻናት የማህበረሰቡን ወግና ልማድ እንዲጠብቁና መልካም ስነ-ምግባር እንዲላበሱ የማድረግ ፋይዳ እንዳለው አስፍረዋል። ማህተመ ስላሴም (1961፤47-48) ቃል-ግጥም ስራን ለማፋጠንና ድካም እንዳይሰማ የማድረግ ፋይዳ እንዳለው እንዲህ አስፍረዋል፤...ገበሬዎች በማኅበር በሚሰሩበት ጊዜ ድካማቸውን በግጥም ያቃልላሉ፤እረኞች ከብቶቻቸውን በሚጠብቁበት ወቅት ብቸኝነት እንዳይሰማቸውና ቀኑ እንዳይረዝምባቸው ልዩ ልዩ ግጥሞችን ያሰማሉ፡፡

Jabbour(2004:18-19) ደግሞ የፎክሎርን ፋይዳ በባህል ውስጥና ከባህል ውጭ መመልከት እንደሚቻል ሲገልጹ ፤

> ወደ ባህሉ ውስጥ ስንመለከት ፎክሎር የአንድን ማህበረሰብ ልማድ ያንጸባርቃል፤ እንዲህ በማድረጉም የማህበረሰቡን የማንነት ስሜት ያጠናክራል፤ ከማህበረሰቡ ውጭ ስንመለከት ደግሞ፣ ለተለያዩ ማህበረሰቦች ባህል ልውውጥ፣ መስተጋብር እና ትስስር አይነተኛ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል።

ብለዋል፡፡ ሥነ-ሥርዓትም ሆነ የሽግግር ሥነ-ሥርዓትም ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ፋይዳ እንዳለ ቀደም ባለው ክፍል ተመልክተናል፤ Marshall(2002:361) ይህንን አስመልክተው ሲገልጹ፣ እጅግ በጣም ከታወቁት የስርዓት ፋይዳዎች መካከል ማህበራዊ ትስስርንና

የአንድነትን ስሜት መፍጠር ናቸው ብለዋል፡፡ Galaty(1983:366) ደግሞ Durkheimን ጠቅሰው እንደገለጹት ሥነ-ሥርዓቶች አንድ ሰው አባል ከሆነበት ማህበረሰብ ጋር የሚኖረውን ግንኙነት ያጠናክራሉ በማለት ተመሳሳይ ሀሳብ አስፍረዋል፡፡ ስለዚህ በዚህ መስክ ጥናት የሚያደርግ ሰው እነዚህን ፋይዳዎች መጥቀስ ይኖርበታል፡፡ ሥነ-ሥርዓት ደግሞ ለማህበረሰቡ የሚያበረክተው አስተዋጾ በርካታ ነው፡፡ እነዚህ ማህበራዊ ፋይዳዎች በአስር አይነት ሊከፈሉ እንደሚችሉ ነው (Hilbers,2006:128-163) ያሰፈሩት፡፡

> እነዚህም ሰዎች እንዲሰባሰቡ ማድረግ፤ የእኔነት ስሜትን ማጠናከር፤ በማህበራዊ እሴትነት ማገልገል፤ ማህበራዊ ተጠቃሎነትን መፍጠር፣ ማህበረሰቡን ወደ እራስ ማያያዝ፣ እራስን ከመንፈስ ጋር ማያያዝ፣ በማህበረሰቡ፣ ለማህበረሰቡ ከማህበረሰቡ ጋር ለመማር በመማሪያ ቦታነት ማገልገል፣ ማህበራዊ መያያዝና ትስስርን መፍጠር፣ አንድነትን ህያው ማድረግ እና የፈጠራ ችሎታን ማሳደግ ናቸው፡፡

ማህበራዊነት ስንልም በአንድ ሥነ-ሥርዓት ላይ ጥናትና ምርምር የሚያደርግ ሰው ሥነ-ሥርዓቱ ለማህበረሰቡ የሚያበረክተው ነገር ወይም የሚጫወተው ሚና ምን እንደሆነ መግለጽ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ Beard-Moose(2010) የባህል አተረጓጎምን ስመልክተው Geertz የገለጹትን በመጥቀስ እንዳሰፈሩት፣ ባህልን ሲበይኑ ባህል በተምሳሌት ውስጥ የተካተቱ ታሪካዊ ውቅሮች የሚተላለፉበት፣ ሰዎች የሚግባቡባቸው ስለ ህይወት ምንነት የሚኖራቸውን ግንዛቤና እውቀታቸውን የሚያዳብሩባቸው፣ ሲወርድ ሲዋርድ በተምሳሌት ቅርጽ እየተላለፉ የመጡ ጽንሰ-ሃሳቦች ናቸው ብለዋል፡፡ እነዚህን ተምሳሌቶች እያወጡ መግለጽ ደግሞ ባህልን ማብራራት ነው፡፡

የእኔ ጥናት የሶስቱ ሥነ-ሥርዓቶችን ገለጻ ብቻ ያካተተ አይደለም፡፡ በሥነ-ሥርዓቶቹ ክዋኔ አማካይነት የአካባቢው ማህበረሰብ ስለ ሕይወት ያለውን ግንዛቤ በተምሳሌታዊ ቁሳቁሶችና ድርጊቶች የመግለጹን ሁኔታ ከተለያዩ ጽንሰ-ሃሳቦች አንጻር ተመልክቻለሁ፤ ሥነ-ሥርዓቶቹ ለከዋኞቹ ያላቸውን ፋይዳም ከመዋቅር ጋር በማጣመር አብራርቻለሁ፡፡ ምክንያቱም Svoboda(2010:774) እንደገለጹት የክብረ-በዓላትና የሥነ-ሥርዓቶች ታሪክ፣ ፋይዳ፣ መዋቅር፣ ክዋኔና ተምሳሌት ለሥነ-ማህበረሰብ ጥናት የተያያዙ ውህዶች ናቸው፡፡

የሽግግር ሥነ-ሥርዓት ጽንሰ ሃሳብን በማእቀፍነት በመጠቀም የሰበሰብኩትን መረጃ ያብራራሁትም Dawson(2002) እንደገለጹት የይዘትና የጭብጥ ትንተና ነው፡፡ ምክንያቱም

የሶስቱ ሥነ-ሥርዓቶች ገለጻ የተከናወነው ድርጊቶቹ በሚከናወኑበት ቅደም ተከተል ይዘቶችን በመግለጽ ሲሆን፣ ከተምሳሌት፣ ከአውድ፣ ከመዋቅራዊ ፋይዳዊነት አንጻር ስተነትን ደግሞ ጭብጣዊ ትንተና አከናውኛለሁ፡፡ የጎላ ባይሆንም አልፎ አልፎ ንጽጽራዊ ትንተናንም አከናውኛለሁ፡፡ ይህም ጎልቶ የሚታየው የሥነ-ሥርዓቶችን ለውጥና ቀጣይነት ከቦታ እና ከዘመን አንጻር እያነጻጸርኩ በተመለከትኩበት ወቅት ነው፡፡ እነዚህን የመተንተኛ ጽንሰ-ሃሳቦች ስጠቀምም በመስኩ ያለኝን ቀደምት እውቀት ተጠቅሜያለሁ፡፡ ምክንያቱም McLeod and Rachel Thomson (2010,82) እንደገለጹት ኢትኖግራፊ በቦታ፣ በጊዜ፣ በነገሮችና በባህርያት ገለጻና በግለሰቦችና በቡድኖች ምደባ ይጀምርና ስለማህበረሰቡ ሊገለጽ በተፈለገው ነገር ትንተና ይቋጫል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የጥናቱ ዘዴ

## 3.1 የጥናት ንድፍ

አንድ ሰው ስለ አንድ ጉዳይ ጥናት ለማድረግ በሚዘጋጅበት ወቅት አስቀድሞ ማዘጋጀት የሚገባው የጥናት ንድፍ ነው። ይህም ጥናቱን በምን መንገድና እንዴት እንደሚያከናወነው የሚያመለክተው ንድፍ ነው።Yin (2003:20) የጥናት ንድፍን በሚመለከት እንደሚከተለው አስፍረዋል፤ ጥናቱ በቅድሚያ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች መልስ እንዲያገኙ ለማስቻል ለጥናቱ መሰረታዊ የሆኑ የተለያዩ ነገሮችን ተከታታይነትና ትስስር ባለው መንገድ አዋህዶ ማቅረብ ነው። ስለዚህ የጥናት ንድፍ ለአንድ ጥናት አጀማመር፣ አካሄድና አጨራረስ የጎላ ሚና ይኖረዋል።

የጥናት ንድፍ አራት ነገሮችን እንደሚያካትት Punch (2000:52) ገልጸዋል፤ እነዚህም ስልት፣ የጽንሰ ሀሳብ አጽም፣ ማን ወይም ምን እንደሚጠና እና የምርምሩን መረጃ ለመሰብሰብና ለመተንተን የሚያገለግሉ መሳሪያዎችና ሂደቶች ናቸው። ከዚህ የምንረዳው በጥናት ዘዴነት የሚካተቱ ነገሮች እርስ በእርሳቸው የተያያዙና ጥናቱ ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች መልስ ለማስገኘት የጎላ ሚና የሚጫወቱ መሆናቸውን ነው።

በዚህ ምእራፍ የሚገለጸውም ጥናቱን ለማካሄድ የተከተልኩት የጥናት አቀራረብ እና የጥናት ዘዴ ነው።

### 3.2.የጥናቱ አቀራረብ

አንድ ጥናት በሶስት ዘዴዎች ሊቀርብ ይችላል። በዓይነታዊ፣ በመጠናዊ ወይም በጥምር ዘዴ (Creswell, 2009:3-4)። መጠናዊ ዘዴ ማለት በመጠን ወይም በቁጥር የሚገለጽ መረጃን የሚጠቀም ሲሆን፣ ዓይነታዊ ዘዴ ደግሞ መጠናዊ ወይም አሃዛዊ የሆነ መረጃን የማይጠቀም ነው። የተለመዱትና በአይነታዊ መረጃዎች ስር የሚካተቱትም ትራንስክራይብ የተደረጉ ቃለ መጠይቆች፣ በሚጠናው ቦታ የተያዙ የመስክ ማስታዎሻዎች፣ በቪዲዮ፣ በቴፕ የተቀረጹ መረጃዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ቃለ-ጉባኤ እና ዘገባዎች የመሳሰሉ ሰነዶች

ናቸው። እነዚህን አይነታዊ መረጃዎች በመጠቀም የሚካሄድ የትንተና አይነትም አይነታዊ ትንተና ይባላል።

የጥናት ዘዴየ አይነታዊ ነው፤ዓይነታዊ የጥናት ዘዴን የመረጥኩበት ምክንያትም Thomson (2011:78) እንዳሰፈሩት፣ አንድ ጥናት የሚከናወነው የአንድን ሁኔታ ፍች ወይም አንድ ሁኔታ በተወሰኑ የሰዎች ማህበራዊ ተራክቦ ላይ የሚኖረውን ገጠመኝ ለመረዳት ከሆነ፣ ትክክለኛው የጥናት ዘዴ ዓይነታዊ ዘዴ ነው፡፡ የሰበሰብኳቸውን አይነታዊ መረጃዎች በመረጥኳቸው የመተንተኛ ዘዴዎች (ጽንሰ-ሃሳቦች) የተነተንኳቸውም፣ ዓይነታዊ ዘዴን በመጠቀም ነው፡፡ ምክንያቱም ያለው(1998፣250) እንዳሉት መረጃዎቹ ዓይነታዊ ሆነው በገለጻና በሀተታ የቀረቡ ከሆነ፣ ዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎችን መጠቀም የግድ ይላል፡፡

### 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

አንድ ተመራማሪ ለጥናቱ በግብዓትነት የሚያገለግሉትን መረጃዎች የሚሰበስብባቸው የተለያዩ መሳሪያዎች አሉ። ይህም እንደ ጥናት ርእሱ የሚወሰን ቢሆንም፣ ዋና ዋና የሚባሉት ምልከታ፣ ቃለ-መጠይቅ እና መጠይቅ ናቸው(ፈ.ቃደ፣1991፣90)። እነዚህን መሳሪያዎች እንዳስፈላጊነቱ በተናጠል ወይም በጥቅል መጠቀም ይቻላል። ተመራጩ ግን አጣምሮ መጠቀሙ ነው፤ ምክንያቱም በአንዱ መሳሪያ ማግኘት ያልተቻለውን መረጃ በሌላው ማግኘት ከመቻሉም በላይ፣ የመረጃዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥም ያስችላል። Murchison(2010:49) እንደ ገለጹት በኢትኖግራፊ ላይ ተመስርቶ የሚከናወን ጥናት እንደ ጥናት ስልትነቱ ሶስት ቁልፍ ዘዴዎችን በጥምረት ይጠቀማል፤ እነዚህም ተሳትፏዊ ምልከታ፣ ቃለመጠይቅና ምስሎችን ማካተት ናቸው፡፡

ለጥናቴ የተጠቀምኩትን መረጃ የሰበሰብኩት ቅይጥ ወይም ድብልቅ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን በመጠቀም ነው። እነዚህም ምልከታ፣ ቡድን ተኮር ውይይት፣ ቃለ መጠይቅ (የግልና የቡድን) የውይይት መድረክ ናቸው። ምክንያቱም ቅይጥ ወይም ድብልቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን መጠቀም አስተማማኝነት ያላቸውን መረጃዎች ለመሰብሰብ ያስችላል፡፡

መረጃ ለመሰብሰብ የተጠቀምኩባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አጠቃቀምም ቀጥሎ እንደተገለጸው ነው።

### 3.3.1 ምልከታ

በስፋት የሚታወቁት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ምልከታ፤ ቃለ-መጠይቅና ጸሁፋዊ መጠይቅ ናቸው፡፡ (Pauline and Calvin,1998:163;Yin,2003 93:Matthews, and Liz Ross,2010:55) እንዳሰፈሩት ደግሞ ምልከታ በሁለት መንገዶች ሊከናወን ይችላል። በተራ ምልከታ እና በተሳትፏዊ ምልከታ። መስከኛው ፋይዳ ያለውና በተግባር የተፈተነ መረጃ ለመሰብሰብና የማህበረሰቡን ጠባይ ለመግለጽ የሚያስችለው መሰረታዊ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያም ተሳትፏዊ ምልከታ ነው። በዚህ የምልከታ ዓይነት መረጃ የሚሰበስብ ተራ ተመልካች ሳይሆን በድርጊቱ ክዋኔ ላይ ተሳታፊ የሚሆን ነው (Yin, 2003, 93-94)፡፡

ሰባት የተለያዩ የተሳትፏዊ ምልከታ አይነቶች አሉ፤ እነዚህም በአይነትነት የተጠቀሱት ሁለት መስፈርቶችን በመጠቀም ነው፤ አንዱ የመረጃ ሰብሳቢው በመረጃ አቀባዮቹ መረጃ መሰብሰቡ መታወቅና አለመታወቅ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ መረጃ መሰብሰቡ ታውቆ በድርጊቱ ላይ የሚሳተፍበትን መጠን የሚመለከት ነው፡፡ መረጃ ሰብሳቢው መረጃ እንደሚሰበስብ በመረጃ አቀባዮቹ በኩል በመታወቅና ባለመታወቅ መስፈርት ተሳትፏዊ ምልከታ በግልጽና በስውር ሊከናወን ይችላል፡፡ እንደ Dawson(2002:147) ግልጽ የሚባለው ተመራማሪው በተሳትፏዊ ምልከታ መረጃ እንደሚሰበስብ በተጠኚዎቹ የሚታወቅበት ሲሆን፣ ስውር ደግሞ ሳይታወቅ መረጃ የሚሰበሰብበት መንገድ ነው፡፡ አንድ መስከኛ መረጃውን መሰብሰብ ያለበት በግልጽ እንጂ በስውር መሆን እንደሌለበት Wilson(1989:228) ሲገልጹ፣ ሰዎች ተሞክሯቸውን በሚያጋሩህ ወቅት ባህል ተሸካሚዎች ናቸውና ሊከበሩ ይገባል፤ማለትም መረጃህን ተደብቀሃቸውና ያለፈቃዳቸው መሰብሰብ የለብህም ይላሉ፡፡ይህም እንደ ርእሱና መረጃ ለመሰብሰብ እንደሚገጥመው ችግር የሚወሰን ይሆናል፡፡

መረጃ የሰበሰብኩት በድብቅ ሳይሆን መረጃ አቀባዮቹ ለምን እንደማጠና አውቀውት በግልጽ የተካሄደ ነው፡፡ ስለዚህ ቀደም ሲል ከተጠቀሱት ሁለት የተሳትፏዊ የምልከታ

አይነቶች መካከል እኔ የተጠቀምኩት ግልጽ ተሳትፏዊ ምልከታን ነው፡፡ ምክንያቱም ወደ መረጃ መሰብሰብ ያመራሁትና የሰበሰብኩት፣ መረጃውን ለምንና በምን መሳሪያ እንደምሰበሰብ ለመረጃ አቀባዮቼ ገልጬና ፈቃደኝነታቸውን አረጋግጬ ነው፡፡

የመረጃ ሰብሳቢውን የምልከታ ተሳትፎ መጠን መለኪያ በማድረግ ደግሞ ተሳትፏዊ ምልከታ በአምስት አይነት እንደሚከፈል Spradley(1980) አስፍረዋል፡፡ እነዚህም የተሳትፎውን መጠን ማነስና መብዛት በቅደም ተከተል የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት የመጀመሪያው ውጫዊ ተሳትፎ ሲሆን ይህም መረጃ ሰብሳቢው ከቪዲዮ ወይም ከቴሌቪዥን መረጃ የሚሰበስብበት እንጂ እሱ በቀጥታ በድርጊቱ የማይሳተፍበት ነው፡፡ ሁለተኛው አይነት ደግሞ መረጃ ሰብሳቢው በክዋኔው ተገኝቶ ነገር ግን በንቃት የማይሳተፍበት የተሳትፎ አይነት ነው፡፡ ሶስተኛው ደግሞ መረጃ ሰብሳቢው ለክዋኔው እንደ ውጫዊም እንደ ውስጣዊም ሰው ሆኖ በድርጊቱ የሚሳተፍበት ተመጣጣኝ ወይም መካከለኛ ተሳትፎ ነው፡፡ አራተኛው ደግሞ ሌሎች የክዋኔው ተሳታፊዎች እንደሚሳተፉት ንቁ ሆኖ የሚሳተፍበት ሲሆን፣ አምስተኛው ደግሞ መረጃ ሰብሳቢው ከፍተኛ የሆነ ተሳትፎ የሚያደርግበት ሙሉ ተሳትፏዊ የሚባለው የምልከታ አይነት ነው፡፡

እኔም ከመስክ መረጃ የሰበሰብኩት ለፎክሎር ጥናትና ምርምር ትክክለኛ መረጃ ሊያስገኙ የሚችሉትን ሁሉንም የተሳትፏዊ ምልከታ አይነቶች በጥምረት በመጠቀም ነው። ይኸውም ማህበረሰባዊ ሁኔታዎቹ እንድሳተፍ በማይፈቅድልኝ ንቁ ያልሆነ ምልከታን ተጠቅሜያለሁ፤ በመሆኑም በዚህ ምልከታ መረጃ የሰበሰብኩት እኔ ተሳታፊ ለመሆን በማልችልበት የሥነ-ሥርዓቶቹ ክዋኔ ወቅት ነው፡፡ ለአብነት ያህል በወሊድ ስርዓት በምጥ ወቅት፣ በሠርግ ወንዶች በሚያከናውኗቸው ስራዎች፣ በቀብር ሥነ-ሥርዓት ሀዘንተኞች በአንድ የማልቀሻ ቦታ ክብ ሰርተው በሚዞሩበት ወቅት… ወዘተ ነው፡፡ በክዋኔዎቹ ባለ መሳተፌ የጎደለን የመረጃ ክፍተትም በቀረጻ አማካይነትና በቃለ-መጠይቅ እንዲሟላ አድርጌያለሁ። ስለዚህ በነዚህ ክዋኔዎች ከተሳትፏዊ ምልከታ አይነቶች መካከል ከአንደኛ እስከ ሶስተኛ የተገለጹትን ተጠቅሜያለሁ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ማህበረሰባዊ ሁኔታውና አውዱ እንድሳተፍ በሚፈቅድልኝ ሁሉ መረጃ የሰበሰብኩት ንቁ እና ሙሉ ተሳትፏዊ ምልከታ በማድረግ ነው፡፡ ለአብነት ያህል በወሊድ የገንፎ አበላልና እልልታ፣ በሠርግ አመጋገብ፣ በሠርግ የሴቶች ጭፈራ፣ በቀብርና በቀጠሮ

ለቅሶ (አጎበር) ተሳታፊ በመሆን መረጃ ሰብስቤያለሁ፡፡ ለአካባቢውና ለባህሉ እንግዳ ባለ መሆኔና ቀደም ሲል በተለያዩ ጊዜያት፣ በሰርግና በለቅሶ ሥነ-ሥርዓቶች ስለተሳተፍኩ ማህበረሰቡ በእነዚህ ሥነ-ሥርዓቶች ተሳታፊ በሚሆን ሰው ላይ የሚጠብቀውንና የማይጠብቀውን፣ የሚወደውንና የሚጠላውን አውቀዋለሁ፤ ስለሆነም መረጃ በምሰበስብበት ወቅት ተሳትፏዊ ምልከታ ለማከናወን የጎላ ችግር አላጋጠመኝም፡፡

### 3.3.2 ቃለ መጠይቅ

የተለያዩ የቃለ መጠይቅ አይነቶች እንዳሉ O'Reilly(2005:116) Pauline and Calvin, (1998:183) እና ያለው(1998፣178) አስፍረዋል። እነዚህም ውሱን ቃለ-መጠይቅ፣ ነጻ ቃለ-መጠይቅ እና ከፊል ነጻ ቃለ-መጠይቅ ናቸው። የመጀመሪያው በቅድሚያ ለተዘጋጁ ጥያቄዎች ብቻ መልስ የሚሰጥበትና ተመራማሪው ሌላ ጥያቄ የማያክልበት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ተመራማሪው በቅድሚያ ጥያቄዎችን ሳያዘጋጅ፣ ርእሱን ለመረጃ አቀባዩ በመግለጽ፣ ተጠያቂው ዘና እያለ በነጻነት ሀሳቡን የሚገልጽበት ነው፤ ሶስተኛው የሁለቱም ቅልቅል ነው።

እኔም ውሱንና ነጻ የቃለ መጠይቅ አይነቶችን ተጠቅሜያለሁ። ምክንያቱም Thomson(2011:78) እንዳሰፈሩት ለአይነታዊ የጥናት ዓይነት የሚሰበሰበው መረጃ በቃለ-መጠይቅ፣ በመስክ ማስታወሻ፣ በምልከታ፣ በቪዲዮና በሌሎች ምስላዊና ጽሁፋዊ ነገሮች ቢሆንም፣ ዋናው ግን በቃለ-መጠይቅ ነው፡፡ ውሱን ቃለ-መጠይቅን የተጠቀምኩት በሥነ-ሥርዓቶቹ (የወሊድ፣ የጋብቻ እና የሞት) ክዋኔ ላይ ምልከታና ቀረጻ ከማድረጌ በፊት፣ በሂደትና በኋላ ነው፡፡ ይህም ስለ ሥነ-ሥርዓቶቹ አከዋወን ቃለ መጠይቅ ላደረግሁላቸው ሰዎች ሲሆን፣ ነጻ ቃለ-መጠይቅን ደግሞ የሥነ-ሥርዓቶቹ ክዋኔ ሃይማኖታዊ ዳራ እንዳለውና እንደሌለው ለማጣራት ስል፣ ለሃይማኖት መሪዎች ቃለ መጠይቅ ባደረግሁበትና የመረጃ ክፍተት የታየባቸውን ጉዳዮች በሞላሁበት ወቅት ነው፡፡

ቃለ መጠይቅ ያደረግሁትም የግልና የቡድን ነው፡፡ የቡድን ቃለ መጠይቁም በርከት ላሉ ሰዎች በአንድ ላይ ቃለመጠይቅ ያደረግሁበት ነው፡፡ በዚህም የአንድ ወረዳና ከተለያዩ ወረዳዎች የመጡ የመረጃ አቀባዮችን እና የተወሰኑ ሴቶችን ባንድ ላይ በማድረግ የቡድን ቃለ መጠይቅ አድርጌያለሁ፡፡

### 3.3.3 ቡድን ተኮር ውይይት

ሌላው ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀምኩት ቡድን ተኮር ውይይት ነው፡፡ Dawson( 2002:29-30) እንዳሰፈሩት ቡድን ተኮር ውይይት ማለት የተወሰኑ ሰዎች ለሚጠየቁት ጥያቄ በቡድን ሆነው በመወያየት መልስ የሚሰጡበት መንገድ ሲሆን ውይይቱን የሚመራ ሰውም ይገኝበታል፡፡ ቡድን ተኮር ውይይት ያደረግሁትም ከስድስቱም ወረዳዎች ለተውጣጡና ስለ ጥናቴ ምንነት ግንዛቤ ይኖራቸዋል ለተባሉ በአራት ቡድን ሃያ አንድ ሰዎች ነው፡፡ በርእሰ-ጉዳዩ ላይ በነጻነት ለመወያየት እንዲችሉም ወንዶችን ለብቻ ሴቶችን ለብቻ አወያይቻለሁ፡፡ የውይይቱ መሪም እኔ ነበርሁ፡፡ በዚህ የውይይት ዓይነት ለሴቶች በመወያያነት የቀረበው በብዛት የወሊድ ሥነ-ሥርዓትን በሚመለከት ሲሆን ለወንዶች ደግሞ የጋብቻና የሞት ሥነ-ሥርዓቶች ነው፡፡

### 3.3.4 የውይይት መድረክ

የውይይት መድረክ የተከናወነው ከሁሉም ወረዳዎች የሰበሰብኩት መረጃ ከተቀናበረና ለደረጃ ማበልጸጊያ ከቀረበና ከፈታኞች መጨመር ያለባቸው ጉዳዮች ከተገለጸ በኋላ ነው፡፡ የውይይቱ ዓላማም በሶስቱ ሥነ-ሥርዓቶች ክዋኔ ገለጻ ላይ ከየወረዳዎቹ የሚከናወኑ ነገር ግን በጥናቱ ውስጥ ያልተካተቱ ነጥቦች ካሉ እንዲካተቱ ለማድረግ ነው፡፡ የውይይቱን መድረክ ያዘጋጀውና ከየወረዳው ለመጡ የውይይቱ ተሳታፊዎች ለአበልና ለመስተንግዶ ወጭ ያደረገውም የዋግ ኸምራ ብሄረሰብ አስተዳደር ዞን ጽ/ቤት ነው፡፡

በውይይቱም ከስድስቱም ወረዳዎች የተወከሉና የየወረዳዎቹ የባህልና ቱሪዝም ሰራተኞችም የተገኙበት ሃያ፣ (አስራ አራት ወንድና ስድስት ሴት) ተሳታፊዎች ሆነዋል፡፡ አጥኚዋ የሶስቱን ሥነ-ሥርዓቶች ክዋኔ ካቀረበች በኋላ የመድረኩ ተሳታፊዎች በሶስት ቡድን ተከፍለው ተወያይተዋል፤ መጨመር አለባቸው ያሏቸውንም በቡድን ተወካዮቻቸው አማካይነት አቅርበዋል፤ እኔም እነዚህን ተጨማሪ መረጃዎች ተጠቅሜያለሁ፡፡ ውይይቱም ለአንድ ቀን የተካሄደ ነው፡፡ አብዛኛው መረጃ የተሰበሰበው በአማርኛ ቢሆንም የተወሰነ ደግሞ በአገውኛ (በኸምጣኛ) ተሰብስቧል።[25]ምክንያቱም ምንም እንኳ የዞኑ የስራ ቋንቋ አማርኛ ቢሆንም፣ በሥነ-ሥርዓቶቹ ክዋኔ ወቅት ማህበረሰቡ በሁለቱም ቋንቋዎች

[25] በሠርግ የሴቶች ዘፈን ላይ በትግርኛ የተዜሙ በጣም የተወሰኑ ዜማዎችና አዝማቾችም በምልከታ ተገኝተው በጥናቱ ውስጥ ተካተዋል፡፡

ሀሳቡን በመግለጹ ነው። ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹ የመረጃ አቀባዮቹ ለጥያቄዎቹ በአማርኛ መልስ ለመስጠት የሚቸገሩ ስላልነበሩ ብዙውን ቃለ መጠይቅ ያደረግሁትና መረጃ የሰበሰብኩት በአማርኛ ነው፡፡ በአማርኛ መልስ ለመስጠት የሚቸገሩ የተወሰኑ መረጃ አቀባዮችን ስጠይቅ ደግሞ፣ እኔ ያልተረዳሁትን (በተወሰነ መጠን በኽምጣኛ ስለምግባባ) አስተርጓሚ በመጠቀም መረጃውን ተቀብያለሁ፡፡ በሥነ-ሥርዓቶቹ ክዋኔ ወቅት በኽምጣኛ የተገለጹትንም (ለአብነት ያህል በሠርግ ሥነ-ሥርዓት ሸኙነ ሸኙነ) አጠቃቀማቸውን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ለማሳየት እንዲቻል በኽምጣኛ እና ትርጉማቸውን ደግሞ በአማርኛ አስፍሬያለሁ፡፡

ከተጠቀሱት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በተጨማሪ ከሰነዶችም መረጃ ሰብስቤያለሁ፡፡ ስለዚህ ሶስት ጎንዮሽ የመረጃ የመሰብሰብ ዘዴን ተጠቅሜያለሁ፡፡ ምክንያቱም Reichardt and Thomas D.Cook(1985:94) እንዳሰፈሩት ይህ መንገድ ባንዱ ዘዴ ያላገኘሁትን መረጃ በሌላው ዘዴ እንዳገኝ አስችሎኛል፡፡

### 3.4. የመረጃ አቀባዮች ወይም ምንጮች

አንድ ተመራማሪ ወደ መስክ ወጥቶ መረጃ በሚሰበስብበት ወቅት መረጃ ሊያቀብሉት የሚችሉትን አካላት አስቀድሞ ማመቻቸት ይጠበቅበታል። ለዚህም ይረዳው ዘንድ ጥናቱ የሚያነሳቸውን ጥያቄዎች መልስ ሊያስገኙለት የሚችሉትን አካላት ለይቶ ማወቅ ተቀዳሚ ተግባሩ ይሆናል። በዚህ መሰረት የዚህ ጥናት መረጃ (በምልከታ እና ከሰነዶች ካገኘሁት በተጨማሪ) የመረጃ አቀባይ የሆኑት የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው፤ እነዚህም በምልከታና በቀረጻ ሥነ-ሥርዓቶቻቸውን በመቅረጽና በመመልከት በምንጭነት ካገለገሉት የሥነ-ሥርዓቶቹ ተዋናዮች በተጨማሪ የታዳሚዎችና የሥነ-ሥርዓቶቹን ክዋኔና ሂደት በሚመለከት ግንዛቤ አላቸው የሚባሉ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ናቸው፤ እነዚህም ወንዶች፣ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ አዛውንቶች የሃይማኖት መሪዎች፣ በለቅሶ የሙሾ ቃል-ግጥም ደርዳሪዎች፣ የልምድ አዋላጆች ወዘተ. ናቸው። በዚህም መሰረት የመረጃ አቀባዮቹ መጠን ሴት ሰላሳ አንድ[26] ወንድ ስልሳ ስድስት በጠቅላላ ዘጠና ሰባት ነው፡፡ ከእነዚህ መካከል ቁልፍ የመረጃ አቀባይ የሆኑት[27] ሃያ ስድስት ናቸው፤ አስራ ስምንቱ ደግሞ ቁልፍ ያልሆኑ

[26] የሴቶች ቁጥር ከወንዶች አነስተኛ የሆነው ስለአካባቢው ባህል የሚያውቁ ሰዎች ሳጠያይቅ የምጠቆመው በብዛት ወንዶች ስለሆኑ ነው፡፡
[27] ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች በብዛት መረጃ ያቀበሉ ሲሆኑ፣ ቁልፍ ያልሆኑት ደግሞ ስለ አንድ ክስተት ብቻ መረጃ ያቀበሉ ናቸው፡፡

የመረጃ አቀባይ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ ሃምሳ ሶስቱ ደግሞ በቡድን ቃለ መጠይቅ፣ በቡድን ተኮር ውይይትና በመድረክ ውይይት የተሳተፉ የመረጃ አቀባዮች ናቸው፡፡

### 3.5. ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች የተሰበሰቡበት አውድ

ክዋኔንና አውድን መሰረት አድርጎ የሚሰበሰብ መረጃ፣ በኢትኖግራፊ ላይ ይመሰረታል፡፡ ኢትኖግራፊ ደግሞ አጥኚው ጥናቱን ወደሚያከናውንበት ማህበረሰብ ውስጥ ዘልቆ በመግባት መረጃውን ከሚሰበስብበት ማህበረሰብ ጋር ቆይታ በማድረግ ከመስክ የሚሰበስባቸውን መረጃዎች ለጥናቱ የሚጠቀምበት ዘዴ ነው። ለዚህ ጥናት ያገለገለው መረጃም በኢትኖግራፊ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ምክንያቱም መረጃው የተሰበሰበው ወደ ተጠኚዎቹ አካባቢ በመግባትና ቆይታ በማድረግ ነው፡፡ መረጃውንም የሰበሰብኩት ከቀዳማይ ወይም የመጀመሪያ ደረጃ እና ካልአይ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ምንጮች ነው። በዚህም መሰረት አብዛኛውን መረጃ የሰበሰብኩት አራት ጊዜ ወደ የጥናቱ ቦታ የመስክ ጉዞ በማድረግና እና ለስድስት ወራት ያህል በዚያው በመቆየት፣ የመጀመሪያ ደረጃ ምንጮችን በመሰብሰብ ነው። ስለ የጥናቱ ቦታና ማህበረሰቡ፣ ስለ ጥናቱ ርእሰ-ጉዳይ ጽንሰ-ሀሳብና ተዛማጅ ስራዎች የሚገልጹ ውሱን ካልአይ ወይም የሁለተኛ ደረጃ ምንጮች መረጃዎችን ደግሞ ከቤተ-መጻህፍት አግኝቼ ተጠቅሜያለሁ፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ መረጃ ደግሞ ከተለያዩ አውዶች ሊሰበሰብ ይችላል፡፡ ፊቃደ(1991፣122-123) እንደገለጹት፣ የፎክሎር መረጃ ከመስክ የሚሰበሰብባቸው ሶስት የመቼት ዓይነቶች አሉ፤ እነዚህም ተፈጥሯዊ መቼቶች፣ አርቲፊሻል መቼቶች እና ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼቶች ናቸው። የመጀመሪያው መቼት፣ አንድ የፎክሎር ዘውግ በማህበረሰቡ ሲከወን በቦታውና በጊዜው በመገኘት መረጃ የሚሰበሰብበት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ መረጃ ሰብሳቢው የፎክሎር ዘውጉ በተፈጥሯዊ አውድ (በቦታውና በሚፈጸምበት ጊዜ) ሲከወን መረጃውን ማግኘት በማይችልበት ወቅት፣ መረጃ አቀባዮቹ የተፈጥሯዊ መቼትን አስመስለው እንዲከውኑለት የሚፈጥረው አውድ ነው። ሶስተኛው ደግሞ ተመራማሪው፣ ማንኛውም መረጃ አቀባይ በተገኘበት ቦታና ጊዜ ከአውዱ ውጭ መረጃ የሚሰበሰብበት የመቼት አይነት ነው።

ቀዳማይ ወይም የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎችን የሰበሰብኩት፣ ተፈጥሯዊ እና አርቲፊሻል መቼቶችን በመጠቀም ነው።ዋናው ግን ተፈጥሯዊ መቼት ነው፤ ምክንያቱም Wilson(1989 :242) እንደገለጹት ከሌላዎቹ የትምህርት መስኮች ይበልጥ ፎክሎር በተፈጥሯዊ መቼት መታየት ስላለበት ነው፡፡

በዚህ አውድም ሃያ ሁለት ማለትም፣ ስምንት የወሊድ፣ ስምንት የጋብቻ እና ስድስት የሞት ሥነ-ሥርዓቶችን ምልከታ እና ቀረጻ ለማካሄድ ባቅድም ምልከታና ቀረጻ ያደረግሁት ግን ሃያ አንድ ማለትም አምስት የወሊድ፣ አስር የጋብቻ እና ስድስት የሞት ሥነ-ሥርዓቶችን ነው፡፡ ክንውኑ ካቀድኩት በአንድ እንዲያንስ ያደረጉ ምክንያቶች አሉ፡፡ እነዚህም በመስክ ቆይታየ ወቅት የሥነ-ሥርዓቶቹ አለመከሰት፣ ቢከሰቱም ምልከታ እንዳደርግ መረጃ አቀባዮቹ ፈቃደኛ አለመሆን (ለአብነት ያህል ቤት ውስጥ የሚከናወንን ወሊድ)፣ ሥነ-ሥርዓቶቹ ወደ የሚከወኑበት ለመሄድ ቦታው ለትራንስፖርት አመቺ አለ መሆንና በትራንስፖርት ችግር ምክንያት ነው፡፡ ሥነ-ሥርዓቶቹ በሚከወኑበት ቦታና ጊዜ ወይም በተፈጥሯዊ መቼት በመገኘት፣ በምልከታ፣ ማስታወሻ በመያዝና በምስልና በድምጽ በመቅረጽ የመጀመሪያ ደረጃ መረጃ መሰብሰብ መቻሌም የሥነ-ሥርዓቶቹን ክዋኔ፣ አውድና መዋቅር ለመረዳትና ለመግለጽ አስችሎኛል። ከዚህም በተጨማሪ ተገቢ የሆኑ የመረጃ አቀባዮችን እንዳገኝና በቃለ መጠይቅ ተጨማሪ መረጃ እንድሰበስብ ረድቶኛል፡፡

በሌላ በኩል አርቲፊሻል መቼትን የተጠቀምኩት ደግሞ፣ ስለ ሥነ-ሥርዓቶቹ ሂደትና ምንነት ማብራሪያ በምፈልግበት፣ በሥነ-ሥርዓቶቹ ወቅት አገልግሎት ላይ የዋሉ ቁሳቁሶችና የተከናወኑ ድርጊቶች ተምሳሌትነታቸው ምን እንደሆነ ለማወቅ፣ ሥነ-ሥርዓቶቹ ለማህበረሰቡ የሚሰጡትን ጥቅምና ሃይማኖታዊ ትስስርን ለመረዳት፣ መረጃ አቀባዮቹ በሚገኙበት በየትኛውም ቦታና ጊዜ በቃለ መጠይቅ መረጃ በሰበሰብኩበት ወቅት ነው።

## 3.6. የመቅረጫ መሳሪያዎች አጠቃቀም

ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው ይህ ጥናት የተከናወነው እኔ ወደ ተጠኚዎቹ አካባቢ በመሄድና ከእነሱ ጋር ቆይታ በማድረግ ምልከታና ቀረጻ በማከናወን ነው፡፡ መረጃ የሰበሰብኩባቸው ሶስቱ ሥነ-ሥርዓቶች ደግሞ የፎክሎር ዘውጎች ናቸው፤ የፎክሎር መረጃ ደግሞ በተለያዩ

መሳሪዎች እገዛ ሊሰበሰብ ይችላል፤ በመቅረጸ-ድምጽ፣ በፎቶና በመቅረጸ-ምስል። በእነዚህ መሳሪያዎች መረጃን መሰብሰብ የሚሰጠውን ጠቀሜታ አስመልክተው Pink(2007:163) እንዲህ ይላሉ፤ በእነዚህ መሳሪያዎች መረጃ መሰብሰብ በጽሁፍ ለመግለጽ አስቼጋሪ የሆኑትን ቅርጽ፣ ቀለምንና ንድፍን ለመቅረጽ ከማስቻላቸውም በላይ በአንድ ወቅት የተቀረጸ ነገር ለማንኛውም ጊዜ እንዳለ ሆኖ ሊያስረዳ ይችላል። O'Reillyም (2005:161) የመቅረጫ መሳሪያዎችን ተጠቅሞ መረጃን መሰብሰብ ለባህል ጥናት የሚኖረውን ጠቀሜታ አስመልክተው ሲገልጹ፣ የመቅረጫ መሳሪያዎችን ተጠቅሞ መረጃን መሰብሰብ የጽሁፍ መረጃን ለመደገፍ እና ትንታኔውም ጥንካሬና ጥልቀት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

ባህል በቃላት ብቻ የሚገለጽ አይደለም፤ በአካልና በድርጊትም እንጂ፤ ስለዚህ ፎቶ መጠቀም እነዚህን ለመግለጽ ያስችላል። ይህም በቃላት የሚገለጸውን ሀሳብ ጥንካሬ እንዲኖረው ያደርገዋል ብለዋል። Gottliebም (2006:570) በፎቶ መረጃ መሰብሰብ ያለውን ጠቀሜታ አስመልክተው እንዲህ አስፍረዋል፡፡ በሺ ቃላት ሊገለጽ የሚችለውን በፎቶ መግለጽ በመቻሉ መስክ ላይ ቆይታ በማድረግ መረጃ የሚሰበስቡ አጥኚዎች በስራቸው ውስጥ ፎቶዎችን ማካተት ጀምረዋል ብለዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳው የባህልን ጥናት በተገቢው መንገድ ለማከናወን የሚያስፈልገው መረጃ በቃላት ብቻ ሳይሆን በምስልም ተደግፎ መቅረብ እንደሚገባው ነው፡፡ ይህም የሚጠናውን ነገር ገጽታ በመግለጽና በማሳየት በኩል ፋይዳው ላቅ ያለ ነው፡፡

እኔም መረጃ የሰበሰብኩት የተሟላ የፎክሎር መረጃ ሊያስገኙ የሚችሉትን የመቅረጫ መሳሪዎች፣ መቅረጸ-ድምፅ፣ ፎቶ ካሜራ እና መቅረጸ-ምስል በመጠቀምና ማስታወሻም በመውሰድ ነው። ቀረጻውን ያከናወኑልኝም በዞኑ የተለያዩ መስሪያ ቤቶች (በዞንና በወረዳ ማስታወቂያ ጽ/ቤቶች) የሚሰሩ የቪዲዮ ካሜራ ባለሙያዎች ሲሆኑ፣ እነሱን ለማግኘት ባልቻልኩበት ወቅት (በራሳቸው የቢሮ ስራዎች በተጠመዱበት ወቅት) ደግሞ ቀረጻውን እራሴ አከናውኛለሁ፡፡ በዚህ ወቅት እኔ በተወሰነ ክዋኔ ቀረጻ ላይ ስሆን በሌላ አካባቢ የሚከናወንና ማስታወሻ በመውሰድ ሊያዝ የሚችል የድርጊት መረጃ ሊያመልጠኝ መቻሉ የሚታወቅ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህንን መረጃ የቀረጻ ባለሙያ ባገኘሁበት በሌላ ተመሳሳይ ሥነ-ሥርዓት ክዋኔ ወቅት መረጃ በመሰብሰብ አሟልቸዋለሁ፡፡

ሌላው መረጃ ለመሰብሰብ የተጠቀምኩበት ዘዴ ማስታወሻ መያዝ ነው፤ ምክንያቱም ፎቶና ቀረጻ በጽሑፍ ለሚሰበሰብ መረጃ አጋዥ ቢሆኑም፣ በማስታወሻ የሚያዝ መረጃን ግን አይተኩም፡፡ ለዚህ ነው Dawson(2002:107) የመስክ ማስታወሻ መሰረታዊ የመረጃ መሰብሰቢያ መንገድ ነው ያሉት፡፡ ስለዚህ በተለይ ቀረጻው በሌሎች ባለሙያዎች ሲከናወን እኔም ጎን ለጎን ማስታወሻ ይዣለሁ፤ ቀረጻውን እራሴ በማከናውንበት ወቅት ደግሞ ከቀረጻ በኋላ ማስታወሻ ወስጃለሁ፡፡ ይህንን መረጃም በሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ለሰበሰብኩት መረጃ ማጠናከሪያ አድርጌዋለሁ

### 3.7 የመስክ ጉዞ

ለዚህ ጥናት ቅድመ ሁኔታዎችን ለማመቻቸትና መረጃ ለመሰብሰብ ወደ ጥናት ቦታው የተጓዝኩት አራት ጊዜ ነው፡፡ የመጀመሪያው ጉዞ በሚያዝያ ዘጠኝ ተከናውኖ እስከ ሰኔ አምስት 2004 ዓ.ም ለሃምሳ ስድስት ቀናት በመስክ ቆይታ የተደረገበት ነው፡፡ በዚህ ጉዞ መጀመሪያ ከትምህርት ክፍሉ የተጻፈልኝን የትብብር ደብዳቤ በመያዝ ወደ ዋግ ኽምራ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት በመሄድ የጥናቴን አላማ ለዋና አስተዳዳሪው ካስረዳሁ በኋላ፣ የመስክ መኪና ያላቸው መምሪያዎች ትብብር እንዲያደርጉልኝ ለዞን መምሪያዎች ደብዳቤ አጻፍኩ፡፡ ቅድመ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት እንድችል የተጻፈልኝን የትብብር ደብዳቤ ይዤ ወደ ስድስቱም ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤቶች አመራሁ፡፡ ከሥነ-ሥርዓቶቹ ተዋናዮች ውጭ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮችን እንዲጠቁሙኝ ጠየቅኋቸው፡፡ እነሱም የየወረዳዎቹ ባህልና ቱሪዝም ባለሙያዎች አስፈላጊውን ትብብር እንዲያደርጉልኝ ገለጹላቸው፡፡ እነዚህ ባለሙያዎችም አስፈላጊውን እገዛ አደረጉልኝ፡፡

በዚሁ የመጀመሪያ ጉዞየ አንድ የወሊድ፣ ስድስት የሰርግ፣ አንድ የቀብርና አንድ የአጎበር ሥነ-ሥርዓቶችን በመመልከትና በመቅረጽ መረጃ ሰበሰብኩ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቁልፍና ቁልፍ ላልሆኑ የመረጃ አቀባዮችም ቃለ-መጠይቅ በማድረግ መረጃ አግኝቻለሁ፡፡

ሁለተኛውን የመስክ ጉዞ ያደረግሁት ደግሞ በታህሳስ ሃያ አምስት ሲሆን እስከ ጥር ሃያ ዘጠኝ 2005 ለሰላሳ አራት ቀናት በመስክ ቆይቻለሁ፡፡ በዚህ ጊዜም አራት የሠርግሥነ-ሥርዓቶችን ለመመልከት፣ ለመቅረጽና ቃለ መጠይቅም ለማድረግ ችያለሁ፡፡ ሶስተኛው የመስክ ጉዞ ደግሞ በሁለቱ ጉዞዎች የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች ትራንስክራይብ ካደረግሁ፣

የወሊድ፣ የጋብቻና የሞት በማለት በይዘታቸው ካደራጀሁ፣ በአገውኛ (በኽምጣኛ) የተሰበሰቡትን ካስተረጎምኩና ከተነተንሁ በኋላ የተካሄደ ነው፡፡ ይህም በግንቦት ሶስት 2005 በመንቀሳቀስ እስከ ሰኔ አምስት ለአንድ ወር አካባቢ በመስክ ቆይታ ያደረግሁበት ነው፡፡ ይህ ጉዞ የተደረገው ከደረጃ ማበልጸጊያ በፊት በሰበሰብኳቸው በአብዛኛው የመረጃ ክፍተትን ለመሙላት ነው፡፡ ስለሆነም ክፍተት ያለባቸውን መረጃዎች በቃለ መጠይቅ ያሟላሁበትና አንድ የለቅሶ (የአጎበር) ሥነ-ሥርዓት ምልከታና ቀረጻ ያደረግሁበት የመስክ ጉዞ ነው። አራተኛው ጉዞ ደግሞ ከጥናቴ ደረጃ ማበልጸጊያ በኋላ ከየካቲት ሃያ ሁለት እስከ ሚያዝያ ሰላሳ 2006 ዓ.ም ለሁለት ወር ከሳምንት ቆይታ ያደረግሁበት ነው፡፡ በዚህ የመስክ ቆይታም አራት የወሊድና ሶስት የሞት ሥነ-ሥርዓቶችን ምልከታ አድርጌያለሁ፤ የግልና የቡድን ቃለ መጠይቅ፣ ቡድን ተኮር ውይይትና በዞን ደረጃ የውይይት መድረክ የተካሄደበት ነው፡፡ በጠቅላላው የመስክ ቆይታ ያደረግሁት ከስድስት ወራት በላይ ነው፡፡

## 3.8. የመስክ ገጠመኝ

የመስክ ገጠመኝን አዎንታዊና አሉታዊ በማለት በሁለት ከፍየ እንደሚከተለው እገልጸዋለሁ፤ ምክንያቱም ምንም እንኳ የጥናት ቦታው የትውልድ ቦታየ ቢሆንም ችግሮችም አልጠፉም፤ ምክንያቱም Gottlieb(2006:60) እንደገለጹት አንድ አጥኚ የጥናት አካባቢው ሰው መሆኑ የመስክ ስራው ያለ ምንም ችግር ይከናወናል ማለት አይደለም፡፡

### አዎንታዊ ገጠመኝ

ለዚህ ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ወደ መስክ በወጣሁበት ወቅት የመጀመሪያው አዎንታዊ ገጠመኝ ከስድስቱም ወረዳ ለመጡ የውይይት መድረክ ተሳታፊዎች የሚሆን ገንዘብ ከዋግ ኽምራ ብሄረሰብ አስተዳደር ዞን ለማግኘት መቻሌ ነው፡፡ ሌላው ከስድስቱም ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤቶች የመስክ መኪና ትብብር ማግኜት መቻሌ ነው፡፡ ይህም ከሰቆጣ ከተማ ወደ ወረዳ ከተማዎችና ምልከታ ወደማደርግባቸውና መረጃ ወደምሰበስብበባቸው ቀበሌዎች ለመጓዝ ያስቻለ የመስክ መኪና ማግኘቴ ነው፤ ምክንያቱም የህዝብ ማመላለሻ መኪናዎች በየጎጡ ስለማይደርሱና መረጃው አለ በተባለበት ወቅት እንደ ልብ ስለማይገኙ፣ የግድ ከመንግሥት መስሪያ ቤቶች የመስክ መኪና ትብብር መጠየቅና ማስፈቅድ በማስፈለጉ ነው፡፡ እነዚህ የመስክ መኪናዎች የሚገኙት ደግሞ በዞኑና በወረዳው የሴክተር መሥሪያ

ቤቶች ነው፡፡ ስለዚህ የእነዚህን መሥሪያ ቤቶች ኃላፊዎች ትብብር በምጠይቅበት ወቅት የጥናቱን ዓላማ በመረዳታቸው፣ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካላጋጠማቸው በስተቀር አብዛኛዎቹ የመስክ መኪና አልነፈጉኝም ነበር፤ ድጋፋቸውን ባይለግሱኝ ኖሮ ከመኪና መስመር ውጭ ወደሚገኙ ቀበሌዎች በእግር ተጉዤ ለጥናቱ የሚያስፈልገውን መረጃ ለመሰብሰብ ባልቻልኩ ነበር፡፡

ሌላው አዎንታዊ የመስክ ገጠመኝ ለአካባቢውና ለማህበረሰቡ ባህል አዲስ አለ መሆኔ ነው፡፡ ምንም እንኳ በሚያውቁት አካባቢ ማህበረሰብ ላይ ጥናትና ምርምር ማድረግ ምንም አይነት ችግር አያጋጥምም ለማለት ባያስደፍርም፣ ለማጠናበት ማህበረሰብ ባህል አዲስ አለመሆኔ፣ በደስታውና በሀዘኑ ከማኅበረሰቡ ጋር ተመሳስየ በመገኘት መረጃየን ለመሰብሰብ አስችሎኛል፡፡ ወደ ገጠር ቀበሌዎች በምጓዝበትም ወቅት የየወረዳው የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ባለሙያዎች፣ የቀበሌዎቹ ሊቃነመናብርትና ስራ አስኪያጆች አላማየን ለመረጃ አቀባዮች በማስረዳት በኩል ትብብራቸውን ለግሰውኛል፤ በእግር መጓዝ በሚያስፈልገኝ ወቅትም ራሳቸው አብረው በመጓዝ ካልሆነም መንገዱን የሚያውቅ ሰው በመስጠት መንገድ በመምራትና ማረፊያ ቤት በመስጠት ተባብረውኛል፡፡

በከፊል በአዎንታዊ ገጠመኝ የምገልጸው ቀደም ሲል በዞኑ የባህል መሥሪያ ቤት መስራቴ ነው፡፡ ይህም ምንም እንኳ እንደተማሪ ሳይሆን እንደ የመንግስት አካል እየተቆጠርኩ በመረጃ ሰጭዎች ላይ ተጽእኖ ቢፈጥርብኝም፣ የመስክ መኪና፣ የቪዲዮ ካሜራ ባለሙያዎችና የመረጃ አቀባዮች ትብብር እንዳገኝ ግን ምቹ ሁኔታ ፈጥሮልኛል፡፡

ሌላው አዎንታዊ ገጠመኝ የዘመድ የሰርግና ለቅሶ ሥነ-ሥርዓት ለማግኘት መቻሌ ነው፡፡ ይህም አንዳንዶቹ ሥነ-ሥርዓቶቹን እንድቀርጽ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ሲቀሩ፣ እነዚህ ግን ምንም እንኳ ባንዳንድ ሰዎች ተቃውሞ ቢደርስባቸውም እንድቀርጽ ፈቅደውልኛል፡፡ ሌላው ለምልከታና ለቀረጻ በምሄድባቸው በአብዛኛዎቹ ሥነ-ሥርዓቶች ሁሉ የጥናቴን አላማ ለማስረዳት የሚችሉ የሰቆጣ ከተማ ሰዎች ማግኘቴ ነው፡፡ እነዚህም ለደጋሾቹ የቅርብ ዘመዶች ስለነበሩ ማሳመን የሚችሉና ተቀባይነት ያላቸው ሰዎች ነበሩ፡፡

## አሉታዊ ገጠመኝ

ምንም እንኳ ቀደም ሲል የተገለጹት አዎንታዊ ገጠመኞች ቢኖሩም አሉታዊም አልጠፉም፤ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡፡ ከአሉታዊ ገጠመኞቹ መካከል በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሰው አንዳንድ ሥነ-ሥርዓቶች የሚከወኑባቸው የገጠር ቀበሌዎች ወጣ ገባ፣ በጣም ሞቃታማ፣ ርቀት ያላቸውና የመኪና መስመር ያልገባላቸው መሆናቸው ነው፡፡ ይህንን መንገድም በመስክ መኪና መጓዝ ስለማይቻል በእግር መጓዝ ይጠይቅ ነበር፡፡ መንገዱ ከርቀቱ በተጨማሪ ወጣ ገባ በመሆኑ ለእኔ ብቻ ሳይሆን፣ ለካሜራ ባለሙያዎችም በጣም አስቸጋሪ ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ በድካም ምክንያት በሚቀጥሉት ቀናት ወደ መስክ ለመጓዝ አልቻልኩም ነበር፡፡ ቢሆንም የመስክ ቆይታየን በማራዘም ለጥናቴ አስፈላጊ የሆነውን መረጃ ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

ሁለተኛው ደግሞ ምንም እንኳ አብዛኛዎቹ የዞንም ሆነ የወረዳ አስተዳድር አካላት የመስክ መኪና ለመተባበር ፈቃደኛ ቢሆኑም መረጃ ለመሰብሰብ ወደምሄድባቸው ቦታዎች የሚገቡ መኪናዎች ዓይነት የተወሰኑ መሆናቸው ግን ሥነ-ሥርዓቶቹ በሚከወኑበትና በፈለግሁት ጊዜ ለማግኘት አልቻልኩም፤ ሊተባበሩኝ እንደሚችሉ ፈቃደኝነታቸውን ከገለጹልኝ በኋላ ድንገተኛ ወደ መስክ የሚያስወጣቸው ስራ ማጋጠም ሌላው ችግር ነበር፡፡ ምክንያቱም ቅድሚያ የሚሰጡት ለመንግሥት ስራ ነውና፣ ያንን በመተው ለእኔ ሊሰጡኝ ባለመቻላቸው የመስክ ጉዞየ የተደናቀፈበት ወቅት ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ምልከታ ላደርግበት የነበረውን ሥነ-ሥርዓት በመተው ሌላ ሥነ-ሥርዓት በመመልከት መረጃውን ለማግኘት ችያለሁ፡፡ ሶስተኛው ለመረጃ አሰባሰብ አስቸጋሪ የነበረው በገጠር ቀበሌዎች የመብራት አገልግሎት አለመኖር ነው፡፡ አብዛኛዎቹ የሠርግ ሂደት ክዋኔዎች የሚከወኑት በሙሽራዋ ዳስ ውስጥ የሙሽራው ወገን ከገባ በኋላ ነው፡፡ ይህም በአብዛኛው ከምሽቱ ከሶስትና ከአራት ሰዓት በኋላ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የሠርግ ሥነ-ሥርዓቶቹን አንዳንድ ክዋኔዎች ለመቅረጽና ፎቶ ለማንሳት አልቻልኩም፡፡ በዚህም ምክንያት በተለይም በሴት ዳስ ውስጥ የሚከናወነውን የጋብቻ ውል (የሰማንያ አፈጻጸም) መረጃ የሰበሰብኩትና የስርዓቱን ሂደት ለመረዳትና ለመግለጽ የቻልኩት በምልከታና ማስታወሻ በመያዝ ነው፡፡

አራተኛው አስቸጋሪ ገጠመኝ ከቀረጻ ጋር ተያይዞ የነበረው የማህበረሰቡ የግንዛቤ ችግር ነው፡፡ ምንም እንኳ ለምልከታና ለቀረጻ በሄድኩባቸው በአብዛኛዎቹ ቦታዎች ስለ ቀረጻ

አስፈላጊነት ግንዛቤ ያላቸው አንዳንድ ሰዎች ቢያጋጥሙኝም፣ አብዛኛው ሰው ግን ጥሩ አመለካከት አልነበረውም፤ በዚህም ምክንያት በተለይ በሃዘን የቀብርንና የአኅበር ሂደትን ለመቅረጽና ፎቶ ለማንሳት በጣም ተቸግሬያለሁ፤ ፈቃደኝነታቸውን ስጠይቅም አሉታዊ መልሳቸው «ደስታ እንጂ እንዴት ሀዘን ይቀረጻል፡፡» የሚል ነው፡፡ በዚህና በሌሎች ምክንያቶች ለመቅረጽና ፎቶ ለማንሳት ፈቃድ ያጣሁበትን ክዋኔ በምልከታና ማስታወሻ በመያዝ መረጃ ሰብስቤያለሁ፡፡ አንድ የአኅበር ለቅሶ ክዋኔ ግን የዘመድ በመሆኑና ከሰቆጣ ከተማ የሄዱ የሥነ-ሥርዓቱ ተሳታፊዎች ሀዘንተኞቹን በማግባባታቸውና በማሳመናቸው ለመቅረጽ ችያለሁ፡፡

አንዳንድ የሠርግ ሥነ-ሥርዓቶችንም ቀረጻ እንዳደርግ አልተፈቀደልኝም፤ ምክንያቱም ምንም እንኳ መረጃውን የምፈልገው ለጥናት መሆኑን በየቀበሌ ሊቃነመናብርት ሳይቀር ለማስረዳት ቢሞክርም፣ አንዳንድ የመረጃ አቀባዮች ግን ለሰርጉ ዳስ እና እንጀራ ማስቀመጫ የቆረጡትን ዛፍና የተጋቢዎቹን እድሜ ለመቆጣጠር ከመንግሥት የተላክሁ እየመሰላቸው መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አልነበሩም፤ ይሁን እንጂ ስለጥናቴ ግንዛቤ ባላቸው ሰዎች አግባቢነት መረጃውን ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡ አምስተኛው አሉታዊ የመስክ ገጠመኝ የወሊድ ሥነ-ሥርዓትን የሚመለከት ነው፡፡ እንደሚታወቀው ባሁኑ ጊዜ እናቶች በጤና ተቋማት መውለድ እንደሚገባቸው እየተገለጸ ነው፡፡ ይሁን እንጂ መረጃ ለመሰብሰብ በሄድኩበት አካባቢ በቤት ውስጥ የሚከናወን የወሊድ ሥነ-ሥርዓት አልታጣም፡፡ ነገር ግን የመውለጃ ቀናቸው የተቃረቡ ሴቶችን በመከታተል የሚገምቱትን የመውለጃ ቀን እንዲነግሩኝ ስጠይቃቸው አርቀው በመናገር በወሊድ ስርዓቱ እንድገኝና መረጃ እንድሰብስብ አልሆነም፡፡ ለዚህ ነው የወሊድ ሥነ-ሥርዓት ምልከታየ አምስት ብቻ የሆነው፡፡ ይህንንም እንድመለከት እንጂ እንድቀርጽም ሆነ ፎቶ እንዳነሳ አልተፈቀደልኝም፤ ምክንያቱም የቀረጻውም ሆነ የፎቶው መረጃ በጤና ተቋም ያልወለዱትን እና ቤተሰባቸውን ችግር ላይ ይጥላል በሚል ስጋት ነው፡፡ እኔም መረጃ አቀባዮች ችግር ያደርስብናል ያሉትን መረጃ በማስገደድ መቀበል ስለማይገባኝ መረጃውን በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ አሟልቸዋለሁ፡፡

ስድስተኛው አሉታዊ የመስክ ገጠመኝ ለሙሽራዋ ከወንድ በሚሄድላት አልባሳትና ጌጣጌጥ ከማጋጌጧ አስቀድሞ ሙሽራዋን ለመመልከት ፈቃድ አለማግኘቴ ነው፡፡ ይህም በሁለት

ምክንያቶች ነው፤ አንደኛው ያለ እድሜና ያለ ምርመራ ጋብቻን የምቆጣጠር መስሏቸው ሲሆን፣ ሌላው ምክንያት ደግሞ ሙሽራዋ ከባሏ ጋር ወደ ዳስ ከመግባቷ በፊት ሌላ ሰው ሊያያት አይችልም በሚል ልማድ ምክንያት ነው፤ ይህ የሚከናወነው ደግሞ ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው በጨለማ በመሆኑ መረጃውን በምልከታ ከማግኘት ውጭ ፎቶ ለማንሳትም ሆነ ለመቅረጽ አላስቻለኝም፡፡ በዚህ ምክንያት ከአንድ ሠርግ በስተቀር፣ ሙሽራዋ በእናት ወገን ታዝላ ስትወጣ ለመቅረጽ ወይም ፎቶ ለማንሳት አልቻልኩም፡፡ ይህን ክፍተትም ከወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ /ቤቶች ምስሎችን በመውሰድ አሟልቻለሁ፡፡

ሰባተኛው አሉታዊ ገጠመኝ ደግሞ አንዳንድ መረጃ አቀባዮች ትክክለኛ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆናቸው ነው፡፡ ይኸውም ለአንዳንድ ድርጊቶች መከወን ምክንያቱን እንዲገልጹልኝ ስጠይቃቸው፣ በዘመኑ ከሚሰጣቸው የስልጠና ይዘት ጋር የሚጋጭ መስሎ ከታያቸው ምክንያቱን ቢያውቁትም፣ ‹‹ከአባቶቻችን የወረስነው ባህል ስለሆነ ነው፡፡›› የሚል ድፍን ያለ መልስ ሰጥተውኛል፡፡ ለአብነት ያህል ሙሽራዎቹ ወንዝ ሲሻገሩ ለምን ጫጩት ይታረዳል? ደም እንዲፈስ ይደረጋል? ሙሽራው ወደ ሙሽራዋ ዳስ ሲገባ ለምን በአመድ ይረጫል? ወዘተ. ለመሳሰሉት ጥያቄዎች የሰጡኝ መልስ ‹‹ከአባቶቻችን የወረስነው ባህል ነው፡፡›› የሚል ነው፡፡

### 3.9. የጥናቱ አከዋወን ሂደት

ጥናቱን ሳከናውን የተከተልኳቸው ቅደም ተከተላዊ ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡፡ የመጀመሪያው የቅድመ መረጃ ትንተና ተግባራትን ማከናወን ነው፡፡ በተሰበሰበው መረጃ ላይ ትንተና ከማከናወኔ አስቀድሞ የሚከተሉትን የቅድመ መረጃ ትንተና ተግባራት አከናውኛለሁ፡፡ የመጀመሪያው የምላሽ ማጣራት ስራ ማከናወን ነው፡፡ ይህም የመረጃ አቀባዮቹ ለጠየቅኳቸው ጥያቄዎች የሰጡኝ ምላሽ መልስ ተገቢ መሆን አለ መሆኑን ማጣራት ነው፡፡ መረጃ አቀባዮች ለጠየቅኋቸው ጥያቄዎች የሰጡኝ መልስ ትክክለኛ መሆን አለመሆኑን ለመረዳትና፣ ክፍተት የሚታይበትን ለመለየት አላዳገተኝም፡፡ ስለዚህ በየመስክ ጉዞየ የሰበሰብኳቸው መረጃዎች ያለባቸውን ክፍተትና ስህተት በመልቀም፣ በሚቀጥሉት የመስክ ጉዞዎች እንደገና በመጠየቅ ማስተካከያ ተቀብያለሁ፡፡

ሌላው መረጃን ኮድ ማድረግ ነው፡፡ ከመስክ የተሰበሰበን ጥሬ መረጃ ትርጉም በሚሰጥ መልክ ማደራጀትና መረጃውን ለትንተና ማዘጋጀት አይቀሬ ተግባር ነው፤ በመሆኑም ቀደም ሲል እንደተገለጸው መረጃ ከመስክ የሰበሰብኩት በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ፣ ማስታወሻ በመውሰድ፣ በቴፕ በመቅረጽ፣ የመብራት አገልግሎት ባላቸውና የመረጃ አቀባዮቹ ፈቃደኛ በሆኑበት ሥነ-ሥርዓት ደግሞ በቪዲዮ በመቅረጽና ፎቶ በማንሳት ነው፡፡ በነዚህ መሳሪያዎች የተሰበሰበው መረጃ ከመቀናበሩ አስቀድሞ ትርንስክራይብ መደረግ ይኖርበታል፤ በቪዲዮ የተቀረጸውን መረጃ ለመሰብሰብ ደግሞ የቪዲዩ ካሴቱን ወደ ሲዲ ማስገልበጥ ያስፈልጋልና ወደ ሲዲ አስገልብጫለሁ፡፡ በቴፕ የተቀረጸውን መረጃም ትርንስክራይብ አድርጌያለሁ፡፡ ይህም በየመስክ ጉዞየ አራት ጊዜ ተከናውኗል፡፡ ያመለጠን መረጃ ለማግኘትና ለመልቀም ሲባልም ትራንስክራይብ የማድረጉ ስራ የተከናወነው በተደጋጋሚ ነው፡፡

በኽምጣኛ ቋንቋ የተሰበሰበውን መረጃም ወደ አማርኛ አስተርጉሜያለሁ፡፡ በመቅረጫ መሳሪያዎች የተሰበሰበውን መረጃም በምልከታና በማስታወሻ ከሰበሰብኩት መረጃ ጋር አቀናብሬያለሁ፡፡

ቀደም ሲል እንደ ገለጽኩት በተለያዩ ዘዴዎች የሰበሰብኩትን መረጃ ካደራጀሁ በኋላ፣ ችግርና ክፍተት የሚታይባቸውን እንደገና የመረጃ ማጣራትና ማሟላት ስራ አከናውኛለሁ፤ ይህም በሁለት መንገድ የተከናወነ ነው፤ የመጀመሪያው መረጃውን የሰጡኝን ሰዎች በማነጋገር ሲሆን እነሱን ማግኘት ባልቻልኩበት ወቅት ደግሞ ጉዳዩን ያውቃሉ የሚባሉ ሌሎች ሰዎችን በመጠየቅ ነው፡፡ ወደ መረጃ ትንተና ያመራሁትም ይህን ካከናወንኩና ከሞላ ጎደል በቂ መረጃ ማግኘቴን ካረጋገጥኩ በኋላ ነው፡፡

በመጨረሻም የደረጃ ማበልጸጊያ ካደረግሁ በኋላ በዞን ደረጃ የውይይት መድረክ እንዲካሄድ አድርጌያለሁ፡፡ ከዚህ ውይይት ያገኘኋቸውን ጠቃሚ መረጃዎች በማካተትም ይህንን የጥናት ጽሁፍ አጠናቅሬያለሁ፡፡

### 3.10. የጥናትና ምርምር ስነ-ምግባር

አንድ ጥናትና ምርምር የሚያደርግ ሰው ለጥናቱ የሚያገለግሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ወደ መስክ በሚወጣበት ወቅት መረጃ የመሰብሰብ ሂደቱ፣ ትንታኔውና የጥናት ውጤቱ

ስኬታማ ይሆን ዘንድ ትኩረት ሊሰጣቸውና ሊያከብራቸው የሚገቡ የስነ-ምግባር ዝግጅቶች አሉ። እነዚህም የጥናትና ምርምር ስነ-ምግባር ይባላሉ፡፡ Gomm(2008:365) እንደገለጹት፣ የጥናትና ምርምር ስነ-ምግባር የሚያመለክተው የተመራማሪውን መልካም ስነ-ምግባር መላበስና መረጃ የሚቀበልባቸውን አካላት አደጋ ላይ እንዳይወድቁ መጠበቅን ነው፤ Seale(2005:116) ደግሞ ስነ-ምግባራዊ ጉዳዮች ከጥናቱ መጀመሪያ ጀምሮ የጥናቱ ሪፖርት እስከሚጻፍ ድረስ ስራ ላይ የሚውል መሆኑን አስመልክተው እንዲህ ብለዋል፤ ስነ ምግባራዊ ጉዳዮች የጥናት ጥያቄዎችን ከማዘጋጀት ጀምሮ ንሙና ስናካሂድ፣ መረጃ አቀባዮችን ስናገኝ፣ መረጃ ስንሰበስብ፣ ስንተነትንና ስንጽፍ ጠቀሜታ ያላቸው ናቸው፡፡ Jansen(1983:53) ደግሞ የምርምር ስነ-ምግባር የሚመለከተው መረጃ አቀባዩንና ተመራማሪውን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም እንደሆነ ይገልጻሉ። ሌሎች የተባሉትም ወደፊት ጥናትና ምርምር የሚያደርጉ አካላት፣ የጥናቱ ውጤት ተደራሲዎችና የትምህርቱ መስክ ናቸው።

በመሆኑም የጥናትና ምርምር ስነ-ምግባር አጥኚው መረጃውን ከመሰብሰቡ በፊት፣ በሂደትና በኋላ በሚከናወኑ የጥናትና ምርምር ደረጃዎችና ሂደቶች የሚቀጥል እንጂ ለአንድ አፍታ ስራ ላይ ውሎ የሚቋረጥ አይደለም(Creswell,2009:92-93)። McLeod and Rachel Thomson(2010:74) ደግሞ ከጥናትና ምርምር ስነ-ምግባር አንዱ የመረጃ አቀባዮችን መረጃ የመስጠት ፈቃደኝነት ማረጋገጫ ስምምነት ማግኘት እንደ ሆነ ሲገልጹ፣ አንድ ከመስክ መረጃ በመሰብሰብ ጥናትና ምርምር የሚያደርግ የተጠኚዎቹን መረጃ የመስጠት ፈቃደኝነት ማረጋገጫ ለማግኘት፣ መረጃ አቀባዮች ጉዳዩን እንዲያውቁትና ፈቃደኝነታቸውን እንዲገልጹለት ግንዛቤ የመፍጠር ስራ መስራት አለበት ብለዋል። ሌላው ውድ ጊዜያቸውን መስዋእት አድርገው መረጃ ለሚሰጡ የመረጃ አቀባዮች ማበረታቻ መስጠት ነው፡፡ የዚህን ስጦታ አስፈላጊነት አስመልክተው Pink(2007:56) ሲገልጹ አንድ ነገር መልሶ መስጠት የሚያመለክተው ከመስክ መረጃ ያሰባሰበው ሰው መረጃ ወስዶ፤ ከዚህ በኋላ መረጃ ላገኘባቸው/ላገኘችባቸው አካላት አንድ ነገር ስጦታ መስጠት ነው፡፡

እኔም መረጃ ለመሰብሰብ ወደ መስክ በሄድኩበት ወቅት፣ የመረጃ አሰባሰብ ሂደቴ የተሳካ ይሆን ዘንድ የጥናትና ምርምር ስነ-ምግባርን አክብሬያለሁ። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በመጀመሪያ ከዩኒቨርሲቲው የተጻፈልኝን የትብብር ደባዳቤ ለዋግ ኽምራ አስተዳደር ዞንና፣

ለስድስቱም ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤቶች እና መረጃ ለምሰበስብባቸው ልዩ ስፍራዎች የቀበሌ አመራሮች በማሳየትና የጥናቴን አላማ በማስረዳትና ግልጽ በማድረግ የመረጃ አሰባሰብ ሂደቴ እንዲመቻች አድርጌያለሁ። ለተጠኚዎቹም መረጃ ከመስጠታቸው አስቀድሞ የጥናቴን አላማ አሳውቂያቸዋለሁ፡፡ መረጃ አቀባዮቼ የሚሰጡኝ መረጃ ለምን እንደሚውል በማስረዳትም መረጃ ለመስጠት ፈቃደኝነታቸውን በቃል እንዲያረጋግጡልኝ አድርጌያለሁ። የመረጃ መሰብሰብ ሂደቱን በግልጽ እንዲያውቁት ለማድረግ ያስችል ዘንድም መረጃ የምሰበስበው በመቅረጸ-ምስልና ድምፅ እንዲሁም በፎቶ ካሜራ በመታገዝም እንደሆነ አሳውቂያቸዋለሁ፤ የተቀበልኩት መረጃም በእርግጠኝነት መረጃ አቀባዮች ያሉትን ብቻ መሆኑን እንዲያረጋግጡ አልፎ አልፎ በቴፕ የተቀረጸውን መረጃ አቀባዮቼ እንዲያዳምጡት አድርጌያለሁ፡፡ በተጨማሪም መረጃ በምሰበስብበት ወቅት በሰላምታ ልውውጥ፣ በሃዘንና በሠርግ ሥነ-ሥርዓቶች ወቅት በአለባበስ የአካባቢውን ወግና ባህል በመጠበቅ፤ ማህበረሰቡ የሚያስደስተውን አከናውኛለሁ፤ ከሚያስከፋው ተቆጥቤያለሁ።

# ምዕራፍ አራት

## የዋግ ኽምራ ህብረተሰብ የወሊድ ሥነ-ሥርዓት

የወሊድ ሥነ-ሥርዓትን ገለጻ ቅድመ-ወሊድ፣ ወሊድና ድህረ-ወሊድ በማለት በሶስት ከፍየ ተመልክቼዋለሁ፡፡ በቅድመ-ወሊድ የሚገለጸው ለነፍሰ-ጡር ሴት የሚደረግ እንክብካቤ እና ጥንቃቄ፣ የምግብና የመጠጥ ዝግጅት ሲሆን፣ ወሊድ ደግሞ አንዲት ነፍሰ-ጡር ሴት ምጥ ከተያዘችበት ጊዜ ጀምሮ እስከምትገላገል ድረስ ያለውን ሂደትና ክዋኔ ይመለከታል፡፡ ድህረ ወሊድ ደግሞ ነፍሰ-ጡሯ ከተገላገለች በኋላ የሚከናወኑ ድርጊቶች የሚገለጹበት ነው፡፡ እነዚህን ሶስት ክፍሎች ቀጥሎ አንድ ባንድ እገልጻለሁ፡፡

### 4.1 ቅድመ ወሊድ

በዚህ ክፍል የሚገለጹት ክዋኔዎች አንዲት ሴት ነፍሰ-ጡር መሆኗ ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ በማህበረሰቡ የሚደረግላት እንክብካቤና አክብሮት፣ በቅድሚያ የሚዘጋጁ ነገሮች፣ ነፍሰ-ጡር ሴት ከዘወትራዊ እንቅስቃሴዋና አመጋገቧ በተለየ ሁኔታ የሚታይባት ነገርና ነፍሰ-ጡሯ ሴት የመውለጃ ቀኗን አውቃ የምታደርጋቸው ቅድመ-ዝግጅቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ክዋኔዎች በሚገለጹበት ወቅት አውዱም ተካቷል፡፡

#### 4.1.1 ለነፍሰ-ጡር ሴት የሚደረግ እንክብካቤ እና ጥንቃቄ

ከቅድመ ወሊድ ክዋኔዎች መካከል አንዱ ማህበረሰቡ ለነፍሰ ጡር ሴት የሚያደርገው እንክብካቤ ወይም አክብሮት ነው፡፡ አንዲት ሴት ነፍሰ-ጡር ከመሆኗ በፊት በማንኛውም ግላዊና ቡድናዊ ስራ ትሳተፋለች፤ ነፍሰ-ጡር መሆኗ ከታወቀ ጀምሮ ግን በአረም፣ በአጨዳ ወዘተ. በመሳሰሉት የህብረት ስራዎች በአካባቢው አገላለጽ በወበራ፣ እንድትሳተፍ አይደረግም፡፡ የሴቶችን የስራ እገዛ በሚጠይቁ በጎረቤት የሰርግ፣ የክርስትና፣ የዝክር ወዘተ. ስራዎች በሚኖሩበት ወቅትም አቅም ካላትና የመውለጃ ጊዜዋ ካልደረሰ፣ ባትሰራም ብቅ ብላ ትታያለች እንጂ እንድትሰራ አይደረግም፡፡ እንዳትሰራ ከምትከለከላቸው መካከል አንዱ እህል መውቀጥ የለባትም የሚለው ነው፡፡ ምክንያቱም ስትወቅጥ የህጻኑ ጭንቅላት ያብጥና በምጥ ጊዜ እናትየዋ እንድትቸገር ያደርጋታል ይባላል፡፡ በመስከረም ተልባ ነቀላም መሳተፍ የለባትም ይባላል፤ ምክንያቱም መሬቱ ሞቃት ስለሆነ በማህጸኗ በኩል

ምች ይመታትና ለአደጋ ትጋለጣለች ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህም አባባል ብቻ ሳይሆን በተጨባጭ ለአደጋ ሲያጋልጥ የሚታይ ነው፡፡ መሬቱ በጣም ስላልመጠጠ ወደ ላይ ስለሚጨስ ነፍሰ-ጡሯ ህይወቷን የምታጣበት አጋጣሚም አለ ይላሉ ወ/ሮ አልማዝ (ቁ.የ.መ.አ.25)፡፡ ስለዚህ ለእሷም ሆነ ለጽንሱ እንክብካቤ የሚደረገው በግሏ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ትብብር ጭምር ነው፤ በተለይም ‹‹ይህን አድርጊ ይህን አታድርጊ ›› የሚሉ ልምድ ያላቸው እናቶች እገዛ ትልቅ ቦታ ይሰጠዋል፡፡

ነፍሰ-ጡር ሴት ማጥባትም የለባትም፤ ወተቱ ለሕፃኑ ጥሩ አይደለም፤ ምክንያቱም የሚጠባው ሕፃን ሆድ ይነፋል፤ በአካባቢው አገላለጽ ይቆዘራል ወይም ተቅማጥ ይይዘውና ይጎዳል በማለት ነው እንደ አንዳንድ መረጃ አቀባዮቹ አገላለጽ ከሆነም (ቁ.የ.መ.አ.1)፡፡ ጽንሱም ይቀጭጫል ወይም ይመነምናል፡፡ ስለዚህ ጡት ለማስጣል ስንዴ ቆሎ በመቁላት የእናትየዋን ጡት ወተት ከላይ በማፍሰስ ‹‹እርም ነው›› ሲባል ይተዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ እሬትም ይቀባል (ቡ.ቃ. 3)፡፡ በዚህ ምክንያት ነፍሰ-ጡር ሴት በአማካይ እስከ ሶስት ወር ድረስ እንድታጠባ ሲደረግ፤ ከዚያ በኋላ ግን ሕፃኑ ለመጥባት ፈልጎ ጡቷን አለቅ ቢልም ታስጥለዋለች፡፡

ነፍሰ-ጡር ሴት እንዳትበላ የምትከለከላቸው የምግብ ዓይነቶችም አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል አንዱ ሰናፍጭ ነው፤ ይህም የሚከለከለው ሶስት ወር እስኪሞላት ነው፡፡ ሰናፍጭ እንዳትበላ የምትከለከለው ጽንሱን አውጥቶ ስለሚጥል፣ ለውርጃ ስለሚዳርግ ነው (ቁ.የ.መ.አ.8)፡፡ ነፍሰ-ጡር ሴት አረቂም አትጠጣም፤ምክንያቱም ጽንሱን ይጎዳዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ የስንዴ፣ የሽንብራ ቆሎ እና ሽንብራ እሸት እንዳትበላ ይደረጋል፤ ምክንያቱም ከወሊድ በኋላ ጭራሞ የሚባል ከባድ የሆድ ቁርጠት ህመም አለና እሱ እንዳያማት ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ነፍሰ-ጡሯ የመውለጃዋ ጊዜ ሲደርስ ደግሞ ድፍድፍና ገንፎ እንዳትበላ ትከለከላለች፤ ምክንያቱም ድፍድፉና ገንፎው ከህጻኑ/ኗ ጭንቅላት ተለጥፎ ይገኛል ተብሎ ስለሚታመን ነው (ቡ.ቃ.3)፡፡

ሌሎች ግን ነፍሰ-ጡር ሴት አንድን ምግብ መብላት ሲያስጠላት ብቻ ነው እንጂ፣ ሁሉን የምግብ አይነቶች ትበላለች፤ ነገር ግን የስንዴ ቆሎና ያልበሰለ ነገር መብላት የለባትም፤ ምክንያቱም ለጽንሱ ጥሩ አይደለም፤ በምጥ ወቅትም ያስቸግራታል፤ የሚል ቃል ሰጥተውኛል፡፡ እነዚህ ሴቶች ነፍሰ-ጡር ሴት እንዳትበላና እንዳትጠጣ የምትከለከላቸውን

የምግብ አይነቶች ሲዘረዝሩም ጠላ፣ አጓት፣ ቅቤ፣ የመሳሰሉት መሆናቸውን ገልጸዋል (ቡ.ቃ.1)፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ፣ ነፍሰ-ጡር ሴት ቃሪያና አገዳ እንዳትበላ ትከለከላለች፤ ምክንያቱም ቃሪያው ጽንሱን እንዳያቃጠለው ሲሆን፣ አገዳው ደግሞ የሚወለደው ልጅ ልጋግ የሚያንጠባጥብ እንዳይሆን ነው ያሉ የመረጃ አቀባዮች አሉ(ቁ.የ.አ.24 እና ቡ.ቃ.1)፡፡

ነፍሰ-ጡር ሴት ከባድ ስራም አትሰራም፤ ለአብነት ያህል እንጨት፣ ድንጋይ፣ ዱቄት አትሸከምም፤ ምክንያቱም ፅንሱንም እሷንም እንዳይጎዳ ነው፡፡ የውሃ እንስራም በጎኗ እንጂ በሆዷ አታወርድም፤ ምክንያቱም በሆዷ ካወረደች የሕፃኑ አፍንጫ ደፍጣጣ ስለሚሆን ነው ይባላል (ቁ.የ.መ.አ.8)፡፡ ጽንሱን ከአደጋ ለመከላከል እንዲቻልም በጎኗ ትተኛለች፤ ጸሀይ ከመታው ድንጋይ ላይም አትቀመጥም፤ ከግቢ ውጭ ሜዳ ወይም ጫካ (በረሃ) ላይ ስትጸዳዳም ጥላ ላይ ነው እንጂ ጸሀይ በመታው ቦታ ላይ አትጸዳዳም፡፡ ምክንያቱም ጸሀይ ከመታው ቦታ ላይ ከተጸዳዳች ጽንሱ እንዲቋረጥ ወይም ለውርጃ እንድትዳረግ ያደርጋታል ተብሎ ስለሚታመን ነው (ቁ.የ.መ.አ.10)፡፡ ነፍሰ-ጡር ሴት እሩቅ መንገድም አትጓዝም፤ ምክንያቱም ትክክለኛ የመውለጃ ቀኗን ባለ ማወቅ ቀኗን አሳስታ መንገድ ላይ እንዳትወልድና ለችግር እንዳትዳረግ በማለት ነው፡፡

### 4.1.2 የምግብና የመጠጥ ዝግጅት

ሌላው የቅድመ ወሊድ ተግባር፣ በወሊድ ጊዜና ከወሊድ በኋላ ለእሷም ሆነ በወሊድ ወቅት ለሚሳተፉት ሴቶች የሚሆን የምግብና የመጠጥ ዝግጅት ማድረግ ነው፡፡ ነፍሰ-ጡር ሴት እንዲዘጋጁ የምታደርጋቸው የምግብ ዓይነቶችም ቅባቱ እስከሚወጣ ድረስ በማድቀቅ የተወቀጠ (የተለጠለጠ) ተልባ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ዘይት፣[28] ለገንፎ የሚሆን ዱቄትም ቀደም ሲል ከስንዴ በተለይም በአካባቢው በንጣቱ ከሚታወቀው ኪንኪና ስንዴ ብቻ፣ አሁን አሁን ደግሞ ገብስም በመቀላቀል ታዘጋጃለች፡፡ መጠኑም ሀብታም ከሆነች በዛ አድርጋ ድሃ ከሆነች ደግሞ እንዳቅሟ በመጠኑ ነው፡፡ ነፍሰ-ጡሯ ሀብታም (ያላት) ከሆነችም የእርድ ፍየል፣ የተነጠረ ቅቤና ማር ታዘጋጃለች፡፡ በመጠጥ በኩል ደግሞ ለኮረፌ የሚሆን ደረቆትና በወፍራሙ የሚጋገር የኮረፌ ቂጣ (አብሽሎ) ታዘጋጃለች፡፡ በዋግ ኽምራ ዞን

[28] ቀደም ሲል በአካባቢው በባህላዊ መንገድ ከሱፍ ወይም ከኑግ የሚዘጋጅ ቅባኑግ እንጂ ዘይት አይታወቅም ነበር ፡፡

ኮረፌ የአራስ ዘወትራዊ መጠጥ ነው፤ምክንያቱም ኮረፌ ያጠነክራታል ተብሎ ስለሚታመን፣ በወፍራሙ የሚጠመቅ ኮረፌ (ድቋ) ስለምትጠምቅ (ስለምትደቆዱቅ) ነው፡፡ በዋግ ኽምራ ነፍሰ-ጡር ሴት ለመውለጃዋ ከማሽላ ወይም ከበቆሎ፣ አሁን አሁን ደግሞ በብዛት ከሌላ ቦታ ወደ አካባቢው ከሚገባው ዳጉሳ የሚዘጋጅ ቀጠን ያለ ባህላዊ የመጠጥ አይነት (ዝልል) አታዘጋጅም፡፡ ምክንያቱም ይህ የመጠጥ ዓይነት ሆዷን ይሸረሽራታል ተብሎ ስለሚታመን ነው (ቁ.የ.መ.አ. 25)፡፡

ከነዚህ የምግብና የመጠጥ ኣይነቶች በተጨማሪም ለመውለጃዋ የሚያስፈልጓትን ሌሎች ነገሮችም ታዘጋጃለች፤ እነዚህም አዲስ ምላጭ(ቤሳ፣ችግሬ)፣ ለእትብቱ ማሰሪያ የሚሆን ከፈትል፣ ከልቃቂት(ከማግ ወይም ከልቅ) የተዘጋጀ ክር፣ እንዲሁም ለሚወለደው ሕጻን መቀበያ ጨርቅ ወዘተ.ናቸው፡፡ የሚዘጋጀው ጨርቅም አዲስ ሳይሆን ውሃ ወይም ወዝ የነካው፣ ነገር ግን ንጹህ የሆነ ነው፡፡ ለንጽህናው ሲባልም ጥሩ ሽታ ባላቸው ወገርት እና ቡክቡካ በሚባሉ ተክሎች ጢስ እንዲታጠን ይደረጋል፡፡

ሕጻኑ እንደ ተወለደ የሚቃመሰው(አፉን የሚያሟሸው) ቀደም ሲል በንጹህ የጸጉር ቅቤ፣ (የላስታ ቅቤ) ሲሆን፣ አሁን አሁን ግን በብቅል ስለሆነ፣ የብቅል ዱቄትም ታዘጋጃለች[29] (ቁ.የ.መ.አ13 እና19)፡፡

## 4.2 ጊዜ ወሊድ[30]

በቅድመ-ወሊድ ለአንዲት ነፍሰ-ጡር ሴት የሚደረግላትን እንክብካቤና ለእሷ እና ለጽንሱ ደህንነት ሲባል እንዳትሰራ የምትከለከላቸውን ስራዎችና እንዳትበላ የሚደረጉ የምግብ ዓይነቶችን ገልጫለሁ፤ቀጥሎ ደግሞ በወሊድ ጊዜ የሚከናወኑ ተግባራትን እገልጻለሁ፡፡

አንዲት ሴት የመውለጃ ቀኗ መቃረቡን ካወቀች ምጡ ሳይጀምራት ጸጉሯን ሹሩባ ትሰራለች፤ ቅቤ ትቀባለች፤ ሀብት ያላት ከሆነችም አናቷ ላይ ብዙ ቅቤ ታስቀምጣለች (ጉብ ታደርጋለች)፡፡ የመውለጃ መደቧንም ታጸዳዳለች፤ ለመኝታዋም ከቆዳ የተዘጋጀውን ምንጣፍ፣ጀንዴ ወይም ነት ታመቻቻለች፤ በቤቷ ውስጥ የሚገኙት ሰዎችም እሳት በማንደድ ቤቱ ሙቀት እንዲኖረው ያደርጋሉ፤ ቡናም ይፈላል፡፡ ምጡ ሊጀምራት ሲልም

[29] የወሊድ ስርዓቱ በህክምና ቦታ ከተከናወነ ግን ማቃመስ ነገር አይኖርም፡፡

[30] በዚህ ክፍል የሚቀርበው በቅድመ-ምጥና በወሊድ ጊዜ የሚከናወን ተግባር ነው፡፡

የቅርብ ቤተሰቦች፣ የልምድ አዋላጅና ጎረቤቶች እንዲጠሩ ይደረጋል፡፡ አስቀድማ ባዘጋጀችው ምንጣፍ ላይ በጉልበቷ በመበርከክ፣ የልምድ አዋላጅዋ በግርጌዋ፣ የቅርብ ዘመድ የሆኑ ሴቶች በህይወት ካለችም እናቷ ደግሞ በራስጌዋ በመሆን የጽንሱን መምጣት ይጠባበቃሉ፡፡

በአቅራቢያዋ እንዲገኙ ወይም ምጥ ወደ ያዛት ሴት ቤት እንዲገቡ የሚፈቀድላቸውም የወለዱ ሴቶች ብቻ ናቸው፡፡ ገና ያልወለደች እና መካን የሆነች ሴት ወደ ቤት እንድትገባም ሆነ ካጠገቧ እንድትደርስ አይፈቀድላትም፤ ምክንያቱም በአካባቢው ያልወለዱ ሴቶች ድፍን ቅሎች ናቸው ተብሎ ይታመናል(ቀ.የ.መ.አ.8)፡፡ ያልወለደች ወይም መካን ሴት ካሁን በፊት ለመውለድ ሲባል የምጥን ጭንቀት ስላላየች፣ አሁንም የጭንቀቱ ተካፋይ ሆና የምጡ ጊዜ እንዲያጥርና ምጥ የተያዘችው ሴት ቶሎ እንድትወልድ ልታደርግ አትችልም ተብሎም ይታመናል፡፡

በምጥ ወቅት ሴቶች መቀነታቸውን፣ ውጭ የሚገኙት ወንዶች ደግሞ ቀበቷቸውን እንዲፈቱ ይደረጋል፡፡ የተቆለፈ ሳጥን(ሳንዱቅ) ካለም እንዲከፈት ይደረጋል፤ ምጥ ሲዘገይ ቀይ ወንድ ዶሮ ነፍሰ-ጡሯን በማዞር ይታረድና በነፍሰ-ጡሯ ጀርባ ላይ ደም እንዲፈስ ይደረጋል፡፡ ባልንም ቀደም ሲል ‹‹ሽምቀቆህን (ከፈትል ጨርቅ የተሰራ ቀበቶ) ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ቀበቶህን አላላ፤ተንቀሳቀስ›› ይባላል፡፡ እሱም እስከሚደክም ድረስ ይሮጣል፡፡ ይህም ጽንሱም ይገላበጥና ምጡ እንዲቀልና ሚስትየዋ ቶሎ እንድትወልድ የሚያደርግ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ አሁን አሁን ደግሞ ማሰሪያ ያለው ጫማም እንዲፈታ ይደረጋል፡፡ ያልተነደለ ድፍን ቅል ከቤት ውስጥ ካለም ከቤት እንዲወጣ ይደረጋል (ቁ.የ.መ.አ.10፣25፣26 እና ቡ.ቃ.3)፡፡ ሴቶቹ ባንድ ቦታ ላይ ዝም ብለው መቀመጥ የለባቸውም፤መንቀሳቀስ ወይም ፍልኽልኽ ማለት አለባቸው፡፡ ስለዚህ በጉልበታቸው ተንበርክከው፣ ‹‹ማርያም ማርያም›› በማለት ድንግል ማርያም ምጥ የያዛትን ሴት በሰላም እንድታገላግላት በጭንቀት ይለምናሉ፤ ይማጸናሉ፡፡ ምክንያቱም ስሟን ስንጠራ ትደርስልናለች፤ በሰላም እንድንገላገል ታደርገናለች ብለው ያምናሉ (ቁ.የ.መ.አ.10)፡፡

ምጡ በጣም በሚዘገይበት ወቅት ደግሞ ምጥ የያዛትን ሴት ከበው በጭንቀት የሚገኙት ሴቶች የተለያዩ ድርጊቶች እንዲከናወኑ ያደርጋሉ፤ ከእነዚህም መካከል ምጥ የያዛትን

ሴት ሊያስደነግጡ የሚችሉና ጽንሱ እንዲወለድ ያደርጋሉ የሚባሉ ድምጾችን ማሰማት አንዱ ነው፡፡ ስለዚህ የብረት ምጣድ በድንጋይ ይደበደባል፤ ጠብመንጃ (መሳሪያ) ይተኮሳል፤ ከሌለ ወይም መተኮስ ክልክል ከሆነም የቆርቆሮ ክዳን ቤት ካለ የዚያ ቤት ጣራ በድንጋይ ይደበደባል፤ ጅራፍ እንዲጮህ ይደረጋል፡፡ የሩፋኤል ጠበል ወይም ድግምት ይረጫል (ቂ.የ.መ.አ.19፣ 24 እና ቡ.ቃ.3)፡፡ ሩፋኤል በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና ከመላእክት መካከል አንዱ ነው፡፡ የሩፋኤል ጸበል መርጨትን አስመልክተው መጋቢ ምስጢር እንዲህ ብለዋል፤

> በምጥ ወቅት መልኩም ይደገማል፤ ጸበሉም ይረጫል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት መላእክት የተለያየ ስልጣን አላቸው፡፡ ሚካኤል የፍጥረታት ሁሉ አማላጅ፣ ቅዱስ ገብርኤል የምስራች ተናጋሪ እንደሆነ ሁሉ መልአኩ ሩፋኤልም በደረጃ ሶስተኛ ይበላል፣ እንስሳትም ሆኑ ሰዎች በምጥ ጊዜ የሚራዳ መሆኑ በመልኩ ተጽፎ ይገኛል፡፡ ሴት ምጥ ሲይዛት ሴቶች የሩፋኤልን ጸበል የሚረጩትም የማህጸን መፍታት ስልጣን የተሰጠው ለሩፋኤል መልአክ ስለሆነ ነው (ቂ.የ.መ.አ.2)፡፡

በመልክአ ሩፋኤል ላይም ተስፋ(1991፣47-48 እና 60-61) ወልደ ነጐድጓድ ዮሐንስ እንደተናገረው ጳግመኛ የወላድን ማኅፀን ሁሉ እንድትፈታ ሥልጣን ተሰጥቶሃል፡፡…በወሊድ ጊዜ የሰውንም የእንስሳትንም ማኅጸን የምትፈታ አንተ ነህ…የሚል ሰፍሮ ይገኛል፡፡

ከዚህም ሌላ የተደቀሰ ተልባ ተሙቆ እንድትጠጣ ይደረጋል፤ እነዚህ ሁሉ ተከናውነው ካልተገላገለችና ምጡ ለረዥም ጊዜ የሚቆይ ከሆነ ግን ወደ ጤና ጣቢያ፣ በጤና ጣቢያ ካልተገላገች ደግሞ ሰቆጣ ከተማ ወደሚገኘው የተፈራ ሃይሉ መታሰቢያ ሆስፒታል ይወስዷታል፡፡

ምንም እንኳ ባሁኑ ጊዜ በወሊድ ምክንያት የሚከሰትን የእናቶች ሞት ለመቀነስ፣ በጤና ተቋማት እንዲወልዱ መንግሥት ጥረት እያደረገ ቢሆንም፣ በዋግ ኽምራ ዞን አሁንም ቢሆን እቤታቸው የሚወልዱ ሴቶች በርካታ ናቸው፡፡ እኔም ወደ ጤና ተቋም ሳይወሰዱ እቤታቸው የወለዱ የሶስት ሴቶችን የወሊድ ስርዓት ተመልክቼ ነበር፡፡ ከእነዚህ መካከል የአንዱን እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡

እለቱ ጥር ሃያ 2004 ነው፡፡ በማግስቱ የሚከናወነን የሠርግ ሥነ-ሥርዓት ከዋዜማው ጀምሮ ለመመልከትና ለመቅረጽ ከሰቆጣ ከተማ ሰላሳ ኪሎ ሜትር ወደ ሰሜን ወጣ ብሎ በሚገኝ ማይ ግንዶ[31] በተባለ ቀበሌ ነበር የተገኘሁት፡፡ በዋዜማው የሠርግ ድግስ ዝግጅት የሙሽራዋ ታላቅ ወንድም ሚስት የሆነችው ወ/ሮ በለጡ አሰፋ መውለጃዋ የተቃረበ፣ ነፍሰ-ጡር ሴት በስራው ለመሳተፍ ሳይሆን፣ ተቀምጣም ቢሆን ተቆርቋሪነቷን ለማሳየት ወደ ሠርግቤቱ መጥታ ነበር፤ መደብ ላይ ተቀምጣም የሚሰራውን ትከታተል ነበር፡፡ እስከ ምሽቱ ሁለት ሰዓት አካባቢ በሰርጉ ዝግጅትና ዘፈን ላይ በተገለጸው መንገድ ተሳታፊ የነበረችው ወይዘሮ በለጡ፣ አመመኝ ብላ ወደ ቤቷ ሄደች፡፡ ከምሽቱ አራት ሰዓት አካባቢ የሙሽራዋ እናት የወ/ሮ በለጡ አማት ሲጠሩ ለወሊድ መሆኑን አወቅሁና እኔም ወደ ወ/ሮ በለጡ ቤት ሄድኩ፡፡

እቤቷ እንደ ደረስንም አማትየዋ ፈጠን ብለው ወደ ቤት ገቡ፣ እኔ ግን መግባት ስለማይፈቀድልኝ በውጭ ሁኜ በደጅ አፉ በኩል ወደ ቤቱ ውስጥ ተመለከትኩ፣ ቤቱ ተሟሙቋል፤ ቡናም ቀራርቧል፡፡ በርከት ያሉ ሴቶችም መቀነታቸውን ፈትተው፣‹‹ማርያም ማርያም›› እያሉ በእንብርክክ ላይ ነበሩ፤ እውጭ ደግሞ ባሏን አቶ አበባውን ጨምሮ የተወሰኑ ወንዶች ቀበቷቸውን ፈትተው ነበር፤ በጸጥታና በጭንቀትም ወዲህ ወዲያ ይላሉ፡፡

ወ/ሮ በለጡ የተፈላው ቡና እስከሚጠጣ እንኳ ሳትቆይ ወዲያው በአማቲቱ አዋላጅነት ስድስተኛ ሴት ልጇን (በእለቱ ከተወለደችው በፊት ሁለት ወንዶችና ሶስት ሴቶች ልጆች አሏትና፣) በሰላም ተገላገለች፤ የተወለደችው አራተኛ ሴት ልጅ መሆኗ ነው፡፡ ወ/ሮ በለጡ እንደገለጹልኝ ህጻኗን በላስታ ቅቤ አቃምሰዋታል (ቁ.የ.መ.አ.3)፡፡

ማቃመስን በሚመለከት ሌላዋ የመረጃ አቀባየ እንደሚከተለው ብለዋል፡፡

> በዋግ ኽምራ አዲስ ለተወለደ ሕፃን ቅምሻ የሚባል አለ፤ ብቅልም፣ ዱቄትም ላስታ ቅቤም አድርገን የብር ድኮት አምጥተን ‹‹በወይሽም ወሸምነት፣ በዊዝር ዊዝርና በቁስ ቅስና፣ በዲያቆን ድቁና፣ በቀጥቃጭ ቅጥቅጥና፣ በሸማኔ ቁጢጥ፣ በአለቃ እልቅና ብለን ሕፃኑን አቃምሰን፡፡

[31] የቀበሌው ስም በሂደት ማይ ግንዶ ተባለ እንጂ መጠሪያው ግን ማይ (በትግርኛ ውሃ) ገንቦ እንደነበር አንድ አባት ነግረውኛል፤ ምክንያቱንም ሲገልጹ በአካባቢው በድርቅ ጊዜም ቢሆን የማይደርቁ በርካታ ምንጮች ስለነበሩ ነው፡፡

> ወንድ ሰባት ለሴት ሶስት ጊዜ እልል እንላለን፡፡ የእልልታ ልዩነቱ ካባታችን የተገኘ ስለሆነ ነው (ቁ.የ.መ.አ.19)፡፡

ትንሽ ቆየት ብለውም ሶስት ሴቶች ጥራጊ የሚመስል አፈር ይዘው እንግዴ ልጁን ለመቅበር ወደ ጓሮ ሄዱ፡፡ በወሊድ ጊዜ የእንግዴ ልጁን አንዲት ሴት ብቻዋን አትጥልም፤ ምክንያቱም ሰይጣን ወለፍ ያደርጋታል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ እነዚህ ሴቶችም ቢላዋ (ካራ) ይዘው ነበር የጣሉት፡፡ ወዲያውም «የማርያም መሽኛ» ተብሎ ገንፎ ተገነፋና እኔም ከሴቶቹ ጋር ተመገብኩ፡፡ በልተን ከጨረስን በኋላም እጃችንን በጋራ እየታጠብን፣ ሶስት ጊዜ እልል አልን፡፡ አካባቢው መብራት ስለ ሌለውና ቃለ-መጠይቅ ለማድረግም ሁኔታው ስለማይፈቅድልኝ የወሊድ ሥነ-ሥርዓቱን አስመልክቶ የማደርገውን ቃለ መጠይቅ በይደር አቆይቼ፣ የዋዜማውን የሠርግ ዝግጅት ለመመልከት ከሙሽራዋ እናትና ከሌሎች ሽኚ ወንዶች ጋር ወደ የሰርጉ ዳስ ተመለስሁ፡፡

በማግስቱ በጧት ለወ/ሮ በለጡ ቃለ-መጠይቅ ለማድረግ፣ የአራስ ቤት ገጽታዋ ምን እንደሚመስል ለመመልከትና ለመቅረጽ[32] እንድችል ወደ መኖሪያ ቤቷ ሄድኩ፡፡ የቤቱ ግድግዳ ነጭ ቀለም ባለው አፈር(ነጭ በረቅ) እና አልፎ አልፎ በቀይ አፈር ተቀብቷል (ተለቅልቋል)፤ በቤቱ ውስጥ አንዲት ተለቅ ያለች ሴትና የስምንተኛ ክፍል ተማሪ የሆነችው የአራሷ ልጅ ነበሩ፡፡[33] በቤቱ መካከል ላይ ከጭቃ በተሰራ ተንቀሳቃሽ ምድጃ (በእንክርትት) ላይ እሳት ይነዳል፤ ፍሙ ተርከክ ብሎ ቤቱን አሙቆታል፤ በሩ አጠገብ ከሸክላ በተሰራች ትንሽ የጢስ ማጤሻ ላይ የወገርትና የቡክቡካ ጢስ ይጤሳል፡፡ በአካባቢው ከሚገኙ ነገሮች የተሰሩ የቤት ቁሳቁሶች በግድግዳው ላይ ከቀንድ በተዘጋጀ መስቀያ ላይ በስርአት በስርአት ተሰቅለዋል፡፡ እነዚህም ወንፊት፣ ሞሰብ፣ ሌማት፣ ሰፌድ፣ እንቅብ፣ ባርና፣ ቁና፣ ቆለምሸሽ፣ ወንጠፍት፣ የወተት ማለቢያ ቅል (ባሻ)፣ የወተት መግፊያ፣ መናጫ ትልቅ ቅል(ላጋ) እና ላክሽም ናቸው፡፡ ከግድግዳው ጥግ በጭቃ ከተሰራው የእቃ ማስቀመጫ(ድምድማት) ላይም የማብሰያ ቁሳቁሶች፣ በገፈጀች(መገፈጆች)፣ ድስቶች፣ የብረት ድስቶች በስርዓት ስትር ብለው ተቀምጠዋል፡፡ አለፍ ብሎ ከበሩ አጠገብም የእርሻ መሳሪያዎችና አንድ ትልቅ ከጭቃ የተሰራ ጎታና በብዙ ጆንያዎች(ኬሻዎች) የተቋጠረ እህል ተደርድሯል፡፡

[32] በቪዲዮ ለመቅረጽም ሆነ ፎቶ ግራፍ ለማነሳት ፈቃደኛ ስላልሆኑ በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ ብቻ መረጃየን ለማግኘት ተገድጃለሁ፡፡
[33] የአራሷ ባል ግን በእህቱ ሠርግዝግጅት ላይ በዋና አስተባባሪነት ይሰራ ነበር፡፡

ከዚህ የወ/ሮ በለጡ አሰፋ ቤት ገጽታ የምንረዳው ነገር አለ፤ይኸውም፣ ነፍሰ-ጡር ሴት አስቀድማ የምታዘጋጀው ለምግብና ለመውለጃ የሚሆኑ ነገሮችን ብቻ ሳይሆን፣ ወልዳ የምትተኛበትንም ቤት እንደምታስውብና የቤት እቃዎቿንም በስርዓት በስርዓት እንደምታስቀምጥ ነው፡፡ ምክንያቱም ስትወልድ ለመጠየቅ የሚመጡት ሰዎች እሷን ብቻ ሳይሆን የሚጠይቁት፣ የቤቱን ገጽታም ይመለከታሉ፤ ከባለሙያነቷ አንጻርም ማንንቷን ይገምታሉ፡፡

የበለጡ ጠያቂዎች ደግሞ በአይቷ ሠርግ ምክንያት በርካታ ናቸው፤ ይህንን እውነታም ቃለ መጠይቅ እያደረግሁላት ባለሁበት ወቅት ከመጡ ሁለት ወንዶች ጠያቂዎች ለመረዳት ችያለሁ፡፡

በለጡ ኸምጣኛ እንጂ አማርኛ  በትክክል መናገር ስለሚያስቸግራት፣ ቃለ መጠይቁን ወደ አማርኛ የተረጎመችልኝ፣ ከበለጡ ልጅ  ጋር በመሆን እያረሰቻት ያገኘኋት የበለጡ የአጎት ልጅ ሚስት የሆነችው ወ/ሮ ስንዴወይ ወልዴ ናት፡፡ ወ/ሮ በለጡ በቤቱ በስተምስራቅ፣ ጥግ ላይ በምትገኝ ትንሽ መደብ በነጠላ መጋረጃ  ተጋርዳ ተኝታለች፤ መጋረጃ ውስጥ መሆንዋም ብርሃኑ የህጻኗን ዓይን  እንዳያንጸባርቅና አይኗን እንዳይጎዳት  ለማድረግ መሆኑን  ነው  ወ/ሮ ስንዴወይ የገለጸችልኝ፡፡ በአራሷ አናት ላይ ትልቅ  የጸጉር ቅቤ ቁጭ ተደርጓል፡፡ በሁለቱም እጆቿ ላይ ድኮት አድርጋለች፡፡ ለወ/ሮ በለጡ ቃለ-መጠይቅ በማደርግበት ወቅት  ሁለት ወንዶች ለሰርጉ መጥተው፣  መውለዷን እዚያው እንደሰሙ በመግለጽ፣ በኸምጣኛ ‹‹ማርያም ዋርዝነ፣ እነየው ማርያምም እጀው፣ ወዝ ካውር ሊኻ ጻሸት›› (ማርያም ታጫውት፣ እንኳን ሁለት ራስሽን አደረገሽ፣ እንደዚህ ያለች ማርያምም የለች) ብለው በውጭ ሆነው አራሷን ሲጠይቁ፣ ወ/ሮ ስንዴወይ አሜን(አሚን) አለች፤ ጠያቂዎቹም ትንሽ እንደቆዩ ሳይቀመጡ በቁማቸው ሆነው  በኸምጣኛ፣ ‹‹ቻዝ ዲሽና( ሞልቶ ደስ ያድርገን)›› ብለው  ወደ መጡበት ሊመለሱ ሲሉ፣ ወ/ሮ ስንዴወይ፣ ‹‹ቁጭ ብላችሁ ተነሱ እንጂ፣ በቁማችሁ ከሄዳችሁ እኮ ልጇቷ አልቃሻ ትሆናለች›› አለቻቸው፤ በዚህ ጊዜ ሁለቱም ወንዶች ፈገግ ብለው ተቀመጡና ተነስተው ሄዱ፡፡

አራሷ በሌሎች ሰዎች እየተጠበቀች የምትቆየውም እንደ አቅሟ እና የአራሷ ቤተሰብ ሁኔታ ነው፡፡ አንዳንዶቹ በሰባት ቀናቸው የሚነሱ አሉ፤ እስከ አስራ ሁለት ቀን ድረስ የሚቆዩም አሉ(ቁ.የ.መ.አ 20)፡፡ በአራስ ቤት-ጸላኢ ሰናይ እንዳይቀርባት ተብሎ መጥፎ ጠረን ያለው

ስራ ስር ባዲስ ቅል እንዲዘፈዘፍ ይደረግና ከደጃፍ ላይ እንዲሰቀል ይደረጋል፡፡ ይህ ስራ ስር የሚዘጋጀውም በወንድ ነው፡፡ ሴት ልትነካው አይገባም፡፡እስከ ሰባት ቀን ከአራስ ቤት ፍም(እሳት) አይጫርም፤ ምክንያቱም ከተጫረ ልጁ ጨቅጫቃ ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡ በስሃላና በዝቋላ ወረዳ ወንዶች ‹‹ለማርያም›› ብለው ሸክም እንጨት ወደ አራሷ ቤት ይወስዱላታል፡፡ አራሷ እንዳትቃዥ የሚያደርግ የቁም ጽሁፍም አራሷ ከተኛችበት መደብ ፊት ለፊት ይዘረጋል (ቁ.የ.መ.አ.19)፡፡

በዝቋላና በስሃላ ወረዳዎች (አልፎ አልፎ በሰቆጣ ወረዳ) ደግሞ ከአራስ ቤት ‹‹የማርያም ቅጠል›› ተብሎ የደደሆ ቅጠል ከቤቱ ደጃፍ ይሸጎጣል፡፡ የሚቆየውም አራሷ ከአራስ ቤት እስከምትወጣበት ጊዜ ድረስ ነው፡፡ መውለዷን ያልሰሙና ቤቷ ላይ የደደሆ ቅጠል መሸጎጡን የሚያዩ ሰዎችም ሴትየዋ መውለዷን በቅጠሉ ምልክትነት ተረድተው ይጠይቋታል፡፡

ቤተክርስቲያን ውስጥ በመግባት የሚያስቀድሱ ሰዎች እስከ ሶስት ቀን ድረስ አራሷን ለመጠየቅ ቢመጡም፣ በውጭ ሆነው ነው እንጂ ወደ ቤት ውስጥ አይገቡም፡፡ ምክንያቱም ቤቱ ጸበል ስላልተረጨ ነው፡፡ በሶስተኛው ቀን ግን ቤቱ ጠበል ይረጫል፣ አዋላጇም ሆኑ ሌሎችም ይረጫሉ፡፡ ይህም በወሊድ ጊዜ የተፈጠረውን የቤቱን መርከስ ለማንጻት ሲባል ነው (ቁ.የ.መ.አ.12)፡፡

በዋግ ኽምራ ወንድ ሲወለድ ሰባት ጊዜ፣ ሴት ስትወለድ ደግሞ ሶስት ጊዜ እልል ይባላል፤ የእልልታው መጠን ከሴት ይልቅ ለወንድ ልጅ ከፍተኛ ስለ መሆኑ በመረጃ ሰጪዎቹ የተገለጸው ምክንያት የተለያየ ነው፤ ለአብነት ያህል ውቢት ኪዴ፣ ቀደም ሲል በአካባቢው ወንዶች በዋግ ሹምነት፣ በፊታውራሪነት፣ በቀኛዝማችነት፣ ባጠቃላይም በአስተዳደር ስራ ላይ ስለ ነበሩ፣ ወንዶች መፍረድ ይችላሉ፤ ከሚለው አመለካከት ጋር የተያያዘ ይመስለኛል ትላለች (ቁ.የ.መ.አ.10)፡፡ አንዳንድ መረጃ አቀባዮቹ እንደ ገለጹት ደግሞ ወንድ ሩቅ ቦታ የሚሄድና ወንዝ የሚሻገር ጠንካራ ነው፣ ሴት ግን ብቻዋን ወንዝ መሻገር ስለማትችል ነው (ቁ.የ.መ.አ.26)፡፡ ወ/ሮ ጠጄ ደግሞ፣ የእልልታው መጠን የተለያየው ከአባታችንም ሆነ ከእናታችን የወረስነው ባህል ስለሆነ ነው ብላለች (ቁ.የ.መ.አ.1)፡፡

የሃይማኖት አባቶች ደግሞ በእርግጥ እልልታ አለ፣ ይህም ሰው ሰውን ሲወልድ በእልልታ እግዚአብሄርን ለማመስገን ነው፡፡ የእልልታው መጠን ለወንድና ለሴት መለያየቱ ደግሞ፣ በሃይማኖቱ ከሰው ልጅ አፈጣጠር ጋር በማያያዝ፣ ወንድ አስቀድሞ ከአራቱ ባህርያት( ከውሃነት፣ ከነፋስነት፣ ከመሬትነትና ከእሳትነት) በመፈጠሩ፣ ሴት ደግሞ ከሱ በኋላ መፈጠሯን ለማመልከት ሲባል ነው እንጂ ሌላ ሃይማኖታዊ ምክንያት የለውም ይላሉ፡፡ አያይዘው ሲገልጹም፣ ማህበረሰቡ በራሱ የፈጠረው ነው እንጂ፣ መጽሀፍ ቅዱሳዊ ህግ የለውም (ቁ.የ.መ.አ.12)፡፡

በዞኑ ከሴት እናቶች ይልቅ ለወንድ እናቶች የሚሰጠው አክብሮት ላቅ ያለ ነው፡፡ ምክንያቱንም የመረጃ አቀባዮቹ እንደሚከተለው ብለዋል፤ ሴት ስታገባ ለወንድ ቤተሰብ ስጦታ ይዛ የምትሄድ ናት፡፡ ወንድ ግን በጋብቻው ወቅት ለእናት ለአባት በሬ ወይም በቅሎ የመሳሰሉትን ንብረቶች ወይም ብር የሚያመጣ ነው (ቡ.ቃ.3)፡፡ የሃይማኖት አባቶች በገጠሩ ‹‹እከሌ ወንድ ልጅ ወለደ ወይም አምስት ወንድ ልጅ አለው›› ሲባል በቤት ውስጥ የሴቷ ጥቅም ቢበልጥም፣ ወንድ በውጭ በእርሻ ስራ ስለሚያግዝ፣ በወንድ ልጅ የመከበር፣ ሴትን አሳንሶ የማየት ሁኔታ ስለነበር ነው፤ በክርስትና ሃይማኖት ግን ሁሉም እኩል ነው ይላሉ *(ቁ. የ.መ.አ.12)*፡፡

በዋግ ኽምራ አንዲት ነፍሰ-ጡር ሴት እናቷ በህይወት የሌለች ካልሆነ በስተቀር የመጀመሪያ ልጇን የምትወልደው በእናቷ ቤት ነው፡፡ ለአብነት ያህል ጭላ በሚባለው ቦታ የተመለከትኳት አራስ ከምትኖርበት ከሰቆጣ ከተማ እናቷ ወደምትገኝበት ድሃና ወረዳ ሂዳ በእናቷ ቤት ነው የታረሰችው፡፡

ለዚህም በምክንያትነት የሚጠቀሰው ለእንክብካቤ ሲሆን፣ አራሷ የሚያስፈልጋትን ደፍራ መጠየቅ የምትችለው ከባእድ (ከአማቷ) ይልቅ ወላጅ እናቷን ነው ያሉም አሉ፡፡ የወደፊት አመጋገቧን በሚመለከት ጥንቃቄ እንድታደርግም እናቷ ምክር ትለግሳታለች፡፡ እናቷ ያላረሰቻት አራስ ደሟን አትተካም (ሰውነቷ አይጠገንም) ይባላል (ቁ.የ.መ.አ.25)፡፡ ለዚህም ያግዛት ዘንድ የመውለጃዋ ቀን ሲደርስ ከምትኖርበት የወንድ ቤተሰብ ቤት ወደ እናቷ ቤት እንድትሄድ ይደረጋል፡፡ የመውለጃ ቀኗን አሳስታ ከራሷ ቤት ብትወልድ እንኳ፣ ወላጅ እናቷ መጥታ ወደ ቤቷ ትወስዳታለች እንጂ ከወንድ ቤተሰብ ቤት እንድትታረስ አታደርጋትም፡፡ እንደ መረጃ አቀባዮቹ አገላለጽ፣ እንዲህ የሚደረገው ‹‹ለኩራትና

ለእንክብካቤ፣ በላችም አልበላችም እናት ደሞዜ››፤ ስለሆነ ነው፡፡ አንዳንዶች ደግሞ በምክንያትነት የሚገልጹት ሴት ልጅ አብዛኛውን ጊዜ የምትፈልገውን በግልጽ መናገር ይከብዳታል፤ ለዚህ ደግሞ አማቷንና እናቷን እኩል አታያቸውም፤ አማቷን ታፍራታለች፤ ትፈራታለች፤ እናቷን ግን አታፍራትም፤ አትፈራትም፤ ልክ እንደ እራሷ ስለምታያት የምትፈልገውን ሁሉ በግልጽ ትጠይቃታለች፤ ደም የነካና የሚታጠብ ልብስ ወይም እቃ ሲኖርም፣ እናቷ ያለ መጸየፍ ታጥብላታለች፡፡ በደንብም ታሳርሳታለች የሚል ነው (ቡ.ቃ.1)፡፡

ሕፃኑ(ሕፃኗ) ክርስትና የሚነሳው (የምትነሳው) ግን በወንድ ቤተሰብ ቤት ነው፤ ስለዚህ እራሷ የወለደችው ወንድ ከሆነ ወደ ሰላሳ ቀኗ አካባቢ፣ ሴት ከሆነች ደግሞ ወደ ሰባ ቀኗ አካባቢ ወደ አማቾቿ (የባሏ ቤተሰቦች) ቤት ትሄዳለች፡፡

## 4.3. ድህረ ወሊድ

በድህረ ወሊድ የሚካተቱት ከወሊድ በኋላ የሚከናወኑ ድርጊቶች ናቸው፡፡ ስለዚህ በዚህ ክፍል የሚገለጹት ተግባራት ወይም ድርጊቶች ሴትየዋ እንደወለደች ወዲያው የሚከናወኑ ተግባራት ብቻ አይደሉም፤ የክርስትና አነሳሱንና የስም አወጣጡንም (አሰያየሙን) የሚመለከቱ ናቸው፡፡

### 4.3.1. የአራስ ቤት ቆይታ እና አራስን መጠየቅ

የወለደችውን አራስ ሴት ለመጠየቅ ወደ አራሷ ቤት የሚመጡ ወይም ወደ ቤት የሚገቡ ሰዎች፣ ‹‹ማርያም ታጫውትሽ (**በኽምጣኛ ማርያም ዋርዝና**)፣ ‹‹ማርያም እንኳን ሁለት እራስሽን አደረገችሽ›› (**በኽምጣኛ ወዝ ማርያም ካውር ሊኘ ጳሽት**) ይላሉ፡፡ ጠይቀዋት ሲመለሱ ወይም ከቤት ሲወጡ ደግሞ፣ ‹‹ሞልቶ ደስ ያድርገን (**በኽምጣኛ ቻዝ ዲሽ ሽነ**)፣ ማርያም ጭንሽን ታሙቀው (**በኽምጣኛ ማርያም ኪዲብ ድብርዝና**)፣ ጀርባሽን ታሙቀው (**በኽምጣኛ ክሲጊድ ድብርዝና**)፣ የምታዝይ ያድርገው (**በኽምጣኛ ቦውረር ጻብና**) ይላሉ፡፡

በወሊድ ጊዜ ነፍሰ-ጡር ሴት ምጥ ስትያዝ ሴቶች የድንግል ማርያምን ስም በተደጋጋሚ ይጠራሉ፤ ስትወልድም ‹‹የማርያም አራስ›› ትባላለች፡፡ የሚጠይቋትም የማርያምን ስም

ይጠቅሳሉ፡፡ በዝቋላና በስሃላ ወረዳዎች ደግሞ ከአራስ ቤት ‹‹የማርያም ቅጠል›› ተብሎ የደደሆ ቅጠል ከቤታቸው ደጃፍ ይሸጎጣል፤

ይህም ማህበረሰቡ ከሚከተለው ሃይማኖት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ይህ ለድንግል ማርያም የሚከናወን ልመና እና መማጸን ሃይማኖታዊ ምክንያት እንዳለው ነው ቃለ መጠይቅ ያደረግሁላቸው የሃይማኖት አባቶች የገለጹት፡፡ ለአብነት ያህል ሊቀጠበብት ሀረገወይን አገዘ ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፤

> እመቤታችን ቅደመ-ወሊድ፣ ጊዜ-ወሊድ፣ ድህረ-ወሊድ ድንግል ናት፡፡ ለመውለድም የተጨነቀች አይደለችም፡፡ ነገር ግን የወለደችበት አካባቢ መከራ የበዛበት ቤተልሄም ዋሻ ውስጥ ነው፣ ልጇን ከሄሮዶስ ለማዳን ስትልም ሶስት ዓመት ከሶስት ወር በስደት የኖረች፣ ለልጇ ስትል ያለቀሰች፣ የተሰደደች፣ የተሰቃየች መከራ የተቀበለች ናት፡፡ ይህም የእናትነት ፍቅር ማሳየቷን የሚያመለክት ነው፡፡ ስለዚህ የእናቶቻችን ችግር ለእመቤታችን ቅርብ ነው፡፡‹‹ማርያም ማርያም›› ሲሉ፣ አንደኛ፣ እናቶቻችን ለእመቤታችን ያላቸውን ፍቅር የሚያመለክት ነው፣ ሁለተኛ ደግሞ የእመቤታችን አማላጅነት ለእናቶቻችን ፍቅር ፈጥኖ የሚደርስ እንደሆነ ስለሚታመን ነው፡፡ ስለዚህ እናቶቻችን የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ስም ከአንደበታቸው አይለዩም፡፡ በመሆኑም ሴቶች ተሰባስበው ‹‹ማርያም ማርያም›› ይላሉ፤ እናትም አማላጅም ስለ ሆነችም ስሟን ይጠራሉ፤ ይጠቀማሉ (ቁ.የ.መ.አ.13)፡፡

መጋቢ ምስጢር ገ/ህይወትም በተመሳሳይ፣ በምጥ ወቅት የሴቶች ‹‹ማርያም ማርያም›› ማለት የእመቤታችንን ጭንቅ አማላጅነት በመረዳት ነው ይላሉ፡፡ ምክንያቱን ሲገልጹም፣

> ቀደም ሲል እናቶቻችን እንጨት ሰብረው፣ ውሃ ቀድተው፣ አረም ሲያርሙ፣ ነዶ ሲሸከሙ ውለው ሲመለሱ መንገድ ላይ ልጃቸውን አሸዋ ላይ፣ አፈር ላይ፣ ጸሐይ ላይ ወልደው በአገልግል ይዘው ነበር ወደ ቤታቸው ይመለሱ የነበሩት፤ይህ ሁሉ በእመቤታችን አማላጅነት እንደሚፈጸም እናቶቻችን ስለሚያምኑ ነርሷ፣ ሆስፒታሏ፣ ጤና ጣቢያዋ አንዲት እሰዋ ናት፡፡ በምጥ ለተያዘች ሴት እመቤታችን ደርሳ ማገላገሏን የሚመለከትም በታምረ ማርያም በሁለት ቦታ ላይ ሰፍሮ ይገኛል ይላሉ (ቁ.የ.መ.አ.2)፡፡

የመጀመሪያው ታምር ማኅጸኗ ስለ ታሰረ ስለ አንዲት ሴት የሚገልጽ ሲሆን፣ ይህም የሚከተለው ነው፤

> …የመውለጃዋ ስዓትም በደረሰ ጊዜ ማኅጸኗ ታሠረና ወይም ለሞት እስከሚደርስ ታላቅ ጭንቀት ደረሰባት፡፡ በዚያን ጊዜ ቤተሰቦች በአልጋ ተሸክመው አምላክን የወለደች ወደ እመቤታችን ቤተክርስቲያን ወሰዷት፡፡ ከዚያም ከቤተክርስቲያኑ ቅጽረ ግቢ ከውጭው በር ሲደርሱ አንገቷ ተፍታታና ወንድ ልጅ ወለደች፡፡ (ተስፋ፣1993፣357)፡፡

ሁለተኛው ደግሞ፣ እመቤታችን ጸንሳ የነበረችን ሴት ከባህር መስጠም እንዳዳነቻት በሚል ርእስ የሰፈረው ነው፡፡

> …የምትወልድበት ቀን ፈጽሞ የደረሰ አንዲት የጸነሰች ሴት ነበረችና ሰዎች ሁሉ ሲሸሹ ባየች ጊዜ ይረዷት ዘንድ ወደ ሳቸው መልሳ ጮኸች፡፡ ወደ ሷም የተመለሰ የለም፡፡ የሰውን ረዳትነት ተስፋ በቆረጠች ጊዜ ወደ ልኡል እግዚአብሄር ይቅር ባይ ክብርት ሰው ወዳጅ ወደምትሆን በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ ወደ ጸናች ክብርት እመቤታችን ለመነች፡፡ ድንግል ማርያም ሁለንተናዋን አለበሰቻትና በቤት ውስጥ እንዳለች ሆነች፡፡ በባህር ውስጥም ሳለች ለመውለድ ምጥ ያዛትና አምላክን የወለደች በደንጋሌ ነፍስ የጸናች ክብርት እመቤታችን እየጠበቀቻት ወንድ ልጅ ወለደች፡፡ እመቤታችን ተኣምራትን የምታደርግ ናትና ምጥ አልተሰማትም ምንም አላገኛትም (ኢ.ኦ.ተ.ቤ1989፣ 255-256)፡፡

በወሊድ ሥነ-ሥርዓት ከሚከናወኑ ሃይማኖታዊ ድርጊቶች መካከል ሌላው ደግሞ አራስ ሴት ሲያባትታት የቁም መጽሀፍ ከፊት ለፊቷ ይሰቀልና ያንን እንድታይ ሲደረግ መባተቷን ትተዋለች ተብሎ ይታመናል (ቡ.ቃ.3)፡፡ የዚህን ሃይማኖታዊ መነሻ አስመልከተው መጋቢ ምስጢር የተባሉት የመረጃ አቀባየ እንደሚከተለው ብለዋል፡፡ የቁም ጽሁፍ ልክ እንደ ክታብ ነው፡፡ ሰዎችን ከጸላኢ-ሠናይ የሚከላከል ነው ብለው የቤተክርስቲያን ሰዎች (መሪጌታዎች) የሚያዘጋጁት ነው፡፡ አንዳንዶች በአንገታቸው ያስሩታል፤ በወሊድ ጊዜ ደግሞ ተዘርግቶ አራሷ እንድታየው ይደረጋል (ቁ.የ.መ.አ.2)፡፡ አራሷ በቤት ውስጥም ሆነ ለመጸዳዳት ወደ ውጭ በምትወጣበት ጊዜ ብቻዋን መሆን የለባትም፤ ሌላ ሰው ይጠብቃታል፤ ይከተላታል፡፡ በመኝታዋ አካባቢም አንካሴ ወይም ብረት ነገር ይደረጋል፤ ቀደም ሲል እንደ ተጠቀሰውም ለመጠበቂያነት ከእጇ ድኮት(አምባር) ታደርጋለች፡፡

አንዲት ሴት በአራስነት ቆይታዋ የምትመገበው እንደ አቅሟ የሚወሰን ቢሆንም፣ በብዛት ገንፎ፣ በቅቤና በበርበሬ የተቀባ ትኩስ እንጀራ ወይም ቂጣ (እቃተኛ)፣ በበርበሬ የተሰራ እርጎ (ስልስ ወጥ) እና የተፈረፈረ (ቁልቁል የገባ) እንጀራ፣ አቅም ከፈቀደም በግ፣ ፍየልና

ዶሮ እየታረደም በስጋ ወጥ ትመገባለች፡፡ በብዛት የምትጠጣውም ድቋ፣ ሙቅ (አጥሚት) እና ካላትም ወተትና የወተት ተዋጽኦዎችን ነው፡፡ ለአራስ ሴት ኮረፌ እንጂ ዝልል አይወሰድላትም፤ ምክንያቱም ሰውነቷ አይችልም፤ ኮረፌ ግን እንቅልፍ ስለሚፈጥር አራሷ እረፍት እንድታገኝ ያደርጋታል (ቁ.የ.መ.አ.25)፡፡

አራሷን የሚጠይቁ ሴቶችም ለአራሷ ምግብና መጠጥ ይወስዱላታል፡፡ የሚወስዱትም በቅርብ የሚገኙት ገንፎ፣ በስልስ ወጥ እንጀራ፣ ቁልቁል የገባ እንጀራ ሲሆን፣ ራቅ ካለ ቦታ የሚመጡት ደግሞ እንደ ቀረቤታቸው የጸጉር ቅቤ፣ ትኩሴና አንባሻ ነው፡፡ የቅርቦቹም አልፎ አልፎ  እንደ እሩቆቹ ሁሉ አንባሻና ትኩሴም ይወስዳሉ፡፡ በመጠጥ በኩል ደግሞ ካላቸው ወተት፣ ከሌላቸው ደግሞ ድቋና ኮረፌ በመውሰድ ይጠይቋታል፡፡

የወለደች ሴት የአራስ ቤት ቆይታ፣ እንደ አቅሟ የሚወሰን ነው፡፡ አቅምና የሚያርስ ቤተሰብ ካላት ከፍ ሲል እስከ ሰላሳ ቀንና በተለይ ወንድ ከሆነ ክርስትናው ድረስ ዝቅ ሲልም እስከ 12 ቀን ትታረሳለች፤ አቅምና የሚያርስ ቤተሰብ ከሌላት ደግሞ ሰባት ቀን ብቻ ነው የምትታረሰው (ቁ.የ.መ.አ.19)፡፡

አራሷ እንደ ተነሳችም ወደ የቤት ውስጥ ስራዋ ታመራለች፡፡ በተለይ የተወለደው ወንድ ከሆነ፣ ክርስትና የሚነሳው (የሚጠመቀው) በአርባኛው ቀን ስለሆነ፣ ለክርስትናው ድግስ የሚያስፈልገውን የጠላ ዝግጅት ትጀምራለች፤ ቆሻሻውን ከእህሉ ትለያለች (ትለቃቅማለች) ብቅል ትነክራለች፤ ለኮረፌ የሚሆን ደረቆትም ትቀቅላለች፡፡ እነዚህን ስራዎች የምታከናውነው በህይወት ካለች በእናቷ፣ ከሌለችም በቤተዘመድና በጎረቤት እገዛ  ነው፡፡

### 4.3.2. የአራስ ሴት ልብስ አጠባ

የአራስ ልብስ በሌሎች ሴቶች በተለያየ ጊዜ ይታጠባል፤ የሚታጠብበትን ጊዜ በሚመለከት ከመረጃ አቀባዮቼ መካከል አንዳንዶቹ ሁለት ጊዜ ይታጠባል ሲሉ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ሶስት ጊዜ ነው ይላሉ፡፡ ወ/ሮ ጠጇ የአራስ ሴት ልብስ በሌሎች ሴቶች የሚታጠበው ሁለት ጊዜ ነው፤ በወለደች በሶስተኛውና በሰባተኛው ቀን ስትል (ቁ.የ.መ.አ.1) ሶስት ጊዜ ይታጠባል የምትለው ደግሞ ውቢት ኪዴ ደግሞ አስራ ሁለተኛውን ቀንም ትጨምራለች (ቁ.የ.መ.አ.10)፡፡ ደም የነካው የአራሷ ልብስ በሶስተኛው ቀን የሚታጠብበት የልብስ አጠባ ‹‹የስርቆት አጠባ›› ይባላል፡፡ የስርቆት

አጠባ የተባለበትም ምክንያት ማርያም የማትወደው አጠባ ስለሆነ ነው ይላሉ የመረጃ አቀባየ (ቁ.የ.መ.አ.13)፡፡ ሌላዋ ደግሞ የስርቆት የሚባለው ሶስተኛው ቀን በሰንበት ቢሆን በሃይማኖቱ ተከታዮች በሰንበት ልብስ የማይታጠብ ሲሆን የአራስ ልብስን ግን ደም የነካ ስለሆነ በመስረቅ ስለሚታጠብ ነው፡፡ በተጨማሪም በአጠባው የሚሳተፉት ሴቶች ሌሎች እንዳይሰሙ በማድረግ የተወሰኑና የቅርብ ዘመዶች ብቻ መሆናቸው በድብቅ ወይም በስርቆት ያስብለዋል ትላለች (ቁ.የ.መ.አ.25)፡፡ በዚህ የልብስ አጠባ ላይ የሚሳተፉትም የአራሷ እናት፣ እህትና አይት ናቸው፡፡ በቁጥር የተወሰኑ የቅርብ ዘመዶችና ጎረቤቶችም ይሳተፋሉ፡፡ ምክንያቱም የሚታጠበው ልብስ ደም የነካ ስለሆነ ቤተዘመድ ያልሆኑት ለማጠብ እንዳይጠየፉ በማለት ነው፡፡ ልብስ አጣቢዎቹ ወደ ወንዝ ሲሄዱም (ወንዝ በቅርብ ባይኖርም እሩቅ ቦታ ወደሚገኝ ወንዝ ሂደው ያጥባሉ)፣ ለሌሎች ጥሪ እንዳይሆን በማለት ድምጽ ሳያሰሙ ጸጥ ብለው ይሄዳሉ፤ ማጭድ ወይም ቢላዋም ይይዛሉ፡፡

በሰባተኛው ቀን የልብስ አጠባ ላይ ግን የአራሷ የቅርብ ቤተሰቦች ብቻ ሳይሆኑ፣ ጎረቤቶችና ሌሎችም ይሳተፉበታል፡፡ የሰባተኛ ቀን አጠባነቱን በማስታወስ ለሌሎች ጥሪ ለማድረግና ሴቶቹ ወደ ወንዝ እየሄዱ መሆናቸውን ለማሳወቅም ገና ከቤት ሲወጡ ጀምሮ ወንዙ እስከሚደርሱ ድረስ ‹‹እልል›› ይላሉ፡፡ በዚህ ወቅትም ቢላዋ ወይም ብረት ነገር ይዘው ይሄዳሉ፡፡ የተወሰኑት ሴቶች ለልብስ አጠባ ወደ ወንዝ ሲሄዱ የተወሰኑት ደግሞ እቤት ቀርተው ገንፎ ያገነፋሉ፡፡

ሴቶቹ ልብሱን አጥበው ወደ ቤት ሲመለሱ፣ ከወንዝ ይዘውት የሚመጡት ነገር አለ፡፡ ይኸውም የተወለደችው ሴት ከሆነች ወደፊት ጎጆ ስትወጣ ከቤተሰቦቿ የምትወስዳቸውን የቤት እቃዎች ማለትም ላክሽም፣ እንዝርት፣ ወንፊት፣ ማንዘርዘሪያ፣ ቅል፣ ወስከንቢያ፣ ሙዳይ፣ ከመሳሰሉት መካከል የተወሰኑትን፣ የተወለደው ወንድ ከሆነ ደግሞ ጠብመንጃ (መሳሪያ)፣ ከእርሻ መሳሪያዎች መካከል ወስኮና ማረሻ በአካባቢው ከሚገኝ ስራ ስር፣ ልጥ ወይም ቅጠል አስመስለው በመስራት ያመጣሉ፡፡

እነዚህ ቁሳቁሶች ለወንድ የወንድ እቃዎች፣ ለሴት ደግሞ የሴት እቃዎች ናቸው፡፡ ከእነዚህ እቃዎች መካከል አብዛኛዎቹ ሕፃኑ ወይም ሕፃኗ ወደ ፊት በምን ዓይነት ስራ ላይ ሊሰለፍ ወይም ልትሰለፍ እንደሚችል ወይም እንደምትችል መተንበያ ናቸው፡፡

ሴቶቹ ልብስ አጥበው ከወንዝ ሲመለሱም፣ እስከ አራሷ ቤት ድረስ ‹‹እልል›› ይላሉ፡፡ በዚህ ወቅት አራሷን ‹‹ከመኝታሽ ተነሽ፣ ውጪውን እዪ›› ይሏታል፡፡ አጣቢዎቹ እንደ ተመለሱም፣ ሌሎች በልብስ አጠባው ያልተሳተፉ ሴቶችም ጭምር ተጠርተው፣ አራሷ ካላት በቅቤ ከሌላት ደግሞ ቀደም ሲል በአካባቢው በሚዘጋጀው ቅባኑግ አሁን አሁን ደግሞ በዘይት፣ በሰሊጥ ወይም በተልባ ልጥልጥ በትልቅ ሳህን ወይም ቅባት በጠገበ ገበታ በጋራ ሆነው ገንፎ ይበላሉ፤ ለአራሷም ለብቻዋ ይሰጧታል፡፡ በዝቋላና በስሃላ ወረዳዎች የሚቀርበው ገንፎ ብቻ ሳይሆን ቂጣ እና አሚዛም ነው (ው.መ)፡፡ በልተው እንደ ጨረሱም፣ እጃቸውን በአንድ ላይ እየታጠቡ፤ ሶስት ጊዜ ‹‹ማርያም ማርያም ማርያም›› እያሉ እልል ይላሉ፤ ከቤቱ ከመውጣታቸው በፊትም፣ ‹‹ለእናት ለአባትህ/ሽ ሁን/ሁኚ፣ ማርያም በሽልም ታውጣሽ›› በማለት መርቀው ይለያያሉ፤ይህንን አስመልክተው ወ/ሮ አልማዝ እንደሚከተለው ብለዋል፡፡

> በሰባተኛው ቀን አጠባ ገንፎ በልተን እጃችን በጋራ ታጥበን እልል እንላለን የታጠብንበትን ውሃ መሃን የሆነች ሴት ስትጠጣውም ለመውለድ ያስችላታል ተብሎ ይታመናል፡፡ ስንወጣም በሽልም ታውጣሽ፣ ጭንሽን ታሙቀው እንላለን፡፡ ምክንያቱም አንዲት ወላድ ልጇን ካላቀፈች ጭኗ አይሞቅም፡፡ ጭኗ የሚሞቀው የደም ሙቀት ያለውን ህጻን ስታቅፈው ነው፡፡ ከሞተባት ግን ነፋስ ስለሚገባባት ጭኗ አይሞቅም (ቁ.የ.መ.አ.26)፡፡

በዝቋላ ወረዳ በአራሷ አስራ ሁለተኛ ቀንም ልብሷ በቅርብ ቤተሰቦቿ ይታጠባል፡፡ ከዚያ ወደ ደጅ ወጥታ እራሷ ልብሶቿን ታጥባለች፡፡

## ግርዛት

በዋግ ኽምራ የሕጻናት የግርዛት ጊዜ ወጥ አይደለም፤በደጋውና በቆላው የተለያየ ነው፡፡ በደጋው ሴትም ወንድም የሚገረዙት በተወለዱ በሰባተኛው ቀን ነው፡፡ ይህንንም የመረጃ አቀባዮቹ እንደሚከተለው ገልጸውታል፡፡

> ሰነፍ እናት ካልሆነች በስተቀር ከሰባት ቀን ማሳለፍ የለባትም፤ ምክንያቱም ቆዳው እንዳይገረዝዝና ነፍስ አውቆ ቁስሉን እየነካካ ማልቀስ ከጀመረ፣ ወደፊትም አልቃሻ ይሆናል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ በግርዛት ጊዜም ሶስት ትንንሽ ቂጣ (ቋቋቴ) ይጋገርና ቁስሉን በዚያ ተኮሰ ተኮስ አድርጎ ለውሻ ይሰጣል፡፡ ‹‹የውሻ ቁስል ያደርግልሽ/ህ›› ይባላል፡፡ ውሻው ቂጣውን ከበላው ቁስሉ ቶሎ

> ይድናል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከዚያ ልብስ ባልተለበሰበት ከባዶ ጫንቃ ላይ ይታዘላሉ፣ ይህም ሽንታቸው ቁስሉን እንዲያደርቅ ያደርጋል ተብሎ ስለሚታመን ነው (ቁ.የ.መ.አ.25 እና ቡ.ቃ.3)፡፡

የቆላውን በሚመለከት ደግሞ ወ/ሮ ማርያሙ እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡

> በቆላው ቋሚ የግርዛት ቀን የለም፤ አንዱም ፍየል እስከሚውል(ፍየል ለመጠበቅ እስከሚበቃ) ይቆያል ቁስሉ እንዲድን ቀቀባ የምትባል ቅጠል ቀጥቅጠን ጨምጥጠን (ጨምቀን)ና ኩል ደቁሰን ይተመተማል፣ የፍየል ቅልጥም መቅኔም ከቁስሉ ላይ እንቀባለን፡፡ ይህም ቁስሉ እንዲደርቅ ያደረጋል፤ በአካባቢያችን የግርዛት ድግስ ቀድሞም የለም አሁንም የለም (ቁ.የ.መ.አ.19)፡፡

በዝቋላ ወረዳ ሴትም ወንድም ይገረዛሉ፤ ቋሚ ቀን ግን የለም፤ ሴቶች አይገረዙ እየተባለ እንዲገረዙ የሚደረገውም ካልተገረዙ ሲያድጉ እቃ ይሰብራሉ፤ ጸባያቸውም መጥፎ ይሆናል የሚል እምነት ስላለ ነው፡፡

### 4.3.3 የክርስትና አነሳስ (የመጠመቅ) ስርዓት

የጥናት ቦታየን ማህበረሰብ ማንነት በቅኝት እንደ ገለጽኩት፣ ከመቶው ከዘጠና ዘጠኝ በላይ የሚሆነው የዞኑ ማህበረሰብ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና እምነት ተከታይ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና እምነት መሰረት ደግሞ ማርቆስ ምእራፍ 16 ቁጥር 16 ‹‹ያመነ የተጠመቀም ይድናል፣ ያላመነ ግን ይፈረድበታል፡፡›› በሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መሰረት፣ ወንድ በተወለደ በአርባኛው፣ ሴት በተወለደች በሰማንያኛዋ ቀን ክርስትና ይነሳሉ (ይጠመቃሉ)፤ የመጠመቅ ስርዓቱ የሚከናወነውም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ባሳተመችው መጽሀፈ ክርስትና (የክርስትና መጽሃፍ) ላይ ባሰፈረችው መሰረት ነው፤ ሂደቱን አስመልክተው አባ በንኑ እንደሚከተለው ብለዋል፤

> በየቤተክርስቲያኑ፣ በየደብሩ ወይም በየገዳሙ ክርስትና የሚነሳባቸው የተለዩ ቦታዎች አሉ፡፡ ክርስትና አስነሺዎች፣ አንሺዎች እንደዚሁም አጃቢዎች የቅዳሴ ስነ ስርዓቱ ከመካሄዱ አስቀድሞ ለመጠመቂያ የሚያስፈልገውን ውሃ በቅል[34]ይዘው፣ በዚህ ቦታ ይገኛሉ፡፡ ከዚያም ስርዓቱ እንደሚከተለው ይቀጥላል፡፡ በመጀመሪያ ስርዓተ-ቅዳሴ በከፊል ይከናወናል፤ በመቀጠል ከመጠመቁ በፊት ቄሱ የክርስትና

[34] ቀደም ሲል በገጠሩ ለክርስትና ማንኛ የሚሆን ውሃ ከፕላስቲክ በተሰራ መያዣ አይወሰድም ነበር፤ ምክንያቱም መያዣውን የሌላ እምነት ተከታይ ሰርቶት ሊሆን ይችላል በሚል ስጋት ነው፡፡

> አባት ወይም እናት ለመሆን የቀረቡትን እናት ወይም አባት ትንሽ ጣት ከሕጻኑ ትንሽ ጣት ጋር በማቆላለፍ፣ ‹‹ሌት ከወለድኩት ቀን የወለድኩት የመንፈስ ቅዱስ ልጅ ይበልጣል፤ እድረዋለሁ፤ እኩለዋለሁ፤ አስተምረዋለሁ፡፡›› ብሎ ቃል እንዲገባ ያደርገዋል፡፡ የመጠመቂያውን ውሃ ቄሱ ከባረኩ በኋላ፣ ሕጻኑን ውሃው ውስጥ በመዘፈቅ እንደ ጾታው ወንድ ከሆነ፣ ‹‹አጠምቀከ በስመ አብ ወወልድ ወመነፍስ ቅዱስ፣ ይኩን ስምከ ወልደ-/ገብረ-›› ብሎ (በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቅሃለሁ፤ ስምህም ወልደ-ወይም ገብረ... ይሁን)፣ ሴት ከሆነች ደግሞ፣ ‹‹አጠምቀኪ በስመ አብ ወወልድ ወመነፍስ ቅዱስ፣ ይኩን ስምኪ ወለተ../አመተ...›› (በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቅሻለሁ ፤ስምሽም ወለተ-/አመተ-ይሁን) በማለት አጥምቆና የህጻኑን አካል አልፎ አልፎ ሜሮን (ቅብአ ቅዱስ) ቀብቶና ንሳ መንፈስ ቅዱስ ( መንፈስ ቅዱስ በህጻኑ ላይ እደር፡፡) ብሎ ክርስትና የመነሳት ወይም የመጠመቅ ምልክት የሆነውን ማተብ ከውሃው በመንከር አስሮለት/ላት፣ ሶስት ጊዜ አዙሮ፣ ለክርስትና አባት ወይም እናት ይሰጣቸዋል (ቁ.የ.መ.አ.19)፡፡

ከዚያም በቄሱ የማሳረጊያ ጸሎት[35]ተሰጥቶ የጥምቀት(የክርስትና አነሳስ) ስርዓቱ ይጠናቀቃል፡፡ ክርስትና አስነሺዎችና አጃቢዎቻቸው የቅዳሴ ስርዓቱ እየተከናወነ ቢሆንም፣ ወደ ቤተክርስቲያኑ ውስጥ ገብተው ያስቀድሳሉ፡፡ ሊቀጠበብት ሐረገወይን አገዘ እና መጋቢ ምስጢር ገ/ህይወት ኪዳነ ማርያምም በአርባ ቀንና በሰማንያ ቀን ክርስትና መነሳትን አስመልክተው እንዲህ ይላሉ፡፡ ይኸውም በጥንተ ኦሪት ወንድ በተወለደ በአርባ ቀኑ፣ ሴት በተወለደች በሰማንያ ቀኗ ወደ ቤተ-መቅደስ ተወስደው መስዋእት አቅርበው ተባርከው፣ ይመለሱ ነበርና ክርስትና መነሳትም ይህንኑ የተካ ነው፡፡ ሞገስም (1969፣71) እንዲህ በማለት ተመሳሳይ ሃሳብ አስፍረዋል፤

> በክርስትና ጊዜ አበልጅ ሊሆን የተጠራው ሰው ቀርቦ ሕጻኑን ታቅፎ፣ስለ ሕጻኑ ጸሎተ ሐይማኖትን ይደግማል፡፡ስለዚህ ለሕጻኑ የሃይማኖት ዋስ መሆኑ ነው፡፡...የክርስትና አባት እናት የተፈለጉበት ምክንያት...አምኖ የተጠመቀ...ያለውን ክርስቶሳዊ ቃል ለመፈጸምና ሕጻኑም ካደገ በኋላ ለማመኑ ተያዥ ዋስትና እንዲሆኑ ማለት እንደ እናት እንደ አባት እንዲመክሩትና እንዲያስተምሩት ነው፡፡

[35] የማሳረጊያ ጸሎት እንደ አውዱ የተለያየ ነው፡፡ ወሊድ ከሆነ የተወለደው ህጻን እንዲያድግ፤ጋብቻ ከሆነም ጋብቻው የሰመረ እንዲሆን፣ ቀብር ከሆነም የሞተው ሰው ነፍስ እንዲማር በመለምን፤አቡነ ዘበሰማያትና በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል የሚጸለይበት ነው፡፡

ይህ ስርዓት ሕፃኑን ከእምነት አልባነት ወደ ክርስትና እምነት ተከታይነት ወይም ወደ የክርስቲያን ማህበረሰብ አባልነት የሚያሸጋግር ነውና ክርስትና መነሳት እንደ አንድ ንኡስ የሽግግር ሥነ-ሥርዓት የሚታይ ነው፡፡

ክርስትና በሚኖርበት ወቅት ቅዳሴ እንዲቀደስ ወላጆች አስቀድመው የክርስትናውን ቀን ለነፍስ አባታቸው ያሳውቃሉ፤ ለቤተክርስቲያኑም ግብር ተብሎ ስንዴ ይወሰዳል፡፡ ግብር መውሰድ የማይችሉና በተለያዩ ምክንያቶች ልጆቻቸውን ክርስትና ያላስነሱ ወላጆች ደግሞ ልጆቻቸውን በጥምቀት (ጥር አስራ አንድ ቀን) ክርስትና ያስነሳሉ፡፡

ለክርስትና የተለያዩ ቅድመ ዝግጅቶች ያስፈልጋሉ፤ የመጀመሪያው የክርስትና ድግስ ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ወላጆች ልጆቻቸውን የሚያነሱላቸው የክርስትና እናት ወይም አባት መምረጥና ፈቃደኝነታቸውን መጠየቅ ነው፡፡ ለዚህም ቀኑ ከመድረሱ ቢያንስ ከአስራ አምስት ቀናት በፊት፣[36] ዝምድናው (ዝምድናዋን) እናጥብቅ የሚሉትን (የሚሏትን) አባትና እናት ባልና ሚስት ተመካክረው በጋራ ይመርጣሉ፤ ይወስናሉ፡፡ ምክንያቱም አንዱ የፈለገውን ሌላው ካልፈለገው ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ከተስማሙ በኋላ ግን ሕፃኑ ወንድ ከሆነ አባትየው፣ ሴት ከሆነችም እናትየዋ ወደተመረጠው (ወደተመረጠችው) ሰው ቤት በጥዋት በመሄድ ጥያቄ በማቅረብ ይለምናሉ፡፡ የሚለምኑትም ቁመው ‹‹ዘመድ ትሆነኝ (ትሆኚኝ) ብየ፣ እንፋቀራለንና ፍቅራችንን ቋጠሮ እናበጅለት ብየ ካንተ (ካንቺ) መጥቻለሁ፡፡›› ብለው ነው፡፡ ተጠያቂው (ዋ) ም ተመርጦ (ጣ) እና ተፈልጎ (ጋ) የተለመነ (ነች ) መሆኑን (ኗን) ስለሚረዳ (ስለምትረዳ) እሺ ይላል(ትላለች) እንጂ እምቢ አይልም (አትልም) (ቁ.የ.መ.አ.26)፡፡ ወ/ሮ ሙሉ ወርቅ አወጣም የክርስትና አባትና እናት አጠያየቅን አስመልክተው እንዲህ ገልጸዋል፤

> የክርስትና አባትንና እናትን (በሽምጣኝ አልየ እና አሊያ) የሚመርጡት ባልና ሚስት ተመካክረው ነው፡፡ አባት የሚጠቁመውን የሕጻኗ እናት የማትፈልጋት ሴት ከሆነች እኔ እሷን አልፈልግም እንላለን፡፡ በማግስቱ ጧት ተነስቶ ይሄድና ‹‹ዘመድ ልትሆነኝ ከዝምድና ላይ ዝምድና ለመጨመር ልጄን እንድታነሳ፣ የክርስትና እናት ወይም አባት (አበልጅ) እንድትሆነኝ ለመለመን መጣሁ፡፡ ይላል (ቁ.የ.መ.አ.14)፡፡

[36] የክርስትና አባትና እናት ጥየቃ (ልመና) ቀደም ብሎ የሚደረገው አባትና እናት ለሚሆኑት ሰዎች ዝግጅት ሲባል ነው፡፡ይኸውም ለማስነሻ የሚሆን ልብስ ለመግዛትና ለትኩሴ የሚሆን ስንዴ ለማዘጋጀት ወይም ለመሸመት ነው ፡፡

በዚህ መንገድ የክርስትና እናትና አባት የማይለመንበት (የማይጠየቅበት) ጊዜም አለ፡፡ ይኸውም አስቀድሞ የወላጆቹ ጓደኞች ነፍሰጡሯን ‹‹ወንድ ከወለድክ አባቱ እኔ ነኝ፣ ሴት ከወለድሽ እናቷ እኔ ነኝ›› ካሉና ተጠያቂዎቹ ‹‹ እሺ፡፡›› ካሉ፣ ሌላ ማፈላለግ ሳያስፈልግ በቃላቸው ጸንተው የክርስትና እናትነቱን ወይም አባትነቱን ቃል ለገቡላቸው ሰዎች ይሰጧቸዋል፡፡ የክርስትና እናት ወይም አባት አስፈላጊነትም ከሃይማኖት ጋር የተያያዘ መሆኑን የሃይማኖት አባቶች ያስረዳሉ፡፡

> በስጋ የወለዷቸው ወላጆች ልጆቻቸውን ለስጋ ፍላጎታቸው እየላኩ ሲያሳድጉ፣ ለመንፈሳዊ ህይወታቸው ደግሞ ጎን ለጎን አስተማሪ እንዲሆን፣ ለወንድ የክርስትና አባት ለሴት ደግሞ የክርስትና እናት ያስፈልጋቸዋል፡፡ እነዚህም የሃይማኖትን ነገር አስተማሪዎች እንዲሆኑ ነው፡፡ ጥቅሙም ስጋዊ ወላጆቻቸው የሚንከባከቧቸው ለምድራዊ ህይወታቸው ሲሆን፣ እነዚህ ግን ለሃይማኖታዊና ለመንፈሳዊ ህይወታቸው ነው፡፡ በመሆኑም ከስጋ ወላጆች የመንፈስ እናት አባቶች ይበልጣሉ፡፡ ልጆች የስጋ ወላጆቻቸውን ባጡ ጊዜም ልክ እንደ አባትና እናት አሳዳጊ ይሆናሉ፡፡ የመንፈስ አባትና እናት የመንፈስ ወላጆች ናቸው፡፡ ለዚህም ነው የክርስትና አባቶችና እናቶች በክርስትና ልጆቻቸው የሠርግ ስጦታ ወቅት እንደ ቤተሰብ አባል ተቆጥረው ዳስ ውስጥ ስጦታ የሚሰጣቸው፤ወደ ቤታቸውም ስጦታ የሚወሰድላቸው (ቁ.የ.መ.አ.2 እና 13)፡፡

በድግሱ ለሚጋበዝ ቤተዘመድና ጎረቤትም በክርስትናው ዋዜማ ‹‹ነገ ልጃችሁን ቆማችሁ ክርስትና እንድታስነሱ›› በማለት ይጠራሉ፡፡ እሩቅ ለሚገኙ ቤተሰቦችም ከዚያ አስቀድመው ቀኑን በማሳወቅ ጥሪ ያደርጋሉ፡፡ ሞገስ(1969፣92) የክርስትና መነሳትን አስፈላጊነትና ስለድግሱ መጠን አስመልክተው ሲገልጹም፣

> ክርስቲያን የሆነ ሁሉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምኖ ሲጠመቅ በጸጋ የሥላሴ ልጅ ይሆናል፣ ስሙም በወልድ ውሉድ በክርስቶስ ክርስቲያን ይሆናል፣ ስለዚህ ክርስትና በሚነሣበት ዕለት ወላጆቹ ዓቅማቸው የፈቀደውን ያህል ደግሰው ወዳጆችን ቤተሰቦችን እንዲሁም ተስፋ አጣ የሆኑትን ጠርተው ያበላሉ ያጠጣሉ ክርስቲያናዊ ልማድ ነው፡፡...ድግሱ ወይም ግብዣው እንደ ባለቤቱ ችሎታ እንጂ ካህናት ይገባናል ብለው አይከራከሩበትም፡፡ሊከራከሩበትም አይገባም ግብዣው የፈቃድ እንጂ የግዴታ መሆን የለበትም ይላሉ፡፡

ወላጆች የልጆቻቸውን የክርስትና ልጅነት ለታቦት[37] የሚሰጡ ከሆነም፣ ሰው ማፈላለግና መለመን አያስፈልጋቸውም፤ ሲጠመቅ (ስትጠመቅ ) አባቱ ወይም እናቱ እከሌ ነው (ናት) ብለው የታቦቱን ስም ለቄሱ ይናገራሉ፡፡ በተለይ እናቶቻቸው የአንድን ታቦት ወንጌል አዝለው ወይም ጠበል ጠጥተው በስለት የተወለዱ ሕፃናት ከሆኑ ልጁ/ልጇቱ በክርስትና ልጅነት የሚሰጠው (የምትሰጠው) ለታቦት ነው፡፡ ለአብነት ያህል ለአቡነ ሳሙኤል ተስለው የሚወልዱ እናቶች ልጆቻቸውን በክርስትና ልጅነት የሚሰጡት ለአቡነ ሳሙኤል ነው፤ በዚህም ምክንያት የክርስትና ስማቸውም ሆነ አለማዊ ስማቸው ከታቦቱ ጋር የተያያዘ ነው፤ ወንድ ከሆነ ሳሙኤል፣ ሴት ከሆነች ደግሞ ሳሙኤሉ ትባላለች፡፡ በዞኑ ሳሙኤል ወይም ሳሙኤሉ የሚል መጠሪያ ያላቸው ሰዎች ሁሉ የአቡነ ሳሙኤል የስለት ልጆች ናቸው፡፡

አቡነ ሳሙኤል በዞኑ ከሚገኙ አዳብርት መካከል መካን የነበሩ ሴቶች ወንጌሉን በማዘል ወይም ጸበሉን በመጠጣት እንዲወልዱ ያደርጋል ተብሎ የሚታመን ታቦት ነው፡፡ የሚገኘውም በሰቆጣ ወረዳ በህሙሲት ዜሮ ሁለት ቀበሌ ልዩ ስሙ አቡነ ሳሙኤል በሚባል ቦታ ነው፡፡ በዚሁ ወረዳ ብርብር ጊዮርጊስ ከተባለው ደብር ጋር የሚገኘው አባ ኪሮስም ሌላው ተጠቃሽ ነው፡፡ እናቶቻቸው የአባ ኪሮስን ወንጌል አዝለው ወይም ጠበል ጠጥተው ከተወለዱም የሕፃናቱ የክርስትናም ሆነ የአለማዊ ስማቸው ወንድም ሴትም ኪሮስ[38] ሴት ደግሞ ኪሮሱ ትባላለች፡፡ በጋዝጊብላ ወረዳ የሚገኘውን የዛሮታ ተክለሓይማኖትን ጸበል በመጠጣት የተወለደ ደግሞ ተክለሃይማኖት ይባላል (ቡ.ቃ.3)፡፡

በዋግ ኽምራ የክርስትና ስም አሰጣጥን በሚመለከት ከታቦት ልጆች በስተቀር፣ በአብዛኛው ክርስትና በሚነሱበት እለት የሚውለውን (ወርሃዊ ወይም የንግስ እለት የሆነውን) የታቦት ስም በመጥቀስ ነው፡፡ በአብዛኛው ሴት ከሆነች ወለተ-፣ ዓመተ-፣ ወንድ ከሆነ ደግሞ ወልደ፣ ገብረ- የሚሉትን ቅጥያዎች ከታቦቱ ስም አስቀድሞ በመቀጥል፣ የጥምቀት (የክርስትና) ስም ይሰጣቸዋል፡፡ አልፎ አልፎም አስራት-እና ብስራት-የሚሉ ቅድመ ግንድ ቅጥያ የሚቀጠልባቸው ስሞችም አሉ፡፡ ለአብነት ያህል ወር በገባ በአስራ ሁለተኛው ቀን ክርስትና ለሚነሳ (ለምትነሳ) (ለሚጠመቅ/ለምትጠመቅ) እለቱ የቅዱስ ሚካኤል ወርሃዊ በዓል ስለሆነ (የንግስ በዓልም ሊሆን ይችላል) ወንዱ፣ ኃይለ ሚካኤል፣ ወልደ ሚካኤል

[37] በዚህ አገባብ ታቦት የሚለው ቃል ፍች የጽላት መቀመጫ ሳይሆን የመድሐኒአለም፣ የድንግል ማርያም፣ የመላእክት፣ የጻድቃን እና የሰማእታት ስም ነው፡፡

[38] ይህ ስም ለወንድም ለሴትም በመጠሪያነት የሚያገለግል ነው፡፡

ወይም ገብረ ሚካኤል፣ ሴቷ ደግሞ ወለተ ሚካኤል ወይም አመተ ሚካኤል ልትባል ትችላለች፡፡

ካልሆነ ደግሞ ወላጆች ልጆቻቸው የቤተሰቦቻቸውን የክርስትና(የጥምቀት ስም) በማስታወሻነት እንዲይዙላቸው ከፈለጉ እነሱ በመረጡት ስም እንዲጠሩ ይደረጋል፡፡ ለአብነት ያህል የእናትየዋ አባት ሟች ቢሆንና የክርስትና ስሙ ገብረ ስላሴ ቢሆን፣ ሴትየዋ ይህንን የሟች አባቷን የክርስትና ስም ለልጇ እንዲሰጥላት በክርስትና ስም አወጣጥ(አሰጣጥ) ወቅት ለቄሱ ትናገራለች፤ እሳቸውም ተቀብለዋት ‹‹ስምህ ገብረስላሴ ይሁን›› ይላሉ፡፡ በዚህ የክርስትና ስም የሚጠሯት/የሚጠሩትም የክርስትና አባትና እናት እና የነፍስ (የንስሃ) አባት ናቸው፡፡


ለክርስትና መነሻ (መጠመቂያ) የሚሆነው ውሃ ወደ ቤተክርስቲያን የሚወሰደው በቅል[39] ነው፡፡ ምክንያቱም ውሃው ካነሰ ሕፃኑ/ሕፃኗ ገራም አይሆንም/አትሆንም ተብሎ ስለሚታመን ብዙ ውሃ ለመውሰድ ነው (ቁ.የ.መ.አ.20)፡፡ ቅሉ ዛፍ ላይ ይሰቀላል ወይም ሶስት ጉልቻዎች ላይ ይቀመጣል፡፡ ድንጋይ ላይ መቀመጡ የጥምቀት ውሃ የተቀደሰ ስለሆነ መሬቱን ጻድቅም ሐጥእም ስለሚረግጠው እንዳይረክስ ነው (ቁ.የ.መ.አ.25)፡፡

ሕፃኑ(ሕፃኗ) ለታቦት በክርስትና ልጅነት ከተሰጠ/ች ከተጠመቀበት/ችበት አቅፎ ወደ ቤተክርስቲያን የሚያስገባው/የሚያስገባት ዲያቆን ነው፡፡ ሕፃኑን/ሕፃኗን) አቅፎ መንበረ ታቦቱን ካሳለመ በኋላ ለእናቱ/ቷ ይሰጣል፡፡ ለታቦት የተሰጠ/ች ካልሆነ/ካልሆነች ግን፣ ሴት ከሆነች የክርስትና እናቷ፣ ወንድ ከሆነ ደግሞ የክርስትና አባቱ ሚስት አዝለው ወደ ቤተክርስቲያን ያስገቡና ለእናቷ/ቱ ይሰጣሉ፤ ሲመለሱ ግን የክርስትና እናቷ፣ ወይም የክርስትና አባቱ ሚስት ያዝሏታል/ያዝሉታል፡፡

ሕፃኑ/ሕፃኗ ክርስትና ተነስቶ/ተነስታ አስነሽዎቹ ወደ ቤት በሚመለሱበት ወቅት የተለያዩ ድርጊቶች ይከናወናሉ፡፡ ይኸውም ክርስትና የተነሳችን ሴት ልጅ ያዘለቻት የክርስትና እናት ወደ ቤት ከመግባቷ አስቀድሞ በድንጋይ ወፍጮ ቋት ላይ፣ ክርስትና የተነሳን ወንድ ልጅ ያዘለች ደግሞ ወንበር ላይ እንድትቀመጥ ይደረጋል፡፡

---

[39] አሁን አሁን ግን ከፕላስቲክ በተሰራ የውሃ መያዣም እየተወሰደ ነው ፡፡



**ክርስትና የተነሳችን ሕፃን የክርስትና እናቷ አዝላት ቋት ላይ ተቀምጣ (ፎቶ በአፀደ ተፈራ)**

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የሕፃኑን/ሕፃኗን ክርስትና መነሳት ወይም መጠመቅ ምክንያት በማድረግ ወላጆች እንዳቅማቸው ድግስ ይደግሳሉ፡፡ የድግሱ ዝግጅትም እንጀራው በብዛት ድጉሎ ሲሆን በወጥ በኩል ደግሞ ከብት ወይም ፍየል ታርዶ ወይም በክክ ወጥና በእልበት በመጠጥ በኩል ደግሞ በደጋው በብዛት ኮረፌ በቆላው ደግሞ ዝልል ነው፡፡ በተለይ ሕፃኑ/ሕፃኗ የመጀመሪያ ልጅ ከሆነ/ች ድግሱ ከፍ ያለ ይሆናል፡፡ የክርስትናው ድግስ ታዳሚ ከሆኑት መካከል የክርስትና አባትና እናት፣ ትኩሴ ይወስዳሉ[40]፡፡ ሴቶቹ ደግሞ እንደ ቀረቤታቸው፣ ትኩሴ፣ አምባሻና በመሶብ እንጀራ ሲወስዱ፣ አብዛኞዎቹ ግን ዱቄት ይወስዳሉ፡፡ ወንዶቹ ግን በልተው ጠጥተውና ‹‹ይደግ እናት አባቱን ጧሪ ያድርገው፤ ሰርጉንም/ጓንም ያብላን›› ብለው መርቀው ከመሄዳቸው በስተቀር ምንም አይነት ስጦታ አያመጡም፤ አይሰጡም፡፡ ምርቃቱ በሴቶቹም ይገለጻል፡፡

---

[40] በቆላው እንደተመለከትኩት የባሌቤቷ እና የክርስትና አባት ወይም እናት ትኩሴ ወደ ቤተክርስቲያን ተወስዶ ለካህናቱ እና ቆመው ላስነሱት ይሰጣል፡፡ በደጋው ግን ሁሉም የሚቆረሰው በክርስትናው ማግስት እቤት ነው፡፡

ሕፃኑ/ሕፃኗ የሚኖረው/የሚኖራት የክርስትና ስም ብቻ አይደለም፤ አለማዊ ስም ጭምርም ነው ፡፡ ስለዚህ ይህ ስምም በወሊድ ሥነ-ሥርዓት በሽግግር ሥነ-ሥርዓትነት ይጠቀሳል፡፡ የዋግ ኽምራ የስም አወጣጥም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

በዋግ ኽምራ የሕፃኑ(ሕፃኗ) ስም እከሌ ነው ብሎ ለቤተሰብ ከመግለጽ፣ ወይም እናትና አባት ‹‹ልጁን/ልጅቷን ማን አላችሁት/ አላችኋት?›› ተብለው ሲጠየቁ ‹‹እከሌ ብለነዋል›› ብለው መልስ ከመስጠታቸው ውጭ የተለየ የስም አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት አይከናወንም፡፡ ለሕፃኑ(ሕፃኗ) አለማዊ ስም የሚወጣው(የሚሰየመው/የምትሰየመው) ግን በዘፈቀደ አይደለም፡፡ መነሻ ምክንያት ይኖረዋል፤ ከእነዚህ ምክንያቶች መካከል ለአብነት ያህል ልጁ/ልጇቷ ሲወለድ/ስትወለድ ቤተሰቦቹ/ቿ ከሚያጋጥማቸው ነገር ጋር ተቆራኝቶ፣ የልጁ መወለድ በቤተሰቦቹ ላይ ያሳደረውን ስሜት መነሻ ተደርጎ፣ የሟችም ሆነ በህይወት ያሉ ቤተሰቦችን ስም ለማውሳት ወይም የመልክ ተመሳሳይነት ለመጠቆም ተፈልጎ፣ ከዚያ በፊት ልጅ አላድግላቸው ብሎ እንደ ነበር ለመጠቆም ወዘተ. መጥቀስ ይቻላል፡፡ ለአብነት ያህል ቀደም ሲል የገለጽኩት በአክስቷ ሠርግ ዋዜማ እለት የተወለደችውን ሴት ልጅ ቤተሰቦቿ ፋሲካ እንደሚሏት ገልጸውልኛል፡፡ ይህም ቤተሰቦቿ ልጅቷ ስትወለድ ከነበሩበት የሠርግ ደስታ ድባብ ጋር የተዛመደ ነው፡፡

ከመረጃ አቀባዮቼ መካከል የተወሰኑት የስማቸውን መነሻ ምክንያት በሚመለከት ሀሳባቸውን እንዲህ ይገልጻሉ፡፡ የጸመራ ቀበሌ አስተዳደር ሊቀመንበር የሆኑት አቶ ጣፈጠ ወልዱ[41]፣ ስማቸው የሴት አያታቸው አባት መጠሪያ ሲሆን፣ ቅድመ አያታቸው በጋብቻ ምክንያት ከሰቆጣ ወረዳ ወደ ድሃና ወረዳ ሄደዋል፡፡ ስለዚህ ስማቸው በጸመራ አካባቢ እንዳይጠፋና እንዲታወስ ሲባል ለእሳቸው በመጠሪያነት መሰጠቱን ከቤተሰቦቻቸው እንደ ተነገራቸው ገልጸውልኛል፡፡ ሌላዋ አበባ አያሌው የምትባለው ደግሞ ‹‹እኔ አበባ የተባልኩት (በአያቴ) የእናቴ እናት ስም ነው፡፡ እናቴ ስትነግረኝ፣ እናቷን በጣም ትወዳት ስለ ነበርና መልኬም እሷን ስለሚመስል የእሷን ስም አውጥተንልሻል ብላኛለች፡፡›› ብላለች፡፡ ሶስተኛዋ ደግሞ ‹‹ እናቴ ውቢት የሚለውን ስም ያወጣችልኝ፣ የእህቷን ስም ነው፡፡ ‹‹ስም ከመቃብር በላይ ይውላል፡፡›› እንደሚባለው ከጥሩና መጥፎ ድርጊት በተጨማሪ መጠሪያም እንዳይረሳ ለማድረግ ነው፡፡ ምክንያቱም ውቢት የምትባለው የእናቴ

[41] ከስያሜያቸው በስተቀር ሌላ መረጃ ስላልሰጡኝ በመረጃ አቀባይነት አልጠቀስኳቸውም፡፡

እህት ሟች ስለሆነች ማስታወሻዋ እንድሆን ነው ትላለች (ቡ.ቃ.1)፡፡ ወ/ሮ ጠጂም የሟች ስም ለልጅ የሚሰጥበትን ምክንያት አያይዘው እንዲህ ይገልጻሉ፤ ‹‹የሟች ስም ለልጅ የሚሰጠው ሟች ድምጹ ጠፍቶ እንዳይቀር እንጂ የሞተው እንዲመጣ ወይም ቀሪው ሟችን የሚያድነው ሆኖ አይደለም፤ ስሙ ግን ለልጅ ይሰጣል፤ ለምሳሌ ጠጂ የሚለው የእኔ ስም የአያቴ (የእናቴ እናት) ስም ነው አሉ፤ እኔ አላውቃቸውም፤ ስሜ ሲጠራ ግን ሌላው ዘመድ ደስ ይለዋል (ቂ.የ.መ.አ.1)፡፡

ወላጆች የሚወልዷቸው ልጆች በተከታታይ ሲሞቱባቸው ኖሮ የተወለደን/ችንም ልጅ በአብዛኛው ካሳ፣ ካሳወይ፣ ደባሽ፣ ደባሹ፣ ደብሳ፣ ደበሱ፣ አስረስ/አስረሱ በኽምጣኛ ሚሰው፣ ሚሰነ፣ ሚስረይ (ማስረሻ፣ መርሻ፣ የምታስረሳ) አወጣ፣ አወጡ፣ ይሏቸዋል፡፡ እናት ከገበያ ስትመለስ የምትወለድን/የሚወለድን ደግሞ ገብያነሽ/ገበያው፣ ቤተሰቦች ከመጥፎ ዘመን ወደ ጥሩ ዘመን ሲሸጋገሩ የተወለደን/የተወለደችንም መለሰ/መለሱ፣ ጥጋቡ/ጥጋቢቱ ሙላቱ፣ በቆላው ጣምተው(ጣፈጠ)፣ ጣምትረይ (ጣፈጡ)፣ በንኑ፣ በንኒ የተፈለገ፣ የተፈለገች ሳሩ/ሳርኒ ማሩ/ማሪቱ የመሳሰሉት የኽምጣኛ ስሞች የተዘወተሩ ናቸው፡፡ በዞኑ ለቀይ ልጅ ከሚሰጡ ስሞች መካከል ስንዴውና ስንዴወይ፣ ጸሀዩ፣ ጸሀይነሽ፣ ቡላ፣ ቡሊት የሚሉ ስሞች ይጠቀሳሉ፡፡

ቤተሰቦቻቸው ከሞቱ በኋላ ለሚወለዱም ባየ/ባዩሽ ይሏቸዋል፡፡ የዋግነህና የዋግነሽ የሚሉት ስሞች ደግሞ በአብዛኛው በዋግ ኽምራ ለሚወለዱ ወይም ሌላ ቦታ ቢወለዱም የዞኑ ተወላጅ መሆናቸውን ለመጥቀስ የሚሰጡ ስሞች ናቸው፡፡

ቀደም ሲል ልጅ እየሞተባቸው የተቸገሩ ወላጆች የሚወልዷቸውን ወንዶች ልጆች እንደ ሴት ‹‹አንቺ›› ተብለው እንዲጠሩ ይደረግ ነበር፡፡ ጸጉራቸውን በሚላጩበት ወቅትም፣ የእራሳቸውን ግማሽ ጸጉር ብቻ በመላጨት ግማሹ እንዲቀር ይደረግ ነበር፡፡ አሁንም ጎልቶ ባይታይም አልጠፋም፡፡ ይህ የሚደረገውም ወንድ ሆነው በሴት ሲጠሩና የእራሳቸውን ግማሽ ጸጉር መላጨት የሰሙና የተመለከቱ ሰዎች ለምንድን ነው? ብለው ጡር (ምክሃ) እንዲናገሩና የተንቋሸሹ ሆነው እንዲያድጉላቸው በማሰብ ነው (ቂ.የ.መ.አ.7)፡፡

በዋግ ኽምራ በስሞች መጨረሻ ላይ በብዛት -ወይ የሚል ድህረ-ግንድ ቅጥያ ተቀጥሎ ይገኛል፤ለአብነት ያህል እህትወይ፣ ጥሩወይ፣ የሺወይ፣ ወርቅወይ፣ እንወይ፣ ሙሉወይ

ወዘተ.፡፡ የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡ -ወይ በሌላ አካባቢ -ዬ ከሚለው ድህረ-ግንድ ቅጥያ ጋር ተመሳሳይ ፍች አለው፡፡ እህትዬ፣ ጋሽዬ፣ ጥሩዬ ወዘተ.እንደሚባለው፤ ከዚህም በተጨማሪ ቅጥያው አንድን ሰው በቁልምጫ ለመጥራትም ያገለግላል፤ለምሳሌ፣ አበራየ፣ ለማለት አበራወይ ይባላል፡፡ ይህ የቁልምጫ ቅጥያ ከዞኑና አካባቢው ያልተለመደ በመሆኑ ከዚህ ውጭ ያሉ ሰዎች ቅጥያው ያለባቸውን ስሞች በትክክል ሲጠሩ አይደመጡም፡፡

በቆላው አካባቢ ደግሞ ሕፃኑ/ሕፃኗ የመጀመሪያ ልጅ ከሆነ ወይም ከሆነች ስም የሚወጣው በተክቶ ማውጣት (በኽምጣኛ በስኳ) ነው፡፡ በዚህም መሰረት ወንድ ልጅ ከሆነ የአባት(የወንድ ወገን) ስም ይወጣለታል፤ አለማዊ ስሙም የክርስትና ስሙም የወንድ ወገኑ ስም ይሆናል፤ ሴት ከሆነች ደግሞ የ(እናት) ሴት ወገን ስም ይወጣላታል፤ የእሷ የአለማዊውም ሆነ የክርስትና ስሟ የእናቷ ወገን ስም ይሆናል፡፡ የሚሰጠው ስም በህይወት ያሉ ወይም የሌሉ ሰዎች ስም ሊሆን ይችላል፡፡ የዝቋላ ወረዳ ስጓን አስመልክተው ወ/ሮ ማርያሙ እንዲህ ይላሉ፡፡ ‹‹እኔ ክርስትና የተነሳሁት በግንቦተ ማርያም ስለሆነ ማርያሙ ተብያለሁ፡፡ ቤቴ (ቤተሰቦቼ) በሙሉ የመጀመሪያዎቹ ሴቶች ልጆች ማርያሙ ተብለዋል፡፡ ልጄም የመጀመሪያ ሴት ልጇን ማርያሙ ብላታለች፡፡ የአባቷን ስም ተክሌን ደግሞ ለመጀመሪያ ወንድ ልጇ ሰጥታለች (ቁ.የ.መ.አ.19)፡፡

ይህ አሰያየም የሚች ቤተሰብ ስምን ለልጅ ከመስጠት ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም፣ የእናት ወገን ስምን ለመጀመሪያ ሴት ልጅ፣ የአባት ወገን ስምን ደግሞ ለመጀመሪያ ወንድ ልጅ በመስጠት ይለያል፡፡

በአሁኑ ጊዜ ግን አልፎ አልፎ ከላይ የተገለጹትን የስያሜ መነሻዎች የማያጣቅሱ ዘመናዊ የሚባሉ እንደ አልማዝ አስቴር፣ መቅደስ ፣ብርቱካን ወዘተ.እና ኤርሚያስ፣ ናትናኤል፣ ዮሴፍ ወዘተ. የመሳሰሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ስሞች ለሕጻኑ/ኗ እየተሰጡ ነው፡፡[42]

### 4.4 በወሊድ ሥነ-ሥርዓት የባል ተሳትፎ

ቀደም ሲል በተመለከትኳቸው ወሊድ፣ ቅድመ-ወሊድና ድህረ ወሊድ ንኡሳን ርእሶች ተግባራት ላይ የባል ተሳትፎ የለም ማለት አይደለም፤ እንዲያውም እገዛውና ድጋፉ

[42] ከገጠር ወደ ከተማ ከሚገቡ ሰዎች መካከል አንዳንዶቹ ወላጆቻቸው ያወጡላቸው ስሞች የኋላ ቀርነት መግለጫ አድርገው በመውሰድ፣ በእነዚህና በመሳሰሉት ስሞች ሲቀይሩ ይስተዋላሉ፡፡

የሚጀምረው ነፍሰ-ጡሯ ሴት ከባድ ስራዎችን መስራት በሚያቅታት ወቅት ነው፡፡ በዚህ ወቅት ከቤት ውስጥ ሌላ ሴት ልጅ ከሌለች የቤት ውስጥ የሴት ስራ የሚባለውን ጭምር ያከናውናል፤ ይኸውም አህያ ካለው በአህያ ከሌለው ደግሞ በትከሻው ተሸክሞ ውሃ ከወንዝ ያመጣል፡፡ የማገዶ እንጨት ከጫካ የሚያመጣውም እሱ ነው፡፡ እህል ወደ ወፍጮ ቤት ወስዶም ያስፈጫል፡፡ ከመውለዷ በፊት ለወሊድ የሚያስፈልጉ ነገሮች እንዲዘጋጁም ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ አቅም ካለው ፍየሉንና ቅቤውን ጭምር ያቀራርባል፡፡

ሚስቱ ስትወልድም በቤት ውስጥ ሌላ የሚጠብቃት ሰው ከሌለ ወይም ጠባቂ ብትኖርም እሷ ወጣ ስትል፣ ቁጭ ብሎ ይጠብቃታል፡፡ ለክርስትና የሚያስፈልገውን የድግስ ወጭም ከወዲሁ አስቦበት ያዘጋጃል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## የዋግ ኽምራ ህብረተሰብ የጋብቻ ሥነ-ሥርዓት

በዚህ ምዕራፍ የሚገለጸው የዋግ ኽምራ ህብረተሰብ፣ የጋብቻ ሥነ-ሥርዓት አከናወን (አፈጻጸም) ነው፡፡ ለመንደርደሪያነትም በዞኑ የሚፈጸሙትን የጋብቻ አይነቶች አስቀድሜያለሁ፡፡

### 5.1 የጋብቻ አይነቶች

በዋግ ኽምራ በተለይም በገጠሩ በክብር መዝገብ ሹም ፊት ከሚፈጸመው በስተቀር ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ የጋብቻ ዓይነቶች ይፈጸማሉ፡፡ በብዛት የሚከናወነው ባህላዊ የጋብቻ ዓይነት ሲሆን፣ በሃይማኖታዊ የጋብቻ አይነት ጋብቻቸውን የሚፈጽሙት ግን የተወሰኑ ተጋቢዎች ሲሆኑ አብዛኛዎቹ ወንዶችም የቤተክርስቲያን አገልጋዮች ናቸው፡፡ ምልከታ ካካሄድኩባቸው አስር የሠርግ ሥነ-ሥርዓቶች መካከል ሃይማኖታዊ ጋብቻ የነበሩት ሶስት ብቻ ናቸው፡፡ ሰባቱ በባህላዊ የጋብቻ አይነት የተፈጸሙ ናቸው፡፡ በዚህ የጋብቻ አይነት ስር የሚካተቱ ንኡስ የጋብቻ አይነቶችም አሉ፤ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡፡

የመጀመሪያው የጋብቻ አይነት የሁለቱም ተጋቢዎች ሠርግ በአንድ ቀን ተደርጎ፣ የጋብቻ ውላቸውም(ሰማንያቸውም) በጎጆ ወይም በሲሶ ተብሎ በዚያው በሰርጉ እለት በዳስ ውስጥ የሚፈጸመው ነው፡፡ በጎጆ ማለት ሙሽራው ሙሽራዋን ወደ ቤተሰቦቹ ቤት ከወሰደ በኋላ፣ ከመልስ እንደ ተመለሱ የግላቸው ወደ ሆነ ቤት በመግባት፣ ራሳቸውን ችለው ጎጆ የሚወጡበት ነው፡፡ በሲሶ ማለት ደግሞ ሙሽራው ሙሽራዋን ወደ ቤተሰቦቹ ቤት ከወሰደ በኋላ፣ የግላቸው ቤት ኑሯቸው ጎጆ የሚወጡበት ሳይሆን ከሙሽራው ቤተሰቦች ጋር አብረው እየሰሩ ከርመው በሚቀጥለው ዓመት ወይም በሚቀጥሉት ወይም ዓመታት፣ ከተገኘው ምርት አንድ ሶስተኛውን በመካፈል ጎጆ የሚወጡበት ነው፡፡ በአንዳንድ አካባቢ (ለምሳሌ በደጋው አካባቢ) ይህ የሰማንያ አፈጻጸም **በአፈረ-ፈጪ** ወይም **በከራሚ** ይባላል፡፡ የስያሜው ምክንያትም ሙሽራዎቹ በተዳሩበት ዓመት ራሳቸውን ችለው ጎጆ አለመውጣታቸው ወይም የእርሻ ስራ እየሰሩ መክረማቸው ነው፡፡

ሁለተኛው የጋብቻ አይነት ደግሞ የምስል ጋብቻ፣ አግብተሽ/ህ ክረሚ/ክረም (በኽምጣኘ ዱውር ጫር) የሚባለው ነው፡፡ ይህ የጋብቻ አይነት ከሁለቱ ተጋቢዎች መካከል የአንዱ/የአንዷ ቤተሰብ ሠርግ ደግሶ፣ ለሌላኛው/ኛዋ ግን ሳይደገስለት/ሳይደገስላት በአንዱ/በአንዷ የሠርግ ዳስ ላይ፣ በጎጆ ወይም በሲሶ ተብሎ ሰማንያው የሚፈጸምበት ነው፤ ያልተደገሰለት ወይም ያልተደገሰላት ተጋቢም በሚቀጥለው ወይም ቤተሰቦች ለመደገስ የሚያስችል ምርት በሚያገኙበት ዓመት ይደገስላታል/ይደገስለታል፡፡ ይህም ከአንድ ዓመት በላይም ሊቆይ ስለሚችል፣ ሴቷ ሁለት ከወለደች በኋላም ሊከናወን የሚችል መሆኑን ነው ከገጠመኞቸው በመነሳት መረጃ አቀባዮቼ የገለጹልኝ፡፡ ከረጂም ጊዜ በኋላ ሠርግ መደገስ ያስፈለገውም፣ ሴቷን ሌሎች ሴቶች ‹‹ጥፍርሽን ያልተቆረጠሽ፡፡›› ብለው በየወንዙ እንዳይሰድቧት፣ ወንዱንም ‹‹ሰርግህን አልበላንም›› ብለው እንዳይሰደቡት ነው (ቁ.የ.መ.አ.8)፡፡

ለአብነት ያህል በ19/9/04 ምልከታ ባደረግሁበት የጋብቻ ሥነ-ሥርዓት ላይ፣ በሙሽራው፣ በአዳነ ግርማይ ቤት ምንም አይነት ድግስ አልነበረም፡፡የሠርግ ድግስ ሳይኖር ልጃቸው ጋብቻውን ለምን እንደ ፈጸመ አባቱ አቶ ግርማይ አስናቀ ሲገልጹ፣

> ልጂቱም ለአቅመ ሄዋን፣ እሱም ለአቅመ አዳም ስለደረሱና ልጁ በዚህ ዓመት ሲሶየን (ቤተሰብ ጋር ሆኖ ከሰራበት አንድ ሶስተኛውን) ስጠኝ፣ ራሴን መቻል አለብኝ ብሎ ሲሶውን ስለወሰደ ነው፡፡ እኔ ግን ዘንድሮ ለመደገስ አቅም ስለሌለኝ፣ ከእኔ ቤት ድግስ የለም፤ በሚስቱ ቤት ግን አለ፤ሰማንያውም ዛሬ በሴቷ ሠርግ ዳስ ላይ ይፈጸማል፡፡ የሱ ሠርግ የሚሆነው ግን በሚቀጥለው ዓመት ከታላቅ ወንድሙ፣ ከአቻሙ ጋር ነው ብለዋል (ቁ.የ. መ.አ.9)፡፡

አቻሙ ዲያቆንና አስረኛ ክፍልን ያጠናቀቀ ሲሆን፣ ጋብቻውን የፈጸመው ከሁለት ዓመት በፊት በ2002 ነው፡፡ ለሚስቱ የሠርግ ድግስ ተደግሶላት ለእሱ ግን ሳይደገስ፣ ሰማንያው በሲሶ ተብሎ፣ በ2003 ዓ.ም ባልና ሚስት ከወንድ ቤተሰብ ጋር አብረው ሲሰሩ ከከረሙ በኋላ ሲሷቸውን ወስደዋል፡፡ ከወላጆቹ ቤት አጠገብም አዳራሽ ሰርተዋል፤ ጎጆ ወጥተውም ለብቻቸው እየኖሩ ነው፤ ሚስቱን ወደ ቤተሰቦቹ ቤት ካመጣና ጎጆ ከወጣ ሶስት ዓመት ቢሆነውም የእሱ ሠርግ ግን በ2005 ዓ.ም ነው የሆነው፡፡ ስለዚህ የሁለቱ ወንድማማቾች የጋብቻ ዓይነት በአግብታችሁ ክረሙ (ድውር ጫር) የተፈጸመ ነው፡፡

እንዲሁም በ23/08/04 ዓ.ም ደስታ አሰፋ ወደ ተባለች ልጅ ሠርግ ምልከታና ቀረጻ ለማድረግ በምጓዝበት ወቅት፣ አንዲት በቅሎ ላይ የተቀመጠች ሙሽራ በሚዜዎች ሆታ

ሳትታጀብ፣ በሁለት ወጣት ወንዶች ቀዳሚነትና ተከታይነት ብቻ ስትጓዝ በመንገድ ላይ አግኝቻት ነበር፡፡ ሙሽራዋ ፊቷን በጥቁር ሻሽ ተሸፍናለች፣ ኩል ተኩላለች፤ ጸጉሯን ቁንጮና ጋሜ ሽሩባ ተሰርታለች፣ ቅቤም ተቀብታለች፡፡ እድሜዋም ከአስራ ሶስት የሚበልጥ አይመስልም፡፡‹‹ወንድ ሙሽራ ሳይኖር፣ ሴት ሙሽራ ብቻ ይዛችሁ የምትሄዱት ወዴት ነው? ለምንስ ነው?›› በማለት በቅሎ የሚስበውንና ሙሽራዋን ደግፎ የያዘውን ጠየቅሁት፡፡ እሱም ወደ ጳግብጂ[43] እየሄዱ መሆናቸውንና ሙሽራዋ የተዳረችውም በድውር ጫር መሆኑ ገለጸልኝ፡፡ በእለቱም ጀርባ ዮሀንስ ከሚባለው ቤተክርስቲያን ዲያቆን ከሆነው ባሏ ጋር ቆርበው (ጋብቻቸውን በቤተክርስቲያን ሥነ-ሥርዓት ፈጽመው) እሷ ወደ ቤቷ እየተመለሰች መሆኑን ነው የገለጹልኝ፡፡ የሙሽራው ሠርግ በሳምንቱ በ30/8/04 ዓ.ም ሆኗል፤ እሷንም ከቤቷ መጥቶ ይወስዳታል፤ የእሷ ሠርግ ግን ለከርሞ ነው የሚሆነው ብለውኛል፡፡ ስለዚህ የሴቷ የጋብቻ ዓይነት በአግብተሽ ክረሚ የሚከናወን ነው ማለት ነው፡፡

የሁለቱን ወንድማማቾች አግብታችሁ ክረሙ ተመልክተናል፡፡ ስለዚህ አግብተህ ክረም/ ክረሚ ለወንድም ለሴትም እንደሚያገለግል ከአብነቶቹ መረዳት እንችላለን፡፡

ሶስተኛው የጋብቻ ዓይነት ‹‹ድሃ ለድሃ ይዳራል በውሃ›› የሚባልለት ለማጫ የሚሆን ሀብት የሌላቸው ተጋቢዎች የሚጋቡበት ‹‹በማጭድና በመቆፈሪያ›› ጋብቻ ነው፡፡ሶስተኛው የጋብቻ ዓይነት ‹‹ድሃ ለድሃ ይዳራል በውሃ›› የሚባልለት ለማጫ የሚሆን ሀብት የሌላቸው ተጋቢዎች የሚጋቡበት ‹‹በማጭድና በመቆፈሪያ›› ጋብቻ ነው፡፡ አራተኛው የጋብቻ ዓይነት ደግሞ በድጋሚ የሚፈጸም ጋብቻ ነው፡፡ ይህም በተለያየ ምክንያት የመጀመሪያ ባሏን ወይም ሚስቱን የፈታች/የፈታ ወይም ሚስቱ የሞተችበት/ባሏ የሞተባት የሚፈጽሙት የጋብቻ ዓይነት ነው፡፡ በዚህ ጋብቻ ተጋቢዎች የሚኖራቸው መተዳደሪያ በሽማግሌዎች አማካይነት የሚገለጽ ሲሆን፣ ሴቷ ወደ ወንዱ ቤት ስትሄድ ዱቄትና በርበሬ የመሳሰሉትንና የቤት ቁሳቁሶችን ይዛ ትሄዳለች፡፡ የመረጃ አቀባየ አቶ ሞገስ አወጣ ሀብት የሌላቸው ሰዎችንና የድጋሚ ጋብቻ ዓይነቶችን አስመልክተው እንዲህ ይላሉ፤

> ሀብት የሌላቸው ተጋቢዎችና አግብታ የፈታች የጋብቻ ሁኔታ፣ ከመጀመሪያ የጋብቻ አይነት በጣም የተለየ ነው፤ ከወንድ ሂዳ የነበረች[44] ከሆነ በሽምግልናም ሆነ በታዳሚነት ወደ ሴቷ ቤት ሰው

[43] በሰቆጣ ወረዳ ከሚገኙት ቀበሌዎች መካከል አንዱ ነው፡፡

[44] ድንግል ያልሆነች ለማለት ሳይሆን አግብታ የፈታች ለማለት ነው፡፡

> በብዛት አይሄድም። የንስሃ አባትን ይዘው አስር ሰዎች ያክል፣ ይሄዳሉ፤ ሴትየይቱ ሁለት ማድጋ ያህል (አንድ ማድጋ ሃያ ጣሳ ወይም በግምት ሰላሳ ኪሎ የሚሆን ነው) ዱቄት ወይም ለዘር የሚሆን እህል ጭና ነው ወደ ባሏ ቤት የምትሄደው (ቁ.የ.መ.አ.15)።

ከእነዚህ የሰማንያ ጋብቻዎች ውጭ የተለያዩ ከሚስት ውጭ የሚከናወኑ የውሽምነት ተግባራት አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል አንዱ ቅምጥ ነው፡፡ ይህም አንድ ወንድ ቤት ውስጥ የሰማንያ ሚስት እያለው በሌሎች ቦታዎች ሌላ ሴት በቅምጥነት የሚይዝበት ነው፡፡ ሚስቶች ባሎቻቸው በየቦታው ቅምጥ እንዳላቸውና ማንነታቸውንም በሚገባ ያውቃሉ፡፡ እነዚህም ጣውንቶች ይባላሉ፡፡ ለጣውንትና ቅምጥ ለያዘ ባል ከሚገጠሙ ቃል ግጥሞች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

ቅምጧ - ፊቷን አትታጠብ መስታውት አታይ፣

የሷን ባል ቢቀሙት ኩነኔ አለው ወይ፡፡

ሚስትም- ፊቴን ባልታጠብ መስታውት ባላይ፣

የልጆቼን አባት ልትቀሚኝ ነወይ፡፡ በማለት መልስ ትሰጣለች፡፡

ሚስት ባሏ ወደ ቅምጡ እየሄደ ሲያስቸግራትም፣

አንተ ለሁሉ ሞትኩኝ ለሁሉ ስልም፣

ወፍጮ እንኳን ይለያል ሽርክትና ልም፡፡

በማለት ባሏን ታሽሙረዋለች (ቡ.ቃ.3)፡፡

በውይይት መድረኩ በአብርገሌ ወረዳ ተወካዮች እንደተገለጸው ‹‹የቅምጥ ጨረታ›› የሚባል አለ፤ ይህም አንድ ወንድ ለአንዲት ሴት ይህን ያህል ብር እሰጥሻለሁ፤ የእኔ ቅምጥ ሁኚ ሲላት፣ ሌላው ደግሞ ከእሱ የበለጠ ብር እሰጥሻለሁ እያለ የሚጫረትበት ነው፡፡ ለአብነት ያህል በመስከረም ወር/ 2006 ዓ.ም ጨረታው ከ5 ብር ተነስቶ ወደ 205 ብር ደርሶ እንደ ነበር የውይይቱ ተሳታፊዎች ገልጸዋል፡፡ ይህም በተጫራቾቹ መካከል ጠብ እንዲፈጠር ምክንያት እየሆነ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ የጭን ገረድ ነው፡፡

> የጭን ገረድ ሁለት ዓይነት ነው፡፡ አንደኛው አንድ ወንድ ከቤተሰቦች ጋር እየኖረ ከእጮኛው ውጭ የጭን ገረድ የሚይዝ አለ፡፡ሌላ ሲያገባም የጭን ገረዱ ድራው ኩላው ደሞዟን ይዛ ወጥታ

ትሄዳለች፡፡ ሌላው አንድ ሰው የልጆቹ እናት ስትሞትበት በቁርጥ (ደሞዟ በዓመት ይህን ያህል ብር ወይም እህል ተብሎ) የጭን ገረድ የሚይዝ አለ፡፡ ይህች ሴት ‹‹ከቤት እንደ ሚስት ከውጭ እንደ ገረድ›› የምትባል ናት፡፡ ከወለደች ግን የሰማንያ ሚስት ልትሆን የምትችልበት አጋጣሚም አለ (ቡ.ተ ው. 2፣3፣4 እና ው.መ)፡፡

ከላይ ከተዘረዘሩት የጋብቻ ዓይነቶች መካከል ከፍተኛ ቅድመ-ዝግጅት የሚጠይቁትና ቅደም ተከተላዊ ክዋኔ የሚበዛባቸው ሁለቱ ናቸው፡፡ እነዚህም በሁለቱም ተጋቢዎች ቤት የሠርግ ድግስ የሚደገስበት እና በአንዱ ወይም ባንዱ ቤት ብቻ ተደግሶ በአግብተህ/ሽ ክረም/ሚ ጋብቻ የሚፈጸምበት ናቸው፡፡ በእነዚህ የጋብቻ ዓይነቶች የሚፈጸምን ጋብቻ፣ ቅድመ-ሠርግ፣ ሠርግና ድህረ-ሠርግ በሚሉ ሶስት ንኡሳን ርእሶች እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡

## 5.2 ቅድመ-ሠርግ

በዋግ ኽምራ የሠርግ ሥነ-ሥርዓት ከመፈጸሙ አስቀድሞ በርካታ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ ከእነዚህ ተግባራት መካከል ዋና ዋናዎቹ በወደ ፊት ተጋቢዎች መካከል ያለውን የዝምድና ርቀት ማጣራት፣ የእጮኝነት ሂደትና አፈጻጸም፣ የሠርግ ቀን አወሳሰን (አቆራረጥ) እና የሠርግ ድግስ ዝግጅት ናቸው፡፡እነዚህን በቅደም ተከተል አንድ ባንድ ተመልክቻቸዋለሁ፡፡

### 5.2.1 የዝምድናን ርቀት ማጣራት

የጋብቻ ሁኔታ ከቦታ ቦታ ከማህበረሰብ ማህበረሰብ የተለያየ ቢሆንም፣ አንድ ሰው የትዳር ጓደኛ ልትሆን የምትችለውን ሴት የሚመርጥበት መስፈርት አለው፡፡ እንደ አብዛኛው የኢትዮጵያ የገጠሪቱ ክፍል ማህበረሰብ ሁሉ፣ በዋግ ኽምራም አሁንም ቢሆን የወደፊት የትዳር ጓደኛ ምርጫ የሚከናወነው በወደፊት ተጋቢዎች ሳይሆን (የተማሩ የሚባሉትንና የመንግስት ሰራተኛ የሆኑትን አይመለከትም) በወላጆች አማካይነት ነው፡፡ በመሆኑም የዝምድናን ማጣራት ስራ የሚያከናውነው ወላጅ ነው፡፡ አንዳንድ የወደፊት ተጋቢዎች፣ በግል ትውውቅና ምርጫ ወደ ጋብቻ ሊያመሩ ቢፈልጉ እንኳ፣ የተጋቢዎቹ ተገቢነት ወይም ትክክለኛ ምርጫ በቤተሰብ በኩል ስምምነት እንዲያገኝ ይደረጋል፣ የማን ልጅ

ነው? ናት? የሚለው የማጣራት ስራ ይከናወናል፡፡ ከሚጣሩት ነገሮች መካከል አንዱ ደግሞ በተጋቢዎቹ መካከል ዝምድና መኖር አለመኖር ነው፡፡

አንዲትን ልጅ ለአንድ ልጅ ለማጋባት የማጨት ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት በቅድሚያ የስጋ ዝምድና ርቀቱ ተጠንቶ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ ከመረጃ አቀባዮቼ እንደ ተገኘው መረጃ ከሆነ ቀደም ሲል በዋግ ኽምራ ለጋብቻ የስጋ ዝምድና ርቀት የሚቆጠረው እስከ አስራ ሁለት ቤት ነበር፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ተቀባይነት አግኝቶ ሲሰራበት የነበረው እስከ ሰባት ቤት ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን የዝምድና እርቀቱ ወደ ሶስትና አራት ቤት ወርዷል (ው.መ)፡፡

ለዚህ የመጀመሪያው ምክንያት ተጋቢዎች ቤተሰብ እንዲጠየቅ ሳያደርጉ እርስ በእርስ ተጠያይቀው በመጋባታቸው ነው፡፡ ማህበረሰቡ ግን እነዚህን ተጋቢዎች እያገለላቸው ነው፡፡ ይህንንም አቶ መኮነን እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡ ‹‹እኛም ከእነዚህ ዘመድ ጋር ተጋቢዎች ጋር በሀዘኑና በደስታው እንዳንገናኝ መስቀል መትተን እየተማማልን ነው፡፡ በህግ ግን የፈለጉትን ያግቡ እየተባለ ነው፡፡ እኛ ግን እስከምንሞት ድረስ ያባቶቻችንን አደራ መወጣት አለብን እያልን ነው›› (ቁ.የ.መ.አ.22)፡፡

ለጋብቻ የዝምድና ርቀት ወደ ታች መውረድ ሌላው በምክንያትነት የሚገለጸው የተጋቢዎች አለመተዋወቅ ነው፡፡ ምክንያቱም ቀደም ሲል የስጋ ዝምድና ያላቸው የቤተሰብ አባላት ቁጥራቸው የተወሰነ ስለነበር ሁሉም በየድግሱ እየተጠራሩ ይገባበዙ፤ የስጋ ዝምድና ያላቸው እርስ በእርስ ይተዋወቁ ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን የእያንዳንዱ ቤተሰብ አባላት ቁጥር እየጨመረ ስለሄደ፣ በመተዋወቂያነት በሚያገለግለው ድግስ ላይ የሚሳተፉት ሰዎች የተወሰኑ ናቸው፡፡ በዚህም የተነሳ ባለመተዋወቅ ምክንያት የቅርብ የስጋ ዝምድና ባላቸው ሰዎች መካከል ጋብቻ እየተፈጸመ ነው፡፡

ይህም አሳሳቢ እየሆነ መምጣቱን ነው፤ አቶ አካሉ ግርማይ የተባሉት የመረጃ አቀባዩ የገለጹልኝ፡፡ በአብነትነት የጠቀሱትም በራሳቸው ቤተሰብ ውስጥ በሶስት ቤት የዝምድና ርቀት መካከል የተካሄደውን ጋብቻ ነው፤ ስለዚህ ዘመድ ከዘመድ ጋር የመጋባትን ችግር ለመቅረፍ እንዲቻል የቤተሰብ መሰባሰቢያ ማህበር መመስረት (መቆርቆር) አስፈላጊ ነው ይላሉ፡፡ ይህም የቤተ-ዘመዱ ዋና ዋና ወይም የመጀመሪያ ተጠሪዎች (ግቺዎች)

እየተገናኙ፣ ማን ማንን ማግባትና አለማግባት እንዳለበት የመመካከር ስራ ለመስራት ያስችላል፤ የሥጋ ዝምድና ያላቸውንና የማይተዋወቁትን ሰዎችም ያስተዋውቃል፤ ያቀራርባል ይላሉ (ቂ.የ.መ.አ.11)፡፡

በዋግ ኽምራ ጋብቻ የማይፈጸመው የስጋ ዝምድና ባላቸው ሰዎች መካከል ብቻ አይደለም፡፡ በክርስትና አባትና እናት እና በንስሃ ልጅ ቤተሰቦች መካከልም ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው የክርስትና አባትና እናት እንደ ወላጅ አባትና እናት ይቆጠራሉ፤ በዞኑ ‹‹ሴት ከወለዱት ቀን የወለዱት ይበልጣል፡፡›› ይባላል፡፡ በሁለቱ ቤተሰቦች መካከል የስጋ ዝምድና ባይኖርም በክርስትና ልጅነትና አባትነት ወይም እናትነት ምክንያት ዝምድና አለ፤ በዘመድ መካከል ደግሞ ጋብቻ አይፈጸምም፡፡ ከዚህም ሌላ አልፎ አልፎ በንስሃ(የነፍስ) አባትና ልጅ መካከልም ጋብቻ አይፈጸምም፤ ምክንያቱም የንስሃ አባት፣ አባትነታቸው የእናት ወይም የአባት ብቻ ሳይሆን፤ ወደ ፊት ለጋብቻ የሚፈላለጉት ልጆችም ነው፡፡

ስለዚህ አንዲትን ሴት ለማጨት የዝምድናን ርቀት የማጣራት ስራ የሚከናወነው፣ የስጋ ዝምድና ብቻ ሳይሆን፣ በወደፊት ተጋቢዎች መካከል የንስሃ አባት እና የክርስትና አባትነትና እናትነት መኖር አለመኖርም ጭምር ነው፡፡

### 5.2.2 የማጨት ስርዓት

የማጨትን ስርዓት ሂደቱንና በስርዓቱ የሴቶች (የእናቶች) ተሳትፎ ምን እንደሚመስል እንደሚከተለው አቅርቤዋለሁ፡፡

#### 5.2.2.1 የማጨት ስርዓት ሂደት

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ‹‹የቤተሰብ ህግ›› አንቀጽ አንድ የቅድመ-ጋብቻ ትጭጭትን በተመለከተ፣

> ትጭጭት ለአካለ መጠን የደረሱ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ለወደፊት ትዳር እንደሚመሰርቱ በይፋ ገልጸውና የጋብቻ መፈጸሚያ ቀን ቆርጠው በመስማማት የእጮኛውና የእጮኛይቱ ቤተ-ዘመዶች ተወካዮችና ምስክሮቻቸው በታዛቢነት በተገኙበት ሥነ ስርዓት ፈቅደው የሚለዋወጡበት የራስ በራስ ቃል ኪዳን ነው፡፡

ቢ.ልም፣ ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው በዋግ ኽምራ የመተጫጨት ሂደት የሚከናወነው በወላጆች አማካይነት ነው፡፡

ስለዚህ የወንድ ቤተስብ የስጋ ዝምድና እንደሌላት ወደ ተጠቆመች፣ ለጋብቻ ወደ ተመረጠችውና ወደምትፈለገው ሴት ቤተሰብ ሽማግሌዎችን በመላክ ፈቃደኝነታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ አንድ አባት ለልጁ ሚስት ልትሆን የምትችለውን ልጅ ፍለጋና ጥቆማ የሚያከናወነው ደግሞ የወደ ፊት ተጋቢዎች ሳይወለዱ(ሳይጸነሱም) ቃል በመግባትና ከተወለዱ በኋላም ለአቅመ ሔዋን ሳይደርሱ በሕፃንነታቸው ነው፡፡

ቃል መግባት(በኽምጣኛ ቃል ጥወነው) ይባላል፤ ይህም የወደፊት ተጋቢዎቹ ወላጆች፣ ሀብታም ወይም ጓደኛሞች ከሆኑ፣ ልጅቷ ገና ሳትወለድ ወይም ሳትጸነስ "አንተ ወንድ ከወለድክ፣ እኔም ሴት ከወለድኩ ልጄን ለልጅህ"፤ ወይም ያንዱ ሚስት ነፍሰ ጡር ከሆነች፣ ወንድ ልጅ ያለው ጓደኛ "ሚስትህ ሴት ከወለደች ለልጄ ትሰጠኛለህ።" ይባባሉና ቃል ይገባባሉ። ቃል የተገባቡት ወላጆች ቢሞቱም እንኳ፣ ይህ ቃል በሚስቶቻቸው አማካይነት ተከብሮና ተጠብቆ ተግባራዊ ይሆናል። ባሁኑ ጊዜ ቃል ገብቶ ልጆችን ማሳጨት እየቀነሰ ቢሆንም ከመረጃ አቀባዮቼ ያገኘሁት መረጃ የሚያመለክተው ግን ሙሉ በሙሉ እንዳልቀረ ነው (ቡ.ተ.ው.3)፡፡

ሁለተኛው የሚስት መፈለጊያ መንገድ ደግሞ፣ ወንድ ልጅ ያለው አባት ለልጁ የምትሆነውን ሴት በመፈለግና በመጠቆም የሚከናወን ነው፡፡ ፍለጋውና ጥቆማው የሚከናወነውም በቤተሰብ አማካይነት ነው፡፡ የወንድ ወላጅ አንድ ዘመድ በሚኖርበት አካባቢና በሌላ አካባቢ በጠቋሚዎች አማካይነት ያጠያይቃል፡፡ ጠቋሚውም ልጅቷ ለሌላ አለመታጨቷንና የወላጆቿን የዘር ሀረግ፣ ሀብት ወዘተ. ያጠናል፡፡ ስለ እሷ እና ስለቤተሰቦቿ ሁኔታ በስለላ ያገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግም የትዳር ጓደኛ ለሚፈለግለት ልጅ ሚስት ልትሆን እንደምትችል ያመነባትን ልጅ፣ ‹‹ያልታጨች የእከሌ ልጅ አለች ፡፡›› ብሎ ለወንድ ቤተሰብ ይጠቁማል፡፡

የወንድ ቤተሰብም ቃል የተገባለትንም ሆነ የተጠቆመችውን ሴት ለማግኘት የቤተሰቦቿን ፈቃደኝነት የማረጋገጥ ስራውን ይቀጥላል፤ ስለዚህ ሽማግሌዎችን በመላክ የጋብቻ ፍላጎት ጥያቄውን ያቀርባል፡፡ በሽማግሌነት የሚመረጡትም ሰዎች፣ በአካባቢው ተቀባይነት

የሚኖሩቻቸው፣ የሚከበሩ፣ የሚፈሩ እና የሴትን ቤተሰብ ያሳምናሉ ተብለው የሚታመንባቸው ናቸው፡፡ ይህም የሚሆነው  አስቀድሞ ቃል ለተገባለት ወዲያው እንደ ተወለደች ሲሆን፤ በጥቆማ ለታወቀችው ደግሞ፣ በሽማግሌነት የሚሄዱት ሰዎች ተመካክረው አመቺ ጊዜ በማመቻቸት ነው፡፡ የሽምግልና ወራቱና ቀናቱም አብዛኛውን ጊዜ አርሶ አደሩ በብዛት በእርሻ ስራ የማይጠመድባቸው ወራት ሲሆኑ፣ ቀናቱ ደግሞ፣ ሰኞ፣ ማክሰኞና ሐሙስ ናቸው፡፡ ረቡእ እና አርብ የጾም ቀናት፣ ቅዳሜና እሁድ ደግሞ በዓላት በመሆናቸው ሽማግሌዎች ለጋብቻ ጥያቄ ወደ ሴቷ ቤት አይሄዱም (ቡ.ተ.ው.4)፡፡ የሽምግልና ሂደቱም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

በመጀመሪያ ሶስት አማጭ(በኽምጣኘ ዘርና) (አንዱ የነፍስ አባት ወይም ቄስ መሆን አለበት)፣ የልጁ አባትና አንድ የቅርብ ዘመድ ሽማግሌዎች (በኽምጣኘ ሽመቅል) አማጭ  ሆነው በጧት ተነስተው ወደ ሴቷ ቤተሰቦች ቤት ይሄዳሉ፡፡

ከዚህ በተለየ መልኩ ደግሞ በአሁኑ ዘመን የወደፊት ተጋቢዎች፣ በተጋቢዎች የእርስ በርስ ትውውቅ በዘመናዊ መንገድ የሚጋቡ ቢኖሩም፣ ወደ የሴቷ ቤተሰብ፣ ገጠር ድረስ ሽማግሌዎችን  መላክና የቤተሰብን ፈቃደኝነት ማረጋገጥ የግድ ይሆናል፡፡ ለአብነት ያህል በ14/8/2004 ዓ.ም የጋብቻ ሥነ-ሥርዓታቸውን በቤተክርስቲያን በስርዓተ-ተክሊል ፈጽመው ሰርጋቸውን በሳምንቱ በ21/8/04 ዓ.ም ያከናወኑትን ወ/ሪት አደነቁሽ ግዛትንና ዲያቆን ነጋሽ ዳምጤን መጥቀስ ይቻላል፡፡ አደነቁሽ እንደ ገለጸችልኝ ከሆነ ሁለቱም ተጋቢዎች በግላቸው ከተዋወቁ ከአንድ ዓመት በላይ ሆኗቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ወደ ጋብቻ ከማምራታቸው በፊት ገጠር ወደሚገኙት ቤተሰቦቿ ሽማግሌዎች ተልከው  ፈቃደኝነታቸው ተጠይቋል፡፡ እነሱም ‹‹አንቺ የወደድሽው፣ የመረጥሽው  ይሁን አሉ እንጂ እምቢ አላሉም፤ ስለዚህ ጋብቻችንን የፈጸምነው በቤተሰቦቼ ፈቃድ ነው፤ ያለ እነሱ ፈቃድ  የሆነ ነገር የለም፡፡›› ብላለች (ቁ.ያ.መ.አ.1)፡፡

ሽማግሌዎቹ ከሴቷ ቤተሰብ ቅጥር ግቢ እንደ ደረሱ፣ ‹‹እዚህ ቤት›› በማለት ድምጽ ያሰማሉ፡፡ የሴቷ ቤተሰቦችም ውሻ ያላቸው ከሆነ፣ ውሻው ሲጮህ፣ ከሌላቸውም የሽማግሌዎቹን ድምጽ በመስማት አባት (ሟች ከሆነም እንጀራ አባት፣ አሳዳጊ አጎት፣ አያት ወይም ታላቅ ወንድም) ‹‹ማን ነው?›› በማለት ከቤት ወጥቶ ይጠይቃል። ‹‹ማን ነው?›› ማለቱ፣ የመጣው ሰው ማን እንደ ሆነ ያላወቀ ለመምሰል ነው እንጂ፣ ጠቋሚው ሽማግሌዎቹ

ለጥየቃ የሚመጡበትን ቀን አስቀድሞ አሳውቋቸው፤ ወደ ሌላ ቦታ ሳይንቀሳቀሱ ተዘጋጅተው በመጠባበቅ ላይ ናቸው፡፡

ሽማግሌዎቹም በሴቷ ወላጆች ቤት ደጃፍ እንደ ደረሱ፣ ልብሳቸውን በትእምርተ መስቀል አጣፍተው በመልበስ ሶስት ጊዜ ፣ ‹‹እንደምን አደራችሁ? እንደምን አደራችሁ? እንደምን አደራችሁ?›› በኽምጣኛም "እው ግሪኍ? እው ግሪኍ? እው ግሪኍ?" ይላሉ። የሴት አባትም‹‹እግዚአብሄር ይመስገን፤ በኽምጣኛም እምዜናና›› በማለት መልስ ይሰጣቸዋል፡፡ ሰላምታ እንደ ተለዋወጡም፣ የሴቷ አባት ውጭ ላይ ምንጣፍ አንጥፎ፣ ሽማግሌዎቹን ‹‹ተቀመጡ፤›› ይላቸዋል፤ ሽማግሌዎቹ ግን የጋብቻ ዝምድና መፈለጋቸውን ተናግረውና ተጠያቂው እሺ እስካላላቸው ድረስ አይቀመጡም፤ እንዲያውም አደግድገው በመቆምና ትህትና በተላበሰ ቅላጼ፣ እንዲህ ብለው ጥያቄ ያቀርባሉ፤ ‹‹እኛ የመጣነው እናንተን ፈልገን፣ ከእናንተ በረት፣ ከእናንተ ፍግ ልንቀመጥ፣ ልንወድቅ ብለን ነው፤ በኽምጣኛ ‹‹ ክትዛረይን ሊቭነ ተርኑን ፡፡›› ይላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ልጅቷ ያልታጨች ብትሆንም እንኳ፣ አባት ወይም ተጠያቂው ባንድ ጊዜ ‹‹እሺ ሰጥቻለሁ›› አይልም፡፡ የሚጠየቅለትን ልጅና የቤተሰቦቹን ሁኔታ ለመመርመር፣ ለማጣራትና ለክብር ሲባል ‹‹ለሰው ሰጥተናል፤ ተቀድማችኋል›› በማለት መልስ ይሰጣል፤ ሽማግሌዎቹም ከሴት ወገኖች ለመጀመሪያ ጥያቄያቸው ለሌላ ሰጥተናል የሚል መልስ ያገኙት፣ በቀጥታ ሰጥተናችኋል ላለማለት መሆኑን ስለሚያውቁ ‹‹የእናንተ ልጅ የሺህ ወገን እንደ ሆነች እናውቃለን፤ ለሰው ከሰጣችሁም እኛንም እጣ ጣሉልን፤ እኛንም ከእጣው አስገቡታችሁ ቁጠሩን፡፡›› በማለት የተማጽኖና የልመና ቃላቸውን አሰምተው ይመለሳሉ።

በዚህ ጊዜ ደንብ ስለሆነ፣ በውጭ አነጋግረው፣ ደጅ ረግጠው ይመለሳሉ እንጂ፣ ወደ ቤት አይገቡም፤ የመጀመሪያው የሽማግሌዎች ጉዞም፣ **ደጅ መርገጫ** (በኽምጣኛ ቢዘ ደደነው) ይባላል።

ሽማግሌዎቹ ለመጀመሪያ ጥያቄያቸው ‹‹ተቀድማችኋል፡፡›› ቢባሉም አሉታዊ መልስ ተሰጥቶናል ብለው ተስፋ አይቆርጡም፤ ባንድ ጉዞ በተከናወነ ጥያቄ አያቆሙም፡፡ በድጋሚ ወደ ሴቷ ቤተሰቦች ቤት ተመልሰው ይሄዱና ጥያቄያቸውን ያቀርባሉ። የሴቷ ቤተሰቦችም መስጠት ቢፈልጉም በሁለተኛውም፣ ‹‹እስቲ እንግዲህ መቼም ምክሩን ለቤተሰቦቻችን ነግረናልና፣ ከነሱ መልስ እንጠብቅ፣ ተመካክረን እንቆያለን›› ብለው

አሁንም ለሶስተኛ ጊዜ በመቅጠር ሽማግሌዎቹን ይመልሷቸዋል። ይህም ለመጨረሻው ደጅ ጥናት ቀጠሮ የሚሰጥበት ነውና ቀን መቅጠሪያ(በሽምጣኛ ግርጼ ቻጽረነው) ይባላል፡፡

ልጅቷ ለሌላ ሰው ቃል ያልተገባላት ከሆነና ቤተሰቦቿ መስጠት ከፈለጉ እሺ ከማለታቸው በፊት፣ በወንዱ ቤተሰብ ሁኔታ ላይ ጥናት ያካሂዳሉ። ጥናቱም በሚከተሉት ነገሮች ላይ ትኩረት ያደርጋል፤ የወንዱ ቤተሰብ ከእነሱ ጋር በሀብት አቻ መሆን አለመሆኑን፣ የወንድ ቤተሰቦች ከሴቷ ቤተሰቦች ጋር ደም ያልተቃቡ መሆናቸውን (ባላንጋራ አለመሆናቸውን) በሁለቱ ቤተሰቦች መካከል የቆየ ጸብ አለመኖሩን፣ እከሌ በልቶኛል[45]፣ እከሌ በድሎኛል እና በዘር ሀረጉ የማን ወገን እንደሆነ ይጣራል፡፡

ቀደም ሲል ‹‹የሸክላ ሰሪ ወይም የቀጥቃጭ ዘር ያልሆነና አጥንቱ የጠራ›› የሚለውም ይጣራ ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ ይህ መስፈርት ሙሉ በሙሉ ባይጠፋም የጎላ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ቀደም ሲል በዞኑ ለተወሰነ የህብረተሰብ ክፍል ተለይቶ ይሰጥ የነበረው የእደ ጥበብ ስራ በአሁኑ ጊዜ ሌሎችም እየተሳተፉበት ነው፡፡ ለአብነት ያህል በሰቆጣ ወረዳ ስሬል በሚባለው ቦታ ይኖሩ የነበሩት፣ በሸክላና በቅጥቀጣ ስራ ይተዳደሩ የነበሩት፣ በአካባቢው አጠራር ‹‹ካይላ›› ይባሉ የነበሩት የእደ-ጥበብ ባለሙያዎች፣ በ1977 ዓ.ም ወደ እስራኤል በመሄዳቸው፣ የሸክላና የቅጥቀጣ ስራውን ተረክበው በማከናወን ላይ የሚገኙት ‹‹ ጨዋ ›› ይባሉ የነበሩት ሰዎች ናቸው፡፡

የዝምድና ማጣራት ስራው እርግጠኛ ይሆን ዘንድም፣ እያት ካለ ለአያት ይነገርና ጥናቱ ይቀጥላል። ከዚህ የማጣራት ሂደት በኋላ የሴት ቤተሰቦች ለጋብቻ የሚከለክል ነገር ካጋጠማቸው ወደ ሌላ አካል ሳይመሯቸው፣ እራሳቸው ‹‹ተቀድማችኋል፤ ለሌላ ሰጥተናታል›› በማለት ቁርጠኛ የሆነ አሉታዊ መልሳቸውን አጠናክረው ገልጸው ይመልሷቸዋል፡፡ ለጋብቻ የሚከለክል ነገር ካላጋጠማቸውና ለመስጠት ፈቃደኛ ከሆኑ ግን፣ በሁለተኛው ሽማግሌዎቹን ‹‹ከእኔ በላይ ወደ አለው ወደ እከሌ ሂዱና ጠይቁ፡፡››ይሏቸዋል (ቡ.ተ.ው.2)።

[45] ከዚህ በፊት በክርክር ጉዳይ የወሰደው ገንዘብ አለና ይመለስልኝ ማለት ነው ፡፡

ሽማግሌዎቹም በሴቷ ቤተሰቦች ወደ ተጠቆሙበት ዘመድ ቤት የሚሄዱበትን ቀን ተነጋግረው ሂደው ይጠይቃሉ፤ ከእነሱ ያገኙትን መልስም ወደ ወላጆቿ ቤት በመሄድ ይገልጻሉ፡፡ መልሳቸው አዎንታዊ ከሆነ ወላጆችም ‹‹ሰጥተናል፡፡›› ይላሉ፡፡ ለእጮኝነት ጥያቄው ከሴቷ ቤተሰቦች ለሽማግሌዎቹ የእሽታ መልስ የሚሰጠው፣ ቢያንስ በሶስተኛው ጉዟቸው ነው ማለት ነው፡፡ ይህም ቀን መቁረጫ (በኽምጣኛ ግርዬ ቋርጸነው) ይባላል፡፡ ምክንያቱም እርግጠኛው መልስ የሚሰጥበትና የሽማግሌዎች ምልልስ የሚያቆምበት እለት ነው፡፡

የሽማግሌዎች የመመላለስ ድግግሞሽ እንደ ተጠያቂው ሰው ፈቃደኝነት የሚወሰን ነው፡፡ ይህንንም መቶ አለቃ ወዳጆ አደራ ሲገልጹ እንደሚከተለው ብለዋል፡፡

> የሽምግልና ቀናትን መጠን በሚመለከት ይህን ያህል ቀን ይጨርሳል፤ ብሎ መናገር ይከብዳል፤ምክንያቱም እናትና አባት ‹‹ዝምድና ጥብቅ ነው››፤ እናጣራ›› እያሉ፣ ብዙ ጊዜ ያመላልሱናል፡፡ በአንደኛው እሺ እንደማይባል እናውቃለን፤ በሁለተኛውም ወደ አያት ወይም ወንድምና እህት ሂዱ ተብለን ከሆነም፣ ወደ እነሱ ሄደን ጥያቄያችንን እናቀርባለን፤ እነሱ እሺ ካሉን ተመልሰን ወደ እናትና አባት በመሄድ፣ ‹በዚህም በዚያም ጠይቀናል፤ ለግቢ የሚከለክል ነገር የለም፤ልጃችንን እንሰጣለን፤ ብለዋል› እንላለን፡፡ አንዳንዶች ግን ‹‹ግቢውን አንፈልግም፤›› ብለው ይከለክሉናል፡፡ እኛም ምክንያቱን እንዲገልጹልን አጥብቀን እንይዛቸዋለን፡፡ ከወገን ከዘመድ ጠብ እንዳላቸውም እንዲነግሩን እንጠይቃቸዋለን፤ንክኪ አለ ካሉንም መጀመሪያ እንዲታረቁ እናደርጋለን፡፡ ከዚያ በኋላ የሴቷ ወላጆችም፣‹‹እነሱን ካስታረቃችሁማ እኛም ጥተናል›› ይላሉ፡፡ እኛም፣ ‹‹ቃል ግቡልን፡፡›› እንላቸዋለን፡፡ እነሱም፣ እንደሚሰጡን ፈቃደኝነታቸውን ቃል ይገቡልናል (ቁ.የ.መ.አ.18)፡፡

በዚህ ጊዜ የሁለቱም ቤተሰቦች፣ ለሽማግሌዎቹ መጠነኛ ግብዣ ያደርጉላቸዋል። በመጀመሪያ፣ ለሽምግልናው ወይም ለአማጭነቱ አዎንታዊ መልስ ለመስጠታቸው በምልክትነት የሚያገለግለውን የተጋበዙልን ጥያቄ ለሽማግሌዎች የሚያቀርቡት የሴት ቤተሰቦች ናቸው፤ ‹‹ተቀመጡ፤ እንጀራ ብሉ፡፡›› ይሏቸዋል፡፡ ሽማግሌዎቹም በደስታ ግብዣቸውን ይቀበላሉ፤ ከተስተናገዱ በኋላም ምስጋናቸውን በመለገስና እጅ በመንሳት ተሰናብተው ጉዞ ይጀምራሉ፤ በዚህ ጊዜ በሴቷ ወላጆች የተወሰነ እርቀት ይሸኛሉ ፤ ይህም የሴት ወገን ለሽማግሌዎቹ ያላቸውን አክብሮት ለመግለጽ ነው፡፡ በመቀጠልም ሽማግሌዎቹ ወደ ወንድ ቤተሰብ ቤት በመሄድ፣ ከሴት ወገን ያገኙትን የእሽታ መልስ ያበስራሉ፡፡

የወንድ ቤተሰቦችም በተገኘው መልስ ተደስተው፣ ይጋብዟቸዋል፤ በአካባቢው አገላለጽ እህል ውሃ ይሏቸዋል (ቡ.ተ.ው 4)፡፡

ቀደም ሲል ከተመለከትናቸው ‹‹ልጅህን ለልጄ›› እና በጥቆማ ከሚከናወን መተጫጨት በተጨማሪ ዝምድናን ለማጠናከር ሲባል፣ በአያት ቅድመ አያት ፍቅር መነሻነትም መተጫጨት ይፈጸማል፡፡ ለአብነት ያህል አቶ ደሳለኝ አማረ ሲገልጹ፣

> የ10ኛ ክፍል ተማሪ የሆነችውና በየካቲት አንድ ቀን 2004 ዓ.ም ጋብቻዋን የፈጸመችው ልጄ አለምጸሀይ ደሳለኝ የታጨችው በ1987 ዓ.ም የሶስት ዓመት ልጅ እያለች ነው፡፡ በዚህ እድሜ እንድትታጭ ምክንያት የሆነውም፣ ቀደም ሲል የእኔና የልጁ ወላጆች በነበራቸው ፍቅር ነው፡፡ ስለዚህ በሁለታችን ቤተሰቦች መካከል ቤተሰባዊ ግንኙነት ስለነበር ያንን ለማጠናከር ስንል ጋብቻው እንዲመሰረት አደረግን (ቂ.የ.መ.አ.5) ብለዋል፡፡

ይሁን እንጂ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኝ ቤተሰብ ያላቸው ሴት ልጆች ግን በሕፃንነታቸው አይታጩም፡፡ ይህንንም ወ/ሮ ትንሳኤ እንደሚከተለው ይገልጻሉ፤‹‹ልጄ የድሃ ልጅ (ኮማሪ፣ ጠላ ሻጭ በመሆኔ) በመሆኗ በልጅነቷ አልታጨችም፣ ዘንድሮ በ19 ዓመቷ ታጨች ወዲያው እንደኔ ዲቃላ ወላጅ እንዳትሆን በማለት ዳርኳት፣ ስለዚህ በእጮኝነትና በሠርግ ጊዜ መካከል ረጂም ጊዜ አልነበረም፡፡››

ሽማግሌዎች ለማጨት ወደ ሴቷ ቤተሰቦች የሚሄዱት በሁሉም ቀናት አይደለም፤ ቀናቱ የተመረጡ ናቸው፤ ምርጫውም በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትን እምነት የጾምና የብሎት ቀናት የሚባሉትን በመለየት ነው፡፡ ስለዚህ ቀናትን በመምረጥ በጾም አርብና እሮብ አይሄዱም፡፡ የሚሄዱት ሰኞ፣ ማክሰኞና ሐሙስ ነው፡፡ እነዚህ ቀናት ደግሞ ወራቱ የጾም ካልሆነ የብሎት ቀናት ናቸው፡፡ ቅዳሜና እሁድ ደግሞ በዓላት በመሆናቸው ሽማግሌዎች ለጋብቻ ጥያቄ ወደ ሴቷ ቤት አይሄዱም፡፡

ለሽምግልና የሚሄዱት ሰዎችም ሶስት ናቸው፤ ለምን ሶስት እንደሆኑ የመረጃ አቀባየ የሰጡት መልስ ስላሴዎች ሶስት ስለሆኑ ነው የሚል ነው (ቂ.የ.መ.አ.4)፡፡ የሃይማኖት አባቶችም የሽማግሌዎቹን ሶስት መሆን እንደሚከተለው ይገልጻሉ፤

የመጀመሪያው ምክንያት፣ መጽሀፍ እንደሚለው ማንኛውም ነገር ሊጸና የሚችለው በሶስት ሽማግሌዎች ነው፡፡ እነዚህ ሽምግሌዎች አጭተውና አስፈቅደው የሚያበቁ ብቻ ሳይሆኑ እስከ መጨረሻው ሴቷንና ወንዱን ጋብቻ እንዲመሰርቱ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ሁለተኛው ምስጢር ደግሞ፣ በሃይማኖት እግዚአብሔር አንድም ሶስትም ነው፡፡ ማንኛውም ፍጡር ግን አንድም ሶስትም መሆን አይችልም፤ ከሚለው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና እሳቤ የመነጨ ነው፡፡ ከሶስቱ ሽማግሌዎች ጋር እግዚአብሄር አለ ለማለት ነው፡፡ በሌላ መልኩ ኦሪት ዘፍጥረት ም.14-18፣ ስላሴ ወደ አብርሐም ቤት በገቡበት ጊዜ አንድ ጊዜ ሶስት፣ አንድ ጊዜ ደግሞ አንድ ሆነው ያነጋግሩት ነበር (ቁ.የ.መ.አ. 2 እና13)፡፡

ለእጮኝነት ጥያቄ ወደ ሴቷ ቤተሰብ ቤት የሚሄዱት ሽማግሌዎች ጋቢያቸውን በመስቀል ቅርጽ አጣጥለው መልበሳቸው፣ ለሴት አባት በሶስቱ ስላሴዎች ሶስት ጊዜ ሰላምታ መስጠታቸው፣ ሚዜዎችም በሙሽራዋ ዳስ ውስጥ የማጫ እና የስጦታ ጥያቄ ሲያቀርቡ መስቀለኛ ለብሰው ሶስት ጊዜ ሰላምታ መስጠታቸውም ቀደም ሲል ከተጠቀሰው ሶስቱ ስላሴዎች ጋር የተያያዘ ነው፡፡

የወንድየው ቤተሰቦች ልጅቷ ከተሰጠቻቸው በኋላ የሴት ቤተሰቦችን ቤት የማየት (በኽምጣኛ ቿን ቃለነው) ዝግጅት ያደርጋሉ፡፡ ይህም የቅርብ ቤተሰብ የሚሳተፍበት ነው፡፡ ወደ ሴቷ ቤተሰብ ቤት የሚሄዱት ሰዎች መጠናቸው ሊለያይ ቢችልም፣ አነስተኛ የሚባለው ግን ሰባት ነው፡፡ ይዘው የሚሄዱትም እንደ አቅማቸው ይወሰናል፤ እስከ ሁለት ወይም ሶስት መሶብ ትኩሴ፣ ሁለት ሞሰብ እንጀራ ሊሆን ይችላል፡፡ ወደ ሴቷ ቤተሰብ ቤት ሄደውም ለሁለት ቀናት ያህል እየበሉና እየጠጡ እርስ በእርሳቸው እየተዋወቁ ቆይተው ይመለሳሉ፡፡ ይህ የሴት ቤተሰቦችን ቤት የማየት ጉዞም **መተዋወቂያ**(በኽምጣኛ **እርችሽተነ**) ይባላል (ቁ.የ.መ.አ.15 እና ቡ.ተ.ው.2)፡፡

ከእጮኝነት እስከ ሠርግ ባለው ጊዜ ውስጥም፣ ሁለቱ የወደፊት ተጋቢ ቤተሰቦች በክፉም ሆነ በደጉ ይጠያየቃሉ፡፡ ያንዱ ቤተሰብ ዘመድ ሲሞት፣ ሌላው ለዘመዶቹ በመንገር የአማች ተብሎ በርከት ያለ እንጀራ ይወስዳል፤ የሴቷ ወይም የወንዱ እናት ስትወልድም፣ እንደ አቅም ፍየል፣ ትኩሴና ዳቦ በመያዝ ይጠያየቃሉ፡፡ በተለይም በአካባቢው ጎልቶ በሚታየው የክብረ በዓል ድግስ ወቅት የሴቷ ወገን በወንዱ ወገን፣ የወንዱ ወገን ደግሞ በሴቷ ወገን እየተጠራሩ ይበላሉ፤ ይጠጣሉ፤ ይጠያየቃሉ (ቡ.ተ. ው.3 እና4)፡፡

እሬጭኝነቱ የተከናወነው በሕፃንነቷ ከሆነ ልጂቱ ከፍ እንዳለች ወይም እግር ተክላ መሄድ ከጀመረች የወንድ ወገኖች የእሬጭኝነት ምልክት የሆነውን ልብስ፣ ጫማ፣ መሀረም(ባውንድ) ወደ ሴቷ ቤት ይወስዳሉ፡፡ ከዚያም ማርዳ[46] ያመጣሉ፡፡ማርዳ የሁለት ነገሮች ቅልቅል ነው፤ ከብር ወይም ከኒኬል የሚሰራው የጠልሰም እና የድባ ፡፡ ከብር ወይም ከኒኬል የሚሰራው ጠልሰም ሶስት አይነት ቅርጽ አለው፡፡ የሶስት ማእዘን፣ የክብ፣ እና የአራት ማዕዘን፡፡ ጠልሰሙና ድባው በጥቁር ለስላሳ የሃር ክር(ካሉስ) የሚደረደር ሲሆን፣ ከመሃልም ትልቅ የቀራኒዮ መስቀል ይቀላቀልበታል፤ ከዚህም በተጨማሪ ከብር የተሰራ ክብ የጆሮ ጌጥ(አላድ) አብሮ ይኖራል፡፡በማርዳው ውስጥ የሚገኘው የጠልሰም መጠን እንደ የወንድ ቤተሰብ አቅም የሚወሰን ቢሆንም፣ ዝቅተኛው ግን 30 ነው፡፡ ይህም ከእያንዳንዱ ቅርጽ አስር አስር ሲሆን፣ ድባውም 30 ይሆናል፡፡ ለአብነት ያህል በ23/5/05 ጸመራ በተባለ ቦታ ላይ ያገኘኋት ልጅ ያሰረችው ማርዳ መጠኑ 54 ነው፡፡ ስድስቱ በቆይታ መጥፋቱን የልጅቷ እናት ነግራኛለች፡፡



**ማርዳ ያሰረች ልጅ (ፎቶ በአፀደ ተፈራ)**

[46] የጌጥ ስም፡፡ እንደ ዶቃ በልጆች አንገት የሚደረግ(ደስታ፣1962፣805)

በስጦታው ወቅት የሴት ወገንም (እናትና አባት) እነዚህን ነገሮች በስነ ስርዓት ይቀበላሉ፤ ልጂቱም ትቀርብና እንድታጌጥበት ይደረጋል፤ በዚህም አጋጣሚ ለመጀመሪያ ጊዜ አማቾቿን ታያቸዋለች፡፡ እነሱም መርቀዋት ይሄዳሉ።

አማቾቿ የወሰዱላትን ልብስ መልበስና ማርዳ ማሰር ስትጀምርም ልጅቷ መታጨቷ ይታወቃል፡፡ ቀደም ሲል በዋግ ኽምራ ለሴት ልጅ የመታጨት ምልክት ሆኖ ያገለግል የነበረው ማርዳ ነበር፡፡ አሁን አሁን ግን አንዲት ልጅ መታጨቷ የሚታወቀው ማርዳ በማሰሯ ብቻ ሳይሆን፣ በወሬም ሆኗል፡፡ ማርዳው እየቀረ የመጣውም በተለያዩ ምክንያቶች ነው፡፡ የመጀመሪያው ጠልሰሙ የሚሰራበት ብር በመወደዱና ድባውም በገበያ ላይ ባለ መገኘቱ ነው፡፡ ሌላው ምክንያት ደግሞ ‹‹ከውድነቱ በተጨማሪ እንደ ቀድሞው ሁሉም ሴቶች በልጅነታቸው ስለማይታጩ ነው ይላሉ(ቋ.የ.መ.አ.11 እና ቡ.ተ.ው.4)፡፡ በዚህ ምክንያት በመስክ ቆይታየ ማርዳ አስራ ያገኘሁት አንድ ልጅ ናት፡፡

ቀደም ሲል በልጅነቷ የታጨች ሴት እጮኛዋንና ዘመዶቹን ስለምታፍራቸው አታያቸውም ነበር። የእጮኛዋ ወገኖች መሆናቸውን ካወቀች ወይም ከሰማችም ላለማየት ትሸሻለች፡፡ ወንዱም ቢሆን ከሠርጉ በፊት አማቾቹን አያያቸውም፤ ለዚህም በድሃና ወረዳ ልዩ ስሙ ሲልዳ በሚባለው አካባቢ አንድ ገደል አለ፡፡ የገደሉ ስም የሙሽራ ገደል ነው፡፡ ይህን ስም አገኘ የሚባለውም አንድ ሙሽራ አማቾቹ ከፊት ለፊቱ ሲመጡ ተመልክቶ ሊሸሽ ሲል በዚያ ገደል ወድቆ በመሞቱ ነው ይባላል (ቡ.ተ.ው.3)፡፡

ከእጮኛነት እስከ የሠርግ ቀን መቁረጥ ድረስ ባሉት ጊዜያትም የተለያዩ ስራዎችን እንዲሰራ፣ የሴት ወገን የወንድ ወገንን ያዛል። ስራውም **አማች እዝ (በኽምጣኛ አስንዋ እዝ)** ይባላል፡፡ የስራው አይነትም አረም፣ አጨዳ ወይም ቤት የሚሰራ ከሆነ ለቤት መስሪያ የሚሆን እንጨትና ሰንበሌጥ እንዲያመጣ የሚታዘዝበት ነው (ቋ.የ.መ.አ.5 እናቡ.ተ.ው 2)፡፡ ይህም Vaughn(2010:167) የሙሽራ ዋጋ ወይም የሙሽራ ሀብት (Bride price or bride wealth) ያሉት አይነት ነው፡፡ የሙሽራ ዋጋ ማለት ከሙሽራው ቤተሰቦች ወደ ሙሽራዋ ቤተሰቦች የሚተላለፍ ቁሳቁስ ወይም ገንዘብ ነው፡፡ ይህም ከሙሽራው ወደ አማቾቹ በተወሰነ

ጊዜ ወደ ሙሽራዋ ቤተሰቦች የሚተላለፍ የጉልበት አገልግሎት ነው፡፡ የወበራ[47] አይነት ነው። ሂደቱም እንደሚከተለው ነው፡፡

የሴት አባት የሚሰራው ስራ ምን ያህል ሰው እንደሚያስፈልገው በመጥቀስ ‹‹ይህን ያህል ሰው፣ ለአብነት ያህል ሰላሳ ሰው፣ አርባ ሰው ይዘህ እንድትመጣና እዚህ ቦታ የሚገኘውን ስራ እንድትሰራ›› በማለት የወንድ አባትን ያዛል። የወንድ አባት ግን ስራው በተገለጸው የሰው መጠን ላይጠናቀቅ ይችላል የሚል ጥርጣሬ በማሳደር በስራው የሚሳተፉትን ከማሰባሰቡ አስቀድሞ እንዲሰራ የታዘዘውን ማሳ ዞሮ ይመለከታል፤ ከዚህ በኋላ ‹‹በዚህ ቀን በእዚህ ቦታ የአማች እዝ ስላለብኝ እንድትመጡ›› ብሎ በስራው ይሳተፉልኛል ለሚላቸው ሰዎች ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡ ከተጠየቀው የሰው መጠን ላይም ጨምሮ ይወስዳል፡፡ ስራውን የሚሰሩትም እንደ ማንኛውም የወበራ ስራ የተለያዩ ባህላዊ ዘፈኖችን በመዝፈን ነው፡፡ ማታም በሴቷ ቤተሰብ ቤት ድግስ ተደግሶ ይጠብቃቸዋል፤ እነሱም ሆ እያሉ ወደ ቅጥር ግቢው ገብተው ትንሽ ከዘፈኑ በኋላ፣ በልተውና ጠጥተው ቢመሽም እንኳ ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ እንጂ በአማቾች ቤት አያድሩም፡፡ የሴት ቤተሰቦችም አማቾቻቸው የሰሩበትን የጉልበት ዋጋ ግምት እንደ አቅማቸው ቃንጃ በሬ ወይም ጥንድ በሬ ይሰጧቸዋል። ስጦታው ስራው በተሰራበት እለት ሊሰጥ፣ ካልሆነም በሰርጉ እለት በሚሰጠው ማጫ እና ስጦታ ወቅት ግምት ውስጥ ሊገባ ይችላል (ቡ.ተ.ው.3)፡፡

### 5.2.2.2 በእጮኝነት ሂደት ወቅት የሴቶች (የእናቶች) ተሳትፎ

በመጀመሪያው የሽማግሌዎች የጥያቄ ቀን ሴት በሽማግሌነት አትሄድም፤ የተጠያቂዋ ልጅ እናትም ለሽማግሌዎች በሚሰጠው መልስ አትሳተፍም፤ ከቤቷም አትወጣም፤ ከቤት ወጥቶ መልስ የሚሰጠው አባት ወይም አሳዳጊ የሆነው ወንድ ነው። ምክንያቱን ወ/ሮ አልማዝ የተባሉት የመረጃ አቀባየ እንደተናገሩት፣ ሴቶች ወጥተው መልስ መስጠት በአካባቢው ያልተለመደ ባህል በመሆኑ ነው (ቂ.የ.መ.አ.26)፡፡

አቶ ተቀባ እና አቶ መኮንን ደግሞ ሴቶች ሽማግሌ ሆነው የማይሄዱበትን ምክንያት አስመልክተው እንደሚከተለው ብለዋል፡፡

[47] ደቦ፣ ጅጌ ማለት ነው

ድሮ ደብር ከደብር የወንዝ ልጅ ስለሚባል አይጋቡትም ነበር፤ወንዝ ተሻግሮ ነበር የሚጋቡት፣ ይህም ወንዱ ባንድ አካባቢ ችግር ቢፈጥር በመደበቂያነት ያገለግል ነበር፡፡ ስለዚህ ሴት ወንዝ ተሻግራ አትሄድምና ሽማግሌ መሆን አትችልም፡፡ ይሁን እንጂ እሺ እምቢ ለማለት ሚስቱን ስለሚያማክራት ዘራቸው ችግር ካለበት ጋብቻውን ማስቀረት ትችላለች (ቁ.የ.መ.አ.27 እና 22)፡፡

ይሁን እንጂ እናት ሽማግሌ ሁና ባትሄድም፣ ልጇን የሚጠይቁ ሽማግሌዎች ሲመጡ መልስ ባትሰጥም፣ ለጥያቄው ባይተዋር አይደለችም፤ ምክንያቱም ባሏ ‹‹ልጃችንን ለእከሌ ልንሰጥ ነው፡፡›› ብሎ ያማክራታል፡፡ የተጠያቂው ሚስት ለትዳር የምትፈለገውን ልጅ የማትወልዳት ከሆነም፣ ሽማግሌዎቹ ወላጅ እናቷ ወደምትኖርበት አካባቢ ሂደው እንዲጠይቋት ይደረጋል፡፡ እሷም ለጋብቻ በሚጠይቁትና በቤተሰቧ መካከል ያለውን ሁኔታ በማጠያየቅ ሀሳብ ትሰጣለች፡፡ በእጮኛነት ወቅትም አባት ለሽማግሌዎቹ፣ ‹‹ባለቤቴ ትምጣና እሷም ትጠየቅ›› ይላል፡፡ በዚህ ጊዜ በሷ ወገን ጠብ ካለ ለእሽታው እንቅፋት የሚሆንበት ጊዜ ይኖራል፡፡ ስለዚህ የመጨረሻው የእጮኛነት ስምምነት የሚፈጸመው ሁለቱ (አባትና እናት) ባሉበትና ባመኑበት ነው (ቁ.የ.መ.አ.18፣ ቡ.ቃ. እና ቡ.ተ. ው.4)፡፡

ሴቶች ለማጨት ሽማግሌ ሆነው ባይሄዱም፣ ‹‹ያልታጨች የእከሌ ልጅ አለች ፤›› ብለው ለወንድ ወገን መጠቆም ይችላሉ፡፡ ጠቋሚ ሆነውም ቤት ለማሳየት ወደ ሴቷ ቤተሰብ ሽማግሌዎቹን ይዘው መሄድ ይችላሉ (ቁ.የ.መ.አ.4)፡፡

### 5.2.3 የሠርግን ቀን መወሰን (የሠርግ ቀን ቆረጣ)

ከእጮኛነት እስከ የሠርግ ቀን የሚኖረው የጊዜ ርዝማኔ ቋሚ ወይም የተወሰነ አይደለም፤ ምክንያቱም በተለያዩ ምክንያቶች የሚወሰን ነው፡፡ የመጀመሪያው ምክንያት የተጋቢ ቤተሰቦች ለመደገስ ያላቸው አቅም ነው፡፡ የወንድ ወገን ‹‹ልጃችንን በውሃ አጥበህ ስጠን፣ ዘንድሮ ብርም ድግስም አልፈልግም፤›› ብሎ የሴት ወገንን በሚጠየቅበት ወቅት ፣ የሴት ወገን ለመደገስ አቅም ባይኖረውም ልጆቹ ይጋባሉ፤ጥሩ ምርት ሲገኝ ድግሱ (ሰርጉ) ይደረጋል፡፡ ሌላው ምክንያት የተጋቢ ቤተሰቦች የሚገኙበት የእድሜ እና የጤንነት ሁኔታ ነው፡፡ የልጁ ወይም የልጅቷ ወላጆቿ በእድሜ የገፉ ከሆኑና ‹‹ሳንሞት የልጃችንን አለም ማየት አለብን›› በማለት ሴቷ ለአካለ መጠን ባትደርስም እንኳ፣ እንድትዳርና ከባሏ ቤተሰቦች ጋር እንድታድግ የሚደረግበት ሁኔታ አለ (ቁ.የ.መ.አ.22 እና 23)፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የሚያገባው ልጅ፣ ‹‹በዚህ ዓመት ዳሩኝ፤ ራሴን መቻል አለብኝ፤›› ካለም በድግስ ባይሆንም በአግብተህ ክረም (በድውር ጫር) ጋብቻው ሊፈጸም ይችላል፡፡ ለአብነት ያህል ቀደም ሲል የተገለጸው፣በ19/07/04 ዓ.ም በአግብተህ ክረም የተዳረው አዳነ ግርማይ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

ልጅቷ የታጨችው ለአቅመ ሔዋን ከደረሰች በኋላ ከሆነና የተጋቢዎቹ ቤተሰቦች ለመደገስ አቅም ከሌላቸውም፣ የምርት ወቅት ሳይጠበቅ በታጨበት ዓመት በመጠነኛ የሠርግ ድግስ ሊዳሩ ይችላሉ፡፡

ሠርግ በኽምጣኛ ቅየን ይባላል፡፡ የሠርግ ቀን ቆረጣ የሁለቱ የወደፊት ተጋቢዎች ቤተሰቦች፣ ሠርጉ የሚደረግበትን ወርና ቀን የሚወስኑበት ነው፡፡ የሠርግ ቀን የሚቆረጠው በሁለቱ ተጋቢዎች ቤተሰቦች ስምምነት ነው፡፡ በመጀመሪያ ፣‹‹ልጄን ስጡ›› ብሎ የሴት ቤተሰብን የሚጠይቀው ግን የወንድ ቤተሰብ ነው፡፡ ለዚህም ፈቃደኝነታቸውን የሚጠይቅ ሰው ይልካል፡፡ ሰውየውም ‹‹ወንድማችሁ አቶ እከሌ፣ ልጄ ደርሷልና ልጄን ስጡኝ ይላችኋል፡፡›› ብሎ ይጠይቃል፡፡ የሴት ቤተሰብም፣ ‹‹እሺ ከቤተሰብ ጋር ተመካክረን መልሱን እንሰጣለን፡፡››ይላሉ፡፡ የሴት አባት ቀኑን እራሱ ከመቁረጡ (በዚህ ቀን ነው ብሎ ከመወሰኑ) በፊት ቤተሰቦቹን ያማክርና፣ መቼ መሆን እንዳለበት ለወንድ ቤተሰብ ቀኑን ያሳውቃል፤ የወንድ ቤተሰብም የተቆረጠለትን ቀን መቀየርና እምቢ ማለት ስለማይችል ይስማማል፤ ሁለቱም ዝግጅታቸውን ይቀጥላሉ።

የተጋቢዎቹ ቤተሰቦች የሠርግ ቀን ከመቁረጣቸው በፊት ባጋጣሚ ከአንዱ ቤተሰብ በሞት ቢለይ ግን ሰርጉ እንዲዘገይ ይደረጋል፡፡ ቀኑ ከተቆረጠና ድግስ መደገስ ከተጀመረ ግን የሠርጉ ድግስ ይቀጥላል፡፡ ለአብነት ያህል አብያ ሊባኖስ በተባለው ቀበሌ፣ ጥር ሁለት 2005 ዓ.ም የተሰረገው ሠርግ፣ የዳሪው ታናሽ እህት ልጅ በሞተ በሳምንቱ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የአብዛኛው ቤተሰብ ገጽታ የሠርግ ሳይሆን የለቅሶ ታዳሚ ይመስል ነበር፡፡ ዳሱ ውስጥ እንደተመለከትሁት ፊታቸውን የላጡ፣ ጸጉራቸውን የነጩና ሽሩባቸውን በጨርቅ የቋጠሩ ሴቶች እና ነጠላቸውን ዘቅዝቀው የለበሱ ሴቶችና ወንዶች በርካታ ነበሩ፡፡

## የሠርግ ወራትና ቀናት

በዋግ ኽምራ በሠርግ በርካታ ጋብቻዎች የሚፈጸሙት በጥርና በየካቲት ነው፤ አልፎ አልፎም ከፋሲካ በኋላ በሚያዚያ ወር ይፈጸማል፡፡ በግንቦት የሚካሄድ ጋብቻ ግን አይጸናም ተብሎ ይታመናል፡፡ በሌላ በኩል ግንቦት ሰውም መሬቱም እህል የሚፈልግበት በአብዛኛው አርሶ አደር ቤት የእህል እጥረት የሚታይበት ወር በመሆኑ ሙሽራዋንም በምግብ መንከባከብ አይቻልም፤ እንዲያውም የስራ ወቅት ስለሆነ በቀጥታ ወደ ስራ ትገባለች፡፡ ይህ ወቅት ለክረምት ከጫካ እንጨትና ኩበት የሚሰበሰብበት ወቅት ስለሆነም በሙሽራዋ ላይ የሥራ ጫና ይደረግባታል (ቄ.የ.መ.አ.26)፡፡ ይሁን እንጂ በአሁኑ ጊዜ በግንቦት ወርም ሠርግ እየተደረገ ነው፡፡

በብዛት ሠርግ የሚደረገው ግን በጥርና በየካቲት ነው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ወራት ምርት የሚገባባቸውና አርሶ አደሩ ከእርሻ ስራው እረፍት የሚያገኝባቸው ናቸው፡፡ ከዚህም ሌላ በተለይ በቆላው አካባቢ በእነዚህ ወራት ውሃ እንደልብ ይገኛል፡፡ በሚያዝያ እና በግንቦት ወራት ግን[48] ብዙ ሠርግ አይደረግም፡፡ ምክንያቱም ትናንሽ ወንዞችና ምንጮች ስለሚደርቁ የውሃ ችግር ያጋጥማል፤ አርሶ አደሩም ወደ የእርሻ ስራው ያመራል፡፡

የሠርግ ቀናቱም የተመረጡ የበዓል ቀናት ናቸው፡፡ ከሳምንቱ ቀናትም የሠርግ ቀናቱ ሰኞ፣ ማክሰኞና ሀሙስ ናቸው፡፡ በገጠር እሁድና ቅዳሜ ተዝካር እንጂ ሠርግ አይደረግም፡፡ እሁድ ሠርግ አለ ከተባለ የእስላም እንጂ የክርስቲያን አይደለም፤ ምክንያቱም ቀደም ሲል ዳስ ይሰራ የነበረው በእለቱ ከጫካ (ከበረሃ) በሚቆረጥ እርጥብ የደደሆ ቅጥል ስለነበርና፣ ለማገዶ የሚሆነውም እንጨት በሰርጉ እለት እየተሰበረ ይመጣ ስለነበር፣ በዓል እንዳይሻር ነው፡፡ እሮብና አርብም የጾም ቀናት በመሆናቸው፣ በእነዚህ ቀናት ሠርግ አይደረግም፤ የጋብቻ ውልም አይፈጸምም(ሰማንያ አይፈጅም) (ቡ.ተ.ው.3)፡፡

የሠርግ ወራትንና ቀናትን አስመልክተው፣ አቶ ሞገስ አወጣ ደግሞ የሚከተለውን ሀሳብ ሰጥተዋል፤

[48] በሚያዚያና በግንቦት 2004 ዓ.ም.ስድስት የሠርግሥነ-ሥርዓቶችን ለመመልከት ብችልም፣ ከስድስቱ ሶስቱ ወንድ ሙሽራዎች የሰቆጣ ከተማ ነዋሪዎች ሲሆኑ፣ ከሴት ሙሽራዎቹ መካከል ደግሞ ሁለቱ የኮሌጅ፣ አንዷ የቴክኒክና ሙያ ተማሪዎች፣ አንዷ ደግሞ የመንግስት ሰራተኛ ናት፡፡ የኮሌጅ ተማሪዎቹ ሠርግ በሚያዝያ ወር የሆነውም ጥርና የካቲት የተማሪዎቹ የፈተና ጊዜ ስለነበር ነው፡፡ ስለዚህ የሰርጉ ወር ከጥር ወደ ሚያዝያ የተላለፈው በአስገዳጅ ሁኔታ ነው፡፡

> ሠርግ የሚደረግባቸው ወራት ጥርና የካቲት ናቸው፡፡ ምክንያቱም ይህ ወቅት ለአርሶ አደሩ የእርሻ ክስከሳ ስራ ገና በመሆኑ፣ ለእህል ውሃም የምርት ወቅት በመሆኑ እህል እንደ ልብ ስለሚገኝና ገቢ ያለው ወቅት ስለሆነ ነው፡፡ በነዚህ ወራት ወገንም የሚድረውን ሰው፣ በገንዘብም በጉልበትም ሊያግዝ ይችላል፡፡ በሚያዝያ ግን ዳሪው ልዳር ቢልም እንኳ አቅም አይኖርምና፣ ወገን ‹‹አይሆንም፤ብቻህን ልትድር ነው፡፡››ይለዋል (ቂ.የ.መ.አ.14)፡፡

የሠርጉ ቀን ሲቃረብም የወንድና የሴት ቤተሰቦች እንደ ድግሳቸው መጠን አብዝተውም ሆነ አሳንሰው ታዳሚያቸውን ይጠራሉ። ጥሪው የሚከናወነውም ዘመድ በሚገኝበት አካባቢ ሁሉ በቃል ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ጥሪው በተንቀሳቃሽ ስልክ እየተከናወነ ነው፡፡

የሠርግ ቀን ከተቆረጠ በኋላ የወደፊት ሙሽራዎች ወንዝ አይሻገሩም፤ብቻቸውንም ከቦታ ቦታ አይንቀሳቀሱም፤ ምክንያቱም ከሌላው ቀን ይበልጥ በሠርጋቸው ሰሞን እርኩስ መንፈስ በእነሱ ላይ ያድራል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ለዚህ መከላከያ ይሆን ዘንድም ሴቷ በእጇ ድኮት ታደርጋለች፤ ወንዱም የብረት ዘንግ ይይዛል፡፡

### 5.2.4 የሚዜ ምልመላ

ከቅድመ ሠርግ ተግባራት ሌላው የሚዜ (በ'ሽምጣኝ ምዘ) ምልመላ ማካሄድ ነው፡፡ በዋግ 'ኽምራ በተለይም በገጠሩ ሚዜ የሚያስፈልገውና ምልመላ የሚያከናውነው ወንዱ ሙሽራ ብቻ ነው፤ ሴቷ ሙሽራ ሚዜ አይኖራትም፡፡ ምልመላውን የሚያከናውነውም የሠርጉ ቀን እንደተቆረጠ ወዲያውኑ ነው፡፡ ሚዜዎቹን የሚመርጠውም ብቻውን ሳይሆን ከአባቱ እና ከወንድሞቹ ጋር በመመካከር ነው፡፡ ሚዜነት ዝምድና መጨመሪያም ነው፡፡ ለምልመላ በመስፈርትነት የሚያገለግሉትም፣ ጓደኝነትና አብሮ አደግነት፣ የማጫ እና የስጦታ አጠያየቅና የመዝፈን ችሎታ መኖር ሲሆኑ፣ ትልቁና ዋናው መስፈርት ግን ከቤተሰብ የሚመጣ ፍቅር ነው፡፡ በ14/8/2004 የጋብቻ ሥነ-ሥርዓታቸውን የፈጸሙት ዲያቆን ነጋሽ ዳምጤ ሚዜ ለመመልመል ትኩረት ያደረጉባቸውን ወይም በመስፈርትነት ያገለገሉትን ከሚዜ ተግባራት ጋር አጣምረው እንዲህ ይገልጻሉ፤

> በዋናነት በመስፈርትነት የተጠቀምሁት የዳስ ስርዓት ልምድ ያለው መሆንን ነው፤ ለዚህም አንደኛ ሚዜየ የሆነውና ከሴቷ ዳስ ሸኙነ ሸኙነ (ስሽዝጥን ስሽዝጥን) ያለው ሚዜየ ይህ ችሎታ ስላለው የመለመልሁት ነበር፡፡ እንደ አባቶቻችን ሁሉ ሚዜ ዘመድ ያልሆነ መሆን እንዳለበትም ተመልክቻለሁ፡፡ የሚዜ ፋይዳ በርካታ ነው

> አንደኛ ለሙሽራው አክብሮት ለመስጠት ነው፡፡ ሁለተኛ ሙሽሪትን ለማለማመድ ነው፤ በዚህም ሚዜዎቹ እስከ ሳምንት ወደ ቤቴ እየተመላለሱ ሙሽራዋን አለማምደዋታል፡፡ ሶስተኛ በሠርግ ወቅት በስራ ማገዝ ነው፤ ለዚህም ሚዜዎቹ ዳስ በመስራትና እቃ በማጓጓዝ ወዘተ. አግዘውኛል (ቁ.ያ.መ.አ.10)፡፡

አንደኛ ሚዜ ከሌሎች የተለየ ተግባራትን ያከናውናል፣ ለምሳሌ፣ ስቨዝጥን ስቨዝጥን፣ በአማርኛ ሸኙነ ሸኙነ የሚለውን በቅደም ተከትል ማወቅ ከአንደኛ ሚዜ የሚጠበቅ ነው፡፡ ሚዜ ምልመላና የሚዜ ተግባራትን አስመልክተው፣ አቶ ተበጀ በላይ የተባሉት የመረጃ አቀባየ ሲገልጹ ደግሞ እንዲህ ይላሉ፣

> ቀደም ሲል የወንድ ሚዜ ዋና ተግባር በስራ ማገዝ ነበር፤ የሚዜ አገልግሎት ከዘመድ አዝማድ የበለጠ ነበር፡፡ ወደ ተጠያቂው ቤት ሂዶ የሚለምነውም የሙሽራው አባት ነበር፡፡ በዚያን ወቅት ሚዜ የከበረ ነበረ፤ አሁን ግን እየተናቀ ነው፤ ሚዜ ቃል ኪዳኑን[49]ካፈረሰ ምን ይሆናል እየተባለ፣ ሙሽራው ወንድሙን ነው ይዞ የሚሄደው ፣ ባህላችንን እያረከስን ነው (ቁ.የ.መ.አ.4)፡፡

ቀደም ሲል ቃል ስለሚገባ በዋግ ኸምራ ዘመድ ሚዜ አይሆንም ነበር፤ አሁን አሁን ግን የስጋ ዝምድና ያለውና ወንድምም በሚዜነት እየተመለመለ መሆኑን ለመመልከት ችያለሁ፡፡ ለአብነት ያህል በአዳነ ግርማይ ሠርግ የወንድ ወገን ወደ ሴቷ ቤት በሚዘምትበት ወቅት፣ ከሚዜዎቹ መካከል አንዱ የሙሽራው ታላቅ ወንድም ነበር፡፡

የሚዜ መጠን የተወሰነ አይደለም፤ ሊበዛም ሊያንስም ይችላል፡፡ የሚወሰነውም በሴት ቤተሰብ የድግስ መጠንና የማስተናገድ አቅም ነው፡፡ በተለይ የሴቷ ቤተሰብ ድግስ በጣም አነስተኛ ከሆነ የሚዜዎቹ ቁጥር ከሶስት የማይበልጥበት ጊዜ አለ፤ ምክንያቱም የወንድ ቤተሰብ ወደ ሴቷ ከመዝመቱ አስቀድሞ፣ ስንት ሰው ይዞ መሄድ እንዳለበት ይገለጽለታል፡፡ የሴት ቤተሰብ ‹‹የማስተናግድበት አቅም ስለሌለኝ፣ ይህን ያህል እራስህን ሆነህ ና›› ካለ የወንድ ቤተሰብም መጠነኛ ጭማሪ ሊያደርግ ቢችልም በጣም ሊያበዛ ግን አይችልም፡፡ ምክንያቱም የሴት ቤተሰብ ለማስተናገድ ካቀደው ውጭ እንዳይሆንና በመስተንግዶው ላይ ተጽእኖ እንዳያደርግ ነው፡፡

---

49 ሚዜዎች የሚገቡት ቃል በድህረ-ሠርግ ይገለጻል፡፡

ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው በዋግ ኽምራ፣ ሴት ሙሽራ ሚዜ አልነበራትም፣ አሁንም በገጠር የላትም፡፡ ምልከታ ካከናወንኩባቸው ዘጠኝ የሴት ሙሽራ ሠርጎች መካከል ከመኪና መስመር ወጣ ባሉት ስድስት የገጠር ቀበሌዎች የሚገኙ ሴት ሙሽራዎች የሴት ሚዜ አልነበራቸውም፡፡ ሙሽራዋን የምታጥባትና የምታስውባትም ድንግል የሆነች፣ የቄስ ሚስት የሆነች ወይም ያገባችም ከሆነ ከአንድ በላይ ያላገባች፣ በመጀመሪያ ጋብቻዋ (በሰማንያዋ) ጸንታ የምትገኝ ሴት ናት፡፡

ተጋቢዎቹ የሰቆጣ ከተማ ነዋሪ ሆነው፣ ሰርጋቸው በገጠር የሆነ ሴት ሙሽራዎች ግን በዘመናዊነትና በከተሜነት ምክንያት የሚዜ ምልመላ አከናውነው ነበር፡፡ ለአብነት ያህል፣ ከሰቆጣ ከተማ ከ30 ኪሎ ሜትር በላይ ርቀው ቢገኙም፣ መስመር ላይ ባሉት፣ ስሬል፣ ማይግንዶና ሀሙሲት በተባሉት ቀበሌዎች ሴት ሙሽራዎች ከሰቆጣ ከተማ ሄደው ሠርጋቸው ገጠር በመደረጉ ምክንያት የሴት ሚዜ ነበራቸው፡፡ በ14/8/04 ፋያ ማርያም በሚባለው ቤተክርስቲያን  የጋብቻ ሥነ-ሥርዓቷን የፈጸመችው አደነቁሽ ግዛት በ21/8/04 ማይ ግንዶ በተባለው ቦታ ላይ በነበረው ሠርጓ ሶስት የሴት ሚዜዎች ነበሯት፣ በጥር 2005 ዓ.ም በአስከተማና በጽጽቃ የወረዳ ከተሞች በነበሩት ሰርጎችም የሴት ሚዜዎች ነበሩ፡፡

ከእነዚህ መካከል የሙሽሪት ስር ወይም ትልቅ ሚዜ የነበሩት መለሱ ጌታወይ፣ ለምን ስር ሚዜ እንደ ሆኑ? መቼ እንደ ተነገራቸው? የሴት ሚዜ ጥቅም ምን እንደ ሆነ? ሙሽራዋ በአካባቢዋ የማይደረገውን የሴት ሚዜ ምልመላ ለምን እንዳከናወነች እና የሴት ሚዜ ተግባራት ምን ምን እንደሆኑ እንደሚከተለው ገልጸዋል፤

> ከሶስቱ የሴት ሚዜዎች መካከል አንደኛ (የስር) ሚዜ ስሆን፣ሚዜ እንድሆን የተነገረኝም ከሁለት ወር በፊት ነው፡፡ ሚዜ የሆንኩበት ምክንያትም የሙሽራዋን ሚስጢር ስለማወቅ ነው፤ በዚህም ምክንያት  ከሰቆጣ ከተማ ጀምሬ እዚህ ድረስ ልጄን አዝየ በእግሬ መጥቻለሁ፡፡ ምክንያቱም አደነቁሽ፣ ስታመም የምትደርስልኝ ልዩ ጓደኛየ ስለሆነች ለሷ ያልሆነ ብየ የተቀበልኩት ሀሳብ ነው፡፡ ጓደኛየ ብላ አክብራ ስለጠራችኝ፣ እሷን (ሙሽራዋን) ለማክበርና ለማስደሰት ካልሆነ በስተቀር ሚዜ መሆን ለእኔ ሌላ ጥቅም የለውም፡፡ ሙሽራዋ ሴት ሚዜ የያዘችበት ምክንያትም፣ እሷ ከተማ ስላደገች ነው እንጂ በገጠር የሴት ሚዜ የለም፡፡ የሴት ሚዜዎች ከምናከናውናቸው ተግባራት መካከል ሙሽራዎቹን የምናቃምስበትን እንጀራ

> እንጋግራለን[50]፣ዳቦእንደፋለን፣ሽንኩርት እንከትፋለን፣ ለሙሽራዎቹ ማቃመሻ የሚሆን፣ የደሮ ወጥ እንሰራለን፣ የወንድ ወገን ያመጡትን ምኩትም ለሙሽራው ሚዜዎችና ከከተማ ለሚመጡት የሙሽራው አጃቢዎች እንዲሆን ለብቻ ወጥ እንሰራለን[51] (ቁ.ያ.መ.አ.2 )፡፡

ሙሽራዋ አደነቁሽ ግዛትም፣ የሴት ሚዜዎቿን አስመልክታ እንዲህ ገልጻለች፣

> የተወለድኩት ገጠር ቢሆንም ያደግሁት ከተማ ነው፣ ከከተማ ያየሁትን ደግሞ ልክ እንደ ከተማ ማድረግ ስላለብኝ ነው እንጂ፣ በገጠር የሴት ሚዜ አይታወቅም፡፡ (እጽንኦት የራሴ) ሶስት ሚዜዎች አሉኝ፣ አንዷ ዘመዴም ጓደኛየም ናት፣ ሶስት ሌሎች ሴት አጃቢዎችም አሉኝ፡፡[52]ከእነዚህ አንዷን ትልቅ ሚዜ ያደረግሁዋት በብዙ ነገር ለክቻት ነው፣ ብዙ ነገር ታውቃለች፣ በበሽታየ ትደርሳለች፣ በበሽታዋ እደርሳለሁ፡፡ ምስጢሬን ካወቀች ሁሉን ነገር ታውቃለች ብየ ነው፡፡ የሴትን ሚዜ ጠቀሜታ በሚመለከትም እኔን ያዘጋጃሉ፣ ያጅባሉ፣ ሰርጉንም ያደምቃሉ፡፡ የሚመለከታቸውንም ስራ ይሰራሉ (ቁ.ያ.መ.አ.1)፡፡

ሙሽራዋ በሠርጓ ቀንም በስራ ትጠመዳለች እንጂ እንደ ከተሜዋ ከሠርጓ ቀን ቀደም ብሎ ጀምሮ በተለያዩ መዋቢያዎች መዋዋብ አትጀምርም፣ በእርግጥ በእለቱ ጸጉሯን ሽሩባ ትሰራለች፣ የጸጉር ቅቤ በመጠኑ ትቀባለች፣ ኩል ትኳላለች፣ እጇንም እንሶስላ ትሞቃለች፣ ወደ ዳስ ስትወጣም ፊቷን በጥቁር ሻሽ(ባውንድ) ትሸፍናለች፡፡ ወደ ወንዝ ወርዳ ውሃ ካለመቅዳቷ በስተቀር፣ ከመደበኛ ስራዋ አትታቀብም፡፡ ለአብነት ያህል አደነቁሽ የማብሰያና የምግብ ማቅረቢያ እቃዎችን በየቤቱ እየዞረች ታሰባስብ፣ እንጀራ ለሚጋግሩት እንጨትና ሊጥ ታቀራርብ ነበር፡፡ ሌላዎቹ ሴቶችም፣ በሰርጉ እለት ይዋባሉ፣ በዚህም ምክንያት ለምልከታ በሄድኩባቸው ሰርጎች ሙሽራዋን ከሌሎች ሴቶች ለመለየት እቸገር ነበር፡፡ እሷን ከሌላዎቹ ለመለየት የቻልኩትም ሌሎች ሴቶችን ጠይቄ ነው፡፡

በአመጋገብ በኩል ግን ሙሽራዋ ከሌሎች ጓደኞቿ ትለያለች፡፡ ምክንያቱም በስራ ላይ የተጠመዱት ሴቶች ያገኙትን ሁሉ ሲበሉና ሲጠጡ፣ የሙሽራዋ አመጋገብ ግን ከዘወትሩ ይለያል፡፡ እልበት እንድትበላ አይደረግም፣ ብዙም አትመገብም፡፡ ምክንያቱም ከአማኞች

---

[50] ከገጠር ለሚመጡ የሠርጉ ታዳሚዎች የተዘጋጀው እንጀራ በወፍራሙ የተጋገረ ድጉሎ ሲሆን፣ ከሰቆጣ ከተማ የሚመጡ እንግዶችን ለማስተናገድ የተዘጋጀው ግን በስሱ የተጋገረ የጤፍ እንጀራ ነው፡፡

[51] ከገጠር ለሚመጣው የሠርጉ ታዳሚ የሚቀርበው የከብት ስጋ ወጥ የተሰራው እንጀራውን ለመፈትፈት እንዲመች ቀጠንጠን ተደርጎ ሲሆን፣ ከሰቆጣ ከተማ ለሚመጣው ታዳሚ የተሰራው ወጥ ግን የፍየል ስጋ ሲሆን፣ በሳህን እየጨለፉ ለማቅረብ እንዲያመችም፣ ሽንኩርቱ በዛ ውሃው አነስ ተደርጎ በወፍራሙ ነበር፡፡

[52] በገጠር ሴት ሙሽራ በተውሳኽነት አብሯት ከሚሄደው አንድ ወንድም ወይም ዘመድ በስተቀር የሴት አጃቢ የላትም፡፡

ቤት ስትሄድ ሆዷን ቢያማት፣ ቶሎ ቶሎ ወደ መጸዳጃ ቦታ ልሂድ ብላ እንዳታስቸግር በማሰብ ነው (ቁ.የ.መ.አ.20 እና ቡ.ቃ.3)፡፡

### 5.2.5.ሙክትና በማሰሮ ቅቤ መውሰድ

በዋግ ኸምራ ከቅድመ ሠርግ ክንዋኔዎች መካከል ሌላው የወንድ ቤተሰብ ለሙሽራዋ የክርስትና እናት እና ወደ ሴቷ ቤት ሙክትና የማሰሮ ቅቤ መውሰድ ነው፤ ወደ ሴቷ ቤት የሚወሰደው ለወንድ ወገን ዘማቾች (ሽማግሌዎችና ሚዜዎች) ለብቻቸው ለሚሰራላቸው ወጥ ነው፡፡ የሚከናወነውም ለክርስትና እናት ከሰርጉ ከአንድ ወር ቀደም ብሎ፣ ወደ ሴቷ ቤት ደግሞ በሠርጉ ዋዜማ ነው፡፡ የሙሽራዋ አባት አቅም ያለው ከሆነ፣ የሙሽራውን አባት ‹‹እዚህ ቦታ ለምትገኘውና እከሊት ለምትባለው ለሙሽራዋ ክርስትና እናት(አበልጅ) አንድ ምኩትና ማሰሮ ቅቤ ይዘህ እንድትሄድ ›› ብሎ ያዘዋል። የሙሽራው አባትም፣ የክርስትና እናቲቱ የምትኖርበት አገር ሩቅ ቢሆንም፣ ‹‹እሺ›› ብሎ በሁለት ሙክት ሳቢዎች አማካይነት፣ ሙክትና ንጥር ቅቤ በማሰሮ ይልካል። ሙክቱ ከጆሮው ምንም ቆራጣ(ቆርጣጣ) የሌለው፣ ቀለሙም ጥቁር ያልሆነ መሆን አለበት፤ ማሰሮዋም ምንም ሸራፋ የሌለባት፣ የምትንጠለጠልበት አጭርና ቀጭን ጠፍር(ጠሎታ)ም ሙሉ የሆነችና ተበጥሳ ያልተቋጠረች መሆን አለባት (ቁ.የ.መ.አ. 11፣ ቁ.ያ.መ.አ.4 እና ቡ.ተ.ው. 3 ቁ.የ.መ.አ.)፡፡

ሙክትና የማሰሮ ቅቤ የተወሰደላት የክርስትና እናትም፣ አቅም ካላት ሁለቱንም ታስቀራለች፡፡ አቅም ከሌላት ግን፣ ቅቤውን ብቻ አስቀርታ፣ ሙክቱን ‹‹ይዛችሁ ተመለሱ፡፡›› ብላ ሙክት ሳቢዎቹን አመስግና ትሸኛቸዋለች፡፡ ምክንያቱም ምኩቱንም ካስቀረች፣ በሰርጉ እለት የምትመርቀው የገንዘብ መጠን የሙክቱንና የማሰሮ ቅቤውን ዋጋ ግምት ውስጥ ያስገባና አውራጅ እንድትይዝም ስለሚያስገድዳትም ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሙሽራዋ ወደ ባሏ ቤት ስትሄድ የምትወሰዳቸውን አንዳንድ የሴት እቃዎች የምታሟላውም የክርስትና እናት ነች፡፡ የሙሽራዋ የክርስትና እናት በህይወት ከሌለች ግን፣ የወንድ ወገን ወደ የክርስትና እናት ቤት ሙክት እንዲስብ አይገደድም፡፡

የተሳበውን ሙክት የክርስትና እናት ተቀብላ ካስቀረች፣ የሴት አባት ለወንድ ወገን ፣‹‹ ከኔ ዳስ ሽማግሌዎችህንና የልጅህን (የወንዱን ሙሽራ ማለት ነው) ሚዜዎች ከሌላው ታዳሚ የተለየ ምግብ ማብላት ከፈለግህ፣ ጥሩ ምኩት ይዘህ እንድትመጣ›› ብሎ በድጋሚ ያዘዋል፤

የወንድ አባትም አቅም ካለው ‹‹እሺ፡፡›› ይልና በሰርጉ ዋዜማ ሙክትና በማሰሮ ቅቤ ይልካል፡፡ ሙክቱን የሚያርዱትም ስበው የሚሄዱት የወንድ ወገኖች ሲሆኑ፣ የማሰሮ ቅቤውን ግን ወጡ ሲሰራ ልታስረክብ ለምትችልና ታማኝ ለሆነች የሴት ወገን ይሰጣሉ፡፡ ሙክት ሳቢዎቹ ሙክቱን አርደው ወጥ የሚሰሩላቸውን ሴቶች ያመቻቻሉ፤ ወጡ የሚሰራውም ፍሪምባው ሳይቆራረጥ ነው፡፡

ለአብነት ያህል በ21/08/04 ምልከታ ባደረግሁበት ሰርግ፣ ሙክት ሳቢ የነበሩት ቄስ ወርቁ ጉለሽና አቶ አምባው አለማየሁ ስለሳቡት ሙክት ዋጋ፣ ቀለምና የወጥ አሰራር እንዲህ ገልጸዋል፤

> ስበን ያመጣነው ምኩት አንድ ሺህ አራት መቶ ብር የተገዛ ሲሆን፣ ቀለሙም ነጭና ጥቁር የሆነ መልከኛ ነው፤ ጥቁር ምኩት ሁሉም ሰው ስለማይበላው፣ ወደ የሴት ቤት አይሳብም፤ እኛ ያመጣነው ምኩት ለእኛ ለዘማቾች ለብቻችን የሚሆን ወጥ እንዲሰራ ነበር፡፡ ነገር ግን የሴቷ ወገኖች ፍሪምባውም ተቆራርጦ ተሰርቶ፣ ከሰቆጣ ከተማ የሚመጣውን እንግዳ መሸኘት አለበት አሉን፤ መጀመሪያ እንደ ባህላችን መሆን አለበት ብለን እምቢ ብለን ነበር፤ነገር ግን ሙሽራው ከሰቆጣ ስልክ ደውሎ፣ ‹‹እሺ በሉ›› ስላለን፣ ቅር እያለንም ቢሆን እሺ ብለናቸዋል፡፡ ስለዚህ ከከተማ የመጡት ሴቶች ቆራርጠው እየሰሩት ነው፡፡ ለእኛ ማስተናገጃነት የሳብነው ምኩት ሌሎችም ሊስተናገዱበት ነው (ቁ.ያ.መ.አ.4 እና5)፡፡

የተሳበው ሙክት ስጋ ለብቻ ወጥ እንዲሰራ የሴት ወገኖች ፈቃደኛ ካልሆኑም፣ ተቆራርጦ ብዙ ሰው እንዲሚያስተናግድ መሰራት ተጀምሯል፤ የተለመደ ግን አይደለም፡፡

የሴት ወገን የሠርግ ድግስ አነስተኛ ከሆነ ግን፣ የሴት አባት የወንድ አባትን ሙክት እንዲስብና በማሰሮ ቅቤ እንዲያመጣ አያስገድደውም፡፡ እንዲያውም ‹‹አቅም የለኝም፤ ድግሴ አናሳ ናት፤ ባለኝ ወጥ ተቃመሱ እንጂ፣ የተለየ ወጥ አላሰራላችሁም›› ይለዋል፡፡ ለአብነት ያህል፣ ዛንዚራ ተክለሃይማኖት በተባለው ጎጥ በነበረው ሠርግ ምልከታ ባደረግሁበት ወቅት፣ ለወንድ ወገን ተለይቶ የተሰራ ወጥ አላየሁም፡፡ ምክንያቱን የሙሽራዋ አባት እንደ ገለጹልኝ ‹‹አቅም ስለሌለኝ ከአማቾች ምኩትና ማሰሮ ቅቤ እንዲመጣ አላደረግሁም፤ የወንድ ወገኖችም ለሌላው እንግዳ ባዘጋጀሁት ወጥ እንዲበሉ አድርጌያለሁ፤ ለዚህም አስቀድሜ ዘምታችሁ ስትመጡ ሰው (ሚዜና ሽማግሌ) አታብዙብኝ ስላልኳቸው አስር እራሳቸውን (አስር ሆነው) ነው የመጡት›› ብለዋል (ቁ.ያ.መ.አ.8)፡፡

የወንድ ወገን ወደ የሴቷ ሠርግ ሙክት ከሳቡ፣ የሴቷ ወገን ማጫ በሚሰጥበት ወቅት፣ የሙክቱንና የቅቤውን ዋጋ ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡ ለዚህ ሲባል ነው፣ አቅምን በማገናዘብ አስቀድሞ እንዳይሳብ የሚደረገው፡፡

ቀደም ሲል በዞኑ በሚገኙ በሁሉም ወረዳዎች የሙሽራዋ ሁለት፣ የሙሽራው ሁለት ቀናት በድምሩ አራት የሠርግ ቀናት ነበሩ፡፡ በመጀመሪያ የሚሆነውም የሙሽራዋ ሠርግ ነው፡፡ ስለዚህ የመጀመሪያው ቀን የወንድ ወገን (ሙሽራው፣ ሚዜዎቹና ሽማግሌዎች) ወደ ሴቷ ቤት የሚሄዱበት ወይም የሚዘምቱበት የዘመቻ ቀን(**በኸምጣኛ ዝምረ**) ይባላል፡፡ በዘመቻው ቀን ታዳሚው ሲበላና ሲጠጣ ይውላል ፤ያድራል፡፡ በማግስቱ ደግሞ የሠርጉ ታዳሚ እንደ ቀረቤታውና እንደ አቅሙ ለደጋሹ ብር የሚሰጥበት(**የሚጣልበት**) **የምረቃ**(**የአዋጅ** ) ቀን (**በኸምጣኛ ጊውረ**) ይባላል፡፡ እያንዳንዱ ሰው የሚሰጠው የገንዘብ መጠንም ዳሱ ውስጥ ለሚገኘው ታዳሚ በአዋጅ ነጋሪ አማካይነት እየተገለጸ ይጻፋል፡፡

የወንድ ወገን ወደ ሴቷ ቤት በሚዘምትበት እለት፣ በሴቷ ቤትም ታዳሚው እየበላና እየጠጣ የሚውልበትና የሚያድርበት ነው፡፡ በማግስቱም ብር የሚጣልበት እለት ነው፡፡ የወንድ ወገን ከተሰበሰበው ገንዘብ[53]፣ ማጫውንና ስጦታውን ተቀብሎ ወደ የወንዱ ቤት የሚመለሰውም በዚሁ ቀን ነበር፡፡

በዚህ ወቅት የሩቅ ዘመድ ሁሉ እስከ ቤተሰቡ ተሰብስቦ፣ ወደ የሰርጉ ቤት በመምጣት እስከ ሳምንት እየበላ እየጠጣ ይቀመጥ፣ ደጋሹንም ያራቁት ነበር፡፡ ከቅርብ ጊዜ ከ1980ዎቹ ወዲህ ግን የማህበረሰቡ የመደገስ አቅም እየቀነሰ በመምጣቱ፣ የሁለቱም (የወንዱም የሴቷም) የሠርግ ሥነ-ሥርዓት በአንድ ቀን ሆኗል፡፡ ይህ ቀን በአካባቢው አገላለጽ **ደርሶ መልስ፣ ጥልፎሽ** ተብሏል፤ ስያሜውን ያገኘውም የወንድ ወገን በሙሽራዋ ቤት ሳይውል ሳያድር፣ ሙሽራዋን ይዞ ወዲያውኑ በእለቱ ወደ ቤቱ ስለሚመለስ ነው (ቁ.የ.መ.አ.26 ቡ.ተ.ው.3 እና 4)፡፡

ግብዣውም፣ የገንዘብ ምርቃቱም፣ ለወንድ ወገን ከሴት ወገን የሚሰጠው የማጫ እና የስጦታ ስርዓቱም በአንድ ቀን ይከናወናል፤ የሠርጉ ታዳሚዎችም በእለቱ ወደ ቤታቸው

[53] በማጫነት የሚሰጠው ገንዘብ የግድ የተጣለው ብር በሙሉ ወይም ብቻ ላይሆን ይችላል፤ ከሰርገኞቹ ከተገኘው ብር ከፍ ያለ ከሆነ የሴቷ አባት ከግሉ ሊጨምር ይችላል፡፡ የተጣለው ብር ከበዛም ሊተርፍለት ይችላል፡፡

ይመለሳሉ፤ ከፍ ያለ ድግስ እንዳይደገስና በሠርግ ድግስ ይባክን የነበረው ምግብና መጠጥም እንዲቆጠብ አስችሏል፡፡

ለምልከታ እና ለቀረጻ ከተገኘሁባቸው አስር ሠርጎች መካከል በአንዱ ብቻ የወንድ ወገን አድሮ በማግስቱ[54] ሙሽራዋን ይዞ ተመልሷል፡፡ በቀሪዎቹ ግን የማጫ እና የስጦታ አሰጣጥ ስርዓቱ እስመሽቷቸውና ከምሽቱ አምስት ሰዓት በላይ ቢሆንም እንኳ፣ ሙሽራዋን ይዘው ወደ ወንድ ቤት የተመለሱት በእለቱ ነው፡፡[55]በእርግጥ አሁንም ቢሆን ከርቀት የሚመጡትን ዘመዶች ‹‹እህል ውሃ አለ፤አድራችሁ ሂዱ፡፡›› የሚሉ የሠርግ ደጋሾች መኖራቸውንም ተመልክቻለሁ፡፡ ይህም እንደ አቅም ሁኔታ የሚወሰን ነው፡፡

## 5.3 ሠርግ

ቀደም ሲል የተዘረዘሩት ቅድመ-ሠርግ ተግባራት ከተከናወኑ በኋላ ሰርጉ ይቀጥላል፡፡ ይህንንም ቀጥሎ እንመለከተዋለን፡፡

### 5.3.1 የሠርግ ድግስ ዝግጅት

የሠርግ ቅድመ ዝግጅቶች ከተከናወኑ በኋላ የሚቀጥለው ተግባር የሠርጉን ድግስ ማዘጋጀት ነው፡፡ በዋግ ኽምራ ለሠርግ ድግስ ይደገሳል ቢባልም ወጭው ግን ይህን ያህላል ተብሎ የሚወሰን አይደለም፡፡ እንደ ደጋሾች አቅም የሚወሰን ነው፡፡ ለአብነት ያህል ምልከታ ካደረግሁባቸው ሠርጎች መካከል አነስተኛ የሠርግ ድግስ የነበረው ዛንዚራ ተክለ ሃይማኖት በተባለው ጎጥ በ23/8/04 ዓ.ም የነበረው የደስታ አሰፋ ሠርግ ድግስ ነበር፤ ድግሱም በአንዲት ትንሽ ፍየል ስጋና በሁለት ጋን ጠላ ብቻ ነበር፡፡ ከፍተኛው ደግሞ ከቤት ካለው የእርሻ ምርት ወጭ የሆነውን የእህል ዋጋ ሳይጨምር ለሙሽራዋ አልባሳት፣ ለዘይት፣ ለበርበሬና ቅመማ ቅመም በጥቅሉ ከሌላ ቦታ ለተገዙ ነገሮች ብቻ ከሃያ አምስት ሺህ ብር በላይ ወጭ ተደርጎ በሰፌ ዳስ ሁለት ልጆች (አንድ ወንድ አንድ ሴት) የተዳሩበት የ29/08/04 ዓ.ም የስሬል ሊባኖስ ሠርግ ነው፡፡

[54] ለዚህም ምክንያቱ የወንዱ ሙሽራ እና የሴቷ ሙሽራ አገር እጅግ የተራራቀ በመሆኑና የወንድ ወገን ወደ ሴቷ ዳስ ከምሽቱ አንድ ሰዓት አካባቢ በመድረሱ ነው፡፡ ከዚህ ሰዓት በኋላ የማጫ፣ የስጦታ፣ የውል እና የመስተንግዶ ስርዓት በማካሄድ ሙሽራዎቹን መሸኘት አልተቻለም፡፡ ሰርጉ ጥር ሁለት ሀሙስ ቀን ነበር ፤ ሙሽራዎቹ ወደ ወንድ ቤት የተሸኙት ግን በማግስቱ አርብ ነው፡፡ ምንም እንኳ አርብና እሮብ ሙሽራዎች አይወጡም ቢባልም ሰማንያው፣ ማጫውና ስጦታው ተጠናቆ ያደረ ነው፡፡

[55] የወንድ ወገን ሲመለስ ስለሚጨልምና ርቀት ያለው መንገድ ስለሚጓዝ፣ሚዜዎቹ ከሙሽራው ጋር በእለቱ ሲመለሱ ሽማግሌዎቹ ግን አድረው በማግስቱ የሚመለሱበት አጋጣሚም አለ፡፡

የሠርግ ድግስ የሚዘጋጀው በደጋሹ ወጪ ብቻ አይደለም፡፡ በድግሱ ዝግጅት ወቅት የዘመድና የጎረቤት እገዛ የጎላ ነው፡፡ እገዛውም ለደጋሹ ምክር በመለገስና በሀሳብ በመደገፍ፣ በጉልበትና በገንዘብ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህም የሠርጉ ድግስ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የሚቀጥል ነው፡፡ እገዛውንም የወንዶች፣ የሴቶችና የወዳጅ ዘመድ እገዛ በማለት እንደሚከተለው አቅርቤዋለሁ፡፡

### የሴቶች የስራ እገዛ

ሴቶች በሠርግ ድግስ ወቅት፣ ከአማካሪነታቸው በተጨማሪ በጉልበት እገዛ በኩልም በርካታ ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል አበይት የሆኑትን እንመልከት፡፡

በዋግ ኽምራ ለሠርግ ድግስ የሚውለው እህል በአብዛኛው መጠኑ በጣም ብዙ ነው፡፡ ይህንን የሰርጉ ደጋሽ ሴቶች ብቻቸውን አበጥረው የሚጨርሱት አይደለም፤ የግድ የሌሎችን እገዛ ይጠይቃልና ለጎረቤቶችና ዘመዶች የእህል ማበጠሪያው እለት ይገለጻል፡፡ የሰሙትም፣ ‹‹ የእከሌ ሠርግ የእህል ማበጠሪያ ቀን በዚህ እለት ነው፡፡›› እያሉ ላልሰሙት ሴቶች በመንገር ተጠራርተው ወደ የሰርጉ ደጋሽ ቤት ያመራሉ፡፡ ለጠላ (ለዝልልና ለኮረፌ) የሚሆነውን እህል፣ ማሽላ፣ በቆሎና ገብስ ቆሻሻውን በማንሳት(በመልቀም)፣ ለእንጀራ (ለጣቢታና ለድጎሎ) የሚሆነውንም እህል ያበጥራሉ፡፡ እንደ ሰፌድ፣ ወንፊት፣ ማንዘርዘሪያ እና የመሳሰሉትን ለመልቀምም ሆነ ለማበጠር የሚያስፈልጉትን ቁሳቁሶች ከየቤታቸው የሚያመጡትም የስራው ተሳታፊዎች ናቸው፤ ስለዚህ የጉልበት ብቻ ሳይሆን የቁሳቁስ እገዛውም የሚጠበቅና የማይቀር ነው፡፡

እንደ አሁኑ ጊዜ በየቦታው የእህል ወፍጮ ባልነበረበት ቀደም ባለው ወቅት ደግሞ፣ መጠኑ ከፍተኛ የሆነውን ለሠርግ ድግስ የሚሆን እህል፣ የሠርጉ ደጋሽ ሴቶች ብቻቸውን ፈጭተው የሚጨርሱት አልነበረም፤ ስለዚህ ሌሎች ሴቶች ተከፋፍለው ወደ ቤታቸው በመውሰድ ይፈጩት ነበር፤ ባሁኑ ጊዜም እህሉ፣ ቀደም ሲል ‹‹እስክር›› እየተባለ በድንጋይ ወፍጮ ይፈጭ የነበረው ብቅል ሳይቀር በወፍጮ ቢፈጭም፣ ሴቶቹ ግን ‹‹የወፍጮ (የማስፈጫ)›› እያሉ ለደጋሽዋ እገዛ የሚሆን ብር ይሰጧታል፡፡ ሊጡ(ብሆው) የሚቦካውም እንዲሁ በሴቶች ነው፤ ብዙ ከሆነና ከሴቶቹ አቅም በላይ ከሆነም፣ ወንዶችም በማቡካቱ ስራ ላይ ይሳተፋሉ፤ ለወጥ የሚሆነው አተር ወይም ባቄላ የሚከካውም እንዲሁ በሴቶች ነው፡፡

በሰርጉ ወቅት ከክክ ወጥ ጋር የሚቀርበው እልበት (በኽምጣኛ **እዞም**) የሚዘጋጀው በሴቶች እገዛ ነው፤ ሴቶቹ ለእልበት የሚሆነውን ሱፍና ሌሎች ማጣፈጫዎችን ይደቁሳሉ፡፡

በእንጨት ሙቀጫ ይወቀጥ የነበረው በርበሬ በአሁኑ ጊዜ በወፍጮ ቢፈጭም፣ ለወጉ እንደ ቀድሞው ጨው ደቆሳ ተብሎ ሴቶች ወደ የሠርጉ ቤት እንጀራ ይወስዳሉ፤ እልል እያሉ መጠነኛ የሆነ ዘፈንም ይዘፍናሉ፡፡ ከሚዘፈነው ዘፈን ቃል ግጥም መካከልም፣ የሚከተለው አዝማች ይገኝበታል፡፡ በእልልታ ታጅቦም ይዜማል፡፡

አቀ. ሙሽራ አበባ ሙሽራ አበባየ፣

ተቀ. ነይማ ነይ፡፡

ለድግሱ የሚሆነው ኮረፌ ወይም ዝልል አብሽሎ የሚጋገረውም በሴቶች እገዛ ነው፡፡ የጠላ ዝግጅቱ ከተጀመረ ጀምሮ (በብዛትም በሠርጉ ዋዜማ እና በእለቱ) ከወንዝ ወይም በአቅራቢያው ከሚገኝ ቧንቧ ውሃ ያመጣሉ፤ በእነሱ አቅም ሊሸፈን የማይችል ከሆነም በትከሻቸው ወይም በአህያ በመጫን በሚያመጡ ወንዶች ይታገዛሉ፡፡ የድግሱ እንጀራ በምጣድ(በምኅኅ )[56]የሚጋገረውም በሴቶች ነው፡፡ ከሠርጉ እለት ዋዜማ ጀምሮ በበርሜል ወይም በጋን ጠላ (ኮረፌ) የሚጠመቀውም በሴቶች ነው፡፡ ኮረፌውን የሚጠምቁትም በወንጠፍት ሲሆን፣ የወንጠፍቱ ጫፍ ኮረፌውን ነክቶ እንዳይርስና እንዳይበጣጠስ፣ እንዲሁም የሚጠመቅበት ጋን በጠማቂዋ ጫና ምክንያት እንዳይጎዳ ሲባል ወንጠፍት የሚቀመጥበት የእንጨት እርብራብ በሳር ተደልድሎ ይዘጋጃል፡፡ ይህ ለጠላ መጥመቂያነት የሚያገለግል እርብራብ በአማርኛ *መጥመቂያ* ሲባል፣ በኽምጣኛ ደግሞ **መደቋድቁ** ይባላል፡፡ ይህ *መጥመቂያ* የውሃ ጀሪካንን ወይም እንስራን ለማውረድም ስለሚያገለግል፣ ሌሎች ሴቶችን ‹‹አውርዱልን›› እያሉ በመጠየቅ እንዳያስቸግሩ ይረዳል፡፡

በዋግ ኽምራ በሠርግ ድግስ የሚቀርበው ወጥ ሁለት ዓይነት ነው፡፡ የስጋ (በአካባቢው አጠራር **የመረቅ**) እና የክክ (በአካባቢው አጠራር **የእህል ወጥ**)፡፡ የክክ ወጡ የሚሰራውም በሴቶች ነው፡፡ የክክ ወጥ አሰራር ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቅ በመሆኑ በባልቴት ሴቶች በትእግስትና በማያቋርጥ ክትትል ነው የሚሰራው፤ ስለዚህም የአሮጊት ሴቶች ስራ ተብሎ

[56] በዋግ ኽምራ ለስላሳው ጠፍጣፋውና ጥቁር ቀለም ያለው እንጀራ የሚጋገርበት ሸክላ ምኅኅ ሲባል፣ ምጣድ ግን ለምግብ ወይም ለጠላ የሚሆን ቂጣ ( **አብሽሎ** ) የሚጋገርበት ቀላ፣ ጎድጎድና ሸከር ያለ የሸክላ አይነት ነው፡፡

ይመደባል፡፡ የስጋ ወጡ በወንዶች ቢሰራም ወጡን ከሚሰራበት እቃ ለማስተናግድ ወደሚቀርብበት ድስት፣ ወይም የብረት ድስት የሚቀዱት ግን ሴቶች ናቸው፡፡ በተዘረዘሩት የስራ እገዛዎች ወቅት፣ ደጋሾቹ ለሴቶቹ ኮረፌ እና እንጀራ በአዋዜ ያቀርቡላቸዋል፡፡

**የወንዶች የስራ እገዛ**

እንደ ሴቶቹ ሁሉ ወንዶችም የሠርጉ ድግስ ከተጀመረ ጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ እገዛቸውን ይቀጥላሉ፡፡ ለድግሱ የሚሆነውን እህል ወደ ወፍጮ ቤት ለመውሰድ የማጓጓዣ አህያ ወይም በቅሎ ያውሳሉ፡፡ እንደ አሁኑ የበርበሬ ወፍጮ ባልነበረበት ጊዜ ወንዶች በርበሬ ይወቅጣሉ፡፡ ለድግስ የሚቦካው ሊጥ ብዙ ከሆነም በማቡካትና ውሃ በማምጣት ሴቶችን ያግዛሉ፡፡ የማገዶ እንጨት ከገበያ ስለማይገዛ ከጫካ(ከበረሃ) የሚያመጡትም ወንዶች ናቸው፡፡ በአሁኑ ጊዜ እንደ ተፈለገ ደንን በመጨፍጨፍ የማገዶ እንጨት በገፍ ማጓጓዝ አይቻልም፤ በየቀበሌው ለሚገኝ የደን ኮሚቴ አስቀድሞ ማስፈቀድ ያስፈልጋል[57]፡፡ የዳስ ስራው የሚከናወነውም በወንዶች ነው፡፡ የሠርጉ ድግስ ከፍ ያለ ከሆነ በሬው፣ ዝቅ ካለም ፍየሉ የሚታረደው፣ ስጋው የሚቆራረጠው፣ የስጋ ወጡ በትልቅ ብረት ድስት(በጎላ) የሚሰራው በወንዶች ነው፡፡

ወንዶች ለድግሱ የሚያስፈልጉ እቃዎችን ከየቤቱ በማፈላለግም ያሰባስባሉ፡፡ ኮረፌውን ወይም ዝልሉን ከጋን ወይም ከበርሜል የሚቀዱትና በሰርጉ እለት ለተስተናጋጆች የሚያድሉትም ሆነ ወጥ የሚያወጡት(የሚጨልፉትም) ወንዶች ናቸው፡፡ ለማስተናገድ እንዲቻል እንጀራውን ስድስት ስድስት ወይም አምስት አምስት በመቁጠር በመሶብ በመሶብ ወይም በሌማት በሌማት የሚመድቡት(በመስሪያ በመስሪያ የሚያዘጋጁት)፣ አጣጥፈው ለብሰው ከዳሱ መግቢያ ላይ በመቆም ተስተናጋጆችን ቦታ ቦታ የሚያሲዙት አስተናባሪዎች(**አጋፋሪዎች**) ወንዶች ናቸው፡፡ የሰርጉን ታዳሚ የሚያስተናግዱትም (**የሚያሳልፉት**) ወንዶች ናቸው፡፡ ከዚህም ሌላ የድግሱን መጠን፣ ማጫውንና ስጦታውን አስመልክቶ ለወንዱም ሆነ ለሴቷ ወገኖች የሚያማክሩት እና ስጦታውንና የጋብቻውን ውል የሚያከናውኑትም ወንዶች ናቸው፡፡

---

[57] በ21/ 09/05 ማይ ግንዶ በተባለው ቦታ በነበረው ሠርግ ላይ ደጋሾቹ ቀደም ብለው ባለማስፈቀዳቸው እንጀራ የሚጋገርበት እንጨት እርጥብ በመሆኑ ጋጋሪዎቹ በመቸገራቸውና በዚያም ላይ ዝናብ ጥሎ ምጣድ ወደ ተተከለበት ቦታ ጎርፍ በመግባቱ ምክንያት፣ ሙሽራዋ በስራ ተጠምዳ ላይ ታች ከማለቷም በላይ አምርራ ስታለቅስ « በሰርገሽ አታልቅሽ » ተብላ ስትገለገል ነበር ፡፡

ባጠቃላይ በሠርግ ድግስ የሚበላውንና የሚጠጣውን ደጋሾቹ ቢያወጡም፣ ስራው ሙሉ በሙሉ የሚሰራው ግን በጎረቤትና በቤተ-ዘመድ እገዛ ነው፡፡ በ29/08/04 ዓ.ም ስሬል ሊባኖስ በተባለ የገጠር ቀበሌ ላይ፣ ባንድ የሠርግ ድግስ ሁለት (ሴትና ወንድ) ልጆቻቸውን የዳሩት ቄስ አለሙ ወረታ የታገዙትን እንዲህ ገልጸውታል፤ ‹‹የእኔ ጉልበት ብዙም አይደለም፤ አንድ ሶስተኛውን አልሸፈነም፤ የድግሱን ስራ የሰራው ዘመድና ጎረቤት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ለጉልበት ያወጣሁት ወጭ አነስተኛ ነው›› (ቁ.የ.መ.አ.6)፡፡


በጾታ በመለየት ካሳየሁት እገዛ በተጨማሪ በሁለቱም ጾታዎች የሚታገዝም አለ፤ይህም የወዳጅ ዘመድ እገዛ ነው፡፡

**የወዳጅ ዘመድ እገዛ**

ለሠርግ ደጋሾች የሚደረገው እገዛ በሃሳብና ጉልበት ብቻ አይደለም፤ ድግስ በመደገስም ነው፤ ይህም አጋሮቹ ለደጋሾቹ ባላቸው ዝምድና እና ቀረቤታ ይወሰናል፡፡ በጣም ቅርብ ዘመድ ወይም ጥብቅ ወዳጅ የሆኑ አውራጅ ይይዛሉ፡፡ ይህም ዝቅተኛው አስራ ሁለት ድስት ወጥ፣ ከፍተኛው ደግሞ እስከ አስራ አራትና አስራ አምስት ድስት ወጥ፣ አንድ ጋን ጠላና መቶ ሃያ እንጀራ ነው፤ ስልሳ እንግዳም ይስተናገድበታል[58]፤ ይሸኝበታል። ባንድ ሠርግ አራት አውራጅ ያገኙ ቢኖሩ፣ 240 እንግዶችን ያስተናግዳሉ፡፡

ቀደም ሲል ግን በአንድ አውራጅ የሚስተናገደው ሰው መጠን የተወሰነ እንዳልነበር አቶ ተቀባ የተባሉት የመረጃ አቀባየ ገልጸውልኛል (ቁ.የ.መ.አ.27)፡፡ አውራጅ ያገዙ የክክ ወጥና አዞ ወይም እልበትም ያዘጋጃል፡፡ ቀደም ሲል የአውራጅ ምግብ አቀራረብ በሁሉም ቦታ የደደሆ ቅጠል በተደለደለበት ላይ እንጀራ ተደርጎ እዛ ላይ ወጥ በማድረግ ነበር፡፡ አሁን አሁን ግን አልፎ አልፎ እንደ ዋናው ሠርግ በመስሪያ እየቀረበ ነው፡፡

[58] በዝቋላ ወረዳ ግን አንድ አውራጅ ሁለት ጋን ጠላ ፣ አስራ ሁለት ድስት ወጥና 160 እንጀራ ሲሆን ፣ የሚስተናገደው 32 ሰው ነው፡፡



የአውራጅ ምግብ አቀራረብ (ፎቶ በአፀደ ተፈራ)

አውራጅ ለመያዝ አቅም የሌላቸው ደግሞ ጋን ጠላ በመጥመቅ ደጋሹን ያግዛሉ፡፡ መጠኑ እንደ ደጋሹ ካሁን በፊት አውራጅ እንደያዘውና ጋን ጠላ እንደጠመቀው መጠን (እጅ) የሚወሰን ነው፡፡

ለአብነት ያህል በ29/08/04 ስሬል ሊባኖስ ላይ በተመለከትኩት ሠርግ አራት አውራጅ ተይዞ ነበር፤ በ2/5/05 አቢያ ሊባኖስ በተባለው ቦታ በተመለከትኩት ሠርግ ደግሞ ሁለት አውራጅ ተይዟል፤ አርባ ጋን ጠላም በሌሎች ተጠምቋል፡፡

ከድግስ እገዛ በተጨማሪ ለደጋሹ የገንዘብ ድጋፍም ይደረጋል፡፡ ይኸውም በሠርጉ እለት ታዳሚው ብር ወይም በአይነት ከብት ይሰጣል(ይጥላል፤ይመርቃል)፡፡ በተለይ የምትዳረው ሴት ከሆነች፣ ለወ'ንድ ወገ'ን ለሚሰጠው ስጦታ ድጋፍ እ'ንዲሆ'ን የሚጣለው ብር በዛ ያለ ይሆናል፡፡ ይህ ብር(ውድቂት) ይባላል፤ ብሩ የሚሰበሰበውም በአገልግል ወይም በመሶብ ነው፤ ይህ አገልግል ወይም መሶብ ብሩ ከመጣሉ አስቀድሞ እንጀራ ይደረግበትና በካህን አማካይነት ጸሎት ተደርጎበት ለገንዘብ ማሰባሰቢያነት ይዘጋጃል፡፡ ያ እንጀራም ተቆራርሶ

በዳሱ ውስጥ ለሚገኙ ሰዎች ይታደላል፤ ባንዳንድ ቦታዎች ላይም ከፊሉ እዛው ከሚሰበሰበው ብር ጎን ይቀመጣል፡፡

ከሠርጉ ታዳሚዎች መካከል አዋጅ ነጋሪና ጸሀፊ የሚሆኑ ሰዎች ይመደባሉ፡፡ አዋጅ ነጋሪ የሠርጉ ታዳሚያን ለደጋሹ የሚሰጡትን፣ የሚጥሉትን ወይም የሚመርቁትን ብር ከእያንዳንዱ ሰው እየተቀበለ ሳይበዛ የተወሰነ የተወሰነውን የሚያሰባስብ ነው፤ ይህንን የሚያደርገውም ነጠላውን አጣጥሎ በመልበስና ከታዳሚዎቹ መካከል በመንቀሳቀስ ነው፡፡ ብር የሚሰጠው ሰው አድራሻው የት እንደሆነ ድምጹን ከፍ አድርጎ በመግለጽም የሰበሰበውን ብር ለሌላ ተረካቢ ሰው ያስረክባል፡፡ አዋጅ ነጋሪ ልምድና ጥሩ ድምጽ ያለው መሆን አለበት፡፡ የአዋጁ ወይም ማን ምን ያህል ብር እንደጣለ የማስተጋባቱ አስፈላጊነትም እያንዳንዱ ታዳሚ በዚያ ሠርግ ምን ያህል ብር እንደ ጣለ እንዲታወቅ ነው፤ አዋጅ መባሉም ለዚህ ነው፡፡ አዋጅ ነጋሪ መሆን ያለበትም ወንድ ነው፤ ምክንያቱን መረጃ አቀባዮቹ ሲገልጹ፣ በባህላችን ሴቶች አዋጅ ነጋሪ አይሆኑም፡፡›› የሚል ነው (ቡ.ቃ 3እና4)፡፡ አቢያ ሊባኖስ በተባለው ቦታ ሠርግ ላይ እንደተመለከትኩት ደግሞ፣ ብር መጣል ያለበት የሠርግ ታዳሚ ሁሉ መስጠቱ ከተረጋገጠ በኋላ፣ እያንዳንዱ ሰው የጣለው የብር መጠን በትክክል መመዝገቡን ለማረጋገጥ እንዲችል የተጻፈው ለታዳሚው ተነቧል፡፡ ይህም ምግብ ከመቅረቡ በፊት የተከናወነ ሲሆን፣ ገንዘብ የሰጡት ሰዎች በሙሉ ከዳሱ አልወጡም ነበር፡፡ በሌላዎቹ በተመለከትኳው ሰርጎች ላይ ግን ታዳሚዎቹ ብራቸውን እየጣሉ በልተው ጠጥተው ይሄዳሉ እንጂ፤ የጣሉት የብር መጠን በትክክል መጻፉን እንዲያረጋግጡ አልተነበበላቸውም፡፡ በሠርግ ላይ የሚጣለው የገንዘብ መጠን እኩል አይደለም፡፡ እንደ ሰው አቅምና እንደ ቀረቤታ ይወሰናል፡፡ ወዳጅና ቤተ-ዘመድ የሚጥለው የገንዘብ መጠን ከሌላው የሠርግ ታዳሚ በዛ ያለ ነው፡፡ በተመለከትኳቸው ሰርጎች ዝቅተኛ የተጣለው ሁለት ብር ሲሆን፣ ከፍተኛው ደግሞ ሰባት መቶ ብር ነው፡፡ የጣለው/ለችው ሰው ሲድር/ስትድር ደግሞ ሲሆን ተጨምሮ (ሃምሳ ለጣለው ስልሳ ተደርጎ) ካልሆነ ደግሞ የተሰጠው ካልተመለሰ ያወቃቅሳል ይላሉ የመረጃ አቀባዮቹ (ቡ.ቃ.4)፡፡



አዋጅ ነጋሪ ገንዘብ ሲሰበስብ (ፎቶ በመብራት መኮንን)

ብር የሚጥሉት አብዛኛዎቹ ወንዶች ሲሆኑ ሴቶች ግን በብዛት ብር አይጥሉም፡፡ ሴቶች ቀደም ሲል፣ እንጀራ በመሶብ አሸክመው ወደ ሠርጉ ቤት ይወስዱ ነበር፤ አሁን አሁን ግን የሚወስዱት ዱቄትና እህል ነው፡፡ ይህም የተጀመረው ከ1980ዎቹ ወዲህ መሆኑንና ምክንያቱም ብክነትን ለመከላከል መሆኑን ነው የመረጃ አቀባዮቼ የገለጹት፡፡ ምክንያቱም ደጋሾቹ ከታዳሚው የሚመጣውን የእንጀራ መጠን ግምት ውስጥ ሳያስገቡ፣ ብዙ እንጀራ ስለሚያስጋግሩ፣ ከታዳሚው በርካታ እንጀራ ስለሚመጣ፣ ብዙ እንጀራ ተበላሽቶ ይቀር ነበር፡፡ ዱቄቱና እህሉ ግን ቢቀመጥም ስለማይበላሽ ደጋሾቹ ወደ ፊት በሚያስፈልጋቸው ወቅት ሊጠቀሙበት ይችላሉ (ቁ.የ.መ.አ.5 እና11)፡፡

የዱቄቱ ወይም የእህሉ መጠንም በአብዛኛው ዝቅተኛው ሁለት ጣሳ (በግምት ሶስት ኪሎ) ሲሆን፣ ከፍተኛው ግን የሠርጉ ታዳሚዎች ለደጋሾቹ ባላቸው ቀረቤታ የሚወሰን ነው፡፡ አብዛኛዎቹ ሴቶች የሚያመጡትና የሚያስረክቡት በግላቸው አይደለም፤ አምስት ስድስቱ ተሰባስበው በጆንያ(ኬሻ) ወይም አቅማዳ፣ የማን የማን እንደ ሆነ በመናገር ነው፡፡

ተረካቢዎቹም የሚመጣውን ዱቄትና እህል እየተቀበሉ ከመዘርገፍ በስተቀር፣ መጠኑን በመለካት ሲረከቡ አልተመለከትኩም፡፡

**የዳስ (በኽምጣኛ ደዘ) አሰራር**

የሠርግ ድግስ የሚደገሰውና ታዳሚው የሚስተናገደው በትልቅ ዳስ ውስጥ ነው፡፡ ዳሱም የሚሰራው ቀደም ሲል ከጫካ በሚቆረጥ የደደሆ ቅጠል ብቻ ነበር፡፡ አሁን አሁን ደግሞ ደን እንዳይጨፈጨፍ በማለት ከተወሰነ የደደሆ ቅጠል፣ ከባህር ዛፍ፣ ከቄንጾ በርበሬ ቅጠልና በፕላስቲክ(ኬንዳ) ነው፡፡ ዛፉ እንደ ተገኘ አይቆረጥም፤ ከሠርጉ ቀን አስቀድሞ የሚመለከታቸውን አካላት ማስፈቀድ ያስፈልጋል፡፡ ይህንን አስመልክተው አቶ ተበጀ በላይና አቶ ደሳለኝ ስዩም ሲገልጹ፣ ‹‹ለሠርግ ዳስ መስሪያ የሚሆን የደደሆ ዛፍን በሚመለከት ፈቃድ የሚጠየቅ የደን ኮሚቴ አለ፡፡ ከወር በፊት ሠርግ እንደሚደረግና የሠርጉ መጠን ከቀበሌው ተረጋግጦ በተወሰነ ቦታ ብቻ እንዲቆረጥ ወስኖ ይሰጣል፡፡ ይህም ከሚታረስ እርሻ እንጂ እንደ ቀድሞው የተገኘው ሁሉ አይቆረጥም፡፡›› ብለዋል፡፡ለዳሱ የሚሆነው ባላም እንደ ቀድሞው ዛፍ እየተቆረጠ ሳይሆን ተፈላልጎ ከጎረቤቶች የሚመጣ እንደሆነ ነግረውኛል (ቁ.የ.መ.አ.7)፡፡ የዳስ ስራው የሚከናወነው በሰርጉ ዋዜማ ሲሆን[59]፣ የሚሰራውም በሠርጉ አካባቢ በሚገኙና ከሩቅ ቦታ በሚመጡ የደጋሹ የቅርብ ወንድ ዘመዶች፣ ‹‹የዳስ ስራው ዛሬ ነው፤ አንዳንድ እንጨትና የቄንጾ በርበሬ፣ የባህር ዛፍና ኬንዳ ያላችሁም ይዛችሁ እንድትመጡ›› ተብሎ ተነግሯቸው ነው፡፡

እንደተመለከትኩት ከሆነ ዳሱ የተለያዩ ተግባራት ይከናወኑበታል፡፡ እንጀራ ይጋገርበታል፤ ይከማችበታል፤ ጠላ ይጠመቅበታል፤ ወጥ ይሰራበታል፤ የሠርጉ ታዳሚ ይስተናገድበታል፤ እንደ ከተማ የተለየ ከፍ ያለ የሙሽራዎቹ መቀመጫ ስቴጅ ባይሰራም፣ ሙሽራዎቹ ከፍ ያለ ቦታ ተመርጦ የሚያርፉትም እዚሁ ዳስ ውስጥ ነው፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚገባው የዳሱ ስፋት ነው፡፡ መጠኑ የተወሰነ አይደለም፤ በርከት ያለ ድግስ የሚደግስ ሰው፣ ‹‹ፈረስ ያስጋልባል!›› የሚባልለት አይነት ሰፊ፣ ውሱን ድግስ የሚደግስ ደግሞ ጠበብ ያለች ዳስ ያሰራል፡፡ ለአብነት ያህል ስሬል በተባለው ቀበሌ

[59] ለድግስ ስራው የመኖሪያ ቤታቸው ጠባብ የሆነባቸው ደጋሾች ግን፣ ለተለያዩ ስራዎች የምታገለግል ግጭላ የምትባል ትንሽ ዳስ አስቀድመው ይሰራሉ፤ ይህች ዳስ አውራጅ የሚይዙ ሰዎችም ከዋናው ዳስ ውጭ ማስተናገድ ከፈለጉ እንግዶቻቸውን የሚያስተናግዱባትም ናት፡፡

ሁለት ልጆቻቸውን የዳሩት የቄስ አለሙ ወረታ ሠርግ ዳስ፣ የሌላዎቹን አራት እጥፍ የሚያክል ነበር፡፡ ምክንያቱም ድግሳቸው በጣም የበዛ ከመሆኑም ሌላ፣ የምግብ ዝግጅታቸውና የማስተናገጃ ዳሳቸውም ለከተማ እና ለገጠር ሰው ተብሎ በሁለት የተከፈለ ነበር፡፡

ቀደም ሲል ዳሱ እስከ ሳምንት ሳይፈርስ ይቆይ ነበር፤ ምክንያቱም የሠርግ ቀናቱ ሁለትና ከዚያ በላይ በመሆኑ፣ ከሩቅ የሚመጡት ታዳሚዎች የሚውሉበትና የሚያድሩበት ስለነበር ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን የሰርጉ ቀን አንድ ቀን ብቻ በመሆኑ፣ ዳሱ በማግስቱ ወይም በሶስተኛው ቀን ይፈርሳል፡፡ ዳሱ ሲፈርስ ንፍሮ ይቀቀላል፤ ቆሎ ግን አይቆላም፤ ምክንያቱም ንፍሮ ካልተቀቀለበት የጉንፋን በሽታ ይይዛል ተብሎም ይታመናል፡፡ ለዚህም መከላከያ እንዲሆን ማንም ሰው ከመቅመሱ በፊት ንፍሮ ወደ ውጭ እንዲረጭ ይደረጋል፡፡ ይህም በአካባቢው ለሚገኘው ቆሌ ለማቋደስ ነው፡፡ ጎረቤቶችም ወደ ፊት ህመም እንዳይዛቸው በማሰብ እየተጠሩ ይቀምሳሉ፡፡

### የሠርግ ድግስ ወጥ አሰራር


በዋግ ኽምራ የሠርግና የሌላ ድግስ ወጥ የሚሰራው ሙሉ በሙሉ በሸክላ ድስት ብቻ ነበር ቀደም ብለውም በትእዛዝ በርካታ የሸክላ ድስት ይገዙ ነበር፡፡ ደጋሾቹን ከፍተኛ ወጭ ከሚያስወጣቸው አንዱ የሸክላ ድስት መግዣ ነበር፡፡ ለአብነት ያህል አቶ ተቀባ የተባሉትን አምደወርቅ የሚኖሩትን የመረጃ አቀባየ መጥቀስ ይቻላል፤ ልጆቻቸውን ሲድሩ ከከተማው ወጣ ብሎ ከሚገኝ አርቢት ከምትባል ቦታ እስከ መቶ የሸክላ ድስት ይገዙ እንደ ነበር ነግረውኛል (ቁ.የ.መ.አ.27)፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከደገሱ ሰዎች በትውስት ያሰባስቡ ነበር፡፡ ለዚህም በርካታ ሴት የወጥ ሰሪዎች በስራው ይጠመዱ ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን በአብዛኛው ወጥ የሚሰራው በትልቅ የብረት ድስት(በጎላ) ነው፤ የሚሰራውም በወንዶች ነው፡፡ በትልቅ የብረት ድስት የተሰራው ወጥ ለማስተናገድ የሚቀርበው ግን ወደ የሸክላ ድስት ወይም ትናንሽ የብረት ድስቶች ተቀድቶ ነው፡፡ ምልከታ ካከናወንኩባቸው አስር የሠርግ ድግሶች መካከል በአንዱ ብቻ ነበር ወጡ ሙሉ በሙሉ በድስት ብቻ ተሰርቶ የተመለከትኩት፤ ይህም በለዛ ማርያም(በለዛ ተክለ ሃይማኖት) በተባለው ቦታ በነበረው ሠርግ ነው፡፡ ወጥ የተሰራባቸውና ወስከንቢያ የተከደኑ ድስቶች ተደርድረዋል፤ ለወጥ ስራውም በርካታ ሴቶች ተሰልፈው ነበር፡፡



**ወጥ ከተሰራባቸው የሸክላ ድስቶች ውስጥ በከፊል (ፎቶ በአፀደ ተፈራ)**

ይህ የሚያመለክተው በመኪና መንገድ ላይ ከሚገኙ የገጠር መንደሮች ራቅ ሲባል፣ እንደ ቀድሞው ሁሉ ወጡ በትልቅ የብረት ድስት ሳይሆን፣ በብዙ የሸክላ ድስት እየተሰራ መሆኑን ነው፡፡

ወጥ በሸክላ ድስት ከሚሰራ ይልቅ በትልቅ የብረት ድስት መሰራቱ ጠቀሜታ እንዳለው ነው ወ/ሮ ሙሉወርቅ አወጣ እንዲህ የገለጹት፤‹‹እንጨት ይቆጥባል፤ በተወሰኑ ወንዶች በአንድ ላይ ስለሚሰራም ጉልበትንና ጊዜን ይቆጥባል፤ በርበሬውና ቅባቱም የተመጣጠነ ይሆናል፤ በተለያዩ ሴቶች በተለያየ መንገድ በመሰራቱ ልዩነት የነበረው የወጥ ጣእምም አንድ ዓይነት ይሆናል›› (ቁ.የ.መ.አ.14)፡፡



**ወንድ በጎላ ወጥ እየሰራ (ፎቶ በጋዝጊብላ ወረዳ ባቱ)**

የክክ ወጥ የሚሰራው ደግሞ በእንስራ ወይም በቶፋ ነው፤ እንስራው ወይም ቶፋው የሚጣደውም ዙሪያውን እሳት በማንደድ ከታች ግን የጤፍ ገለባ ተደልድሎ በተቆፈረ ጉድጓድ ውስጥ በመቅበር ነው፡፡ እ'ንስራው ወይም ቶፋው በጉልቻ የማይጣድበት ምክ'ንያትም እ'ንሰራው እ'ንዳይጎዳና ወጡም እ'ንዳይጎረና ነው፡፡ የክክ ወጡ'ን የሚሰሩትም እረጋ ያሉና በእድሜ የገፉ እናቶች ናቸው፡፡ ወጣት ሴቶች ደግሞ ወደ ፊት እነሱ መስራት እንዲችሉ እንዴት እንደሚሰራ ካጠገባቸው ተቀምጠው ይመለከታሉ፡፡

## የሠርግ ታዳሚዎች አቀባበልና በዳስ ውስጥ አቀማመጥ

ወንዶችም ሆኑ ሴት የሠርግ ታዳሚዎች ወደ የሠርግ ቤት የሚሄዱት፣ እንዳቅማቸው ጸዳ ያለ ልብሳቸውን ለብሰው ነው፡፡ ሴቶቹ ጸጉራቸውን አዲስ ሹሩባ ይሰራሉ፤ ቅቤ ይቀባሉ፤ ንጹህ ቀሚሳቸውንና ነጠላቸውን ይለብሳሉ፤ የክት መቀነታቸውንም ይታጠቃሉ፤ እመጫት ከሆኑም በዛጎልና በድባ በተዋበው አንቃልባ(ማዘያ)ልጆቻቸውን ያዝላሉ፡፡ ወንዶችም በተለይ በእድሜ ገፋ ያሉት ሱሪ ይለብሳሉ፤ ኩታቸውን ይደርባሉ፤ ወጣቶቹም ቁምጣቸውንና ኳርቶ ሸሚዛቸውን ይለብሳሉ፡፡

የሠርጉ ታዳሚዎች በቀጥታ ሰተት ብለው ወደ ዳሱ አይገቡም፤ ከዳሱ ፊት ለፊት ተሰልፈው ይቆማሉ፤ በዚህ ጊዜ የዳሱ አስተናባሪዎች (አጋፋሪዎች) ሰላምታ ከሰጧቸው በኋላ ከወንዶቹ የሠርጉ ታዳሚዎች በትራቸውን፣ ከሴቶቹ ደግሞ ያመጡትን ዱቄት ወይም እህል የተቋጠረበት ከረጢት[60]በመቀበል፣ ወንዶቹን በወንድ ቦታ፣ ሴቶቹን ደግሞ በሴት ቦታ ያስቀምጧቸዋል፤ አቀማመጣቸውም እንደ እድሜያቸው ከፍ ያሉት ከፍ ባለ፣ ዝቅ ያሉት ደግሞ ዝቅ ባለ ቦታ ላይ ነው፡፡

ለመቀመጫነት የሚያገለግለውም በረድፍ በረድፍ ሆኖ መሬት ላይ የተደለደለ ገለባ፣ የማሽላ አገዳ፣ ከተገኘም አግዳሚ እንጨት ወይም ጣውላ ነው፡፡ ተስተናጋጆች ቦታ ቦታቸውን እንደ ያዙም፣ በጆንያ የመጠጪያ ፎሌ(ሽክና) ይዘው የሚያስተናግዱ ወጣቶች፤ ለታዳሚያኑ መጠጫ በማደል ኮረፌ ለሚፈልገው ኮረፌ፣ ዝልል ለሚፈልገው ደግሞ ዝልል ይቀዳሉ፡፡ በአብዛኛው ከምግብ በፊት የሚቀርበው ግን ኮረፌ ነው፡፡ ምክንያቱም ‹‹ዝልል ሆድን ይሸረሽራል፤››ስለሚባል ከምግብ በፊት አይቀርብም፡፡ መጠጪያን በሚመለከት በአብዛኛዎቹ የሠርግ ድግሶች የተመለከትኩት በፋብሪካ ከፕላስቲክና ከቆርቆሮ የተሰራ መጠጪያና ፎሌ ተቀላቅሎ ነው፡፡ ከመኪና መንገድ ወጣ ባሉት የገጠር ቀበሌዎች ግን በብዛት መጠጫ የነበረው ፎሌ ነው፡፡ መጠጪያ የሚሰበሰበውም ከሠርጉ ታዳሚዎች እና ከደጋሾቹ ነው፡፡ ምክንያቱም ደጋሾቹ ብቻ ለሠርጉ ታዳሚዎች የሚሆን በርካታ መጠጪያ ለማቅረብ አይችሉም፡፡ ስለዚህ ከድግሱ ቦታ በቅርብ ርቀት አካባቢ የሚመጡ የሰርጉ

[60] ለሠርግ የሚወሰደው እህልና ዱቄት መጠን እንደ ታዳሚዎቹ አቅም፣ ካሁን በፊት በተወሰደላቸውና ከደጋሾቹ ጋር ባላቸው ቀረቤታ የሚወሰን ቢሆንም፣ በብዛት ግን ከሁለት ጣሳ (ሶስት ኪሎ) በላይ ነው፡፡

ታዳሚዎች መጠጫ ፎሌያቸውን ይዘው ይመጣሉ፡፡ ከዚህም ሌላ እያንዳንዱ ጎረቤት ከየቤቱ ሁለት ሁለት ፎሌ እንዲያመጣ የሚታዘዝበት ጊዜ አለ፡፡



ዳስ ውስጥ የወንዶች አቀማመጥ፣ በፎሌ ኮረፌ እየጠጡ(ፎቶ በአፀደ ተፈራ)

## አመጋገብ

በዋግ ኽምራ በሠርግ ድግስ ላይ ሴቶች፣ ወንዶችና ህጻናት፣ ባንድ ቦታ ላይ አብረው ተቀምጠው አይመገቡም፤ ሶስቱም ለየብቻ ነው የሚስተናገዱት፡፡ እንዲያውም ዳሱ ጠባብ ከሆነ ወንዶች ዳስ ውስጥ ሲስተናገዱ፣ ሴቶችና ህጻናት ደግሞ ከዳስ ውጭ ይስተናገዳሉ፡፡ ከተመለከትኳቸው አስር የሠርግ ድግሶች መካከል፣ ሰፊ ዳስ ከነበራቸው ስሬልና ማይግንዶ ከተባሉት አካባቢዎች ሰርጎችና እንደ ሰቆጣ ከተማ እንጀራው ተቆርሶ ለእያንዳንዱ ሰው ለየብቻ በተሰጠበት ሀሙሲት በሚባለው የገጠር መንደር ከነበረው ሠርግ በስተቀር፣

ዳሶቻቸው ጠባብ በነበሩባቸው በሌላዎቹ ሠርጎች ግን ወንዶች ዳስ ውስጥ ሆነው ሲመገቡ፣ ሴቶችና ህጻናት የተመገቡት ግን ከዳስ ውጭ ነው፡፡ ሴቶች ለምን ለብቻቸው እንደሚመገቡ አቶ ተበጀ በላይ ሲገልጹ ‹‹ምክንያቱም ወንዱ እንጀራውን ወደ አፉ ለመውሰድ እጁ ፈጣን ነው፤ ሴቶች ግን ትንሽ ትንሽ ስለሚቆርሱና ቀስ ብለው ስለሚበሉ ይጎዳሉ፤ ብዙ ብዙ እንጀራ ጠቅለል አድርገው እንዳይጎርሱም ወንዶቹን ያፍሯቸዋል፡፡›› ብለዋል (ቁ.የ.መ.አ.4)፡፡



**ሴቶች[61] ሲመገቡ (በከፊል) (ፎቶ በአፀደ ተፈራ)**

[61] መሃል ላይ የሚገኙት ወጣት ወንዶች ወጥ አውጭዎች ናቸው፡፡



ወንዶች ሲመገቡ (በከፊል) (ፎቶ  በአፀደ ተፈራ)

የእንጀራው አቀራረብም ቀደም ሲል በአውራጅ አቀራረብ እንደ ተመለከትነው፣ ወንድ ባንድ ረድፍ፣ ሴት በሌላ ረድፍ ተቀምጠው በርካታ እንጀራ በደደሆ ቅጠል ላይ ይደረግና ከዛ ላይ ወጡ እየፈሰሰ ነበር፤ ይህም ብዙ እንጀራ እንዲበላሽ ያደርጋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን በአንድ የመመገቢያ ምድብ (መስሪያ) አምስትና ስድስት እንጀራ፣ ከተገኘ ከላይ ሳህን በተደረገበት ካልተገኘም በመሶብ ወይም በሌማት ላይ ይቀርባል፡፡ በአንድ መስሪያም አምስት ወይም ስድስት ሰው በመመደብ በመጀመሪያ በድስት ወይም በትንሽ የብረት ድስት የስጋ ወጥ(መረቅ) ይቀርባል፤ ወጥ አውጭው(ጨላፊው) የልብሱን እጅጌ ወደ ላይ ሰብሰብ አድርጎ እና እጁን በደንብ ታጥቦ፣ በመጀመሪያ ከወጡ ስጋ ያለውን አጥንት ያወጣል፡፡ ከዚያም እንጀራውን ቆራርሶ በመረቁ ይፈተፍትና ወደ ሳህኑ፣ ሌማቱ ወይም ሞሰቡ ላይ ይገለብጣል፤ የስጋ ወጡ ከተበላ በኋላ የክክ ወጡንና እልበቱን ድስቱ ላይ በማቀላቀል[62]እንጀራውን ፈትፍቶ ወደ መስሪያው በመዘርገፍ ታዳሚያኑ እንዲመገቡት ያደርጋል፤ ተስተናጋጆቹም በስጋ ወጡ በልተው ቢጠግቡም፣ ሁል ጊዜ የምናገኘው የክክ ወጥንና እልበትን ነው በማለት ይቀምሳሉ፤ ለወጥ አውጭውም ያጎርሱታል፡፡ ከዚያም ወጥ

[62] የክክ ወጥና እልበት በአብዛኛው የሚቀርበው በቅል ሲሆን፣ አልፎ አልፎ ግን የክክ ወጥ በቅል፣ እልበት ደግሞ በዘይት መያዣ ቆርቆሮ ሲቀርብ ተመልክቻለሁ ፡፡

አውጭው ለቃቅሞ ያወጣውን ስጋ ያለው አጥንት እንደ መጠኑ፣ በእድሜ ከፍ ላሉት ወንዶችና ሴቶች ያድላቸዋል፡፡ የወጥንና የእንጀራን መጠን በሚመለከት፣ የስጋ ወጡ አንድ ድስት ብቻ ሲሆን፣ የክክ ወጡ የእልበቱና የእንጀራው መጠን ግን የተወሰነ አይደለም፡፡ ታዳሚው እስከሚጠግብ ድረስ እየታየ ይጨመራል፡፡

በሴቷ ዳስ ውስጥ የወንድ ወገን አመጋገብ ብቻ ሳይሆን፣ የወጥ አሰራሩም የተለየ ነው፡፡ ወጣቸው የሚሰራውም ፍሪምባው ሳይቆራረጥ ተዘልዝሎ በአንድ ላይ ነው፡፡ መጀመሪያ እንዲመገቡ የሚደረጉት ሽማግሌዎቹ ናቸው፡፡ ሽማግሌዎቹ ከተመገቡ በኋላ ሚዜዎች የእነሱን ትራፊ እንጀራ በመጨመር ይመገባሉ፡፡



ለሽማግሌዎች የቀረበ ዝልዝል ፍሪምባ (ፎቶ በሰቆጣ ወረዳ ባቱ)

## የልጆች አመጋገብ

የልጆች አመጋገብ እንደ እድሜያቸውና ጾታቸው የተለያየ ነው፡፡ ከአምስትና እና ከስድስት ዓመት በታች ለሚሆኑት ህጻናት ልጆች፣ እናቶቻቸው ከሚመገቡት ቆንጠር አድርገው

በወስከንቢ.ያ ይሰጧቸዋል፣ ከእናቶቻቸው አጠገብ ተቀምጠውም ይመገባሉ፡፡ ተለቅ ያሉት ልጆች ግን ወላጆቻቸው ከተመገቡ በኋላ ከተረፈው ላይ ተጨማሪ እንጀራ፣ የክክ ወጥና እልበት ተደርጎ ሴቶችና ወንዶች ለየብቻቸው ቀርቦላቸው ይመገባሉ፡፡ እነዚህ ታዳጊዎች ከትርፍራፊው ይቀምሳሉ እንጂ፣ ለብቻቸው የስጋ ወጥ አይቀርብላቸውም፡፡



ልጆች ሲመገቡ በከፊል (ፎቶ በመብራት መኮንን)

## 5.3.2 የወንድ ወገን ወደ የሙሽራዋ ቤት ዘመቻ እና የዳስ ውስጥ ሥነ-ሥርዓት

ሙሽራው በራሱና በሚስቱ የሠርግ ቀን በሚዜዎቹና በሽማግሌዎች ታጅቦ ወደ ሴቷ ሙሽራ ቤት ለመሄድ(ለመዝመት) ይዘጋጃል፡፡ ሚዜዎች ይሰበሰባሉ፤ ከዘገዩም የመጥሪያ ምልክት የሆነው ጥሩንባ(ቱልቱላ) ይነፋል፡፡ መጥተውም ሙሽራውን ያጥቡታል፤ ያጋጌጡታል፤ ኩል ይኩሉታል፤ ሻሽ ይጠመጥሙለታል፤ ባርኔጣ ይደፉለታል፤ ነጭ ጋቢ ያለብሱታል፤ በትውስት ከቤተክርስቲያን የመጣን ካባም ይደርቡለታል።

ከዚያም ሙሽራው ወደ ዳስ በመግባት ይመረቃል፤ መራቂ ቤተሰቦችም እንደ አቅማቸውና ቀረቤታቸው ብር ይሸልሙታል፡፡ ሙሽራው ከዳሱ በሚወጣበት ወቅት፣ የወንድ ወገን ሴቶች በአማርኛ ‹‹በላየ በላየ ሙሽራው በላየ›› በኽምጣኛ ደግሞ ‹‹አሩር አሩር ለወ

ኻፍዝር ኻፍዝር ለው›› እያሉ በመዝፈን፣ ይሸኙታል፡፡ ትርጉሙም አፍሰህ አፍሰህ ፣ ዝቀህ ዝቀህ ተጠቅመህ ተመለስ ማለት ነው፡፡ ቃል-ግጥሙ ከሴቷ ሙሽራ ቤት ለሙሽራው እና ለቤተሰቦቹ የሚሰጠው ማጫ እና ስጦታ ብዙ እንዲሆን መፈለግን የሚገልጽ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ አቀንቃኞቹ ሙሽራውንና ወላጆቹን በቃል ግጥም ያሞግሷቸዋል፤ ከእነዚህ ቃል ግጥሞች መካከልም የሚከተለው ይገኝበታል፡፡

አዲሱ ሙሽራ ሻሽ የጠመጠመው፣

ልቤን እንደ ቆሎ አሽቶ ቆረጠመው፡፡

የዘፈኑ አቀንቃኞችም የመዝፈን ችሎታ ያላቸው ዘመዶች፣ ጎረቤቶች ወይም የሰርጉ ታዳሚ የሆኑ ሴቶች ናቸው፡፡ ለዚህም ነው፣

እኔ ምን ቸገረኝ ቃሌ ባያምር፣

አይደለሁ አዝማሪ ብር አልቀበል፡፡የሚሉት፡፡

በመቀጠል ሙሽራው በየቤቱ እየዞረ ይመረቃል፡፡ ከመራቂዎች መካከል አንዳንዶቹ ብር ይሸልሙታል፤ያንን ብርም ትልቅ ሚዜው ይሰበስባል፤ አንዳንዱም ብር ሳይሰጥ‹‹ ቆርባቸሁ ሰግዳችሁ እደሩ፤ ውለዱ ክበዱ!›› ብሎ ይመርቃል። ሙሽራው በመንደሩ ሰው እየዞረ ከተመረቀ በኋላ፣ ወደ ማታ ወደ ሴቷ ቤት በሚዜዎች ሆታ ታጅቦ ከሽማግሌዎች ጋር ይዘምታል፤ ሩቅም ቢሆን ወደ ሴቷ ቤት የሚሄዱት ወደ ማታ ነው፤ ምክንያቱም በቀን የሴት ወገኖች እንግዳዎቻቸውን እንዲሸኙ በማለት ነው፡፡ በዚህ ወቅት የሙሽራው አባት ‹‹አማችና አይን ጉድፍ አይወድምና ነገር እንዳትፈጥሩ›› ብሎ ሚዜዎቹን ያስጠነቅቃቸዋል፡፡

ዘማቾቹ ወደ ሴቷ ቤት በሚሄዱበት ወቅት በመንገድ ላይ ቤተክርስቲያን ካጋጠማቸው፣ ሙሽራው ከበቅሎው ወርዶ ይሳለማሉ፡፡ በዚህ ጉዞ ወቅት የያዘ እንስራ እንጂ ባዶ እንስራ የተሸከመች ሴት ዘማቾቹን አቋርጣ ማለፍ የለባትም፤ ባዶ እንስራ ተሸክማ ሙሽራዎቹን ለማቋረጥ ከሞከረች ሚዜዎቹ እንስራዋን ይሰብሩባታል፡፡

የወንድ ሙሽራ ወገን ዘማቾች ከሙሽራዋ መንደር አቅራቢያ እንደ ደረሱ፣ መምጣታቸውን የሚያስተጋባውን ወይም የሚያሳውቀውን ጥሩምባ ደጋግመው ይነፋሉ፤ ዘፈናቸውንም ሞቅ

ያደርጋሉ፤ የአካባቢው ወንዶችና ሴቶች ልጆችም ከእነሱ ጋር በመቀላቀል ጨዋታውን ያደምቁታል፡፡ ከሴት ወገን ወደ ዳስ እንዲገቡ ፈቃድ እስከሚያገኙ ድረስም፣ በአቅራቢያው በሚገኝ ከፍተኛ ቦታ ወይም ዛፍ አጠገብ ተቀምጠው እየዘፈኑ ይጠባበቃሉ። ሌላው ታዳሚና የወንድ ወገን ዳስ ውስጥ የሚቀመጡት ለየብቻ ስለሆነ፣ የሴት ወገን የማስተናገጃ ቦታ ካመቻቹላቸው በኋላ አንድ ሰው በመላክ ‹‹ግቡ›› በኸምጣኘ‹‹ጥውጥን››። ተብሎ ይነገራቸዋል። የወንድ ወገን ‹‹ሆ!›› እያለ ወደ ዳስ ለመግባት ሲሞክር፣ የሙሽራዋ ሴት ቤተሰቦች ከበሯቸውን ይዘው ‹‹በላየ በላይ በላይ ሆ በላይ ሙሽራው በላየ›› እያሉ በመዝፈን ይቀበሉታል፡፡ በዚህ ወቅት የሚገጠሙት ቃል ግጥሞች ይዘትም ሙሽራዋንና የሙሽራዋን ቤተሰቦች የሚያሞግሱ(የሚያወድሱ) ናቸው፡፡

ከእነዚህ ቃል ግጥሞች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል[63]፡፡

ሀ/ ለሙሽራዋ እናት የሚገጠም[64]

የሙሽሪት እናት ውጪ ተጠየቂ፣
የጠመቅሽው ጠላ ወይን ነው አረቂ።
ወይን ነው ወይን ነው ወይን ነው ጠላሽ፣
እስከ ቆላ ደጋ ተሰማ ዝናሽ፣
ተሰምቶም አልቀረ እኛም አየንሽ።
የሙሽሪት እናት ዘንከትከት[65] ያለችው፤
ከማጀቱ ገብታ ምኑን ሰበረችው፡፡
የሙሽሪት እናት ዝለቂ ባጥር፤
ባለሰጋር በቅሎ ባለደንገጡር[66]
ሰዎች ተሰብስበው እርሻ ሲካፈሉ፣

63 ቃል ግጥሞቹን የሰበሰብኳቸው ምልከታ ካደርግሁባቸው ሰርጎች ነው፡፡ ጭብጣቸውም ወደ ፊት በሥነ-ሥርዓቱ ፋይዳ ትንተና ላይ የሚታይ ይሆናል፡፡

64 ኸምጣኘ በሚነገርባቸው ቀበሌዎችም በአማርኛ የተገጠሙ ቃል ግጥሞችን አዳምጫለሁ፡፡ ምክንያቱም በመግቢያው እንደተገለጸው አብዛኛዎቹ የ ኸምጣኘ ተናጋሪዎች አማርኛም አንዳንዶቹም ትግርኛም ይናገራሉ፡፡

65 ረዘም

66 የሴት ሰራተኞች

የሙሽሪት እናት ደንበር ትሁን አሉ፡፡

ወንዝ ውሃ ሂጄ ጸሃዩ በላኝ፣

የሙሽሪት እናት ኮረፌሽ ታየኝ፡፡



የወንድ ሙሽራ (ፎቶ በአፀደ ተፈራ)



**የሴት ወገን ሴቶች ሙሽራውን በዘፈን ሲቀበሉት (ፎቶ በጋዝጊብላ ወረዳ ባቱ)**

### ለ/ ለሙሽራዋ አባት የሚገጠም

ይኸው ከዚያ ማዶ የስንዴው ክምር፣
ይኸው ከዚያ ማዶ የገብሱ ክምር፣
ምንኛ አማረበት እከሌን ሲድር፡፡
የሙሽሪት አባት ደስ ይበልህ ደስ፣
ፈረስ ያስጋልባል ያሰራኸው ዳስ፡፡
አትሙት አትታመም ኑር እንደ ሰንበት፣
እከሌ (እስከ አባት) የእከሊት (የሙሽራዋ) አባት፡፡
ጠላው ፈሶ ፈሶ መሬቱን አራሰ፣
እንጀራው ተጋግሮ ዳሱን አለበሰ፣
የሙሽሪት አባት በጎሸን አረሰ፡፡

በዚህ ወቅት የዘፈኑ ተቀባዮች ዘፈኑን ሞቅ ሞቅ ካላደረጉት፣ አቀንቃኟ የሚከተለውን የመቀስቀሻ ቃል-ግጥም ትገጥማለች፡፡

አውራ ዶሮ ታርዶ የታለ መረቁ፣

የ…አገር ሴቶች እልልታም አያውቁ፡፡

አፋችሁ ምንኛ ጉንፋን ይዝጋልኛ፣

እጃችሁ ምንኛ እሾህ ይውጋልኛ፣

የ…አገር ሴቶች የቂጣ ደመኛ[67]፡፡

ሞቅ ሞቅ እናድርገው በገዛ ዳሳችን፣

ለሰው እንተርፋለን እንኳን ለራሳችን፡፡

ከበሮውን ምቱት እያሰማማችሁ፣

እህትን የላትም ታሰኟታላችሁ፡፡

በዚህ ጊዜ የዘፈኑ ታዳሚዎች በቃል ግጥሞቹ አማካይነት ለዘፈኑ ድምቀትና ለሙሽራዋ ያላቸውን ተቆርቋሪነት አልገለጻችሁም ተብለው በመሰደባቸው እልልታውን፣ ጭብጨባውንና የዘፈኑን አቀባበል ያማሙቁታል፡፡ ስለዚህ የተጠቀሱት ቃል-ግጥሞች የዘፈኑን ተቀባዮች በመቀስቀስ፣ ቀዝቀዝ ብሎ የነበረውን ዘፈን ሞቅ ደመቅ እንዲል ያደርጋሉ፡፡ የዘፈኑ አቀንቃኞች በህይወት የሌሉ የሴት ወገኖችንም በቃል ግጥሞቻቸው ያነሷቸዋል፡፡ ለአብነት ያህል በ2/5/05 ዓ.ም አቢያ ሊባኖስ በተባለው የገጠር ቀበሌ በነበረው ሠርግ ላይ ሟች ቤተዘመድን የሚያወሱ የሚከተሉት ቃል ግጥሞች ተገጥመው ነበር፡፡

ደባሹወይ ግርማይ[68] የማርያም ዘበኛ[69]፣

ንግስታወይ እሸቱ[70] የማርያም ዘበኛ፣

እናንተ ብትተውት አደረግነው እኛ፡፡

የማይሞት ሰው የለም የማይበሰብስ፣

ደባሹወይ ግርማይ  ካሁኑ ድረስ፡፡

አዳማጩን ሲያጣ እምቧ ይላል በሬ፣

[67] ቂጣ በብዛት የሚመገቡ

[68] በጎጡ ታዋቂ የነበሩ የሙሽራዋ አያት (የአባቷ አባት ) ናቸው፡፡

[69] በየትኛውም ደብር  ወይም ቤተክርስቲያን ለአብነት ያህል በደብረ ገነት መድሐኒዓለም ወይም በቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን የተቀበሩትን ሁሉ የሚመለከት ነው፡፡ የግድ የማርያም ደብር  ወይም ቤተክርስቲያን ባለበት የተቀበረ ማለት አይደለም፡፡

[70] የሙሽራዋ የአባቷ አክስት ናቸው፡፡

ደባሹወይ ግርማይ ወዴት ውሿል ዛሬ፡፡

እነዚህ ቃል ግጥሞች በሚገጠሙበት ወቅት ከሰርጉ ታዳሚዎች መካከል የሚች ዘመድ የሆኑት ሚችን በማስታወስ ሲያለቅሱ ተመልክቻለሁ፡፡ ለአፍታም ቢሆን በዳሱ ውስጥ የነበረው የደስታ ድባብም ወደ ሀዘን ተለውጦ ነበር፡፡ ከዚህ የምንረዳው በደስታ ጊዜ ማዘንም ሊያጋጥም የሚችል፣ ሀዘንና ደስታ የማይነጣጠሉ መሆናቸውን ነው፡፡

ሐ/ ለሙሽራዋ የሚገጠም

ትወስዳት እንደሆን አይተህ ተመልክተህ፣
በብር ቀለበት ወገቧን ለክተህ፤
አይዋ ሙሽሬ ምን ይዘሃል ዋጋ፣
የእኛስ እህታችን ብር ናት አለንጋ፡፡
ሰቆጣ ልወጣ ለአይኔ ኩል ልገዛ፣
እንኳን ለእህቴ ልጅ ለእከሊት ዋዛ፡፡

አማጭም እንደሚከተለው በቃል ግጥሞች የተሰደበ መስሎ ይሞገሳል(ይወደሳል)፡፡

ምን አይነት አማጭ ነው የተክለፈለፈ፣
ባህርና ባህሩን[71] ደብልቆት አረፈ፡፡

ሴቶቹ በተሟሟቀ ሁኔታ እንዲህ በመዝፈን ላይ እያሉ፣ ሙሽራው ወደ ዳስ ሊገባ ሲል ከመካከላቸው አንዷ ሴት በተበጠበጠ አመድ፣ የሙሽራዋ ቤተሰቦች አቅም ካላቸውም በወተት ሙሽራውን በመርጨት ለማበላሸት ትሞክራለች፡፡ ሚዜዎቹም ሙሽራው በሚረጨው አመድ እንዳይበላሽ በነጠላቸውም በእጃቸውም እየገራረዱ ይከላከላሉ፤ ይህም ለቀልድና ለጨዋታ ሲባል የሚከናወን ነው፡፡ በተመለከትኳቸው ሠርጎች ግን ሴቶቹ የወንድ ወገንን ወደ ዳስ አናስገባም ብለው አመድ አልረጩም፤ ምክንያቱን ሲገልጹም የሁለቱ (የሴቷም የወንዱም) ሠርጋቸው በአንድ ቀን ስለሆነ የወንድ ወገኖች አምሽተው ስለመጡና፣ ለመመለስ ስለሚመሽባቸው ጊዜ ለመቆጠብ ስንል ነው የተውነው ብለዋል (ቁ.ያ.መ.አ.7)።

[71] ዘመድ -ብዙ የሆኑትን የሴትና የወንድ ሙሽራ ወገኖች ለማለት ነው፡፡

የወንድ ወገኖች በሆታ ወደ ዳስ ሲገቡም፣ ዳስ ውስጥ የሚገኝ የሰርጉ ታዳሚ ሁሉ ከተቀመጠበት ተነስቶ በእልልታ ይቀበላቸዋል፡፡ ለብቻቸው በተዘጋጀላቸው ቦታም ይቀመጣሉ፡፡ ሙሽራውንም በነጣላ በመከለል በከፍተኛ ቦታ እንዲቀመጥ ያደርጉታል፡፡ በነጠላ የመከለሉ ምክንያትም ሙሽራዋን ይዞ ወጥቶ ሳይመረቅ ተገልጦ መቀመጥና መታየት የሌለበት ስለሆነ ነው፡፡



ሙሽራው ተጋርዶና[72] በሚዜዎቹ ታጅቦ (ፎቶ በአፀደ ተፈራ)

የሴት ወገን የሆኑት ሴቶችም ለተወሰነ ጊዜ ዘፈናቸውን ቀጥለው ቃል-ግጥሞቻቸውን ይደረድራሉ፡፡ የሙገሳው ቃል ግጥም ሲገጠምም እልልታው ይደምቃል፤ የሙሽራዋ እናት እራሷ ላይ ወስከንቢያ በማድረግ ወደ ጨዋታው መሀል ገብታ በክብ ዙር እየዞረች እስክስታ ስትወርድ(ስትትል)፣ እልልታውና ጨዋታው ይበልጥ ይደምቃል፤ እስክስታ ስትመታም ከሌሎች ሴቶች[73] ሽልማት ይጎርፍላታል፡፡ በአብዛኛዎቹ ሠርጎች እንደ ተመለከትኩት

[72] ለፎቶ ሲባል ተገልጦ ነው፡፡

[73] በዚህ ጊዜ የሴት ወገን ወንዶች የወንድ ወገንና ሌሎች የሰርጉ ታዳሚዎች ለማስተናገድ ሽር ጉድ ስለሚሉ፣ በሙሽራው አቀባበል ጭፈራ ላይ አይሳተፉም ፡፡

ተሸላሚዎች ሽልማታቸውን ተቀብለው ዝም ሲሉ፣ በ19/09/04 ፋ.ያ ማርያም በተባለው ቦታ ላይ በነበረው ሠርግ ግን ብር ስትሸለም የሙሽራዋ እናት ሸላሚዎቿን አንድ በአንድ ትስማቸው ነበር፡፡ ሴቶቹ ለተወሰነ ጊዜ ዘፈናቸውን ከቀጠሉና እስክስታ ከወረዱ(ከመቱ) በኋላ ጨዋታቸውን ያቆማሉ፤ ወደ ዳስ ገብተውም ስራቸውን ይቀጥላሉ፡፡

በአንድ ሠርግ የወንድ ወገን አቀባበል የተለየ ሁኔታ ተመልክቻለሁ፡፡ በ23/08 /04 ዛንዚራ ተክለሃይማኖት በተባለው ቦታ በነበረው ሠርግ፣ የወንድ ወገን ወደ ዳስ ሊገባ ሲል እንደ ተለመደው ሁሉ፣ የሴት ወገን እናቶችና ልጃገረዶች ከበሯቸውን ይዘው አቀንቃኟ ‹‹በላየ በላየ ሆ በላየ ሙሽራው በላየ›› ስትል፣ ተቀባዮችም ይህንኑ በመደጋገም ይዘፍኑ ነበር፡፡

ለሙሽራዋ እናትም በብዛት ሽልማት ይሰጣት ነበር፤ በዚህ ወቅት ግን ያልተጠበቀ ነገር ተከሰተ፤ ስታቀነቅን የነበረችው የሙሽራዋ አክስት፣ ‹‹ዛሯ ወረደ›› ተብለና መሬት ላይ ተዘርራ ወደቀች፤ ጨዋታውን በማጨብጨብና በመቀበል፣ እስክስታ መቺዎችንም ለማየት እየተጋፉ፣ እራሳቸውም የግላቸው የጨዋታ ቦታ አመቻችተው በእናቶቻቸው ዘፈን እስክስ ሲሉ የነበሩት በርካታ ልጆችም በድንጋጤ ወደ ኋላቸው ሸሹ፡፡ የድርጊቱ ሁኔታ ወደ ዳሱ ውስጥም ተሰማና፤ የወንድ ወገንን ተቀብሎ ለማስተናገድ ቦታ በማመቻቸት ላይ የነበረው፣ ‹‹ዛሯ ተነሳባት›› የተባለችው ሴት ባልም በፍጥነት በመምጣት ተሸክሞ ወደ ቤት ወሰዳት፤ የሙሽራው መቀበያ ዘፈንም ባጋጣሚ በተፈጠረው አስደንጋጭ ሁኔታ ሳይጠበቅ ተቋረጠ፡፡ የዘፈኑ የደስታ ድባብም ወደ ድንጋጤና ሀዘን ተለወጠ፡፡

የወንድ ወገኖች ወደ ዳስ ከገቡ በኋላም፣ በመጀመሪያ ለሴት ወገን ያመጡትን አስራ ሁለት ጧፍ፣ አስራ ሁለት ፎሌ፣ የሙሽራዋን አልባሳትና መዋቢያዎች ለሴት ወገን ሸማግሌዎች አንድ ባንድ እየቆጠሩ አስረከቡ፡፡ ያመጡትንም ሌላው ታዳሚም እንዲያየው ያደርጉ ነበር፡፡ ለሙሽራዋ ከሚወሰዱ ነገሮች መካከል ቀሚስ፣ መቀነት፣ ነጠላ፣ ካባ፣ ጫማ፣ ሻሽ (ባውንድ)፣ ሱሪ(ቦላሌ)፣ አዲስ ያልተሰፋ(ነዶ) ጨርቅ ወዘተ.ነው፡፡

ጧፍ ወደ ሙሽራዋ ቤት የሚወስደውም የማጫ እና የስጦታ ስርዓቱ የሚከናወነው በጨለማ ስለሆነ፣ ለመብራት አገልግሎት እንዲውል ነው፡፡ ምልከታ ካደረግሁባቸው አስር ሠርጎች መካከከል በመኪና መስመር ላይ ለሚገኙትና የኤሌክትሪክ መብራት አገልግሎት በሚገኝባቸው ማይግንዶ፣ ስሬልና ሃሙሲት ቀበሌዎች ጧፍ አልተወሰደም፡፡

እንዲሁም ማሩን የሚይዘው የሙሽራው የቅርብ ዘመድ ነው፤ ሚዜዎች ከያዙት ማሩን ልሰው ሰፈፉን ወደ መያዣው ሊከቱ ይችላሉ ተብሎ ስለሚታሰብ ሚዜዎች እንዲይዙ አይፈቀድላቸውም፡፡ በዚህ ምክንያት በ19/09/04 ፋያ ማርያም በተባለው ቦታ ላይ በነበረው ሠርግ የወንድ ወገን ዘመቻ ወቅት በርካታ ሚዜዎች እያሉ ማሩን የያዘው ግን የሙሽራው ሶስተኛ ታላቅ ወንድም ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ የሙሽራው አባት ማሩን ለሙሽራዋ ዘመድ እንጂ ለሌላ ሰው እንዳይሰጥ ማስጠንቀቂያ ሰጥተውታል፡፡ እሱም ወደ ሴቷ ዳስ እንደገባ ማሩን ያስረከበው ለሙሽራዋ አክስት ነው፡፡

ማሩ ለሶስት ነገሮች ያገለግላል፤ የወንድ ወገን ወደ ሴቷ ዳስ ለመግባት ፈቃድ ለማግኛ፣ ለሙሽራዋ ገላ መታጠቢያና የሴት ሙሽራ ወገን የሆኑ ሴቶች፣ ሙሽራዎቹ ከሴቷ ዳስ ሲወጡ፣ እየዘፈኑ ሸኝተው ሲመለሱ የሚጠቀሙበት ነው፡፡ ማሩን ከኮረፌ ድፍድፍ ጋር ለውሳ በወንጠፍት በመያዝ ወደ ሴቶቹ የምትቀላቀለውም የሙሽራዋ እናት ናት፡፡

የወንድ ወገን ወደ ዳስ ገብቶ ትንሽ ከጨፈረ በኋላ፣ ትልቅ ሚዜው (በኽምጣኛ ኽየው መዘ) እና ትንሽ ሚዜው (በኽምጣኛ እጥን መዘ) አጣጥለው ለብሰው ከዳሱ መሀል ይቆማሉ፤ ብር የተሰባሰበባትን ወይም እየተሰበሰበባት ያለችውን አገልግል ወይም መሶብ ከበው፣ በጠፍር አልጋ ወይም በከፍተኛ ቦታ ላይ የተቀመጡትን የሴት ወገን ወንድ ሽማግሌዎች እየተመለከቱም፣

**የሙሽራው ወገን** ‹‹ጤና ይስጥልን፤ እንደ ምን ዋላችሁ ይላሉ እናት አባት›› (ሶስት ጊዜ)

**እስን[74] ዊግን** ‹‹ትኽነ ነይነ ዳኽነ ግሪርንቅመ ይኻኩ ኩያ ቅል›› (ሶስት ጊዜ)

**የሙሽራዋ ወገን** ‹‹እግዚአብሄር ይመስገን ብለዋል በል››፣

**ስሪት ዊግን** ‹‹እምዘይናነ ይኻኩ ዪ››

**የሙሽራው ወገን** ‹‹አምሽተን በሰራነው ሁሉ ማሩን ማሩን ማሩን››፣

**እስን ዊግን** ‹‹ኩንነው ግረሽነውዝ ኹርትል ቀረ ቢሽታው ፣ሳቁጥን ሳቁጥን ሳቁጥን ፣››

**የሙሽራዋ ወገን**‹‹ገብታችሁ እስከምትወጡ ድረስ ፣ እጅ እግራችሁን እንድታርሙ፣ ምረናችኋል፡፡››

---

[74] በኽምጣኛ የወንድ ሙሽራ እስን ሲባል፣ የሴት ሙሽራ ደግሞ ስሪት ትባላለች፡፡

**ስሪት ዊግን** ‹‹ክትናልኩድ አምርምን ጥውርን ፈርትኒስቅ ሻቁርንኩ ››፣

**የሙሽራው ወገን** ‹‹እልል›› **አስን ዊግን** ‹‹እልል››

**የሙሽራው ወገን** ‹‹የዳስ አስተዳዳሪ ስጡን››

**አስን ዊግን** ‹‹ይና ደዘ ቱ ጭሰጭሰነ ይውጥን››፣

በመቀጠል የወንድ ወገን ከሴት ወገን የዳስ አስተዳዳሪ[75] እንዲሰጣቸው እንዲህ ብለው ይጠይቃሉ፤

**የሙሽራዋ ወገን** ‹‹እከሌን ሰጥተናችኋል፡፡››

**ስሪት ዊግን** ‹‹እከለይስ ይውኩን፡፡››

የዳስ አስተዳዳሪ የወንድ ወገን በሴቷ ዳስ ውስጥ ቆይታ በሚያደርግበት ወቅት፣ ከሴት ወገን የሚፈልጉትን የሚጠይቁትና የሚያቀርብላቸው ወይም የሚያስተዳድራቸው ነው፡፡ የዳስ አስተዳዳሪውም ለወንድ ወገን ማስተናገጃ የተመደበውን መጠጥ ያስረክባል፡፡ በዚህ ጊዜም የወንድ ወገንን ለደንቡ ‹‹የጋን መክፈቻ ስጡን፡፡›› ብሎ ይጠይቃል፤ እነሱም ሃያ ብር[76] ይሰጣሉ፡፡ ከዚያም የወንድ ወገን አረፍ ብለው ለብቻቸው የተሰጣቸውን ጠላ መጠጣት ይጀምራሉ[77]፡፡ ትንሽ እንደ ቆዩም የማጫ በኸምጣኛ ቆደ እና የስጦታ ስርዓት እንዲጀመር በትልቅ ሚዜው ተናጋሪነት በትንሽ ሚዜው አጃቢነት የሴት ወገንን እንደሚከተለው ይጠይቃሉ፤

**የሙሽራው ወገን** ‹‹ሸኙነ ሸኙነ ይላሉ እናት አባት›› ሶስት ጊዜ ይላል፡፡

**አስን ዊግን** ‹‹ስሽዝጥን ስሽዝጥን ይኻኩ ኩየ ቅል›› ሶስት ጊዜ

ጥር 5/2005 ዓ.ም አቢ.ያ ሊባኖስ በነበረው ሥርግ ደግሞ ‹‹ሸኙነ ሸኙነ ወንዝ ተሻግረን ተራራ ዙረን የመጣን ነን ይላሉ እናት አባት›› ሲሉ አድምጫለሁ፡፡

---

[75] ጥር 5/2005 አቢ.ያ ሊባኖስ በተባለው ቦታ ላይ በነበረው ሥርግ ደግሞ አሸጋጋሪ ስጡን ሲሉ ሰምቻለሁ፡፡

[76] ይህ ብር የሚመለስላቸው ስለሆነ ነው፡፡

[77] ድግሱ አነስተኛ ከሆነ ግን ለወንድ ወገን የተለየ ጋን ጠላ አይቀርብለትም፤ ሌላው ታዳሚ ከሚጠጣው ይጠጣል፡፡ምግብም እንዲሁ የተለየ ሳይሆን ሌላው የሚመገበውን ይመገባል፡፡ ይህንንም ዛንዚራ ተክለሃይማኖት በተባለው ቦታ ሥርግ ተመልክቻለሁ፡፡



ትልቅና ትንሽ ሚዜዎች የሸኙን ሸኙን ጥያቄ ሲያቀርቡ (ፎቶ በጋዝጊብላ ወረዳ ባቱ)

ይህ ጥያቄ በወንድ ወገን ከመቅረቡ በፊት የሴት ወገን ሽማግሌዎችና አባቷ አስቀድመው ለእናት ለአባት፣ ለወንድም ለእህት፣ ለክርስትና አባት፣ ከሙሽራው ጋር አብረው ለዘመቱት ሽማግሌዎች የእግር ጫማ፣ ለነፍስ አባት፣ ለአማቿ ለሙሽራው ደግሞ የልብስ ይሆን ያህል፣ ለበቅሎ ይሆን ያህል ለጉልበት ይሆን ያህል ብለው ለማጫና ለስጦታ የሚሰጡትን ያቅዳሉ፤ ይመድባሉ፡፡ ጥያቄው ሲቀርብላቸው ገና ያላዘጋጁና ያልወሰኑ ከሆነ ግን ‹‹እሺ እየተጫወታችሁ ትንሽ ጠብቁን›› ይላሉ፡፡ ሚዜዎችም የማጫውና የስጦታ ስርዓቱ እስከሚጀመር ድረስ ዘፈናቸውን ይቀጥላሉ፡፡

የሴት ወገን የሚሰጠውን ተመካክሮ ካዘጋጀም ለጥያቄው የሚከተለውን መልስ ይሰጣል፡፡

**የሙሽራዋ ወገን** ‹‹እሺ ከመሸንታችን አስቀድሞ፣ የልጆቻችንን መተዳደሪያ እንያዝ፤

**ስሪት ዊግን** ‹‹እሺ ስሽዝነ በርነ ይናቹርዝቁ ጨነ በውገ ጻይነ››

**የሙሽራው ወገን** ‹‹መጀመሪያ እናንተ ባርኩ (ጀምሩ)››

**አስን ዊግን** ‹‹ይናነጥ በርክትን››

**የሙሽራዋ ወገን** ‹‹ወንድ አይደለም እንዴ የሚባርከው፣ እናንተ ባርኩ (ጀምሩ)፡፡ ››

**ስሪት ዊግን** ‹‹ግለወ ቃየው በርኮድ ክትን በርክጥን፡፡››



**ዳስ ውስጥ የሚዜዎች ጭፈራ (ፎቶ  በአፀደ ተፈራ)**

የሙሽራው ወገን ለማጫ ሊሰጥ ያዘጋጀውን ከብት፣ እርሻ ወይም ብር ይገልጻል፡፡ የሙሽራዋ ወገንም የወንድ ወገን ለመስጠት ከገለጸው መጠን  ጋር ተመጣጣኝ የሆነ እንደሚሰጥ ይገልጻል፡፡

እንደ የመረጃ አቀባዮቹ አገላለጽ፣ ‹‹ማጫ በተያይቶ ነው፤›› በተያይቶ ማለት በአንድ በኩል በመጠን እኩል መሆን  ነው፡፡ የሴት ወገን የወንድ ወገን የሚሰጠውን አይቶ፣  ያንን ያህል ይሰጣል፤ በመጀመሪያ የወንድ ወገን ይህን ያህል መሬት፣ ብር፣ ከብት፣ በሚልበት ወቅት፣ የሴት ወገንም ያንን ያህል መስጠት ይኖርበታል፤ ስለዚህ የሴት ወገን አምስት ከብት ካለ፣ የወንድ ወገንም አምስት ይላል፤ ሁለት ካለም ሁለት ይላል። አንድ ካለም አንድ ይላል። በሌላ በኩል በተያይቶ ማለት በማረጋጋጥ ነው፡፡ ምክንያቱም በዳስ የተዋሸው ከብቱም ሆነ እርሻው ስለማይኖር ሽማግሌ ሂዶ በማየት አረጋግጦ ማጫ ይመታል፡፡ ምክንያቱም የሌላቸውም አለን ብለው ማጫ ያስመቱ ስለነበር ነው፡፡ ስለዚህ በማጫነት የሚያዘው በትክክል ያለው እንጂ የሚነገረው አይሆንም (ቁ.የ.መ.አ.21፣ ቡ.ተ.ው. 3 እና 4)፡፡

ባጋጣሚ ትርፍ ካለ ግን የብቻ ንብረት ሆኖ ይያዛል፡፡ የዳር (የሁለቱ ያልሆነ) ትርፍ ማጫ መኖር ግን ችግር እንዳለው ነው የመረጃ አቀባዮች የገለጹልኝ፡፡ ምክንያቱም ባሏ ‹‹አባትሽ ምን ሰጥቶሻል፡፡›› እያለ ሚስቱን ሊረብሻት ይችላል፡፡ ሚስቱ ለወይፈኑ ገለባ ባትሰጠው ለጭቅጭቅ መንስኤ ይሆናል፡፡ ወንዱ ‹‹በእኔ ወይፈን አርሼ አላበላሽም›› ይላታል፡፡ ሴቷም ‹‹የወይፈኑን በረት አልጠርግም›› ብትል በትዳራቸው ላይ ችግር ይፈጥራል (ቡ.ቃ2፣ ቁ.የ.መ.አ.26 እና ቡ.ተ.ው 4)፡፡

አንዳንድ ሀብታም የሆኑ የሴት አባቶች ግን የግራ የቀኙን (የሴቷንም የወንዱንም) ማጫ አሟልተው ይሰጣሉ፡፡ (ቡ.ተ.ው. 2) የሴት ወገን የሚሰጠውን የማጫ መጠን ሲገልጽም፣

**የወንድ ወገን** ‹‹እልል›› **ይላል፡፡ አስን ዊግን** ‹‹እልል››[78]

ከማጫ በተጨማሪ የሴት ወገን ለወንድ ወገን የተለያዩ አካላት ስጦታ ይሰጣል፤ ይህ ስጦታ በአቅም የተወሰነ ቢሆንም የማይቀር ነው፡፡ ስለዚህ ትልቁ ሚዜ ስጦታ ሊሰጠው ሲገባ ያልተሰጠው ማን እንደ ሆነና ምን ብሎ እንደሚጠይቅ ከወንድ ወገን አባቶች ጋር ተነጋግሮ እንደገና በዳሱ መሃል በመቆም ጥያቄውን እንዲህ በማለት ያቀርባል፡፡

**የሙሽራው ወገን** ‹‹ሸኙነ ሸኙነ ይላል ልጃችሁ ፣ ያየሁትን ሁሉ ልለብስ ያየሁትን ሁሉ ልታጠቅ ››፣

**አስን ዊግን** ‹‹ስቭስጥን ስቭስጥን ይኻኩ ሻታኹር ቃለውድቅ ሲጨ፣ ቃለውድቅ ክምጨ ፡፡››

**የሙሽራዋ ወገን** ‹‹አቅማችንን ታውቂታላቸሁ ፤ ለልጃችን ሶስት መቶ ብር ለበቅሎ፣ ሁለት መቶ ብር ለልብስ ፡፡››

**ስሪት ዊግን** [79] ‹‹ይናቅምዝ አርቀነውድ፤ ሻቐ ላ ቢቅለ ፣ ሊኻ ላ አልቨ ይናኹርዝ ››

የሙሽራዋ ወገን በሙሽራው ወገን መጠየቃቸው ለማይቀረው አካልም ገና ሳይጠየቁም እንደሚከተለው ይሰጣሉ፡፡

**የሙሽራዋ ወገን** ‹‹ለልጃችን ለዘር መግዣ አምስት መቶ ብር››

---

[78] ከሴት ወገን የማጫ እና የስጦታ ብር በሚገለጽበት ወቅት የወንድ ሚዜዎች እልል ይላሉ፤ ተዘናግተው ዝም ቢሉ እንኳ ሽማግሌዎቹ «እናንተ እልል በሉ፤ በኸምጣኘ እፈ እልል ዪ» ፣» እያሉ ያስታውሷቸዋል፡፡

[79] በ23/08/04 ዛንዚራ ተክለሃይማኖት ከነበረው ሠርግ የተወሰደ፡፡

ስሪት ዊግን ‹‹ይናቹርድ ዚረ ጅሸነው አኮ ላ ቹርሺ››

የሙሽራዋ ወገን ‹‹አቅማችንን ታውቂታላችሁ፣ ለአባት ለእናት (ለሙሽራው) ሁለት መቶ ብር››

ስሪት ዊግን ‹‹ይናአቅምድ አርቆቅ ይናቅሊዝ ሊኘ ላ ቹርሺ››

የሙሽራዋ ወገን ‹‹እሺ ትንሽ ትልቁን አናውቅም፤ ለቤተዘመድ ሁለት ሁለት ብር››[80]

ስሪት ዊግን ‹‹እሺ ኸየው እጥን አርቃይናቅ፣ ዚነ ዘመተድ ሊኘ ሊኘ ቹርሺ››

ገንዘብ የሚሰጣቸው የወንድ ወገን ሽማግሌዎችም ገንዘቡን ሲቀበሉ ከመቀመጫቸው ይነሳሉ፤ የሴት ወገንን እጅ እየነሱም ‹‹ወልደው ከብደው ይደሩ›› ብለው ሙሽራዎቹን ይመርቃሉ፡፡ ጥር 2/05 በአቢያ ሊባኖስ ሠርግ ላይ ግን ከሌላዎቹ ሰርጎች የተለየ ነገር ተመልክቻለሁ፤ ይኸውም የሙሽራው ታላቅ ወንድም አስር ብር እንደ ተሰጠው ሲገለጽለት፣ ከመቀመጫው ተነስቶ ወደ ሴት ወገን ሽማግሌዎች በመሄድ የሙሽራዋን አባት ጉልበት ሳመ፡፡ ይህን ያደረገውም በሴት ወገን ገንዘብ ስለ ተሰጠው፣ ከሌሎቹ በተለየ አክብሮቱን ለመግለጽ ነው፡፡

ለወንድ ወገን የነፍስ (ንስሃ) አባትም ይህን ያህል ብር ተብሎ ይሰጣል፡፡ በዚህ የስጦታ ጊዜ አማጭ (በኸምጣኘ ዘርና)ብር ካልተሰጠው፣ በባህሉ መሰረት እሱም ስጦታ እንደሚያስፈልገው ትልቅ ሚዜው እንዲህ በማለት የሙሽራዋን ወገን ይጠይቃል፡፡

የሙሽራው ወገን “እኔ ቀረሁ፤ እኔ ቀረሁ፤ እኔ ቀረሁ፤ ይላል አማጭ፣ በዓመት በዓል ሚስቴን ያላስገደፍኩ (ጾም ያላስፈታሁ) ለጫማየ የአውራ በሬ ምንጣፍ የጨረስሁ፣ አባይንና ጣናን ያገናኘሁ፡፡

አስን ዊግን ‹‹ያን ዳቹን ያን ዳቹን ይኘኩ ዘርና አምር በልዝ ይውነት ግድፍስቅር፣ቿን ዋጸ አብዝር፣ አባይስመ ጻነስ ዲምቅር ያን ዳቁን፡፡››

አቢያ ሊባኖስ በተባለው ቦታ በነበረው ሠርግ ግን ጥያቄው እንደሚከተለው ነበር በአማርኛ የቀረበው፡፡ ‹‹ወንዝ ተሻግሬ፤ ደጋ ቆላውን፣ አቀበት ቁልቁለቱን ወጥቼ ወርጄ፣ በጸሃይ

[80] የሙሽራው ቤተሰብ የሆኑትን አባት፣ እናት፣ ወንድም፣ እህት መጠናቸውን ባናውቅም ለእያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ብር ለማለት ነው፡፡

በውርጭ ተንከራትቼ፣ የአንድ በሬ ቆዳ የሚሆን ጫማ የጨረስሁ፣ ጠጁን ከውሃው ጋር ያዋሃድኩ እኔ ቀረሁ ይላል አማጭ።"

የሙሽራዋ ወገን ‹‹እሺ እኛ እንኳ የተገናኘነው እኛ በእኛ ብለን ነበር፣

አማጩን አቁሙና እንወቀው››

ስሪት ዊግን ‹‹እሺ ይን እንኳ ይናስ ድምቅሽኑን ይን ዊኑን፣ ቀሰው ይና ዘርነድ

ችሽስጥን ቃልነ››

የሙሽራው ወገን ‹‹አማጫችን መለሰ አብተው ነው ይላሉ››

አስን ዊግን ‹‹እሺ ይናዘርነድ መለሰ አብተው የሻ ይኻኮ››

የሙሽራዋ ወገን ‹‹ አቅማችንን ታውቁታላችሁ፤ በእኛ በኩል ሃያ ብር

ሰጥተናል፤ በእናንተ በኩልም ሃያ ብር እንድትሰጡ አዘናል፡፡ [81]››

ስሪት ዊግን ‹‹ይናቅም አርቅነውድ ይናቼይዝ ለርን ክታቼዝ ለርን ቁርሺ

ይኻኮ››

በዚህ ጊዜ በወንድ ወገን አማጭ ተብሎ አርባ ብሩን የተቀበለው ሰው አማጩ ሳይሆን ጠቋሚው በመሆኑ፣ አማጭ ሁኜ ብሩን መቀበል ያለብኝ እኔ ነኝ የሚል ተከራካሪ በዳሱ መሃል በመቆም ተቃውሞውን እንዲህ በማለት አቀረበ፤ ‹‹በር ያንኳኳሁት፤ውሻ የተከላከልኩት፤ ከወዲያ ወዲህ ተመላልሼ ሁለቱን ያስማማሁ፤ እኔ ብቻ ሳልሆን ሚሽቴ (ሚስቴ) ወይዘርም ጭምር የተመላለሰችውና የደከመችው እያለሁ፣ እንዴት የጠቆመው ይወስዳል፤ እኔ የምከራከረው ለራሴ ብቻ ሳይሆን ያባት ደንብ መፍረስ የለበትም ብየ ነው›› አለ፡፡

በዚህ ወቅት የደስታ ድባብ ይታይበት የነበረው የሠርግ ዳስ፣ በጭቅጭቅ ተሞላ፡፡ ሠርገኛውም የተፈጠረው ነገር ስላስደነገጠው ጭቅጭቁን በጸጥታ ይከታተል ጀመር፡፡ ከሌላ ቀበሌ የመጡት የሰርጉ ታዳሚዎችም እየተነሱ፣ ልምዳቸውን ገለጹ፤ ለአብነት ያህል ቋራ አቦ ከተባለው ቦታ የመጡት አቶ ተበጀ በላይ እንዲህ ብለዋል፤

[81] ለአማጭ የሚሰጠው ብር መጠኑ የሚወሰነው በወንድ ሳይሆን በሴት ወገን ነው፡፡

> ወንድ ሴት ያልወለደ የለም፤ ገንዘቡ መሰጠት የሚገባው በር ከፋች ለሆነው ለአማጩ ነው፤ ምክንያቱም ይህ እንዲህ ያለ ነው፤ ይህች ደግሞ እንዲህ ያለች ናት፤ ያለው እሱ ነው፡፡ በሀገራችን የነበረ ስሪት[82] አለ፡፡ ከምን ተነስተን ከምን አረፍን የሚለውን እንጂ ብሩን ማየት የለብንም፡፡ እንደ እኔ ያለ ውሽታም አለ[83]፡፡ ልጁ እንዲህ ያለ ነው፤ ልጂቱ እንዲህ ያለች ናት የሚለውን ተጋፍጦ ለዚህ ያደረሰው፣ በሩን ያንኳኳው ነውና ለእሱ መሰጠት አለበት (ቁ.የ.መ.አ.4)፡፡

ይሁን እንጂ ክርክሩ በመቀጠሉ ሌላው ታዳሚ በመፍትሄነት የሚከተለውን ሀሳብ አቀረበ፡፡ ‹‹አንድ የጋራ (አማጭ የተባለውም የጠቋሚውም) የሆነ ዘመድ ዳኛ አርባ ብሩን ይያዝና ይፍረድ፤ ሁላችን ግን ፍርዱን ይዘን መሄድ አለብን››[84] አለ፡፡ ተቃዋሚውም እንደገና ተነስቶ፣ ‹‹እኔም ዋግ ያለው ስሪት እንዲጠበቅ ብየ ነው እንጂ ብሩን ፈልጌ አይደለም፤ ስለዚህ ዳሱ ፍርዱን እንዲሰጠኝ ነው የተናገርሁት›› አለ፡፡

በሁለቱም ወገን ጭቅጭቁ ቀጥሎ፣ ለሙሽራዎቹ የሚሰጠው የስጦታ ሂደት በመቋረጡና እየመሸ በመሄዱ፣ ለነገሩ ወዲያውኑ እልባት መስጠት አልተቻለም፡፡ በየጥጋ ጥጉ ሆነው የማጫ እና የስጦታ ስርዓቱን በጸጥታ ይከታተሉ የነበሩት ሴቶች ሳይቀሩ፣ በየግላቸው ፍርድ የመስጠት ያህል ሀሳብ በመሰንዘር እርስ በእርሳቸው ጭቅጭቃቸውን ቀጠሉ፡፡ በዚህ ምክንያትም ሳቅና ደስታ ሰፍኖበት የነበረው ዳስ የቅሬታ ድባብ ተላበሰ፡፡ የቅሬታው መነሻም ተያይዞ የመጣው ማህበረሰባዊ ደንብ እንዳይጣስና ጠብቆ ለማቆየት ሲባል ነው፡፡ በመጨረሻም አማጭ ተብሎ ለጠቋሚው የተሰጠው አርባ ብር ለሁለቱ (ለጠቋሚውና ለአማጩ) የጋራ ዘመድ ተሰጠ፤ ጉዳዩም በሌላ ጊዜ ውሳኔ እንዲሰጥበት ከሁለቱም አንዳንድ ሽማግሌ ተጠቁሞ ጉዳዩ በይደር ተያዘና[85] ሌላው የስጦታ ጥያቄና መልስ ሂደት ቀጠለ፡፡

**የሙሽራው ወገን** ‹‹ሴት ከወለዱት ቀን የወለዱት ይበልጣልና እኔ ቀረሁ እኔ

ቀረሁ ይላል የክርስትና አባት ››

---

[82] ሁሉም አምኖበትና አውቆት የሚተዳደርበት የማህበረሰቡ ያልተጻፈ ደንብ ወይም ህግ ነው፡፡ (ደስታ፣1962፣895)ም ካያት ከቅድመ አያት ሲያያዝ የመጣ ብለውታል፡፡

[83] በሴትም በወንድም በኩል እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን እየጠቃቀሰ፣ እጮኝነቱ እንዳይፈጸም ይሯሯጥ የነበረን ሰው ሀሳብ ውድቅ አድርጎ ስኬታማ ለመሆን የጣረ ለማለት ነው፡፡

[84] በተሰጠው ውሳኔ መዳኘት አለብን ለማለት ነው፡፡

[85] በዚህ ሠርግ ወደ የሴት ቤተሰብ ቤት ተመላልሼ እሺ ያሰኘሁት እኔ ነኝና ብሩ (ለጠቋሚው የተሰጠውን የአማጭ ብር) ለእኔ መስጠት አለበት ያለውን አማጭ በሌላ ሠርግላይ አግኝቼው ነበር፡፡ ለእሱ ተወስኖለት አርባ ብሩን መቀበሉን ነግሮኛል፡፡ ስለዚህ ለአማጭ ተብሎ የሚሰጠው ብር ለጠቋሚው አልሆነምና ነባሩ ደንብ አልተሻረም፡፡

**አስን ዊግን** ‹‹ያን ዳቁን ያን ዳቑን ይኻኩ አሸልጅ ኻር እሁርኑሽ ፣ ጊርቀ

እኹርኑ ኸየውኩ ››

**የሙሽራዋ ወገን** ‹‹እሺ የክርስትና አባቱን አሳውቁን ?››

**ስሪት ዊግን** ‹‹ እሺ አይርድ አርቅጥን?››

**የሙሽራው ወገን** ‹‹የክርስትና አባቱ ይርሴ ወ/ገብርኤል ነው›› ይላሉ፡

**አስን ዊግን** ‹‹አይርድ ይርሴ ወ/ገብርኤል የቛ ይኻኩ››

**የሙሽራዋ ወገን** ‹‹ለክርስትና አባት አምስት ብር›› ይላሉ፡፡

**ስሪት ዊግን** ‹‹አይርዝ አኰ ቁርሽን ይኻኩ››

ለሙሽራው ቤተሰቦች የነፍስ አባትም አምስት ብር ተሰጠ፡፡ ከሙሽራው ጋር አብረው ለመጡት ለአራት ሽማግሌዎችም ስማቸውን በመጥራት ለእያንዳንዳቸው ስድስት ስድስት ብር ተሰጣቸው፡፡ ሙሽራውን ኩል ለኳለችውም፤ ‹‹ለኳሊታ›› ተብሎ አምስት ብር ተሰጣት፡፡

የወንድ ወገንም ለተሰጠው ማጫ እና ስጦታ ምስጋናውን ለመግለጽ፣ ‹‹እልል›› ካለ በኋላ፣ የወንድ ወገን ሽማግሌዎች፣ ሚዜዎቹን የተሰባሰበውን ብር የያዘውን ሚዜ፣ ‹‹መጪ መጪ በሉ (በኽምጣኛ መጭ መጭ ይጥን) አሏቸውና ሌላዎቹ ሚዜዎች ‹‹መጭ፣ መጭ›› አሉ፤ ይህም ከሴት ወገን በማጫነትም ሆነ በስጦታነት የተሰጠው ብር ከፍተኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው፡፡

ለአማጭ የሚሰጠው የገንዘብ መጠን የተወሰነ አይደለም፡፡ ከተመለከትኳቸው ሰርጎች ለአማጭ የተሰጠው ዝቅተኛው በ23/08/04 ዛንዚራ ተክለሃይማኖት በነበረው ሠርግ በሴት ወገን ሃያ በወንድ ወገን ሃያ አርባ ብር ሲሆን፣ ከፍተኛው ደግሞ በ29/8/2004 ስሬል ላይ በነበረው በሴት በኩል መቶ በወንድ በኩል መቶ ብር በድምሩ ሁለት መቶ ብር ነው፡፡ በዚህ ጊዜ የስሬሉ አማጭ በደስታ ከመቀመጫው ተነስቶ ወደ ዳሱ መሃል በመሄድ፣ ብሩን ተቀብሎ፣ ለሁለቱም (ለወንዱና ለሴቷ) ወገኖች ምስጋናውን፣ ለሙሽራዎቹም መልካም ጋብቻ እንዲሆንላቸው ምርቃቱን ለግሷል፡፡ ለሌሎች ሽማግሌዎች የእግር ጫማ ሲሰጥም ለአማጭም እየተጨመረ ነው (ቁ.የ.መ.አ.21 እና ቡ.ተ ው.3)፡፡

ለማጫ እና ለሙሽራው፣ ለሽማግሌዎች፣ ለአባት ለእናት፣ ለወንድም ለእህት፣ ወዘተ.የሚሰጠው የስጦታ መጠንም፣ እንደ የሴት ቤተሰብ አቅም የተለያየ ነው፡፡ ይህንንም በ29/8/2004 ስሬል በተባለው ቦታ ላይ ባንድ ሠርግ ሁለት ልጆቻቸውን ድረው ስጦታ የተቀበሉትና የሰጡት ቄስ አለሙ ወረታ ሲገልጹ፣

> እኔ ለልጆቼ የሰጠሁት ማጫ አሁን የሰጠኋቸው ብቻ አይደለም፡፡ ከፍተኛ ወጭ አውጥቼ ወደ ሰቆጣ ከተማ እየላክሁ ማስተማሬ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ለባህሉ እና የመጡት እንግዶች ዝም ብለው እንዳይሄዱ ስል፣ ለልጄ ለሴቷ ሙሽራ ማጫ እና ሽልማት ስምንት ሽህ ሁለት መቶ ብር ሰጥቻለሁ፡፡ ትላንትና ከሴት ወገን ለወንዱ ልጄ የተሰጠኝ ግን ሁለት ሽህ አምስት መቶ ብር ብቻ ነው፡፡ የልዩነቱ ምክንያት ከአቅም ጋር የተያያዘ ነው፤ በምርቃቱ እኔ ያገኘሁትን ያህል እነሱ (የልጃቸው ሚስት ቤተሰቦች) ያገኙት አነስተኛ ስለሆነ ነው አነስተኛ የሰጡኝ፡፡ የእኔና የእነሱ በመለያየቱ ቅር አላለኝም፤ ምክንያቱም በባህላችን የሚኮራው ሰጪ ነው እንጂ ተቀባዩ አይደለም፡፡ ብለዋል (ቁ.የ.መ.አ.6)፡፡

በሌላ በኩል ሴት ልጃቸውን ጥር4/2006 መሸሃ ላይ የዳሩት አቶ ወ/ማርያም ደግሞ፣

> ማጫ ሃያ ሺህ ብር ሰጥቻለሁ፣ የወንድ ወገንም እንዲሁ ሃያ ሺህ ብር ሰጥቷል፡፡ ለወንድ ወገን የሰጠሁት ስጦታ ደግሞ ወደ ሁለትና ሶስት ሺህ ብር ደርሷል፡፡ የተጣለው አስራ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር ነው፡፡ ስምንት ፍየልም ተጥሏል፡፡ ስለዚህ ለማጫ የሰጠሁት ሰባት ሺህ አምስት መቶ ብር ከእራሴ (ከተመረቀው ውጭ) ጨምሬ ነው የሰጠሁት፡፡ ለድግስ ያወጣሁት የእህሉን አልባ ለፈረዳ፣ ለጨው፣ በርበሬ ለሽንኩርት ለጌሾ አስራ አንድ ሺህ ብር ነው፡፡ ስምንት ጋን ጠላ በሌሎች እገዛ ተደርጎልኛል፡፡ አውራጅ የያዘ አልነበረም፡፡ ብለውኛል (ቁ.ያ.መ.አ19)፡፡

በሌላዎቹ የስጦታ ስርዓት ላይ ያልተመለከትኩት በ2/05/05 አቢያ ሊባኖስ በተባለው ቦታ በነበረው የተመለከትኩት አለ፡፡ ይህም የማጫውንና የስጦታውን ሂደት ላስፈጸሙት ሁለት ሚዜዎችም ስጦታ መስጠት ነው፡፡ የተሰጡትም፣ ‹‹ሌላዎቹ ሲበሉ አልበሉ፣ ሲጠጡ አልጠጡ፣ ስላደከምናቸው ለትልቅ ሚዜ ሶስት ብር ለትንሽ ሚዜ ሁለት ብር›› ተብሎ ነው፡፡ ካጠገቤ ተቀምጦ የስጦታውንና የማጫውን ስርዓት ይከታተል የነበረውን ሰው ስለ ሚዜዎቹ ስጦታ ጠየቅሁት፤ እሱም፣ ‹‹ካሁን በፊት ለሚዜዎች አይሰጥም ነበር፤ አሁን አሁን ግን

ለወንድ ወገን ስጦታውና ማጫው ሲሰጥ፣ ሁለቱም ቆመው በመቀበልና በማስተጋባት ስለቆዩ ለማበረታታት ሲባል እየተጀመረ ያለ ነው›› ብሎኛል፡፡

የማጫውና የስጦታው ስርዓት እንደተጠናቀቀም ሚዜዎቹ ‹‹እልል›› አሉና ‹‹ተሳሳቢ ስጡን?›› ብለው የሴት ወገንን ይጠይቃሉ፤ ተሳሳቢ የሚባለው በወንድም በሴትም ወገን ምን ያህል ገንዘብ ወይም በአይነት ከብት፣ እርሻ፣ ቤት ወዘተ. እንደ ተሰጠ ሂሳብ የሚሰራ ነው፡፡ የወንድ ወገኖች የሙሽራዋን ቤተሰቦች እያወደሱ ተቀመጡ እስከሚባሉ ድረስ ይጨፍራሉ፡፡ ከዚያም የወንድ ወገኖች ምግባቸውን ከበሉ በኋላ ሙሽራዋና ሙሽራው ከተገኘ በዶሮ ወጥ ካልተገኘም ሌላው ከተስተናገደበት የስጋ ወጥ ለሙሽራ መቃመሻ ተብሎ ልዩ ሆኖ በተሰራ ወጥ ይቃመሳሉ፡፡ የዶሮ ወጥ ከተሰራ በመጀመሪያ በጋራ የሚቃመሷት መቋደሻዋን(ጫንጭራዋን) ነው፡፡ በአቀማመሱ ወቅት ትልቅና ትንሽ ሚዜ እንዲሁም ምግቡን በጸሎት የሚባርኩ ቄስ ይሳተፋሉ፤ የምታቃምሳቸውም የቄስ ሚስት ወይም አንድ ባል ብቻ ያገባችና በመጀመሪያ ባሏ (በአሚን ባሏ) የጸናች ሴት ናት፡፡ የምታቃምሰውም ለሙሽራዋ ሶስት ጊዜ፣ ለሙሽራውም ሶስት ጊዜ ነው፡፡ በሶስተኛው ከእንጀራው ጋር ጠቅልላ የብር ቀለበት ወይም ሳንቲም ለሙሽራው ለማጉረስ ስለምትሞክር፣ ከሚዜው ብርቱ ጥንቃቄ ያስፈልጋል፡፡ ሳንቲሙን ወይም ቀለበቱን በእንጀራው ጠቅልላ ለሙሽራው ልታጎርስ ስትል ሚዜው ተከታትሎ እጇን ይይዛል፤ ሳንቲሟን ወይም ቀለበቷንም የራሳችን ሲሳይ ናት ብሎ ይወስዳል፡፡

ይህ የሚደረገው ሙሽራው ሆዳም ወይም ጥንቁቅ፣ ብልህ አለዚያም ሞኝ መሆኑን ለመለየት ነው፡፡ ከዚያም ሙሽራው ለሙሽራዋ፣ ሙሽራዋ ለሙሽራውም ይጎራረሳሉ፤ ሙሽራዎቹ የሚቋደሱት በሩን ዘግተው ሲሆን፣ ሚዜዎች ደግሞ ከውጭ ሆነው በሩ እስከሚከፈት ድረስ በጉጉት ይጠባበቃሉ፤ በሩ ሲከፈትም አንዱ ሚዜ ወደ ቤት ይገባና ትራፊውን ወደ ውጭ አውጥቶ፣ ተሻምተው (ተዋረው) ይበላሉ።

ከዚያም ሙሽራዋ በአጎቷ (በእናት ወንድም) አጎቷ ባይኖር የሴቷ የናቷ ወገን የሆነ ሌላ ሰው አዝሎ ወደ ዳስ ያመጣታል። ምክንያቱም አዝላ ያሳደገቻት እናቷ ስለሆነች ነው (ቁ.የ.መ.አ.11) ፡፡ ይህ ሰው በአካባቢው አሽጋጋሪ ይባላል፡፡ ሙሽራዋ ፊቷን በጥቁር ሻሽ ትሸፈናለች፤ ምክንያቱን በሚመለከት የመረጃ አቀባየ ሲገልጹ በሌሎች ተገልጣ እንዳትታይ ነው ይላሉ (ቁ.የ.መ.አ.20)፡፡




**ሴት ሙሽራ[86] (ፎቶ በጋዝጊብላ ወረዳ ባቱ)**

በወንድ ሚዜዎች ሆታ ታጅባም ከሙሽራው ጋር ወደ ዳስ ትገባለች፡፡ በወንድና በሴት ወገን የተሰጠውን ማጫ(እርሻውን፣ ብሩን ከብቱን) የሚያውቁ፣ ለሙሽራዎቹ ተያዥ የሚሆኑና ወደ ፊት በተጋቢዎች መካከል ችግር ቢፈጠር የሚያስታርቁ፣ ከሁለቱ ወገን አንዳንድ ሰው እንዲመረጡም በአባቶች ይጠየቃል፡፡ ሁለቱም ተራ በተራ እየተነሱ ዋስ ለመሆን ፈቃደኝነታቸውን ይገልጻሉ፡፡ ከዚያም እነዚህ ሰዎች ጋቢያቸውን አጣጥፈው በመልበስና ሁለት እጆቻቸውን አጠላልፈው በሁለት ፎሌ የተሞላ ጠላ ይዘው፣ ከወንድና ከሴት ወገን ሽማግሌዎች ፊት ለፊት በመቆም፣ በመጀመሪያ የሴት የዳስ አባት ወይም ዋስ፤ ‹‹እኪሊትን (ሙሽራዋን ነው) ለልጄ እከሌ (ለሙሽራው) ሰጠሁ፤›› ይላል፡፡

86 ጸጉሯ አጭር ስለሆነ ሽሩባ አልተሰራችም፡፡

በመቀጠል ደግሞ የወንድ የዳስ አባት፣‹‹ልጄን እከሊትን ተቀብያለሁ›› ይላል፤ ይህም ቃል የመግባት ወይም የሰማንያ ስነ-ስርዓትን መፈጸም ነው (ቡ.ተ ው.4)፡፡



**የእናቷ ወንድም ሙሽራዋን አዝሎ ወደ ዳስ ሲያስገባት(ፎቶ በጋዝጊብላ ወረዳ ባቱ)**

ሙሽራዎቹ ከሙሽራዋ ዳስ ከመውጣታቸው በፊት በጋቢ ተሸፍነው፣ በከፍተኛ ቦታ ላይ ከተቀመጡበት ተነስተው ወደ የሴት ወገን ሽማግሌዎች ፊት ለፊት ይቆማሉ፡፡ የነፍስ አባትም ጢፍ አብርቶ ትንንሽ ጣቶቻቸውን በማጠላለፍ፣ ‹‹የአብርሃምንና የሳራን ጋብቻ የባረከ አምላክ የእናንተንም ጋብቻ ይባርክላችሁ›› በማለት ጸሎት ያደርጋሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ሌላው ታዳሚ ጸጥ ብሎ ያዳምጣል፡፡ የሚችለውም በማሳረጊያ የጸሎት ሥነ-ሥርዓቱ ይሳተፋል፡፡ ቄሱ ጸሎት በማድረጋቸውም፣ ከሴት ወገን ብር ይሰጣቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ የሁለቱም ወገን ሽማግሌዎችና በዳስ ውስጥ የሚገኙ ሌሎች ታዳሚዎች ሙሽራዎቹን ‹‹ ያጣምራቸው !›› ብለው ሲመርቋቸው ሚዜዎች እልልታቸውን ያስተጋባሉ፡፡

ሙሽራዎቹ ከዳስ ከመውጣታቸው በፊት፣ በመጀመሪያ በሙሽራዋ እናትና አባት፣ በመቀጠል ደግሞ ዳስ ውስጥ በሚገኙ ትላልቅ ሰዎች ጎንበስ ብለው ይመረቃሉ፡፡ በዚህ ጊዜ እናት አባትም ሆኑ ሌላዎቹ መራቂዎች ያቅማቸውን ለሙሽራዎቹ ብር ይሰጧቸዋል፡፡ ይህንን ብር የሚሰበስቡት ደግሞ ሚዜዎች ናቸው፡፡ ከዚያም ሙሽራዎቹ ዳስ ውስጥ በሚገኝ ሰው ይመረቃሉ፡፡ ሚዜዎቹም ወስከንቢያ ይዘው ሙሽራዎቹን በመከተል ‹‹የሙሽራ መመረቂያ›› እያሉ ብር ይጠይቃሉ፡፡ እያንዳንዱ ሰው የተቻለውን ሲሰጥ ተቀባዮቹ ሚዜዎች የሰጪዎቹን ስም በመጥቀስ አንዱን ብር መቶ ብር፣ ሁለቱን ብር ደግሞ ሁለት መቶ ብር እያሉ ይገልጻሉ፡፡ የሚሰጠው የሽልማት ብር ብዙ ተደርጎ የሚገለጸውም ዳሱን ለማሟሟቅ ሲባል ነው፡፡

ለሙሽራዎች በምርቃት የሚሰጠው ብር አነስተኛ ከሆነ ምስር ተሸምቶበት ለብቻ ይዘራል፤ ከፍተኛ ከሆነም ሴት ፍየል ይገዛበትና እንድትረባ ይደረጋል፡፡ ምክንያቱም ሽልማት ከሰጡት ሰዎች መካከል አንድ እድለኛ ወይም እርጥብ የሆነ ሰው ስለሚኖር ምርቱ ወይም የሚወለዱት ግልገሎች የሚራቡ ይሆናሉ ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡

ሙሽራዎቹ ከዳስ ከመውጣታቸው በፊት የወንድ ሚዜ አጣጥሎ ለብሶ፣ ወደ ሴት ወገን በመመልከት፣ ‹‹ጠገብነ ጠገብነ!(በኽምጣኛ እፍትርኑን!)›› ይላል፡፡ ይህም የሰጣችሁን ማጫ እና ስጦታ ብዙ ነው ለማለት ነው፡፡ የሴት ወገንም ‹‹እናንተም በቤታችሁ የጠገባችሁ ናችሁ›› የሚል መልስ በመስጠት ለምስጋናቸውም ለወንድ ወገን ከሴት ወገን የተወሰነ ብር ይሰጣቸዋል፡፡ ከዚያም ሙሽራዎቹ በሚዜዎቹ ሆታ እና በሴት ወገንና የሰርጉ ታዳሚ ሴቶች ዘፈን ታጅበው ከዳስ ይወጣሉ፡፡ የሴት ወገን ሴቶችም ትንሽ ሸኝተዋቸው ሲመለሱ በመንገድ ላይ፣

በአማርኛ ‹‹ሸኘቹ መጣሁ ሸኘቹ፣

ለባላምበራስ ሰጥቼ ፡፡›› እያሉ በመዝፈን ወደ ዳስ ይገባሉ፡፡

በኽምጣኛም አደ ክቑረድ ነስኑን፤ እናቴ ልጅሽን አመጣን፤

ስሪ በትረቑድ ነይትርመ፤ ሙሽራዋ ካተረፈችው ትሰጭኛለሽ ወይ

አስን በትረቑድ ነይትርመ፡፡ ሙሽራው ካተረፈው ትሰጭኛለሽ ወይ

አደ ክቁረድ ቃለ ፊስኑነ፤ እናቴ ልጅሽን ወሰድን፤

ፈሰነኩን ተክንነ ቃል ዊስኑነ፡፡ ወስደን አልቀረንም መለስን

ወደ ዳስ ገብተውም፣

በትግርኛ ‹‹ነበረየየ ኻመይ ዶ ኻመየ›› የአማርኛ ትርጉም- ነባሩ ልማዳችን

እንዲህ ነውን?

በኽምጣኝ አደ አውል ፊሪች? (እናቴ፣ የሙሽራዋን እናት ነው?) ወዴት ሄደች?

አቆይልመ ፊሪች? (ውሃ ልታመጣን ሄደች?)

ያን ፊጩ ዊኖደይ፡፡ (እኔ ወደ ወንዝ ሄጄ አመጣላት የነበረውን::

በማለት ይዘፍናሉ፡፡

ከእነዚህ የዘፈን ቃል ግጥሞች የምንረዳው ከወረዳ ወረዳ መጠኑ የተለያየ ቢሆንም፣ በዞኑ ሶስቱም ቋንቋዎች (አማርኛ፣ ትግርኛና ኽምጣኝ) ስለሚነገሩ፣ የሠርግ ዘፋኞችም በሶስቱም ቋንቋዎች መዝፈን መቻላቸውን ነው፡፡ አልፎ አልፎም የኽምጣኝ ቃል ግጥሞቻቸውን የሚገጥሙበት የከበሮ አመታት የትግርኛ አመታት የሚሆንበት አጋጣሚ አለ፡፡ ለአብነት ያህል ቀደም ሲል የተገለጸው አደ ክቁረድ...የሚ ለው የኽምጣኝ ቃል ግጥም የተገጠመው በትግርኛ የከበሮ አመታት ቅላጼ ነው፡፡

የዘፈኑ አቀንቃኞች የሴቷ ዘመዶች ወይም ዘመድ ያልሆኑ ነገር ግን ችሎታው ያላቸው የሰርጉ ታዳሚዎች ናቸው፡፡ የሠርግ ዘፈንን በማድመቅ በኩል አዝማሪዎችም የራሳቸውን ሚና ይጫወታሉ፡፡ በዚህ ወቅት በዳሱ ውስጥ ዘፈኑ ይሟሟቃል፡፡ ለተወሰነ ጊዜ ጨዋታው ከቀጠለ በኋላ ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው የሙሽራዋ እናት ከሙሽራው ቤት የመጣውን ማር ከድፍድፍ ጋር ለውሳ በወንጠፍት ይዛ ትመጣለች፡፡ በዚህ ጊዜ እልልታው ይደምቃል፡፡ እሷም ድፍድፉን እንደ ያዘች ከጨዋታው መሃል ገብታ ትተላለች[87]፡፡ እስክስታም ትመታለች፤ ሽልማትም ይጎርፍላታል፡፡ ከዚያም ‹‹ጨዋታው ይብቃችሁ፡፡›› ይባላሉ፡፡ ሴቶቹ በመጀመሪያ በማር የተለወሰውን ድፍድፍ ይልሳሉ፡፡ የሙሽራዎቹ ሸኝዎችም ‹‹ተቀመጡ›› ተብለው ይስተናገዳሉ፡፡

[87] ክብ በሆነ የዘፈን ቦታ መሃል ገብታ ክብ ቅርጹን እየተከተለች ትወዛወዛለች፡፡

ሙሽራዋ ወደ ሙሽራው ቤት ስትሄድ የምትወስዳቸው አስራ ሁለት የሴት እቃዎች የሚባሉ አሉ፡፡እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፤



የሙሽራዋ ዘመድ አስራ ሁለቱን እቃዎች እያሳየች (ፎቶ በአፀደ ተፈራ)

በቁኒ[88] የተለወሰ የጸጉር ቅቤ(ላስታ ቅቤ)፣ በዛጎል የተዋበች ትንሽ ቅል(ላክሽም)፣ ቀደም ሲል ዋንጫ አሁን አሁን ደግሞ ብርጭቆ፣ ሁለት (አንዱ ለሙሽራዋ አማት የሚሰጥ) ወስከንቢያ (በኽምጣኛ ጻብ ደቋ)፣ በተለያየ ቀለም በተነከረ ሳር(አለላ) የተሰፋች ሙዳይ፣ መርፌና ክር መርፌው ከሚሰካበት ቀሰም(ቀለም)ጋር፣ ለሹሩባ መፍቻና መሰሪያ የሚያገለግል ወስፌ፣ ምላጭ፣ ኩል፣ መስታወት፣ ሽቶ፣ ማር በዋንጫ፣ ሳሙና እና ሌላዎቹ እቃዎች የሚያዙበት የእቃ መያዣ አቅማዳ(በኽምጣኛ ኀዝ መር) (ባሁኑ ጊዜ ፌስታል) ናቸው፡፡ እነዚህን እቃዎች ቆጥሮ የሚረከበውም ትልቅ ሚዜው ነው፡፡

[88] የቅቤውን ሽታ ጥሩ ለማድረግ በአካባቢው ከሚገኙ እጽዋቶችና ሙጫዎች ማለትም ከአደስና ከከርቤ አልፎ አልፎም ከገላ ሳሙና ሽርፍራፊ ተደቁሶ የሚዘጋጅ ነው፡፡

ሙሽራዋ ወደ ወንዱ ቤት ስትሄድ ከእሷ ወገን አንድ ሰው አብሯት ይሄዳል፤ ይህም ለሙሽራዋ የሚያስብላት ወንድሟ ወይም የስጋ ዝምድና ያለው፣ የአክስቷ ወይም የአጎቷ ልጅ ሊሆን ይችላል፤ ተውሳኽም ይባላል፡፡ ቃሉ የትግርኛ ሲሆን የአማርኛ ትርጉሙም ተጨማሪ ማለት ነው። በኽምጣኛ ተጠባብቅሸው ወይም ሊልምደው ይባላል፡፡ በድሃና እና በጋዝጊብላ ወረዳዎች ደግሞ ወንዝ አሻጋሪ ይባላል፡፡ ይህም ታዛቢ እና ተቆጣጣሪ ነው፡፡ ህግ አስከባሪና አለማማጅም ይባላል (ቁ.የ.መ.አ.21፣ ቡ.ተ.ው.3 እና 4)፡፡

የዚህ ሰው ተግባራትም ሙሽራዎቹ የሚሄዱበት አገር እሩቅ ከሆነና ሙሽራዋ የምትሄደውም በበቅሎ ከሆነ ለበቅሎ የማይመች ቁልቁለት መንገድ ሲያጋጥም ሚዜዎች እንዲያዝሏት እንጂ በእግሯ እንዳትሄድ ማድረግ፤ ከአማቾቿ ቤት ስትሄድ ለአካባቢው እንግዳ ስለሆነች ማለማመድ፤ያለ ምንም ክፍያ ሱሪ እንዳትፈታ(እንዳታወልቅ) መጠብቅና በሙሽሪትና በሙሽራው መካከል በመተኛት ከመልስ በፊት ሙሽራው ከሙሽሪት ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት እንዳያደርግ መከላከል ናቸው። ተውሳኹ የሙሽራዋን ክብረ-ንጽህና እንዲወስድ ለሙሽራው የሚፈቅድለትም መልስ በሚሄዱበት በሶስተኛው ቀን ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ተውሳኽ ከሙሽራው ብር ይቀበላል፣ ብሩም የሱሪ ማውለቂያ(በኽምጣኛ ሱሪ እክሰነው) ይባላል፡፡ መጠኑም ቀደም ሲል አንድ ብር ከሃምሳ ሳንቲም ብቻ የነበረ ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ ግን ሶስት ብር ሆኗል፡፡ ተውሳኽ ወደ ቤቱ የሚመለሰው ከሙሽራዋ ጋር በመልስ ጊዜ ነው (ቁ.የ.መ.አ.23 እና ቡ.ተ.ው.3)፡፡ ሙሽራዎቹ ወደ ወንዱ ቤት የሚሄዱት ወንዱ በበቅሎ ሴቷ ደግሞ በሚዜው ታዝላ ነው፡፡[89]የተመለከትኳቸው አብዛኛዎቹ ሴት ሙሽራዎችም ለመታዘል አስቼጋሪ አልነበሩም፤ የወንዱ ሙሽራ ቤት ከሴቷ ቤት በጣም የራቀ ከሆነ ግን ሴቷ ሙሽራዋም በበቅሎ እንድትሄድ ይደረጋል፡፡ ሙሽራዋና ሙሽራው ሁለቱም በበቅሎ፣ ወይም ሙሽራው በበቅሎ እሷ ታዝላ፣ ወደ የወንዱ ቤት በሚጓዙበት ወቅት ባል ሚስቱን ጠብቆ ለመሄድ እንዲችል፣ ፊት ፊት የምትሄደው ሙሽራዋ ናት፡፡

ሙሽራዎቹ ከሴቷ ቤት ወደ ወንዱ ቤት በሚሄዱበት ወቅት፣ባዷቸውን አይሄዱም፡፡ የወንድ ወገን ሽማግሌዎችና ሚዜዎች ተመግበው ካተረፉት እንጀራ(ኮሸሮ) ቀደም ሲል በአቅማዳ አሁን አሁን ደግሞ በፌስታል ቋጥረው ይይዛሉ፡፡ ይህም አዝመራ (በኽምጣኛ አዝመረ) ይባላል። ሙሽራዎቹ የሚሄዱት በአውቶቡስ ቢሆንም ደንብ ነውና አዝመራ

89 የወንድ ሙሽራዎች ቤት ሰቆጣ ከተማ የሆነው ሶስቱ ሙሽራዎች ወደ ወንዱ ቤት የሄዱት በአውቶቡስ ነው፡፡

ቋጥረው መያዛቸው አይቀርም፡፡ ለአብነት ያህል ከሀሙሲት ወደ ሰቆጣ ከተማ በአውቶቡስ የተጓዙት ሙሽራዎች፣ አዝመራ በፌስታል ቋጥረው ወስደዋል፡፡ አዝመራ በመንገድ ላይ ሴቶች ሚዜዎቹን ‹‹የደንባችንን ስጡን፡፡›› ብለው ሲይዟቸው ቆንጠር አድርገው የሚሰጧቸው ነው፡፡ ሴቶች አዝመራ የሚጠይቁት ሙሽራዎች በጋብቻቸው እለት ሃብት (በረከት) ይወርድላቸዋል ተብሎ ስለሚታመን ያንን ለመጋራት ነው (ቡ.ተ. ው.3 እና4)፡፡

ስለዚህ በመንገድ ላይ በሚገኙ መንደሮች የሚገኙ ሴቶች ሁሉ ሙሽራዎች ባጠገባቸው ማለፋቸውን በጥሩንባ ድምጽና በሚዜዎች ሆታ ሲያውቁ፣ ከየቤታቸው እየወጡና ‹‹እልል›› እያሉ አዝመራ ይጠይቃሉ፡፡ ሚዜዎቹ አዝመራ አልሰጥም ካሉ ግን፣ ሴቶቹ ሙሽራው የተቀመጠባትን በቅሎ በመያዝ አናሳልፍም ይላሉ፡፡ ስለዚህ ላለመንገላታትና የደንቡን ለመፈጸም ሲባል፣ አዝመራ መስጠት የግድ ይላል፡፡ አዝመራ እንዲሰጣቸው የሚጠይቁት ሴቶች እንጂ ወንዶች አይደሉም፤ ምክንያቱም አዝመራ ይዞ የሚሄደው ወንዱ ሲሆን የሚወስደውም ከሴቷ ቤት ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ መንገድ ላይ ሙሽራዎቹን የሚያገኟቸው ሴቶች ነጠላቸውን መሬት ላይ በማንጠፍ ወንዱን ሙሽራ ከበቅሎው ወርዶ፣ በክብ ቅርጽ ጭፈራ እንዲወዛወዝ (እንዲቶል) እና እስክስታ እንዲወርድ ይጠይቁታል፤ ሙሽራውም በሚዜዎቹ ታጅቦ እስክስታ ይወርዳል፡፡ ሴቶቹም በደስታ ሙሽራዎቹን ‹‹ቁረቡ ስገዱ!›› ብለው መርቀው ይሸኟቸዋል፡፡

በ2/5/2005 አቢያ ሊባኖስ ላይ በነበረው ሠርግ እንደ ተመለከትኩት፣ ሙሽራዎቹ ከሴቷ ዳስ ከተሸኙ በኋላ ከሚዜዎቹ መካከል ሁለቱ የብርሃን ብለው ወደ ሴቷ ቤት ሲመለሱ ከርቀት የተመለከቷቸው ሁለት የሴት ወገን ወጣት ወንዶች ሙሽራዋ ታጥባ ወደ ወጣችበትና ሙሽራዎቹ ወደተቃመሱበት ቤት ሩጠው ሄዱ፡፡ እዛም የተበጠበጠ አመድ በሁለት ሽክና ይዘው የወንዱን ሚዜዎች ይጠብቋቸው ጀመር፡፡ ይህንን ያደረጉት ለምን እንደሆነ ለጠየቅሁት ጥያቄ መልሳቸው፣

> ከጥንት አባቶቻችን እንደ ተረከብነው ሚዜዎቹ የሙሽራ ስሟን ይዘው በመምጣትና አድፍጠው ወደ ቤት በመግባት የቤቱን ምሰሶ ከያዙ፣ ወይም ከቤቱ ጣራ ላይ ወጥተው እልል ካሉ፣ አንድ ገንቦ ድቋ (በሽምጣሻ ጭምቆ) አንድ እግር የፍየል ስጋ፣ እቃተኛ፣ እና የብርሃን መሬት፣ ከሴት ወገን ይሰጣቸዋል፡፡ ነገር ግን ሚዜዎቹ ወደ ቤት ገብተው ምሰሶውን

ከመጨበጣቸው ወይም ጣራ ላይ ወጥተው እልል ከማለታቸው በፊት፣ እኛ በአመድ ብጥብጥ ከረጨናቸው የተዘረዘረው ሁሉ አይሰጣቸውም፤ የብርሃን መሬትም አያገኙም የሚል ነው፡፡

በጭቃ ለምን አትረጯቸውም? ለሚለው ጥያቄየ የወጣቶቹ መልስ ‹‹ከጥንት ደንባችን በአመድ ስለሆነ በጭቃ አይሆንም›› የሚል ነበር፡፡ ሚዜዎቹ በርቀት ሆነው ሲመለከቱና ህጻናትን በመላክ ሲያጣሩ፣ የሚጠባበቋቸው ወጣቶች መኖራቸውን አረጋገጡ፡፡ ስለዚህ ወደ ኋላ ተመልሰው የሄዱ መስለው ከርቀት ሆነው የተበጠበጠ አመድ ይዘው የሚጠባበቋቸውን ወጣቶች ከቤት እስከሚወጡ ሲከታተሉ ቆይተው፣ ሲወጡላቸው ወደ ቤቱ በመግባት የቤቱን ምሰሶ ይዘው እልል አሉ፤ የደንቡም ከመሬት በስተቀር ሶስቱ ተሰጣቸው፡፡ በአመድ ባለ መረጨታቸውም ከሴት ቤት የተሰጣቸው ሁሉ ከወንድ ቤትም እንደሚሰጣቸው ነው ሚዜዎቹ የገለጹልኝ፡፡ በሌላ ጊዜም የምስራች ‹‹ልጂቱ እንደ እናቷ ሆነች ክብረ ንጽህናዋን ለባሏ ሰጠች›› ይባላል (ቁ.የ.መ.አ.26)፡፡

ሙሽራዎቹ ወደ ወንዱ ቤት ሲሄዱ፣ ወንዝ የሚሻገሩ ከሆነ ወንዙ ላይ ሴቷ ይዛ ወንዱ በማረድ የጫጩት ደም አፍሰው ይሻገራሉ። ሙሽራዎች ወንዝ ሲሻገሩ ጫጩት የማረድን አስፈላጊነት አስመልክተው፣ የመረጃ አቀባዮቹ ሲገልጹ፣ ‹‹በሴቷ ቤትና በወንድየው ቤት መካከል ወንዝ ከተገኘ ሴቲቱ ጫጩቷን ትይዛለች፤ ወንድየው ቆርጦ ይጥላል፤ ከዚያ ተሻግረው ይሄዳሉ። ሙሽራዎቹ ብዙ ወንዝ የሚሻገሩ ቢሆን ጫጩት የሚያርዱት የመጀመሪያውን ወንዝ ሲሻገሩ ነው (ቁ.የ.መ.አ.5 እና ቡ.ተ.ው.3 እና4)፡፡



**ሚዜዎች ወንዝ ላይ የምትታረደውን ጫጩትና የሴት እቃዎች ይዘው (ፎቶ በአፀደ ተፈራ)**

ሁለት ሙሽራዎች መንገድ ላይ ከተገናኙ ሁለቱም ከበቅሏቸው ወርደው ይሳሳማሉ፤ ይመራራቃሉ። ከያዙት አዝመራ በመጎራረስም ይቃመሳሉ፤ ‹‹እንከዳዳም›› ተባብለውም ቃል ይገባባሉ፡፡ በመንገዳቸው ላይ ቤተክርስቲያን ካለም ሙሽራዎቹ ዝም ብለው ማለፍ

የለባቸውም[90]፡፡ ከበቅሏቸው ወርደው መሳለም አለባቸው፡፡

ሙሽራዎቹ ወደ ወንዱ ቤት ዳስ ሲገቡም ካላቸው ፍየል ከሌላቸውም ጫጩት አርደው ተሻግረው ይገባሉ። በአንዳንድ አካባቢም ሁለቱም የቤቱን ምሰሶ ይዘው ‹‹እልል›› ይላሉ፡፡ በወንድ ቤት ሙሽራዋን የምትንከባከበውም በሴቷ ቤት ስጦታ የተሰጣት፣ የሙሽራው እህት ወይም ዘመድ ናት፡፡

በሚቀጥለው ንኡስ ርእስ ደግሞ የድህረ ሠርግ ተግባራትን አቀርባለሁ፡፡

[90] በዋግ ኽምራ ዞን ፣ ወደ ዝቋላ ወረዳ ሲኬድ መንገድ ላይ አንድ ሙሽራው ተራራ የሚባል አለ፡፡ የተራራው ቅርጽ ሁለት ሰዎች በበቅሎ ላይ ተቀምጠው ነው፡፡ የአካባቢው አባቶች የስያሜውን አፈ-ታሪክ ሲገልጹ፣ ባንድ ወቅት ሙሽራዎች በዚያ በኩል በሚያልፉበት ወቅት ከተራራው በታች የሚገኘውን ቤተክርስቲያን(አሁንም አለ) ሳይሳለሙ አልፈው በመሄዳቸው አምላክ ተቆጥቶ አድርጓቸው ነው ይላሉ፡፡

## 5.4 ድህረ ሠርግ ተግባራት

በድህረ ሠርግ ተግባራት የሚቀርቡት ሙሽራዎቹ በሴቷ ዳስ ቃል ኪዳናቸውን ፈጽመው፣ ወደ ወንዱ ቤት ከሄዱ እና የወንዱም ሠርግ ከተጠናቀቀ በኋላ የሚከናወኑት ናቸው፡፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 5.4.1 የሙሽራዎች የጫጉላ ቤት ቆይታ

በዋግ ኽምራ በተለይም በገጠሩ የሙሽራዎች የጫጉላ ቤት ቆይታ ለሶስት ቀናት ያህል ብቻ ነው[91]፤ ምክንያቱም በሶስተኛው ቀን ወደ ሴቷ ቤት መልስ(**ምላሽ፣ በኽምጣኛ ዋጥር**)ተጠርተው ስለሚሄዱ ነው፡፡ የጫጉላ ቤት የሚሆነውም በወንድ ቤተሰብ ቤት ለጫጉላ ቤት የሚሆን ትርፍ ቤት ከሌላቸውም በጎረቤት ቤት ነው፡፡ በቆይታቸውም ጎረቤትና ቤተ-ዘመድ ለሙሽራዎች ምግብ ይወስዳል፤ይህ ምግብ በኽምጣኛ **አስኹር**(የአማርኛ ትርጉም እንካ/እንቺ ልጅ) ይባላል፡፡ የአስኹር አይነት እንደ የምትወስደው ሴት አቅምና ከሙሽራው ቤተሰብ ጋር እንዳላት ቀረቤታ የሚወሰን ነው፤ በዝምድና ቀረብ ያሉትና አቅም ያላቸው በዶሮ ወጥ፣ በስጋ ወጥ፣ በስልስ ወጥ እንጀራ ወይም እቃተኛ ሲወስዱ፣ ራቅ ያሉት ወይም አቅም የሌላቸው ደግሞ በክክ ወጥ እንጀራ ይወስዳሉ፡፡ የሚወስዱትን አስኹርም በቀጥታ ለሙሽራዎቹ አይሰጡም፤ በመጀመሪያ የሚያስረክቡት ለሚዜዎቹ ነው፡፡ የመጀመሪያው አስኹርም በቄስ ተባርኮ በስርዓት የሚበላ ሲሆን፣ ከዚያ በኋላ የሚመጣውን ግን የምታመጣው ሴት ደብቃ ካልያዘች በስተቀር፣ ሚዜዎች ከመንገድ በመቀማት ተሻምተው (**ተዋረው**) ሊመገቡት ይችላሉ፡፡ ተከታትሎ በብዛት የሚመጣን አስኹር ደግሞ አንድ እጁን ለሽማግሌ በመስጠት፣ ሁለት እጁን ለሚዜ በማድረግ ይመገባሉ፡፡ **አስኹር** መውሰድ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው ‹‹እከሌ ልጄን ስድር አስኹር አላመጣችም›› ተብሎ መቀየም ስላለ ሁሉም እንደ አቅሙ ይወሰዳል (ቁ.የ.መ.አ.14፣25፣ ቡ.ተ.ው.3 እና 4)፡፡

### 5.4.2 ሙሽራዎቹ ከሚዜዎች ጋር ቃል መግባት

ሙሽራዎቹ ወደ ሴቷ ቤት መልስ ከመሄዳቸውና ሚዜዎችም ወደየቤታቸው ከመበታተናቸው አስቀድሞ ቃል መግባት ይኖርባቸዋል፡፡ የወንዱ ሚዜ የሙሽራዋ ዘመድ ከሆነ ከሙሽራዋ

[91] የሙሽራው አገር ከሙሽራዋ እራቅ ያለ ከሆነ ግን እስከ ሳምንት ሊራዝም ይችላል ፡፡

ጋር ቃል አይገባም፡፡ ሚዜዎቹ ቃል የሚገቡትም እንዲህ ብለው ነው፣ ሴቷን ሙሽራ ‹‹ወንዝ ላይ ባገኛት ወንዝ አሻግራታለሁ›› ሲሉ ሴቷ ደግሞ፣ ሚዜዋ ወደ ቤቷ ሲመጣ፣ ‹‹ሊጥ በማቡካት ላይ ብሆንም ሊጥ ይዤለሁ ብየ ችላ ሳልል ሚዜየ(ይመዘ) ብየ በፍጥነት ወጣ በማለት እቀበለዋለሁ›› ብላ ቃል ትገባለች፡፡ ይህም የሚከናወነው በቅደም ተከተል ነው፡፡ በመጀመሪያ ትልቅ (ስር)ሚዜውን ከሙሽራዎቹ ጋር ቃል የሚያጋቡት ቄስ ናቸው፡፡ በመቀጠልም ሌላዎቹ ሚዜዎች በትልቅ ሚዜው አማካይነት ቃል ይገባሉ፡፡ ከቃል መግባት በኋላ ሚዜና ሚዜ ዘመዶች ስለሆኑ መጋባት አይፈቀድላቸውም፡፡

በዚህ ቀን የሚዜዎች የመሸኛ ወይም የመለያያ የልብስ አጠባም ይካሄዳል። ይህም በኽምጣኛ **ዲቨሲግ (ዘግተህ ውቀጥ)** ይባላል። ከሙሽራዎቹ ጋር ወደ ሴቷ ቤት መልስ የሚሄዱት ከሙሽራው ቤት ሲቀሩ፣ ሌላዎቹ ሚዜዎች ግን በየቤታቸው ይሄዳሉ፡፡

### 5.4.3 መልስ (ምላሽ) (በኽምጣኛ ዋጥር)

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ የሙሽራዎቹ የመጀመሪያው መልስ የሚከናወነው በሰርጉ በሶስተኛው ቀን ነው፡፡ በመልስ የሚሄዱት ሰዎች መጠንም እንደ ሴቷ ቤተሰብ አቅም የሚወሰን ነው፡፡ ሙሽራዋ በሰርጓ እለት የተወሰደላትን የነዶ ልብስ አሰፍታ በመልበስ፣ ትኩሴ ይዛ ትሄዳለች፡፡ ከሴቷ ቤትም ሙሽራዎቹ ዱለት ሳይቀምሱ ቀሩ እንዳይባል (በአቅም የሚወሰን ነው) ፍየል ይታረዳል፡፡ ለሶስት ለአራት ቀናት ተስተናግደውም ወደ ወንድ ቤት ይመለሳሉ፡፡ ሙሽራዋ ከቤተሰቦቿ ወደ ባሏ ቤት ስትመለስ፣ በተመሳሳይ ትኩሴ ይዛ ትመለሳለች፡፡ ከዚያ በኋላ በሚካሄዱ መልሶች ግን ወደ ቤተሰቦቿ ስትሄድና፣ ስትመለስ የምትይዘው **እንባሻ** ነው፤ ለአብነት ያህል የአንዲት ሙሽራን የመልስ ሁኔታ አባቷ ሲገልጹ፣

> ሙሽራዎቹ መጀመሪያ ሲመጡ፣ አምስት እራሳቸውን[92]ሆነው መጡ፤ ሙሽራዋ ተሞሽራ ከነበረችበት ቤት ለብቻቸው እንዲሆኑ ተደረገ፡፡ በመጀመሪያ እቃተኛ ተሰጣቸው፤ ሲዘፍኑም አንድ ገንቦ ዱቃ ተሰጣቸው፡፡ ቅዳሜ መጥተው በሶስተኛው ቀን ሰኞ ተመለሱ፤ ሙሽራዋ በመጀመሪያ ስትመጣ ትኩሴ ይዛ መጣች፤ ከእኛም ትኩሴ ይዛ ተመለሰች፤ ከዚያ በኋላም ሁለት ጊዜ ምላሽ ጠርተናቸው ነበር፡፡ በእነዚህ ቀናት ግን ይዛ የመጣችውና ከእኛም የወሰደችው አንባሻ ነው ብለዋል (ቁ.የ.መ.አ.5)፡፡

[92] መጠናቸው አምስት የሆነ

በመልስ ወቅት ከሚከናወኑ ነገሮች መካከል አንዱ ሙሽራዎቹ (ባልና ሚስት) ስማቸውን እንዲጠራሩ ማድረግ ነው፤ ምክንያቱም በአካባቢው ሚስት የባልን፣ ባል ደግሞ የሚስትን ስም መጥራት ያልተለመደ ነው፡፡[93] ስለዚህ ባንዳንድ ቦታዎች ሚዜዎቹ የመስቀል ቅርጽ ባለው እንጨት የሙሽራዎቹን መቀመጫ በመምታት ስማቸውን እንዲጠራሩ ያስገድዷቸዋል፤ ከተጠራሩም የባልን ወይም የሚስትን ስም በመጥራታቸው አብረዋቸው የሚገኙት ሰዎች በሙሉ ይስቃሉ፡፡ ሚዜዎች የሙሽራዎችን ስም መጠራራት በመዝናኛነት ይጠቀሙበታል (ቁ.የ.መ.አ.16)፡፡

ለሙሽራዎቹ የሚደረገው የመልስ ጥሪ መጠን እንደ አቅም የሚወሰን ቢሆንም፣ ቢያንስ ቢያንስ ግን አንድ አባት ልጁን ሶስት ጊዜ መልስ መጥራት አለበት፡፡

### 5.4.4 የሙሽራ ስም አወጣጥ

ከድህረ ሠርግ ክዋኔዎች መካከል አንዱ የወንድ ቤተሰቦች ለሙሽራዋ የሙሽራ ስም ማውጣት ነው፡፡ የሚያወጡላትም የወንድ አባትና እናት ናቸው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ሙሽራዋ ከወንዱ ቤት ሳትደርስ በመንገድ ላይም በሙሽራው አባት የሙሽራ ስም እየወጣላት መሆኑን ነው ጥር 2/2005 አቢያ ሊባኖስ ላይ በነበረው ሠርግ የተመለከትኩት፡፡ ምክንያቱም የብርሃን ይዘው የሚሄዱት የሙሽራ ስሟ ትውረስ መሆኑን የገለጹት ሚዜዎች ከመንገድ ተመልሰው ነው፡፡

የሙሽራው ቤተሰቦች የሙሽራ ስም የሚያወጡት እንዳስፈለጋቸው ወይም በዘፈቀደ አይደለም፤ ለስያሜያቸው ምክንያት የሚሆኗቸው ወይም ግምት ውስጥ የሚያስገቧቸው ነገሮች አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ሙሽራዋ ይዛው የሄደችው የማጫና የስጦታ (ገንዘብ፣ በቅሎ፣ ከብት) መጠን፣ በጋብቻው ወቅት አማቾቿ የሚገኙበት ሁኔታ፣ እና ሙሽራዋ ለወንዱ ቤተሰብ ስንተኛ ሙሽራ መሆኗ ወዘተ.ናቸው፡፡ ሙሽራዋ ብዙ ማጫና ስጦታ ይዛ የሄደች ከሆነ ከሚሰይሟት መካከል ታፈሱ፣ የብር ዛፍ፣ ሙሉነሽ፣ ሙሉ ወርቅ፣ የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡ የሙሽራው እናት ወይም አባት በጣም አቅመ ደካማ ከሆኑ እንኳዬ፣ ሟች ከሆኑ ደግሞ ባዩሽ ይሏታል፡፡ ለወንዱ ቤተሰብ (እናትና አባት) የመጀመሪያ ሙሽራ

[93] ከወለዱ በኋላም ቢሆን ለተወሰነ ጊዜ እርስ በእርሳቸው ስማቸውን ላለመጠራራት አንተ/አንቺ ወይም ልጆቻቸውን አባትህ/ እናትህ እያሉ ይጠራራሉ፡፡

ከሆነች ደግሞ፣ ብርሐኔ፣ አለማየሁ፣ የመጨረሻ ከሆነች ደግሞ ትውረስ ወይም ሁሉላንቺ ትባላለች፡፡

ለአብነት ያህል የካቲት 1/2004 ዓ.ም የጋብቻ ሥነ-ሥርዓቷን የፈጸመችው አለምጸሀይ ደሳለኝ የሙሽራ ስሟ ታፈሱ ነው፡፡ ምክንያቱን አባቷ ሲገልጹልኝ፣ ከማጫው በተጨማሪ ለስጦታ ከአራት ሺህ ብር በላይ በመስጠታቸው ነው (ቁ.የ.መ.አ.4)፡፡ ሚያዚያ 21/2004 ዓ.ም የጋብቻ ሥነ-ሥርዓቷን ለፈጸመችው ለአደነቁሽ ግዛት የወጣው የሙሽራ ስም ደግሞ ሙሉነሽ ነው፤ ስሙ የተመረጠውም፣ መሰረት፣ ሳራ፣ ጸሃይነሽና ሙሉነሽ የሚሉ አራት ስሞች ከተጠቆሙ በኋላ ነው፡፡ ለሙሉነሽ መመረጥ ምክንያቱ፣ ሙሽራው እናቱና አባቱ ሟች ስለሆኑ፣ ሚስቱ ለሙሽራው የእነሱ ማሟያ እንድትሆንለት ነው (ቁ.ያ.መ.አ.10)፡፡

ሙሽራዋ የሙሽራ ስም እስከሚወጣላት ድረስ ከአማቷ ቤት አትገባም፡፡ ብዙ ስሞች ተጠቁመው ስም እንዲሆኑ ሲጠሩ የሙሽራው እናት ላልጠቆመችው ስም ሚዜዎቹ ‹‹ሚያው›› ይላሉ፡፡ እናት ለጠቆመችውና ስም መሆን ላለበት ደግሞ አቤት አቤት ይላሉ፡፡ (ቁ.የ.መ.አ.26) ሙሽራዋን በሙሽራ ስሟ የሚጠሯትም የወንድ ወገኖችና ጎረቤቶቹ ናቸው፤ የስጋ ዘመዶቿ በዚህ ስም አይጠሯትም፡፡ ዘመዷ የሆነ ሰው ተድራ በሄደችበት አገር የሚኖር ቢሆን ወይም ቢሄድ የሚጠራት በሙሽራ ስሟ ሳይሆን በአለም (እናት አባቷ ባወጡላት) ስም ነው፡፡

### 5.4.5 ጎጆ አወጣጥ

የሙሽራዎቹ ጎጆ መውጫ ጊዜ በሰርጋቸው እለት በተገለጸው የሰማንያ አፈጻጸም ይወሰናል፤ በሰርጉ እለት የሙሽራዋና የሙሽራው ወገኖች አስቀድመው የሚወስኑት አለ፤ ይህም በጎጆ ነው ወይስ በሲሶ የሚል ነው፡፡ በጎጆ ከሆነ ከሠርጋቸው ከሳምንት ወይም ከወር በኋላ ሙሽራው ‹‹ሙሃቻህን ለይ››ተብሎ ሙሽራዎቹ ወደ ተዘጋጀላቸው የግል ቤታቸው በመግባት ጎጇቸውን ይቀልሳሉ፡፡ በሲሶ ከሆነ ግን ጎጆ ለመውጣት የሚያስችላቸው በቂ አቅም ስለማይኖራቸው፣ ከወንዱ ቤተሰብ ጋር አብረው እየሰሩ ይከርሙና ሲሷቸውን ይወስዳሉ፤ ይህም ከተገኘው ምርት አንድ እጅ ለእነሱ ሁለት እጅ ለቤተሰቦቹ በመከፋፈል ነው፡፡ ሲሷቸውን ከተካፈሉ በኋላም እህላቸው እንዳይቀንስባቸው

እስከ ጥር ድረስ ከሲሷቸው አይበሉም፡፡ ከዚያ ባገኙት እህል ጎጆ ይወጣሉ (ቁ.የ.መ.አ.10 እና18)፡፡

ለአብነት ያህል ቀደም ሲል በአግብተህ ክረም የጋብቻ ዓይነት የተገለጸው አዳነ ግርማይ ከሰርጉ አስቀድሞ ሲሶውን ወስዷል፤በሴቷ ሠርግ የሰማንያ አፈጻጸምም ጎጆ መውጣት ስለሚችል በጎጆ ተብሏል፡፡ ስለዚህ ሚስቱን ወደ ቤቱ እንዳመጣ በሳምንቱ ከአባቱ ቤት አጠገብ በተሰራችው ጎጆ፣ በተዳሩበት ዘመን በ2004 ዓ.ም ጎጆ እንደወጡ አባቱ ነግረውኛል (ቁ.የ.መ.አ.9)፡፡

ለሙሽራዎቹ ጎጆ መውጫ የሚሆነው ቁሳቁስም ከወንድና ከሴት ወገን ይሰጣቸዋል፡፡ ሞፈር ቀንበርና ሌላ ለእርሻ ስራ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች በወንድና በሴት አባት፣ የቤት ቁሳቁሶች ደግሞ በሴት እና በወንድ እናቶች ይሰጣሉ፡፡ የሴት እናት፣ ጨው(ጥሬ ጨው) ሰፌድ፣ ሌማት ድስት፣ ወስከንቢያ፣ የውሃ መቅጃ እንስራ፣ የመሳሰሉትን ስትሰጣቸው፣ የጠፍር አልጋ፣ ምንጣፍ፣ የውሃ መገልበጫ ትልቅ እንስራ፣ መሶብ የሊጥ እቃ(ሙሃቻ) የመሳሰሉትን ደግሞ፣ የወንድ እናት ትሰጣለች፡፡ በጎጆ መውጫ ቁሳቁስ ላይ የሙሽራዎቹ ወላጆች ብቻ ሳይሆኑ፣ ቤተዘመድም ይሳተፋል፤ ይኸውም ሙሽራዎቹ ጎጆ የወጡበትን ቤት ለማየት ብለው በሚሄዱበት ወቅት፣ ሴቶቹ የቤት ቁሳቁሶችን፣ ወንዶቹ ደግሞ የእርሻ መሳሪያዎችን ይዘውላቸው ይሄዳሉ (ቡ.ተ.ው 2 እና 3)፡፡

ሙሽራዎቹ ጎጆ የሚወጡት በብዛት በወንድ ቤተሰብ ቤት አካባቢ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ የወንድ ቤተሰቦች የኢኮኖሚ አቅማቸው ደካማ ከሆነና ወንዱ ከሴቷ ቤተሰብ ጋር እየሰራ የኖረ ከሆነ ግን በሴት ቤተሰብ አካባቢም ጎጆ ይወጣሉ፡፡ ይህም ወንዱን **ቁልቁል ገባ(በኽምጣኛ አውርሳ)** ያስብለዋል፡፡ ምክንያቱም የተዘወተረው የሙሽራዎች የጎጆ መውጪያ አካባቢ ሴት ወደ የወንድ ቤተሰብ በመሄድ እንጂ ወንድ ወደ የሴት ቤተሰብ አካባቢ በመሄድ አይደለም (ቁ. የ.መ.አ.15፣ ቡ.ተ.ው 3 እና 4)፡፡

ይህም በዋግ ኽምራ ዞን ብቻ ሳይሆን በአማራ ክልል በሚገኙ በሌሎች ዞኖችም የሚከናወን መሆኑን ዋጋው(2001፣51) እንደሚከተለው አስፍረዋል፤

> ማንኛውም ቤተሰብ ጋብቻ ከተመሰረተ በኋላ የሚኖርበት ቀየ (አካባቢ) ህብረተሰቡ ባለበት የኢኮኖሚ ደረጃ፣ የመሬት ይዞታና

የቤተሰብ አወቃቀር አንጻር በልምድ ይወሰናል፡፡ በአማራ ክልል በገጠሩ ክፍል የአባትን ቀየ የቤተሰቡ መኖሪያ ማድረግ በሁሉም ስፍራዎች የሚዘወተር በጣም የቆየ ልማድ ነው፡፡ በባህሉ መሰረትም ተጋቢዎች የአዲሱ ትዳራቸውና የቤተሰባቸው መኖሪያ የሚሆነው የወንዱ አባት ቀየ ነው፡፡ ስለዚህም፣ ወንዶች ቤተሰባቸው አካባቢ ቤት ሰርተው ከሌሎች ወንድሞቻቸውና እኅቶቻቸው ጋር የመኖር እድል ሲገጥማቸው ሴቶች ግን በጋብቻ ወደተሳሰሩት ቤተሰብ የመሄድ ግዴታ አለባቸው ፡፡ (አጽንኦት የራሴ) አልፎ አልፎ ግን አንዳንድ ቤተሰቦች ልጆቻቸው በሙሉ ሴቶች ሲሆኑና ቤተሰቡን የሚደግፍ፣ ሃብቱንና ንብረቱን የሚያስተዳድር ወንድ ልጅ ሳይኖራቸው ሲቀር ልጆቻቸውን ካጋቡ አማቾቻቸው ውስጥ አንደኛውን ወይም ሁለቱን በእነርሱ ቀየ ጎጆ ወጥተው እንዲኖሩ የማድረግ ልምድ እንዳለ ይነገራል፡፡ ዳሩ ግን በጠቅላላው በእማች ቀየ ወይም በሴት አባት ቀየ መኖር ብዙም የሚዘወተር አይደለም፡፡(አጽንኦት የራሴ)

ባጠቃላይ የዋግ ኽምራ ህብረተሰብ የጋብቻ ሥነ-ሥርዓት ቅደም ተከተላዊ ክዋኔዎቹ በሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ተሳትፎ የሚከናወን ማህበራዊ ድርጊት መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

## የዋግ ኽምራ ዞን ህብረተሰብ የሞት ሥነ-ሥርዓት

በዚህ ምዕራፍ የሚቀርበው የዋግ ኽምራ ዞን የሞት ሥነ-ሥርዓት ገለጻ ነው፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ ስለሞት ያለው አመለካከት፣ የቅድመ ቀብር፣ የቀብርና የድህረ ቀብር ክዋኔ በምን ዓይነት አውድ እንደሚከወን እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡

### 6.1 ህብረተሰቡ ስለ ሞት ያለው አመለካከት

የተለያየ የህብረተሰብ ክፍል ሞትን በተለያየ መንገድ ሊረዳው ይችላል፡፡ ለአብነት ያህል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አገልጋዮች ሞትን የሚረዱበት መንገድ ከሌላው የእምነቱ ተከታይ ይለያል፡፡ ይኸውም ለእነሱ ሞት ማለት ከሚያልፈው አለም ወደ የማያልፈው አለም መሸጋገር ነው፤ በእነሱ የነፍስ ሞት ነው እንጂ የስጋ ሞት ቦታ አይሰጠውም፡፡ ከአጀማመሩ ጋር አያይዘውም ሞትን እንደሚከተለው ይገልጹታል፤

> ሞትን የፈጠረው ሰው ራሱ ነው እንጂ አምላክ የሰውን ልጅ የፈጠረው እንዲሞት አልነበረም፤ አዳም አትብላ የተባለውን በመብላቱ ሞትን አመጣ፡፡ አታድርግ እየተባለ በማድረጉ ሞትን ቀምሷል፡፡ ሞት ከዚህኛው ዓለም ወደ እዚያኛው ዓለም፣ ከምድራዊው ወደ ሰማያዊው፣ ከመከራ ወደ እርካታ ያለበት ዓለም መዛወር ነው፡፡ ስለዚህ የመሸጋገሪያ ድልድይ ነው፤ በመሆኑም ሞት የሁሉም ናት፤ ሞትን ሳያይ ህያው ሆኖ የሚኖር የለም፡፡ በሌላ በኩል ሞት ጽድቅን የሚያሰራ መሳሪያም ነው፡፡ ሰው እሞታለሁ ብሎ መልካም ነገር እንዲሰራ ይጋብዘዋል (ቁ.የ.መ.አ.13)፡፡

ስለዚህ የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ሞትን በጎ አድርጋ እንጂ መጥፎ አድርጋ ስለማትመለከተው፣ የነፍስ ከስጋ መለየት ሞት ሳይሆን እረፍት ነው ይላሉ (ቁ.የ.መ.አ.2)፡፡

ምንም እንኳ የዋግ ኽምራ ማህበረሰብ የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታይ ቢሆንም፣ አብዛኛው ለሞት ያለው እይታ ግን ከእምነቱ መሪዎች የተለየ ነው፡፡ አብዛኛው ሰው ‹‹ በሰማይም ህይወት አለ፡፡›› ሲባል ቢሰማም፣ ሞትን የሚረዳው ግን ከዚህ በተለየ መንገድ ነው፡፡ ይኸውም ዘላለማዊ እረፍትና መለያየት ነው ይላል፡፡ ሞቱንም የስጋ ብቻ ሳይሆን የነፍስም ያደርገዋል፤ በዚህ ምክንያት ሀዘኑ የመረረ ነው፤ ቤተክርስቲያን የምታወግዘውን ሴቷ ሽሩባዋንና ፊቷን ትልጣለች፤ትነጫለች፤ ወንዱም ፊቱን ይልጣል፡፡ አንዳንድ ወደ

ቤተክርስቲያን ሰዎች  በጣም ጠጋ ብለው ስለ እምነቱ የሚያውቁ ግን ሞት ከምድራዊው አለም ወደ ሰማያዊው ዓለም መጓዝ መሆኑንና ጸጉር መንጨትና ፊት መላጥ አስፈላጊ አለመሆኑን እንደሚከተለው ይገልጻሉ፤

> የተዘራው እህል ፈርሶ እንደ ገና በቅሎ እንደሚያፈራ ሁሉ ሰውም ይነሳል፤ ነገር ግን ማህበረሰባችን ይህንን አይረዳም፡፡ ያለ ማወቅ ካልሆነ በስተቀር ሞቶ መቅረት አይደለም፤ መጥፎ የሰራ መጥፎ ነገር፣ ጥሩ የሰራ ደግሞ ጥሩ ነገር ያገኛል፡፡ ፊትን መላጥና ጸጉርን መንጨትም አባቶች[94]ያቆዩት ነው እንጂ ሃይማኖታዊ አይደለም (ቁ.የ.መ.አ.11)፡፡

ይህ አገላለጽ የሃይማኖት አባቶች የሞትን ምንነት አስመልክተው ከገለጹት ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም የአብዛኛው ሰው አመለካከት አይደለም፡፡

በዋግ ኽምራ ዞን ‹‹እከሌ ሞቷልና ወደዚህ ቦታ ሂዳችሁ እንድትቀብሩ፣›› ብሎ የሚያሳስብ፣ የእድር ለፋፊ የለም፡፡ በዚህ ምክንያት የሞትና የሀዘን ሥነ-ሥርዓት ሲወሳ፣ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሰው በዞኑ እድር አለመኖሩ ነው፤ እድር የሚወደድም አይመስልም፤ ምክንያቱም፣

አዙረህ አዙረህ ካገሬ መልሰኝ፣

በሹም የታዘዘ[95] አፈር አታልብሰኝ፡፡

የሚለው ቃል-ግጥም ማህበረሰቡ ስለ እድር ያለውን አመለካከት በሚገልጽ መንገድ በአካባቢው ባህላዊ ዘፋኞች ዘንድ በተደጋጋሚ ይገጠማልና፡፡ የቃል-ግጥሙ ጭብጥ አንድ ሰው ሲሞት ሰዎች ወደ ቀብር ቦታው መሄድ ያለባቸው በራሳቸው ፈቃድ ተነሳስተው እንጂ በሌላ አሳሳቢ (የእድር ለፋፊ) ሰው ታዘው መሆን የለበትም የሚል ነው።

ይሁን እንጂ ማህበረሰቡ የቀብርና የማስተዛዘን ሂደቱን የሚያከናውንበት ባህላዊ ሥነ-ሥርዓት አለው፤ ይህን ሥነ-ሥርዓትም በቅደም ተከተል በቅድመ-ቀብር፣ቀብርና ድህረ ቀብር ንኡስ ርእሶች እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡

---

[94] ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ለማለት ነው ፡፡

[95] በእድር ለፋፊ የሚታዘዝ የቅበሩ ጥሪ ለማለት ነው፡፡

## 6.2. የቅድመ-ቀብር ሥነ-ሥርዓት

ሞት በተለያየ ምክንያት ሊመጣ ይችላል፣ በእርጅና፣ በአደጋ፣ በህመም፣ ራስን በማጥፋት ወዘተ. በህመም ላይ የሚገኝ ሰው ወደ ሞት እያመራ ወይም ጣዕረ-ሞት ላይ መሆኑን የሚያመለክቱ ምልክቶች አሉ፤ እነዚህን በሚመለከት አቶ ተበጀ በላይ እንዲህ ገልጸዋል፡፡ ‹‹ጣዕረ ሞት ላይ የሚገኝ ሰው አተነፋፈሱ ወደ ላይ ነው፤ በመጨረሻ ግን ሲቅ ሳይል ነፍሱ አትወጣም፤ ስለዚህ አስታማሚዎች በዚህ ምልክት ሰውየው/ሴትየዋ እንደሚሞት/እንደምትሞት ያውቃሉ›› (ቁ.የ.መ.አ.4)፡፡

አንድ ሰው መሞቱን የሚያመላክቱ ነገሮች ከታዩበትና በመድከም ላይ ከሆነ፣ ከሞተ በኋላ ቤተሰቦቹ ለጭቅጭቅና ለጥላቻ እንዳይዳረጉ ሲባል፣ የነፍስ አባት ወይም በአቅራቢያው የሚገኝ ቄስና ሌሎች ሁለት እማኞች በተገኙበት ሀብትና ንብረቱን በሚመለከት እንዲናዘዝ ይደረጋል፡፡ በኑዛዜው ወቅት ተናዛዡ የተናገረውን በትክክል ይገልጹልኛል(ይሆኑኛል) የሚላቸው ዘመዶችና ጎረቤቶች ይጠራሉ፡፡ሚስትና ልጆችም ገብተው ኑዛዜውን ያዳምጣሉ፡፡ በገጠር የሚጽፍ ከሌለ ኑዛዜው በቃል ይከናወናል፡፡ እንደ አቶ አካሉ ግርማይ ከሆነ ደግሞ፣ በዞኑ በህመም ላይ የሚገኝን ሰው የማስታመም ችግር አለ፤ ታሞ የነበረው ከሞተ በኋላ ግን ‹‹እኔም ንብረት ማግኘት አለብኝ፡፡›› በማለት በኑዛዜው መሰረት ከወረሱት ጋር ጠብ የሚፈጥሩ አሉ፡፡ ይህም የኑዛዜው ቃል እንዲፈርስና ችግር እንዲፈጠር ያደርጋል (ቁ.የ.መ.አ.11)፡፡

በድንገትም ሆነ በህመም ሲሰቃይ የነበረ ሰው ሲሞት፣ ካጠገቡ ሆነው ሁኔታውን በመጠባበቅ ላይ በሚገኙት ቤተሰቦቹ ለቅሶ ሞቱ ይስተጋባል፤ ጎረቤትም ለቅሶውን ሲሰማ በድንጋጤ እያለቀሰ ወደ ሟቹ ቤት ይሄዳል፡፡ ለቀስተኛው ከየአቅጣጫው ይሰባሰብና ለቅሶው ተሟሙቆ ይቀጥላል፡፡

አንድ ሰው የሞተው ከሰዓት በኋላ ከሆነ በእለቱ እንዳይቀበርና እንዲያድር ለማድረግ በቤተሰብ አማካይነት ለብዙ ጊዜ እንዳይለቀስ ይደረጋል፡፡ ምክንያቱም ከተለቀሰ በእምነቱ መሰረት እሬሳው ሳያድር መቀበር ይኖርበታል፤ ካህናቱ ለቅሶውን ሰምተው በመምጣት እንዲቀበርም ያስገድዳሉ፡፡ ሳያድር ወዲያው የማይቀበረውም ያልቀበረው ወገን እየተንጠባጠበ በመምጣት የሟችን ቤተሰብ እንዳያስቸግር ነው፡፡ ካደረ ግን ከያለበት

እንዲጠራና ባንድ ጊዜ ቀብሮ እንዲያስተዛዝን ይሆናል፡፡ እንዲሁም በአነስተኛ ወገን ከመቅበር ይልቅ በዛ ባለ ሰው እንዲቀበር ያደርጋል፡፡

ስለዚህ አስከሬኑ ወደ ቀብር ቦታ ከመወሰዱ አስቀድሞ የቀባሪዎች ጥሪ ይደረጋል፤ ይህም ቡታ ነገራ ወይም እሪታ (በሽምጣዣ ድቻኬ) ይባላል (ቡ.ተ ው.2፣3 እና4)፡፡

**የቀባሪዎች ጥሪ፣ ቡታ ነገራ፣ እሪታ (በሽምጣዣ ድቻኬ)**

ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው ሟችን ወዲያው መቅበር ከማይፈለግባቸው ምክንያቶች አንዱ፣ ወገን ከያለበት ተሰባስቦ በመምጣት እንዲቀብር ለማድረግ ነው፡፡ በገጠር ደግሞ ቤተሰብ የሚገኘው በተለያየና በተራራቀ ቦታ ላይ ነው፡፡ ስለዚህ መቅበር ይገባዋል የሚባል ወገን ይኖርበታል ወደ ተባለበት ቦታ ሁሉ የሞተውን ሰውና የቀብር ቦታ በመግለጽ የቅበሩ ጥሪ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም ቡታ(እሪታ) ነጋሪዎች ይላካሉ። እነዚህም ሰዎች በእርግጠኝነት ጥሪውን የሚያስተጋቡ፣ ታማኝ(ቁርጥ) መልእክተኛ የሆኑ ናቸው፡፡ የቡታ ነጋሪዎች መጠንም ሁለት መሆን አለበት፡፡

ጥሪው የሚከናወነውም ሁለቱ ቡታ ነጋሪዎች ከፍተኛ ቦታ ላይ ሆነው፣ በጎጡ ውስጥ ታዋቂ የሆነውን የአንድ ሰው ስም በመጥራት "እገሌ ተጎድቷል[96]፤ ቀብሩም እዚህ ቦታ ነው እንድትመጡ፣ እናንተም ወገን ወዳለበት ቦታ ቡታውን እንድትነግሩ" በማለት የሰማው ሰው ላልሰማው እንዲነግር በማሳሰብ ነው። የሰሙት ደግሞ ከነሱ አጠገብ ለሚገኙት እየተቀባበሉ በመንገር ቡታው እንዲዳረስ ያደርጋሉ (ቡ.ተ.ው 2፣3 እና 4)፡፡ በአሁኑ ጊዜ ወደ ገጠርም ስልኩ ካላቸው የቅበሩ ጥሪው የሚከናወነው በተንቀሳቃሽ ስልክ እየሆነ ነው፡፡

**አገናነዝ**

የቡታ ነገራው በተጠቀሰው መንገድ ሲቀጥል፣ ሬሳውን ለቀብር የማዘጋጀቱ ስራ ደግሞ በቤት ውስጥ ይከናወናል፡፡ በመጀመሪያ ሬሳው ይታጠባል፤ እሬሳ የሚታጠበው በእንባጮ፣ በደደሆ ወይም በለምልም ቅጠል ነው(ቁ.የ.መ.አ.11እና21)፡፡ የሚቀጥለው ተግባር እሬሳውን መገነዝ ነው፡፡ የሚገነዘውም በአዲስ ሻሽ ወይም በአቡጀዴ እና በሰሌን ነው፡፡ በመጀመሪያ ሬሳው በሻሽ ወይም በአቡጀዴ ይጠቀለልና ወደ ሰሌኑ ገብቶ በገመድ ይታሰራል፡፡

[96] የሞተውን ሰው ስም በመግለጽ አርፏል ለማለት ነው፡፡

ሲታሰርም ለመሃይም (የቤተክርስቲያን ትምህርት ለሌለው) ሰባት ጊዜ፣ ለካህን ደግሞ በአስራ ሁለቱ ሀዋርያት ተምሳሌትነት አስራ ሁለት ጊዜ ተጠምጥሞ ነው (ቁ.የ.መ.አ.19)፡፡ ግነዛው እንደ ሟቹ ጾታ እና ማንነት የተለያየ ነው፤ የሚገንዘው ወይም የምትገንዘውም ወንድን ወንድ፣ ሴትን ሴት፣ መለኩሲትን መለኩሲት፣ መለኩሴን መለኩሴ፣ ቄስን ቄስ ወዘተ. ነው፡፡

ስለዚህ ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የተለያየ አገናነዝ ይደረጋል፡፡ በፍትሐ ነገሥት (1995፣277) ላይ እንደሚከተለው በሰፈረው መሰረትም ይከናወናል፡፡

> ባህታውያንን እጃቸውን ከዓይናቸው ላይ ጥለው ይገንዟቸዋል፡፡ በዓይናችን ይህንን ዓለም አላየንበትም ሲሉ፣ ቄሳውስትን እጃቸውን አመሳቅለው ይገንዟቸዋል፤በቡራኬ እንደነበሩ ለማጠየቅ፣ ዲያቆናትን እጃቸውን ከአንገታቸው ላይ ጭነው ይገንዟቸዋል፣ በተልእኮ እንደ ኖሩ ለማጠየቅ፣ ሕጋውያንን እጃቸውን ከብልታቸው ላይ ጭነው ይገንዟቸዋል፣በሰጠኸን አካል የሚገባ እንጂ የማይገባ አልሰራንበትም ሲሉ ፣...

በግነዛ ወቅት የእሬሳው አፍ በክር ይታሰራል፤ የቀኝና የግራ እግሮቹ እንዲሁም የቀኝና የግራ እጆቹ አውራ ጣቶችም ባንድ ላይ ይታሰራሉ፡፡ ከዚያም ሬሳው በጀርባው ተስተካክሎ እንዲተኛ ይደረጋል፡፡ ሟቹ በህመም ምክንያት ለረጅም ጊዜ የአልጋ ቁራኛ ሆኖ(ተደይኖ) በመቆየቱ ምክንያት፣ እግሮቹ ቢተጣጠፉም እንኳ ጉልበት ተጠቅሞ እንዲዘረጋ ይደረጋል እንጂ እንደ ታጠፈ አይገነዝም (ቁ.የ.መ.አ.15)፡፡

የህጻናት አገናነዝን በሚመለከት ከሰባት ዓመት በላይ የሆናቸው ይገነዛሉ፡፡ የግንዘት መጽሐፍም ይነበብላቸዋል፡፡ ከሰባት ዓመት በታች የሆኑት ግን አይገነዙም፤ በጨርቅ ተጠቅልለውና ታቅፈው ይወሰዱና ቤተክርስቲያን ውስጥ ይቀበራሉ፡፡ ያልተጠመቀ ያልተጠመቀች (ወንድ ከአርባ ቀን ሴት ከሰማንያ ቀን በታች) ከሆኑ ግን ለቀብር ወደ ቤተክርስቲያን አይወሰዱም፤ በመኖሪያ ቤት ጓሮ ውስጥ ይቀበራሉ፡፡

በሟች ቤት ውስጥ ለቀብር ሥነ-ሥርዓቱ የሚያስፈልጉ ነገሮች ዝግጅትም ይከናወናል፡፡ ወደ ቤተክርስቲያን የሚወሰድ የግብር እህልስንዴ[97]ይዘጋጃል፡፡ ሟች ወደሚቀበርበት

[97] ለቅዳሴ ስርዓት አገልግሎት የሚውል ነው ፡፡

ቤተክርስቲያን ሰው በመላክም የቀብር ቦታ እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡ በዚህ ወቅት ሟቹ ወይም የሟቹ ቤተሰቦች ለቤተክርስቲያን የሚሰጠውን አስራት(ዓመታዊ ክፍያ) ያልከፈለ/ያልከፈሉ ከሆነም እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡ ወደ የቀብሩ ቦታ ተወስዶ ከቀብር መልስ ለቀባሪዎች የሚቀርብ ቆሎም ይቆላል፡፡ ሀዘንተኞቹ የሚቀመጡበት የዳስ ስራም ይከናወናል፡፡

አስከሬኑ ከቤት የሚወጣውም[98] በመጀመሪያ እግሩ ነው፤ ይህም የሚሆነው ያ ቤት ከዚያ በኋላ የሟች አለመሆኑን ለማመልከት ነው፡፡ አስከሬኑ ከቤት ሲወጣ ለቅሶው እጅግ ምርር ያለ ይሆናል፡፡ ይህንን ወ/ሮ ጠጄ በላይ ሲገልጹ፣ ‹‹የአንድ ሰው ሬሳ ከቤት ሲወጣ ሟቹ የኑሮ ቤቱን ትቶ ወደ ሌላ ኑሮ ሄደ፤ ኑሯችን ተለያየ በማለት ሁሉም ጭው ጭው ይላል (በጣም ያለቅሳል)፡፡›› ይላሉ (ቁ.የ.መ.አ.1)፡፡

ታሞ ለሚሞትና በድንገት ለሚሞት ሰው ለቅሶውም ሆነ ሀዘኑ የተለያየ ነው፤ ምክንያቱም ታሞ ያልነበረው በድንገት ሲሞት፣ አደጋ ነውና ያስደነግጣል፤ የሥጋ ዝምድና ያለውም ሆነ የሌለውም(የተወለደውም ያልተወለደውም) በጣም ስለሚያለቅስ ለቅሶው ይደምቃል፤ ሀዘኑም የበረታ ይሆናል፡፡

አስከሬኑ ወደ የቀብር ቦታ በሚወስድበት ወቅት የፍታት ስርዓት ይከናወንለታል፡፡ የፍታቱን መጠን የሃይማኖት አባቶች ሲገልጹ ፣‹‹ለሞተ ሰው ፍታት የሚደረገው ስምንት ጊዜ ሲሆን፣ ይህም በመጀመሪያ በመኖሪያ ቤቱና ከዚያም በጉዞ ላይ ሰባት የጉዞ ፍታት ናቸው፡፡ ሞገስም(1969፣44) ሰባቱን የጉዞ ፍታቶች አስመልክተው እንደሚከተለው አስፍረዋል፡፡

> ሰው ሲሞት ወደ መቃብሩ በሚጓዝበት ጊዜ በሰባት ምእራፍ ሰባት ጊዜ ፍትሀት ማድረግ ይገባል፡፡ ይኸውም እስራኤል የኢያሪኮን ከተማ ሰባት ጊዜ እየዞሩ በጸለዩ ጊዜ የብረት ቅጸሩ ፈራርሶ ወድቋል፡፡የዘመነ ሀዲስ ካህናትም…ለሞተው ምእምን በዚሁ ምሳሌ ሰባት ጊዜ እየጸለዩ ቅጽረ ኃጢአቱን አፍርስለት (ማረው ይቅር በለው) እያሉ ጸሎተ ፍትሐቱን ያደርሱለታል፡፡ ዘኢያ.7፤5…ሰባት ሲባል ሰባት ባህርያት ያለው ሰው ማለት ስለሆነ፣ በሰባት ባሕርዮቹ ተደፋፍሮ የፈጸመውን ኃጢኣት ይቅር ብለህ ማርልን ብሎ መጸለይ

[98] አስከሬኑ ከቤት እንደወጣም ወደ ቀብር የማይሄዱ አቅመ ደካሞችና ሕፃናት ቤቱን እንዲጠብቁ ይደረጋል፤ የሚቀመጡትም ራቅ ብለው ነው፡፡

> ነው፡፡ ሰባት ባሕርያት የተባሉትም አራት ባህርያተ ስጋ፣ ማይ፣ ነፋስ፣ መሬት፣ እሳት፣ ሦስት ባሕርይተ ነፍስ ነባቢነት፣ ለባዊነት፣ ሕያውነት ናቸው፡፡ እንዲሁም በዕብራውያን አቆጣጠር፣ ሰባት ቁጥር ፍጹም ስለሆነ፣ የሞተውን ምእምን መንግሥተ ሰማይ ለመግባት ፍጹም አድርግልን ብሎ መለመን ነው፡፡

ሰባቱ የጉዞ ፍታቶች ከላይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ፣ የተለያዩ ነገሮችን የሚያመለክቱ መሆናቸውን መጋቢ ምስጢር ገ/ህይወት የተባሉት የሃይማኖት አባት እንደሚከተለው ገልጸዋል፤ ‹‹አንደኛ ሟች ከእሁድ እስከ ቅዳሜ ባሉት ሰባት እለታት በነበረበት ሁሉ ተቸንፎ የሰራው ሓጢአት ይሰረይለታል፡፡ ሌላው ሰባት ጊዜ የጉዞ ፍታት መደረጉ የሰባቱ ሆህያት ምሳሌ ነው፡፡ ሟች በሰባቱ ሆህያት ተምሮ አውቆ፣ ባለ መጠንቀቁ፣ ይቅርታ አድርግለትም ይባላል›› (ቁ.የ.መ.አ.2)፡፡

ሌላው አባት ሊቀጠበብት ሀረገወይን አገዘ ደግሞ፣ የሰባቱን የጉዞ ፍታቶች ምንነት እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡ ‹‹ሰባት በእብራውያን አቆጣጠር ፍጹም ነው ይባላል፡፡ በእኛም ሰባቱ አጽዋማት፣ ሰባቱ የጸሎት ጊዜያት፣ ሰባቱ ሚስጢራተ-ቤተክርስቲያን ወዘተ. የሚሉ ብዙ ሰባቶች አሉ፡፡ ለሟች ሰባት ጊዜ ፍታት የሚደረግለትም ፍጹም ድሕነት ተደረጎለት፣ ያጎደለውን ነገር እግዚአብሄር ይቅር እንዲለው ነው›› (ቁ.የ.መ.አ.13)፡፡

በገጠር ከቦታው ወጣ ገባነት የተነሳ ሰባቱ ፍታቶች የሚደረጉባቸው ቋሚ ቦታዎች አሉ፡፡ ለማጠኛው የሚያገለግል ፍም እንዲኖርም ሴቶች በሰባራ ገል እሳት እያነደዱ ከአስከሬኑ ፊት ፊት ይጓዛሉ፡፡

## የለቅሶ ሂደት

አስከሬኑ የጉዞ ፍታት እየተደረገለት ወደ የሚቀበርበት ቤተክርስቲያን በሚወሰድበት ወቅት፣ በቡታ ወይም በቅበሩ ጥሪ ከተለያዩ ቦታዎች ተጠራርተው የሚመጡት ቀባሪዎችም አንዳንዶቹ እንጀራና ወጥ፣ ሌላዎቹ ደግሞ ቆሎ በአህያ ጭነው ወደ ቀብሩ ቦታ ይመጣሉ፡፡ ለሟች የቅርብ ዘመድ የሆኑት ደግሞ እንጀራና ቆሎ ያመጣሉ፡፡ እንጀራና ቆሎ ወደ የቀብር ቦታ የሚመጣበት ምክንያትም ለቀስተኛው ከሩቅ ቦታ በጧት ተነስቶ ስለሚመጣና ርቀት ወዳለው የሃዘንተኞቹ ቤት ሳይሄድ ከቤተክርስቲያን ተሰናብቶ ወደ ቤቱ ስለሚመለስ ከቀብር መልስ ምግብ ቀምሶ ወደ ቤቱ እንዲሄድ ነው፡፡ ከየቦታው ተሰባስበው የሚመጡት

ቀባሪዎች ወደ የቀብሩ ቦታ (ቤተክርስቲያን) ቀረብ ሲሉ፣ አስከሬኑ እስከሚመጣና ሌሎች ቀባሪዎችም እስከሚሰባሰቡ ድረስ ጥግ ጥግ ይዘው ወይም በዛፍ ተጠልለው ተቀምጠው ይጠብቃሉ። በዚህ ወቅትም የቅርብ ዘመዶች ከሆኑ እያለቀሱ፣ ራቅ ያሉትም ማህበራዊ ጉዳዮቻቸውን እየተወያዩ ይቆያሉ፤ በውይይቱ ወቅት የሚያስቅ ነገር ካለም ፈገግ ይላሉ፤ በጣም መሳቅ ግን አይፈቀድም፡፡ ከቀብር በፊት ከተለያየ አካባቢ የሚመጡ ሰዎች ሰላምታ መለዋወጥ ማለትም መሳሳም አይፈቀድላቸውም፡፡ ምክንያቱም መሳሳም የደስታ መግለጫ ሲሆን ያሉበት ቦታ ግን የሃዘን ነውና ሰዎች መሳሳም የለባቸውም፤ ከቀብር በኋላ ግን መሳሳም ይቻላል፡፡ የቅበሩ ጥሪ የተደረገለት ሁሉም ዘመድ መምጣቱ እንደ ተረጋገጠም ሀዘንተኞቹ ከተቀመጡበት ይነሱና፣ ከቀብር በፊት የለቅሶ ስርዓት ወደ ሚፈጸምበት ሜዳማ ቦታ(ማርገጃ ቦታ) ይሄዳሉ። አስከሬኑን በቅርብ ተከትለው የሚሄዱት ወንዶች ሲሆኑ፣ የቅርብ ዘመዶች ቀድመው ራቅ ያሉት ደግሞ እነሱን ይከተላሉ፡፡ ሴቶች ደግሞ ከወንዶቹ በኋላ ይሆናሉ፡፡

በዚህ ጊዜ ከየቦታው የመጡት ቀባሪዎች እያለቀሱ ከሀዘንተኞቹ ጋር ይቀላቀላሉ። ወንዶቹ እኛም አዝነናል ለማለትና ለሀዘንተኞቹ አክብሮት ለመለገስ ሲሉ በጋቢያቸው ፊታቸውን ፈግፈግ ያደርጋሉ። ከዚህም ሌላ የያዙትን በትር ወደ መሬት ጣል አድርገው ያነሳሉ። በቀብር ወይም በቀጠሮ ለቅሶ ጊዜ በትሩን ትከሻው ላይ አድርጎና እራሱን ተከናንቦ የሚመጣ ‹‹ይህ ሰው ለሃዘን ሳይሆን ለነገር የመጣ ነው›› ይባላል (ቁ.የ.መ.አ21)፡፡

ሀዘንተኛ ሴቶች ደግሞ ለሟች እንዳላቸው ቀረቤታ ፊታቸውን ይልጣሉ፤ ጸጉራቸውን ይነጫሉ፤ ምክንያቱም ‹‹እከሌት እናቷ ወይም አክስቷ ስትሞት እራሷን(ጸጉሯን) ሙልጭ አድርጋ ነጨች›› እየተባለ በመልካም ነገር ስለሚገለጽ ነው፡፡ አንዳንዶችም የጸጉራቸውን ጆፌ በነጭ ጨርቅ ያስራሉ፤ ጥቁር ጥለት ያለው ወይም ቆሸሽ ያለ ልብስ ይለብሳሉ፤ ዘመድ የሆኑት ጫፉን ይቋጥራሉ፤ ያልሆኑት ደግሞ የነጠላቸውን ጥለት ዘቅዝቀው ይለብሳሉ፡፡ ቀደም ሲል ሁሉም ሴት ለቀስተኞች የነጠላቸውን ጫፍ ይቋጥሩ ነበር፤ አሁን አሁን ግን የነጠላ አለባበስም የቅርብና የሩቅ ዘመድ መለያ ሆኗል፡፡ ጥቁር ሻሽ (መሐረም፣ባውንድ)ይጠመጥማሉ፡፡ በሌላ ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና እምነት ተከታይ መሆናቸውን ለማመልከት የሚያስሩት ማተብ ጥቁር ቀለም ያለው ክር ሲሆን፣ ሀዘንተኛነታቸውን ለማሳወቅ ደግሞ ነጭ ክር ያስራሉ፡፡

እስከሬኑ ወደ ቤተክርስቲያን እንደ ተቃረበ፣ የመጨረሻውና ሰባተኛው የጉዞ ፍታት ስርዓት በካህናቱ ሲቀጥል፣ ሌላው ለቀስተኛ ደግሞ በማርገጃው ቦታ ላይ ተሰባስቦ ክብ ይሰራና የለቅሶ ሥነ-ሥርዓቱን ይቀጥላል፤ በዚህ ወቅት የሟች ልጅ፣ ወንድም እህት፣ ባል፣ ሚስት ከእስከሬኑ በቅርብ ርቀት ላይ ሆነው አንዳንዶቹ ወገባቸውን በጠፍር ታስረው እየዘለሉ ያለቅሳሉ (ወለህ ማርያም[99] በተባለችው ቤተክርስቲያን በተመለከትኩት የቀብር ሥነ-ሥርዓት የሟች ባል በገመድ ታስሮ እየዘለለ ያለቅስ ነበር)፤ ቀረብ ያሉት ዘመዶች ደግሞ ቆመው ያለቅሳሉ፤ የቅርብ ዘመዶችን ተከትለው የሚመጡት ግን ራቅ ብለው ይከተላሉ፤ ፈቀቅ ብለው ቆመውም ከማልቀስ ይልቅ ሊያወሩም ይችላሉ፡፡ በለቅሶ ሥነ-ሥርዓቱ ሟቹ/ቿ ሀብታም ከሆነች ከብቶች ይነዳሉ፤ የተሸለሙ በቅሎዎችም ይሳባሉ፤ ሰንደቅ አላማ(ባንዲራ)ይውለበለባል፡፡ ጥሩንባ(ቱልቱላ)ይነፋል፡፡ ሀዘንተኞች የሟቹን/ቿን አልባሳትና ጌጣጌጥ በመያዝ ያለቅሳሉ፤ ያስለቅሳሉ፡፡ ለምሳሌ ሟቹ አርበኛ ከሆነ በአርበኝነት ወቅት ላደረገው ተጋድሎ የተሸለመው ሊሻን ካለ ይያዛል፡፡ ገበሬ ከሆነ ደግሞ ከእርሻ መሳሪያዎች መካከል ጅራፍ፣ ማረሻ፣ ይያዛል፤ መነኩሴ ከሆነ/ከሆነችም ቆብ፣ ባላና መቁጠሪያ ይወጣል፡፡ ቆንጆ[100] ከሆነች ደግሞ ጥልፍ ቀሚሶቿና በህይወት እያለች ታጌጥባቸው የነበሩት ጌጣጌጦች ማለትም ድሪ፣ መስቀል፣ አምባር ወዘተ. በእንጨት ላይ ታስረው ለማስለቀሻነት ይያዛሉ፤ ወጣት ከሆነም ጃኬቱና ቁምጣው ወይም ሱሪው(ቦላሌው)፣ እመጫት ከሆነችም አንቃልባዋ(ማዘያዋ) ለማስለቀሻነት ይወጣል፡፡

ለማስለቀሻነት የሚያዙት ነገሮች ሟች በህይወት እያለ ያከናወናቸውን ነገሮች ወይም የሟችን ሙያ የሚያመለክቱ ሲሆኑ፣ በለቅሶ ሥነ-ሥርዓቱ ወጥተው ሲታዩ ደግሞ፣ ሀዘንተኛው ያለቅሳል፤ ያዝናል፤ እንባ ያፈሳል፤ ስለዚህ እንባ ማብገ ይሆናሉ፡፡ እነዚህ የስራ መሳሪያዎች፣ አልባሳትና ጌጣጌጦች በማስለቀሻነት ለምን እንደሚያዙና የሚሰጡትን

---

[99] ይህች ቤተክርስቲያን የምትገኘው በፋሽሽት ኢጣሊያ ወረራ ወቅት ታላቅ ተጋድሎ በማድረግ አንገታቸውን ለመሰዋት የበቁት ሌቴናል ጀኔራል ሃይሉ ከበደ በተሰውበት ቦታ ነው፡፡ ይህንንም ያሳተመውን የግጥም መድበል በሳቸው የሰየመው አስራት ታደሰ እንደሚከተለው አስፍሯል፤...አባ መረብ የጀግናው ደጃች ሐይሉ ከበደ የፈረስ ስም ነው፡፡ ይህ ጀግና በዘመነ ኢጣሊያ ወረራ በከፍተኛ ጀግንነት ሀገሩን ከጠላት የተከላከለና በመጨረሻም በአሁኑ መጠሪያው በዋግ ኽምራ ብሄረሰብ አስተዳደር ልዩ ስሙ **ወለህ** (አጽንኦት የራሴ) በሚባል ቦታ በተካሄደ ጦርነት ሀምሌ 1929 በእለተ አርብ እንደ አጼ ዮሃንስ አንገቱን ተሰየፈ፡፡(አባ መረብ ሃይሌ፣ሃይሌ አባ ይባስ፣አንገቱን የሰጠው እንደ ዮሐንስም ይባልላቸዋል ) መሞቱን ያላመነው የኢጣሊያው መሪ አንገቱ ተቆርጦ እንዲመጣለት አዘዘ፡፡ የኢጣሊያ ጦርም በታዘዘው መሰረት የጀግናውን አንገት ቆርጦ ወደ ሮም እንዲሄድ አድርጓል፡፡ ግማሽ አካሉ በሰቆጣ ከተማ መድሃኒአለም ቤተክርስቲያን በሕዝብ ትብብር የተቀበረ ሲሆን፣ ደጃች ሃይሉ ከበደ በፈጸመው ወደር የሌለው ጀግንነት ህይወቱ ካለፈ በኋላ በአጼ ሃይለስላሴ የሌቴናል ጀኔራልነት ማእረግ ተሰጥቶታል፡፡ በስሙ የተሰራ ሃውልት ባይኖርም በአዲስ አበባ ከተማ ከራስ መኮንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ የሚወስደው መንገድ በስሙ የተሰየመ ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪም በትግራይ ክልል በኮረም ከተማ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት፤ በአማራ ክልል ሰቆጣ ከተማ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት በሌቴናል ጀኔራል ሃይሉ ከበደ ስም ተሰይሟል ፡፡

[100] ጎልማሳ ሴት ለማለት ነው፡፡

ጥቅም አስመልክተው ወ/ሮ ጠጄ በላይ እንደሚከተለው ገልጸዋል፤‹‹የሞተን ልጅ ማውሳት መሳሳት ቢሆንም፣ ነገ እኔም ያው ነኝ በማለት የተወለደውም ያልተወለደውም ያንን እያየ እንዲንሰፈሰፍ ያደርጋል››(ቁ.የ.መ.አ.1)፡፡

በሠርግ እና በለቅሶ የሚሳቡ (የሚያዙ) በቅሎዎች የሚያጌጡበት የሽልማት አይነት ተመሳሳይ ነው፤ የበቅሎዎቹ መጠን ግን ይለያያል፤ በሠርግ የሙሽራዋና የሙሽራው ቤት ቅርብ ከሆነ አንድ በቅሎ ብቻ ይያዛል፣ እሩቅ ከሆነና የሙሽራው ቤተሰቦች ሀብታም ከሆኑ ግን ሶስት አራት በቅሎዎች ሊይዙ ይችላሉ፡፡ በቀብርና በአንበር (በቀጠሮ ለቅሶ) ላይ ግን ከዚያ በላይ በቅሎዎች ሊሳቡ ይችላሉ፡፡ በተለይ የሟች ወገኖች ሀብታም ከሆኑ ከአስር በላይ በቅሎዎችም ሊሳቡ ይችላሉ፤ ስለዚህ የበቅሎዎቹ መጠን ከፍ ማለት ሟች የሀብታም ወገን መሆኑን ማሳያ እና ለለቅሶው ማድመቂያም ሆኖ ያገለግላል (ቁ.የ.መ.አ.11)፡፡ እንዲሁም በቀብር፣ በአንበርና በሠርግም ሰንደቅ አላማ ይውለበለባል፤ መጠኑ ግን ይለያያል፡፡ በሠርግ በዳሱ ላይ አንድ ሰንደቅአላማ ብቻ ሲውለበለብ በቀብርና በአንበር ግን መጠኑ ከዚያ በላይ ነው፤ ከየጎጡ የሚመጣ ቀባሪ አንድም ሁለትም ሰንደቅዓላማ እያውለበለበ ሊመጣ ይችላል፡፡ በቀብር፣ በአንበርና በሠርግ ጥሩንባ(ቱልቱላ) ይነፋል፡፡ በሁለቱ የሚሰጠው አገልግሎት ግን የተለያየ ነው፤ ይኸውም በሠርግ ሚዜዎችን ከየቤታቸው ለመጥራትና ዘፈኑን ለማድመቅና ለደስታ ሲያገለግል፣ መጠኑም አንድ ነው፡፡ በለቅሶ ግን መጠኑ ብዙ ሲሆን አገልግሎቱም ለቅሶውን ለማድመቅና ለሀዘን ነው፡፡



**በማርገጃ ቦታ በአስተባባሪዎች አማካይነት ልቅሶ ሲካሄድ (ፎቶ በብዙ አየሁ ማሞ)**

ለቅሶው በከፍተኛ ሁኔታ በመጨረሻ የሚበረታው በቤተክርስቲያን አጠገብ በሚገኝ (የማርገጃ) ቦታ ላይ ነው፡፡ በዚህ ቦታ ላይ ሃዘንተኛውም ሆነ ቀባሪው ተሰባስቦ ክብ በመስራት ለቅሶው ይቀጥላል፡፡ በዚህ ጊዜ መሃል ላይ በመሆን የለቅሶ ስርዓቱን የሚያስቀጥሉ አስተባባሪ ወንዶችም ይኖራሉ፡፡ ከፎቶው ከሌላው ለቀስተኛ ተነጥለው የምናያቸው ሁለት ሰዎች አስተባባሪዎች ናቸው፡፡

በዚህ ቦታ ላይ አስለቃሽም ይኖራል፡፡ በአንድ የቀብር ወይም የአጎበር ሥነ-ሥርዓት ላይ አስለቃሽ መኖሩ የተለያዩ ጥቅሞች አሉት፡፡ የመጀመሪያው አስለቃሹ ሲያስለቅስ ሌላው በጸጥታ ማዳመጥ ስላለበት ሀዘንተኞቹ እረፍት እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡ ሌላው አስለቃሹ ስለ ሟቹ ማንነት በመግለጽ የሟቹን ማንነት የማያውቁት እንዲያውቁት ይሆናል፡፡ ሆድ ውስጥ የሚብሰለሰል ሀዘን ገንፍሎ እንዲወጣም ያደርጋል፤ በዚህ ምክንያት አስለቃሹ ማስለቀሱን ሲያቆምና ሌላው ማልቀስ ሲጀምር ለቅሶው የደመቀ ይሆናል፡፡ ‹‹የአስለቃሽ መኖር እነ እከሌ ቢያበሉ ቢያጠጡ ተለቀሰላቸው›› ለማለት ለዝናም ያገለግላል፡፡ አስለቃሽ ገንዘብ ሊሰጠውና ላይሰጠው ይችላል፡፡ መሸሃ ላይ በነበረው አጎበር እንደተመለከትኩትም

ለአስለቃሹ ገንዘብ አልተሰጠውም፤ ምክንያቱም የሟች ዘመድ ስለሆነ ነው፡፡ ይሁን እንጂ (እየተገዙ) ገንዘብ እየተከፈላቸው የሚሄዱ መኖራቸውም ተገልጾልኛል (ቡ.ተ.ው2)፡፡

በአስለቃሹ አማካይነት ቃል-ግጥሞች ይደረደራሉ፡፡ቃል-ግጥሞቹም እንደ ሟቹ ማንነትና ሙያ የተለያዩ ናቸው፡፡ ከሚደረደሩ ቃል ግጥሞች መካከል ለአብነት ያህል የመረጃ አቀባዮቹ ከጠቀሱልኝና ምልከታ ሳደርግ ካዳመጥኳቸው መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ[101]፡፡

ሀ/ እናት ስትሞት የሚገጠም

እባክሽ እናቴ ጥሬ ቆልተሽ በገል፣
ታውቂዋለሽና የሰውን ቤት ነገር።
አወይ ይህ መጥረቢያ ስለቱ መብዛቱ፣
የወላጅን አንጀት የቆረጠበቱ።
እንዴት እናት ትሙት ትሂድ አጎንብሳ፣
እንኳን ቁማ ሂዳ ታማ ብትተኛ፣
ለልጇ ናትና ወስከንቢያ መከደኛ፡፡
እንዴት እናት ትሙት የቤት ጎረቤት፣
ከእርሻ ውለህ መጥተህ ፍትፍትን መብላት፣
ዝልል መጠጣት፣
ተበድረህ በልተህ የለኝም ማለት፡፡

ለ/ አባት (ባል) ሲሞት የሚገጠም

እንዴት ወንድ ይሙት ያ ሞኝ ተላላ፣
አበጥሮ ግሮ ካልሰጡት አይበላ፡፡
ቆርቆሮ ቢመታ ቢሰራ ደብር፣
ባለቤት ከሌለ የለው ቁም ነገር።

[101] ያሬድ ተሾመ ባሰባሰባቸው የዋግ የሃዘን ስርዓት ግጥሞች ስብስብ ውስጥም ይገኛሉ፤ የግጥሞቹ ጭብጥ ወደፊት በሥነ-ሥርዓቱ ፋይዳ የሚታይ ይሆናል፡፡

ግልገል በቅሎ ገዛሁ በጣሙን አጉድየ፣

ደግ አባት በቅሎ  አይገኝም ብየ።

እጄን አትሰሩት እኔ እዋሰዋለሁ፣

በዚያ በክፉ ቀን በልቼበታለሁ።

የዋጉ ባላባት የትግሬው እዳይት፣

እንዴት አድርጎት ሄደ ያን ሁላ[102]እንደበት።

ጮማን እንደ  ጎመን የበላንበቱ፣

ጠጅን እንደ ውሃ የጠጣንበቱ፣

እገሌ ፈረሰ በጀ አለ ለሞቱ።

እንኳን በአርባ ጾም በማይበላው፣

እንኳን አርብና እሮብ  በማይበላው፣

እሁድ ጦሙን ያድራል እቴት[103]የሌለው፡፡

ሐ/ ልጅ ሲሞት የሚገጠም

አትቅበሩኝ አለ ካንገቴ በላይ፣

ናፋቂ ነኝና እናቴን እንዳይ፡፡

የናትም ሞት ቢሆን የየቅል የየቅል[104]፣

የወንድም ሞት ቢሆን የየቅል የየቅል፣

የልጅ ሞት ክፉ ነው ካንጀት የሚበቅል።

እቴዋ እገሊት ዘጠኝ ወር አርግዘሽ፣

አምጠሽ ወልደሽ፣

ልጅሽ ተመልሶ ገባ ካንጀትሽ፡፡

ልጄ ልጄ ማለት ክፉ አማርኛ፣

---

102 ሁሉ

103 ባል/ሚስት፣ በዚህ አገባብ ሚስት ለማለት ነው፡፡

104 የተለያየ

እንቅልፍ አያስወስድ በጎን አያስተኛ።

አላያችሁም ወይ የልጅን ጣእም፣

በለበቅ ቢመቱት፣

በጠፍር ቢመቱት፣

ከእግር መጠምጠም፡፡

**መ/ እህት ስትሞት የሚገጠም**

የእህት ሞት ክፉ ነው ለወንድም ይብሳል፣

ለእህትም ይብሳል፣

ባል ሚስት ያገባል፣ ልጅ ገንዘብ ይወርሳል፡፡

**ሠ/ እርሶ አደር ሲሞት የሚገጠም**

አራሽ አደፋራሽ በሰፊ ድግር፣

እርሶ ጠገብ ጌታ የንጉስ ገባር፣

እንኳንስ በጠላ በእርጎ የሚያሰክር፣

ውሸቴ ከሆነ መላው[105] ይመስክር፡፡

የአቶ እከሌ በሮች አለቀሱ እንባ አወጡ እንደ ሰው፣

ያረባው ገበሬ እያንከላበሰው[106]፡፡

በሬው ሞልቶ ነበር በረቱን አልብሶ፣

ጸጋው ሞልቶ ነበር ማጀቱን አርሶ፣

ሁሉም አለቀሰ ውሉ ባንተ ፈርሶ፡፡

**ረ/ ቆንጆ ሴት ስትሞት የሚገጠም**

ያልታደለው መስቀል ካልታደለች ደርሶ፣

ከተገዛው ገበያ ሊሸጥ ነው መልሶ፡፡

የአይደ ሽፋሽፍትን ሸፍኑት በሻሽ፣

---

105 ሁሉም

106 ወዲህ ወዲያ እያደረገው

አፈር እንዳይገባ እንዳትበላሽ፡፡

እክሊትዋዬ የወስከንቢያ አለላ፣

መልምሎ ወሰዳት አፈሩ ሊበላ፡፡

**ሰ/ ካህን ሲሞት የሚገጠም**

የእክሊ መስቀል አለቀሰ እንባ አውጥቶ እንደ ሰው፣

የእክሊ ዳዊት አለቀሰ እንባ አውጥቶ እንደ ሰው፣

የማይረባው ካህን እያንከላበሰው፡፡ (ቁ.የ.መ.አ.17፣22፣ እና 24)

ለቀስተኛው በተገለጸው መንገድ ከተላቀስ እና ሰባተኛው የጉዞ ፍታት ከተጠናቀቀ በኋላ፣ አስከሬኑን ለቀብር ያንቀሳቅሱታል፡፡ ወደ የቀብር ቦታ ከመወሰዱ አስቀድሞም ወደ ቤተክርስቲያን ይወሰድና ቤተክርስቲያኑን ለማሰናበት ሲባል ያሰግዱታል፤ እንዲሰግድ የሚደረገውም እግሩ ወደ ምስራቅ ራሱ ወደ ምእራብ ተደርጎ ነው፡፡ በሁኔታዎች አለመመቻቸት ሰዎች እንደ ተመቻቸው ቢተኙም፣ በህይወትም ሲተኛ እንደዚያ እንዲሆን የሚፈቀድ መሆኑን ነው የመረጃ አቀባዩ የገለጹልኝ (ቁ.የ.መ.አ.19)፡፡

## 6.3 የቀብር ሥነ-ሥርዓት

አስከሬኑ ወደ ተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ በሚገባበት ወቅት፣ ልክ የሟች ነፍስ ሲወጣ እና አስከሬኑ ከቤት ሲወጣ እንደ ነበረው አይነት ሁሉ ለቅሶው በጣም ከፍ ያለ ይሆናል፡፡ ምክንያቱ ምን እንደ ሆነ አቶ ውበት ጌታሁን እንዲህ ገልጸዋል፤ ‹‹ሬሳው ግባተ መሬት ሲገባ ለቅሶው የሚደምቀው ህብረተሰቡ ነገም ለራሱ ስለሆነ እኛም ወደ እሱ ነው የምንሄደው፣ ኑሯችን ተለያየ በማለት ነው›› (ቁ.ያ.መ.አ.4)፡፡

በሞት ለቅሶ የሚበረታባቸው ጊዜያት ሶስት ናቸው፤ የሟች ነፍስ ሲወጣ ሬሳው ከቤት ሲወጣና ወደ መቃብር ሲወርድ፡፡ ይህም ማህበረሰቡ እንደ ባህል የያዘው ብቻ ሳይሆን ሃይማኖታዊም ነው፡፡ ይህም በሃይማኖት አባቶች እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡

> ቤተክርስቲያን ለቅሶ የምትፈቅደው ሶስት ጊዜ ነው፡፡ አንደኛ ነፍሱ ከስጋው ስትለይ፣ ሁለተኛ አስከሬኑ ከቤቱ ሲወጣ፣ ቆሞ ሲወጣበት ሲገባበት ከነበረው ቤቱ ተንጋሎ በሰው ትከሻ ሲወጣ፣ ይህም ከኖረበት ቤት፣ ከሞቀ ከደመቀ ሀብቱ ሲለይ፣ እርሱ ተለየ ለማለት

> ብቻ ሳይሆን ሰዎች ‹‹እኛም እንዲሁ እንለያለን ማለት ነው፡፡››እያሉ ሞታቸውን እያሰቡ የሚያለቅሱበት እና ሶስተኛ ግብአተ-መሬት ሲገባ ናቸው፡፡ ወደ መሬት ወደ ጥንተ ርስቱ ሲገባ እራስን እያስታወሱ እሱም ተለየን ደህና ሁን ርስቱን ያውርስህ ለማለት ነው፡፡ በዚህ ጊዜም ለቀስተኞቹ እኛም ያው ነን በማለት ለቀሷቸው የመረረ ይሆናል፡፡ ስለዚህ እንዲለቀስ የሚፈቀደው ሶስት ጊዜ ብቻ ነው፤ ይህም እንባ ማፍሰስ ነው(ቂ.የ.መ.አ.2 እና13 )፡፡

በቀብር ጊዜ ለቅሶውን የሚያደምቁት የሚች የቅርብ ዘመዶች ብቻ አይደሉም፤ የሩቅ ዘመድ ሆነው ነገር ግን ቀደም ሲል ዘመድ የሞተባቸውም ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች በእለቱ እንደ አዲስ የሚያለቅሱት በወቅቱ የሞተውን ሰው ለቅሶ ሲመለከቱ፣ የሞተውን/ተችውን አባታቸውን፣ ወንድማቸውን፣ እናታቸውን፣ እህታቸውን፣ ወይም ልጃቸውን ስለሚያስታውሱ ነው፡፡ ስለዚህ የሞቱባቸውን ሰዎች ስም እየጠቀሱ በሚያለቅሱበት ወቅት በብዛት እንባ ይመጣቸዋል፡፡

በሌላ ሰው ቀብር ወቅት ቀደም ሲል የሞተ ዘመድን እያነሱ ማልቀስ በሴቶች የጎላ ቢሆንም፣ በእነሱ ብቻ የተወሰነ ነው ማለት አይቻልም፤ በወንድም ቢሆን የማዘን ስሜት ካለው ምን ጊዜም ሚችን ያስታውሳል፤ በለቅሶ ወቅት የውስጥ ስሜቱ ይቀሰቅስና ገንፍሎ ሲወጣ ያለቅሳል፡፡ ይሁን እንጂ ቀደም ሲል የሞተን ሰው እንደ አዲስ እያነሱ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው የሚያለቅሱት ከወንዶች ይልቅ ሴቶች ናቸው፡፡ በተለይ ሚች ወገኖቻቸው ወደ ተቀበሩበት ቤተክርስቲያን ከሄዱ መቃብራቸውን አይተው፣ እነሱን እያስታወሱ የሚያለቅሱበት የጊዜ እርዝማኔ ከፍ ይላል፤ በዚህ ምክንያትም ለቅሷቸውን እንዲያቆሙ እንደ አዲስ ሀዘንተኛ ይገለገላሉ፡፡

ለመሃኖችና ሳያገቡ ለሚሞቱ ደግሞ የለቅሶው ሁኔታ መረር ያለ ነው፡፡ በተለይ መሃን ሴት ስትሞት በቤተሰቦቿ፣ ‹‹ቀሪ የለሽ እወይ›› እየተባለች ይለቀስላታል፡፡ በዚህ ጊዜ ሌሎች መካን ሴቶችም የወደፊቱ የራሳቸው ሁኔታ እያሳሰባቸው ወይም ‹‹ነገም በእኔ ያው ነው፡፡›› ብለው ለቅሶውን ያደምቁታል፡፡

የቀብር ቆይታው እንደ ሚቹ ማንነት ይለያያል፤ ለመሀይም አጠር ያለ ከአራት ሰዓት ያልበለጠ ሲሆን፣ ለካህን ግን ቆይታው እስከ ዘጠኝ ስዓት ረዘም ይላል፡፡ ይህም ካህኑ በህይወት ዘመኑ ለቤተክርስቲያን ለሰጠው አገልግሎት የሚከፈል ዋጋ ነው፡፡

አባ በንኑ የተባሉት አባት የካህንን የቀብር አፈጻጸም መለያየት ሲገልጹ እንዲህ ይላሉ፤

> በግብዓተ-መሬት ወቅት አስከሬኑ ወደ ጉድጓድ ከገባ በኋላ ለካህን አስራ ሁለት መስቀል በመቃብሩ ዙሪያ ተተክሎና አስራ ሁለት ጧፍ በርቶ፣ (ለመሃይም ግን መስቀልም አይተከልም፤ ጧፍም አይበራም፡፡) ቄሱ አህዱ አብ ቅዱስ፣ አህዱ ወልድ ቅዱስ አህዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ሲል፣ ህዝብም ተቀብሎ፣ ካህኑ ይባርክና መቃብሩ ይዘጋል፡፡ የካህኑን አስከሬን የሚሸከሙትም ግብዓተ-መሬት የሚያስገቡትም ካህናት ሲሆኑ አፈሩንና ድንጋዩን ግን ከተገኙ ካህናት ካልሆነ መሃይምም ሊጭን ይችላል (ቁ.የ መ.አ.19)፡፡

የመቃብር ቦታ ምርጫም በሟች ቤተሰቦች አቅም ይወስናል፤ የመቃብር ቤት፣ ወይም መቃብሩን በስሚንቶ የሚሰሩ ከሆነ የቦታ ምርጫ ይደረጋል፤ ካልሆነ ግን በተገኘው ቦታ እንዲቀበር ይደረጋል፡፡ መቃብር የሚቆፈረውም በወርድና በቁመት ነው፡፡ ወርዱ በግምት ሲሆን ቁመቱ ግን የሬሳው ቁመት በበትር ተለክቶ ነው (ቁ.የ.መ.አ.11)፡፡ ከቀብር በኋላም አንዱን መቃብር ከሌላው ለመለየት እንዲቻል፣ የቁልቋል ተክል ዝንጣፊ፣ የቁንዶ በርበሬ ወይም የቅንጭብ ዝንጣፊ ከመቃብሩ ላይ ይተከላል፡፡ በቆላ ደግሞ ዝንጣፊውን ምስጥ ስለሚበላው ሾጣጣ ድንጋይ ይደረግበታል፡፡ አንዳንድ ሀብታሞች ግን መደቡን በሲሚንቶ ያሰሩታል፡፡ አቅም ያላቸውም የመቃብር ቤት[107] ያሰራሉ፡፡ ለቀብር ወደ ቤተክርስቲያን የማይሄዱም አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል አቅመ-ደካማዎች፣ መውለጃዋ የተቃረበ ነፍሰ-ጡር ሴትና ልጆች ናቸው፡፡ልጆችን በሚመለከት እንደ ሁኔታው ይወሰናል፡፡ አብዛኛዎቹ ወደ ቀብር ቦታ ባይሄዱም፣ አባታቸው ወይም እናታቸው ከሞቱባቸው ግን ሃዘናቸው እንዲወጣላቸውና ተስፋቸውን እንዲቆርጡ በማለት ወደ የቀብር ቦታ ተወስደው መቃብሩን እንዲያዩ ይደረጋል፡፡

## 6.4 ድህረ-ቀብር ክዋኔዎች

ከቀብር በኋላ የሚከናወኑ በርካታ ክዋኔዎች አሉ፤ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 6.4.1 ስንብት

የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ ከተፈጸመ በኋላ፣ በንስሃ አባት(በነፍስ አባት) (ባጋጣሚ እሳቸው ባይኖሩም በሌላ ካህን) አማካይነት የቀብር ስርዓቱ መጠናቀቁን የሚያሳውቅ የጸሎት

---

[107] ይህ ቤት ለቆሎ ተማሪዎች፣ ለመነኩሳትና እና ለነዳያን መኖሪያነት ስለሚያገለግል የሟቹ ነፍስ እንዲማር ያደርጋል የሚል እምነት ከመኖሩም በላይ ወደ ፊት ለሚሞቱ የቤተሰብ አባላት ለመቀበሪያነት እንዲያገለግልም ለቦታ መያዣነት ይረዳል፡፡

ስርዓት ይከናወናል፡፡ በዚህ ጊዜ ሁሉም (ሀዘንተኛውም ጭምር) ጸጥ ብሎ ያዳምጣል፡፡ ከዚያም (አጎበር) የቀጠሮ ለቅሶ ቀንና ቦታ ይገለጻል። ለቀስተኞቹ ከመበታተናቸው በፊትም፣ ከሟች ቤት በአህያ ተጭኖ በመጣው ቆሎ፣ እንጀራ፣ እልበትና ወጥ እንዲሁም ቀባሪዎች ባመጡት እንጀራና ቆሎ ይስተናገዳሉ፡፡ ሀዘንተኞቹም እንዲመገቡ ይደረጋል፤ ለመብላት ቢያንገራግሩም እንኳ ‹‹እየተበላ ነው የሚለቀሰው፣ ካልተበላ እንባ አይወጣም፤ አይፈስም›› እየተባሉ ተገልግለው እንዲመገቡ ይደረጋል፡፡ በቀብር ወቅት ወደ ቀብር ቦታ የሚመጣውና ለቀስተኞቹ የሚመገቡትም ንፍሮ ሳይሆን ቆሎ ነው፡፡

በመቀጠል የስንብት ሥነ-ሥርዓት ይካሄዳል፡፡ስንብት የሚካሄደውም ቀብር ከተከናወነበት ቤተክርስቲያን ወጣ ተብሎ በሚገኝ ሜዳማ ቦታ ላይ ወይም በማርገጃው ቦታ ላይ ነው፡፡ ወንድ ሀዘንተኞች ለብቻ ሴት ሀዘንተኞች ደግሞ ለብቻ ይቀመጣሉ፡፡ እንዲህ ተለያይተው መቀመጣቸውም ወንዶቹ ወንድ ሀዘንተኞችን፣ ሴቶቹ ደግሞ ሴት ሀዘንተኞችን እንዲያስተዛዝኑና እንዲሰናበቱ ነው፡፡ በዚህ ወቅት የማስተዛዘኛና የማጽናኛ ቃላትም ይሰነዘራሉ፤ በአንድ ልጃቸው በሞተባቸው የቀብር ሥነ-ሥርዓት ስንብት ወቅት እናትን የሚሰናበቱ ሴቶች ከገለጹት ውስጥ ‹‹ተይ ኋላ ታለቅሻለሽ፣ አሽክሞሽ የለ፤ ተቀዳድሞ መሄድ ያለ ነው፤ የሞት አመጣጡ አይታወቅም፤ አንቺ እያለሽ እሱ፣ ላንቺ ነው የመጣው፤ ወዴት ትደርሻለሽ፤ እኛ ወደ እሱ እንሄዳለን እንጂ እሱ አይመለስም ‹‹መግቢያ መውጫሽን ታጫለሽ[108]፣ ተይው፣ ጤና የለሽ ወጥተሽ ብትገቢ ይሻላል፤ የሰጠሽን መቻል ነው፤ የት ይድረሳል፤ ወትም ትሂጂ፤ የማይገፋውን ተይው፤ ቻይው አታልቅሺ፤ ጥናቱን ይስጥሽ፤ ማርያም ማርያም እያልሽ[109]ያለሽ ሰው፣ ተላልከሽ(እልህ ውስጥ ገብተሽ) ተይው፤›› የሚሉት ይገኙበታል፡፡

የሚሰናበተው ሰው ብዙ ከሆነም በተናጠል ሳይሆን በጎጥ በጎጥ በመሆን በአንድ ትልቅ ሰው መሪነት ብቻ በአንድ ላይ ሆነው ሀዘንተኞቹን ይሰናበታሉ፡፡ በስንብት ወቅት ከሚነገሩ ማስተዛዘኛዎች መካከል፣ ‹‹እግዚአብሄር ያጥናህ፣ ተው ይበቃሃል፣ያስችልህ፣ የሞት ጋር መታገል ትርጉም የለውም፤ ይበቃል፤ ተለቅሷል፡፡›› የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

---

108 አይንሽን ያምሻል ለማለት ነው፡፡
109 አይንሽ ለማየት አስቼግሮሽ በቋፍ ላይ መሆንሽን እያወቅሽ



ስንብት በከፊል (ፎቶ በብዙአየሁ ማሞ)

ስንብት ማድረግ ሃዘንተኞቹን ከማስተዛዘኑ በተጨማሪ በቀብሩ ላይ የተገኘውንና ያልተገኘውን ወገን ለመለየትም ያገለግላል፤ ስለዚህም ወደ ቀብሩ መምጣት ሲገባው ያልመጣውን ወገንም፣ በአጎበሩ ያልተገኘው ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት አጋጥሞት መሆኑን በመልእክተኛ በኩል ለሀዘንተኞቹ ይገለጻል፡፡

ጽጽቃ እና መሸሃ ላይ እንደተመለከትኩት ደግሞ ስንብት የሚከናወነው ከማስተዛዘኛ ንግግር በተጨማሪ የሀዘንተኛዋን/ውን ትከሻም ነካ በማድረግም ነው፡፡

ከዚያም አብዛኛው ቀባሪ ወደ መጣበት ሲመለስ፣ የቅርብ ዘመድና ጎረቤት የሆኑት ግን የሀዘንና የማስተዛዘን ስርዓቱን ለመቀጠል ወደ ሟቹ ቤት ያመራሉ፡፡ ወደ ቤት እንደ ተመለሱም እሬሳ ወደ ወጣበት ቤት በቀጥታ አይገቡም፤ በመጀመሪያ ከአንድ በላይ በሆኑ ሴቶች አማካይነት ቤቱ እንዲጸዳ ይደረጋል፡፡ የሚያጸዱትም፣ በቅጠል፣ በውሃ እና በእሳት ነው፤ ሶስቱንም ይዘው ወደ ቤት በመግባት፣ በመጀመሪያ ውሃ ይረጫሉ፤ በመቀጠልም እሳት በማንደድ በቅጠል ይጠርጋሉ፡፡

### 6.4 2 ማስተዛዘን (መደበስ)

ቀደም ሲል እንደ ተጠቀሰው በዋግ ኸምራ እንደ ሌላው አካባቢ ለቀብርም ሆነ ለማስተዛዘን አገልግሎት የሚውል እድር የለም፡፡ ስለዚህ ሀዘንተኞች የሚስተዛዘኑት በሌላ አካል ትእዛዝና ተራ በተራ ሳይሆን በግለሰቦች በጎ ፈቃደኝነት ነው፡፡ ሀዘንተኞች በቶሎ ተነስተው ወደ ስራቸው ስለሚሄዱ ለማስተዛዘን ብለው ለብዙ ቀናት ባይቀመጡም፣ ለሰባት ቀናት ያህል ግን ማስተዛዘኛ ይወስድላቸዋል(ይደበሳሉ)፡፡ ለማስተዛዘኛነት የሚወሰደው ነገር አይነትና መጠን ደግሞ፣ አስተዛዛኙ(ደባሹ) ለሀዘንተኞቹ ባለው የዝምድናና የጉርብትና ሁኔታ የሚወሰን ነው፡፡ በአብዛኛው የሚወሰደው እንጀራ፣ ጠላና ቡና ነው፡፡ ጎረቤቶችና የቅርብ ዘመዶች ደግሞ እስከ ሰባት ቀን ድረስ ወደ ቤታቸው ሳይሄዱ ሀዘንተኞቹ ጋራ ያድራሉ፡፡ አስተዛዛኞች ለሀዘንተኛው የጉልበት እገዛም ያደርጉለታል፤ይኸውም ወቅቱ የእርሻ፣ የአረም ወይም የአጨዳ ከሆነ፣ ጎረቤቶችና የቅርብ ዘመዶች፣ የሀዘንተኛውን እርሻ ያርሱለታል፤ ያርሙለታል፤ያጭዱለታል (ቁ.ያ.መ.አ.14 እና15)፡፡

ሃዘንተኛን ማስተዛዘንም ሃይማኖታዊ መነሻ ያለውና ረጂም እድሜ ያስቆጠረ መሆኑን የሃይማኖት አባቶች ገልጸዋል፡፡ ይህም ከመጀመሪያዎቹ ሰዎች ከአዳምና ከሄዋን ጋር የተያያዘ ነው ይላሉ፡፡ አጀማመሩን አስመልክተውም ሊቀጠበብት ሃረገ ወይን አገዘ እንዲህ በዝርዝር ይገልጹታል፡፡

> ማስተዛዘን የተጀመረው በአዳምና በሔዋን ነው፤ አዳምና ሔዋን አቤልና ቃየል የሚባሉ ሁለት ወንዶች ልጆች ነበሯቸው፡፡ ቃየል ማሰብና ማገናዘብ አቅቶት በምቀኝነት ተነሳስቶ፣ ወንድሙን አቤልን ገደለው፡፡ ከዚያ በፊት ሞት አይታወቅም ነበር፡፡ ከሁለቱ ልጆቻቸው መካከል አንደኛው ገድሎ ጠፋ፤ሌላው ሞተ፤ አዳምና ሔዋን ብቻቸውን ቀሩና በጣም አዘኑ፤ እንባ እንዴት ይውጣቸው፣ማልቀስ ማዘን አይታወቅም፤ ልጆቻቸውን በማጣታቸው ግን ውስጣቸው በጣም አዝኗል፡፡ አዳም እንባው ወደ ውስጥ እየገባ ሰውነቱ ተነፋፋ፤ በዚህ ጊዜ መላእክት ክንፋቸውን ዘርግተው እያማቱ መጥተው ሲያጫውቱት፣ ሲያስለቅሱት፣ እንባው ቦሸሸ ብሎ ሲወርድ፣ ሲወጣለት ጤነኛ ሆነ፤ ሀዘኑን አወጡለት(አጽንኦት የራሴ) ( ቁ.የ.መ.አ.13)፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ሰዎች ወደ ሀዘንተኞች ቤት ለማስተዛዘን መሄዳቸውም፣ ሃይማኖታዊ መነሻ እንዳለው የመረጃ አቀባዮቹ ከመጽሃፍ ቅዱስ ጋር በማያያዝ እንዲህ ጠቅሰዋል፤ አልአዛር በሞተ በአራተኛው ቀን እህቶቹ ማርያምና ማርታ ምርር ብለው ሲያለቅሱ ጌታ

እየሱስ ሲያይ፣ አልአዛርን ሊያስነሳው ቢሆንም ጌታችን ምርር ብሎ አለቀሰ፡፡ እንባውን አፈሰሰ፤ አላቀሳቸው፡፡ አያይዘውም የማላቀስን ወይም የማስተዛዘንን ፋይዳ እንዲህ ያብራሩታል፤ ማላቀስ ማለት ማረጋጋት፣ ማስረሳት ሀዘኑን ማስቀነስ፣ ሰዎች ተስፋ ትንሳኤን እንዲያስቡ፣ እኛም ነገ እንሞታለን፤ ከመቃብርም እንነሳለን፤ ብለው እንዲያስቡ ማድረግ ነው (ቂ.የ.መ.አ.2)፡፡

### 6.4.3 አጎበር (በኸምጣኛ አግበር)

አንድ ሰው ሲሞት ሩቅ ቦታ የሚገኝ ዘመድ እንዲቀበር የቅበሩ ጥሪ የማይደረግበት ወቅት አለ፤ ይህም ክረምት ሆኖ ወንዝ ሲሞላና ለመሻገር ሲያስቸግር፣ ሟች የሞተው በድንገት ሆኖ ቀባሪ ወገንን ከያለበት ለመጥራት አመቺ ሳይሆን ሲቀር ነው፡፡ ስለዚህ ወዳጅ ዘመድ ተሰባስቦ እንዲያለቅስ የሚያገለግል(አጎበር)የቀጠሮ ለቅሶ ይደረጋል፡፡ አጎበር ማለት በተለያየ ምክንያት ቀብር ያልተገኙ ሰዎች በአንድ ቦታ ላይ ተሰባስበው እንደገና የለቅሶ ስርዓት የሚከናወንበት የቀጠሮ ለቅሶ ነው፡፡ ወ/ሮ አዳኑ አበራ ብዙ ሰው ለቀበረው አጎበር የማይደረግበትን ምክንያት እንዲህ በማለት ይገልጻሉ፤

> የድንገት ሞት ከሆነና ሬሳው የማያድር ሆኖ የቅበሩ ጥሪ(ቡታ) ለወገን ሳይነገር ከተቀበረ፣ አጎበር ይደረጋል፡፡ብዙ ሰው ተገኝቶ ለተቀበረ ግን አጎበር በዝባኙ ስለሆነ አይደረግም፣ ምክንያቱም በቀብር ወቅት ቆሎ ያመጣው ሰው፣ በአጎበር በድጋሚ እንጀራ ስለሚያመጣና ለአጎበሩ ታዳሚዎች ማስተናገጃ የሚሆነው፣ እንጀራና ወጥ በሀዘንተኞቹም ስለሚዘጋጅ ጎጂ በመሆኑ ቀርቷል (ቂ.ያ.መ.አ.14)፡፡

የአጎበርን ምንነትና የሚደረግለትን ሟች በሚመለከት አቶ በሪሁን ጸጋይ የተባሉት የመረጃ አቀባየ እንዲህ ይገልጻሉ፤ ‹‹አጎበር ማለት መገናኛ ነው፣ አንድ ሰው ሞቶ ከሩቅ ያሉ ሰዎች ለቀብር ስለማይደርሱ እየተንጠባጠበ የሚመጣ የለቅሶው ደራሽ የሟች ቤተሰቦችን፣ ተደራሾችንም እንዳናስቸግር፣ አንድ ላይ ሆነን ተሰባስበን የምንሸኝበት አባቶች ያቆዩልን የመገናኛ ባህል ነው፡፡ አጎበር የሚደረገውም የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ እዚሁ በትውልድ ቦታው ሳይሆን በሌላ አገር[110]ለተከናወነ ነው፡፡›› (ቂ.ያ.መ.አ.12)፡፡

[110] ከትውልድ መንደሩ ውጭ ለማለት ነው፡፡ ለምሳሌ ወልድያ፣ ደሴ፣ አዲስ አበባ ወዘተ. ከተቀበረ ሌላ ሀገር ይባላል፡፡

ሌሎቹ የመረጃ አቀባዮቼ ደግሞ አንበር የሚሆነው ሌላ አገር ለተቀበረ ብቻ አለመሆኑን ይገልጻሉ «የቅበሩ ጥሪው(ቡታው) በበዓል ቀን ሆኖ ብዙ ሰው በተገኘበት ሟች በደንብ ከተቀበረ አንበር አይደረግም፡፡ ቀብሩ በስራ ቀን ሆኖ ሟች ባጣዳፊ ከተቀበረ (ግና) ግን አንበር ይደረጋል (ቡ.ተ.ው.3 እና4)፡፡

ምልከታና ቀረጻ ያደረኩባቸው አንበሮችም የቀብር ሥነ-ሥርዓታቸው በሌላ አገር ለተከናወነ ሟቾች ብቻ ሳይሆን በትውልድ ቦታቸው ለተከናወነም ጭምር ነው፡፡ ከሶስቱ አንበሮች መካከል ሁለቱ በትውልድ መንደራቸው ለተቀበሩ የተደረጉ የቀጠሮ ለቅሶዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ አንበር የሚደረገው ሌላ አገር ለተቀበረ ብቻ ሳይሆን በአካባቢው ለተቀበረ ነገር ግን በተለያየ ምክንያት ብዙ ሰው በቀብሩ ላልተገኘለት ጭምር ነው፡፡ የቀበሩትም ቢሆን በአንበሩ መጥተው ሀዘናቸውን ይገልጻሉ፤ ያስተዛዝናሉ እንጂ ቀብረናል ብለው አይቀሩም።

የስሃላ ወረዳ የቀጠሮ ለቅሶ ማከናወኛ ቦታ ከሌላዎቹ ወረዳዎች የተለየ ነው፡፡ ምክንያቱም በሌላዎቹ ወረዳዎች ለቅሶው የሚካሄደው ሟች በተቀበረበት ወይም የሟች የቅርብ ዘመድ በሚገኝበት በአንድ ቦታ ብቻ ነው፡፡ በስሃላ ግን ለቅሶው የሚደረገው ሟች በተቀበረበት ወይም የቅርብ ዘመድ ባለበት ቦታ ብቻ አይደለም፡፡ ወገን በብዛት ባለበት በተለያየ ቦታ ሁሉ ይደረጋል፤ በወረዳው ዋና ከተማ የተመለከትኩት አንበርም በወረዳው ውስጥ በሌላ ቀበሌ ለተቀበረች ሴት የተቀጠረ ለቅሶ ነው፡፡

አንበር የሚደረገው በአብዛኛው ወንዝ ባለበት አካባቢ ቢሆንም፣ በዛፍ ጥላና በቤተክርስቲያን አጠገብ በሚገኝ ሰፊ ቦታ ላይም ሊከናወን ይችላል፡፡ በወንዝ አጠገብ እንዲሆን መደረጉ የአንበሩ ታዳሚዎች ከለቅሶው በኋላ ውሃ እንዲጠጡ ታስቦ ነው፡፡ ከወንዝ አካባቢ ውጭ ከተደረገም በበርሜል ውሃ ተቀድቶ ለመጠጥነት ይዘጋጃል፡፡

የአንበር ቀን የሚቀጠረው በብዛት ከቀብሩ እለት ከሳምንት እስከ አስራ አምስት ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ በበዓል ቀን ነው፡፡ ይህ ቀንም በቀብሩ እለት ይገለጻል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ «የእከሌ አንበር በዚህ ቀን ነው፤» እየተባለ በየደብሩና በየአብያተክርስቲያኑ፣ በየገበያ ቦታውም ይነገራል፤ ይለፈፋል፡፡

አኅበር ዝግጅት የሚጠይቅ ነው፤ምክንያቱም ሀዘንተኞቹ ለአኅበር የሚሆን እንጀራ ይጋግራሉ፤ ወጥ ይሰራሉ፡፡ ክክ ወጥ ብቻ ሳይሆን እልበትም በማባያነት ይቀርባልና ሀዘንተኞቹ ያዘጋጃሉ፤እልበቱ በብዛት በባለቤቶቹ ቢዘጋጅም፤ አልፎ አልፎም በቅርብ ዘመዶችም(በቁርጠኞች) ተዘጋጅቶ ይመጣል፡፡ የአኅበር ታዳሚዎችም ወደ አኅበሩ ሲመጡ በወገን በወገናቸው አንድ ላይ በመሆን እንጀራና ወጥ ይዘው ይመጣሉ፡፡[111]ይህም ለሟች ባላቸው የዝምድና ርቀትና ቅርበት የሚወሰን ነው፡፡ ራቅ ያሉት እንጀራ ብቻ ቀረብ ያሉት ደግሞ ወጥ በዛ ካለ በቶፋ አነስ ካለም በቅል ያመጣሉ፡፡ በአገልግል እንጀራ ይዘው የሚመጡትም የለቅሶው ስርዓት ተጠናቆ እርክክብ እስከሚካሄድ ድረስ አገልግላቸውን ዛፍ ላይ ያንጠለጥላሉ፡፡

በአኅበሩ ቀን የለቅሶው ታዳሚዎች ከየአቅጣጫው እስከሚመጡ ድረስ የለቅሶ ሥነ-ሥርዓቱ አይጀመርም፡፡ የአኅበሩ ለቀስተኞች አኅበሩ ወደሚካሄድበት ቦታ ሲቃረቡ ጥሩንባ ይነፋሉ፤ ይህም በዚያ አቅጣጫ መምጣት ያለባቸው ወገኖች መምጣቸውን ማረጋገጫ ነው፡፡ ሀዘንተኞቹና ቀድመው በቦታው የሚደርሱት ለቀስተኞችም በየቦታው ተሰባስበው በመቀመጥ ለቅሷቸውን ይቀጥላሉ፡፡

ሀዘንተኞቹ ከሌላው ታዳሚ አስቀድመው፣ በአኅበር ቦታ[112]ይገኛሉ፤ ሌላዎቹ ለቀስተኞች በሚመጡበት ወቅትም እያለቀሱ ከሀዘንተኞቹ ጋር ይቀላቀላሉ፤ ለአኅበር ስርዓቱም በቅሎ እንዲያጌጥ ይደረጋል(ይሸለማል)፤ ሰንደቅ ዓላማ ይያዛል፤ ጥሩባም ይነፋል፡፡ ሁሉም የአኅበሩ ለቀስተኛ መምጣቱ ከተረጋገጠ በኋላም ሜዳማ ቦታ ላይ የለቅሶ ስርዓቱ ይጀመራል፡፡ ለቅሶው የሚከናወነው ክብ ተሰርቶ፣ ወንዱ ለብቻ ሴቱ ለብቻ ተራ በተራ ክቡን በመዞር ነው፡፡ ይህንንም የሚያስተባብሩና የሚያስፈጽሙ ሰዎች (ወንዶች) ይኖራሉ፡፡ ወንዶቹም ሆኑ ሴቶቹ ሀዘንተኞች ፊት ለፊት በመሆን ለቅሷቸውን ይቀጥላሉ፡፡ ሴቶቹም ወንዶቹም አንዳንድ ጊዜ በክብ ዞረው ከተላቀሱ በኋላ፣ በካህን ጸሎት የለቅሶ ስርዓቱ ይጠናቀቅና ሁሉም ለቅሷቸውን አቁመው፣ ያመጡትን እንጀራ ወደሚያስረክቡበትና ወደ ሚመገቡበት ቦታ ያመራሉ፡፡

---

[111] መሸሃ ላይ እንደተመለከትኩት ለቀስተኞቹም ሆነ ሀዘንተኞቹ አዘጋጅተው አኅበሩ ወደሚካሄድበት ቦታ ያመጡት አንጀራ ሳይሆን ቆሎ ነው፡፡ ከአኅበሩ መጠናቀቅ በኋላ ከቤተክርስቲያን እልፍ ብለው በየዛፉ ተጠልለው የቆረጠሙትም ቆሎ ነው ፡፡

[112] በሁኔታዎች አስገዳጅነት ካልተቀየረ በስተቀር፣ በየደብሩ አኅበር የሚደረግበት ቋሚ ቦታ አለ፡፡



ለአኅበር በአገልግል የመጣው እንጀራ ከእርክክብ በፊት በከፊል (ፎቶ በብዙአየሁ ማሞ)

በዚህ ጊዜ ሃዘንተኞቹ ከፍተኛ ቦታ ላይ ይቀመጣሉ፤ ለቀስተኞቹም ያመጡትን የእንጀራና የወጥ መጠን ለአስረካቢዎች በመንገር ይሰጣሉ፤ አስረካቢዎችም የመጣውን የእንጀራና ወጥ መጠንና ያመጡትን ሰዎች ማንነት እየገለጹ፣ ለሀዘንተኞቹ ተራ በተራ በማሳየት ያስረክባሉ። በርክክቡ ወቅት እንጀራ እና ወጥ ያመጣው ሰው ስም የሚገለጸው የሁሉም ሰው ዝርዝር ሳይሆን የአባት ወይም የአያት ስም ነው፡፡ ይህም ለሀዘንተኛው ባለው ዝምድና ነው፡፡ ዝምድናው በአባት ከሆነ የአባት ወገን፣ በእናት ከሆነ ደግሞ የእናት ወገን ስም ይጠራል፡፡ እንጀራና ወጥ የሚያመጣው ሰው እየታየ ከማስረከቡ በስተቀር ስም ዝርዝርና የመጣው እንጀራና ወጥ መጠን አይመዘገብም፡፡ ምክንያቱን አቶ በሪሁን ጸጋየ ሲገልጹ፣ ‹‹ምዝገባ የለም፤ ምክንያቱም እንኳን ለአኅበር የመጣው የቀበረም እንኳ አንድ አይረሳም፤ተረካቢዎቹም ከተለያየ ቦታ የሚመጡ ወገኖች በመሆናቸው የአካባቢያቸውን ሰው የሚያውቁ ናቸው፡፡



**የአኅበር እንጀራ እርክክብ (ፎቶ በብዙአየሁ ማሞ)**

አብሯቸው የመጣውን ሰው የሚያስታውሱ ናቸው፡፡ ስለዚህ ምዝገባ አያስፈልግም፡፡›› ይላሉ(ቁ.ያመ. አ.12)፡፡ የአኅበሩ ለቀስተኞች ያመጡት እንጀራና ወጥ እርክክብ መጠናቀቁ ሲረጋገጥ፣ ሀዘንተኞቹ፣ ለቀስተኞቹን “ያመጣችሁትን አውቀነዋል፤ እንግዳችሁን ሸኙበት” ይሏቸዋል፡፡ ለመመገቢያ የሚሆን መሶብ ወይም ሳህን ስለማይኖር፣ በየራሳቸው አገልግል ለለቀስተኞቹ ይሰጣቸዋል፡፡ አመጋገባቸውም እንደ ሠርግ ድግስ አመጋገብ ሁሉ፣ ወንዶች ለብቻ ሴቶች ለብቻ ነው፡፡ የሚያስተናግዱትም ከየጎጡ ከመጡት መካከል ለሚች ዝምድና ያላቸውና ወጣት የሆኑት ወንዶች ናቸው፡፡

ለቀስተኞቹ ባመጡት እንጀራ፣ ወጥና በባለቤቶቹ በተዘጋጀው ወጥ ተከትሏቸው የመጣውን እንግዳ ከሸኙና ራሳቸውም ከተመገቡ በኋላ፣ የተረፈውን እንጀራ ለሀዘንተኞቹ ትተውላቸው ይሄዳሉ። ወንዝ የሚሻገሩ ደግሞ ኮሸሮ ይሰጣቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ይህንን እንጀራ መንገድ ላይ ይበሉታል እንጂ ይዘው ወደ ቤታቸው አይገቡም፡፡ ወደ ቤታቸው እንዲወስዱት የማይደረገው ሀዘንተኞቹን ለመርዳት ሲባል ብቻ አይደለም፤ ለሀዘን የተወሰደ እንጀራ ትራፊ ስለሆነ፣ ለሚወስደው ሰው ‹‹ሀዘን ይድረስብህ›› እንደ ማለትም ይቆጠራል፡፡(ው.መ.)



ወንዶች ሲመገቡ በከፊል (ፎቶ በብዙአየሁ ማሞ)



ሴቶች ሲመገቡ በከፊል (ፎቶ በብዙአየሁ ማሞ)

ሀዘንተኞቹም የተረፈውን እንጀራ በማረካከብ ስራ ላይ የነበሩ ሰዎችን ካስተናገዱበት በኋላ፣ ሌላውን እንዳይበላሽ አድርቀው ኮሸሮ በማድረግ ይጠቀሙበታል፡፡

ለቀስተኛው ከተመገበ በኋላ ወደ መጣበት ከመበታተኑ አስቀድሞ ባንድ ላይ ላይ ተሰባስቦ በድጋሚ ይላቀሳል፡፡ ከዚያም ሀዘንተኞቹን ተሰናብቶ ይሄዳል፡፡ ስንብቱም እንደ ቀብር እለቱ ሁሉ ወንድ፣ ወንድ ሀዘንተኛን፣ ሴት ደግሞ ሴት ሀዘንተኛን በማስተዛዘንና በመታየት ነው፡፡ የጎላ ባይሆንም ከወረዳ ወረዳ መጠነኛ ልዩነት እንዳለ ተረድቻለሁ፡፡ ለአብነት ያህል በዝቋላ ወረዳ በአንዳንድ ቦታዎች ለአጎበርና አንዳንድ ሃብታሞች ሲሞቱ ድንኳን ይተከላል (ው.መ.)፡፡

የስሃላ ወረዳ አጎበር ከሌላው ይለያል፤ የሚደረግበት ቦታ ሟች በተቀበረበት ወይም የሟች ዘመድ በሚገኝበት ባንድ ቦታ ላይ ሳይሆን ዘመድ በብዛት በሚገኝበት ቀበሌ ነው፡፡ የተመለከትኩት አጎበር የተደረገው በታህሳስ ወር በሌላ ቀበሌ ለሞተች ሴት ሲሆን መሸሃ ላይ የተደረገውም አብዛኛው ዘመዷ የሚገኘው በዚህ ቦታ ላይ በመሆኑ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በሌላዎቹ ወረዳዎች ለቀስተኛው እንጀራ ይወስዳል፤በሥነ-ሥርዓት ያስረክባል፡፡ በስሃላ ወረዳ ግን እንጀራ አይወሰድም፡፡ በለቅሶው ቦታ የሚቀርበው ቆሎ ነው፡፡ ይህንንም ሀዘንተኛውም ያዘጋጃል ለቀስተኛውም እያዋጣ ይዞ ይመጣል፡፡ በተመለከትኩት አጎበርም የለቅሶው ሥነ-ሥርዓት እንደተጠናቀቀ ለቀስተኛው በየዛፉ ጥላ ተጠልሎ የተስተናገደው በቆሎ ነው፡፡

**የሀዘንተኞች ገጽታ**

የዋግ ኸምራን የሀዘንተኞች ገጽታ የሴትና የወንድ ብሎ በሁለት በመክፈል መመልከት ይቻላል፡፡ በቅድሚያ ጎላ ብሎ የሚታየውን የሀዘንተኛ ሴት ገጽታን እገልጻለሁ፡፡

የዋግ ኸምራ ሀዘንተኛ ሴት ነጣ ያለና ንጹህ የሆነ አዲስ ልብስ አትለብስም፡፡ ቆሸሽ ያለና አሮጌ(ሀፍላውን) ትለብሳለች፤ ቀሚሷ በጥልፍ ያጌጠ (የተጠለፈ) ከሆነና ሌላ መቀየሪያ ከሌላት ደግሞ ገልብጣ ትለብሰዋለች፤ ጥለት ያለውን ቀሚሷንም እንዲሁ ወደ ውስጥ ገልብጣ ትለብሳለች፡፡ መቀነቷ የተለያየ ቀለም ባላቸው ክሮች የተዋበ ከሆነም ስትታጠቅ ወደ ውስጥ ትደብቀዋለች(ትሸጉጠዋለች) እንጂ አታጌጥበትም፡፡ ለሟች እንደሚኖራት

ቀረቤታም ሽሩባዋን ትነጫለች፣ ወይም የጆፌውን ጫፍ በነጭ ጨርቅ ታስረዋለች፣ ከተወሰነ ጊዜ ቆይታ በኋላም ትላጨዋለች፡፡ ፊቷንም ትልጣለች፡፡ የሃዘንተኛነት ምልክት የሆነውን የነጭ ክር ማተብና ጥቁር ሻሽ ታስራለች፡፡

የአካባቢው ሴቶች ጸጉራቸውን የሚነጩበትንና ፊታቸውን የሚልጡበትን ምክንያት አስመልክተው ወ/ሮ አዳኑ አበራ እንዲህ ይገልጻሉ፣ ‹‹ሰው ሲሞት ጸጉር የሚነጨው ያገር ትድረት(ወግ) ልማድ ሆኖ ነው፡፡ ሀዘንተኛዋ ሽሩባዋን ባትነጭና ፊቷን ባትልጥ ግን ለማህበረሰቡ ሃሜት ትጋለጣለች፣ ነገ የሚበቅለው ጸጉሯ ከእንትኗ[113]በልጦባት ነው ትባላለች›› (ቁ.ያ.መ.አ.11)፡፡ ሃዘንተኛዋ ጸጉሯን ቅቤ አትቀባም፣ ይህም የሚቀጥለው ሌሎች ሴቶች ቅቤ ቀብተዋት ሃዘኑን ተይ እስከምትባል(እስከምትደበስ) ድረስ ነው፡፡ ያላትን ጌጣጌጥም ለአብነት ያህል ድኮቷን፣ ድሪዋን፣ ጉትቻዋን፣ መስቀሏን አወላልቃ ታስቀምጣለች፡፡ ነጠላዋንም በመጀመሪያዎቹ የሀዘን ወራት ጫፉን ቋጥራ ወደ ኋላ ደግሞ፣ ጥለቱን ወደ ላይ አድርጋ ወይም ዘቅዝቃ ትለብሳለች፣ ራሷንም በምግብ ትቀጣለች፣ ስለዚህ በወቅቱም አትመገብም፣ የምትተኛውም አልጋ ወይም መደብ ላይ ሳይሆን መሬት ላይ ነው፡፡

ይህ የሀዘንተኛ ሴት ገጽታ የሚቀጥለውም እንደ ሟች ቀረቤታ እና እንደ ሀዘንተኛዋ ሁኔታ ነው፡፡ አንዳንዶች ‹‹ሀዘን ያጠብቃሉ›› ይባላሉ፣ እነዚህም የሀዘንተኛ ገጽታቸውን ለረጅም ጊዜ የሚያቆዩ ናቸው፡፡ አንዳንዶች ደግሞ በቶሎ ሀዘናቸውን ትተው ወደ ዘወትራዊ ገጽታቸው ይመለሳሉ፡፡ ለሃዘንተኛነት ገጽታ ማጠር አንዱ ምክንያት የሰውየው/የሴትየዋ የጤንነት ሁኔታ ነው፡፡ ህመምተኛ ከሆኑ የሀዘንተኛ ገጽታቸውን ቶሎ ይተዋሉ፣ እነዚህ ሀዘናቸውን በቶሎ ተው ተብለው በማህበረሰቡም አይነቀፉም፡፡ ጤነኛ ሆነው ቶሎ ካቆሙ ግን ሃሜቱ አይቀርላቸውም፣ ‹‹ለእከሌ ያልሆነች፣ ድሮ እከሌ አፈር ለብሶ እሷ እንዲህ ታጌጣለች›› ወዘተ. ይባላሉ፡፡ ስለዚህ በሃዘንተኛነት ገጽታ ለረጂም ጊዜ መቀጠል ምክንያቱ የውስጥ ስሜት መጎዳት ብቻ ሳይሆን፣ ውጫዊ ወይም ማህበረሰባዊ ትችት ፍራቻም ነው፡፡ ሀዘንተኛ ወንድ ደግሞ ፊቱን ይልጣል፣ ቆሸሽ ያለ ልብስ ይለብሳል፣ ፀጉሩን ይላጭና ጥቁር

[113] ሟችን ለማለት ነው

ቆብ ይደፋል። ጢሙንም ያሳድጋል፡፡ በደጋው[114]አካባቢ ደግሞ እንደ ሴቶቹ ነጠላውንም ዘቅዝቆ ይለብሳል።

በእርግጥ ማንኛውም ሰው የሚሞትበት (የምትሞትበት) ሁሉ ያዝናል፤ የሀዘኑ መጠን ግን የተለያየ ነው፤ ይህ ልዩነትም ጾታን መሰረት ያደረገ ሊሆን ይችላል፡፡ ሴቶች እጅግ በጣም ያለቅሳሉ፤ የሀዘን ገጽታቸውም ከወንዶች ይልቅ ጎልቶ የሚታይ ነው፡፡ ይህንን ገጽታቸውንም ለረጂም ጊዜ ያቆዩታል፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት በሟች ምክንያት ጉዳት ወይም ችግር የሚደርስባት ከወንድ ይልቅ ሴት በመሆኗ ነው፡፡ ስለዚህ ሚስቱ ከምትሞትበት ወንድ ይልቅ ባሏ የሚሞትባት ሴት ለችግር ትዳረጋለች፡፡ ምክንያቱም የምትተዳደረው በጋራ ሰርተው በሚያገኙት የእርሻ ስራ ምርት እንጂ የራሷ የሆነ ሌላ የገቢ ምንጭ እና መተዳደሪያ ስለማይኖራት ነው፡፡

ይህንን አስመልክተው ወ/ሮ ጠጄ ሲገልጹ፣

> የወንድና የሴት ሀዘን የተለያየ ነው፤ ወንድ ቢያዝንም ሚስት አምጥቶ ወዲያው ይተወዋል፡፡ ምክንያቱም በተለይ ልጆች ካሉት አብስሎ የሚያበላቸው ስለሚያስፈልጋቸው ነው፡፡ የሟች ሚስት ቤተሰቦችም ልጆቹ እንዳይራቡ፣እንዳይጠሙ በማለት ቶሎ እንዲያገባ ግፊት ያደርጋሉ፡፡ ወንዱ ግን ሚዛኑን ወደ አዲሷ ሴት ያደላል፤ ከሟች ሚስት የተወለዱ ልጆችም እያለቀሱ ይኖራሉ፡፡ ሴቷ (ባሏ የሞተባት) ግን ልጆቿን አብስላ ስለምታበላቸው ዘግየት ትላለች፤ ጸጉሯን እየተላጨች፣ ልጆቿን እያየች እያለቀሰች ትኖራለች፤ ትከሳለች፤ ትዳር (ላግባት የሚል ወንድ) ቢመጣም እንኳ ልጆቹን ሳላሳድግ ትላለች፡፡ የሴት ሀዘን ከባድ ነው፤ ወንድ ሞቶ ሴት ወደ ኋላ ከቀረች እናቲቱ ትባክናለች እንጂ ልጆቿ ስር ይይዛሉ ይላሉ (ቁ.የ.መ.አ.1)፡፡

### 6.4.4 የሟች መታሰቢያዎች (መዘከሪያዎች)

ለሟች ተብለው የሚደረጉ በርካታ መዘከሪያዎች አሉ፤እነዚህም የሚጀመሩት ሟች በተቀበረ በሶስተኛው ቀን በሳልስት ነው፡፡ በሳልስት አንድ ገንቦ ጠላና አምስት እንጀራ ወደ ቤተክርስቲያን ይወሰዳል፤ ከዚያ በሰባት አንድ እንስራ ጠላና አስር እንጀራ፣ በአስራ ሁለት እና በሰላሳ ጋን ጠላና ሃያ እንጀራ እና በአርባው ደግሞ ከፍ ያለ ድግስ ተደግሶ ይቀጥላል፡፡ ከእነዚህ መካከል በአርባው የግድ በግ፣ ፍየል አቅም ካለም በሬ መታረድ

[114] በቆላው ግን ሴቶች እንጂ ወንዶች ነጠላቸውን አይዘቀዝቁም፡፡

ወይም ደም መፍሰስ አለበት፡፡ ከእነዚህም በተጨማሪ ባመቱ የሚደገስ አመታትም ይገኝበታል (ቡ.ተ.ው.1፣2፣3 እና 4)፡፡

ሌላው ደግሞ የቁም ተዝካር ነው፡፡ ይህም ሁለት አይነት ነው፡፡ አንደኛው ሰዎች ከሞቱ በኋላ መዘከሪያ የሚያደርግልኝ አይኖርም ብለው፣ እራሳቸው በቁማቸው የሚያደርጉት የመዘከሪያ ምትክ ነው፡፡ ይህም ለሟች መዘከሪያ እንደሚሆነው ሁሉ በቁም ያሉ ሰዎች ስለሚደግሱት የቁም ተዝካር ይባላል፡፡ ይህንን አስመልክተው የመረጃ አቀባዮቹ እንደሚከተለው ብለዋል፡፡

> እኔ ከሞትኩ ባለቤቴን ወይም እህቴን ማን ያነሳታል በማለት ሰውየው ከመሞቱ አስቀድሞ ይናዘዝና ከእሱ ጋር አብሮ/ራ እንድትዘከር ይደረጋል፡፡ባሏ ከሞተም ሴቲቱ ትልቅ ከሆነች ባሏ ጋር ትፈታለች፡፡ወይም ሚስቱ ከሞተች ባል በህይወት እያለ ሚስቱ ጋር ይፈታል፤ይዘከራል፡፡ ስለዚህ ሚስት ከባል ጋር ወይም ባል ከሚስት ጋር ይፈታል፡፡ይህ የሚሆነው ትልቅ ከሆኑና እንግዲህ ወደ ሞት ነው ሌላ የለኝም ሲሉ ነው፡፡ ተዝካር የሚደረግለት/የሚደረግላት በቁም ያለው/ያለችው ግን እንደ ሟች ተደርጋለችና ከድግሱ አትቀምስም
>
> (ቁ.የ.መ.አ.21፣ ቡ.ተ.ው.1 እና 4)፡፡

የእነዚህ መዘከሪያዎች ዝግጅት ምክንያታቸው ወይም ምንጫቸው ሃይማኖት መሆኑን የሃይማኖት አባቶች እንደሚከተለው ይገልጻሉ፤‹‹በነዚህ ቀናት የሟቹ ስም እንዲነሳ፣ ነፍሱ እንዲታሰብ፣ እንዲታወስ ቤተክርስቲያን ትፈቅዳለች፤ ደጋሹን የሚያራቁት ድግስ ደግሱ ግን አትልም፡፡ በርግጥ የቀደሱ አባቶች፣ አፋቸውን እንዲሽሩ ትንንሽ ነገሮች ማባያዎችን ትፈቅዳለች፤ ምእምኑ ግን ሌላው ሰው ‹‹ሳትጠራኝ ቀረህ፡፡›› ስለሚለው ብቻ እንደ ሠርግ ድግስ በመደገስ ከፍተኛ ወጭ ያወጣል›› (ቁ.የ.መ.አ.13)፡፡

የመዘከሪያን አስፈላጊነት በሚመለከት በፍትሐ ነገሥት (1995፣275-276)ም እንደሚከተለው ሰፍሮ ይገኛል፤

> …ስለ ሞቱ ሰዎች በሶስተኛው ቀን መታሰቢያ አድርጉላቸው ዳዊት እየደገማችሁ፣ እየጸለያችሁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሶስት መአልት ሶስት ሌሊት በከርሰ መቃብር አድሮ በሶስተኛው ቀን ስለተነሳ፣ በሰባተኛውም ቀን የሙታንን የሕያዋንን መታሰቢያ አድርጉላቸው ሠላሳውም ቀን ሲፈጸም እስራኤል ያደርጉ እንደ ነበር መታሰቢያ

አድርጉላቸው፡፡ ዓመቱ ሲፈጸም እስራኤል መታሰቢያ ያደርጉ እንደነበር...መታሰቢያ አድርጉላቸው፡፡...ባስራ ሁለተኛው ቀን...ሁለት ወር ሲፈጸም በ60 ቀን መሥዋእት ሠውላቸው...)

ከዚህ የምንረዳው ድግሱ ይብዛም ይነስም የመዘከሪያው መነሻ ግን ሃይማኖት ነው፡፡

አንድ ሰው ለሟች ወላጆቹ የሚጠበቅበትን መዘከሪያ ካላደረገ በማህበረሰቡ በኩል ‹‹ የአባቱን ወይም የእናቱን አፍ ያላበሰ ወይም እናቱን ከወደቀችበት ያላነሳ፡፡›› ተብሎ ሀሜትና ስድብ ይደርስበታል፡፡ እንደ መረጃ አቀባየ አገላለጽ፣ ‹‹ለእናት ለአባቱ ያልሆነ ምን ሰው ነው ተብሎ ከሰው ቁጥር ስለማይቆጠር ከማህበረሰቡ ይገለላል›› (ቁ.የ.መ.አ.21)፡፡

ከዚህ የምንረዳው የተለያዩ መዘከሪያዎች ለሟች የሚደረጉት ሃይማኖቱ በሚፈቅደው መሰረት ለሟች ነፍስ ይማርነት ሲባል ብቻ ሳይሆን ለቋሚም በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት ነው፡፡

ባጠቃላይ እነዚህ ሶስት ሥነ-ሥርዓቶች እርስ በርሳቸው የተያያዙ ናቸው፤ ጋብቻ የሚፈጽሙት የተወለዱ ናቸው፤ ለሞት የሚዳረጉትም ሁልጊዜም ባይሆን(ከጋብቻ ውጭም ሊወለዱ ይችላሉና) በጋብቻ ከተሳሰሩ አካላት የተወለዱ ናቸው፡፡

# ምዕራፍ ሰባት

## የሶስቱ ሥነ-ሥርዓቶች ትንተና፣ ማጠቃለያና ይሁንታ

በዚህ ምዕራፍ በሶስቱ ሥነ-ሥርዓቶች ላይ ትንተና ያደረግሁት ከተምሳሌታዊና መዋቅራዊ-ፋይዳዊነት አንጻር ነው፡፡ ምክንያቱም በመተንተኛ ማእቀፍነት ከጠቀስኳቸው መካከል ተነጣጥለው ሊታዩ የማይችሉትን ሁለቱን (ክዋኔና አውድን) ከምዕራፍ አራት እስከ ስድስት ሶስቱን ሥነ-ሥርዓቶች በምገልጽበት ወቅት ተጠቅሜባቸዋለሁ፡፡ ስለዚህ በዚህ ምዕራፍ የመጀመሪያው መተንተኛ ማእቀፍ ተምሳሌታዊነት ነው፡፡ ስለዚህ በሶስቱ ሥነ-ሥርዓቶች ክዋኔ ወቅት የሚገኙ ተምሳሌታዊ ድርጊቶችና ቁሳቁሶች ተምሳሌታዊ ፍቻቸው ምን እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ምክንያቱም የመረጃ መተንተኛ ማእቀፍ ጽንሰ-ሀሳብ ላይ እንደተመለከትነው ሥነ-ሥርዓቶች በተምሳሌት የተሞሉ ናቸው፡፡ ሌላው መተንተኛ ጽንሰ-ሃሳብ ደግሞ መዋቅራዊ-ፋይዳዊነት ነው፡፡ ምክንያቱም ሶስቱ ሥነ-ሥርዓቶች እንደ አበይት የሽግግር ሥነ-ሥርዓት አይነትነታቸው መዋቅር እንዲሁም ለግለሰብም ሆነ ለማህበረሰብ የሚፈይዱት ነገር አለ፡፡ መዋቅራዊነትን የተመለከትኩት ከሽግግር ሥነ-ሥርዓት ደረጃዎች አንጻር ነው፡፡ የሽግግር ሥነ-ሥርዓት ደግሞ ሶስት ደረጃዎች አሉት፤ Turner (1970: 94) Van Gennepን(1960) ጠቅሰው እንዳሰፈሩት በቅደም ተከተል፤ ቅድመ-ማእከል፣ ማእከል እና ድህረ-ማእከል ይባላሉ። Turner በተመሳሳይ ስራቸው እንዳሰፈሩት አንድ አካል በማእከል ደረጃ ላይ ሲሆን ከአንድ አዲስ ከሆነ ነገር ጠርዝ ላይ ሆኖ ከነበረበት ቦታ እና ጊዜ ሽግግር ላይ ይሆናል። በሌላ አገላለጽ ቀደም ሲል እንደነበረውም ወደፊት እንደሚሆነውም አይደለም፤ በመሆኑም በዚህ ደረጃ ላይ የሚገኝ አካል ይህ ነው የሚባል የተወሰነ ቦታ ስለማይኖረው አስቼጋሪ ይሆናል ይላሉ።

በመቀጠል የተመለከትኩትም የሶስቱን ሥነ-ሥርዓቶች ክዋኔ ለውጥና ቀጣይነት ነው፤ ምክንያቱም ከጥናቱ ዓላማ አንዱ የሶስቱን ሥነ-ሥርዓቶች ክዋኔ ለውጥና ቀጣይነት ማሳየት ነው፡፡ በመጨረሻም ማጠቃለያና ይሁንታን አቅርቤያለሁ፡፡

## 7.1 የወሊድ ሥነ-ሥርዓት ትንተና

### 7.1.1 ከተምሳሌታዊነት አንጻር

የወሊድ ሥነ-ሥርዓት ሲከወን በርካታ ተምሳሌታዊ ድርጊቶችና ቁሳቁሶች ይገኛሉ፡፡ዋና ዋናዎቹም የሚከተሉት ናቸው፡፡ በምጥ ወቅት ምጥ ከያዛት ሴት አጠገብ ከማይቀመጡት መካከል ያልወለዱ ሴቶች ይጠቀሳሉ፤ ምክንያቱም እነዚህ ሴቶች ካሁን በፊት ማህጸናቸው ተፈትቶ ልጅ ስላልወለዱ በአካባቢው ድፍን ቅሎች ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለዚህ ያልወለደች ሴት ያልተበሳ ድፍን ቅል ተምሳሌት ናት፡፡ በሌላ በኩል ገና ያልወለደችና መካን ሴት ምጥ ወደተያዘች ሴት ቤት እንዲገቡ አይፈቀድላቸውም፤ ምክንያቱም እነሱ ከገቡ ሴትየዋ በቶሎ አትገላገልም፤ ምጡ ይራዘማል ተብሎ ይታመናል፤ ስለዚህ ገና ያልወለደችና መካን ሴት፣ ቶሎ ያለመገላገል፣ ወላድ ሴት ደግሞ ቶሎ የመገላገል ተምሳሌቶች ናቸው፡፡ ስለዚህ ሁለቱ በተከታታይ በመጥፎ እና በጥሩ ነገር ተምሳሌትነት ይወሰዳሉ፡፡

በምጥ ወቅት ቀደም ሲል መታጠቂያ ሸምቀቆ፣ አሁን አሁን ደግሞ ቀበቶና ማሰሪያ ያለው ጫማም ማሰሪያው ይፈታል፡፡ እቤት ውስጥ ያለ ድፍን ቅልም ወደ ውጭ ይወጣል፡፡ የተቆለፈው ሳጥን ይከፈታል፡፡ እነዚህ የታሰሩና የተዘጉ ነገሮች የነፍሰ-ጡር ሴት ተምሳሌቶች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ሸምቀቆው፣ ቀበቶው፣ ማሰሪያ ያለው ጫማ መፈታቱ፣ ሳጥኑ መከፈቱ የነፍሰ-ጡሯ ሴት ማህጸን ተከፍቶ ቶሎ የመገላገል ተምሳሌቶች ናቸው፡፡ በአንጻሩ እነዚህ ነገሮች አለመፈታታቸው፣ ሳጥን መቆለፉና እቤት ውስጥ ድፍን ቅል መኖር ደግሞ የምጡን ጊዜ መራዘምና ምጥ የያዛት ሴትም በቀላሉ ያለመገላገል ተምሳሌቶች ናቸው፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው አራስ ሴት በእጇ አምባር ታደርጋለች፤ በትራሷም አንካሴ ይተከላል፤ ብቻዋን እንዳትሆንም ጠባቂ ሰዎች ያስፈልጋሉ፡፡ እነዚህ ድኮትና ለአራሷ መጠበቂያነት የሚያገለግሉ ብረት ነክ ነገሮች ሁሉ እሷን የመጠበቂያ አካል ተምሳሌቶች ናቸው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ነገሮች ካጠገቧ ካሉ ከመጥፎ ነገር ይከላከሏታልና ምንም አይነት እርኩስ መንፈስ አይቀርባትም ተብሎ ይታመናል፡፡ በአራስ ልብስ አጠባ ወቅትም አጣቢዎቹ ቢላዋ ወይም ብረት ነገር ይዘው ወደ ወንዝ ይሄዳሉ፡፡ ቀደም ሲል

እንደተጠቀሰው ብረት ነክ ነገሮች መንገድ ላይም ሆነ ወንዙ ላይ የሚገኘን እርኩስ መንፈስ የመከላከያ ሃይል ተምሳሌቶች ናቸው፡፡

በልብስ አጠባ ወቅት ከወንዝ የሚመጡ የተለያዩ ቁሳቁሶች አሉ፡፡ እነዚህም ሕፃኗ ሴት ከሆነች ላክሽም፣ እንዝርት፣ ወንፊት፣ ማንዘርዘሪያ፣ ቅል፣ ወስከንቢያ፣ ሙዳይ፣ ሕፃኑ ወንድ ከሆነ ደግሞ ጠብመንጃ (መሳሪያ)፣ የእርሻ መሳሪያ ወስኮ፣ ማረሻ ወዘተ.ናቸው፡፡ ስለዚህ እነዚህ ቁሳቁሶች በተከታታይ ሴት ስታድግ የምትሰማራበትን የቤት ውስጥ ስራ እና ወንድ ልጅ ሲያድግ የሚሰማራበትን የእርሻ ስራ የሚያመለክቱ ተምሳሌቶች ናቸው፡፡

ወንድ በተወለደ በአርባ ቀኑ፣ ሴት በተወለደች በሰማንያ ቀኗ ክርስትና መነሳታቸውም ተምሳሌታዊ ነው፡፡ ይህንንም ሞገስ(1969፣80) እንዲህ በማለት አስፍረዋል፤ ‹‹ ወንድ ልጅ በተወለደ በ፵ ቀን ሴት ልጅ በተወለደች በ፹ቀን ይጠመቁ ስትል ቤተክርስቲያን ወስናለች...ምሳሌውም አዳም በተፈጠረ በ፵ ቀን ሔዋን በተፈጠረች በ፹ ቀን በመላእክት ታጅበው ገነት ለመግባታቸው ምሳሌ እንደሆነ ከኦሪቱ ልማድ ሲያያዝ የመጣ ነው፡፡›› ስለዚህ ሴት የሔዋን፣ ወንድ ደግሞ የአዳም ተምሳሌት ናቸው፡፡ ለክርስትና ማስነሻ በቅል የሚወሰደው ውሃ ወደ ዳታን ይገለበጣል፤ ይህ ሕፃኑ የሚጠመቅበት የዳታን ውሃም የዮርዳኖስ ወንዝ ተምሳሌት ነው፡፡

ሌላው ተምሳሌታዊ ቁስ ማተብ ነው፡፡ ሕፃን ክርስትና ለመነሳቱ በምልክትነት ማተብ ይታሰርልታል፡፡ ማተብ ማሰር ሕፃኑ የክርስትና እምነት ተከታይ መሆኑን የሚያመለክት ተምሳሌት ነው፡፡ ለዚህ ነው በዞኑ ማተብ ያላሰረ ሰው ከታየ ‹‹እስላምህን ነህ፡፡›› የሚባለው፣ የክርስቲያንነት ምልክት የሆነውን ማተብ ባለማሰሩ የሌላ ሃይማኖት ተከታይ መስለሃል ማለት ነው፡፡

ሕፃኑ በክርስትና ልጅነት ለታቦት ከተሰጠ ወደ ቤተክርስቲያን የሚገባው ታዝሎ ሳይሆን በዲያቆን ታቅፎ ነው፡፡ ይህ ዲያቆንም ለሕፃኑ/ለሕፃኗ የክርስትና አባት ወይም እናት የሆነው ታቦት ተምሳሌት ነው፡፡

### 7.1.2 ከመዋቅራዊ-ፋይዳዊነት አንጻር

የወሊድ ሥነ-ሥርዓትን የመዋቅራዊ-ፋይዳዊነትን ትንተና የተመለከትኩት ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው ከመዋቅራዊነትና ከፋይዳዊነት አንጻር ነው፡፡

#### 7.1.2.1 ከመዋቅራዊነት አንጻር

የወሊድ ሥነ-ሥርዓትን ከሽግግር ሥነ-ሥርዓት መዋቅር አንጻር ስተነትን የተለያዩ አካላትን ተመልክቻለሁ፡፡ ነፍሰ-ጡሯን ሴት፣ ጽንሱን፣ የነፍሰ-ጡሯን ባልና ወላጆቻቸውን፡፡ በመጀመሪያ የነፍሰ-ጡሯን ሴት ሁኔታ እገልጻለሁ፡፡

ቀደም ሲል እንደ ገለጽኩት አንዲት ሴት ከመጸነሷ በፊት ትሳተፍባቸው ከነበሩ በርካታ ስራዎች ትገደባለች፤ ከመጸነሷ በፊት ትመገባቸው ከነበሩ የምግብ አይነቶችም ትታቀባለች፡፡ይህም የሚያመለክተው ነፍሰ-ጡር ከመሆኗ በፊት ከምትሰራቸውና ከምትመገባቸው የምግብ ዓይነቶችና ስራዎች መገለሏን ወይም መነጠሏን ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ወቅት በመለየት ደረጃ ናት ማለት ነው፤ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ነፍሰ-ጡርነቷ ከቀደምት ማንነቷ ስለለያት ነው፡፡ ስለዚህ ነፍሰ-ጡሯ ሴት በዚህ ደረጃ ላይ ስትሆን፣ ከነባር እሷነቷ ተለይታለች፡፡ በዚህ ጊዜ የምትገኝበት የመዋቅር ደረጃም የመሸጋገሪያ ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ደረጃ ይህ ነው ተብሎ የሚወሰን ቦታ የሌለበት፣ ከቀዳሚውም ከሚቀጥለውም የማይሆንበት ደረጃ ነው፡፡ ነፍሰ-ጡሯ ሴትም እንዲሁ ነጻ ሁና እንደ ቀደምት ገጽታዋ አይደለችም፤ ተገላግላም ለመጀመሪያ የወለደች ወይም በካር ከሆነች ካልወለዱ ወይም ከልጅ አልባ ሴቶች ምድብ ወጥታ ወደ እናትነት፣ በካር ባትሆንም ከነፍሰ-ጡርነት ወደ አራስነት አልተሸጋገረችም፤ የምትገኘው በመሀል ላይ ነው፡፡

ነፍሰ-ጡሯ ሴት ከተገላገለች በኋላ ግን ወደ ሶስተኛው የሽግግር ሥነ-ሥርዓት ደረጃ ወይም መዋቅር ትሸጋገራለች፤ ይህም ደረጃ መቀላቀል ነው፡፡ መቀላቀል በሁለት መንገድ ሊገለጽ ይችላል፡፡ በመጀመሪያ ከነፍስ-ጡርነት ወደ ሌጣነት ተሸጋግራ ወደ ቀደመው ማንነቷ ተመልሳለችና ከቢጤዎቿ ጋር ተቀላቅላለች፡፡ በመሆኑም ከማህበረሰቡ የሚጠበቅባትን ስራዎች ነጻ ሆና መስራትና፣ የምትፈልገውን የምግብ ዓይነት መመገብ ትችላለች፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በተለይ የመጀመሪያ ወላጅ ከሆነች ከልጅ አልባ ሴቶች ምድብ ተነጥላ

ወይም ተለይታ ወደ እናትነት ምድብ ትቀላቀላለች፡፡ ይህም አዲስ ማንነትን እንድትላበስ ያደርጋታል፡፡

መዋቅርን በጽንሱና በሕፃኑ በኩልም መመልከት ይቻላል፡፡ ይኸውም የጽንሱ እትብት ተቆርጦ ከእናቱ ማህጸን ሲለይ በመለየት መዋቅር ላይ ይሆናል፡፡ ከእናቱ የማህጸን አለም ወደ እዚህ ዓለም ህይወት በሚቀላቀልበት ወቅት ደግሞ በመቀላቀል ደረጃ ላይ ይሆናል፡፡ ይህም ከነበረበት ዓለም (ቦታ) አንጻር ነው፡፡ ወደ ማህበረሰቡ በመቀላቀል በኩል ግን የሚገኘው በመካከለኛ ደረጃ ላይ ነው፡፡ ምክንያቱም ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው ክርስትና ተነስቶ/ተነስታ ወደ ክርስቲያኖች ማህበረሰብ ገና አልተቀላቀለም/አልተቀላቀለችም፡፡ ስለዚህ በዚህ ወቅት ሕፃኑ/ሕፃኗ በመካከል ደረጃ ላይ ይገኛል/ትገኛለች፡፡

የሕፃኑን የክርስትና መነሳትም ከመዋቅር አንጻር መመልከት ይቻላል፤ ሕፃኑ ክርስትና እስከሚነሳበት ጊዜ የሚገኝበት ደረጃ መካከለኛ ነው፤ ምክንያቱም ቀደም ሲል እንደ ተጠቀሰው ተጠምቆና ክርስቲያን ተብሎ የኦርቶዶክስ ክርስቲያን ምልክት የሆነውን ማተብ አስሮ ወደ እምነቱ ተከታዮች አባልነት አልተቀላቀለም፤ በቀብር ስርዓት እንደ ተገለጸውም ያልተጠመቀ ሕፃን ቢሞት ቤተክርስቲያን ውስጥ አይቀበርም፡፡ ምክንያቱም የእምነቱ ህግ እንደሚያዘው አርባ ወይም ሰማንያ ቀን ሞልቶት/ሞልቷት አልተጠመቀችም፡፡ ካልተጠመቀ ደግሞ ክርስቲያን አልሆነም፡፡ ከተጠመቀና ማተብ ካሰረ በኋላ ግን ክርስቲያን ሆኗልና ወደ ክርስትና እምነት ተከታዮች አባልነት ይቀላቀላል፡፡ ከዚህ በኋላ ቢሞትም ሌሎች የክርስትና እምነት ተከታዮች ወደሚቀበሩበት ቤተክርስቲያን ተወስዶ ይቀበራል፤ ከሌሎች ሟች ክርስቲያኖች የቀብር ቦታ ጋር ይቀላቀላል፡፡

ከመዋቅር አንጻር የሚተነተነው ሌላው አሰያየም ነው፤ አሰያየምን ለመተንተን ዓለማዊ እና መንፈሳዊ ብሎ በሁለት መንገድ ማየት ይቻላል፡፡ ሕፃኑ/ሕፃኗ አለማዊም ሆነ መንፈሳዊ ስም ተሰጥቶት እከሌ ተብሎ እስከሚጠራበት ድረስ የሚገኝበት ደረጃ ማእከላዊ ደረጃ ነው፤ ምክንያቱም ከጽንስነት ወደ እዚህ አለም ቢሸጋገርም ለመለያነቱ ወይም ለመጠሪያነቱ የሚሆን ስም ተሰጥቶት ከሌላዎቹ ጋር አልተቀላቀለም፡፡ ነገር ግን ስም ከተሰጠውና ሙሉ ሰውነቱን ካረጋገጠ በኋላ ስም ወደ ተሰጣቸው ሕፃናት ምድብ ይገባና በመቀላቀል ደረጃ ላይ ይሆናል፡፡

የነፍሰ-ጡሯን ባለቤት ከመዋቅር አኳያ ስንመለከት ደግሞ ባለቤቱ ቀደም ሲል ከተጠቀሱት ስራዎችና ምግቦች ስትገለልና ስትታቀብ፣ እሱ ግን አይገለልም፤ አይታቀብም፡፡ በዘወትራዊ ስራው ይሳተፋል፤ የተለመደውን አመጋገብም ይቀጥልበታል፡፡ ይሁን እንጂ በተለይ ሚስቱ ገና ለመጀመሪያ ጊዜ የጸነሰች ከሆነች፣ እሱም ሚስቶቻቸው ካልጸነሱ ወንዶች ይለያል፡፡ ወልደው ከሳሙትም ጋር ገና ስላልተቀላቀለ በመሸጋገሪያ ደረጃ ይገኛል፡፡ ሚስቱ ስትወልድ ግን ከልጅ አልባነት ወደ አባትነት በመሸጋገር አባት ሆኖ ወደ አባቶች (ልጅ ወደ አላቸው ወንዶች) ምድብ ይቀላቀላል፡፡

ወደ ሌላ የማህበረሰብ ምድብ የሚቀላቀሉት ባልና ሚስት ብቻ አይደሉም፤ ወላጆቻቸውም አያቶቻቸውም ናቸው፡፡ ምክንያቱም ወላጆችና አያቶችም ልጆቻቸው በመለየት ደረጃ ላይ በሚገኙበት ወቅት እነሱም በመለየት ደረጃ ላይ ይሆናሉ፡፡ ልጆቻቸው በመሸጋገሪያ ደረጃ ላይ ሲሆኑም እነሱም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ይሆናሉ፡፡ ልጆቻቸው ወልደው ወላጅ ሲሆኑ (በተለይም የመጀመሪያ ወላጆች ከሆኑ) ደግሞ፣ እነሱም ከአባትነትና ከእናትነት ወደ አያትነት፣ አያቶችም ወደ ቅድመ-አያትነት ይሸጋገራሉ፤ ቀደም ሲል ወደ አልነበሩበት አያትነትና ቅድመ አያትነት ምድብ ጋርም ይቀላቀላሉ፡፡

### 7.1.2.2 ከፋይዳዊነት አንጻር

የወሊድ ሥነ-ሥርዓት የተለያዩ ፋይዳዎች አሉት፤ ዋና ዋናዎቹም የሚከተሉት ናቸው፡፡ ሰዎች ለነፍሰ-ጡር ሴት የሚያደርጉትን እንክብካቤ ስንመለከት፣ በአንድ በኩል የነፍሰ-ጡሯን ጤንነት በመጠበቅ በኩል ግለሰባዊ ጠቀሜታን ሲያስገኝ፣ ሰዎች ለእሷ የሚያደርጉት እንክብካቤና ምክር ደግሞ የእርስ በእርስ መተሳሰብንና መረዳዳትን ያመለክታልና ማህበረሰባዊ ጠቀሜታ አለው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ነፍሰ-ጡሯ ሴት አንዳንድ የምግብ አይነቶችን እንዳትበላና እንዳትሰራ የምትከለከላቸው የምግብና የስራ አይነቶች፣ ማህበረሰቡ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ መጥቶ ያወቀውን እውቀት በመያዙና በማስተላለፉ ነው፡፡ ይህም ሥነ-ሥርዓቱ በማስተማሪያነት ከማገልገሉም በላይ እገዛውና ትብብሩ ቀጣይነት እንዲኖረው ያደርጋል፤ ለማህበረሰቡ ቀጣይነትም ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡

አንዲት ሴት ስትወልድ ዘመድ ወይም ጎረቤት እንደ አቅሙ የአራስ መጠየቂያ ይዞ ይጠይቃታል፡፡ ይህም ግላዊና ማህበራዊ ፋይዳ አለው፤ ፋይዳውንም በኢኮኖሚያዊና በማህበራዊ ትስስር፣ መተሳሰብ እና መተጋገዝ በኩል ብሎ በሁለት መንገድ መመልከት ይቻላል፡፡ በኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በኩል አራሷ በአራስ ቤት ቆይታዋ ወቅት ተጨማሪ ምግብ ያስፈልጋታል፤ የምትመገበውም አስቀድማ ያዘጋጀችውን ምግብ ብቻ አይደለም፤ ከሌሎች የሚመጣላትንም ጭምር ነው፡፡ ይህም ተጨማሪ ምግብ እንድትመገብና ሰውነቷ እንዲጠገንና ጤነኛ እንድትሆን ያግዛታል፤ በተለይ ደግሞ አቅም የሌላት ከሆነች፣ እቤቷ ያላዘጋጀቸው የምግብ አይነት ከዘመድና ከጎረቤት ይመጣላታል፡፡ ስለዚህ ከቤቷ የምታጣውን የምግብ አይነት እንድታገኝ በማድረጉ በኩል እገዛ አለው፤ በአካላዊ ጥንካሬዋ በኩልም ጠንካራ እንድትሆን ያደርጋታል፡፡ ስለዚህ ግለሰባዊ ጠቀሜታ ይኖረዋል ማለት ነው፡፡ አካልን ከማጠናከር በተጨማሪ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳም አለው፡፡ በመተሳሰብና በመጠያየቅ በኩል ደግሞ አራሷ ‹‹ማን ነው የጠየቀኝ? ማን ነው ያልጠየቀኝ?›› ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ታገኝበታለች፤ አሳቢዎቿንና የማያስቡላትን ትለያለች፤ ከጠየቋት ጋር ትስስሯን ታጠብቃለች፣ ካልጠየቋት ጋር ደግሞ ታላላለች፡፡ ይህ መልካምና መጥፎ እይታ የሚፈጠረው ደግሞ በእርሷ እና በጠያቂዎቿ መካከል ብቻ ሳይሆን በቤተሰቦቿም ጭምር ነው፡፡ ስለዚህ ምግብ ይዞ አራስን መጠየቅ ቤተሰባዊ ትስስርን የማጥበቅ ፋይዳ አለው፡፡

በዋግ ኽምራ የሚያውቋትንም ሆነ የማያውቋትን አራስ፣ የማርያም አራስ ናት ብሎ መጠየቅ የተዘወተረ ነው፡፡ ይህም በማህበረሰቡ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ከመሆኑም በላይ በሃይማኖት በኩልም ጠቀሜታው ላቅ ያለ ነው፡፡ ‹‹መልካም ነገር ሰርቻለሁ፡፡›› በማለት ስነ-ልቦናዊ እርካታ ያስገኛል፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድም አንዲት ሴትን ‹‹እከሌ ህብታም ድሃ ሳትል የምትጠይቅ ናት›› ተብላ ማህበረሰባዊ አክብሮትን እንድትቸር ያደርጋል፣ በሃይማኖት አባቶች በኩልም በአርአያነት ያስጠቅሳታል፡፡ እሷም በማህበረሰቡ ዘንድ በአርአያነት በመጠቀሷ ደስተኛ ትሆናለች፡፡

በክርስትና ወቅትም የህጻኑ ወላጆች የቅርብ ቤተሰቦች ለድግስ የሚሆን መጠጥና እንጀራ፣ ሌሎች የድግሱ ታዳሚዎች ደግሞ ዱቄት ይዘው መሄዳቸው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አለው፤ ደጋሾቹ ብዙ ወጭ እንዳያወጡ ይረዳቸዋል፡፡ የመተጋገዝ ባህላቸውንም ያዳብራል፡፡ ከዚህም ሌላ ልክ እንደ የሠርግድግስ ሁሉ በክርስትና ድግስም ቤተሰብና ጎረቤት የጉልበት

እገዛና የቁሳቁስ አቅርቦት ያደርጋል፡፡ ይህም ለደጋሾቹ ከሚኖረው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ሌላ የማህበረሰቡን የእርስ በእርስ መተሳሰብና መተጋገዝ የሚያጠናክር ነው፡፡ አንድ ወላጅ ልጁን ክርስትና ማስነሳቱም እንደ የእምነት ተከታይነቱ፣ ከእምነቱ ተከታዮች ጋር የሚኖረውን ቁርኝትና አንድነት ያጠናክራል፡፡ ማህበረሰቡ ከእርሱ የሚጠብቀውን ድርጊት እንዲያከናውን ያደርገዋል፤ የሚከተለውን የሃይማኖት ትእዛዝ እንደሚያከብርና የሚጠበቅበትን እንደሚያከናውን ማሳወቂያና ማረጋገጫም ይሆንለታል፡፡ በዚህም ድርጊቱ ግለሰባዊና ማህበራዊ ጠቀሜታን ለግሷል፡፡ ምክንያቱም ማህበረሰብ የግለሰቦች ስብስብ ነውና የግለሰብ መልካም ድርጊት ለማህበረሰቡም በመልካም ድርጊትነት የሚጠቀስ ነው፡፡

በቅድመ-ወሊድ፣ ወሊድና ድህረ ወሊድ ወቅት የሚከናወኑ ነገሮችን ነፍሰ-ጡሯ ሴትም ሆነች አራሷ ብቻዋን አታከናውናቸውም፡፡ በክዋኔዎቹ ላይ የቅርብ ዘመድና ጎረቤት የሆኑ ሴቶች አልፎ አልፎም ወንዶችም ይሳተፋሉ፤ በወሊድ ሥነ-ሥርዓት በሚከናወኑ ተግባራት ላይ ዘመድ የሆኑት ሴቶችም ሆኑ ጎረቤቶች የሚያከናውኗቸው ተግባራት የሌላ ሰው ናቸው ብለው በዋዛ ፈዛዛ የሚመለከቷቸው አይደሉም፤ እንደ እራሳቸው ቤት ስራ በባለቤትነት የሚያከናውኗቸው ናቸው፡፡ ይህም የእኔነት ስሜትን የማጠናከር ፋይዳ አለው፡፡ ስለዚህ ከወሊድ ሥነ-ሥርዓት አንዱ ፋይዳ ሰዎች እንዲሰባሰቡ ማድረግ ስለሆነ፤ ማህበራዊ ተጠቃሎነትንም ፈጥሯል፡፡

ወሊድ ከመከናወኑ በፊት የነፍሰ-ጡር ሴት ከተለያዩ ማህበራዊ ስራዎች እንድትታቀብ የሚደረገው በእሷ እውቀትና ፈቃደኝነት ብቻ አይደለም፡፡ የማህበረሰቡ አባላትም ‹‹ይህን ስሪ፤ ይህንን አትስሪ፤ ይህንን ተመገቢ ይህንን አትመገቢ፡፡›› እያሉ ይገልጹላታል፡፡ እንዲህ እያሉ የሚመክሯትና የሚገልጹላትም ከትውልድ ትውልድ ሲሸጋገር የመጣላቸውንና የሚያውቁትን ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ድርጊት ነባሩ ማህበራዊ ክዋኔ ወደ መጪው ትውልድ እየተሸጋገረ ቀጣይነትና ተቀባይነት እንዲኖረው ያደርጋልና በማህበራዊ እሴትነት አገልግሏል፡፡

ሌላው በፋይዳዊነት የሚጠቀሰው የአራስ ሴት ልብስ አጠባ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደ ተጠቀሰው በአራስ ሴት የልብስ አጠባ ወቅት የሴቶች ተሳትፎ የተለያየ ነው፡፡ በሶስተኛው ቀን የአራሷ የቅርብ ዘመዶች ደም የነካውን የአራሷን ልብስ ባለመጠየፍ ማጠባቸው ቤተሰባዊ ቀረቤታቸውን የሚያመለክት ነው፡፡ በሰባተኛው ቀን ሌሎች ሴቶች ደግሞ

ቅዝቃዜው ሳይበግራቸው በሌሊት ተነስተው ወደ ወንዝ ወርደው ማጠባቸው፣ መተሳሰባቸውን የሚያሳይ ነው፤ የእርስ በእርስ ግንኙነታቸውንም ያጠናክርላቸዋል፡፡

በቅድመ ወሊድ፣ ጊዜ ወሊድና ድህረ-ወሊድ ወቅት ከሚከናወኑት ድርጊቶች መካከል ከመንፈስ ጋር የተያያዙም ይገኙበታል፡፡ ለአብነት ያህል ቀደም ሲል እንደተመለከትነው አራስ ሴትና የአራስ ሴት ልብስን የሚያጥቡ ሴቶች ከእርኩስ መንፈስ እንዲከላከልላቸው ብረት ነገር ካጠገባቸው ያስቀምጣሉ፤ ይይዛሉ፤ እነዚህን ብረት ነክ ነገሮች ከአንዳች ዓይነት እርኩስ መንፈስ የሚከላከሉ አድርጎ ማመን ደግሞ፣ እራስን ከመንፈስ ጋር የማያያዝ ፋይዳ እንዳለው እንረዳለን፡፡

በመጀመሪያ የምትወልድ ሴትም ከሌጣነት ወደ ሁለት እራስነት፣ ከልጅ አልባነት ወደ ባለ ልጅነት ትሸጋገራለች፡፡ ከመወለዱ በፊት ብቸኛ የነበሩት ባልና ሚስት የቤተሰብ አባል በመጨመር አዲስ ቤተሰባዊ ህይወት መምራት ይጀምራሉ፡፡ ስለዚህ ቤተሰብ ካላቸው ሰዎች ጋር እኩል በመሆናቸው ሥነ-ሥርዓቱ ማህበረሰቡን ወደ እራሳቸው የማያያዝ ፋይዳ አለው፡፡

ከዚህም ሌላ ወሊድ፣ ወላዷን ሴት በባሏ ቤተሰቦች (በአማቾቿ) ዘንድ አክብሮትና ተቀባይነት እንዲኖራትም ያደርጋታል፤ በዚህም ባለመውለዷ ምክንያት የሚከሰቱ ለሰላማዊ ህይወት እንቅፋት የሚሆኑ ድርጊቶችን ያስወግዳል፤ ጋብቻዋም የሰመረ ይሆናል፤ ምክንያቱም ልጅ በመኖሩ ምክንያት ትዳራቸው ይጠብቃል እንጂ አይላላም፡፡ በባልና ሚስት መካከል አለመግባባት ቢፈጠር እንኳ በመካከላቸው ልጅ ስላለ በአካባቢውም ‹‹ልጅ ማገሩ›› ስለሚባል ችግራቸውን በውይይትና በሽምግልና ፈትተው ሰላም በመፍጠር ልጃቸውን በጋራ ያሳድጋሉ፡፡ ይህም በፍች ምክንያት የሚከሰቱ የተለያዩ ማህበራዊ ችግሮች እንዳይፈጠሩ ያደርጋል፡፡

ሴቷ ባትወልድ ግን በባሏ ቤተሰቦችም ሆነ በሌሎች ሰዎች የሚኖራት ተቀባይነት ዝቅተኛ ነው፡፡ ባልና ሚስት ተጋብተው ለመውለድ ቢዘገዩና ችግሩ የባሏ ሊሆን ቢችልም እንኳ የሴቷ ብቻ እንደ ሆነ በመገመት፣ በአካባቢው ልጅ እንዲወለድ ያደርጋሉ ተብለው ወደሚታመንባቸው ታቦታት ሄዳ ወንጌል የምታዝለው ወይም የምትጸበለው ሴቷ ብቻ ናት፡፡ ከዚህም ሌላ ወደ ቤተክርስቲያን እየሄደችም ‹‹ምነው የድንግል ማርያምን መንገድ

አላሳየኝ አልክ? (ልጅ አልሰጠኸኝ) ከጓደኞቼ በታች አደረግኸኝ? እባክህ ማህጸኔን አርጥበው ? (ልጅ ስጠኝ)›› እያለች ለአምላኳ ምሬቷን ትገልጻለች፤ ከአምላኳ ጋርም በሃዘን ስሜት ትገናኛለች፡፡ ልጅ እንዲሰጣትም ትማጸናለች፤ በዚህ ሁኔታ ላይ እያለች ልጅ ካላት ሴት ጋር ከተጣላችም፣ ‹‹አንቺ በቅሎ፡፡›› ተብላም ትሰደባለች፡፡ በዚህ ጊዜ መጥፎ ስሜት ውስጥ ገብታ ልትደባደብና በተሳዳቢዋ ላይ ችግር ልታደርስ ወይም በእሷ ላይ ችግር ሊደርስባት ይችላል፤ ይህም የሚያሳየው ባለመውለዷ ምክንያት የሚደርስባት የስነ-ልቦና እና ማህበራዊ ችግር መኖሩን ነው፡፡ በአንጻሩ የወለደች ከሆነች ግን ‹‹ተመስገን! የሰጠኸኝን ባርከህ ቀድሰህ ስጠኝ፡፡›› በማለት ከአምላኳ ጋር በደስታና በምስጋና ትገናኛለች፡፡ ምሬትም አይሰማባትም፡፡ በዚህ ምክንያት ሲጋቡ ‹‹ውለዱ ክበዱ!›› ተብለው የተመረቁ ባልና ሚስቶች፣ ሲወልዱና ወላጅ ሲሆኑ፣ በቤተሰቦቻቸውም ሆነ በሌላው የማህበረሰብ ክፍል ዘንድ የሚሰጣቸው ግምት፣ አክብሮትና ቦታ ላቅ ያለ ነው፡፡

በቅድመ ወሊድ፣ ጊዜ ወሊድና ድህረ-ወሊድ ወቅት በማህበረሰቡ የሚከናወኑት ተግባራት፣ ከጊዜ ሂደት ጋር መለወጣቸው ባይቀርም፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገሩ ናቸው፡፡ የሚሻገሩትም ‹‹እንዲህ አድርጉ እንዲህ አታድርጉ፡፡›› የሚል በጽሁፍ ሰፍሮ የሚገኝ ሳይሆን ወጣቶቹና ህጻናቱ ድርጊቱ ሲፈጸም በምልከታ ከሚያገኙት እውቀት እና በቃል ከሚተላለፍላቸው በመረዳት ነው፡፡ ስለዚህ አዲሱ ትውልድ በወሊድ ሥነ-ሥርዓት ሊከናወኑ የሚገባቸውንና የማይገባቸውን ለይቶ ያውቃል፤ በዚህም ሥነ-ሥርዓቱ በማህበረሰቡ፣ለማህበረሰቡ፣ ስለማህበረሰቡ፣ ከማህበረሰቡ ጋር ለመማማሪያነትም ያገለግላል፤ ክዋኔዎቹ የሚከናወኑባቸው ቦታዎችም፣ ለአብነት ያህል ልብስ የሚታጠብባቸው ወንዞችና ለወንድና ለሴት ህጻናት በተምሳሌትነት የሚያገለግሉ እቃዎች የሚሰሩባቸው ቦታዎች፣ ለሌሎች በመማሪያ ቦታነት ያገለግላሉ፡፡ እነዚህን እቃዎች ከተለያዩ ቅጠላ ቅጠሎችና ስራ ስሮች የሚሰሩት ወይም የሚያዘጋጁት ሰዎችም የፈጠራ ችሎታቸውን ለማሳደግ ያስችላቸዋል፡፡

አሰያየምንም ከፋይዳዊነት አንጻር መመልከት ይቻላል፡፡ ቀደም ሲል እንደተመለከትነው የሚች ቤተሰብን ስም ለልጅ መስጠትም ማህበራዊ ትስስርን የሚያጠናክር ነው፡፡ ምክንያቱም የሚች ወገኖች ያንን ስም በሚሰሙበት ወቅት፣የሚችን ማንነት ከማስታወሳቸውም በላይ፣ ያንን ስም ለልጁ የሰጠው ወላጅም፣ ለዝምድና ያበረከተው

አንዳች አስተዋጽኦ መኖሩን በመረዳት፣ በሌሎች የቤተሰቡ አባላት በኩል ትኩረትና ተቀባይነትን ያገኛል፡፡ የተሰጠው ስምም ማን ማንን እንደ ወለደ ለማወቅ ለሚፈልግ ሁሉ በማጣቀሻነት ያገለግላል፤ የዝምድናውን እርቀትና ቅርበትም ያሳውቃል፤ በዚህም ቤተሰባዊ ትስስሩን ያጠናክራል፡፡

በጥቅሉ በቅድመ ወሊድ፣ በወሊድና ድህረ ወሊድ ሥነ-ሥርዓት ወቅት በተናጠልም ሆነ በቡድን ከሚከናወኑት ተግባራትና ቁሳቁሶች መካከል ተምሳሌታዊ የሆኑ መኖራቸውን፣ የድርጊቱ ተሳታፊዎችም በደረጃ የሚሸጋገሩ መሆናቸውን እንረዳለን፤ ከዚህም በተጨማሪ ግለሰባዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ከመስጠታቸውም ሌላ የማህበረሰቡ ማንነት እንዲንጸባረቅና እንዲጠበቅ ያደርጋሉ፤ ማህበራዊ ትስስርን ይፈጥራሉ፤ የማህበረሰቡን አንድነት በማጠናከርም ማህበረሰቡ ቀጣይነት እንዲኖረውና ህያው እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡

## 7.2 የጋብቻ ሥነ-ሥርዓት ትንተና

### 7.2.1 ከተምሳሌታዊነት አንጻር

በጋብቻ ሥነ-ሥርዓት ውስጥ ከሚታዩ ተምሳሌታዊ ድርጊቶችና ቁሳቁሶች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

ለእጮኝነት ወደ ሴቷ ቤት የሚሄዱት ሰዎች መጠን ሶስት ነው፡፡ ለምን ሶስት ሆነ? ለሚለው፣ ከመረጃ አቀባዮቼ መካከል አቶ ተበጀ በላይ ሲነግሩኝ፣ ስላሴዎች ሶስት ስለሆኑ ነው ብለዋል (ቃ.የ.መ.አ.4)፡፡ ስለዚህ ሶስቱ ሽማግሌዎች የሶስቱ ስላሴዎች ተምሳሌት ናቸው፡፡ እነዚህ ሽማግሌዎች ወደ ሴቷ ቤተሰብ ቤት በመግባት ለሴቷ ቤተሰቦች ሰላምታ የሚያቀርቡትም ሶስት ጊዜ ነው፡፡ ሶስት ጊዜ ሰላምታ መስጠትም ቀደም ሲል የተጠቀሰው የሶስቱ ስላሴዎች ተምሳሌት ነው፡፡ ሽማግሌዎች የሴት ቤተሰቦችን ሲጠይቁም‹‹ ከበረታችሁና ከፍጋችሁ ልንወድቅ ብለን መጣን›› ይላሉ፡፡ በረትና ፍግ የሴት ወገን ሃብት ከወንድ ወገን ሃብት ጋር የመቀላቀል እንዲሁም አንድ የመሆን የቤተሰብነት ተምሳሌቶች ናቸው፡፡

የወደፊት ሙሽራዎች የሠርግ ቀናቸው ከተቆረጠ በኋላ ሴቷ ክንዷ ላይ ድኮት ታደርጋለች፤ ወንዱ ደግሞ የብረት ዘንግ ይይዛል፤ ድኮትና የብረት ዘንግ ከእርኩስ

መንፈስ የሚከላከል ሃይል ተምሳሌቶች ናቸው፡፡ በሠርጓ እለት ሙሽራዋን የምታስውባት ባንድ ባል የጸናች ወይም ድንግል የሆነች ሴት ናት፡፡ ምክንያቱም ይህች ሴት ሙሽራዋም እንደ እሷ ሁሉ ባንድ ባል ጸንታ የመኖሯና ድንግልናዋን የመጠበቋ ተምሳሌት ናት፡፡

ወደ ሴቷ ቤትም ሆነ ወደ የክርስትና እናቷ ቤት የሚሳበው ሙክት ምንም እንከን የሌለው፣ ከጆሮው ቆራጣ የሌለበት፣ የቅቤ ማሰሮዋም ምንም ሽራፋ የሌላት፣ ማንጠልጠያዋ ጠፍርም ቋጠሮ የሌለባት ወጥ እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡ እንዲህ እንዲሆኑ መፈለጋቸው፣ ጋብቻው የሰመረ የመሆን ምኞት ተምሳሌቶች ተደርገው ስለሚታመኑ ነው፡፡ ሙክቱ ጥቁርና ከጆሮው ቆራጣ ያለው፤ ማሰሮዋ ሽራፋ፣ ማንጠልጠያዋም ተበጥሳ የተቋጠረች ከሆኑ ግን፣ ሙሽራዎቹ ወደ ፊት በጋብቻቸው ላይ ችግር የማጋጠማቸው፣ ለፍች የመዳረጋቸው ተምሳሌቶች ይሆናሉና ሙክትና ማሰር ቅቤ ሳኪው በእነዚህ ነገሮች ላይ ጥንቃቄ ያደርጋል፡፡

የሠርጉ ታዳሚዎች ለደጋሹ የሚሰጡት ብር የሚሰበሰበው እንጀራ ተደርጎበት በተባረከ አገልግል ወይም መሶብ ነው፡፡ እንጀራው ወደ ፊት የሚሰባሰበው ብር ብዙ እና በረከት ያለው እንዲሆን የሚያመለክት ተምሳሌት ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ የሠርግ ዳስ ሙሉ በሙሉ በደደሆ ቅጠል ባይሰራም ዳሱ እርጥብ ቅጠል ጣል ይደረግበታል፡፡ እርጥቡ ቅጠል የተጋቢዎቹን ጋብቻ መልካምነት የሚያመለክት ተምሳሌት ነው፡፡ ዳሱ ሲሰራም ሆነ ሲፈርስ ንፍሮ እንጂ ቆሎ አይቀርብም፤ ምክንያቱም ንፍሮ እርጥብ በመሆኑ የመልካም ገድ ቆሎ ደግሞ ደረቅ በመሆኑ የመጥፎ ገድ ተምሳሌቶች ናቸው፡፡ በውሃ የተሞላ እንስራ እንጂ ባዶ እንስራ የተሸከመች ሴት ሙሽራዎችን ማቋረጥ የለባትም፡፡ ምክንያቱም የተሞላ እንስራ ለጋብቻው የመልካም ገድ፣ ባዶ እንስራ ደግሞ የመጥፎ ገድ ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

በሠርግ ከወንድ ወገን ለሴቷ ሙሽራ ከሚወሰዱ ነገሮች መካከል ያልተሰፋ አዲስ ጨርቅና ማር ይገኙበታል፡፡ ጨርቁም ሙሽራዋ ያልተነካችና ክብረ-ንጽህናዋን የጠበቀች የመሆኗ ተምሳሌት ነው፡፡ ማሩ ደግሞ ጣፋጭ ነውና የመልካም ጋብቻ ተምሳሌት ነው፡፡

በሴቷ ሙሽራ ዳስ ውስጥ ትልቅና ትንሽ ሚዜዎች የወንድ ወገንን በመወከል፣ የሴት ወገን ወንድ ሽማግሌዎችን እየተመለከቱ፣ ሶስት ጊዜ ‹‹ሸኙን ሸኙን›› ይላሉ፤ የሴት ወገንም ሶስት ጊዜ መልስ ይሰጣል፡፡ ሶስት ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው የሶስቱ ስላሴዎች ተምሳሌት ነው፤ ከዚህም ሌላ ሶስት፣ የሶስት ጉልቻ ወይም የትዳር ተምሳሌትም ይሆናል፡፡

በሴቷ ዳስ ውስጥ አማጭ ስጦታ እንዲሰጠው የሚጠይቀው ‹‹አባይንና ጣናን ያገናኘሁ፡፡ ጠጅና ውሃን ያገናኘሁ›› በማለት ነው፡፡ አባይና ጣና እና ጠጅና ውሃ፣ የባልና ሚስት ቤተሰቦች ተምሳሌቶች ናቸው፡፡ የሴት ወገን ለወንድ ወገን የሚሰጠውን ማጫ እና ስጦታ ካጠናቀቀ በኋላ፣ ብሩን በጨርቁ ሰብስቦ የያዘው ሚዜ የወንድ ወገን ወደ ተቀመጠበት ቦታ እንዲቀላቀልና ብሩን ለወንድ ዘመድ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ በዚህ ጊዜ ሌላዎቹ ሚዜዎች ብሩን የያዘውን ሚዜ ‹‹መጭ መጭ›› ይላሉ፤ ይህም ከባድ ሸክም የተሸከመች በቅሎ ተምሳሌት ተደርጎ ብዙ ብር እንደተሰጣቸው መግለጽ ነው፡፡

በሴቷ ሙሽራ ዳስ ውስጥ ሙሽራዎቹን የምታቃምሳቸውም የቄስ ሚስት ወይም በመጀመሪያ ባሏ (በአሚን ባሏ) የጸናች ሴት ናት፡፡ ይህች ሴት ሙሽራዎቹም ባንድ ባልና ሚስት ጸንተው የመኖር ተምሳሌት ናት፡፡

የሙሽራዎቹ ጋብቻ የሚጸናው ሰማንያ ተፈጽሞ ነው፡፡ ለዚህም በሴቷ እና በወንዱ በኩል አንዳንድ የዳስ አባቶች በሁለት እጆቻቸው በፎሌ የሞላ ጠላ ይዘው ‹‹ሰጠሁ፤ ተቀበልሁ›› ይላሉ፡፡ ሁለቱ የዳስ አባቶች በሁለት በሁለት ፎሌ የሞላ ጠላ መያዛቸውም ሁለት የባልና የሚስቱ፣ በጠላ የሞላው ሽክናም ጋብቻው የተሳካና ወደፊት እንከን የማይገጥመው የመሆን ተምሳሌቶች ናቸው፡፡

የሙሽራዎቹ ጋብቻ ጧፍ በማብራት በካህን ይባረካል፤ ከዚህ የምንረዳው የጧፍ ብርሃን የጋብቻውን አስደሳችነትና ሙሽራዎቹ በጨለማ ከሚመሰለው ብቸኝነት ወደ በብርሃን የሚመሰለው ጋብቻ መሸጋገራቸውንና መጣመራቸውን የሚያመለክት የመልካም ጋብቻ ተምሳሌት መሆኑን ነው፡፡

የወንድ ወገን ከሴት ወገን ማጫ እና ስጦታ ከተሰጣቸው በኋላ ‹‹ጠገብነ ጠገብነ›› ይላሉ፡፡ የተሰጠን አርክቶናል ብዙ ነው ማለት ነው፡፡ ከዚህ አገላለጽ የምንረዳው ለወንድ ወገን የተሰጠው የገንዘብ መጠን ሊያጠግብ የሚችል ምግብ ተምሳሌት መሆኑን ነው፡፡ ሙሽራዋ

ወደ ወንዱ ቤት ስትሄድ ፊቷን በጥቁር ሻሽ ትሸፍናለች፤ ጥቁሩ ሻሽ ከቤተሰቧ ተለይታ በመሄዷ የማዘኗ ተምሳሌት ነው፡፡

ከሴቷ ሙሽራ ወደ ወንድ ቤት የሚወሰደውን አዝመራ እንዲሰጣቸው የሚጠይቁት ሴቶች እንጂ ወንዶች አይደሉም፤ ምክንያቱም አዝመራ ይዞ የሚሄደው ወንዱ ሲሆን የሚወስደውም ከሴቷ ቤት ነው፡፡ ስለዚህ አዝመራ የሃብት፣ የመልካም ገድ ወይም ጥሩ ምርት የሚሰበሰብበት ወቅት ተምሳሌት ነው፡፡ ሙሽራዎቹ ወደ ወንዱ ቤት ሲሄዱ ብዙ ወንዝ ቢሻገሩም በመጀመሪያው ወንዝ ጫጩት ያርዳሉ፤ የጫጩት ደም ሙሽራዎችን ለአደጋ የሚዳርጋቸውን መንፈስ የሚከላከል ሃይል ተምሳሌት ነው፡፡ ሙሽራዎቹ ወደ ወንዱ ቤት እንደገቡ በአንዳንድ አካባቢ የቤቱን ምሰሶ ይዘው ‹‹እልል›› ይላሉ፡፡ ምሰሶው የትዳር ተምሳሌት ሲሆን ሁለቱም ይዘውት በእልልታ መታጀባቸው በትዳራቸው ጸንተው ባንድ ላይ በደስታ የመኖራቸው ተምሳሌት ነው፡፡

በወንድ ሙሽራ ቤት ለሙሽራዎች የሚወሰድ ምግብ በኽምጣኘ አስኹር የአማርኛ ትርጉም እንኩ ልጅ ይባላል፡፡ ይህ ምግብ ስያሜው እንደሚያመለክተው ሙሽራዎቹ ወደ ፊት ልጅ ወልደው የመሳም መልካም ምኞት ተምሳሌት ነው፡፡

### 7.2.2 ከመዋቅራዊ-ፋይዳዊነት አንጻር

የጋብቻ ሥነ-ሥርዓትን ከመዋቅራዊ-ፋይዳዊነት አንጻር ለመተንተን የተመለከትኩት ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው ከመዋቅራዊነትና ከፋይዳዊነት አንጻር ነው፡፡ በመጀመሪያም ከመዋቅራዊነት አንጻር እተነትናለሁ፡፡

በምዕራፍ ሶስት ክለሳ ድርሳን ላይ  በንድፈ-ሃሳብ ቅኝት እንደገለጽኩት፤ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት እንደ የሽግግር ሥነ-ሥርዓት አይነትነቱ መዋቅር እንዲሁም ለግለሰብም ሆነ ለማህበረሰብ የሚፈይደው ነገር አለ፡፡ይህንንም እንደሚከተለው አንድ ባንድ ተመልክቼዋለሁ፡፡

### 7.2.2.1. ከመዋቅራዊነት አንጻር

የጋብቻን ሥነ-ሥርዓት መዋቅር በምመለከትበት ወቅት ትኩረት ያደረግሁት በተጋቢዎቹ ላይ ነው፡፡ ተጋቢዎቹ የሠርግ ቀናቸው ከተቆረጠ በኋላ ከጓደኞቻቸው ይለያሉ፡፡ ከዘወትር ተግባራቸውና እንቅስቃሴያቸውም ይታቀባሉ፡፡ ብቻቸውንም አይንቀሳቀሱም፤ እሩቅ መንገድም አይጓዙም፡፡ ስለዚህ በዚህ ወቅት ላይ ሲሆኑ በመለየት ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡ ጋብቻቸውን መስርተው ከተጋቡ ሰዎች የማህበረሰብ ክፍል ጋር ገና ባለመቀላቀላቸውም በመካከለኛ ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡ ስለዚህ ሁለቱ የወደፊት ተጋቢዎች በዚህ መዋቅር ላይ በሚገኙበት ወቅት ጋብቻ ካልመሰረቱት ጓደኞቻቸው ወይም ትዳር ከመሰረቱት ሰዎች ምድብ አይደሉም፤ መሃል ናቸው፤ ከመዋቅር አንጻር ይህ ደረጃ የሽግግር ደረጃ ነውና በሽግግር መካከለኛ ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡

የሠርግ ድግስ ተደግሶ ከሁለቱም ወገን በተመረጡ የጋብቻ ወይም የሰማንያ ውል አስፈጻሚዎች አማካይነት በባህላዊ መንገድ ጋብቻቸውን መስርተው፣ ከሁለትነት ወደ አንድነት ይጣመራሉ፤ በዚህ ወቅት ወደ ባለ ትዳርነት ይሸጋገራሉ፡፡ ስለዚህ ይህ ደረጃ የመቀላቀል ደረጃ ነው፡፡ ምክንያቱም ከተጋቡ ሰዎች የማህበረሰብ ክፍል ተቀላቅለዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለተወሰኑ ቀናት ቢሆንም በጫጉላ ቤት በሚቆዩበት ወቅት ጋብቻቸውን መስርተው ጎጆ ከወጡ ባለትዳሮች ጋር ገና አልተቀላቀሉምና በመካከለኛ ደረጃ ይሆናሉ፡፡ ስለዚህ ጫጉላ ቤት የሙሽራዎቹ የመሸጋገሪያ ቦታ ነው ማለት ነው፡፡

ሙሽራዎቹ ጎጆ የሚወጡት በአብዛኛው በወንዱ ቤተሰቦች አካባቢ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ሙሽራዋ ከቤተሰቦቿ ተለይታለችና በመለየት ደረጃ ላይ ትገኛለች፡፡ ባልና ሚስት ጎጆ እስከሚወጡ ድረስ ከወንዱ ቤተሰቦች ጋር ይኖራሉ፤ የራሳቸው ቤት የላቸውም፣ ተድረው ጎጆ ከወጡ ሌሎች ባለትዳሮች ምድብ አልተመደቡም ወይም አልተቀላቀሉምና በመካከለኛ ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡ ጎጆ በሚወጡበትና እራሳቸውን ችለው ቤታቸውን ማስተዳደር በሚጀምሩበት ወቅት ግን ወደ ሌላ የህይወት ደረጃ ይሸጋገራሉ፡፡ በቤተሰብ አስተዳዳሪነት ከመኖር በግል ወደ ማስተዳደር ያመራሉ፡፡ ስለዚህ በዚህ ወቅት ጎጆ ከወጡ ባለትዳሮች ጋር ይቀላቀላሉና በመቀላቀል ደረጃ ላይ ይሆናሉ፡፡

ከመዋቅር አንጻር የሚታዩት ሌላዎቹ ወላጆች ናቸው፤ ምክንያቱም ልጆቻቸው በመለየት ደረጃ ላይ ሲሆኑ እነሱም ልጆቻቸውን ካልዳሩት ሰዎች ይለያሉ፣ ሲዳሩ እነሱም ልጆቻቸውን ከዳሩት ሰዎች ጋር ይቀላቀላሉ፤ ልጆቻቸው በሽግግር ደረጃ ሲሆኑ እነሱም በሽግግር ደረጃ ላይ ይሆናሉ፡፡ በወሊድ ሥነ-ሥርዓት እንደተገለጸው ልጆቻቸው ሲወልዱ እነሱ ደግሞ ወደ አያትነት ይሸጋገራሉ፤ ከሌሎች አያቶች ምድባ ጋር ይቀላቀላሉ፡፡

### 7.2.2.2 ከፋይዳዊነት አንጻር

የጋብቻን ሥነ-ሥርዓት ከፋይዳዊነት አንጻር ስመለከት በግንባር ቀደምትነት የሚገለጸው ሁለት ሰዎችን ወደ አንድነት አምጥቶ ህይወታቸውን በጋራ እንዲመሩ ማስቻሉ ነው፡፡ ይህም በግለሰብም ሆነ በማህበረሰብ ደረጃ ፋይዳው ላቅ ያለ ነው፡፡ በግለሰብ ደረጃ ኑሮን በተናጠል መምራት በሚያስቸግርበት በተለይ በገጠር፣ ባልና ሚስት ተባብረውና ተሳስበው መኖር እንዲችሉ ያደርጋል፡፡ ይህም ግለሰቦች ማህበረሰቡ ወደ ማይፈልጋቸው ስራዎች ለአብነት ያህል ሴተኛ አዳሪነት እንዳያመሩና ሰላማዊና የተረጋጋ ህይወት እንዲኖሩ ያደርጋል፡፡ በዚህም ለማህበረሰቡ ሰላማዊ ህይወት አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለማህበረሰብ መሰረቱ ቤተሰብ ነውና የተጋቡ ሰዎች ወልደው ቤተሰብ በሚመሰርቱበት ወቅት የማህበረሰቡን አባላት በመጨመር፣ በሞት የሚለዩትንም በመተካት ቀጣይ የሆነ የማህበረሰብ ክፍል እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ የማህበረሰቡንም ህልውና ያረጋግጣል፡፡

ለእጮኝነት ረዥም ጊዜ መሰጠቱና ከጋብቻ በፊት የወደፊት ተጋቢዎችን ቤተሰቦች ማንነት ሁኔታ ማጣራትም በፋይዳዊነት የሚጠቀስ ነው፡፡ የወደፊት ተጋቢ ቤተሰቦች ማንነታቸው አስቀድሞ ይፈትሻል፤ በመካከላቸው ጋብቻቸውን የሚከለክል ጥል ካለም በሽማግሌዎች አማካይነት እርቅ እንዲወርድ ይደረጋል፤ ጥላቻቸውን እያነሱ እየጣሉ ወደ ፊትም ለሌላ ጥል ከመነሳሳት እንዲቆጠቡ ያደርጋል፤ ሰላማዊ ህይወት እንዲኖሩም ያስችላል፡፡ ለዚህም ለአማጭነት ወደ ሴቷ ቤተሰቦች ቤት የሚላኩት ሰዎች በማህበረሰቡ ዘንድ የተከበሩና ቢናገሩ የሚደመጡ መሆናቸው፣ ጥል ያለባቸውን ከፍ ሲልም ደም የተቃቡ ሰዎችን በማስታረቅ፣ በጋብቻ እንዲተሳሰሩና ጋብቻውንም ለደም ማድረቂያነት እንዲውል ለማድረግ ነው፤ ይህም ግለሰባዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ፋይዳ አለው፡፡

በሙሽራዋ ዳስ ውስጥ ከሚከናወኑት ድርጊቶች መካከል የማጫ እና የስጦታ ስርዓት ይገኝበታል፡፡ ማጫ ለሙሽራዎቹ መተዳደሪያ እንዲሆን ከሁለቱ ቤተሰቦች በገንዘብ ወይም በአይነት መልክ የሚሰጥ ነው፡፡ ይህም ኢኮኖሚን ከቤተሰብ ወደ ልጆች በማሸጋገር ልጆች መተዳደሪያ እንዲኖራቸውና እራሳቸውን እንዲችሉ ያደርጋል፡፡

የማጫው መጠን በተጋቢ ቤተሰቦች አቅምና መተሳሰብ ላይ የተመረኮዘ መሆኑ ደግሞ የተጋቢ ቤተሰቦች ወደፊት በሚኖራቸው የመተጋገዝና የመረዳዳት ስራ ላይ የሚጫወተው ሚና ይኖራል፡፡ ተጋቢዎችም አንዱ ከፍ አንዱ ዝቅ ሳይልና ሳይናናቁ በተመሳሳይ ወይም በተቀራራቢ የኑሮ ደረጃ ላይ ኑሯቸውን እንዲቀጥሉ ያደርጋል፡፡

ስጦታ ደግሞ ቀደም ሲል ጋብቻው እንዲሳካ ላደረጉና ወደ ፊትም ሙሽራዎቹ በጋብቻቸው ጸንተው እንዲኖሩ ያስደርጋሉ ተብለው ለሚታሰቡ አካላት የሚሰጥ የምስጋና ወይም የማበረታቻ አይነት ነው፡፡ ስለዚህ በአንድ ሠርግ ላይ ስጦታ የሚሰጣቸው አካላት ልፋትና ድካማቸው ግምት ውስጥ ገብቷልና ወደፊትም ተበረታትተው ተመሳሳይ ተግባራቸውን እንዲፈጽሙ ያደርጋቸዋል፡፡ ለአብነት ያህል በሴትና በወንድ ወገን ስጦታ ከሚሰጣቸው አካላት መካከል አንዱ አማጭ ነው፡፡ አማጭ የትዳር መሰረት ነው ማለት ይቻላል፡፡ አሁን አሁን የአማጭን ላይ ታች ባይነትና ውጣ ውረድ በመረዳት የሴትና የወንድ ወገን ቀደም ሲል ከነበረው በዛ ያለ ገንዘብ ይሰጣቸዋል፡፡ ይህም አማጮች የልፋታቸውን ዋጋ እንደሚያገኙ ስለሚያረጋግጥ፣ ወደ ፊት አማጭ እንዲሆኑ የሚጠየቁ ሰዎችም የስራውን አስቼጋሪነት በመፍራት እምቢተኛ እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ስሬል ላይ በነበረው ሠርግ ሁለት መቶ ብር የተሰጣቸውን አማጭ በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ የአማጭ ስጦታ በቅርብ ጊዜ የተጀመረ ሳይሆን በማህበረሰቡ ዘንድ የቆየ በመሆኑ፤ ከትውልድ ትውልድ እየተሸጋገረ የመጣውን ወግና ባህል ጠብቆ ለማቆየት ያገለግላልና የስርዓቱን ቀጣይነትም ያረጋግጣል፡፡

ከዚህም ሌላ ስጦታው ከአንድ አካል ወደ ሌላ አካል ገንዘብ እንዲተላለፍ የሚደረግበት ነውና ለኢኮኖሚ ልውውጥ ይረዳል፤ ከሙሽራዎቹ ቤተሰቦች ወደ ሌሎች ሰዎች እንዲሸጋገር የማድረግ ፋይዳ አለው፡፡

በሠርግ ድግስ አውራጅ መያዝ፣ በብዛት ወንዶች ለደጋሹ ብር መጣላቸው፣ ሴቶች እህል መውሰዳቸው፣ ዘፋኞች ወይም አቀንቃኞችና እስክስታ አውራጆች የማበረታቻ ሽልማት ማግኘታቸው በገቢ ምንጭነት የማገልገል ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አለው፡፡ በተለይ አውራጅ መያዝና ገንዘብ መጣል የሠርግ ደጋሾች ለድግሱ የሚያስፈልጋቸውን ወጭ ለመቀነስ ያስችላል፡፡ ከዚህም ሌላ የማህበረሰቡን የእርስ በእርስ መተሳሰብና መተጋገዝ ያጎለብታል፡፡

የሠርግ ታዳሚዎች ከተለያዩና ርቀት ካላቸው ቦታዎች የሚመጡ ናቸው፤ በሰርጉ እለት በሚገናኙበት ወቅት ይጠያየቃሉ፤ ናፍቆታቸውንም ይወጣሉ፤ ከመብላታቸውና ከመጠጣቸው በተጨማሪም የተለያዩ ግላዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን በማንሳት ይነጋገራሉ፤ ይወያያሉ፤ ስለዚህ ሰርጉ የሁለት ተጋቢዎች ጋብቻ መፈጸሚያ ከመሆን አልፎ፣ ለውይይትና ለችግሮችም መፍትሄ ማግኛ መድረክ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ሥነ-ሥርዓቱ ሰዎች የሃሳብ ልውውጥ እንዲያደርጉና በማህበረሰቡ ውስጥ ለሰላማዊ ኑሮ እንቅፋት የሆኑ ነገሮች እንዲወገዱ ለማድረግም ረድቷል፡፡

ከቅድመ-ሠርግ ተግባራት አንዱ ሚዜ ምልመላ ነው፤ በሚዜነት ለመመልመል ከሚያገለግሉት መስፈርቶች አንዱ ደግሞ የወላጆች ቀረቤታ ወይም ፍቅር ነው፡፡ ሙሽራዎቹና ሚዜዎቹም ቃል በመግባት ይተሳሰራሉ፡፡ ይህም ቀደምት መቀራረብንና መተሳሰርን ያጠናክራል፤ ይህ መቀራረብና መተሳሰብም ቀጣይነት እንዲኖረውና ሙሽራዎቹና ሚዜዎቹ ቤተሰባዊ ግንኙነት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ ትልቅ ቦታም ይሰጠዋል፣ በአካባቢው ባህላዊ ዘፋኞች፣

እከሌ ሲናገር እከሌ ያዳምጣል፣

ካልረባ ዝምድና ቃል ኪዳን ይበልጣል፡፡

ከሚባልላቸው ቃል ኪዳኖችም አንዱ ይሆናል፡፡

የሚዜ ተግባራት በርካታ ናቸው፡፡ በተለይ በገጠር ሚዜዎች ከጫካ የማገዶ እንጨት ከወንዝ ውሃ፣ ለዳስ መስሪያ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ወዘተ. ያጓጉዛሉ፤ በድግሱ ዝግጅት ላይ በባለቤትነት ይሳተፋሉ፡፡ በዚህ ተሳትፏቸውም ኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸው የጎላ ቦታ

ይሰጠዋል፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ስራዎች በእነሱ ባይሸፈኑና በክፍያ ቢሰሩ ደጋሾችን ለከፍተኛ ወጭ ይዳርጓቸው ነበር፡፡

ከዚህም ሌላ ሚዜዎች ሙሽራዋን በጀርባቸው ተሸክመው ያጓጉዛሉ፤ በሙሽራዋ ዳስ ውስጥ የማጫና የስጦታ ስርዓቱ በደንቡ መሰረት እንዲፈጸም ያደርጋሉ፤ ሙሽራውን ማስጌጥና በሆታና በዘፈን ማጀብም አይቀሬ ተግባሮቻቸው ናቸው፡፡ እነዚህ ተግባራት ተናጠላዊ ቢመስሉም፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገሩ የማህበረሰቡ የሠርግ ሥነ-ሥርዓት ቀጣይ ሆኖ ህልውና እንዲያገኝ የማድረግ ሚና ይጫወታሉ፡፡

በዋግ ኽምራ ከሚፈጸሙ የጋብቻ አይነቶች መካከል አንዱ አግብተህ/ሽ ክረም ክረሚ/ (ድውር ጫር) ወይም አፈረ ፈጪ ነው፡፡ ይህም በአንድ በኩል አንድ ወላጅ ምርት ባላገኘበት ወቅት ልጁን እንዲድር የማያስገድድ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለአካለ መጠን የደረሱ ተጋቢዎች በወቅቱ ጋብቻቸውን እንዲፈጽሙ ይረዳል፡፡ ተጋቢዎቹ በድግስ በተዳሩ ጓደኞቻቸው ‹‹ከእርጥብ ዳስ አልወጣም፤ አልወጣችም፡፡›› ተብለው እንዳይሰደቡም፣ ምርት በሚገኝበት ወቅት ወላጆቻቸው ብቻቸውንም ሆነ ከሌሎች ወንድሞቻቸው ወይም እህቶቻቸው ጋር ይድሯቸዋል፡፡ ወላጆች ለድገሱ የሚሆን ወጭ ሳይኖራቸው ከሌላ በመበደር እንዲድሩ ባለማድረጉ ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው በተጨማሪ ለተጋቢዎችም መዳር በሚፈልጉበት ወቅት እንዲዳሩ ለማድረግ በማስቻሉ የስነ-ልቦና እርካታ ያስገኛል፡፡

በዋግ ኽምራ በአንድ የሠርግ ድግስ ሁለት ሙሽራዎችን መዳር ይቻላል፡፡ ይህም በኢኮኖሚ በኩል አንድን ልጅ ለመዳር በሚደገስ ድግስ ሁለት ልጆችን በመዳር፣ የሰርጉ ታዳሚዎችም፣ የቅርብ ዘመድ፣ ወዳጅ እና ጎረቤትም ሁለት ጊዜ አውራጅ መያዝንና ብር መጣልን በአንድ ጊዜ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ በጉልበት በኩልም አልፎ አልፎ ለደጋሾች የሚለገስ የጉልበት ድጋፍ መጠንን ለመቆጠብ ይረዳል፡፡ ከተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ አኳያም ለሁለት ሠርግ የሚያስፈልግ የማገዶ እንጨትና ለሁለት ዳስ መስሪያ የሚያስፈልግ የደደሆ፣ የቁንዶ በርበሬም ሆነ የባህር ዛፍ ቅጠል ለአንድ ዳስ ብቻ እንዲሆን በማድረግ እንዲቆጠብ ያደርጋልና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አለው፡፡

ከጋብቻ ሥነ-ሥርዓት ፋይዳ ሌላው ማህበረሰቡ እርስ በእርሱ እንዲረዳዳ ማድረጉ ነው፡፡ ይህ መረዳዳት ከሚታይባቸው ስራዎች መካከል አንዱ በእጮኝነት ወቅት የሴት ወገን የወንድ ወገንን የሚያዘው የህብረት ስራ ወይም የአማች እዝ ነው፡፡ የአማች እዝ ስራ የሚከናወነው በወንድ ቤተሰብ ብቻ ሳይሆን ሊሰራ ይችላል ተብሎ በወንድ ቤተሰብ በሚለመን ባእድ ሁሉ ነው፡፡ በአማች እዝ ስራ የሚለመን ሰው የራሱን ስራ ትቶ በጋራ ስራው ይሳተፋል፡፡ ምክንያቱም አማች ያዘዘው ነውና ሊደናቀፍ አይገባውም፡፡ ስለዚህ ጋብቻው እንዲቀጥል እንደ አንድ መለኪያ ተደርጎ በሚወሰደው የስራ ትእዛዝ በመሳተፍ እርዳታውን ይለግሳል፡፡ ይህም ግለሰባዊና ማህበራዊ ጥቅሞችን ያስገኛል፡፡ በግለሰብ በኩል በተወሰነ ጉልበት፣ ረጅም ጊዜ የሚጨርሰው ስራ በአንድ ጊዜ እንዲጠናቀቅ ያደርጋል፤ በወቅቱ የሚሰጥ የጉልበት ዋጋ ክፍያ ባይኖርም እንኳ አቅም ሲገኝ በሰርጉ እለት እንዲከፈል ይሆናል፡፡ የወንድ ወገንም አጋሮቹን ሰብስቦ ለሰራው ስራ ክፍያ እንዲያገኝ ያደርገዋልና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታም አለው፡፡ በቡድን ወይም በማህበረሰቡ በኩል ደግሞ መተሳሰብንና መተጋገዝን ያበረታታል፡፡

ከጋብቻ በፊት የእጮኛሞቹ ቤተሰቦች በሃዘኑም በደስታውም መጠያየቃቸውም ትስስራቸውንና መተሳሰባቸውን ያጠናክራል፡፡

ማንኛውም ድግስ የሠርግም የሚደገሰው በቤተዘመድና በጎረቤት ትብብር በነጻ እንጂ በክፍያ አይደለም፤ በእርግጥ ይህንን አገልግሎት የሰጡት በሚደግሱበት ወቅት ተመሳሳይ የጉልበት ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡ ስራውንም የቅርብ ዘመድና ጎረቤት ብቻ ሳይሆኑ ከሩቅ የሚመጣ ዘመድና ባእድም በመረባረብ ይሰራል፡፡ ከዚህም ሌላ እንጀራ ለመጋገር፣ እንጨት ለመፍለጥ፣ ሊጥ ለማቡካት፣ ወጥ ለመስራት በጠቅላላው ለድግሱ የሚያስፈልጉት ቁሳቁሶችም ከያሉበት ተሰባስበው የሚፈለግባቸውን አገልግሎት በነጻ እንዲሰጡ ይደርጋል እንጂ ኪራይ አይከፈልባቸውም፡፡ ይህም ደጋሹ ለድግሱ ከፍተኛ ወጭ በማውጣት እንዳይጎዳ ያደርጋል፡፡ ለስራው የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን የሚለግሱትና በስራው የሚሳተፉት ሰዎችም ለድግሱ የሚጠበቅባቸውን በማከናወናቸው የስነ-ልቦና እርካታ ያገኛሉ፤ በደጋሾች ምስጋና፣ በሌሎች ዘንድም አክብሮትንና ተቀባይነትን ያስገኝላቸዋል፡፡

አማጭ ሽማግሌዎች ወደ ሴቷ ቤተሰብ ለመጠየቅ ሲሄዱ የሴቷ አባት ፈጠን ብሎ ለመቀመጫ የሚሆን ምንጣፍ መስጠቱ፣ ሽማግሌዎችም አደግድገው በመቆም በትህትና መጠየቃቸው፣ የሠርግ ታዳሚዎች ወደ ዳስ ሲገቡ አስተናጋጆች በተራቸውን መቀበላቸው፣ የዳስ ውስጥ አቀማመጥም በእድሜ ቅደም ተከተል በእድሜ የገፉ አባቶችና እናቶች ለብቻቸው ከፍ ባለ ቦታ መቀመጣቸው፣ ከዚያ ወጣቶች መቀጠላቸውና መስተንግዶውም በትላልቆች ተጀምሮ በእድሜ ቅደም ተከተል መቀጠሉ መከባበርን የሚያመለክቱ መልካም የስነ-ምግባር መገለጫዎች ናቸው፡፡

በሙሽራዋ ዳስ ውስጥ የወንድ ወገን አመጋገብ መጀመሪያ ሽማግሌዎች ዝልዝል ፍሪምባ መመገባቸው፣ የወንድ ወገኖች ወደ ሙሽራዋ ዳስ ሲቃረቡ ከሴት ወገን ‹‹ግቡ፡፡›› የሚል ፈቃድ ሳያገኙ ወደ ዳስ አለመግባታቸው፣ ለክርስትና እናት ሙክትና ማሰሮ ቅቤ መወሰዱ፣ በሠርግ ለአማጭና ለሌሎች ሰዎች ስጦታ መስጠቱ፣ የማህበረሰቡን የእርስ በእርስ መከባበር የሚያመለክቱ ናቸው፤ ማህበረሰቡ ለሰላማዊ ኑሮ እንቅፋት የሆኑ ነገሮችን በማስወገድ በሰላም ተከባብሮ እንዲኖር የማድረግ ፋይዳም አላቸው፡፡

በሠርግ ከሚከወኑት መካከል አንዱ ዘፈን ነው፡፡ የሠርግ ዘፈን የተለያዩ ሰዎችን በሚያሞግሱ ቃል-ግጥሞች የታጀበ ነው፡፡ እነዚህ ቃል ግጥሞች ደግሞ የተለያየ ፋይዳ አላቸው፤ Alembi (2002:50) በአብዛኛዎቹ *ሥነ-ሥርዓቶች* ክዋኔ ወቅት የሚገጠመውን ቃል-ግጥም ፋይዳ አስመልክተው Kabiranን እና Mutahinን በመጥቀስ እንዳሰፈሩት፣ ከቃል-ግጥም ተግባራት መካከል ማስተማር፣ መረጃ መስጠት፣ ማዝናናት ባህልን ማዳበርና ማስተላለፍ፣ መምከርና ማሰልጠን ይጠቀሳሉ ብለዋል፡፡ በዋግ ኽምራ የጋብቻ *ሥነ-ሥርዓት* ላይ የሚገጠሙ ቃል ግጥሞችም እነዚህን ተግባራት የሚፈጽሙ ናቸው፡፡ ይኸውም በቃል ግጥሞቹ የሚወደሱ ሰዎች ቤተሰቦች ዘፈኑን በእልልታ በማጀባቸው ዘፈኑን ያሟሙቃሉ፡፡ ለአቀንቃኞቹና እስክስታ ለሚወርዱት ሰዎች በሽልማት የሚሰጥ ብር በገቢ ምንጭነት ማገልገሉ እና በቃል-ግጥሞቹ አማካይነት በህይወት የሌሉ ሰዎችም መጠቀሳቸው አልረሳናችሁም ማለትንና ማስታወስን ያሳያል፤ ከዚህም ሌላ ሙሽራዎቹ የእነማን ወገን እንደሆኑ ዳስ ውስጥ በማስተጋባት መረጃ ለመስጠት ይረዳል፡፡ ለሴት ወገኖችም ከእናንተ ጋር ጋብቻ መፈጸማችን ተገቢነት ያለው ነው በማለት በጋብቻ ትስስሩ መደሰትን ማንጸባረቂያ ናቸው፡፡ ቃል ግጥሞቹ የወግ ልማድ ስጦታ እንዲሰጥ ጥያቄ ማቅረቢያም

ናቸው፡፡ ለአብነት ያህል ሙሽራዎቹን በሚሸኙት ሴቶች የሚዘፈነው ‹‹ነበረየ›› የሚገጠመው ቃል-ግጥም የሙሽራዋ እናት በማር የተለወሰ ድፍድፍ ለሴቶቹ እንድትሰጥ የሚጠየቅበት ነው፡፡ በዚህም ሰዎች እየተዝናኑ ወግና ባህላቸውን እንዲያዳብሩና እንዲያስተላልፉ ያግዛል፡፡

ከዚህም ሌላ የቃል-ግጥሙ ገጣሚዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ያስችላቸዋል፤ ሌሎችም በማዳመጥ እንዲቀጥሉበት ያስችላቸዋል፡፡

ስለዚህ የሚገጠሙት ቃል-ግጥሞች ከማዝናናታቸው በተጨማሪ የሥነ-ሥርዓቱን ቀጣይነት በማጠናከር በኩል የራሳቸውን ሚና ይጫወታሉ፡፡

የሠርግ ሥነ-ሥርዓት ቃል-ግጥሞች የሚደረደሩበት ብቻ ሳይሆን ቁሳዊ ነገሮችም ወጥተውና ጎልተው የሚታዩበትም ነው፤ ለዚህም አንዱ ማሳያ ሰዎች አምረውና ተውበው እንዲገኙ ማስቻሉ ነው፤ በተለይ ሴቶች አጊጠውባቸው ላይ ታች ለማለትና ዘወትራዊ የቤት ውስጥ ስራቸውን ለማከናወን በማይመቿቸው ጌጣጌጦቻቸውና በነጫጭ ጥልፍ ቀሚሶቻቸው እንዲዋቡ፣ ጸጉራቸውንም ለደስታ ጊዜ የሚሆነውን ዓይነት ሹሩባ እንዲሰሩ ምቹ ጊዜ ይሆንላቸዋል፡፡ አርሶ አደሩም በስራ የደከመ ጉልበቱንና ውጣ ውረዱን ሲያብሰለስልበት የከረመውን አእምሮውን ዘና ያደርግበታል፤ ለዚህም ዋናው ሞተር ዘፈን ነው፡፡ በሠርግ ዘፈን ወቅት ማጨብጨብ፣ መወዛወዝ፣ እስክስታ መውረድ፣ ከበሮ መምታት፣ ማቀንቀንና መቀበል የወጣቶች ወይም የልጆች ድርሻ ብቻ አይደለም፤ የአዋቂዎችም እንጂ፣ ስለዚህ የሠርጉ ታዳሚ ሁሉ በተጠቀሱት የዘፈን ተሳትፎዎች የእራሱን ድርሻ እየተወጣ ያለውን ችሎታም አውጥቶ እያሳየ ይዝናናል፡፡ ስለዚህ የሠርጉ ታዳሚ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ከግል ችግሩና ማብሰልሰሉ ፋታ ያገኛል፡፡ ስለዚህ ሠርግ በመዝናኛ መድረክነትም ያገለግላል፡፡

የጋብቻ ሥነ-ሥርዓት እንደ ሥነ-ሥርዓት አይነትነቱ አለማዊና ሃይማኖታዊ ክዋኔዎች የሚከወኑበት ነው፡፡ እነዚህን ሃይማኖታዊ ተግባራት የሚያከናውኑ ሰዎች እንደ እምነቱ ተከታይነታቸው የሚጠበቅባቸውን በማከናወናቸው የሥነ-ልቦና እርካታ ያገኛሉ፤ ድርጊቶቹን የሚፈጽሙትንና የሚያስፈጽሙትን አካላትም በእምነቱ መሪዎችም ሆነ ተከታዮች ዘንድ ተቀባይነትን ያስገኝላቸዋል፤ ከእምነቱ ተከታዮች ጋር የሚኖራቸውን ትስስርም ያጠናክራል፡፡

በሠርግ የሚከናወንን እያንዳንዱ ተግባር በመከታተል ልጆች እውቀት ይቀስማሉ፤ በመሳተፍም ችሎታቸውን ያዳብራሉ፡፡ ለአብነት ያህል ከቤታቸው እንጀራ መጋገር ያልጀመሩ ሴቶች በሠርግ ድግስ እንጀራ መጋገር እንዲለማመዱ ይፈቀድላቸዋል፡፡ የወጥ ስራን በሚመለከትም ትላልቆቹ ሲሰሩ ወጣቶቹ ይመለከታሉ፤ በተለይ ሽማግሌዎች ክክ ወጥ በጥንቃቄ በሚሰሩበት ወቅት ወጣት ሴቶችም በመመልከት ወደ ፊት እንዴት እንደሚሰራ እውቀት ይቀስማሉ፡፡

ሌላው የሠርግ ሥነ-ሥርዓቱ ክዋኔ ሁሉ ‹‹ይህን አድርግ ይህን አታድርግ፡፡›› ተብሎ ከአባቶች ወይም ከእናቶች ለሚቀጥለው ትውልድ በጽሁፍ ሰፍሮ የሚገኝ አይደለም፤ ሲከወን በመመልከትና ትምህርት በመውሰድ የሚከወነውና የማይከወነው የሚለይበት ነው፡፡ ስለዚህ በማህበረሰቡ ስለማህበረሰቡ ለማህበረሰቡ ሃገረሰባዊ እውቀትን ማስተላለፊያ ትምህርት ቤት በመሆን የማገልገል ፋይዳ አለው፡፡

የጎጆ ወጪዎች መቋቋሚያ ቁሳቁስ ፋይዳም በግለሰብና በማህበረሰብ በኩል ተብሎ በሁለት መንገድ ሊታይ ይችላል፤ በግለሰብ በኩል ጎጆ ወጭዎች ከተሰጣቸው ማጫ በመቀነስ ቁሳቁሶቹን ለመግዛት ወጭ እንዳያደርጉ ይረዳልና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ ለማቋቋም የረዷቸውንም ለመለየትና እነሱም ወደፊት ድጋፋቸውን እንዲያደርጉላቸው ያደርጋል፡፡ በማህበራዊ ጠቀሜታ በኩል ደግሞ፤ ጥንዶች እራሳቸውን እንዲችሉና ቤተሰባዊ ህይወታቸውን እንዲመሩ ያደርጋል፤ የመተጋገዝ መገለጫም ነው፡፡

የሙሽራዎች ጎጆ መውጣትም ፋይዳ አለው፡፡ ይህንን አስመልክተው Guday(2005:91) እንደሚከተለው ብለዋል፡፡

> ጎጆ መውጣት ግለሰቦችን የመውለድ፣ ልጅ የማሳደግ፣ የአካባቢው ማህበራዊና ሃይማኖታዊ ማህበራት አባል የመሆን የመሳሰሉትን ሃላፊነቶች ለመውሰድ የሚያስችል የሽግግር ሥርዓት ነው፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን በተለይ ብቸኛ ለነበሩ የወንድ ወላጆች ሁለተኛ በመሆን ግቢያቸው እንዲከበርና ደካማ ከሆኑም በተለያዩ ማህበራዊ ተሳትፎዎች እነሱን በመተካት እንዲሳተፉና ሃላፊነቶችን እንዲወጡ ያደርጋል፡፡

ስለዚህ የጋብቻ ሥነ-ሥርዓት ከፋይዳዊነት አንጻር ሲታይ ግለሰባዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጠቀሜታ አለው፡፡ ምክንያቱም የአንድ ማህበረሰብ ተጋግዞና ተከባብሮ በሰላም መኖር ከስርዓቱ ፖለቲካዊ ዓላማ አንዱ ነው፡፡

## 7.3. የሞት ሥነ-ሥርዓት ትንተና

### 7.3.1.ከተምሳሌታዊነት አንጻር

በገጠር የቀብሩ ጥሪ የሚደረገው በቡታ ነገራ ነው፡፡ ቡታውን የሚናገሩትም ሁለት ሰዎች ናቸው፤ አንድ ሰው ቢናገር አደጋ ይደርስበታል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከዚህ የምንረዳው ሁለተኛው የቡታ ነጋሪ ሰው ሌላውን ከመጥፎ አደጋ የሚከላከል ሃይል ተምሳሌት መሆኑን ነው፡፡ የካህን ሬሳ በሚገነዝበት ወቅት አስራ ሁለት ጊዜ ተጠምጥሞ ነው፡፡ አስራ ሁለት ጊዜ መጠምጠሙም የአስራ ሁለቱ ሀዋርያት ተምሳሌት ነው፡፡

ለቀብር የሚመጡ ወንዶች ወደ ለቀስተኞቹ ሲቀላቀሉ የያዙትን በትር ወደ መሬት ጣል አድርገው ያነሳሉ። ይህም ሟች ወደ መሬት የመግባቱ ተምሳሌት ነው፡፡ ሀዘንተኛ ሴት ከዚያ በፊት ታስር የነበረውን ጥቁር ማተብ ፈትታ ነጭ ማተብ ታስራለች፡፡ ይህ የነጭ ክር ማተብም የሀዘንተኛነት ተምሳሌት ነው ማለት ነው፡፡

በቀብር ወቅት ለማስለቀሻነት የሚያዙት ጌጣጌጦች በእርጥብ ሳይሆን በደረቅ እንጨት ላይ መንጠልጠላቸው እንጨቱ ደረቅ ነውና የሟቹ ተምሳሌት ነው፡፡ በቀብር ጊዜ የአስከሬኑ የፊት ገጽታ ወደ ምስራቅ እንዲሆን የሚደረገውም፣‹‹ወደ ምስራቅ መመልከት የእየሩሳሌም አቅጣጫን ለማመልከት ነው (ቁ.የ.መ.አ.20)፡፡ ስለዚህ ምስራቅ የእየሩሳሌም ተምሳሌት ነው፡፡

በቀብር ወቅት ወደ የቀብር ቦታ የሚመጣውና ለቀስተኞቹ የሚመገቡት ቆሎ ነው እንጂ ንፍሮ አይሆንም፤ ምክንያቱም ቆሎ ደረቅ በመሆኑ የሀዘን፣ ንፍሮ ደግሞ እርጥብ በመሆኑ የደስታ ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ስለዚህ ደረቅ መጥፎነትን ርጥብ ደግሞ ደግነት የሚወክሉ ናቸው፡፡

ሬሳ የወጣበትን ቤት የሚያጸዱት፣ በቅጠል፣ በውሃ እና በእሳት ነው፤ ሶስቱንም ይዘው ወደ ቤት በመግባት፣ በመጀመሪያ ውሃ ይረጫሉ፤ በመቀጠልም እሳት በማንደድ በቅጠል

ይጠርጋሉ፡፡ ውሃው በቤቱ ውስጥ የነበረውን ገዳይ ሃይል የሚያቀዘቅዝ ወይም የሚያዳክም ሃይል ተምሳሌት ነው፤ እሳቱ ደግሞ በቤቱ ውስጥ የሚገኘውን ሃይል የማጥፊያ ተምሳሌት ሲሆን፣ ቅጠሉ ደግሞ እርጥብ ነውና ከዚያ በኋላ በቤቱ ውስጥ ሀዘን ተወግዶ ደስታ የመተካቱ ተምሳሌት ነው፡፡

በአጎበር የተረፈ እንጀራ ወደ ቤት አይወሰድም፤ ምክንያቱም ይህ እንጀራ የመጥፎ ገድ ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ሃዘንን ወደ ቤት እንደማስገባት ይቆጠራል፡፡

ከሟች መዘከሪያዎች አንዱ የቁም ተዝካር ነው፡፡በዚህ መዘከሪያ በህይወት ያለው/ያለችውና ተዝካር የሚደረግለትና/የሚደረግላት ከመዘከሪያው ድግስ አይቀምስም/አትቀምስም፡፡ ምክንያቱም ተዝካር የሚደረገው ለሟች ነውና እሷም/እሱም የሟች ተምሳሌት ናት/ነው፡፡

### 7.3.2 ከመዋቅራዊ-ፋይዳዊነት አንጻር

የሞት ሥነ-ሥርዓትን ከመዋቅራዊ-ፋይዳዊነት አንጻር ለመተንተን የተመለከትኩት ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው ከመዋቅራዊነትና ከፋይዳዊነት አንጻር ነው፡፡ በመጀመሪያም ከመዋቅራዊነት አንጻር እተነትናለሁ፡፡

#### 7.3.2.1 ከመዋቅራዊነት አንጻር

የሞትን ሥነ-ሥርዓት መዋቅር የተመለከትኩት ከሁለት ማለትም ከሟችና ከሟች ቤተሰቦች አንጻር ነው፡፡ ምክንያቱም በሞት ስርዓት በሽግግር ላይ የሚሆኑት ሟች ብቻ ሳይሆን በህይወት የሚገኙት ዘመዶችም ናቸው፡፡

ሟቹ ነፍሱ በምትወጣበት ወቅት ከህያውያን ይለያል፤ ነገር ግን ገና ወደ መቃብር ባለመውረዱና ወደ ሙታን መንደር ባለመቀላቀሉ በማእከል ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ ከተከናወነ በኋላ ደግሞ ወደ የሙታን መንደር ይቀላቀላል፤ በሃይማኖት አባቶች እንደሚገለጸውም ከዚህ ምድራዊ ዓለም ወደ ሰማያዊው አለም፣ ከሚያልፈው ወደ የማያልፈው፣ ከጊዜያዊው ወደ ዘላለማዊው ዓለም ይሸጋገራል፡፡

ቋሚውን ወይም የሟች የቅርብ ዘመድን ከመዋቅራዊነት አንጻር በምመለከትበት ወቅት ደግሞ አንድ ሰው ዘመዱ በሚሞትበት ወቅት ከሌሎች ሀዘንተኛ ካልሆኑ ሰዎች ይለያል፣

የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ እስከሚፈጸም ድረስ የኀላ የሀዘንተኛ አለባበስ ስለማይኖረው፣ በሽግግር ላይ ይሆናል፡፡ ከቀብር በኋላ ወንዱም በወንድነቱ፣ ሴትም በሴትነቷ በማህበረሰቡ የሚጠበቅበትን/የሚጠበቅባትን የሀዘንተኛ ሰው አለባበስ በሚለብሱበት ወቅት ደግሞ ከሀዘንተኞች ጋር ይቀላቀላሉ፡፡ ወደ ቀደምት የአለባበስ ገጽታቸው ባለመመለሳቸውም እንደ ገና በሽግግር ወይም በመካከለኛ ደረጃ ላይ ይሆናሉ፡፡ ወንዱም በጓደኞቹና በትላልቅ ሰዎች ተመክሮ፣ ሴቷም በዘመዶቿ ወይም በጎረቤቶቿ አማካይነት የመደበሻ ቅቤ ተቀብታ፤ ከተገኘም እንሶስላም እንድትሞቅ ተደርጋ፣ ሀዘንተኛነታቸውን እንዲተው ይደረጋል፡፡ ከዚህ በኋላም ሴቷ ቀስ በቀስ እንዳታጌጥባቸው ያስቀመጠቻቸውን ጌጣጌጦች ትጠቀምባቸዋለች፤ ጸዳ ያለ ልብሷንም ትለብሳለች፤ የተላጨችው ጸጉር ካደገም ሽሩባ ትሰራለች(ትቆነጠጣለች)፡፡ በዚህ ጊዜም ሙሉ በሙሉ ባንድ ጊዜ ሀዘኗን ባትተወውም ቀስ በቀስ ሃዘኗን በመቀነስ ወደ ሌሎች ሀዘንተኛ ያልሆኑ ሴቶች አጊያጌጥና አለባበስ ትመለሳለች፤ ትቀላቀላለች፡፡ ከመዋቅራዊነት አንጻር በመቀላቀል ደረጃ ላይ ትሆናለች፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የሞተው ባል ቢሆን ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ሚስት ከባለ ትዳርነት ወደ ባል አልባነት፣ ሚስት የሞተበት ደግሞ ከባለትዳርነት ወደ ሚስት አልባነት ይሸጋገራሉ፤ ልጅ የሞተባቸውም ሌላ ልጅ የሌላቸው ከሆኑ ከባለልጅነት ወደ ልጅ አልባነት ይሸጋገራሉ፡፡ በዚህ ደረጃ ከባለትዳሮችና ልጅ ካላቸው ሰዎች ይለያሉ፤ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የሟች ሚስት ሌላ ባል፣ የሟች ባል ደግሞ ሌላ ሚስት በሚያገቡበት ወቅት እንደ ገና ባለትዳር ይሆኑና ከባለትዳሮች ጋር ይቀላቀላሉ፡፡ በዚህ ደረጃ ከመዋቅራዊነት አንጻር በሶስተኛው በመቀላቀል ደረጃ ላይ ይሆናሉ፡፡ ልጅ የሞተባቸውም (ሌላ ልጅ የሌላቸው ከሆነ) ከወለዱ ልጅ ካላቸው ጋር ይቀላቀላሉ፡፡ ካልወለዱ ግን ልጅ ካላቸው ተለይተው ይቀራሉ፡፡ ከመዋቅራዊነት አንጻር በሁለተኛው በመለየት ደረጃ ላይ ይሆናሉ፡፡

### 7.3.2.2 ከፋይዳዊነት አንጻር

የሞት ሥነ-ሥርዓትን ለግለሰብ ከሚሰጠው ፋይዳ አንጻር ግለሰባዊ፣ ከስነ-ልቦና አንጻር ስነ-ልቦናዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖሊቲካዊ ፋይዳ በማለት መመልከት ይቻላል፡፡ ማህበረሰቡ ሟችን ወደሚያሳርፍበት ቦታ ለማሳረፍ በሚያከናውነው ድርጊት፣ የቅርብ ቤተሰብም ሆነ ማህበረሰቡ የሚኖረው ፋይዳ አለ፡፡ ምክንያቱም እንደ አካባቢው ባህል የሟች አስከሬን ወደ ቀብር የሚወሰድበትና ግብዓተ መሬት የሚገባበት ሥነ-ሥርዓት አለ፤ የሚፈጸመውም

ሃይማኖቱን መሰረት አድርጎና ባህሉንም ጠብቆ ነው፡፡ ስለዚህ ማህበረሰቡ በእምነቱም በባህሉም በሚጠበቅበት መንገድ የቀብርና የሃዘን ሥነ-ሥርዓቱን ሲፈጽም ማህበራዊ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡ የሟች የቅርብ ቤተሰቦች ደግሞ በሟች ምክንያት የደረሰባቸውን ሃዘን ለመግለጽና ከእነሱ የሚፈለግባቸውን ሁሉ በመፈጸም ሟች ወደሚጠብቀው የቀብር ቦታ በሥነ-ሥርዓት ሲያሳርፉ ግለሰባዊ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡ ምክንያቱም ማህበረሰቡ የሞተ ሰው የቀብር ሥነ-ሥርዓት እንዴት መፈጸም እንዳለበት በባህሉ የያዘውን ህግ ጠብቆ አስፈጽሟል፡፡

በዚህ የቀብር ሥነ-ሥርዓት ወቅት ለቀብር የሚመጡት ሰዎች ለሟች እንዳላቸው ቀረቤታ እንጀራና ቆሎ በመያዝ ይመጣሉ፤ ቀባሪዎቹ  እንጀራና ቆሎ ይዘው መምጣታቸውም የሟች ቤተሰቦች ብዛት ያለው እንጀራ፣ ወጥና ቆሎ እንዳያዘጋጁና ወጭ እንዳይበዛባቸው ያግዛል፡፡ ስለዚህ ኢኮኖሚዊ ጠቀሜታ አለው ማለት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ደጋፊነታቸውን በመግለጻቸውም የስነ-ልቦና እርካታ ያገኛሉ፤ የእርስ በርስ ትስስራቸውን ያጠናክርላቸዋል፡፡

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የቀብርና የአጎበር ሥነ-ሥርዓት በቃል-ግጥምና በእንጉርጉሮ ይታጀባል፡፡ እነዚህ እንጉርጉሮዎችና ቃል-ግጥሞች ደግሞ ሁለት አይነት ፋይዳ አላቸው፡፡ ባንድ በኩል ለቀስተኛው በእንጉርጉሮዎቹና በቃል-ግጥሞቹ ይዘት በመቀስቀስ ብዙ እንዲያነባ፣ ድምጽ እያወጣ እንዲያለቅስ በማድረግ ለቅሶው የተሟሟቀ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ምክንያቱም ሀዘኑን አምቆ በውስጥ ለውስት ህመም ከመሰቃየት ይገላግለዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በእንጉርጉሮዎቹና በቃል ግጥሞቹ በመቀስቀስ ሀዘናቸውን አምቀው የያዙ ሀዘንተኞች በብዛት እንዲያለቅሱና በውስጣቸው የታመቀው ሀዘን በመጠኑም ቢሆን እንዲቀንስና የስነ ልቦና እፎይታ እንዲያገኙ ይረዳቸዋል፡፡ ስለዚህ የቃል-ግጥም ይዘትና ቅላጼ የሃዘንን ጥልቅ ስሜት ለመግለጽ ያስችላል፡፡ በቀብርና በሃዘን ሥነ-ሥርዓት የሚከናወኑት ተግባራት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገሩት ትላልቆቹ ሲያከናውኑ ወጣቶቹ ተመልክተውና እውቀት ቀስመው ነው፤ እንዴት ቡታ እንደሚነገር፣ እሬሳ የወጣበት ቤት በምን እንደሚጸዳ፣ ለቀብር ምን ተለብሶ እንደሚኬድ፣ ወዘተ. የሚታወቁት በጽሁፍ ተገኝተው አይደለም፡፡ ስለዚህ የሥነ-ሥርዓቱ ክዋኔ  የአካባቢውን የሀዘን ሥነ-

ሥርዓት ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ በትምህርት ቤትነትነት አገልግሏል፤ ማህበራዊ ፋይዳ ለግሷል፡፡

በ16/09/04 በወለህ ማርያም ላይ ምልከታ ባደረግሁበት የቀብር ሥነ-ሥርዓት እንደ ተመለከትኩት የስንብት ስርዓት ከተከናወነ በኋላ በእድሜ ገፋ ያሉ ሰዎች ተሰብስበው ነበር፤ የቀበሌውን ስራ አስኪያጅ ምን እየሰሩ እንደሆነ ጠየቅሁት ‹‹የልማት ቡድን ስብሰባ ነው›› አለኝ፡፡ ለቀብር የመጡት ሰዎች ስለ አካባቢያቸው ልማትም ተወያይተዋልና ሥነ-ሥርዓቱ በመንግሥት አስተባባሪነት ሊከናወኑ የሚገቡ የልማት ሥራዎችን ለማከነወንም አስችሏልና ፖለቲካዊ ጠቀሜታም አለው፡፡

የአጎበር ሥነ-ሥርዓትም በርካታ ፋይዳዎች አሉት፡፡ በደራሾቹ በኩል ‹‹ሀዘንተኞቹን ለማስተዛዘን ዛሬ ነገ እሄዳለሁ፡፡›› በማለት ሳይሄዱ ቀርተው ከዘመድ ጋር ተጣልተው እንዳይቀሩ ያደርጋል፤ ስለዚህ አጎበር በቀብር ወቅት ያልተሳተፈ ሰው፣‹‹እከሌ ሳይቀብር ቀረ›› እንዳይባልና በሃዘንተኞቹ እንዳይጠላ ያደርገዋል፡፡ በዚህም በቤተሰብ መካከል ሊፈጠር የሚችልን ጥል ያስቀራል፡፡ ሰላማዊ ህይወት ያጠናክራል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሚደረሱት ሰዎች በርካታ እና በተለያዩ ቦታዎች የሚኖሩ ቢሆኑ በአጎበሩ እለት በአንድ ላይ ተገኝተው ለማስተዛዘን ያስችላል፡፡ ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው የእንጀራው እርክክብ የሚከናወነው የአባትን፣ የእናትን፣ የአያትን ወይም የቅድመ-አያትን ስም በመጥራት ነው፡፡ ይህም የዘር ግንድን በመጥቀስ የትላልቆችን የበላይነት ያረጋግጣል፤ ማን የማን ወገን እንደ ሆነ ለማስታወስና ለማሳወቅም ያገለግላል፡፡ ስለዚህ የማህበረሰቡን የእርስ በእርስ ትስስር ያጠናክራል፡፡

አጎበር የሚያገለግለው ሀዘንተኛን ለመድረስ ብቻ አይደለም፤ ለቀስተኞቹ ርቀት ካላቸውና ከተለያዩ ቦታዎች የሚመጡ በመሆናቸው ተራርቀውና ተነፋፍቀው የሚኖሩ ናቸው፡፡ ስለዚህ በለቅሶው ምክንያት እንዲገናኙ ያግዛቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ የየግል ችግሮቻቸውን በመግለጽ ይወያያሉ፡፡ በዚህም አጎበሩ የሀዘን መግለጫ አውድ የመሆኑን ያህል ከቤተዘመድና ከጓደኛ ጋር የመገናኛ እና ለችግር መፍትሄ ማግኛ መድረክ በመሆንም ያገለግላል፡፡ በግል ውይይት መፍትሄ ማግኘት ያልቻለ፣ ለቤተ-ዘመድ መቅረብ ያለበት ጉዳይ ካለም ቤተዘመድ ተወያይቶበት መፍትሄ እንዲገኝለት ይደረጋል፤ ለአብነት ያህል በ16/09/04 በወለህ ማርያም እና በ05/09/05 ሀሙሲት ላይ ምልከታ ባደረግሁባቸው

የቀብርና የአጎበር ሥነ-ሥርዓቶች እንደ ተመለከትኩት የስንብት ስርዓት ከተከናወነ በኋላ በርከት ያሉ ወንዶች ተሰባስበው ጥል ያለባቸውን ሰዎች ለማስታረቅ ይነጋገሩ ነበር፡፡ ስለዚህ አጎበር በማህበረሰቡ መካከል በጸብ ምክንያት መራራቅ እንዳይኖርና ሰላማዊ ግንኙነት ለመፍጠር እንዲቻል በመድረክነትም ያገለግላል፡፡

በስነ-ልቦና በኩል ሀዘንተኞች ሀዘናቸውን በውስጣቸው ይዘው ከሚቃጠሉ፣ በርካታ ወገን በተገኘበት እንባቸውን በማፍሰስ የውስጥ ሀዘን ቃጠሏቸው እንዲቀንስላቸው ያደርጋል፡፡

አጎበር ኢኮኖሚያዊ ፋይዳም አለው፤ይህንንም በደራሾቹና በሃዘንተኞቹ በኩል መመልከት ይቻላል፤ በሀዘንተኞቹ በኩል በየጊዜው የሚደርሳቸው ሰው እየተንጠባጠበ ወደ ቤታቸው ሲመጣ ለመስተንግዶ የሚያወጡትን ወጭ ይቀንስላቸዋል፤ እንዲሁም እንግዶቹን ለማስተናገድ እቤት በመዋል የእርሻን ስራ ማስተጓጎልን ያስቀራል፡፡ በደራሾቹ በኩል ደግሞ በተናጠል ለቅሶ ለመድረስ ሲኬድ በርከት ያለ እንጀራ ይወሰዳል፤ በአጎበር ግን እንጀራው የሚሰጠው በቤተ-ዘመድ በዘር ግንድ ተሰባስቦ ስለሆነ ጥቂት እንጀራ እንዲወስዱ ይረዳል፡፡

ከጊዜ አንጻርም አጎበር የሚከናወንበት ቦታ በአብዛኛው ዘመድ ይኖርበታል በሚባልበት አማካይ ቦታ ላይ ነው፤ ስለዚህ ለቅሶ የሚደርሱ ሰዎች ርቀት ያለው መንገድ ለመጓዝ የሚያባክኑትን ጉልበትና ጊዜ ይቆጥብላቸዋል፡፡

የለቅሶ ሥነ-ሥርዓት ሂደትም ሆነ አጎበር ሥነ-ሥርዓት እንዴት እንደሚከናወን ለመጭው ትውልድ ተጽፎ አይሰጥም፤ ወጣቶቹ ክዋኔው በሚከወንበት ቦታና ጊዜ በመገኘትና በመመልከት ነው የሚያከናውኑት፤ ስለዚህ ሥነ-ሥርዓቱ በመማሪያ መድረክነትም አገልግሏል ማለት ነው፡፡ በቀብርም ሆነ በአጎበር ሥነ-ሥርዓት ቀደም ሲል ዘመድ የሞተባቸው ሁሉ የሟችን ስም በማውሳትና በወቅቱ የሞተው ሰው መከፋታቸውንና ሁኔታቸውን እንዲገልጽላቸው በማሳሰብ እያጉረመረሙ ያለቅሳሉ፡፡ ይህ ጉርምርምታም ሁለት ፋይዳ አለው፤ የመጀመሪያው ለቅሶውን ማሟሟቅ ሲሆን ሌላው ደግሞ፣ ከዚያ በፊት ዘመድ የሞተባቸው ሰዎች ሟችን በማጣታቸው የደረሰባቸውን ችግር መግለጫ መድረክ ሆኖ ያገለግላል፤ በሌላ ጊዜ አውጥተው ለሌላ ሰው የማይገልጹትን ብሶታቸውንም ሌላው እንዲሰማውና ያሉበትን ደረጃ እንዲያውቅላቸው ያግዛቸዋል፤ አፋቸውን ከፍተው

እያጉረመረሙ በማልቀሳቸውም ከታመቀው የሀዘን ስሜታቸው ተንፈስ እንዲሉም ይረዳቸዋል፡፡ ስለዚህ ማጉረምረማቸው ለእራሳቸውና ለቀብርና ለአኀበር ሥነ-ሥርዓቱ ክዋኔና አውድ ፋይዳ አለው ማለት ነው፡፡

በሞት ሥነ-ሥርዓት ከሚከናወኑ ድርጊቶች መካከል አንዱ ለሟች መታሰቢያዎችን ማድረግ ነው፡፡ የአባት፣ የእናት፣ የልጅ፣ የወንድም፣ የእህት ወዘተ. መዘከሪያዎችን ማድረግ እንደ ሃይማኖት አባቶች አገላለጽ ሟች በህይወት ዘመኑ እያለ የሰራው ሃጢአት በቤተክርስቲያን ቅዳሴ ወቅት የሟች የክርስትና ስም እየተጠራ፣ ለመዘከሪያ የተደገሰውን ድግስ የተመገቡ ሰዎችም በልተው ሲጨርሱ ‹‹ነፍስ ይማር!›› እንዲሉ ያደርጋል፡፡ በእነዚህ መዘከሪያዎች፣ ትልቁ ጉዳይ ማቱ ቢመስልም ጠቀሜታው ወይም ፋይዳው ግን ለሟች ብቻ ሳይሆን ለቋሚውም ነው፡፡ ምክንያቱም መደረግ ያለባቸውን ወይም የሚጠበቁ የሟች መዘከሪያዎችን ያላከናወነ ሰው፣ ‹‹የሟችን አፍ ያላበሰ!›› እየተባለ ይታማል፤ ካንድ ሰው ጋር ጥል ከፈጠረም ‹‹አንተ የእከሌህን አፍ ያላበስህ!›› ተብሎ ይሰደባል፡፡ ከማህበረሰቡም እንዲገለል ወይም በማናቸውም ማህበራዊ ጉዳዮች ዘና ብሎ እንዳይሳተፍና እንዲሸማቀቅ ያደርገዋል፡፡ በዚህም በማህበረሰቡ የሚጠበቅበትን ባለማከናወኑ የስነ-ልቦና እረፍት ያሳጣዋል፤ ስለዚህ መዘከሪያዎች ማድረግ ለሟች ነፍስ ይማርነት ብቻ ሳይሆን ለቋሚም እንዳይገለልና ማህበራዊ ግንኙነቱም የጠበቀ እንዲሆን ያግዘዋል፡፡

የሶስቱም ሥነ-ሥርዓቶች ፋይዳ የማህበረሰቡን ማንነት የሚያንጸባርቅና ለቀጣይነቱም የራሱን ሚና የሚጫወት ነው፡፡ ይህንን ፋይዳ አስመልክተው Blumenkrantz, DG. & Goldstein, MB. (2010,41) Van Gennepን በመጥቀስ የሚከተለውን አስፍረዋል፤

> የሽግግር ሥነ-ሥርዓቶች ባህላዊ እሴቶችንና እውቀቶችን ለግለሰብ ወይም ለሰዎች የሚያስተላልፉ፣ በማህበረሰቡ የሚከወኑ እና በማህበረሰቡ የሚመሩ ናቸው፡፡ የሽግግር ሥነ-ሥርዓቶች አንድን ግለሰብ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ አዲስ ደረጃ የሚያሸጋግሩ ብቻ አይደሉም፤ ከዚህ አቻ የሆነ ፋይዳም አላቸው፤ ሽግግሩን ለማክበር ሲባል ማህበራዊ ክዋኔዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋሉ፤ ለማህበረሰቡ የሚያስተምሩ፣ የሚመሩና ለማህበራዊ ህልውናቸው መሰረት የሆኑ እሴቶች መኖራቸውንም ማረጋገጫ ናቸው፡፡

በጥቅሉ የዋግ ኽምራን የወሊድ፣ የጋብቻና የሞት ሥነ-ሥርዓት ከመዋቅራዊ-ፋይዳዊነት አንጻር ስመለከተው ፋይዳው ከመዋቅሩ፣ መዋቅሩ ደግሞ ከፋይዳው ተነጥሎ አይታይም፤

ምክንያቱም የሥነ-ሥርዓቶቹ ቅደም ተከተላዊ ክዋኔ ከሌለ ፋይዳው ሊገኝ አይችልም፤ሥነ-ሥርዓቶቹ ፋይዳ ከሌላቸው ደግሞ ቅደም ተከተላዊ ክዋኔው አይኖርም፡፡

## 7.4 ለውጥና ቀጣይነት በሶስቱ ሥነ-ሥርዓቶች

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ለፎክሎር ህልውና መሰረቱ ለውጥና ቀጣይነቱ ነው፤ተለዋዋጭ እንጂ ቋሚ አይደለም፡፡ ከማህበረሰቡ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ለውጥ ጋር አብሮ ይለወጣል፡፡ ሥነ-ሥርዓትም እንዲሁ፤ Hegland(2003:415)ም Kertzerን ጠቅሰው ተለዋዋጭነትንና ቀጣይነትን አስመልክተው እንደ ገለጹት፣ ሥነ-ሥርዓት የቀጣይነትንና የመለወጥን ባህርይ አጣምሮ የያዘ ነው ብለዋል፡፡ ይህ ተለዋዋጭነቱም ነው ለህልውናው መሰረት የሚሆነው፡፡ የዋግ ኽምራ ሶስቱ ሥነ-ሥርዓቶች ክዋኔ ቀጣይነት ሲታይበት ያለምንም ለውጥ አይደለም፡፡ ከማህበረሰቡ የእድገት ደረጃ እና ከዘመናዊነት ጋር ተያይዞ በሥነ-ሥርዓቶቹ አከዋወን ላይ ለውጥ ይታያል፡፡ ከእነዚህ ለውጦች መካከል ጎላ ጎላ ያሉት የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 7.4.1 ለውጥና ቀጣይነት በወሊድ ሥነ-ሥርዓት

ነፍሰ-ጡር ሴት እንዳትበላ ትከለከል የነበረው አሁንም ከምትከለከላቸው የምግብ አይነቶች መካከል ጥራ ጥሬዎች ይገኙባቸዋል፤ እነዚህ ደግሞ ገንቢ ምግብ ከሚባሉት የምግብ ዓይነቶች ውስጥ የሚመደቡ ናቸው፡፡ እነዚህ የምግብ አይነቶች ደግሞ እርሷንና ጽንሷን ለምትመግበው ነፍሰ-ጡር ሴት እጅግ በጣም አስፈላጊ ናቸው፡፡ ለዚህም ነው Guday(2005:87) ሴቶች ነፍሰ-ጡር ከማይሆኑበት ወቅት ይልቅ ነፍሰ-ጡር በሚሆኑበት ወቅት አመጋገባቸው ከፍ ያለ መሆን አለበት፣ የእረፍት ጊዜ ሊኖራቸው ይገባል፤ ማህበረሰባዊ ድጋፍና ጥሩ አካባቢ ያስፈልጋቸዋል ያሉት፡፡ አንዲት ነፍሰ-ጡር ሴት ገንቢ ምግብ ካልተመገበች ግን እራሷንም ጽንሱንም ጉዳት ላይ ትጥለዋለች ማለት ነው፡፡ በልማድ ሴቶችን ምግብ መከልከል በጎጂ ልማዳዊ ድርጊትነት የሚጠቃለል መሆኑንና የሚያስከትለውን ችግር በመግለጽ Kouyate(2009:3) እንደሚከተለው አስፍረዋል፡፡

> የምግብ አይነኬ ማለት ለአንድ የተወሰነ ማህበረሰብ ክፍል፣ በተለይም ለሴቶችና ለሕጻናት፣ በልማድ ምግብ እንዳይወስዱ ማስገደድ ነው፡፡ እነዚህ ምግቦች ደግሞ እንደ እንቁላል፣ ስጋ፣ አሳ የመሳሰሉ አስፈላጊ ምግቦች ናቸው፡፡ እነዚህን ምግቦች የማይወስዱ

> የምግብ እጥረት ያጋጥማቸዋል፤ የሚወልዱትም ልጅ ክብደቱ አነስተኛ የሆነ፣ ለበሽታ የተጋለጠና አንዳንድ ጊዜም ለሞት የሚጋለጥ ሊሆን ይችላል፡፡

ነፍሰ-ጡሯ ሴት የመውለጃዋ ጊዜ ሲደርስ ድፍድፍና ገንፎ እንዳትበላ ስትከለከል ነበር አሁንም ትከለከላለች፤ ምክንያቱም ድፍድፉና ገንፎው ከሕፃኑ/ኗ ጭንቅላት ተለጥፎ ይገኛል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተው እናት የምትመገበው ምግብ በቀጥታ ወደ ጽንሱ እንደሚሄድ ነው፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ምግቦች ወደ ጽንሱ የሚሄዱት አስፈላጊው የመፍጨት ሂደት ተካሂዶ በእናት እትብት አማካይነት ነው፡፡

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው አንዲት ነፍሰ-ጡር ሴት የመጀመሪያ ልጇን ትወልድ የነበረው አሁንም የምትወልደው በወላጅ እናቷ ቤት ነው፡፡ ይህም በወሊድ የሚያጋጥመን አደጋ የሚያበረታታ ነው፡፡ ምክንያቱም በአንድ ጤና ጣቢያ ክትትል ያደርጉ የነበሩ ነፍሰ-ጡሮች ወደ ሌላ ቦታ በሚሄዱበት ወቅት በሄዱበት የጤና ተቋም የሚገኝ የጤና ባለሙያ ስለ ቀደምት ሁኔታቸው ስለማያውቅ በቂ ድጋፍ ሊያደርግላቸው አይችልም፤ ስለዚህ ችግር ቢፈጠር በክትትሉ ጉድለት ሳይሆን በባለሙያው ችግር ነው ስለሚባል ወደ ጤና ተቋም መሄድን ያደናቅፋል፡፡ ለአብነት ያህል ጭላ በሚባለው የድሃና ወረዳ ቀበሌ ላይ የተመለከትኳት አራስ ክትትል ስታደርግ ከነበረው ሰቆጣ ከተማ በሚገኘው ተፈራ ሃይሉ መታሰቢያ ሆስፒታል ሲሆን የወለደችው ግን እናቷ በምትገኝበት ድሃና ወረዳ ጭላ በተባለው ቦታ በሚገኝ ጤና ጣቢያ ነው፡፡

በወሊድ ወቅት ቀደም ሲልም ሆነ ዛሬም ምጥ ሲራዘም የተቆለፉ ወይም ድፍን የሆኑ ነገሮች ከቤት መውጣት ወይም መፈታት አለባቸው፡፡ ከእነዚህ ነገሮች መካከል በቅርብ የመጣው ቀበቶ ቀደም ሲል የነበረውን ሸምቀቆ ተክቷል፤ ቀደም ሲል ያልነበረው ባለማሰሪያ ጫማም ማሰሪያው ይፈታል፡፡ ስለዚህ የታሰሩ ነገሮች መፈታት ቀጣይነትን ሲያመለክት የሚፈቱ ነገሮች መለያየት ደግሞ ለውጥን ያመለክታል፡፡

ሕፃኑን በብቅል ወይም በጸጉር ቅቤ ማቃመስም ድሮም የነበረ አሁንም የቀጠለ ነው፣ ሕጻን ልጅ እስከ ስድስት ወር ድረስ ከእናት ጡት ወተት ውጭ መውሰድ እንደማይገባው የጤና ባለሙያዎች ይመክራሉ፤ ይህም የሕጻኑ ጤንነት እንዲጠበቅ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዋግ ኽምራ ሕፃኑ እንደተወለደ በቅቤ ወይም በብቅል ማቃመስ በሕፃኑ ጤንነት ላይ ጉዳት

የሚያስከትል አልፎም ለሞት የሚዳርግ ነው፡፡ ይህም እንደሚከተለው ተገልጿል፤ ለብዙ ሕፃናት አለዕድሜያቸው መቀጨት ምክንያት ከሆኑት ጎጂ ልማዶችና ባህሎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ለተወለደ ሕጻን ቅቤ ማዋጥ፣ ሴት ልጅን ማስገረዝና ሕፃናትን የፀሐይ ብርሃን እንዳያገኙ ማድረግ ናቸው (ጤ.ጥ.ሚ.1994፣44)፡፡

በወሊድ ሥነ-ሥርዓት ላይ እንደተመለከትነው አቅምና የሚያርሳት ቤተሰብ ያላት አራስ እስከ ክርስትናው ድረስ (በተለይ ወንድ ከሆነ) ተኝታና በመጋረጃ ተጋርዳ ትታረስ ነበር አሁንም ተጋርዳ ትታረሳለች፡፡ ሕፃኑም የጸሐይ ብርሃን እንዲያገኝ አይደረግም፡፡ ይህም በልጁ ጤንነት ላይ ጉዳት የሚያስከትል ነው፤ ምክንያቱም ኢ.ም.ጥ.ድ(1964፣12 እና14) እንዳሰፈረው፣

> የፀሐይ ብርሃን በጣም ጥሩ ምግብ ነው፡፡ እህልም ያለ ፀሐይ ብርሃን ሊያድግ አይችልም፡፡ ሕፃናትም የፀሐይ ብርሃን ካላገኙ ጠንካራ ሆነው ሊያድጉ አይችልም፡፡ የፀሐይ ብርሃን አጥንትትን ያጠነክራል፡፡ የፀሐይ ብርሃን የሚሰጠው ጥቅም ከሌላ ምግብ ልናገኝ አንችልም፡፡ ቢኖርም በጣም ውድ ነው፡፡ ስለዚሕ ሕፃናት በየቀኑ የፀሐይ ብርሃን እንዲያገኙ ያስፈልጋል፡፡ ተወልደው 10 ወይም 15 ቀን ከሞላቸው በኋላ የፀሐይ ብርሃን ሰውነታቸውን እንዲሞቀው ያስፈልጋል፡፡...የፀሃይ ብርሃን ቫይታሚን ይሰጣል ሕፃን የፀሐይ ብርሃን ካላገኘ የአጥንት መልፈስፈስ ይይዘዋል፡፡ የአጥንት በሽታ የያዘው ልጅ ቶሎ ለመቀመጥ አይችልም ...ስለዚህ ለሕፃናት የጡት ወተት እንደሚያስፈልጋቸው ሁሉ የፀሐይ ብርሃን ያስፈልጋቸዋል፡፡

የፀሐይ ብርሃን አስፈላጊነት በሌላ ምንጭ  እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡

> ለሕፃናት የፀሐይ ብርሃን በቀን ሁለት ጊዜ ጧትና ከሰዓት በኋላ ከዘጠኝ እስከ አሥር ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ለአስር ደቂቃ ማሞቅ በጣም አስፈላጊና ጠቃሚ ነው፡፡ ይኸውም ለአጥንት ቅርጽና ጥንካሬ መድህን የሆነው ባይታሚን ‹‹ዲ›› ከፀሐይ ጨረር ስለሚገኝ ነው፡፡ አንድ ሕፃን የፀሐይ ብርሃን አለማግኘት ለሪኬት በሽታ እንዲጋለጥ ያደርገዋል፡፡ ሪኬት የእግሮቹና የደረቱ አጥንት ከማጣመምና ቅርጽ ከማበላሸት አልፎ በሴቶች ላይ የማህፀን አጥንት ጥበትን ያስከትላል፤ እንዲሁም የደረት አጥንቶች ከመጥበብና ከመጣመም የተነሳ ሳምባ በደንብ ለመተንፈስ ስለሚያስቸግረው ከፍተኛ የጤና ችግር ያስከትላል፡፡ (ጤ.ጥ.ሚ፣1994፣41)

ከዚህ እንደምንረዳው ሕፃኑ የፀሐይ ብርሃን አለማግኘቱ ከሌሎች ተጨማሪ ምግቦች ይልቅ አስፈላጊ የሆነው የእናት ጡት ወተትን ማጣት ጋር እንደሚመሳሰል ነው፡፡

በዋግ ኽምራ ዞን የግርዛት ቀኑ በቆላውና በደጋው የተለያየ ቢሆንም፣ በሁሉም ቦታ የሴት ልጅ ግርዛት ድሮም ነበር፤ አሁንም አለ፡፡ የሴት ልጅ ግርዛት ሴቶቹን ከሚጎዱ ድርጊቶች መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህ ድርጊት የሚፈጸመውም በባህሉ ልጅቷን ለመጥቀም ሲባል ቢሆንም ጉዳት እንዳለው በተለያዩ ጥናቶች ተገልጿል፤ ለአብነት ያህል Kouyate(2009:) እና Boyden,Alula Pankhurst,Yisak Tafere,(2012) ያለ እድሜ ጋብቻ እና የሴት ልጅ ግርዛት ከጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች መካከል የሚካተቱ መሆናቸውን አስፍረዋል፡፡

በሰባት ቀን የአራስ ሴት ልብስ አጠባ የገንፎ አመጋገብ ላይ ቀደም ሲል ቅቤ በማይኖርበት ወቅት በቅባኑግ ሲበላ የነበረው አሁን አሁን ደግሞ በዘይት ሲሆን ማቅረቢያው ደግሞ ቀደም ሲል በአካባቢው የእደ ጥበብ ባለሙያዎች በሚሰራው ገበታ ነበር፤ አሁን አሁን ደግሞ በሳህን ሆኗል፡፡ ስለዚህ ገንፎ መብላቱ አለ፤ ማባያውና መብያው ቁስ ግን ተለውጧል፡፡ የቤት ውስጥ ወሊድም ድሮም ነበር ዛሬም እንደቀጠለ ነው፡፡ ለአብነት ያህል ምልከታ ካደረግሁባቸው ከአራቱ ሶስቱ በቤት ውስጥ የወለዱ ናቸው፡፡ የውይይት መደረኩ ተሳታፊዎች ለዚህ ምክንያት ናቸው ካሏቸው መካከል አበይት የሆኑት የሚከተሉት ናቸው፡፡

1.በአካባቢው ወጣ ገባነት በሁሉም ቦታ አምቡላስ ስለማይገባ ነፍሰ-ጡር ሴቶችን ወደ ጤና ተቋም ለማጓጓዝ የትራንስፖርት ችግር መኖሩ፣

2.ማስወለድ የምትችለው ድንግል ማርያም ናት እንጂ ሰዎች አይደሉም በማለት በቤት ውስጥ መውለድ በጤና ተቋም ከመውለድ የተሻለ አድርጎ የመውሰድ የግንዛቤ ወይም የአመለካከት ችግር፣

3.የመውለጃ ቀንን በትክክል አለማወቅ፣

4.ለመጀመሪያ ጊዜ የሚወልዱ ነፍሰ-ጡር ሴቶች የምጥ ህመምን በትክክል አለማወቅ፣

5.በጤና ባለሙያዎች አማካይነት አስፈላጊ የሆነ የምክር አገልግሎት አለማግኘት፣

6.የጤና ባለሙያዎች የአቅም ችግር፣ ለአብነት ያህል አንዷ የውይይቱ ተሳታፊ ምጥ ተይዛ ወደ ጤና ተቋም ስትሄድ ‹‹ደም ማነስ ነው፤ የመውለጃ ጊዜሽ ገና ነው›› ተብላ ወደ ቤቷ ስትሄድ ወዲያው መውለድ፣ ሌላ ሴትም መውለጃሽ ገና ነው ተብላ ወንዝ

ተሻግራ ወደ ቤቷ ልትሄድ ስትል ወንዙ ላይ መውለድና ልጁ ለሞት መዳረግ፤

7.ወደ ጤና ጣቢያ ሲኬድ በስብሰባ ምክንያት ባለሙያዎች አለመገኘት፣

8. የባለሙያዎች የሥነ-ምግባር ችግር፤ ነፍሰ-ጡር ሴቶችን በስነ-ስርዓት አለማስተናገድ፣

9. በቤት ውስጥ ሲወልዱ የሚያዋልዷቸው ሴቶች ስለሆኑ፣ በጤና ተቋም ሲወልዱ ወንዶች ሊያዩን አይገባም በማለት ሀፍረት፣

10. በቤት ውስጥ ሲወልዱ የሚከናወኑ ነገሮች በጤና ተቋም አለመኖር፣ ለአብነት ገንፎ[115]፣ ቀይ ዶሮ፣ ምጥ ለያዛት የሚጠጣ የሞቀ ነገር አለመኖር፣

ከዋግ ኽምራ ጤና መምሪያ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው[116] ከሐምሌ እስከ መጋቢት 2006 ይወልዳሉ ተብሎ በእቅድ የተያዘው የነፍሰ-ጡሮች ቁጥር 10,607 ሲሆን ከእነዚህ መካከል 60% በሰለጠነ ባለሙያ 40% ደግሞ በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች እንደሚወልዱ ታቅዶ፣ በጤና ኤክቴንሽን ሰራተኞች የወለዱት 710፣ በሰለጠነ ባለሙያ የወለዱት ደግሞ 1501 በድምሩ 2211 የእቅዱን 20.84% ነው፡፡ ከዚህ ክንውን መረዳት የሚቻለው ቀሪው 79.16 % የወለዱት በባህላዊ መንገድ በቤታቸው ነው፡፡

በዞኑ ነፍሰ-ጡር ሴቶች በጤና ተቋማት ላለመውለድ በመምሪያው በምክንያትነት የተጠቀሱት ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1.የአመለካከት ችግር-በሰላም የመውለድ ስራ የማርያም ሆኖ እያለ በህክምና ተቋማት መውለድ የድንግል ማርያምን ስራ መጋፋት ተደርጎ የሚወሰድ ነው ማለት፡፡ ካሁን በፊት ልጆቻችንን በቤታችን ውስጥ እየወለድን ነው የኖርነውና ምንም አልሆንም ማለት፡፡ በዚህም አንዲት ነፍሰ-ጡር ሴት ወደ ጤና ተቋም ልትመጣ ስትል ባሏ ብቻ ሳይሆን እናት አባቷ እና ባጠቃላይ ማህበረሰቡም ይቃወማታል፡፡

2.በዞኑ አንዲት ሴት የመጀመሪያ ልጇን መውለድ ያለባት ከወላጅ እናቷ ቤት ነው የሚለውም በነፍሰ-ጡሮች ላይ ችግር እያስከተለ ነው፡፡ ለአብነት ያህል በዚህ ዓመት

[115] በአንዳንድ የጤና ጣቢያዎች ለአብነት ያህል በድሃና ወረዳ ጭላ በተባለው የጤና ጣቢያ ለወሊድ ገንፎ እየተገነፉ ነው፡፡ አንዷ የውይይቱ ተሳታፊ እንደገለጸችው በጤና ጣቢያ ምጡ ሲረዝም ነፍሰ-ጡር ሴቶች ቀይ ዶሮ ያልታረደልን ሆኖ ነው እያሉ ነው፡፡

[116] ከዞኑ የጤና መምሪያ ኃላፊ ከአቶ ይልማ ሞላ በ25/07/06 የተገኘ መረጃ ነው፡፡

ሁሙሲት በሚባለው ቀበሌ በሚገኘው የጤና ጣቢያ ክትትል ስታደርግ የነበረች ነፍሰ-ጡር ሴት የወላጅ እናቷ ወደምትገኝበት ዛሮታ ተክለሓይማኖት ወደሚባል ቀበሌ በሚገኘው ጤና ጣቢያ ለመውለድ ሂዳ፣ ተከታታይ ምርመራዋን በሚመለከት በቂ መረጃ ባለመኖሩ ለህልፈት ተዳርጋለች፡፡

3. ሴት እንጂ ወንድ አዋላጅ አያዋልደኝም የሚሉም አሉ፡፡

4. በሙያው የሰለጠነ ባለሙያ እጥረትና አሉ የሚባሉት ባለሙያዎችም የክህሎት ብቃት ችግር ያላቸው መሆኑ፡፡ ለዚህም አንዳንድ ነፍሰ-ጡሮች ለምርመራ ወደ ጤና ተቋም ሲመጡ ባለሙያዎቹ ‹‹የመውለጃ ቀናችሁ ገና ነው›› ብለው የሚመልሷቸው እነሱ ከገለ ጹት ቀን አስቀድሞ በመውለዳቸው የባለሙያዎቹን እውቀት ተአማኒነት አሳጥቷል፡፡

5. የጤና ተቋማቱ የሚገኙበት መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ነፍሰ-ጡሮችን ለማጓጓዝ ምቹ አለመሆኑ ወይም ወጣ ገባነቱ፣

6.በቂ የጤና ተቋማትና የማዋለጃ ቁሳቁሶች አለመኖርና አለመሟላት፤ በዞኑ ከሚገኙት ሃያ ዘጠኝ ጤና ጣቢያዎች ውስጥ ደረጃቸውን የጠበቁት አስራ ዘጠኙ ብቻ ናቸው፤ እስሩ ግን በማዋለጃ መሳሪያዎች፣ በግንባታውና በሰው ሓይል የተሟሉ አይደሉም፡፡

ከዚህ የምንረዳው በዋግ ኽምራ በጤና ተቋማት ከሚወልዱት ይልቅ በቤት ውስጥ የሚወልዱት ቁጥር ከፍተኛ መሆኑን አስመልክተው የመረጃ አቀባዮቹ በውይይት መድረኩ የጠቀሷቸው ምክንያቶች በዞኑ የጤና መምሪያ ኃላፊ ከተጠቀሱት ጋር ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ መሆናቸውን ነው፡፡ ስለዚህ የቤት ውስጥ ወሊድ ዛሬም የቀጠለ መሆኑን እንረዳለን፡፡

በጤና ተቋማት የሚካሄደው ወሊድ አነስተኛ ቢሆንም ካሁን በፊት ያልነበረ በጤና ተቋማት መውለድና ክትትል ማድረግ ግን በመጠኑም ቢሆን እየተካሄደ ነው፡፡ ይህም ነፍሰ-ጡር ሴት ቤት ውስጥ ስትወልድ የሚከናወኑ ድርጊቶችንና መማጸኖችን እያስቀረ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አሁንም ባንዳንድ የጤና ተቋማት ‹‹የማርያም መሸኛ›› ተብሎ ገንፎ እየተገነፋ ነው፡፡

በወሊድ ሥነ-ሥርዓት ክዋኔ ወቅት ዛሬም ታሪክ ይጠቀሳል፡፡ በምዕራፍ አንድ እንደተገለጸው የዋግ ሹሞች በትረ ስልጣን ያከተመው በ1966 ዓ.ም ነው፡፡ ይሁን እንጂ ባሁኑ ጊዜም በቤት ውስጥ ወሊድ ጊዜ ሴቶቹ ህጻናቱን በሚያቃምሱበት ወቅት ከሚጠሯቸው የሹማምንት ስሞች መካከል አንዱ ዋግሹም ነው፡፡ ይህም ዞኑ ከደርግ ዘመነ መንግሥት በፊት በምን አይነት ገዥዎች ይገዛ እንደ ነበር ታሪክን ማውሳት የቀጠለ መሆኑን እንረዳለን፡፡

ቀደም ሲል ለክርስትና ማስነሻ ወይም ማስጠመቂያ የሚሆነው ውሃ ወደ ቤተክርስቲያን ይወሰድ የነበረው ሙሉ በሙሉ በቅል ነበር፡፡ አሁን አሁን ግን አልፎ አልፎ ከፕላስቲክ በተሰራ የውሃ መያዣም ይወሰዳል፡፡

### 7.4.2 ለውጥና ቀጣይነት በጋብቻ ሥነ-ሥርዓት

ጋብቻ ከመመስረቱ አስቀድሞ መጣራት ካለባቸው ነገሮች መካከል የዝምድና እርቀት ነው፡፡ ቀደም ሲል እስከ አስራ ሁለትና ሰባት ቤት የነበረው የዝምድና እርቀት አሁን ደግሞ ወደ አራትና ሶስት ወርዷል፡፡ ቀደም ሲል የእደ ጥበብ ባለሙያ ያልሆኑ ሰዎች የእድ ጥበብ ባለሙያ ከሆኑ ሰዎች ጋር አይጋቡም ነበር፡፡ አሁን ግን እየተጋቡም ነው፤ አሁን ለጋብቻ መስፈርቱ ምን አላት/አለው ነው፤ እርሻ አላት ደሞዝ አላት ነው እንጂ የማን ዘር ናት የሚለው ቀርቷል፤ወጣቶቹ ተጋቢዎች ‹‹አጥንት አይቆረጠምም፡፡›› እያሉ ነው፡፡ መለኪያው የእደ ጥበብ ባለሙያ ነው አይደለም ሳይሆን ቤቱን/ቤቷን ማስተዳደር የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ አቅም አለው ወይም የለውም የሚል ነው፡፡ ይህንን ለውጥ አስመልከተው አቶ ተቀባ እንዲህ ብለዋል፤ ‹‹ከእደ ጥበብ ባለሙያዎች ጋር ጋብቻ ሲወርድ ሲዋረድ ክልክል ነበር፡፡ አሁን ግን እየተጋቡ ነው፡፡ ዋናው ጠንክሮ ይሰራል የሚለው ነው፡፡‹‹ አጥንቱ አይጋጥም›› ሌላው (አትጋቡ የሚለው ለማለት ነው) ‹‹እዛው ያጉረምርም›› ይባላል (ቁ.የ.መ.አ.27)፡፡

መተጫጨትን በሚመለከት ቀደም ሲል ሙሉ በሙሉ እጮኛነት የሚፈጸመው በወላጆች በጎ ፈቃደኝነት ብቻ ነበር፤ የልጆች መብት የሚጠበቅበት አልነበረም፡፡ ሳይፈላለጉ በጽንስ ላይ እያሉ እና ከአንቃልባ ይታጩ ነበር፡፡ አሁን ግን አልፎ አልፎም ቢሆን ተጋቢዎች እርስ በእርሳቸው ተዋውቀውና ተፈላልገው መጋባት እየተጀመረ ነው፡፡

ቀደም ሲል ማርዳ ማሰር በዞኑ ወስጥ የመታጨት ምልክት ሆኖ ያገለግል ነበር፡፡ ባሁኑ ጊዜ ግን እሱ ቀርቶ በአዲስ ልብስና በመስቀል ተተክቷል፣ የልጅቷ መታጨት ማሳወቂያውም የሚታሰረው ማርዳ ሳይሆን በወሬ ሆኗል፡፡

ቀደም ሲል እጮኛሞች እስከ ሠርጋቸው ድረስ አይተያዩም፣ አይተዋወቁም ነበር፡፡ ቤተሰቦቻቸውንም እንዲሁ አያዩም ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ በአሁኑ ጊዜ ሙሉ በሙሉ የለም ባይባልም መጠኑ ግን ቀንሷል፡፡ ምክንያቱም ያለ እድሜ ጋብቻ እንዳይፈጸም ለማድረግ ሲባል፣ በጋብቻ ስርዓቱ የቀበሌ መስተዳድርና በተዋረድ የሚገኙ የፍትህ አካላት ጣልቃ በመግባት በመቆጣጠር ላይ በመሆናቸው ተጋቢዎች የእድሜና የኤች አይ.ቪ. ኤድስ ምርመራ እንዲያደርጉ በመገደዳቸው ነው፡፡ ይህንንም ከሰቆጣ ወረዳ ቀበሌዎች የአንዱ የሀሙሲት ቀበሌ አስተዳዳሪ የሆኑት አቶ ደሳለኝ ስዩም እንዲህ ይገልጹታል፣

> እኛ አንዲት ልጅ እድሜዋ ከ18 ዓመት በታች ከሆነች ምርመራ እንዲከናወን ሰቆጣ ከተማ ወደሚገኘው ሆስፒታል እንልካታለን፣ እህል ውሃ እንዳይጠፋም ለአባት ለእናት ቅድሚያ ምክር እንሰጣለን፣ እምቢ ብለው እድሜያቸው ለአቅመ ሄዋንና ለአቅመ አዳም ያልደረሱትን ከዳሩም ለህግ እናቀርባለን፣ ካሁን በፊት እንዳይድሩ ከነገርናቸው መካከል እምቢ በማለት የዳረውን ለህግ አቅርበን በአምስት ዓመት እስራት እንዲቀጣ አድርገናል ብለዋል (ቁ.የ.መ.አ.7)፡፡

ምርመራው የሚከናወነውም ሁለቱ የወደፊት ተጋቢዎችና የሁለቱም ቤተሰቦች በተገኙበት ሰቆጣ ከተማ በሚገኘው ሆስፒታል ነው፡፡ በዚህ አጋጣሚ ከሰርጋቸው በፊት የማይተያዩት የወደፊት ተጋቢዎችና ዘመዶች ይተያያሉ፡፡

ቀደም ሲል በዋግ ኽምራ በግንቦት ወር ሠርግ አይደረግም፣ ጋብቻም አይፈጸምም ነበር፡፡ አንዱ ምክንያት ዋና የፈል (የእርሻ ስራ) የሚከናወንበት ወቅት ስለሆነ ነው፡፡ ሌላው ምክንያት ደግሞ በዚህ ወቅት የሚካሄድ ጋብቻ አይጸናም በሚል እምነት ነው፡፡ ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ የድጋሚ ጋብቻ ግን ይካሄዳል ነበር አሁንም ይካሄዳል፡፡ ይህም ለጋብቻው መጽናት ስጋት ቢኖርም ሴቷ ለዘር የሚሆን እህል ስለምታመጣ ‹‹ሲሆን ትዳር ይሆናል ካልሆነ ግን አላባ (ምርት) ይዛ ትመጣለች››ይባላል (ው.መ.)፡፡ አሁን አሁን ግን በግንቦት ወር የመጀመሪያ ጋብቻም እየተፈጸመ ነው፡፡ ቀደም ሲል በክረምት ሠርግ

አልነበረም፤ አሁን ግን በሀምሌም ሠርግ አለ፡፡ የሠርግ ቀናትን በሚመለከት በገጠር እሁድ ሠርግ አይደረግም ነበር፡፡ አሁን አሁን ግን በገጠር ወረዳ ዋና ከተማዎች እሁድም ሠርግ እየተደረገ ነው፡፡ ቀደም ሲል ብዙ ደግሶ ለማብላትና ለክብር መጨነቅ ነበር፤ አሁን አሁን ግን ይህ ጎልቶ አይታይም፡፡ ምክንያቱም በተለይ በገጠር ወረዳ ዋና ከተማዎች የእንጀራ ቁርጥ ማቅረብ ለክብር አለመጨነቅን ያሳያል፡፡ በዚህም በገጠር 100 ሰው የሚስተናገድበት እንጀራ በገጠር ወረዳ ዋና ከተማ 500 ሰው ይሰተናገድበታል፡፡ይህ ለውጥ የሚያመለክተው የኢኮኖሚያዊ አቅም ማነስንና የቁጠባ ግንዛቤ ከክብርና ዝና ፍለጋ ይልቅ ላቅ ያለ ቦታ እየተሰጠው መሆኑን ነው፡፡

የሠርግ ድግስ እህልም በጎረቤቶች ትብብር ‹‹ጤፍ ማፍሰስ›› ተብሎና በሠርግ ጥሪነትም በማገልገል በድንጋይ ወፍጮ ይፈጭ ነበር፡፡ ብቅሉም እንዲሁ በድንጋይ ወፍጮ ሲፈጭ ‹‹አስክር›› ይባል ነበር፡፡ በርበሬውንም ወንዶች በሙቀጫ ይወቅጡ ነበር፡፡ ባሁኑ ጊዜ ግን በየቦታው ወፍጮ በመተከሉ እነዚህ ነገሮች የሚፈጩት በወፍጮ ነው፡፡

የሠርግ ዳስ አሰራርን በሚመለከት ቀደም ሲል ሙሉ በሙሉ በደደሆ ቅጠል ብቻ ነበር፡፡ አሁን ግን የደደሆው ቅጠል እንደልብ ካለመገኘቱና የተገኘውንም መንጥሮ ላለማጥፋት ሲባል በፕላስቲክ፣ በቁንጶ በርበሬና በባህር ዛፍ ቅጠል ይሰራል፤ ነባሩ ባህል እንዳይቀር ግን የተወሰነ የደደሆ ቅጠል ጣል ይደረግበታል፡፡

የሠርግና የሌሎችን ድግሶች የወጥ አሰራር በሚመለከት ቀደም ሲል በሁሉም አካባቢ ሙሉ በሙሉ ይሰራ የነበረው በሸክላ ድስት ነው፤ ባሁኑ ጊዜ ግን ዋጋው በመወደዱ፣ ወጡን ለመስራት ብዙ ሰው በመፈለጉ እና ብዙ የማገዶ እንጨት በማስፈለጉ ከተወሰኑ አካባቢዎች በስተቀር በትልቅ የብረት ድስት እየተሰራ ነው፡፡ ወጡን በድስት የሚሰሩት ሴቶች ብቻ ነበሩ፤ አሁን ግን ሁሉም ባንድ ላይ ሲሰራ ጉልበት የሚጠይቅ በመሆኑ የሚሰራው በወንዶች ነው፡፡ ከዚህም የሴቶች ስራ ይባል በነበው ወጥ ስራ ላይ ወንዶች በመሳተፋቸው ለውጥ እየታየ መሆኑን እንረዳለን፡፡ በትልቅ የብረት ድስት የተሰራው ወጥ ለማስተናገድ የሚቀርበው ግን ወደ የሸክላ ድስት ወይም ትናንሽ የብረት ድስቶች ተቀድቶ ነው፡፡ ይህም ለውጥና ቀጣይነት ተጣምረው መቀጠላቸውን ያመለክታል፡፡

የሠርግ ድግስ ምግብ አቀራረብን በሚመለከት ቀደም ሲልና አሁንም አልፎ አልፎ በአውራጅ ላይ እንደሚታየው እንጀራው በደደሆ ቅጠል ላይ ተደርጎ ነበር፤ ከተጠገበም መግፈፍ (የተረፈውን ለራስህ መውሰድ) ነበር፡፡ እንጀራው በቅጠልና በሳር ላይ ሆኖ ሲቀርብ ደን ይጨፈጨፍ ነበር፡፡ እንጀራውም ይባክን ነበር፡፡ ባሁኑ ጊዜ ግን በብዛት የሚቀርበው ለአምስት ወይም ለስድስት ሰው በተመደበ መስሪያ ሆኗል፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው በገጠር ወረዳ ዋና ከተማዎችም እንጀራው ተቀርጦ ለየግል በሳህን፣ መጠጡም ቀደም ሲል በገንቦ እየቀረበ እንደልብ የሚጠጣው በትንሽ የፕላስቲክ መጠጫ ኩባያ እየቀረበ ነው፡፡ ይህም በሂደት ቁጠባው እየጨመረ መምጣቱን ያመለክታል፡፡

ይህንን የምግብ አቀራረብ ለውጥ በሚመለከት የመረጃ አቀባዮቹ የተለያየ አስተያየት አላቸው፡፡ ይኸውም በአዎንታዊ ጎኑ ቶሎ ቶሎ የሚጎርሰውና ቀስ ብሎ የሚበላው ለየብቻው እንዲበላ ያደርጋል የሚል ሲኖር፣ በአሉታዊ ደግሞ እንጀራው የእስላምና እምነት ተከታይ ሊቀርሰው ክርስቲያን ሊቀርሰው የማይታወቅ ነው፣ የሚሰጠውም እንደ እረኛ በእጅ ነው፡፡ መጠጡም ፍንጃል በምታህል መጠጫ እየቀረበ ነው፡፡ ስለዚህ ቁጠባው ባይከፋም ባህላችን ሳይጠፋ መቀጠል አለበት የሚሉም አሉ (ቡ.ተ.ው.3)፡፡

ሙሽራዋ በሠርጓ እለት ከምግብ ትከለከል ነበር፤ አሁንም ትከለከላለች፤ እንዲያውም በሰርጓ እለት በስራ ተጠምዳ ትውል ነበር አሁንም ትውላለች፡፡ ምክንያቱም ከአማቾቿ ቤት የመጸዳጃ ቦታ ጥያቄ እንዳታቀርብ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት እንድትበላ የሚደረገው በጣም አነስተኛ ምግብ ነው፤ ከተገኘ እቃተኛ ካልተገኘ ደግሞ በወጥ እንጀራ መጠኑ ግን አነስተኛ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ስትለፋ የምትውለው ሙሽራ ተመጣጣኝ ምግብ እንዳታገኝ ያደርጋት የነበረ ዛሬም የቀጠለ ነው፡፡

ቀደም ሲል ሙሽራዎች በጨለማ ሳይሆን ጮራ ተመትተው እየታዩ በመብራት ይውጡ ይባል ነበር፤ አሁን ግን ሙሽራዎች በጨለማም እየሄዱ ነው፡፡

ቀደም ሲል የሠርግ ጥሪ የሚከናወነው ዘመድ በሚገኝበት አካባቢ ሁሉ በቃል ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ አገልግሎቱ ባለበት አካባቢ ጥሪው በተንቀሳቃሽ ስልክም እየተከናወነ ነው፡፡

ቀደም ሲል በዋግ ኽምራ ባእድ እንጂ ዘመድ ሚዜ አይሆንም ነበር፣ ምክንያቱም ቃል በመግባት ዝምድና ለመፍጠር እንደ መሳሪያ ያገለግል ስለነበር ነው፡፡ ባሁኑ ጊዜ ግን ዘመድ (ወንድምም ሳይቀር) ሚዜ ሆኖ ወደ ሴት ቤት እየዘመተ ነው፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በዋግ ኽምራ፣ ሴት ሙሽራ ሚዜ አልነበራትም፣ አሁንም በገጠር የላትም፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን በተለይ በገጠር ወረዳዎች ከተሞች የሴት ሚዜ እየተመለመለ ነው፡፡ ተግባራቱም ቀደም ሲል እንደተገለጸው ከከተማ ለሚመጡ ሰርገኞች ከገጠሮቹ የተለየ ምግብ ለማዘጋጀትና ሙሽራዋን በዘመናዊ መንገድ ለማጋጌጥ ነው፡፡

የሠርግ ቀናት መጠንን በሚመለከት ቀደም ሲል በዞኑ በሚገኙ በሁሉም ወረዳዎች የሙሽራዋ ሁለት ቀናት የሙሽራው ሁለት ቀናት፣ በድምሩ አራት የሠርግ ቀናት ነበሩ፡፡ ባሁኑ ጊዜ ግን ለቁጠባ ሲባል የሁለቱም ባንድ ቀን ሆኗል፡፡

ሴቶች ቀደም ሲል እንጀራ በመሶብ አሸክመው ወደ ሰርጉ ቤት ይወስዱ ነበር፣ አሁን አሁን ግን የሚወስዱት ዱቄትና እህል ነው፡፡ የሚቋጠረውም ቀደም ሲል በአቅማዳ አሁን አሁን ደግሞ በኬሻ ነው፡፡

ከወንድ ወገን ወደ የሴት ሙሽራ ቤት ከሚወሰዱ ነገሮች መካከል አንዱ ጧፍ ነው፡፡ ባሁኑ ጊዜ የመብራት አገልግሎት ባለባቸው ቀበሌዎች ግን አይወሰድም፡፡ እንዲሁም ቀደም ሲል በአካባቢው የእደ ጥበብ ባለሙያና ባካባቢው ከሚገኘው ቀንድ በሚሰራ ዋንጫ ይወሰድ የነበረው ማር አሁን አሁን ደግሞ የፋብሪካ ውጤት በሆነው ብርጭቆ እየተወሰደ ነው፡፡

ለአማጭ ብር መስጠት ድሮም ነበር ዛሬም አለ፣ ቀደም ሲል ለአማጮች ይሰጥ የነበረው ሶስት ብር ነበር፣ አሁን ግን እስከ መቶ ብር አድጓል፡፡ ይህንንም ሰዎች ለመስጠት ፈልገው ሳይሆን ‹‹እከሌ ይህን ያህል ብር ስለሰጠ›› በሚል ብቻ በይሉኝታ ለመስጠት የሚገደዱ አሉ፡፡ ይህም አቅም የሌላቸውን ሰዎች ለችግር የሚዳርግ ነው፡፡ ቀደም ሲል ስጦታ የማይሰጣቸው የነበሩት ትልቅና ትንሽ ሚዜዎችም ባሁኑ ጊዜ ሲሰጣቸው ተመልክቻለሁ፡፡

ከሙሽራዋ ወደ ሙሽራው ቤት የሚወሰዱት የእቃ መያዣ እና አዝመራ መቋጠሪያም ከአቅማዳ ወደ ፌስታል ተቀይሯል፡፡

የዋግ ኽምራ ህብረተሰብ ጋብቻ  የእርስ በርስ ወይም አገው ለአገው Endogamous  ብቻ አልነበረም፤ አሁንም አይደለም፡፡ በተለይም ከአማራ እና ከትግሬ ጋርም ጋብቻ መመስረት ይቻል ነበር፤ አሁንም ይቻላል፡፡ ከእነዚህ የዞኑ አጎራባች ማህበረሰቦች ውጭም ለተለያዩ ጉዳዮች ወደ ዞኑ ከሚመጡ ከተለያዩ የብሄረሰብ አባላት ጋር ጋብቻ መመስረትም የተከለከለ አይደለም፡፡ ስለዚህ ከራስ ማንነት (አገውነት) ውጭም ጋብቻ መመስረት ስለሚቻል በዞኑ የሚከናወነው የጋብቻ ዓይነት ከራስ ማንነት ውጭ Exogamous ነው፡፡ ይህም በቅርብ ጊዜ የተጀመረ ሳይሆን ቀደም ሲልም ይፈጸም እንደነበር የመረጃ አቀባየ እንዲህ ተናግረዋል፡፡

> ድሮ ጋብቻ የነበረው ወንዝ ተሻግሮ ነው እንጂ ያንድ መንደር ልጆች ጋብቻ አንፈጽምም፡፡ ከወንዝ ወዲያ ማዶ ካሉት ጋር መጋባት ያስፈልግ የነበረውም ከወንዝ ወዲህ ማዶ ሰው ብንገድል መሸሸጊያ እንዲሆኑ ተብሎ ነው፡፡ አሁን ግን ጋብቻ በሰፈር ሆኗል፡፡ ከአማራ፣ ከትግሬ፣ ከኦረሞ ጋርም ጋብቻ ነበር፤ አሁንም አለ፡፡ በዋግ ጋብቻ ከዋግ ተወላጆች ጋር ብቻ አይደለም፤ ምክንያቱም ‹‹ቂጣ የሚጣፍጠው ስራና (ከስንዴ ጋር አተር ወይም ባቄላ ሲደባለቅ) ሲሆን ነው፡፡›› ሰውም ደስ የሚለው ገብስማ( ጥቁርና ነጭ ቀለም ያለው) ሲሆን ነው፡፡ ለአብነት ያህል የዋጉ ጀግና የሌቴናል ጀኔራል ኃይሉ ከበደ ባለቤት ወ/ሮ ሸዋነሽ አብርሃ ትግሬ ናቸው (አጽንኦት የራሴ) ( ቁ.የ.መ.አ.27) ፡፡

Wuduም (1995) ከደርግ ዘመን በፊት የነበሩት የዋግ ገዥዎች ከተለያዩ የብሄረሰብ አባላት ጋር በጋብቻ ተሳስረው እንደ ነበር በስራቸው አስፍረዋል፡፡ ለአብነት ያህል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፡፡

1.የአጼ ይኩኖ አምላክ ዘር የሆነው ሮቤል የዋግሹም ጅርወስን የልጅ ልጅን አግብተው ነበር፡፡ (በ14ኛው ክፍለ ዘመን) (19)117

2.ዋግ ሹም አስከራጃን የአጼ ልብነ ድንግል አማች ነበሩ፡፡ (1508-40) (21)

3.የድሃና ገዥ የነበሩት ድሃና ሹም ዘስላሴ፣ የአጼ ፋሲለደስን ልጅ አግብተው ነበር፡፡ (56)

4.ዋግ ሹም ክንፉ የየጁ ገዥ የነበሩትን የራስ ጉግሳ ልጅን አግብተው ነበር፡፡

117 በተከታታይ በዚህ መልክ የተጻፉት፣ በጽሁፉ ውስጥ ሀሳቡ የሚገኝባቸውን ገጾች የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

(120)... የጁየ የሆኑት ዋግ ሹም ጓንጉል የዋግ ሹም ብሩ ልጅን ወ/ሮ ብርሃኔ ብሩን አግብተው ነበር፡፡ (158)

5. የትግሬው ራስ ወልደ ሥላሴ የዋግ ሹም ዳሞ ዘር አለባቸው፡፡ (114)

6.ወደ ኋላ አጼ ተክለ ጊዮርጊስ የተባሉት ዋግ ሹም ጎበዜ፣ ወደ ኋላ አጼ ዮሀንስ የተባሉት የራስ ካሳን እህት ወ/ሮ ድንቅነሽን አግብተው ነበር፡፡ (140) ደጃች ሃይሉ የትግሬ ተወላጁን ወ/ሮ ሸዋነሽ አብርሃን አግብተው ነበር፡፡ የትግሬው ደጃዝማች አብርሃ ሁለት ሴት ልጆቻቸውን ከዋግ ሹም ጓንጉል ልጅና ከደጃዝማች ሃይሉ ከበደ ልጅ ጋር አጋብተው ነበር፡፡(159)

ከዚህ የምንረዳው ዋግ ኽምራዎች ከተለያዩ አካባቢ ሰዎች ማለትም ከሸዋ፣ ከየጁ፣ ከትግሬ ተወላጆች ጋር ጋብቻ ይመሰርቱ እንደነበር ነው፡፡ ይህ የዋጎች ጋብቻም ፖሊቲካዊ ፋይዳ እንደነበረው Heran(2002:80) እንደሚከተለው አስፍረዋል፤... የፋሲለደስ የጋብቻ ትስስር ፖሊሲ ተፈላጊ ግቡን መትቶ ነበር፤ ይህም የዋግ እና የላስታ ሰዎችን ከጎንደር ነገስታት ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ማረጋጋት ነበር፡፡ ምንም እንኳ የገዢዎች ጋብቻን ለፖለቲካ ዓላማ ማዋል ከሥርዓቱ ማክተም ጋር የደከመ ቢመስልም አሁንም ያልጠፋ መሆኑን ሲገልጹም Heran(2002:204) ከኃይለ ሥላሴ ዘመነ-መንግሥት በኋላ ጋብቻን የፖለቲካ ትብብርን ለማጠናከር ለማዋል የነበረ ፍላጎት እየቀነሰ ቢመጣም፣ የዚህ ማህበራዊ ጠቀሜታ ግን ቀጥሏል፡፡ በማለት ገልጸዋል፡፡

ስለዚህ በዋግ ኽምራ ህብረተሰብ ዘንድ አገው ከአገው ጋር ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ማህበረሰቦች ጋርም የመጋባቱ ሁኔታ ድሮም የነበረ ዛሬም የቀጠለ ከሌሎች ማህበረሰቦች ጋር የሚኖርን ግንኙነት የሚያጠናክር መሆኑን እንረዳለን፡፡

ያለ እድሜ ጋብቻም ድሮም ነበር፤ አሁንም ግን ቀጥሏል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ የተለያየ ነው፡፡ የመጀመሪያው ወላጆች የልጆቻችንን ዓለም ሳናይ መሞት የለብንም የሚልና ልጅቷ ለአቅመ ሄዋን ከደረሰች ከጋብቻ በፊት እንዳትደፈር ሲባል ነው (ቁ.የ.መ.አ.23)፡፡ ሌላው ምንም እንኳ አንዲት ልጅ ለጋብቻ መድረስ አለመድረሷ በሆስፒታል ምርመራ

እየተረጋገጠ ቢሆንም[118]አሰራሩ ግን ችግር እንዳለበት የውይይት መድረኩ ተሳታፊዎች ተናግረዋል፡፡ ይህም ትንሽን ልጅ ለመዳር ትልቅን ማስመርመርና ፈቃድ ማግኘት፣ የሠርግ ድግስ ከሆነ ልጅቷ መዳሯ እንዳይታወቅ በዝክርና በአማች እዝ ስራ ድግስ ልጅን መስጠት እየታየ ነው (ው.መ.)፡፡

ስለዚህ የዋግ ኽምራ ህብረተሰብ የሠርግ ሥነ-ሥርዓት ክዋኔ ቀጣይነቱ ከለውጥ ጋር የተጣመረ መሆኑን እንረዳለን፡፡

### 7.4.3 ለውጥና ቀጣይነት በሞት ሥነ-ሥርዓት

ቀደም ሲል ቡታ ነገራ በሁለት ሰዎች አማካይነት ይደረግ የነበረው የቅበሩ ጥሪ ባሁኑ ጊዜ ሙሉ በሙሉ ባይቀርም አገልግሎት ባለበትና ስልኩ ባላቸው ግን በተንቀሳቃሽ ስልክም ይከናወናል፡፡ ቀደም ሲል በለቅሶ ላይ የሚገኙ ሁሉም ሴት ለቀስተኞች ነጠላቸውን የሚለብሱት ዘቅዝቀውና ጫፉን ቋጥረው ነበር፤ አሁን ግን የነጠላ አለባበስ ሀዘንተኞችንና ሌላዎቹን መለያ ሆኗል፡፡ ሀዘንተኞቹ ጫፉን ቋጥረው ሲለብሱ ሌላዎቹ ግን ጥለቱን ዘቅዝቀው ብቻ ይለብሳሉ፡፡ የቅርብ ዘመዶች የነጠላቸውን መሃል ቋጥሮ ትከሻ ላይ ጣል ማድረግ ግን አሁንም ቀጥሏል፡፡ ቀደም ሲል ለቀብር የሚሄዱ ለቀስተኞች ነጭ ነጠላ አይለብሱም ነበር፤ ቆሸሽ ያለውን(ያደፈውን) ነበር የሚለብሱት፡፡ አሁን ግን ነጭ ነጠላም እየተለበሰ ነው፡፡ ልዩነቱ የገረማቸው አንድ አባትም ‹‹አሁን ይህ ህዝብ ታቦት የሚሸኝ እንጂ ሊቀብር የሚሄድ ይመስላል›› ሲሉ አድምጫለሁ፡፡

ቀደም ሲል በዞኑ ዘመድ ሲሞት ይታይ የነበረው የሴቶችና ወንዶች ፊት መላጥና የሴቶች ጸጉር መንጨት አሁንም በብዙዎቹ ወረዳዎች ቀጥሏል፡፡ድርጊቱ ቀደም ሲል በዞኑ በሁሉም ወረዳዎች በስፋት ይታይ ነበር፤ ባሁኑ ጊዜ ግን በዝቋላ ወረዳ ብቻ እየቀረ መሆኑን ተመልክቻለሁ፡፡ በሌላዎቹ ወረዳዎች ግን አሁንም እየተፈጸመ ነው፡፡ ቀደም ሲል በገጠር ከቀብር በኋላ እያስተዛዘኑ ከአዘንተኞች ጋር ለሰባት ቀናት ያህል አብሮ ማደር አልነበረም፤ አሁን ግን የቅርብ ዘመዶችና ጎረቤቶች ከሃዘንተኞቹ ጋር አብረው በማደር ያስተዛዝናሉ፡፡

[118] ሰቆጣ ከተማ ከሚገኘው የተፈራ ሃይሉ መታሰቢያ ሆስፒታል የተገኘው መረጃ እንደሚያመለከተው በ2006 ዓ.ም በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ለጋብቻ የኤች.አይ.ቪ. እና የአድሜ ምርመራ ለማድረግ ከመጡት 560 ተመርማሪዎች ውስጥ ከ18 ዓመት በላይ የሆኑት 422 ሲሆኑ ከ11-17 ዓመት የሆኑትና ማግባት እንደሌለባቸው ደብዳቤ የተጻፈባቸው ደግሞ 138 ናቸው፡፡ ይህም 24.6 % መሆኑ ነው፡፡

በሶስቱም *ሥነ-ሥርዓቶች* ክዋኔ ወቅት እንደተመለከትኩት ሙሉ በሙሉ ባይሆንም አብዛኛዎቹ የመገልገያ ቁሳቁሶች የፋብሪካ ውጤቶች ናቸው፡፡ ለአብነት ያህል በሠርግ ድግስ በሸክላ ድስት ብቻ ይሰራ የነበረው ወጥ በትልቅ የብረት ድስት እየተሰራ ነው፤ በመሶብ ብቻ ይበላ የነበረው እንጀራም በሳህን እየተበላ ነው፡፡ ከሙሽራዋ ወደ ሙሽራው ቤት የሚወሰዱት እቃዎች መያዣ እና አዝመራ መቋጠሪያም ከአቅማዳ ወደ ፌስታል ተቀይሯል፡፡ በአጎበር በመሶብ ይያዝ የነበረው እንጀራ በሳህን፣ በቶፋ ወይም በቅል ይያዝ የነበረው ወጥም በጎማ እየተያዘ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በአካባቢው የእድጥበብ ባለሙያዎች፣ ከአካባቢው ቁሳቁስ የሚሰሩና የህብረተሰቡን የፈጠራ ችሎታ የሚያንጸባርቁ ቁሳቁሶች በመጥፋት ላይ ናቸው፡፡

ምንም እንኳ ኽምጣኛ ለረጂም ጊዜ በዞኑ በአፍ መፍቻ ቋንቋነት ከመነገር አልፎ ከ1988 ዓ.ም ጀምሮ በማስተማሪያ ቋንቋነትና በትምህርት አይነትነት እየተሰጠ ቢሆንም፣ በ*ሥነ-ሥርዓቶቹ* ክዋኔ ወቅት (በሠርግ የዘፈን ቃል ግጥሞችና በቀብር የሙሾ ቃል ግጥሞች) ቋንቋው በአፍ መፍቻ ቋንቋነት በሚነገርባቸው ወረዳዎች ጭምር በቋንቋው የተገጠመ ቃል-ግጥም አላገኘሁም፡፡ ስለዚህ አሁንም ህብረተሰቡ በቋንቋው (በኽምጣኛ) ስነቃላትን እየገለጸ አለመሆኑን እንረዳለን፡፡

በጥቅሉ የሶስቱ *ሥነ-ሥርዓቶች* ክዋኔ ለውጥንና ቀጣይነትን ያጣመረ ነው፡፡

## 7.5 ማጠቃለያ

የሶስቱንም *ሥነ-ሥርዓቶች* ክዋኔ እንደተመለከትነው የየራሳቸው የሆነ የክዋኔ ቦታ እና ጊዜ አላቸው፡፡ ለዚህም ነፍሰ-ጡሯ ሴት ለመውለጃ የሚሆናትን ቦታ አስቀድማ ታመቻቻለች፣ ለሰርግም መጠኑ እንደ ደጋሾቹ አቅም ተወስኖ ቢሰፋ እና ቢጠብም *ሥነ-ሥርዓቱ* የሚከወንበት የእርጥብ ቅጠል ጣል የሚደረግበት ዳስ ይሰራል፤ ሞትም የቀብር፣ የማርገጃ እና የአጎበር ቦታ አለው፡፡ ሶስቱም *ሥነ-ሥርዓቶች* ሲከወኑ በተለያዩ አልባሳትና ጌጣጌጦች ይታጀባሉ፡፡ በሶስቱም *ሥነ-ሥርዓቶች* ክዋኔ ወቅት ሃዘንና ደስታ ተቀላቅለው ታይተዋል፡፡ በወሊድ ምጥ ሲራዘም ጭንቀት፣ ነፍሰ-ጡሯ በቶሎ ስትወልድ ደግሞ ደስታ ተንጸባርቋል፡፡ በጋብቻም ልጅን መዳርና መኳል፣ ለወግ ማእረግ ማድረስ፣ ደስታን ያላብሳል፡፡ በሠርግ ዘፈን ከተገጠሙት ቃል ግጥሞች ይዘት እንደተረዳነው የሙሽራው ወይም የሙሽራዋ ሚች

ቤተሰቦች ሲጠቀሱ የደስታ ድባብ ሰፍኖበት የነበረው ዳስ ለአጭር ጊዜም ቢሆን የሀዘን ድባብ ይሰፍንበታል፡፡ ይህም ሃዘንና ደስታ የማይነጣጠሉ መሆናቸውን አሳይተዋል፡፡ በሶስቱም ሥነ-ሥርዓቶች ክዋኔ ወቅት ተምሳሌታዊ ፍች ያላቸው ድርጊቶች ተፈጽመዋል፤ ተምሳሌታዊ ፍች ያላቸው ቁሳቁሶችም አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ የእነዚህ ተምሳሌታዊ ነገሮች ፍችም ድርጊቱን አጉልቶ አሳይቷል፡፡

ለሶስቱም ሥነ-ሥርዓቶች ምሉእነት የሚረዱ ቅደም ተከተላቸውን የጠበቁ ድርጊቶች ተፈጽመዋል፤ የሥነ-ሥርዓቶቹ ተዋናዮችም በሽግግር ደረጃ የሚያልፉ ናቸው፡፡ ከቀደምት ቦታቸው ይነጠላሉ፤ መካከል ላይ ይሆናሉ፤ ከሥነ-ሥርዓቱ ክዋኔ በኋላ ደግሞ ከቀጣይ ደረጃ አካላት ጋር ይቀላቀላሉ፡፡ በወሊድ ነፍሰ-ጡሯ ነፍሰ-ጡር ካልሆኑት ትነጠላለች፤ ወልዳ ከወላጆች ጋር ባለመቀላቀሏ መሀል ላይ ትሆናለች፤ ስትወልድ ደግሞ ከወላጆች ጋር ትቀላቀላለች፡፡ በጋብቻም ሙሽራዎች የሠርጋቸው ቀን ሲወሰን ለመጋባት ካልተዘጋጁት ይለያሉ፤ ጋብቻቸውን ገና ባለመፈጸማቸው ደግሞ መካከል ላይ ይሆናሉ፤ ሰማኒያቸውን ሲፈጽሙ ደግሞ ካገቡ ሰዎች ምድብ ይቀላቀላሉ፤ሟች ከህያዋን ይለያል፤ እስከሚቀበር ድረስ መሀል ላይ ይሆናል፤ ሲቀበር ደግሞ ከሙታን መንደር ይቀላቀላል፡፡

በሶስቱም ሥነ-ሥርዓቶች በወሊድ አራሷ፣ በጋብቻ ሙሽራዎቹ፣ በሞት ሟችና ሀዘንተኞቹ ዋና ተዋናዮች ቢሆኑም የሌላዎቹም ተሳትፎ ለሥነ-ሥርዓቶቹ ክዋኔና ቀጣይነት ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ በዚህም የሥነ-ሥርዓቶቹ ፋይዳ ለተዋናዮቹ ብቻ ሳይሆን ለሌላው የህብረተሰብ ክፍልም ነው፡፡ በመሆኑም ሥነ-ሥርዓቶቹ ለግለሰብና ለህብረተሰብ ኢኮኖሚያዊ፣ ስነ-ልቦናዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ፋይዳ ለግሰዋል፡፡ ይህ ፋይዳም ከሥነ-ሥርዓቶቹ መዋቅር የተነጠለ አይደለም፤ ስለሆነም መዋቅራዊ-ፋይዳቸው ለህልውናቸውና ለቀጣይነታቸው አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

የተለያዩ ምሁራንም የተለያዩ መስፈርቶችን መለኪያ በማድረግ ሥነ-ሥርዓቶችን በአይነት በአይነት ሲከፍሉ እምነትን እንደ አንድ መስፈርት የወሰዱ አሉ፡፡ ለአብነት ያህል Sims and Stephens(2005,107) ይዘታቸው ከሃይማኖት ጋር የተያያዘ መሆንን እና አለመሆንን መለኪያ በማድረግ፣ ሥነ-ሥርዓቶችን መንፈሳዊና እና አለማዊ ብሎ መክፈል እንደሚቻል ገልጸው፣ አብዛኛዎቹ ሥነ-ሥርዓቶችም መንፈሳዊና አለማዊ ነገሮችን ቀላቅለው የያዙ

ናቸው፤ ለአብነት ያህል የጋብቻና የሞት ሥነ-ሥርዓቶችን ብንመለከት፣ መንፈሳዊውንም አለማዊውንም አዋህደው ያየዙ መሆናቸውን አስፍረዋል። ቀደም ሲል የተመለከትናቸው የዋግ ኽምራ ዞን የወሊድ፣ የጋብቻና የሞት ሥነ-ሥርዓቶችም አለማዊና መንፈሳዊ ይዘቶችን አካተው የሚገኙ ናቸው፡፡

ሥነ-ሥርዓቶቹ በማህበረሰቡ የሚከወኑ ናቸው፤ ማህበረሰብ ደግሞ በውስጣዊም ሆነ በውጫዊ እንቅስቃሴ ምክንያት ለውጥ ያሳያል፤ሥነ-ሥርዓቶቹም ይህ ለውጥ ታይቶባቸዋል፡፡ ስለዚህ ለውጡ ወደፊት ተፋጥኖ አሁን የሚታየው ክዋኔያቸው ከመጥፋቱ አስቀድሞ መሰነዱ ጠቀሜታው ላቅ ያለ ነው፡፡

ሶስቱ አበይት የሽግግር ሥነ-ሥርዓት አይነቶች አራቱን የፎክሎር ዘውጎች አጠቃለው የያዙ በመሆናቸው በክዋኔያቸው የዋግ ኽምራ ማህበረሰብ ቃል-ግጥሞች፣ ማህበረሰባዊ ክውን ጥበባት፣ ልማድና ቁሳዊ ባህል ጎልቶ ወጥቶባቸዋል፤ በጥቅሉ ሥነ-ሥርዓቶቹ የማህበረሰቡን ማንነት ለማሳየት አገልግለዋል፡፡ Napocaም(2011:4) ሥነ-ሥርዓትን ማጥናት ማህበረሰቡንም ማጥናት ወይም የማህበረሰቡን ማንነትም ማየት መሆኑን ሲገልጹ፣ ሥነ-ሥርዓት የአንድን ማህበረሰብ ገጽታ የሚያሳይ መስተዋት ነው ማለታቸው ይህንን እውነታ የሚያመለክት ነው፡፡

## 7.6 ይሁንታ

ይህ ጥናት ያልተመለከታቸው ርእሰ-ጉዳዮች አሉ፤ለወደፊቱ በሌሎች አጥኚዎች ሊታዩ የሚገባቸው ናቸውና መጠቆም እፈልጋለሁ፤ እነዚህም የመጀመሪያው ሶስቱ ሥነ-ሥርዓቶች በሚከወኑበት ወቅት የሚታዩ በሴቶች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ድርጊቶችን የሚመለከት ነው፡፡ ቀደም ብየ እንደገለጽኩት ሶስቱም ሥነ-ሥርዓቶች ለውጥና ቀጣይነትን አጣምረው የያዙ በመሆናቸው የህብረተሰቡ ሥርዓተ-ጾታዊ አመለካከትም ተንጸባርቆባቸዋል፡፡ በዚህ ወቅት ዛሬም ነባሩን አመለካከት በማንጸባረቅ በሴቶች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩ አሉ፤ እነዚህን ማጥናት ተገቢ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በሶስቱ ሥነ-ሥርዓቶች ክዋኔ ወቅት የሚንጸባረቁ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችንና ባእድ አምልኮዎችን የሚመለከቱ ድርጊቶች ናቸው፡

## የዋቢ መጻህፍት ዝርዝር

*ሀ/ የታተሙ*

መሓሪ ረዳኢ። (1995)፡፡ *የተሻሻለውን የቤተሰብ ህግ ለመገንዘብ የሚረዱ አንዳንድ ነጥቦች*።አዲስ አበባ፤ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ማህተመስላሴ ወ/መስቀል፡፡ (1961)፡፡ *ባለን እንወቅበት፡፡የኢትዮጵያ ባህል ጥናት*፡፡አዲስ አበባ፤አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ሞገስ እቁባ ጊዮርጊስ (ሊቀ መዘምራን)፡፡ (1969)፡፡*መርሐ-ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት*፡፡አስመራ፤ኮከበ ጽባሕ ዘማህበረ ሐዋርያት ማተሚያ ቤት፡፡

ብርሃነ መስቀል ደስታ (ደጃዝማች)፡፡ (1951)፡፡ *ዜና ላል ይበላል*፡፡አዲስ አበባ፤ብርሃንና ሠላም ቀ. ኃ.ሥ ማተሚያ ቤት፡፡

ተስፋ ገብረ ሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ፡፡ (1991)፡፡ *መዝገበ ጸሎት ባለ ሃምሳ ሦስት አርእስት (ዓይነት)*፡፡አዲስ አበባ፤ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት ፡፡

----------(አዘጋጅ)፡፡ (1993)፡፡ *ተአምረ ማርያም ባለ ሁለት መቶ ሰባ ምእራፍ* ፡፡አዲስ አበባ፤ ተስፋ ማተሚያ ቤት ፡፡

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ።(1966)።*የኢትዮጵያ ታሪክ፡አክሱም-ዛጉዬ 2ኛ መጸሀፍ*።አዲስ አበባ፤ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ.ማተሚያ ቤት።

ታዬ ገ/ማርያም። (1964)፡፡*የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ*።አዲስ አበባ፤ ሴንትራል ማተሚያ ቤት።

አስራት ታደሰ፡፡ (2004)፡፡ *የአባ መረብ መንፈስ ፤ብዙም ያልተነገረለት የመጀመሪያው ኢትዮጵያ ጀኔራል፡፡ የግጥም መድብል*፡፡አዲስ አበባ፤አልፋ አታሚዎች፡፡

አያሌው ሲሳይ። (2007)።*የአገው ህዝቦች እና የዛጉዌ ስርወ መንግሥት ታሪክ* .አ.አ፤ንግድ ማተሚያ ቤት።

ከፍያለው መራሒ (ቀሲስ)። (1992)። *የሴቶች መንፈሳዊ ህይወት*።አዲስ አበባ፤አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ዓለማየሁ ሞገስ፡፡ (1956)፡፡*ሠርግና ልማድ*፣ አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የባህልና ቱሪዝም ቢሮ፡፡(2001)፡፡ ዋጋው ሀይሉ፡፡ ‹‹የአማራ ባህል ገጽታዎች›› *የአማራ ሕዝብ ባህልና ቋንቋ*፤1-104፡፡አዲስ አበባ፤ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትህ ቢሮ፡፡ (1997)፡፡ *የቤተሰብ ሕግ*፡፡ ባህር ዳር ፤ቅዱስ ገብርኤል ማተሚያ ድርጅት፡፡

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፡፡ (1980)፡፡ *መጽሐፍ ቅዱስ፡፡ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት*፡፡አዲስ አበባ፤ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

የኢትዮጵያ የምግብ ጥናት ድርጅት፡፡ (1964)፡፡ *ብልህ እናት*፡፡አዲስ አበባ፤ንግድ ማተሚያ ቤት

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት፡፡ (1952)፡፡*የፍትሐ ብሔር ሕግ* ፡፡አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ማተሚያ ቤት፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን፡፡ (1989) ፡፡*ተአምረ ማርያም ግእዝና አማርኛ 3ኛ እትም*፡፡አዲስ አበባ፤ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡፡

ያለ ስም፡፡ (1992)፡፡*መጽሀፈ ክርስትና፣መጽሀፈ ተክሊል.መጽሀፈ ቄደር ወመጽሀፈ ቀንዲል*፡፡አዲስ አበባ፤ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡፡

ያለ ስም፡፡ (1995)፡፡ *ፍትሐ ነገሥት ንባብና ትርጓሜው 2ኛ እትም* ፡፡አዲስ አበባ፤ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡(1998)፡፡*የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር*፡፡አ.አ፤አልፋ አታሚዎች፡፡

ዮሀንስ ሃይለ ማርያም። (1940) ፡፡*የዓለም ታሪክ ከጂኦግራፊ ጋር የተያያዘ*።፡፡አዲስ አበባ፤ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

ደስታ ተክለወልድ፡፡ (1962)፡፡*ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት*፡፡አዲስ አበባ፤አርቲስክ ማተሚያ ቤት

ጌታቸው ስንሻው። (2000) ፡፡‹‹የሀምራ ህዝብ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ስርዓት››*በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን የተካሄዱ የባህላዊ አንትሮፖሎጂ ጥናቶች*።አ.አ።ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የቤተሰብ ጤና ክብካቤ መምሪያ፡፡ (1994)፡፡ *ለልምድ አዋላጅ ማስተማሪያ መመሪያ*፡ አዲስ አበባ፤ ግራፊክ አታሚዎች፡፡

ፈቃደ አዘዘ። (1991)።*የሥነ ቃል መምሪያ*፤አዲስ አበባ፤ቦሌ ማተሚያ ቤት።

ፍትህና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት። (1991)። *የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ (ለውይይት የቀረበ)* አዲስ አበባ፤ኢትዮጵያ ብሄራዊ የምርጫ ቦርድ ጽህፈት ቤት ማተሚያ ቤት።

Adhana, Mengsteab.(1988). ‹‹ Ancestor Veneration in Blean Culture, ›› *Proceedings of the Eigth International Conference of Ethiopian Studies.* (Taddese Beyne ed.) Vol.I .747-750.

Anbesa,Tefera. (1999).‹‹ Differences between the Amharic Dialects of Gonder and A.A›› *The Beta Israel in Ethiopia and Israel Studies on the Ethiopian Jews.*ed by Tudor Parfitt and Emanuela Trevisan Semi.Great Britain:Curzon Press..257-274.

Applleyard, D.L.(1988). ‹‹The Agaw Languages: A Comparative Morphological Perspective ›› *Proceeding of Eighth International Conference of Ethiopian Studies.* (Taddese Beyne ed.), Vol.I .581-592.

Aymro, Wondmagegnehu and Joachim Motovu. (1970).*The Ethiopian Orthodox Church.* Addis Ababa:Berhanena Selam H.S.I Printing Press.

Bahru, Zewde. (2002).*A History of Modern Ethiopia 1855-1974.* Addis Ababa:Addis Ababa University Press.

Bascom ,William R. (1965). ‹‹ Four functions of Folklore ›› Alan Dundes.(ed). *The Study of Folklore.*Engle Wood Cliffs:N.J Prentice.298-305.

Bauman, Richard & Briggs L.Charles. (1990)." Poetics and Performance as critical perspectiveves on language and Social Life" Annual Rev.Anthropology, 59-88. Retrieved from: anthro.vancouver.wsu.edu

Beard-Moose, Christina Taylor. (2010 ). ‹‹ *Feminist Anthropology* ›› Birx.James .H.(ed.) *21st Anthropology a Reference Handbook vol. 1 and 2.* edited by H. Jamese Birx,Los Angeles/London: Sage Publication Inc.997-1007. Retrieved from: *knowledge.sagepub.com*

Bell, Cathrine. (1997).*Ritual: Perspectives and Dimensions.* Oxford: Oxford University Press.

Ben-Amos, Dan. (1988).*Folklore in Context Essays.* New Delhi: South Asian.

Bender, M.L. & others (eds.). (1976). *Language in Ethiopia.* London: Oxford University press.

Blumenkrantz, DG., & Goldstein, MB. (2010). *Rites of Passage as a Framework for Community interventions with youth. Global Journal of Community Psychology Practice*, 1(2), 41-50. Retrieved from: *www.gjcpp.org*

Cox James L. (1998). *Rites of Passage in contemporary Africa: Interaction between Christian and African traditional religion.* Cardiff:Cardiff Academic Press.

Creswell J, W, (2009).*Research Design: Qualitative, Quantitative and Mixed Method Approaches 3rd ed.* Losangeles: Sage publications Inc.

Daniel, Kasomo. (2009). ‹‹An analysis of the Rites of Passage and their relation to Chris-tianity.››*International Journal of Sociology and Anthropology*..1(8).156-166. Retrieved from: *www.academicjournals.org*

Davies ,Douglas. (1994).‹‹ Introduction:Raising the Issues.›› in *Rites of Passage* by Jean holm with Hohn Bowker.London:Pinter Publisher Ltd.1-9. Retrieved from: *books.google.co.uk*

Dawson, Catherine.(2002). *Practical Research Methods A user-friendly guide to mastering Research Techniques and projects.* Trowbridge, Wiltshire: Cromwell Press. Retrieved from: *www.amazon.co.uk*

Debika, Saha. (2010). ‹‹ Ceremonies ›› Birx.James .H.(ed.) *21st Anthropology a Reference hand book vol. 1 and 2.* Los Angeles/London:Sage Publication Inc.

764-772. Retrieved from: *knowledge.sagepub.com*

Dorson, Richard.M. (1972) " Introduction: Concepts of Folklore and Folk life studies" in Richard. M.Dorson, (ed.).*Folklore and Folk life: An Introduction.* Chicago and London: the University of Chicago Press.1-50. Retrieved from: *eprints.hud.ac.uk*

Draper, Janet. (2003). ‹‹Men/s passage to fatherhood: an analysis of the contemporary relevance of transiton theory.›› *Nursing Inquiry*, 10(1),66-78. Retrieved from: www. *ncbi.nlm.nih.gov*

Dundes, Alan. (2004)."Foklorstics in the Twenty First Century".*Journal of American Folklore* 118 (470).385-408.

_____.(2007)." From Etic to Emic units in the Structural Study of Folktales".In *The Meaning of Folklore: The Analytical Essays of Alan Dundes* (Edited and Introduced by Simon J.Bronner).Logan, Utah: Utah University Press..88-100.

_______.(2007)." Structuralism and Folklore" *The meanining of Folklore: The Analytical Essays of Alan Dundes* (Edited and Introduced by Simon J.Bronner) Logan,Utah:Utah university Press.145-153.

Duranti, Alessandro.(1997).*Linguistic Anthropology.* Cambridge: Cambridge University Press.

Federal Demicratic Republic of Ethiopia Population Census Commission,Central statistics Agency. (2010).*The 2007 Population and Housing Census of Ethiopia Results for Amhara region part I: Statistical Report on Population size and characterstics.* Addis Ababa: Brana printing Enterprize.

Federal Negarit Gazetta of the Federal Democratic Republic of Ethiopia. 2000.*The Revised Family Code proclamation* No.213`.

Finnegan, Ruth. (1977). *Oral poetry: Its nature, significance and social context.*London, New York, Melbornc: Cambrige University Press.

______.(1984).*Oral Literature in Africa.* Nairobi: Oxford University Press.

Galaty, G, John. (1983) ‹‹Ceremony and Society: The Poetics of Maasai Ritual ›› in Man new Series, 18( 2). 361-382. Retrieved from: *www.siue.edu/*

*Gamst, Frederick. (1968)* The Qemant Agaw of Ethiopia: A study in culture Change of Pagan-Hebraic people. *Ph.d thesis in Anthropology. The University of California.*

Gomm, Roger .(2008).*Social Research Method of Critical Introduction (2nd ed.) Great Britain*: Palygrove Macmillan.

Gottlieb, Alma. (2006) ‹‹Ethnography:Theory and Methodes›› in A *Hand Book for Social Science Field Research: Essays and Bibiligraphic sources on research Design and Methods.* Perecman Ellen and Sara R.Curran(eds.).London:Sage Publication Inc. Retrieved from: *www.sagepub.com*

Hegland,Mary Elaine (2003.)‹‹Shi'a Women's Rituals in Northwest Pakistan:The Shortcomings and Significance of Resistance.›› *Anthropological Quarterly,* 76(3). 411-442. Retrieved from: *books.google.co.uk*

Hill,Jeff & Peggy, Daniels. (2008). *Life Events and Rites of Passage: The Customs and Symbols of Major Life-Cycle Milestones,Including Cultural,Secular and Religious Traditions Observed in the united States.*U.S.A: Omnigraphics Inc. Retrieved from: *books.google.com*

Jabbour, Alan. (2004). *Interacultural and Intercultural : The Two faces of Folklore.In Folklore, Public Sphere and Civil Society.* (Ed. M.D.Muthukumaraswamy and Molly Kausal.New Delhi:IND COM.Press..17-22.

Jansen,Hugh W.M. (1983)." Ethics and the Folklorists " *Hand Book of American Folklore.* Richard Dorson (ed.) Bloomington : Indiana University Press. 52-56.

Kassam, Anessa. (1999). ‹‹ Ritual and Classification: A Study of the Booran Oromo

Terminal Sacred Grate Rites of Passage.›› *Bulletin of the School of Oriental and African Studies* .University of London/62 (3),484-503. Retrieved from: www.isam.org.tr

Kearney,J. Peter.(2009). <<The Barrets town experience: a rite of passage>> *Irish Journal of Sociology* .17(2,) 72—89.

Keesing, M.Roger & Andrew J.Strathern. (1998).*Cultural Anthropology:A Contemporary Perspective* 3rd ed.Fortworth: Harcourt Brace College Publishers.

Kifle, Wodajo, (2002). ‹‹Wedding Customs among the Amhara" in Alula Pankhurest (ed.) *Ethnological Society Bulletin.* I(II),27-29.

Kurtz, Donald V. (2001).*Political Anthropology Paradigms and Power.* USA: West view Press. Retrieved from: ink.springer.com

Laneri, Nicola (ed.). (2008).*Performing Death: Social Analysis of Funerary Traditons in the ancient near east and Mediterranean.*U.S.A:The University of Chicago.

Retrieved from: *https://oi.uchicago.edu*

Leach, Maria (ed.) .(1950).*Standard Dictionary of Folklore Mythology,and Legend* Vol.II. NewYork: New York Publisher.

Leslau,Wolf. (2007).*Concise Amharic Dictionary.*A.A: Shamma Books.

Levine, Donald N.(2000).*Greater Ethiopia:The Evolution of A Multiethnic Society.*Chicago and London: the University of Chicago Press.

Lipsky ,George A. (1962).*Ethiopians: Its people, Its society, Its culture.* New Haven: HRAF Press.

Malefijt, De Waal Annemarie.(1968).*Religion and culture,an introduction to Anthropology of religion.*London : Collier-Macmillan Limited. Retrieved from: *archive.org*

Marshall,Douglas A. (2002.) ‹‹ Behavior, Belonging, and Belief: A Theory of Ritual Practice ›› in *Sociological Theory.* 20 (3) 360-380. Retrieved from: *www.usouthal.edu/*

Matthews, Bob & Liz Ross. (2010).*Research Method: A practical guide for the Methods in Evaluation Research.* London: Sage Publication.

McCann, James. (1987).*From poverty to Famine in Northeast Ethiopia:A Rural History 1900-1935.* Pluladelphia: University of Pennsylvania Press.

Mcleod Julie and Rachel Thomson, (2010) *Researching Social Change.*Los angeles/London/New Delhi:SAGE Publication Ltd.

Murchison, Julian M. (2010). *Ethnography Essentials Designing,Conducting,& Presenting Your Research.*U.S.A: John Wiley and Sons, Inc Retrieved from: *www.wiley.com*

O' Reilly Karen. (2005.) *Ethnographic Methods* .London and New York:T.J, international Ltd.

Oring; Elliot. (1976)." Three functions of Folklore: Traditional functionalism as Explanation Foklorstics" *Journal of American Folklore.* 89 (35).67-80.

Pankhurst, Richard. .(1982).*History of Ethiopian Towns from the middle Ages to the Nineteenth Century.*Wiasbaden: Franz Steiner Verlag Gmbh.

Paulin, V. young & Calvin, Schmidt.(1998).*Scientific Social Survey and Research.* New Delhi Prentice-hall of India.

Pink, Sarah (2007).Doing *visual Ethnography 2nd ed.*London:Sage Publications.

Punch, F.Keith.(2000).*Developing Effective Research Proposals.* London:SAGE Publication Ltd. Retrieved from: *www.uk.sagepub.com*

Randall, Collins. (1988).*Sociology of Marriage and the Family: Gender, Love, and Property 2nd ed.*U.S.A: Nelson-Hall Inc. Retrieved from: *www.scribd.com*

Rappaport, A.Roy. (1999).*Ritual and Religion in the making of humanity.*Cambrige: Cambrige University Press.

Rasing, Thera. (1995).*Passing on the rites of passage:Girls initiation rites in the Conext of an urban Roman catholic Community on the Zambian Copperbelt. Amsterdum*: African studies centre. Retrieved from: *www.tandfonline.com*

Reichardt, Charles S. & Thomas D.Cook. (1985)"Beyond qualitative versus quantitative>> Charles S.Reichardt and Thomas D.Cook (eds.) *Qualitative and Quantitati ve Methods in Evaluation Research.*London: Sage Publication.7-32.

Seale,Clive (ed.) (2005).*Researching Society and Culture.2nd ed.*London:Sage Publiction Ltd.

Sergew Hable Sellassie.(1972).*Ancient and Medieval Ethiopia.Addis Ababa:United Printers.*

Svoboda Cynthia J. W. (2010 )‹‹Festivals and Rituals› Birx James .H.(ed.) *21st Century Anthropology A Reference Hand book.V.I and II.*London:Sage Publication Inc.773-781.Retrieved from: *knowledge.sagepub.com*

Sims ,Martha C. & Martine Stephens. (2005).*Living Folklore: An introduction to the Study of people and their traditions.* Logan, Utah: Utah University Press.

Spradley, p, James. (1980).*Participant observation.* USA: Holt, Reinehart and Winston. *www.uk.sagepub.com*

Taddesse Tamrat .(1972).Church and State in Ethiopia.1270-1527.Oxford: the Clarendon Press.

______.1988." Process of Ethnic Interaction in Ethiopian History: the case of the Agaw" *The journal of African History.* (29).1, 5-18.

______.(2002). "The Mateb," Alula Pankhurest (ed.).*Etnological Society Bulletin 1953-1961.*No.9.354-358.

Thomson,S. B. (2011).‹‹Qualitative Research: Validity.›› JOAAG, 6 (1).77-82. Retrieved from: *joaag.com*

Turner, V.w. (1967).*The forest of Symbols: aspects of Ndembu Ritual.*London: Cornell University press.

_______.(1970).*The Ritual Process: Structure and anti-Structure.* Chicago: Aldine Publishing Company..

Ullendorf, Edward. (1966).*The Ethiopians: An Introduction to Country and People.* Great Britain: Oxford University Press.

Van Gennep, Arnold. (1960).*The Rites of Passage.* Monika, A.B Vijedom and Gabrielle Li Caffee (Trans).Chicago: The University of Chicago Press.

Vansina,Jan.(1985).*Oral Tradition as History.*London:The University of Wisconsin Press. *www.jamescurrey.com*

Vaughn, Lisa M. (2010) ‹‹ Marriage and the Family ›› *in* H. Jamese Birx (ed) *21st Anthropology a Reference handbook vol. 1 and 2.* Los Angeles/London:Sage Publication inc.pp162-173. Retrieved from: *www.sage-ereference.com*

Wilson, Wiliam, A. (1989)." Documenting Folklore", in Elliott Oring, (ed.) *Folk Groups and Folklore Genres: An Introduction.*Logan, Utah: Utah State University Press. .225-254.

Wudu Tafete Kassu. (1998).‹‹The Two Wagshums and the Battle, ›› *Adwa.*Victory Centenary Conference 26 February-2 March 221-235.

Yin, K.Robert. (2003).*Case study Research design and methods 3rd ed.* London: Sage Publications Inc. Retrieved from: *www.amazon.co.uk*

Zebec,Turtko. (1995).‹‹The Carnival Dance event in Croatia as a Rites of Passage›› (trans.) Nina H.Antoljak.NarUmJet.32/1..201-217. Retrieved from: *hrcak.srce.hr*

ለ/ያልታተሙ

መኮንን ዓለማየሁ። (1974)፡፡ ‹‹የዋግ አውራጃ የአማርኛ ግጥሞች›› የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ክፍል፣የባችለር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ።አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ማሞ ብዚል። (1988) ።‹‹በሰቆጣ ከተማ የአሸንድዬ ቃላዊ ግጥሞች ጥናት›› የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ክፍል፣ የባችለር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ።አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ሽቱ አያንና ሌሎችም። (1988) ።‹‹የአዊ ህዝብ ባህላዊ ገጽታዎች ጥናታዊ ጽሁፍ››፣ ለአዊ ባህል፣ ታሪክና ቋንቋ ሲምፖዚየም የተዘጋጀ (ያልታተመ )።

ታደሰ እሸቱ። (1997) ፡፡ ‹‹የሰቆጣ ከተማ እና አካባቢዋ የርሃብ ግጥሞች ይዘት ትንተና›› የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል፣የባችለር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ።አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ታደሰ ወዳጅና አፀደ ተፈራ። (1993) ፡፡ ‹‹በዋግ ኽምራ መስተዳድር ዞን የኽምጣኛ ቋንቋ የስርዓተ ትምህርት ዝግጅትና የፕሮግራም ትግበራ ሂደት ገፅታ ፣ ሂደቱን አስመልክቶ ለሚካሄደው አውደ ጥናት የተዘጋጀ የመወያያ ጽሁፍ ››፡፡

አላምረው ገ/ህይወት። (1986) ። ‹‹የዋግ ታሪክ በአጭሩ››፣*ለለ፣ቅጽ 1፣ቁጥር 1፣11-16።*

አበባው መኮነን፡፡ (2001)፡፡*የዋግ ፖለቲካዊ ጥናት(ከ1967-እስከ ግንቦት1983)*

*አሸናፊ ጌታሁን፡፡(1999) ‹‹የዋግ ብሔረሰብ የሠርግ ስነ-ስርአት አሉታዊና አዎንታዊ ገጽታ ››ለዋግ ኽምራ ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ የተያዘ ጥናት ወረቀት እቅድ ክንውን የተዘጋጀ፡፡*

አፀደ ተፈራ። (1989) ።‹‹ የዋግ ታሪክ ቅኝታዊ ጥናት ››ለዋግ ኽምራ ባህል፣ቱሪዝምና ማስታወቂያ መምሪያ የቀረበ።

_________፡፡(1996)፡፡ *በሰቆጣ ከተማ የክብረ በዓላት አከባበርና ባህላዊ ጨዋታዎች የኢትዮጵ ያ* ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ።አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ዋግ ኽምራ ባህል ቱሪዝምና ማስታወቂያ መምሪያ፡፡ (1993) ፡፡ኽምራ ጎኽ መጽሔት፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ፡፡(1987)፡፡ *ሕገ መንግሥት፡፡አዲስ አበባ፣*

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ፣የማእከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ፡፡ (2003) ፡፡ *ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት፡፡*

ያሬድ ተሾመ፡፡ (1989)፡፡ *የዋግ የሐዘን ስርዓት ግጥሞች፡፡*

ያሬድ ተፈራ ። (2002) ።*በሰቆጣ እና በአብርገሌ ገጠራማ ወረዳዎች የሴቶችና የወንዶች የአለባበስ ና የአጊያጌጥ ማህበራዊ እሴቶች* ፣ የኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ።አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

Alebachew,Merka. (2007). *Socio-economic and Political Issues in Wag Himra Oral Poetry* .M.A.Thesis .Department of Foreign Language and Literature. Addis Ababa University.

Alembi ,*Ezekiel.* (2002).*The Construction of the Abanyole Perceptions on Death through Oral Funeral Poetry.* Doctoral dissertation defended at the University of Helsinki in Finland. Retrieved from: *ir.knust.edu.gh*

Andenet, Gizachew. (2010).*Development-Induiced Displacment and Impoverishment: The Case of Tekeze Hydropower Project and Its Impacts on the affected villages of Wag Hemra Zone,North East Ethiopia.* M.A Thesis in Social Anthropology. Addis Ababa University.

Boyden, Jo, Alula Pankhurst,Yisak Tafere. (2012). *Harmful Traditional Practices and Child Protection: Contested Understandings and Customs of Female Early Marriage and Genital Cutting in Ethiopia.* Fourth Draft. *www.younglives.* Retrieved from: *org.uk*

Callais, Ann Mari. (2002).*Sorority Rituals: Rites of Passge and their impact on Contemporary sorority Women.*A Dissertation Submitted to the Graduate Faculty of the Louisiana State University and Agricultural and Mechanical College in partial fulfill ment of the requirements for the Degree of Doctor of Philosophy.

Carla, Shera.(1993).‹‹A Participant observation Case study Using Van Gennep's Rites of Passage Theory at a Summer transitional Program››.Paper Presented at the Annual Meeting of the National Association of College admission counselors.

Retrieved from: *eric.ed.gov*

Guday, Emirie. (2005) *Early Marriage and Its Effects on Girls' Education in Rural Ethiopia: The Case of Mecha Woreda in West Gojjam, North-Western Ethiopia.* Dissertation Submitted for Doctorate/Doctoral Grade in Ethnology (Social and Culttural Anthropology) to the Faculty of Social Sciences,Georg-August University of Goettingen. Retrieved from: *https://ediss.uni-goettingen.de*

Haile Mariam ,Kebede. (1983). "Cultural and Economical life of the Agew People of Wag Awraja." BA Thesis for Department of Applied Sociology.Addis Ababa University.

Heran, Sereke-Brhan. (2002).*Building bridges,drying bad blood:Elite marriages Politics and Ethnicity in 19th and 20th Century imperial Ethiopia.*U.S.A: PhD.Dissertation. Michigan State University.

Hilbers ,Julianne.(2006).*Celebrations for personal and collective Health and well being.* Ph.D.Dissertation. Doctor of Philosophy Faculty of Education University of Technology .Sydney. Retrieved from: www.researchgate.net

Kiflemariam, Hamde. (1986).*The origin and development of Bilin.* Asmara University.

Kouyate,Morissanda (2009).*Harmful traditional practices against Women and Legislation.* United Nations Division for the Advancement of Women United Nations Economic Commission for Africa Expert Group Meeting on good practices in legislation to address harmful practices against women United Nations Conference Centre Addis Ababa, Ethiopia 25 to 28 May 2009. Retrieved from: *www.un.org*

McCann , James, (1984). *House hold peasants and Rural history in Lasta Northern Ethiopia 1900-35.* Phd dissertation Michigan State University.

Melakneh, Mengstu.(1990) .*The major themes and motif of Southern Agew folktale.* M.A Thesis in Literature. Addis Ababa University.

Napoca, Cluj. (2011). *The great rites of passage: birth, marriage and burial. Judeo Christian religious foundations and their folk reflexes.* PhD.Thesis. Babe-Bolyai University. Retrieved from: *doctorat.ubbcluj.ro*

Teshome ,Belay. (2007). *The Syntax of Determiners in Ximtagna.* MA Thesis Department of Linguistics, Addis Ababa University.

*Vaughan, Sarah. (2003).Ethinicity and power in Ethiopia.Phd Dissertation.The University of* Edinburgh. Retrieved from: *https://www.era.lib.ed.ac.uk*

Wudu, Tafete, Kassu.(1995).*A political History of Wag and Lasta c1543-1919.*M.A Thesis in History.Addis Ababa University.

Zelalem, Leyew.(2000.) *The Kemantney Language:A socio-linguistic a Grammatical Study of Language Replacement.*A PhD Dissertion in linguistics. Addis Ababa University.

## አባሪ አንድ

### የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር

### 1. የግል ቃለ መጠይቅ

### 1.1 ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች

| ተ.ቁ | ስም | ጾታ | እድሜ | ስራ | ቃ.መ.የተደረገ በት ቦታ | ቃ.መ.የተደረገበት ቀን | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወ/ሮ ጠጀ በላይ | ሴ | 40 | የቤ.እ | ጸመራ | 17/08/04 | የልምድ አዋላጅ |
| 2 | መጋቢ. ምስጢር ገ/ህይወት ኪ/ማርያም | ወ | 65 | የመ.ሰ | ሰቆጣ ከተማ | 19/08/04 | በዞኑ የስብከተ-ወንጌል ሃላፊ |
| 3 | ወ/ሮ በለጡ አሰፋ | ሴ | 42 | የቤ.እ | ማይ ግንዶ | 21/08/04 | አራስ |
| | | | | | | | |
| 4. | አቶ ተበጀ በላይ | ወ | 60 | አርሶ አደር | ዘንዚራተክ ለሃይማኖት | 23/08/04 | የሙሽራ አጎት |
| 5. | አቶ ደሳለኝ አማረ | ወ | 52 | መምህር | ስሬል ሊባኖስ | 28/08/04 | የሙሽራ አባት |
| 6 | ቄስ አለሙ ወረታ | ወ | 65 | አርሶ አደር | ስሬል ሊባኖስ | 29/08/04 | የሙሽራ አባት |
| 7. | አቶ ደሳለኝ ስዩም | ወ | 51 | አርሶ አደር | ሀሙሲት | 05/09/04 | የቀበሌው ሊቀመንበር |
| 8. | ወ/ሮ አልማዝ ደሳለኝ | ሴ | 35 | የቤ.እ. | ፋያ ማርያም | 12/09/04 | የሙሽራ እናት |
| 9 | አቶ ግርማይ አስናቀ | ወ | 65 | አርሶ አደር | ቄባ ማርያም | 19/09/04 | የሙሽራ አባት |
| 10 | ወ/ሮ ውቢት ኪዴ | ሴ | 26 | መምህር | አዲስ አበባ | 22 /02/05 እና 24/02/05 | ስለ ወረዳው ባህል የምታውቅ |
| 11. | አቶ አካሉ ግርማይ | ወ | 55 | አርሶ አደር | አቢያ ሊባኖስ | 3/05/05 | የሙሽራ አጎት |
| 12. | አቶ ከበደ ተገኝ | ወ | 51 | የመ.ሰ | ሰቆጣ | 4/05/05 | የሰ.ወባቱጉ |
| 13. | ሊቀ ጠበብት ሀረገወይን አገዘ | ወ | 55 | የመ.ሰ | አዲስ አበባ | 14/06/05 | የስምዓ ጽድቅ ጋዜጣ አዘጋጅ |
| 14. | ወ/ሮ ሙሉወርቅ አወጣ | ሴ | 60 | የቤ.እ. | ጸመራ | 23/05/05 | የሰርግ ታዳሚ |
| 15. | አቶ ሞገስ አወጣ | ወ | 65 | አርሶ አደር | ጸመራ | 24/05/05 | የሰርግ ታዳሚ |
| 16 | አቶ ቀኘ ካሴ | ወ | 46 | አርሶ አደር | ጸመራ | 24/05/05 | የሰርግ ታዳሚ |
| 17. | አቶ ክብረት ተጋፋው | ወ | 37 | አርሶ አደር | ሀሙሲት | 06/09/05 | የአጎበር ታዳሚ |
| 18. | መቶ አለቃ ወዳጅ አደራ | ወ | 95 | ጡረታ | ሰቆጣ | 15/09/05 | ያገር ሽማግሌ |
| 19. | ሊቀ አበው አባ በንኑ ቢሰጠኝ | ወ | 63 | ካህን | ሰቆጣ | 15/09/05 | የሙሽራ የነፍስ አባት |

## አባሪ ሁለት

### ምልከታ የተከናወነባቸው ሥነ-ሥርዓቶች

| ተ.ቁ | የሥነ-ሥርዓቱ ዓይነት | ቦታ | ምልከታ የተደረገበት ቀን | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ጋብቻ | ማይግንዶ | 20 እና 21 / 08 / 04 | የቤተክርስቲያን ጋብቻ |
| 2. | ወሊድ | ማይግንዶ | 20 እና 21 / 08/04 | |
| 3. | ጋብቻ | ዛንዚራ ተክለ ሃይማኖት | 23/08/04 | ባህላዊ ጋብቻ |
| 4. | ጋብቻ | ቋራ አቦ | 28 /08/04 | የቤተክርስቲያን ጋብቻ |
| 5. | ጋብቻ | ስሬል ሊባኖስ | 29/08/04 | ባህላዊ ጋብቻ |
| 6. | ጋብቻ | ሀሙሲት | 5/09/04 | ባህላዊ ጋብቻ |
| 7. | አጎበር | አዲ ዘላይ | 11/09/04 | |
| 8. | ቀብር | ወለህ ማርያም | 16/09/04 | |
| 9. | ጋብቻ | ፋያ ማርያም | 19/09/04 | ባህላዊ ጋብቻ |
| 10. | ጋብቻ | አቢያ ሊባኖስ | 2/05/05 | ባህላዊ ጋብቻ |
| 11. | ጋብቻ | ማይ ግንዶ | 16/05/05 | ባህላዊ ጋብቻ |
| 12. | ጋብቻ | በለዛ ማርያም(ተክለሃይማኖት) | 23/05/05 | ባህላዊ ጋብቻ |
| 13. | ጋብቻ | ጸመራ | 24/05/05 | የቤተክርስቲያን ጋብቻ |
| 14. | አጎበር | ሀሙሲት | 5/09/05 | |
| 15. | ወሊድ | ጽጽቃ | 3/7/06 | |
| 16. | ቀብር | ጽጽቃ | 5/7/06 | |
| 17. | አጎበር | መሸሃ | 7/07/06 | |
| 18. | ወሊድ | መሸሃ | 8/07/06 | |
| 19. | ቀብር | መሸሃ | 9/07/06 | |
| 20. | ወሊድ | ኒውሯቅ | 13/07/06 | |
| 21 | ወሊድ | ጭላ | 16/07/06 | |

አባሪ ሶስት

## መሰረታዊ የቃለ-መጠይቅ ጥያቄዎች

### የወሊድን ሥነ-ሥርዓት በሚመለከት

1.ነፍሰ-ጡር ሴት እንዳትበላ የምትከለከላቸው ምግቦችና እንዳትሰራ የምትከለከላቸው ስራዎች የትኞቹ ናቸው ? ለምንስ ነው የምትከለከለው ?

2.ነፍሰ-ጡር ሴት ታጠባለች ? ለምን ? አንዲት ሴት ብዙ ወተት እንዲወርዳትስ ምን ትበላለች ? ትጠጣለች ?

3.ነፍሰ-ጡር ሴት ለወሊድ የምታዘጋጃቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው ?

4.አንዲት ሴት በመጀመሪያ የምትወልደው የት ነው ? የእናቷ እና የምራቷ እንክብካቤስ ምን ይመስላል ?

5.በአራስ ሴት የልብስ አጠባ ወቅት ለህጻኑ ወይም ለህጻኗ ከወንዝ የሚመጡላቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው ? ትርጉማቸውስ ምንድን ነው?

6.ለህጻኑ ማን ነው ስም የሚያወጣው ? እንዴትስ ነው የሚያወጣው ?

7. የክርስትና አባት ወይም እናት እንዴት ነው የሚመረጠው ? የክርስትና ስሙንስ ማን ነው የሚያወጣው?

8.ሴት ስትወለድ ሶስት ጊዜ ፣ ወንድ ሲወለድ ሰባት ጊዜ እልል መባሉ ፣ ሴት በተወለደች በሰማንያ ቀን ወንድ በተወለደ በአርባ ቀን መጠመቃቸው ከሃይማኖቱ አንጻር ለምን ነው ?

9.በምጥ ጊዜና ከወሊድ በኋላ ሰዎች የድንግል ማርያምን ስም መጥራታቸውስ ለምን ነው ?

### የጋብቻን ሥነ-ሥርዓት በሚመለከት

1.ጋብቻ የሚፈጸመው እስከ ስንት ቤት ተቆጥሮ ነው ? የሚቆጠረውስ ምን ምን ነው ?

2.እጮኛነት እንዴት ይፈጸማል ? ሽማግሌዎች ለጋብቻ ወደምትጠየቀው ልጅ ቤት ስንት ጊዜ ይሄዳሉ ? በቅደም ተከተል ቢገልጹልኝ ? የሚያከናውኗቸው ድርጊቶችስ ምን ምን ናቸው ? በዚህ ወቅት የእናት (የሴቶች) ሚና ምንድን ነው ?

3.ከእጮኛነት እስከ ሰርግ ምን ያህል ጊዜ ይቆያል ? በዚህ መካከል የተጋቢዎች ቤተሰቦች ምን አይነት ግንኙነት ይኖራቸዋል ?

4.የሚዜ ምለመላ የሚካሄደው መቼ ነው ? የመመልመያ መስፈርትስ አለውን ? አስፈላጊነቱስ ለምንድን ነው ? ሴት ሙሽራ ሚዜ አላት ? ለምን ?

5.የሰርግ ቀን በማን ነው የሚወሰነው ? ቀኑ ከተቆረጠ በኋላ የወደፊት ሙሽራዎች እንቅስቃሴ እንዴት ነው ?

6.ማጫና ስጦታ የሚሰጠው እንዴት ነው ? ስጦታ የሚሰጠውስ ለማን ለማን ነው ?

7. በዋግ ኽምራ ስጦታ የሚሰጡት የሴት ወገኖች ናቸው የወንድ ? የስጦታው መጠንስ ቋሚ

ነውን?

8.የሰርግ ድግስ ዝግጅት መቼ ነው የሚጀመረው ? ምን ምን ይዘጋጃል ? ከፍተኛው ዝግጅት በገንዘብ ሲተመን ምን ያህል ነው ? በዝግጅቱ ወቅት የቤተዘመድና የጎረቤት እገዛ እንዴት ነው ?

9. በሰርግ ድግስ ወቅት የወንዶችና የሴቶች የስራ ክፍፍል እንዴት ነው ?

10. በጋብቻ ስርዓት የሚከናወኑ ተግባራት ለአብነት ያህል ለማጨት የሚሄዱት ሽማግሌዎች መጠን ሶስት መሆን ፣ ጧፍ ማብራት ፣ ሃይማኖታዊ መነሻው ምንድን ነው ?

11. የሙሽራን ስም ማን ያወጣል ? እንዴትስ ይወጣል ? አወጣጡ መነሻው ምንድን ነው ? ከሚሰጡ ስሞች መካከል እስከ ምክንያቱ ምሳሌ ቢጠቅሱልኝ ?

12. ሙሽራዎች ጎጆ የሚወጡት መቼና እንዴት ነው ?

### የሞትና የሃዘን ሥነ-ሥርዓትን በሚመለከት

1.በጣእረ-ሞት ወቅት ነፍስ መውጣቷ የሚታወቅበት አተነፋፈስ አለን ?

2.ለግነዛ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ምን ምን ናቸው ? ግነዛውስ እንዴት ነው የሚከናወነው ?

3 የሟች እድሜ መለያየት የቀብር ቦታም እንዲለያይ ያደርጋልን ? እንዴት ?

4.እሬሳው ከወጣበት ቤት ማን ይቀራል ? ለምን ? ሰው ሲሞት በጣም የሚለቀሰው ምን ጊዜ ነው ? እሬሳ የወጣበት ቤትስ በማንና በምን ይጸዳል ?

5.አስከሬኑ ወደ ቤተክርስቲያን በሚወሰድበት ወቅት መንገድ ላይ የሚከናወኑ ተግባራት ምን ምን ናቸው?

6. ሀዘንተኛ እንዴትና በማን ነው ማስተዛዘኛ የሚደረግለት ?

7. የሀዘንተኛ ሴቶችና ወንዶች አለባበስ እንዴት ነው ?

8.የሀዘን ቃል ግጥሞች ለምን ይገጠማሉ ? እንዴትና በማን ይገጠማሉ ?

9. በለቅሶ ወቅት የሟች ቁሳቁሶችና ጌጣጌጦች ለማስለቀሻነት የሚወጡት ለምንድን ነው ?

10.አጎበር ምንድን ነው ? ለምን ይደረጋል ?

11. ለሟች ተብለው የሚከናወኑ ድግሶች (ሳልስት ፣ ሰባት ፣ አስራ ሁለት ፣ ሰላሳ ፣ አርባ ፣ ሰማንያ ተዝካር ወዘተ.) ለምንድን ነው የሚደረጉት ?

## አባሪ አራት

# የአካባቢያዊ ቃላት[1] ፍች[2]

| የአካባቢው ቃል | ፍቹ |
|---|---|
| ሀፍላ | አሮጌና ቆሸሽ ያለ ልብስ |
| ሀድሞ | ክብ ፎቅ ቤት |
| ላስታ ቅቤ | የጸጉር ቅቤ |
| ላክሽም | በዛጎል የተዋበች የጸጉር ቅቤ መያዣ ትንሽ ቅል |
| ላጋ | የወተት መግፊያ (መናጫ) ትልቅ ቅል |
| መለቃቀም | ቆሻሻውን ከእህሉ መለየት |
| መለምጠጥ | መቀባት |
| መረቅ | የስጋ ወጥ |
| መሳሪያ | ጠብመንጃ |
| መስሪያ | በሞሰብ ወይም በሌማት አምስት ወይም ስድስት ሰው ለማስተናገድ የተዘጋጀ እንጀራ |
| መቆርቆር | መመስረት |
| መባቻ | ልደታ |
| መትለል | በክብ ዙር እየዞሩ እስክስታ መውረድ |
| መከተሪያ | የልብስ ቁልፍ |
| መክሰስ | መቆያ |
| መደበስ | ማስተዛዘን |
| መገፊጅ | በገፊጅ |
| መጎጫጫ | ደረጃ |
| መዝመት | ሙሽራው በሚዜዎቹና በሽማግሌዎች ታጅቦ ወደ ሴቷ ሙሽራ የሰርግ ቤት መሄድ |
| መወቀር | መነቀስ |
| ሙሃቻ | የሊጥ እቃ |
| ማርዳ | ለታጨች ልጅ የሚወሰድ የጠልሰም እና የድባ ቅልቅል የሆነ ያንገት ጌጥ |
| ማርገጃ ቦታ | የለቅሶ ስርዓት የሚከናወንበት ሜዳማ ቦታ |
| ማወደስ | ማሞገስ |
| ማግፕ ልቅ | ልቃቂት |
| ማድጋ | ሃያ ጣሳ ወይም በግምት ሰላሳ ኪሎ የሚሆን |
| ማዘያ | አንቃልባ |
| ምላሽ | መልስ |

[1] አማርኛ በርካታ የአካባቢ ዘዬዎች አሉት፡፡ዋና ዋናዎቹ የጎንደር፣የወሎ፣የመንዝና የአዲስ አበባ ናቸው፡፡ሌሎች አነስተኛ ልዩነቶችም አማርኛ በተወሰነ ደረጃ በሚነገርባቸው በሃረር፣በጂማ፣በአሰላ ወዘተም. ውሱን ልዩነቶች ይታያሉ፡፡ከአምስቱ ዋና ዋና የአማርኛ ዘዬዎች መካከል የአዲስ አበባ የአማርኛ ዘዬ መደበኛ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ምክንያቱም የትምህርት መጻህፍት የሚታተሙበት፣ለአስተዳደራዊ ስራዎች የሚውለው ይህ ዘዬ ነው፡፡ይህ ዘዬም ከሌሎች ጋር ለማነጻጸር ያገለግላል (Anbesa,1999: 257) ባሉት መሰረት ለአካባቢያዊ ቃላቱ ፍች የተሰጠው በመደበኛው ዘዬ ነው፡፡

[2] ለቃላቱ ፍች የተሰጠው በጽሁፉ ውስጥ ባላቸው አውዳዊ ፍች መሰረት ነው፡፡

| | |
|---|---|
| ምልስ | ለስንቅ የሚዘጋጅ የተጨባበጠ ትኩስ እንጀራ |
| ምስር ቂጣ | በክብ ቅርጽ ክንድን በእሳት ማቃጠል |
| ምክሃ | ጡር |
| ምጎጎ | ምጣድ |
| ሰለላ | አራት ማእዘን ቅርጽ ያለው ጸጉርን መሃል ላይ ትቶ ሽሩባ መሰራት |
| ሳንዱቅ | ሳጥን |
| ስልስ | ከእርጎና ከበርበሬ የሚሰራ ወጥ |
| ስራና ቂጣ | ከስንዴ ዱቄትና ከአተር ወይም ከባቄላ ዱቄት ቅልቅል የሚዘጋጅ |
| ስቅስቆ | በደቃቁ ከተከተፈ ስጋ የሚሰራ ወጥ |
| ሽምቀቆ | ከፈትል ጨርቅ የሚሰራ ቀበቶ |
| ሽክና | ፎሌ |
| ሽምጥጥ | ከቅጠል የተሰራ አጥር |
| ቀለም | ቀሰም |
| ቁልቁል ገባ | ሙሽራው በሴት ቤተሰብ ቤት ጎጆ ወጣ |
| ቁልቁል የገባ እንጀራ | የተፈረፈረ እንጀራ |
| ቁልቋል | በለስ |
| ቁርንጮ | ከለሰለሰ ቆዳ የተሰራ ለልብስነት፣ለመቀመጫነትና ለመመገቢያነት የሚያገለግል |
| ቁርጥ ሰው | ታማኝ መልእክተኛ |
| ቃቂዳ | ከአሽክት ፍሬና ከስንድድ በክር ተደርድሮ የሚሰራ የራስ ጌጥ |
| ቃንጃ መትር መቀነት | ዋጋው እጅግ በጣም ውድ የሆነ የተለያየ ቀለም ባላቸው ክር የተዋበና ሰፊ ጥለት ያለው መቀነት |
| ቅምጽ በል | ታዘብ |
| ቅርድድ | ከመሀል ጸጉርን በክብ ቅርጽ በመላጨት ሌላውን ሹሩባ መሰራት |
| ቅባኑግ | ከኑግ ወይም ከሱፍ የሚሰራ በባህላዊ መንገድ ዘይት |
| ቅጠልያ፣ወንዝ አይፈሬ | አረንጓዴ |
| ቆለምሽሽ | ከሳር የተሰፋች የቆሎ ማቅረቢያ |
| ቆርጣጣ | ቆራጣ |
| ቋቋቴ | በጣት ጌጥ ወጥቶለት የሚጋገር ቂጣ |
| በረሃ | ጫካ |
| ቡታ ነገራ፣ እሪታ | የቅበሩ ጥሪ |
| ካራ | ቢላዋ |
| ባላንጋራ | ደም የተቃባ |
| ባሻ | የወተት ማለቢያ ቅል |
| ባውንድ | ሻሽ |
| ቢሳ፣ችግሬ | ምላጭ |

| | |
|---|---|
| ብሆ | ሊጥ |
| ብር መጣል | ለደጋሾች ብር መስጠት |
| ብርኩታ | በጋለ ድንጋይ ላይ ተጠፍጥፎ የሚጋገር ቂጣ |
| ቦላሌ | ሱሪ |
| ቦትቦት ተደርጉ | በጥበጥ ተደርጉ |
| ቦትቧቴ | ልክ እንደ ቂጣ ሆኖ ነገር ግን ማታ በጥበጥ ተደርጎ ካደረ ሊጥ የሚጋገር |
| ተለቅልቋል | ተቀብቷል |
| ተላልከሽ | እልህ ውስጥ ገብተሽ |
| ተሸልሞ | ቅርጽ ወጥቶለት |
| ተውሳኽ | ከሙሽራዋ ጋር ወደ ወንድ ቤት የሚሄድ ወንድሟ ወይም ዘመዷ |
| ተዋረው | ተሻምተው |
| ተደይኖ | የአልጋ ቁራኛ ሆኖ |
| ተገብጦ | በጥበጥ ተደርጎ |
| ቱልቱላ | ጥሩንባ |
| ትቆነጣጣለች | መጀመሪያ ጊዜ ጸጉሯን ሹሩባ ትሰራለች |
| ትኩሴ | ድፎ |
| ትድረት | ወግ፣ልማድ |
| ነዶ | አዲስ ያልተሰፋ ጨርቅ |
| ነጭ በረቅ | ነጭ ቀለም ያለው አፈር |
| አላድ | የጆሮ ጌጥ |
| አልባሶ | መደረቢያ ያለው በወፍራሙ የሚሰራ ሹሩባ |
| አሚን ባል | የመጀመሪያ ባል |
| አስር እራሳቸውን | አስር ሆነው |
| አስኹር | ሙሽራዎች ጫጉላ ቤት እያሉ ከቤተዘመድና ከጎረቤት የሚወሰድ ምግብ |
| አሸክት | ቅጠሉ ትንንሽና የሚያጣብቅ ተክል |
| አሻሞ | በወፍራሙ የሚሰራ ሹሩባ |
| አበልጅ | ክርስትና እናት ወይም አባት |
| አበሳ | መከራ |
| አብሽሎ | የኮረፌ ቂጣ |
| አነባብሮ | ሁለት ቦትቧቴ አንድ ላይ ተደርቦ የሚጋገር |
| አውራጅ | በአስራ ሁለት፣ በአስራ አራትና አስራ በአምስት ድስት ወጥ፣ በአንድ ጋን ጠላና መቶ ሃያ እንጀራ ስልሳ እንግዳ የሚስተናገድበት |
| አዝመራ | ሚዜዎች ከሙሽራዋ ሰርግ የሚወስዱት ትርፍራፊ እንጀራ |
| አይጠረቃም | አይጠግብም |
| አጥሚት | ሙቅ |
| አጋፋሪዎች | አስተናባሪዎች |
| አጎበር | የቀጠሮ ለቅሶ |
| አፉን የሚያሟሸው | ለመጀመሪያ ጊዜ እህል የሚቀምሰው |
| እህል ውሃ ማለት | ማብላት ማጠጣት |
| እሪጦ | በኑግ፣በተልባና በድልህ የተቀባ አነባብሮ |
| እሱ በሱ | ከዝሃ ብቻ የሚሰራ ልብስ |
| እስክስታ መምታት | እስክስታ መውረድ |
| እቃተኛ | በአዋዜና በቅቤ፣ ጾም ከሆነም በቅባኑግ የተቀባ ትኩስ እንጀራ |
| እንክርትት | ከጭቃ የሚሰራ ተንቀሳቃሽ ምድጃ |
| እንደርታ ወይም ባራባሶ ጫማ | ከጎማ የተሰራ ጥልፍልፍ ጫማ |
| እንዳሁላ | ወፈርና ለስለሳ ያለ ቅጠል ያለው የተክል አይነት |
| እንዳይጎረና | ጣእሙ እንዳይቀይር |
| እየተገዙ | ገንዘብ እየተከፈላቸው |
| እዳይት | የተለያየ ቀለም ያለው ክር |

| | |
|---|---|
| ኩፍ ካለ | ከተነሳ |
| ኪንኪና ስንዴ | በጣም ነጭ የስንዴ ዓይነት |
| ካሉስ | ለስላሳ ጥቁር ክር |
| ካይላ | በሸክላና በቅጥቀጣ ስራ የተሰማሩና ወደ እስራኤል የሄዱ |
| ኬሻ | ጆንያ |
| ኮረፌ | ከገብስ ብቻ የሚዘጋጅ ወፈር ያለ የመጠጥ አይነት |
| ኬንዳ | ፕላስቲክ |
| ኮሸሮ | ትርፍራፊ እንጀራ |
| ወበራ | ወንፈል፣ ጅጌ |
| ወት | የት |
| ወጥ የሚጨልፉ | ወጥ የሚያወጡ |
| ወዛንታ | ከሸክላ ወይም ከጭቃ የተዘጋጀ ክዳን |
| ውቅራት | ንቅሳት |
| ውድቂት | ለሰርግ የሚጣል ብር |
| ዝልል | ቀጠንና ጠራ ያለ የመጠጥ አይነት |
| የሰርግ ቀን አቆራረጥ | የሰርግ ቀን አወሳሰን |
| የብረት ምጣድ | ምጣድ |
| የተለጠለጠ ተልባ | በጣም ደቆ የተወቀጠ |
| ይረበረባል | ይደለደላል |
| ይሸበለላል | ይለወሳል |
| የተወለደውም ያልተወለደውም | የሥጋ ዝምድና ያለውም ሆነ የሌለውም |
| የእህል ወጥ | የክክ ወጥ |
| የነፍስ አባት | የንስሃ አባት |
| ያላት | ሃብታም የሆነች |
| ይሆኑኛል | ይረዱኛል፤ይደግፉኛል |
| በቅሎ ይሸለማል | እንዲያጌጥ ይደረጋል |
| ይቆዘራል | ሆድ ይነፋል |
| ደብር | ባለ አራት ማእዘን ፎቅ ቤት |
| ዱቃ | ወፍራም ኮረፌ |
| ዲቨሲግ | የሙሽራዎችና የሚዜዎች መለያያ የልብስ አጠባ |
| ድምድማት | ከግድግዳ ጥግ ከጭቃ የሚሰራ የእቃ ማስቀመጫ |
| ድርማሞ | ጫፉ ወይም ዱርላው ተሰብስቦ የሚሰራ ሹሩባ |
| ድባ ዓይነት | ዶቃ አይነት |
| ድጉሎ | ከስንዴ ፣ ከማሽላና ከገብስ ቅልቅል የሚዘጋጅ እንጀራ |
| ድፍን | ሙሉ ጸጉርን ሳይላጩ ሹርባ መሰራት |
| ጀበርባሬ | ከፈትልና ከዝሃ ተደባልቆ የሚሰራ ልብስ |
| ገብስማ | ጥቁርና ነጭ ቀለም ያለው |
| ጉብ ታደርጋለች | ብዙ ቅቤ አናቷ ላይ ትቀባለች |
| ጉንጉን | በጣም ወፍራም ሹሩባ |
| ግቺ | ዋና፣ የመጀመሪያ |
| ግና | ግን |
| ግቫና አቦ | ሀምሌ አምስት |
| ግልብጭ | ገፅታው ተገልብጦ የሚሰራ ሹሩባ |
| ግጫ | ገፅታው ሳይገለበጥ የሚሰራ ሹሩባ |
| ግጭላ | ትንሽ ዳስ |
| ጎላ | ትልቅ የብረት ድስት |
| ጎበዝና ቆንጆ | ወፍራምና ቀጭን ቀላቅሎ የሚሰራ ሹሩባ |

| | |
|---|---|
| ጠልሰም | ከድባና ከብር ወይም ከኒኬል ጋር የአንገት ጌጥ ሆኖ ለታጨች ልጅ የሚወሰድ |
| ጠሎታ | ቀጭንና አጭር ጠፍር |
| ጣቢታ | ከጤፍ ብቻ የሚዘጋጅ እንጀራ |
| ጥልፎሽ | ደርሶ መልስ |
| ጥሬ ጨው | ጨው |
| ጥብቆ | ያልተሸበሸበ ቀሚስ |
| ጭው ጭው ይላል | በጣም ያለቅሳል |
| ፍልቅልቅ ወጥ | ከበርበሬና ከተልባ በችኮላ የሚሰራ ወጥ |
| ፍልኸልኸ ማለት | መንቀሳቀስ |
| ፍቅር ቁምጥ | የቀሚሱ ግማሽ ብቻ የተጠለፈ |
| | |

## አባሪ አምስት

## የኽምጣኛ ቃላት፣ ሀረጋትና ዓርፍተ ነገሮች የአማርኛ ትርጉም[1]

| የኽምጣኛ ቃል | ትርጉም |
|---|---|
| ሊልምደው | ሙሽራዋን በወንዱ ቤት የሚያለማምድ |
| መደቋድቁ | መጥመቂያ |
| መጭ መጭ ይጥን | መጪ መጪ በሉ |
| ሚሰው | ማርሻ |
| ሚሰነ | ማስረሻ |
| ሚስረይ | የምታስረሳ |
| ማርያም ኪዲብ ድብርዝና | ማርያም ጭንሽን ታሙቀው |
| ማርያም ዋርዝና | ማርያም ታጫውትሽ |
| ምዘ | ሚዜ |
| ሳሩ | ማሩ |
| ሳርኒ | ማሪቱ |
| ሱሪ እክሰነው | የሱሪ ማውለቂያ |
| ስሪ በትረቋድ ነይትርመ ? | ሙሽራዋ ካተረፈችው ትሰጭኛለሽ ወይ? |
| ስሪት ዊግን | የሙሽራዋ ወገን |
| ስቭስጥን ስቭስጥን ይኻኩ ሻታ ኹር | ሸኙነ ሸኙነ ይላል ልጃችሁ ፣ |
| ስጓ | ተክቶ ስም ማውጣት |
| ሽላ | ጠላ |
| ሽመቅል | ሽማግሌዎች |
| ቀሰው ስቭዝነ በርነ ይናቋርዝቁ ጨነ በውግ ጻይነ | እሺ ከመሸኘታችን አስቀድሞ፣ የልጆቻችንን መተዳደሪያ እንያዝ፡፡ |
| ቀሰው ይና ዘርነድ ችቭስጥን ቃልነ | እሺ አማጩን አቁሙና እንወቀው |
| በልባል | ቁርንጮ |
| ቃለውድቅ ሲጨ ፣ ቃለውድቅ ክምጨ ፡፡ | ያየሁትን ሁሉ ልለብስ ፣ ያየሁትን ሁሉ ልታጠቅ |
| ቃል ጥወነው | ቃል መግባት |
| ቅየን | ሰርግ |
| ቆደ | ማጫ |

[1] በጽሁፉ ውስጥ ያላቸውን አውድ መሰረት በማድረግ የተተረጎመ ነው፡፡

# Amhara Region by Zone




Waghimra Zone by Woreda
N
W
E
S
Abergele
Sehale Seyemt
Zequala
Sekota
Dehana
Gazgibla
0 5 10 20 30 40
Km